የኑረነቢ ማህደር

Il file di Nurenebi

ተ ስ ፋ ዬ ገ ብ ረ አ ብ

Nur Al Nebi's File - Espionage and Politics
Published by: Gabriel and Son Publishing, LLC.
Virginia, USA

ተስፋዬ ገብረአብ

የኑረነቢ ማህደር - ስለላ እና ፖለቲካ

Tesfaye Gebreab

The Nurenebi File - Espionage and Politics

የመጀመሪያ እትም ግንቦት 2017

Printed in - USA.
በአሜሪካን አገር ታተመ።

የደራሲው መብት በህግ የተጠበቀ ነው - 2017
© Publisher - Gabriel and Son Publishing, LLC. 2017

Gabriel and Son Publishing, LLC.
6301 Stevenson Ave. # 717
Alexandria, VA 22304
USA
E-mail: gdebessay@msn.com
Office: 703-566-6589

www.nurenebi.blogspot.com
nurenebi@gmail.com

ይህን መጽሃፍ ለመተርጎም ወይም ወደ አውድዮ ለመቀየር
የደራሲውና የአሳታሚው የጽሁፍ ፈቃድ ያስፈልጋል።

የመጽሃፉ የዘመን አቆጣጠር - የጎርጎሳውያን።

ሽፋን ዲዛይን - ዳንኤል ሃብተማርያም
የመጽሃፍ ርእስ ፎንት፡ ተስፋ ተክለ
የኢጣልያንኛ ትርጉም - ረድኤት ክፍለ
ቴክስት ሌይአውትና የምእራፍ መግቢያ ግጥሞች - ደራሲው
የደራሲው ፎቶግራፍ - በሙሉጌታ ገብረጊዮርጊስ

የፊት ሽፋን ምስል፡ ኑረነቢ፣ ዛህራ፣ እድሪስ፣ አደም
የጀርባ ሽፋን ምስል፡ ገብርኤል፣ ሉላ፣ መኮነን

ለደራሲው አስተያየት ለመላክ፣
Email: ttgebreab@gmail.com
www.tgindex.blogspot.com

የደራሲው የታተሙ ስራዎች

ያልተመለሰው ባቡር (1996) - የቡርቃ ዝምታ (2000) - የቢሾፍቱ ቆሪጦች (2001)
- የጋዜጠኛው ማስታወሻ (2008) - የደራሲው ማስታወሻ (2010) -
የስደተኛው ማስታወሻ (2013) - የጀሚላ እናት (2014)

ISBN 978-0-692-87774-6

ይህ መጽሃፍ

የህይወት መንገድ ላይ ጉዟቸውን

መጻፍ እየፈለጉ - ገና መጻፍ ላልጀመሩ

የዘመናችን ታሪክ ሰሪዎች - ማስታወሻ ይሁን!

ማ ው ጫ

የትረካ መነሻ 7

ክፍል አንድ
የ ኑ ረ ነ ቢ ማ ህ ደ ር

ምዕራፍ 1 ቻዎ! እንግዲህ ፋና - አልተቻለምና 9
ምዕራፍ 2 ደመና በነነ - ቀይባሕር አዘነ 15
ምዕራፍ 3 ከቦት ባላጋራ - ርቆት ባልንጀራ 21
ምዕራፍ 4 የነጻነት ግዳይ - በሰምሃር ደረት ላይ 51
ምዕራፍ 5 የኡምኩሉ ህላዌ - በዘመነ አርዌ 64
ምዕራፍ 6 መሬቱ ደግ ነበር - ከተቻለ መድፈር 80
ምዕራፍ 7 የአስመራ ፖለቲካ - የምስጢር ቀጠሮ 101
ምዕራፍ 8 ለነጭ መርዝ ምሱ - ጎራዴ ነው ፈውሱ 114
ምዕራፍ 9 ባራትዬሪ አፍሮ - ሲገሰግስ አድሮ 134
ምዕራፍ 10 የድል ዕድል ወረደ - ዳግም ሽጦን ሄደ 151

ክፍል ሁለት
የ ስ ለ ላ ስ ራ

ምዕራፍ 1 ለታሪክ ሰሪ ሰው - ነገም ሌላ ቀን ነው 165
ምዕራፍ 2 የኢጣልያን “ስልጣኔ” አየናት 169
ምዕራፍ 3 ካልያዝከው በዘዴ - ጊዜ እንደ ጎራዴ 184

ምዕራፍ 4 እኔም ወገን አለኝ - ባራኪ መራቂ 197
ምዕራፍ 5 ከት ብሎ ሳቀ - መከዳቱን አውቆ 213
ምዕራፍ 6 ጥቁር ፊት - የአቢሲንያ ቆንጆ 235
ምዕራፍ 7 በጫካው በዱሩ - በእሩምታ ዘመሩ 250
ምዕራፍ 8 እንዴት ነህ ወገኔ - ደናኔ አለሁ እኔ 257
ምዕራፍ 9 ደህና ሁኚ ሮማ - Ciao! ባንቺው ዜማ 269
ምዕራፍ 10 የተንኮል ከረጢት - ያ'ጎት ሳም ጓደኛ 275

ክፍል ሶስት
የሉላ ሳንዱቅ

ምዕራፍ 1 የሸግግር ትውልድ - በቁልቁለት መንገድ 301
ምዕራፍ 2 ታሪክ እንደ ዋጣ - የሚሰማው ሲያጣ 307
ምዕራፍ 3 ከግድግዳው ጓሮ - ያደፈጠ ጆሮ 315
ምዕራፍ 4 እንደ ሙሴ መና - አልታወቀም ገና 333
ምዕራፍ 5 ሳይበረዝ በደም - የባሕሩ ቀለም 342
ምዕራፍ 6 በተራ እርግጫ - ቀይ ድምጽ ተሰማ 349
ምዕራፍ 7 አፍንጫህ ረዘመ? - ያንተው ነው ተሸከም 362
ምዕራፍ 8 የዓዲ ሸሩም ሲቃ - የስጋለት ላንቃ 370
ምዕራፍ 9 ጉንጯ ርሶ በእንባ - ጥርሷ የሳቅ አምባ 383

ድህረ ታሪክ 388

ማጣቀሻዎች (References) *393*
መጠቁም (Index of Names) *395*

የትረካ መነሻ

በ2015 አጋማሽ አስመራ ከተማ ላይ ደበሳይ ከተባለ እንግዳ ሰው ጋር ተዋወቅሁ። ይህ ሰው ከአሜሪካ ወደ ኤርትራ የመጣው ለረጅም እረፍት ነበር። በ1939 ሶማሊያ ዋና ከተማ ሞቅዲሾ ተወልዶ አዲስ አበባ አደገ። ምንም እንኳ ጠጉሩ የመታሕት እርጎ ቢመስልም፤ እድሜው ሰባ ተሻግሯል ብሎ የሚገመት አልነበረም። የአሜሪካን አገር ዜግነት የያዘ ሲሆን፤ ወላጆቹ ኤርትራውያን ነበሩ። የዘር ሃረጉ ከሙስሊም ብሌን፤ ከሓልሓል ቦንስ ይመዘዛል።

በዚሁ በመጀመሪያው ቀን ትውውቃችን ለጥብቅ ጉዳይ እንደሚፈልገኝ ገልጾ የስልክ ቁጥሬን ወሰደ። በቃሉ መሰረት በነጋታው ደወለልኝና ለምሳ ማሳዋ ሬስቶራንት ለመገናኘት ቀጠሮ ያዝን። ተገናኝተን ምሳ ካዘዝን በሁዋላ በቀጥታ ወደ ጉዳዩ ዘለቀ።

ከእጅ ቦርሳው እድሜ የጠገቡ ሰነዶችን እያወጣ ጠረጴዛው ላይ አስቀመጠ። በተለያዩ ቋንቋዎች የተጻፉ ነበሩ። ለጣልያንኛው ሰነድ የአማርኛና የእንግሊዝኛ ትርጉሙ አብሮ ተያይዞለታል። በእጅ ጽሁፍ በፈረንሳይኛ፣ በአማርኛ፣ በትግርኛ የተጻፉም ነበሩበት። ሰነዶቹን ጠረጴዛው ላይ አስቀምጦ ሲያበቃ እንዲህ አለ፣

“እነዚህ ወረቀቶች በእናቴ የብረት ሳንዱቅ ውስጥ የቆዩ ናቸው። እኔ በሃላፊነት ከተረከብኳቸው አስራ ሰባት አመታት አልፏል። አባቴ በአንድ ወቅት የአጼ ሃይለስላሴ መንግስት ባለስልጣን ነበር። እንግዲህ እንደምታየው የእድሜ ነገር አለ። እኔ ካለፍኩ በሁዋላ ሰነዶቹ አጉል ቦታ እንዳይወድቁ ስሰጋ ሰነበትኩ።”

ፋታ ወሰደና ቀጠለ፣

“...እናቴ የተማረች ሰው አልነበረችም። አታነብም፤ አትጽፍም። በሰነዶቹ ላይ ያለውን ታሪክ ግን በዝርዝር ታውቅ ነበር። እነዚህ ሰነዶች ወደ መጽሃፍ እንዲቀየሩም ጥብቅ አደራ አሸክማኝ ነበር። እና ይኸው ወዳንተ መጣሁ። እስኪ እያቸውና አሳብህን ንገረኝ?”

ምሳ እየተመገብን በአጠቃላይ ጉዳዮች ላይ ከተጨዋወትን በሁዋላ ተለያየን። ስምምነታችን ሰነዶቹን ካነበብኩ በሁዋላ ምን ማድረግ እንደሚቻል ለመነጋገር ነበር።

ማምሻውን ረጋ ብዬ አነበብኳቸው።

ፎቶግራፎችንም እየተመለከትሁ ማብራሪያውን አነበብኩ።

በሶስተኛው ቀን ወደ እንግዳው ደውዬ ቀጠሮ ያዝኩ። በድጋሚ ማሳዋ ሬስቶራንት ተገናኝተን እየተጨዋወትን ሳለ ደበሳይ፣ በሰነዶቹ መነሻ መጽሃፍ ልጽፍ እችል እንደሆን ጠየቀኝ።

“ምንድነው የምታወራው?” አልኩ። አያያዝኩና ቀልድ አከልኩ፣ “ይህ ሰነድ መኖሩን ብሰማ ኖሮ በሌሊት በር ሰርሳሪ ልኬብህ እነዚህን ወረቀቶች ሰርቄ እወስድ ነበር።”

ይስቃል ብዬ ብጠብቅም አልሳቀም። ሽከም የወረደለት ያህል በእፎይታ ተነፈሰ። በዚያችው ቅጽበት እኔ ሳልጎብጥ አልቀረሁም።

እነሆ! በተዘበራረቀ መልኩ ከተከማቹ ወረቀቶች ላይ አቀርቅሬ ሰነበትኩ። ሰነዶቹ በምናብ ይዘውኝ በዘመን ሰማይ ላይ ቀዘፉ። የዘመን መስኮትና የዘመን በር በራሱ ጊዜ ተበረጋገደ።

እዝነ ህሊናየ ሁሉን ሰማ። ወጎቻቸውን፣ ቁጣቸውን፣ ሳቃቸውን፣ ለቅሷቸውን ሁሉንም እንደ ወረደ ሰማ። አይነ ህሊናዬ ሁሉን አየ። መስኩን፣ ተራራውን፣ ሁዳዱን፣ መልካውን፣ ገጽታቸውን፣ ግንባራቸውን፣ አይነ ውሃቸውን ጥርት ባለ መልኩ ማየት ቻለ። በቦታው የነበርኩ ያህል ተሰማኝ።

የመቶ አመታት ታሪክ...

እንደ ደንከልያ፣ እንደ ሰምሃር፣ እንደ ሳሕል፣ እንደ ባርካ፣ እንደ ሓልሓል፣ እንደ መንሳዕ፣ እንደ ሓባብ፣ እንደ ሰንሒት፣ እንደ ዓፋር የግመል ጠያሮች ተቀጣጥሎ እየተጓዘ ከፊቴ ተዘረጋ . . .

ክፍል አንድ

ምእራፍ 1

ቻዎ እንግዲህ ፋና!

መቆየት ካንቺጋ - አልተቻለምና

እህል ፍለጋ የትውልድ መንደሩን ሲያስስ ውሎ ወደ ጎጆው ሲመለስ መንፈሱ ልክ አልነበረም። ለራሱ ይሁን ለልጆቹ እናት ባልለየ ምሬት ብሶቱን አጅጎደጎደ። ከጉሮሮው የሚወጣው ድምጽ ምግብ ሳይቀምስ ከሰነበተ ሰው የሚፈልቅ አይመስልም። ቁጭትና መጠቃት የአባወራነት ወኔውን ክፉኛ ነክቶት ከእብደት አፋፍ ላይ አደረሰው።

“በፍጹም የማይሆን ነው! ‘የሰመረጽዮን ቤተሰብ በረሃብ አለቀ’ ቢባል የአያቶቼ መንፈስ መሳቀቁ ነው። የፍረመሃቅ አብሪም ቤተሰብ፣ የጨዋግ ሙሲና የሳምራ ናሺህ ዘር፣ የበኺት የዘር ሃረግ እንዴት ኑረነቢ ላይ ይቋረጣል? ልጆቼ እኔን ይቀብራሉ እንጂ እኔ በቁሜ ልጆቼን አልቀብርም። በፍጹም አይደረግም። አላህ ለምን ጨከነ? ይህ የሆነው ረቢ ፈቃዱ ሆኖ ነው? ምን ስለበደልን?”

ባለቤቱ ዛህራ ተጠቅልላ ከተኛችበት ቀና አለች፣

“ኑረነቢ አርሓብዲ (እባክህ ቁጭ በል።) ጥቂት ጥራጥሬ እንኳ አላገኘህም? ባዶ እጅህን መጣህ?”

“እጅግ አስደናቂ ነው። የሚሸጥ እህል የትም የለም። የፋና ሰው ሁሉ ተሰዷል። ዑስማን ፈካከ ቤተሰቡን ይዞ ባርካ ሄዷል። ሓርቦይ ሁለት ልጆቹንና ሚስቱን ቀብሮ ሲያበቃ ወደ ምጽዋ ተሰደደ። ሙና ሓሊብመንተል፤ የሙስጠፋ ኢል ነቢል ሚስት ባሏን ቀብራ ስታበቃ የምድጃው አመድ አጠገብ ተኝታለች። ኢብራሂም ሰይድ ከሊፋ ከቤቱ የለም። ዘመዴና የልብ ወዳጇ ሓርቤ እንኳ ሳይነግረኝ ሚስትና ልጆቹን ይዞ ሄዷል። የሓርቤ መሄድ ቅስሜን ሰበረው። ወዴት እንደሄደ ማንም አያውቅም። ማን የቀረ አለ? ዑመር አል ዑስማን ቤቱ የለም። ናቡቴ ባሏን ብቻዋን ቀበረች። ከዚያም ሁለት ልጆቿ እንዳይሞቱባት ወደ ባርካ ይዛቸው ሄዳለች። እነ ባህዱራይ፣ ማህራይ፣ በትራይ . . .”

አያይዞ ስሜት በገፋው ድምጽ ቀጠለ፣

“...ወተት በአይን ከታየ ስንት ጊዜው? ብልቱግ ማግኘት አይቻልም። ብልቱግ ከማግኘት ወርቅ ማግኘት ቀለለ። ቦጎስ እንዲህ የጠወለገበት ዘመን በታሪክ አልተሰማም። ዝናብ የለም። ሰማይ ደርቋል፣ ደመና ርቋል። ካልዘነበ ቅጠል እንኳ በጥሶ ማኘክ አይቻልም። የውሃ ጉድጓዶች እየነጠፉ ነው። ምንድነው የሚደረገው? ላስመሓላህ! (አምላክ አይፍረደው።) አላህ ትቶናል። ሌላ አይደለም። መሷኢብ ቀውሚን ሚንደ ቀውሚን ፊዋኢዱ። (የአይጥ ሞት ለድመት ጨዋታ ነው።)”

ዛህራ ጋደም ካለችበት በመከራ ተነስታ ቆመች።

“የአላህ ቁጣ ነው። ረቢ ሰጠ። ረቢ ነሳ። ሁሉ የሱ ነው። ኑረነቢ - ላረኻ እንግገው ጋብ ጋበግ (ግዴለም ኑረነቢ - ዋጋ ቢስ ንግግር አትናገር።) አላህ ከሪም። አልሓምዱ ሊላህ! (አምላክ ቸር ነው፤ አምላክ ይመስገን።)”

ሁለት ጨቅላ ወንድ ልጆች ከምድጃው አጠገብ ተጠቅልለው ተቀምጠው የአባትና የእናታቸውን የመከራ ዘመን ወግ በጸጥታ ያዳምጣሉ። እድሪስ ኑረነቢ የዘጠኝ አመት ልጅ ሲሆን፤ አድም ኑረነቢ ሰባት ነበር። ልጆቹ በቁጣ የሚጨስ አባታቸውን

አልፎ አልፎ ቀና ብለው በፍርሃት ይመለከታሉ። ኑረነቢ ጨሶ ጨሶ ሲደክመው ከልጆቹ አጠገብ መሬቱ ላይ ተረፈቀ። እና የልጆቹን ጠጉር በየተራ እያሻሸ ተከዘ፣

“እድሪስ ልጄ! አድም ልጄ! አይኔ እያየ አልቀብራችሁም። በፍጹም አትሞቱም። ሙስተሒል ሙሓል! (በፍጹም የማይሆን።) እንደ ሙስጠፋ ልጆች አልቀብራችሁም። አልሓምዱ ሊላህ!”

ወደ ዛህራ መለስ ብሎ በጥያቄ አጣደፋት፣

“ምን ያህል የቀረ ምግብ አለን?”

“ጥቂት ጥራጥሬ አለ። ደብቄ ያቆየሁት ቋንጣም አለ። እየተቃመስን አንድ ሰንበት እንሻገር ይሆናል። ኢንሻላህ።”

ኑረነቢ ከተቀመጠበት ተነስቶ ወደ ደጅ ወጣ። ከአንድ አመት በፊት ቄብ ዶሮዎች ይዘምሩበት የነበረው ደጃፍ ጸጥ ብሎአል። በፍየሎች ሙዚቃ ደምቆ የሚያመሸው ሃማጋ ነጥፏል። ላሞች የሚታለቡበት፤ በሬዎች የሚያሙሳኩበት ግርግም አና ቀርቷል። ሞልቶ የተረፈው ጥሪት አልቆ፣ ምልክታቸው ዘራቸውም የለ። የከብቶቹ ፍግና የዶሮዎቹ ኩስ ደርቆ ወደ አቧራነት ተለውጧል። ረሃብና ጥሙን መቋቋም የቻለችው ግመል ብቻ ታሪክ ተራኪ፣ መርዶ ነጋሪ መስላ ሃማጋው ላይ ቆማለች። ሻማል አትንቀሳቀስም። እንደ ሻልኩ አለቶች ተገትራለች።

ወደ ሻማል ተጠግቶ ግንባሯን አሻሻት። ውሃ ከቀመሰች ስንት ቀናት አልፏታል? ምግብ ከየት አግኝታ? ቆዳዋ ከአጥንቷ ተጣብቆ ህይወት ያላት ፍጡር አትመስልም። ኑረነቢ ደግሞ ደጋግሞ ሻማልን ለማረድ አስቦ ነበር። ቆዳና አጥንት እንጂ ስጋ እንደማይገኝባት ሲረዳ ግን ተወው። ለጭንቀቱ መፍትሄ ትሰጠው ይመስል የሻማልን ግንባር እያሻሸ ብዙ ቆየ።

በትዝታ ወደሁዋላ በመመለስ የሻማልን እናት አስታወሰ። ሒማል ትባል ነበር። የፓኪስታን ምርጥ የግመል ዘር ናቸው። ወተቷን እያጠጣች ያሳደገችው የሻማል እናት ሒማል ጥሩ ከተመገበች በቀን አራት ጊዜ እስከ ሃያ ሌትር ወተት ትሰጥ ነበር። ሻማልና ሒማል ዘራቸው ከሙሲ ትውልድ ጀምሮ እየተከታተለ የመጣ ነበር። ከሻማል ጥጆች አንዱ ጋሎል ከአንድ ወር በፊት ታርዶ

ሲበላ፤ ጎሶል ተሸጦ በገንዘቡ እህል ተገዝቶበታል። እነዚህ ቅዱስ ፍጡራን ወተታቸውን እየሰጡ የሰመረጽዮንን የልጅ ልጆች ማሳደጋቸው ሳይበቃ፤ ደማቸውን አፍሰው ስጋቸውን ለቋንጣነት ዳረጉ። ፍቅራቸውን፣ ጉልበታቸውን፣ ወተታቸውን እየሰጡ ካሳደጉት ግመሎች አሁን የቀረችው የመጨረሻዋ ይኸው ሻማል ናት። ኑረነቢ ወደ ጆሮዋ ጠጋ ብሎ “ሻማል! አምላክ አንቺ ነሽ!” ሲል ሹክ አላት። በርግጥም በዚያችው ደቂቃ ሻማልን አምኖ ቤተሰቡን ይዞ ለመሰደድ ወስኖ ነበር። ሻማል የተናገረውን የሰማች ያህል አይኖቿን ከፍታ አየችው። አይኖቿ ኮረት ይመስሉ ነበር።

* * *

የኑረነቢ ነባር ቤተሰብ በድርቁ ምክንያት ፋና ከተባለች መንደር የተፈናቀለበት ዘመን 1888 ነበር። በአፍሪቃ ቀንድ እጅግ አሰቃቂ ሊባል የሚችል ረሃብ ያንጣበበበት ዘመን ነበር። የረሃቡ ጊዜ የከፋ በመሆኑ ተከባብሮና ተሳስቦ የኖረ ህብረተሰብ የተካካደበት ዘመን ነበር። አንዱ ለሌላው በጎ ማድረግ የተወበት ክፉ ጊዜ ነበር። እያንዳንዱ የራሱን ህይወት እንዴት ማቆየት እንዳለበት ብቻ ያስባል። ህጻናት ሲያለቅሱ የሚራራ አንጀት ጠፋ። አንዱ ሌላውን ገድሎ ስንቁን መዝረፍ የተለመደ ሆነ። ረሃቡ ለአራት ተከታታይ አመታት በመቀጠሉ ከመረብ ወንዝ ወዲህና ወዲያ ማዶ ደጋውና ቆላው ምድር በችጋር የተገረፈበት፣ በየእለቱ በሺህዎች የሚረግፉበት የተረገመ ዘመን ነበር።

በዚያ ክፉ ዘመን የዝናብ እጥረት ካስከተለው የረሃብ አደጋ በተጨማሪ “ደስታ” የተባለ የከብት በሽታ ገብቶ ከብቶችን ፈጀ። የበሽታው መከሰት ከኢጣልያ ወደ አካባቢው መምጣት ጋር ተያያዘ። የኢጣልያ ቅኝ ገዢ ሆን ብሎ በሽታውን ማስፋፋቱ ተነገረ። “ከብቶች ካለቁ ወጣቶች የእርሻ ስራ ስለማይሰሩ ለኢጣሊያ በወታደርነት ለመቀጠር ግዴታ ውስጥ ይገባሉ።” ተብሎ ታሰበ። “ጣልያኖች ሆን ብለው ከብቶቻችንን በበሽታ የፈጁብን በተንኮል ነው።” የሚል ወግ የገጠር መንደሮችን አዳረሰ። እንግሊዛዊው ናፒየር አጤ ቴዎድሮስን ለመውጋት በመጣ ጊዜ ከህንድ በመርከብ ባመጣቸው ከብቶች በኩል በሽታው ስለመግባቱም የሚናገሩ ሽማግሌችም ነበሩ። ዞረም ቀረ ብቻ በገጠር ከዚህ ሌላ ወሬ አልነበረም።

ኢጣልያውያን “እግረ ደረቅ” ተሰኙ። የከበሳና የመታሕት አርቢና አራሽ ገጠሬ የዝናብ እጥረት ባስከተለው ድርቅና የኩበት ፈጅ አደጋ ሲጠቃ ጎጆውን እየዘጋ እግሩ ወደመራው ነጎደ። በተለይ ሓልሓል ቀዳሚ ተጠቂ ነበርና የቻለ ጎጆውን እየሸነጠ ሲሰደድ፤ ያልቻለ ከቀዘቀዘ ምድጃው አጠገብ ጋደም እንዳለ ቀረ። በአገሩ ተባይና አይጥ እየበዛ፤ የሰው ዘር እየሳሳ ሄደ። ቁጫጭ ፈላ። አገሩ ዳግም የሰው ዘር የሚኖርበት አልመሰለም። መልካውና ሁዳዱ ቆሌው ተገፈፈ። ወዝና መአዛ ራቀው።

ከ1887 ጀምሮ የተከሰተው ይህ የረሃብ አደጋ ከሸዋ እስከ ኑቢያ፣ ከዓሳውርታ እስከ ሳሕል ሰፊ ሽፋን ነበረው። በሸዋ የተከሰተው ድርቅ በተከታታይ ለአራት አመታት የዘለቀ ባይሆንም በሁሉት ዝናብ አልባ ክረምት ያደረሰው ጉዳት ግን እጅግ ዘግናኝ ነበር። ከብቶች በገፍ አለቁ። ደማቸውና ስጋቸው ምጥጥ ብሎ ደርቆ በቆዳ በተሸፈነው አጥንት ውስጥ ነፍስ መቆየት መቻሏ ከተአምር የሚቆጠር ሆነ። በዚህ ክፉ የረሃብ ዘመን ሸዋ ውስጥ፤ እንሳሮ በተባለ መንደር አንዲት ሴት ሰባት ህጻናትን አርዳ ስጋቸውን ጠብሳ፤ አጥንታቸውን ቀቅላ በላች። ይህች ሴት በፈጸመችው አሰቃቂ ድርጊት ምክንያት ተይዛ እንጦጦ ከአጤ ምኒልክ ችሎት አቀረቧት፣

“እውነት የሰው ስጋ በላሽ?” ሲሉ ንጉሱ ጠየቁ።

“አዎ ጃንሆይ! ቢርበኝ ሰባት ልጆች በላሁ።”

“ልጆቹን የት አገኘሻቸው?”

“ከሚጫወቱበት እያነቅሁ ወሰድኳቸው።”

ይህን የምትናገረው ሴት አንጀቷ ታጥፎ፣ አይኖቿ አባብጠው፣ አመድ የመሰለች ነበረች። ምኒልክ ይህን የዘመነ ድርቅ ጉድ በገዛ ጆሯቸው ሲሰሙ፣ “አገሬ ጠፋ! ደሃዬ አለቀ!” ብለው አለቀሱ። አፈወርቅ ገብረእየሱስ በዚሁ ትረካው ስለዚህ ችጋራም ዘመን ሲጽፍ እንዲህ አለ፣

“አገር ምድሩ ጠነባ። አሞራው፣ ጅቡ፣ ቁራው፣ ተኩላው በየዱሩና በየቤቱ ስራ በዛበት። ወዳጅ ለወዳጅ ቀርቶ እናትና ልጅ መተዛዘን ቀረ። መቃብር ጌጥ ሆነ። የአብዛኛው መቃብር የጅብና የአሞራ ሆድ ነበር።”

በሓልሓል የከብቶችን ማለቅ ተከትሎ የአንበጣ ሰራዊት ባሕር ተሻግሮ እየመጣ ዓንሰባና ቦሳስ ላይ ተራገፈ። የአንበጣው አመጣጥ ልክ እንደ ከባድ በረዷማ ዝናብ ሲሆን፤ በአይን ማየት እስከማይቻል ድረስ ሰማዩን ይሸፍነዋል። አንድ ወረዳ ላይ የበቀለን ሰብል ባዶ ለማድረግ ጥቂት ደቂቃዎች ብቻ ይበቁታል። ሌላው ቀርቶ ሸባካ የተባለው ዝነኛ ባለቅጠል ዛፍ ጎፈሬው በአንበጣ ተላጭቶ የሰምሃር ግራር መሰለ። በጥቂት ደካማ ዝናቦች ያቆጠቆጡ ቅጠልና ሳሮች የአንበጣው ሰራዊት የአንድ ማለዳ ቁርስ ሆኑ። አንበጦች በህይወት ያለ ህጻን ልጅ ላይ ሰፍረው አጥንቱ እስኪቀር እየላሱና እየቆረጠሙ እንደበሉት ወሬው ሲሰማ ዘመኑ “ዘመነ ደስከለ” ተባለ። የእህል ዘር በአይን ማየት፤ ምግብ ባፍንጫ ማሽተት ተናፈቀ። ረሃብና ሞት ጥንቡን ሲጥል፤ ጥንብ አንሳ ሰማዩን ሞላው። የትም ቦታ አጥንታቸው ገጦ የወደቁ ሰዎችን መመልከት፤ በጅብና በነብር ተበልቶ ትርፍራፊው የቀረ የሰው አጥንት ወድቆ ማየት ተራ እለታዊ ልምድ ሆነ። በርግጥ ምድር እንዲህ ሲከዳ ቀይ ባሕር ከልቡ፣ ከአንጀቱ፣ ከጥልቁ አዝኖ ነበር።

በነጋታው ማለዳ እንደ በረሃ ግራር የደረቀችው ሻማል፣ ሁለት ጨቅላ ልጆችን ከእናታቸው ጋር ወገቧ ላይ አሳፍራ፤ በኑረነቢ እየተጎተተች የተወለደችበትን መንደር ለቃ ወጣች። ሻማል የመጨረሻውን ታማኝነትና ጀግንነት ለመፈጸም እግሯን አነሳች። ጀርባዋን ለፋና - ፊቷን ለሮራ መንሳዕ ሰጠች። ሻማል ወደ ቆላው ማዘቅዘቅ ስትጀምር ጀንበር ገና ብቅም አላለች ነበር።

ምእራፍ 2

ጓዙን ወዙን ይዞ - ደመና በነነ
ቀይ ባህር አዘነ!

ኑረነቢ የትውልድ መንደሩን ለመልቀቅ ሲወስን በቅድሚያ ወደ እአምሮው የመጣው የስደት አማራጭ አገር ምጽዋ ሆነ። ታላቅ እህቱ መርየም በኺት ምጽዋ ከተማ ላይ ትኖራለች። እምን ሁኔታ ላይ እንዳለች ግን አያውቅም። ምጽዋንም ቢሆን ከዚህ ቀደም አላያትም። ከሶስት አመታት በፊት በጣልያኖች መያዟን ግን ወሬ ሰምቷል። ስለ ባሕሩ የማይነጥፍ ጸጋም በወሬ ሲሰማ ኖሯል። “ቀይ ባሕር ከአመት አመት አሳ እየዘረገፈ ያቀርባል” ይባል ነበር። እንደ ወሬው ከሆነ አንድ የምጽዋ ሰው ቢያንስ አሳ ቆርጥሞ ያድራል።

ኑረነቢ እህቱንና የቀይ ባሕርን አሶች ተስፋ አድርጎ፤ በአስቸጋሪ ሁኔታ ተጉዞ ምጽዋ ለመድረስ ሁለት ሳምንታት ፈጀበት። ፋና የተባለች የአያት ቅድመ አያታቸውን መንደር ለቀው ሲወጡ ከሻማል ጋር አምስት ነበሩ። ምጽዋ ሲደርሱ ግን ሶስት ቀሩ። በዚህ ፈታኝ ጉዞ ኑረነቢ የልጆቹን እናት መንገድ ዳር ቀብሮ፤ የሻማልን ሬሳ ለአሞሮች ሰጥቶ ጉዞውን ለመቀጠል ተገደደ።

ዛህራ ያረፈችው ደብረሲና ከተባለች የኦርቶዶክስ ቤተክርስትያን ቅጽር ግቢ ደጃፍ ላይ እረፍት ባደረጉበት ጊዜ ነበር። ውሃና ጥቂት ምግብ ከደጅ ሰላሙ ማግኘት ቢችሉም፤ በዛህራ ጉሮሮ

ግን እህል ሊወርድ አልቻለም። አይኗን መግለጥ ተሳናት። አፏን እንደከፈተች በሞትና በህይወት መካከል ለሁለት ቀናት ያህል ካጣጣረች በሁዋላ ባሏንና ልጆቿን በሰቀቀን ተሰናበተች። በትክክል አሟሟቷ እረፍት ነበር።

ኑረነቢ ዶማ ለምኖ ከቤተክርስቲያኑ አጥር ዳርቻ የመቃብር ጉድጓድ መቆፈር ሲጀምር ሟቿ ከቅጽር ግቢው ውስጥ እንድትቀበር ፈቃዳቸው መሆኑን የቤተክስያኑ ቄስ ነገሩት። ኑረነቢ ግን የቀብር ግብጣውን ሳይቀበል ቀረ። ሙስሊም እንደመሆኑ ባለቤቱን ከቤተክርስትያን ቅጽር ግቢ ውስጥ መቅበር አልፈቀደም። ጎልማሳው ቄስ ኑረነቢን በቁፋሮው እያገዘ ጥቂት የማጽናኛ ቃላት ተናገረ፣

“ይህን ስለመሰለ ክፉ ዘመን ከዚህ ቀደም በወሬ እንኳ አልሰማንም። የሰው ልጅ እንዲህ ባለው ጊዜ እምነቱን ያጣል። ቃሉን ይበላል። እንዲህ ባለው ክፉ ጊዜ በአምላክ አምሳል የተሰራው የሰው ልጅ የክብር ጸጋውን ይገፈፋል። እንዲህ ያለ ችግር ሲመጣ እስላም ክርስትያን ሳይል አደጋው ለሁሉ ነው።”

አያያዘናም ጠየቀ፣

“ከየት ነዎት ለመሆኑ?”

“ከፋና ነኝ።”

“ፋና? እዚህ ሓልሓል? ምኑን እስላም ሆኑ ታዲያ? ቤተክርስትያናችን በተዳከመች ጊዜ ግብጻውያን መጥተው ነው ያሰለሟችሁ። ብሌን፣ ማርያ ጸላም፣ ማርያ ቀያህ፣ መንሳዕ፣ ቤት ጁክ፣ ቤት አስገደ ሁሉም ተዋህዶ ነበሩ። በዚያ የግብጽ ወረራ፣ በዚህ የጎበዝ አለቆች ዝርፊያ በዝቶ የህዝቡን ሃይማኖት አፋለሰው። በዚያን ጊዜ ብሌን ከፊሉ እስላም ሆነ፣ ሌላው ወደ ካቶሊክ ገባ፤ ጥቂቱ ‘መድሃኔአለምን ካልሆነ ሌላ አናውቅም’ ወደሚሉት ገቡ። ስማቸው ማነበር ልጄ?”

ለአፍታ አሰብ አደረጉና መልሰው ተውት፣

“ለመሆኑ የእርስዎ አያቶች ማን ይባላሉ?”

“ከዓዲ ሙሲ ነኝ።”

“እንግዲያው ሳምራ ለእርስዎ አያት ናቸዋ?”

“እውነት ነው። ልክ ነው።”

“ወይ ወንድሜን! ርስዎ የሰመረጽዮን ቤተሰብ ኖረዋላ? ታላቅ ቤተሰብ፤ ታላቅ ዘር። ከጥንቱ የአገሩ ጭቃ የናንተው አይደለም እንዴ? አህ! እናንተም እንዲህ ለስደት በቃችሁ? አይ ጊዜ! ወይ ዘመን! ዘመንና ጊዜ ከሃዲ ነው። ናቡከደናጾርን እንደ በሬ ሳር ያስጋጠ አምላክ! አንገቷን አዙራ ስላየች - የሎጥን ሚስት እንደ ሃውልት ያደረቀ ፈጣሪ! እረኛውን ሙሴ - ታላቅ መሪ ያደረገ ጌታ - ኖህን ለይቶ ከውሃ ሙላት ያተረፈ አምላክ! የዳዊትን የከበደ ሃጢአት ያቀለለ ፈጣሪ! ዳንኤልን ከአንበሶች መንጋጋ ለማዳን - አንበሶችን ድመት ያደረገ! ከአሳነባሪ ሆድ ውስጥ - ዮናስን በምኞት ያሳደረ አምላክ! ለሱ ምን ይሳነዋል? ይቅር ይበልን በምህረቱ!”

“ላአራኩም ሱእ።” (ክፉ አያሳያችሁ።) አለ ኑረነቢ።

ኑረነቢ ለመጀመሪያ ጊዜ የተሸነፈ በሚመስል መንፈስ በኩታው ጫፍ አይኖቹን አባበሰ። ሆኖም የሚያቃጥል ሲቃ እንጂ ፈሳሽ እንባ አልወጣውም። እንባ የት ተገኝቶ? የእንባ ቀልቀሎ ነጥፏል። የአይኑ ብሌን ርጥበት ያለው አይመስልም። ሽፋሽፍቶቹ አይንቀሳቀሱም። ህይወት አልባ መስለዋል።

ቄሱ የመቃብሩን ጉድጓድ እየቆፈረ ጥያቄውን ቀጠለ፣

“የሰመረጽዮን ልጆች በሙሲ መጠራታችሁ ለምን ይሆን?”

ኑረነቢ እያመነታ ተናገረ፣

“ዓዲ ሙሲ መባላችን መች በሙሲ ፍረመሃቅ ሆኖ? እውነተኞዎቹ ዓዲ ሙሲዎች ዘራቸው ጠፍቷል። ቀድሞ ዓዲ ሙሲ የሚባሉት በዘር ከኛ ጋር አይገናኙም። አያቶቻችን ዓዲ ሙሲን ካጠፉ በሁዋላ ነው ስማቸውን የወረሱት።”

“ይህን እንኳ አላውቅም። ምን ማለትዎ ነው?”

“እንደሚባለው የዓዲ ሙሲ ሰዎች ሃይለኛ ተዋጊዎችና ነገር ወዳድ ነበሩ። ሓልሓል ቦጎስን አስቸገሩ። እስከ ሰንሒት እየሄዱ ደም ተቃቡ። ከዚህም ከዚያም መጋጨት ልማዳቸው ነበር። ጣውቀ ልጁን ለማየት ሓልሓል ቆይቶ ወደ ዓዲ ተከሌዛን ሲመለስ መንገድ ላይ ገደሉት። በዚህ ድርጊታቸው የጣውቀ ወገን ተቆጣና

ተነሳባቸው። ዓዲ ውሪእ፣ ዓዲ ኢቲን፣ ዓዲ ቴድሮስ፣ ዓዲ ሃመጃይ ተባብረው ዓዲ ሙሲን አጠፉ። እኛ እንግዲህ ከዓዲ ሃመጃይ ነን። ሁዋላ ዓዲ ሙሲን ያጠፉት አራቱ አያቶቻችን የዓዲ ሙሲ ዘር ከነስሙ ጭምር ጠፍቶ ከሚቀር በሚል ስማቸውን ወረሱ። የዓዲ ሙሲ ሰው ግን ይቅርታ መጠየቁን ተጠይፎ በእልህ ሲዋጋ አለቀ።"

ቄሱ ቁፋሮውን አቆመና ቁጭ ብሎ ላቡቱን ጠራረገ፣

"ባገራችን ብዙ አፈታሪክ አለ። አንዳንድ ጊዜ ካንዱ ወደ ሌላው ሲተላለፍ ይጨማመርበትና ከእውነቱ እየራቀ ይሄዳል። በጥንት ጊዜ በቅዱሳን መጻህፍቶቻችን ላይም ቢሆን ተረት መደባለቅ አጋጥሞ ነበር። ያልታረመ አፈታሪክ ዛሬም ቢሆን አለ በርግጥ..."

"መቸም ያው ካባቶች የሰማነው ነው።"

"የሳምራ አያት የተዋህዶ ቄስ እንደነበር አያውቁም?"

"አላህ ከሪም። (እግዚአብሄር ቸር ነው።) በታሪክ ነግረውናል። ግብጾች እስላሞችን አይነኩም ነበር። አላህን ይፈሩና ያከብሩ ነበር። ከደቡብ የሚመጡት ግን እስላም ክርስትያን ሳይሉ ሁሉን አጠፉ። ጎጆ አቃጠሉ። እህል ዘረፉ። ፍየል ሳይበቃቸው ቀረና ግመል እየነጠቁ አረዱ። ለስንቃቸው መጫኛ አጋሰሶችን ነዱ። 'ወገኔ' የሚሉት አልነበራቸውም። የሓልሓልን ሰው ክፉኛ አስቀየሙ።"

ቄሱ ለኑረነቢ ቅሬታ ምክንያት ፈለገለት፣

"ቤተክርስትያናችን ተዳክማ ነበር። ሌላ አይደለም።"

ኑረነቢ ቄሱን በለሆሳስ ድምጽ ጠየቀ፣

"ይህን ሁሉ ማወቅዎ ርስዎስ ከወዴት ቢሆኑ ነው?"

"ከቤት አስገደ ነኝ።"

"ቤት አስገደ ተዋህዶ አላቸው እንዴ?"

"አገሩ ሃይማኖቱን ሲለውጥ ጥቂት ቤትማይ ተዋህዶ እንደሆንን ቆይተናል። ርስዎ እንዳሉት ባላገር ለባለ ዝናር በመገበር ተማሮ ነበር። ጊዜው ጥሩ አልነበረም።"

"ቤት አስገደ በዚህ በድርቁ የኛን ያህል አልተጎዳም። የትግረ ግብር ደግፎ ይዟቸዋል። የዋኣት ሓሊብና የጠሊት ሓሊብ ደምብ

ጉሮሯቸውን እያረጠበላቸው ነው። ድርቁ እንዲሁ ከዘለቀ ግን ትግረ ከራሱ ተርፎ ለቤት አሰገደ የሚገብረው አይኖረውም። ተያይዞ ማለቅ ነው የሚሆነው። አገሩ ጨርሶ እንዳይጠፋ ያሰጋል።"

"አይ! አምላክ መሃሪ ነው። ምህረቱን አይነፍገንም። የአምላክ ጥበብ ረቂቅ ነው። በአምሳሉ የፈጠረውን አያጠፋም።"

ኑረነቢ ተስፋ በማጣት ስሜት እጁን አወናጨፈ፣

"ይህ ዘመን እንኳ የመጨረሻችን ሳይሆን አይቀርም። ገሪኹድግ ጎሄይኹን! (በጣም አዝናለሁ) እነዚህ ልጆች ከዚህ መቅሰፍት ካልወጡ ዘራችን መቋረጡ ነው። ሳናውቅ ምን ሃጢአት ሰርተን ይሆን? እንዴት ዘራችን እኔ ላይ ይቋረጣል?"

ኑረነቢ በተዳከመ ድምጽ ማልጎምጎሙን ቀጠለ፣

"ቅድም የተናገሩት በእውነቱ ትልቅ አባባል ነው። የሰው ልጅ ሁሉ የአንድ አምላክ ፍጡር መሆኑ የሚታየው እንዲህ ባለው የችግር ጊዜ ነው። እንዲህ ያለ ዘመን ሲመጣ እስላም ክርስትያን ሳይል ፈጣሪ ሁሉን እኩል ይቀጣል። ፈጣሪ አንድ ባይሆን ኖሮ የሰው ልጅ መከራውን እኩል ባልተካፈለ። እንግዲህ ዋናው ነገር ልጆቹን ከሞት መንጋጋ ማዳን ነው። ኢንሻላህ! ልጆቹን ማዳን ካልተቻለ የዚህ አለም ነገር ሌላ ምን ትርፍ አለው?"

መንገዱን ሲጀምር ጭምር መናገሩን አላቋረጠም፣

"እግዚአብሄር አይፍረደው። ምን ይባላል ሌላ? አልሐምዱ ሊላህ። ርስዎም ላደረጉልን አምላክ ይባርክዎ! ሙቹላ ቋሊስጊንተት፣ ጃር ቲክሲንኩት! (ክፉ አያሳያችሁ! ፈጣሪ ይባርካችሁ!)"

ኑረነቢ ጉዞውን ወደ ምጽዋ ቀጠለ።

ዶጋሊ ለመድረስ ጥቂት ሲቀራቸው ሻማል እንደ ዘሃራ እሷም በሞት ተሰናበተቻቸው። ውሃ ለመቅመስና የቀትሩን ከባድ ሃሩር ለማሳለፍ ጥላ መርጠው አረፍ ባሉበት ቦታ ሻማል ረጅም አንገቷን ልክ እንደ ገመድ መሬት ላይ ዘረጋችው። ብዙም አላጣጣረች። አይኖቿን ከደነቻቸው። ዘሃራን እና ሻማልን በተከታታይ ያጣው ኑረነቢ በገጠመው ድርብ ፈተና ቢደናገጥም አልተበገረም። "ልጆቼን አልቀብርም" ብሎ ለራሱ በገባው ቃል

መሰረት ሁለቱን ጨቅላዎች ይዞ ቀሪ ጉዞውን ቀጠለ።

በጉዞው ላይ ታላቅየው እድሪስ ደህና ነበር። አድም አቅም አጣ። እግሮቹን እያነሳ መዘርጋቱ እየከበደው ሲሄድ ኑረነቢ አዘለው። እናም እየለመነ እያበላ፤ በመንገደኞች ግመሎች ልጆቹን እያሳፈረ፤ እያረፈ፣ ልጆቹን በህይወት ይዞ ምጽዋ ለመድረስ ቻለ።

ዝንተዓለም ምጽዋ ላይ የሰው ልጅ ሳይበላ ያደረበት ቀን አልነበረም። የባሕሩ ጸጋ ምንጊዜም ኗሪ ነበር። የቀይ ባሕር አሳ ሳይነጥፍ ኖሯል። የደጋው አገር ስደተኞች ምጽዋ እንደደረሱ በፈገግታና በሃዘኔታ ተቀብሎ የሚያስተናግዳቸው የቀይ ባሕር ደረት ነበር። ቀድሞ የመጣ የደጋና የቆላ እንግዳ አሳ የማጥመዱን ጥበብ ለአዲስ መጪዎቹ ያሳያል። እንግዶች አሳ እየተመገቡ ባሕሩ ዳርቻ ይሰፍራሉ። ሰንበትበት ሲሉም ባሕሩ እርሻቸው ይሆናል።

በርግጥ ባሕሩ ሃብታም እና ሰፊ ነበር።

ቢታረስ አያልቅም። ሳይዘሩት ይሰጣል። ምርቱ ማቋረጫ የለውም። ጎተራው በገፍ ነው። ባሕሩ ምንጊዜም እንደ ባሕር አምላክ ቸር ነው። የሰማይ ዝናብ ቢከዳ ባሕር አይደርቅም። አሳ አይነጥፍም። አሳ 'አብሉኝ አጠጡኝ' አይልም። አሳ እንደ ዶሮ፣ እንደ ፍየል መች ሆኖ? ራሱን መግቦ ሲያበቃ ለሌላው ምግብ ይሆናል። አሳ አይከሳም። አሳ አይጠወልግም። አሳ አይራብም። ዝንተ አለም - ምድር ከተፈጠረች ጀምሮ...

ምእራፍ 3

ከብቦት ባላጋራ - ርቆት ባልንጀራ
መርዞ ገደለው - የቤት ውስጥ ዳሞትራ

ኑረነቢ ከሁለት ቀናት የምጽዋ ቆይታ በሁዋላ ታላቅ እህቱን አፈላልጎ ለማግኘት ቻለ። ረፋዱ ላይ ልጆቹን ይዞ ከእህቱ ጎጆ ሲገባ መርየም መጀመሪያ አላወቀችውም። ግር አላት። በመቀጠል ግን እጆቿን ራሷ ላይ ጠምጥማ ኡኡታዋን አስነካችው። ታናሽ ወንድሟ መቃብር ፈንቅሎ የወጣ አስከሬን እንጂ፤ ህይወት ያለው ሰው ሊመስላት አልቻለም። ረጅም መንገድ ተጉዘው ለመጡት እንግዶች የሚጠጣ ውሃና የሚቀመስ ነገር ማቅረብ እንዳለባት እንኳ የተረዳችው ዘግይታ ነበር። እንባዋን ዘርግፋ፣ ዘርግፋ ሲወጣላት መንጎዳጎድ ጀመረች። ውሃ አቅርባ አጠበቻቸው። ጨርቅ ለወጠችላቸው። የሚጠጣና የሚበላ ቤት ውስጥ የተገኘውን አንድም ሳታስቀር ዘረገፈችላቸው። ያላደረገችው የቀረ ነገር ያለ ይመስል ወደ ደጅ እየወጣች፣ መልሳ እየገባች እንዲሁ በጭንቀት ሁለት ሶስት ቀናት ያለ እንቅልፍ፣ ያለ መንፈስ እረፍት አሳለፈች።

እንግዶቹን በተቻለ አቅሟ እየተንከባከበቻቸው፣ በቂ ምግብና በቂ እረፍት ካገኙ በሁዋላ የልጆቹም የአባታቸውም ፊት መለስ አለ። በስድስተኛው ቀን ለመጀመሪያ ጊዜ ከንፈራቸው ተፈልቅቆ ፈገግታ የሚመስል ነገር አሳዩ። የሞከሩት ፈገግታ ምስሉ

አሰቃቂ ቢሆንባት መርየም ሰቆቃው ሊገድላት ደረሰ። በመሳቀቅ ብቻ አላበቃችም። እንባዋን ማቆም እስኪቸግራት ስሜታዊ ሆነች።

ኑረነቢ በእህቱ ቤት በቆየባቸው ጥቂት ቀናት አንዳንድ ነገሮችን መታዘብ ቻለ። ማለትም እህቱ ኑሮዋ "እዚያው ሰራች - እዚያው በላች" ነበር። ገቢዋ ለቀን ጉርሻ መሆኑን ተረዳ። ከማረፊያ ቤቷ ደጃፍ ላይ ከሰል እየቸረቸረች የምታገኘው ገቢ ለራሷም የሚበቃ አልነበረም። በመጡባት እንግዶች መደናገጧ በግልጽ ታየ።

የታላቅ እህቱን ችግር ከተገነዘበ በሁዋላ ኑረነቢ የአባትነት ተፈጥሯዊ ግዴታውን መወጣት እንዳለበት ከራሱ ጋር መከረ። እናም በሰባተኛው ቀን ማለዳ እንደተለመደው የተገኘውን ቁርስ ከቀማመሱ በሁዋላ፤ ስራ ሰርቶ ቤተሰቡን መርዳት እንደሚገባው እህቱን በማሳመን ከቤት ወጣ። ምን መስራት እንደሚችል፣ እንዴት ስራ ማግኘት እንዳለበት ግን እህቱ በምክር ልታግዘው አልቻለችም። ሆኖም ምርጫ አልነበረውም። የኢጣልያ ቅኝ ገዢዎች ወደ ሰፈሩበት ወደ ቀለጠው መንደር፣ ወደ ባሕሩ ዳርቻ በተስፋ አዘገመ።

እስከ እኩለ ቀን በወደቡ ደጃፍ አካባቢ ከመዘዋወር በቀር ሊያደርገው የሚችለው ነገር አልነበረውም። የምጽዋ እምብርት ግርግር አስገረመው። እንዲህ ያለ የደመቀ ከተማ ሲመለከት ለመጀመሪያ ጊዜ ነበር። በተለይም የወደቡ ደጃፍ ትኩረቱን ለመሳብ ቻ። ከወደቡ በርካታ ፈረሶች እየተነዱ በመውጣት ላይ ነበሩ። ኑረነቢ ለፈረስ እንግዳ አይደለም። በአንድ ወቅት የራሱ ፈረሶች ነበሩት። እነዚህ ከወደቡ ሲወጡ የሚያያቸው ፈረሶች ግን እሱ ከሚያውቃቸው ፈረሶች በእጥፍ ይገዝፋሉ። ከዝሆን ከሚስተካከሉት ፈረሶች ላይ አይኑን መንቀል ሳይችል ብዙ ቆየ። ፈረሶቹ በጣልያን ጎረምሶች እረኛነት እየተነዱ ከወደቡ ወጥተው ሲያበቁ የወደቡ ዋና የመግቢያ በር ተዘጋ። መዝጊያው ሲዘጋ፤ ጀርባውን ለወደቡ በመስጠት ወደ ሞቀው መንደር አዘገመ። ቁምጣ የለበሱ ወጣት ኢጣልያውያን አራት - በአራት በሆነ ረድፍ በሰልፍ ባጠገቡ ሲያልፉ ቆሞ ተመለከታቸው። አንድ ሰው መስለው ታዩት። ግንባራቸውን አኮስትረው ፊት ፊታቸውን ከመመልከት በቀር ግራና ቀኝ አይገላመጡም። የሚያየው አዲስ ነገር የህልም አለም መሰለው።

ወደ ባሕሩ ተጥግቶ ሲመለከት ብዛት ያላቸው መርከቦች

ወደብ ላይ ቆመዋል። የሚገቡና የሚወጡ መርከቦችም ነበሩ። ከዚህ ቀደም ሰምቶት የማያውቀው አይነት ደማቅና ሃይለኛ የጥሩምባ ድምጽ እያሰሙ ይገባሉ፣ ይወጣሉ። ወደ ግብጽ አግጣጫ ወይም ወደ ህንድ አግጣጫ ይጓዛሉ። መርከቦቹ ወደቡ ላይ ተጠጋግተው ሲጋፉ ውሃ የተጠሙ ግመሎች ይመስላሉ። በሌላ በኩል እንዲሁ ግራጫ ቀለም ያላቸው ጀልባዎች በማእበሉ ይጫወታሉ። ጀልባዎቹ ከመርከቦቹ ሲተያዩ የታሰሩበትን ገመድ በጥሰው፤ ከእናታቸው ጡት ለመጥባት የቸኮሉ ግልገሎች ይመስላሉ።

በሚያየው እየተደነቀ በምጽዋ ከተማ፣ በባሕሩ ዳርቻ እና በገበያዎች መካከል ሲዘዋወር ካረፈደ በሁዋላ የምሳ ሰአት ሲቃረብ ወደ እህቱ ቤት ተመለሰ። ስለተመለከተው ነገር ለልጆቹና ለእህቱ ለመናገር ፈልጎ ቃላት አጠረው። በተለይም በግምት ከሰላሳ በላይ የሚሆኑት ወደቡ ላይ የቆሙ መርከቦች ጉዳይ ከአእምሮው ሊጠፋ አልቻለም። እነዚያ ሁሉ መርከቦች ወደ ምጽዋ ምን ይዘው እንደመጡ እህቱን ሲጠይቃት ፈገግ ብላ እንደ ዋዛ መለሰችለት፣

“ብዙ ነገር እያመጡ ነው። እህል ያመጣሉ። ጠመንጃና ጥይት ያመጣሉ። በፈረስ የሚጎተቱ፣ ከብረት የተሰሩ ትልልቅ ነገሮች ያመጣሉ። ጦርነት ላይ ይተኩሳሉ ይባላል። መርከቦቹ ወታደሮችንም ያመላልሳሉ። ጥልያን ጠቅልላ እየገባች ነው። መሸት ሲል ወጥተህ ብታያቸው ባሕሩ ዳርቻ መቀመጫ ቀርቶ መቆሚያ አታገኝም። ሲበሉ፣ ሲጠጡ፣ ሲዋኙ ያመሻሉ። ከእነዚህ የሚበዙ ጥልያኖች ደ’ሞ ወደ ሰሓጢ፣ ዳህላክ፣ ዙላ፣ ሕርጊጎ ሄደው ሰፍረዋል ይባላል።”

ኑረነቢ፣ “ለመሆኑ ያገሩ ሰው ምን እያለ ነው?” ሲል ጠየቀ።

መርየም እያመነታች ምላሽ ሰጠች፣

“የተደባለቀ ነው። አንድ ሰሞን ‘ኮሌራ የታመሙትን እየሰበሰቡ ከእነ ህይወታቸው ያቃጥላሉ’ የሚል ወሬ ተሰምቶ ፍርሃትና ድንጋጤ ነበር። በተቀረ ግን በጥልያን መምጣት ተጎዳን የሚሉት ግብጾችና ቱርኮች ናቸው። ድሃው ሲያማርር አልተሰማም። የቱርክን ክፋት ስላየ ይሆናል። እዚህ አገር ስንት ግፍ ይሰራ ነበር? ነጋዴዎች ልጆችን እያመጡ እዚህ ለአረቦች ሲሸጡ ኖረዋል። ጥልያን ከመጣ ወዲህ ግን ሰው መሸጥ ተከልክሏል። ጥልያኖቹ ለሽያጭ የመጡትን ባርያዎች ’ነጻ’ የሚል ወረቀት እየሰጡ ለቀዋቸዋል።

ጠንከር ያሉትን አስካሪ አደረጓቸው። ለሚያሰሩት ስራም ደሞዝ ይሰጣሉ። ብዙ አይደለም እንጂ እህል ያድላሉ። ባርያ ነጋዴዎቹን ግን አጥፍተዋቸዋል፤ አላህ ከሪም!"

ኑረነቢ በመደነቅ በእጆቹ አፉን ያዘ፣

"ላስመሐላህ! ሰው ፍየል አርብቶ ይሸጣል እንጂ የአላህን ፍጡር እንደ እንስሳ መሸጥ ሃጢአት ነው።"

"እምን ካብሪኹ! (እውነት ብለሃል።) እንዳየነው መቸም ጥልያኖች ለሰው አከብሮት አላቸው። እስካሁን ክፉ አመል አላየንባቸውም። መስራት እንጂ መተኛት አያውቁም። እኛ መቸም መኝታና ወሬ እንወዳለን። አንድ ጥልያን የሶስት ሰው ያህል ሲሰራ አይተናል። ሰነፍ አይወዱም። ያልጸዳ አይወዱም። ቆሻሻ የለበሰ ሲያገኙ በዱላ እየመቱ ከነልብሱ ውሃ ውስጥ ይጨምሩታል። ሰዎችን በስም መጥራት ግን አይሆንላቸውም። በአሸከርነት የቀጠሩትን ወንድ ሁሉ ማርዮ ይሉታል። ገረዷን ደግሞ ማርያ ብለው ይጠሯታል። ስምህን ብትነግራቸው አይሰሙህም። መልሰው ማርዮ ይሉሃል። ይሄ መቸም ነውር ነው። ሁሉም የየራሱ ስም አለው። ባገራችን ውሻና ከብት እንኳ ለየብቻ ስም አላቸው።"

እየሳቀች ወጓን ቀጠለች፣

"ከቱርክና ከግብጽ ሲተያዩ ግን ይሻላሉ መቸም። እንደ ቱርክ ጨካኝ አይደሉም። እየሰሩም፣ እየበሉም መጫወት ነው። ሲናገሩም፣ ሲቆጡም፣ ሲያመሰግኑም ድምጻቸው ከሩቅ ይሰማል። መቆጠብ አያውቁም። ጭምት አይወዱም። ውለው አድረው ጠባይ እንዳይቀይሩ እንጂ መቸም እስካሁን . . . "

ኑረነቢ ምሳ ቀማምሶ ሲያበቃ እንደ አገሩ ልማድ እስከ ተስያት ተኛ። ጸሃይ በረድ ሲል እንደገና ቡና ቤቶች ወደበዙበት የወደብ ደጃፍ ሄደ። እስከ እኩለ ሌሊት ከአንዱ ግድግዳ ጥግ ወደ ሌላው ግድግዳ ጥግ እየተዘዋወረ ከመታዘብ በቀር ደፍሮ ስራ መጠየቅ አልቻለም። የሚታየው የሰው አይነትና ብዛት ጭንቀት ለቀቀበት። እህቱ እንደነገረችው ሆኖ አገኘው። ጣልያኖች፣ አረቦች ቱርኮች፣ ህንዶች በደመቁ መንደሮች ውስጥ በከፍተኛ ድምጽ እያወጉ ይበላሉ፣ እየሳቁ ይጠጣሉ፣ በደስተኛ መንፈስ ይዝናናሉ።

የምጽዋ ነዋሪዎች የተለያየ ዘር፣ ባህልና ሃይማኖት ጥርቅም ነበሩ። ነጋዴዎች ብዛት አላቸው። የአውሮፓ ጀብደኞችም አሉ። ራሳቸውን Discoverer፣ Adventurer ሲሉ ይጠራሉ። የህክምና እርዳታና የቀለም ትምህርት ለመስጠት፣ ስለ እየሱስ ክርስቶስ ለመስበክ መምጣታቸውን የሚናገሩ ስዊድናውያንም የምጽዋ ዋና ባልደረቦች ሆነዋል። ወደ መካ መዲና የሚሻገሩ፤ እየሩሳሌም ደርሰው የሚመለሱ ተጓዦች መሰንበቻቸው ምጽዋ ነው። የወጣት ኮማሪዎች አይነትና ብዛት የምጽዋ እለታዊ የምሽት ትርኢት ሆኗል። ተስያቱን ተኝተው ውለው፤ በጀንበር ግባት እንደ አደይ አበባ ምጽዋን ያለብሷታል። ጥቁሮች፣ አረቦች፣ ጠይሞች፣ ነጮች ኮማሪዎች ሰውነታቸው ላይ ጨርቅ ቢጤ ጣል አድርገው በፈገግታቸው ብርሃን ቀይ ባሕርን ያደምቁታል። ሊሸጡ የመጡ ባሮችም በምጽዋ የገበያ ማእከል ይታያሉ። ባርያ ፈንጋዮች ከኢጣልያ ካራቢኔሪዎች እየተሸሸጉ የባርያ ኮንትሮባንድ ንግድ ያካሂዳሉ። ገዢና ሻጭ በጨለማ ውስጥ እየተስማማ ከአቢሲንያ እና ከደጋው ኤርትራ ታፍነው የመጡ ልጆችን በጀልባ ወደ አረብ አገራት ያሻግራል።

ምጽዋ የአፍሪቃ ቀንድ በር ሆና እያገለገለች ነበር። ወርቅ፣ ዝባድ፣ የዝሆን ጥርስ፣ ቆዳ፣ ቅቤ፣ ከብት፣ በግና ፍየል እና ቡና መውጫው የምጽዋ ወደብ ነበር። ግመሎች፣ በቅሎችና ፈረሶች እነዚህን ሸቀጦች እየጫኑ ምጽዋ ይገባሉ። ከሚገባው የሚወጣው ይበዛል። የመን፣ ግብጽ፣ ሳዑዲአረቢያ፣ ህንድና ኢጣልያ ዋና ተቀባዮች ነበሩ። ከሚገቡ እቃዎች ጨርቅ ይበዛል። ከብረት የተሰሩ መሳሪያዎችና መስታወት ይከተላል። ስኳርና ሳሙና፣ ጠመንጃዎችና ጥይቶች በልዋጩ እየተጫኑ ምጽዋን ያጨናንቃሉ። ኢጣልያ እስኪመጣ ህንዶችና አረብ ነጋዴዎች ምጽዋ ግዛታቸው ነበር።

ይህን መሰል ጥርቅምና ድብልቅ ታዲያ በአንዲት ጠባብ ከተማ ውስጥ ግጭት መፍጠሩ የማይቀር ነበር። በቋንቋ አለመግባባት፤ በባህል አለመጣጣም፤ በኮማሪዎች መጋጨት በተደጋጋሚ ያጋጥማል። ጫጫታ ሳይሰማ ጥቂት መቆየት አይቻልም። የአረብኛ፣ የትግርኛ፣ የኢጣልያንኛ፣ የፐርሺያንኛ ስድቦች አየሩን ይሞሉታል። የቀይባሕር ማእበልም በራሱ ነባር ድምጽ እንደ ትራንፔት ጫጫታውን ያጅባል። እና ምጽዋ እንዲሁ ይነጋላታል። ማለትም ከመንጋቱ በፊት ሁሉም ወደ እለታዊ ተግባሩ ይበታተናል።

ኑረነቢ በዚህ በመጀመሪያው ምሽት አለቦታዋ ተገኝታ የደነገጠች ጥንቸል የሆነ መሰለው። ድብልቆቹ ሰዎች የሚናገሩትን ቋንቋ መለየት አልቻለም። ከአቀንቃኞች የሚወጣው ዜማ፣ የሚጫወቱት የሙዚቃ መሳሪያ፣ የኮማሪዎቹ ብዛትና ድምቀት በቀለማት ካሸበረቁት ማሾዎች ጋር ተደበላልቆ ረበሸው። እርቃን ከመሆን ለጥቂት ካመለጠ ሰውነታው ላይ አይኑን መንቀል ተቸገረ።

በነጋታውም እንዲሁ አደረገ።

የምጽዋ ሰዎችን የአሳ አጠባበስ ልማድ ሲመለከት፣ የነጋዴዎችን አለባበስና አነጋገር ሲታዘብ፣ በሙዚቃውና በኮማሪዎች፤ ገበያው ላይ በፈሰሰው የሸቀጥ አይነት ሲገረም ዋለ። በጠባቦቹ መንገዶች እየተዘዋወረ የቤቶቹን አሰራር፤ በቄንጠኛ ዲዛይን የተዋቡ መዝጊያና መስኮቶችን አድንቆ መጨረስ አቃተው።

ወደ ከተማው በተመላለሰ መጠን ቀስበቀስ መላመድ ጀመረ። እንግዳ መሆኑን የተገነዘቡ ኮማሪዎች ከሰረገላዎች ላይ እቃ እንዲያወርድ ጠየቁት። በዚህም ለመጀመሪያ ጊዜ ምሳውን መብላት ከመቻሉም፤ ተጨማሪ አንድ ሊሬ በማግኘቱ በእጅጉ ተደሰተ። መነቃቃት ጀመረ። በዚያን እለት እኩለ ሌሊት ላይ ወደ እህቱ ቤት ሲመለስ ጥቂት ዳቦዎችና ስኳር መግዛት በመቻሉ ሰርቶ ልጆቹን መርዳት እንደሚችል በማሰብ ተስፋ አደረገ።

* * *

በዚያው ሰሞን አንዲት ቱርካዊት ሴት ለምግብ ቤቷ በረዳት ዘበኛነት ቀጠረችው። "ሽማል ሽርቅ ሬስቶራንት" የተመሰገነ የአሳ ጥብስ በማቅረብ የከተማውን ነጋዴዎችና ሹማምንት በደንበኛነት መያዝ የቻለ ነው። ሲመሽ የሰረገላ ማቆሚያ ቦታ አይገኝም። የፈረስና የበቅሎ ድምጽ እንደ አርኬስትራ ባንድ አካባቢውን ያደምቀዋል። የማእበሉ ድምጽም የፈረሶቹን ማሽካካት ያጅበዋል። በመውጣትና በመግባት ሂደት ሰረገላዎች ርስበርስ እንዳይጋጩ፤ መንገድ መምራትና ማስተናበር የኑረነቢ የምሽት ዋና ስራ ነበር።

ሰረገላ ካልበዛ ኑረነቢ ብዙም ስራ አይኖረውም። ርግጥ ነው የሸክም ነገር ሲያጋጥም የሱ የስራ ድርሻ ነው። ከገልዓሎ፣ ከሰሓጢ፣ ከሕርጊጎ ወይም ከዊዓ ሲገሰግሱ የመጡ እንግዶች ሲያጋጥሙም

የሰረገላቸውን አቧራ በማራገፍ ሰረገላ ነጂዎችን ያግዛል። ለፈረሶችም የሚጠጣ ውሃና ምግብ ያቀርባል። ማለዳ ላይ ደጃፉን ሙልጭ አድርጎ መጥረግ ከተጨማሪ ተግባራቱ አንዱ ነው። ርግጥ ነው፤ እንዲህ ያለው ስራ የራሱ ጌታ ሆኖ ለኖረው ኑረነቢ የሚስማማ አልነበረም። ከቅድመ አያቶቹ የወረሰውን የቀድሞ ክብሩን እያስታወሰ መሳቀቁ አልቀረም። ሌላ አማራጭ ግን አልታየውም።

ስራ በጀመረ በሁለተኛው ሳምንት አንድ ምሽት ከበድ ያለ እንግዳ ወደ ሬስቶራንቱ መጣ። ገጽታው ኮስታራ ቢመስልም በከፍተኛ ድምጽ መሳቅ የሚወድ ነበር። ባለ ረጅም አፍንጫ ሲሆን፤ ክብ ጢም ነበረው። ሰውነቱ ላይ ትርፍ ስጋ የለውም። ከሰረገላው ወርዶ ወደ ሬስቶራንቱ እስኪገባ ብቻ ሁለት ጊዜ ሳቀ። ይህ ከባድ እንግዳ ቁምጣ ለብሶ፣ ሸበጥ ተጫምቶ አንድ ኢጣልያዊ ወንድና አንዲት ቱርካዊት ሴት አስከትሎ ከሰረገላ ሲወርድ በአካባቢው የነበረ ሁሉ ከየተቀመጠበት እየተነሳ በክብር ሲቀበላቸው ባለስልጣናት ሊሆኑ እንደሚችሉ ኑረነቢ ጠረጠረ።

ሶስቱ እንግዶች ከገቡ በሁዋላ ሰረገላ ነጂው ወደ ኑረነቢ መጥቶ በወዳጅነት መንፈስ ተዋወቀው። ቄንጠኛ ነበር። ያለማቋረጥ ጥርሱን በእንጨት ያጸዳል። የትኩስ ወተት አረፋ የመሰሉ ጥርሶቹን እንደ ጌታው ለደመቀ ሳቅ እንደሚጠቀምባቸው አሳየ። በአረማመድና በአለባበሱ፣ በአነጋገርና በአስተያየቱ ራሱን እንደ ሰለጠነ ሰው የሚቆጥር ነበር። ከሰላምታ በፊት ኑረነቢን እንዲህ ሲል ጠየቀው፣

“እዚህ የነበረው ዘበኛ ተባረረ እንዴ?”

“ላላ! እኔ ረዳቱ ነኝ።”

ሰረገላ ነጂው ቀብረር እያለ ራሱን አስተዋወቀ፣

“ጊላጊዮርጊስ እባላለሁ።”

ኑረነቢም ስሙን ተናገረ።

በመቀጠል ከአንድ ርእሰ ጉዳይ ወደ ሌላ እየዘለለ ለፈለፈ፣

“ባጭሩ ሰው ሁሉ ጊላጊ ብሎ ነው የሚጠራኝ። ባለፈው ሳምንት እዚህ መጥቼ ነበር . . . አንተን አላየሁህም . . .ለመሆኑ እዚህ መቸ ስራ ጀመርክ? . . . ከየት መጣህ? . . . ከሓልሓል ቦጎስ? .

. . የት ነው እሱ ባክህ? . . . ከረን አልፈህ? . . . ከሓጋዝ ወደ ግራ? . . . በዚያ መስመር ሄጀ አላውቅም . . . እኔ ከከበሳ ነኝ።"

"ከበሳ ከየት?"

"ኩዶፈላሲ። እንዴት ያለ ለምለም አገር! እርሻ እጣ ክፍሌ ስላልሆነ ተውኩት እንጂ አገሬ እንኳ ሃብታም ነበር። የሰጡትን ሁሉ በገፍ መልሶ ይሰጣል። እምቢ አያውቅም። ቢቆፈር ታቹ ውሃ ነው። የእህል አገር። ዋልካ ነው መሬቱ። አሸዋ የሚባል የለውም። ከኩዶፈላሲ ሲወዳደር ጽልማ ምንድነው? ሓልሓለ ብትል፣ ተራ እምኒ ብትል፣ ሰምበል፣ ዓዲኳላ፣ ጎዳይፍ የፈለከውን ብትጠራ አይገናኝም። መረብ ምላሽ ላይ የኩዶፈላሲን የመሰለ መሬት ፈልገህ አታገኝም። ዓዲ ጠስሚ፣ ዓዲ መዓር፣ ዓዲ ሺሻይ..."

ኑረነቢ ወሬ ቀየረ፣

"ያመጣሃቸው እንግዶች ማናቸው?"

ጊላጊ በኩራት አብራራ፣

"ጄኔራል ሳሌታ መሆኑን አላወቅህም?"

"አላወቅሁም። ማነውሱ?"

"እንግዳ በመሆንህ ነው አለማወቅህ። ምጽዋ ላይ ሁሉን አድራጊ ነው። ጥልያን ምጽዋ ሲገባ ሰራዊቱን እየመራ በቅድሚያ የምጽዋን መሬት የረገጠው ሳሌታ ነው። ቁምጣ አድርጎ አይተኸው ነው። ሲለብስ ተወው። ግርማው አራዊትን እንኳ ያሰግዳል። ሳሌታ በጣም ደግ ሰው ነው። አንድ ጠብታ ክፋት እንኳ ልቡ ውስጥ አይገኝም። እሁድ ማለዳ ቤተክርስትያን ደርሶ ሲመለስ ባሕሩ ላይ ከወታደሮቹ ጋር ኳስ ይጫወታል። ከባድ ስራ ወደሚሰሩት እየሄደ ያግዛል። ከስራ ውጭ ከማንም ጋር እንደማንኛውም ሰው ነው። የኛ አገር ባላባት ቢሆን ከእግዚአብሄር በላይ ክብር ይፈልጋል..."

ኑረነቢ በትኩረት እንደሚከታተለው ተረድቶ ቀጠለ፣

"ሳሌታ ተቀይሮ ወደ ሮማ ተመልሶ ነበር። ከዶጋሊ እልቂት በሁዋላ ደ'ሞ መልሰው አመጡት። የሳሌታ ልዩ ጠባይ ምን መሰለህ? አቤቱታ ማሳደር አያውቅም። በሰረገላ እየሄደ እንኳ እዚያው ቆርጦ ለባለጉዳዩ ይወስናል። አንድ ጊዜ ያለ አጃቢ ወደ ባሮች ገበያ ሹልክ

ብሎ ሄዶ መሃላቸው ገባ። ነጋዴዎቹን በሽጉጥ እየነዳ፣ በሽመል እየደበደበ እስር ቤት ጨመራቸው። ንብረትና ገንዘብ ውርስ! ጀልባ ላይ ሊጫኑ የተዘጋጁትን ባሮች ነጻ አወጣቸው። ባለጀልባዎቹ ወደ ናኹራ እስራት ቤት ተላኩ! ጀልባ ውርስ! ቻው!! ቆሎ ጥጥቆ አያውቅም። ሲወስን አንጀት ያርሳል።"

ጊላጊ ሲጋሩን ለኮሰና አንድ ጊዜ መጠጠ፣

"በመጀመሪያ ነጻ ከወጡት ሶስት ልጃገረዶች ጋር እዚህ ሬስቶራንት መጥቶ፤ ሽሪምፕ አዝዞላቸው አብሯቸው ራት ሲበላ ሰው ሁሉ ጉድ አለ። አንዲት የከበሳ ሴት እልልታዋን አቀለጠችው። መሬት እየሳመች አደይ ማርያምን አመሰገነች። ከዚያ በሁዋላ ማን ደፍሮ በግልጽ ባሪያ ሊነግድ? እየተደበቁ በዚህ በገልዓሎ፣ በዙላ፣ በአዱሊስ፣ በሕርጊጎ፣ በበይሉል በኩል መነገድ ቀጠሉ። ይህም አልተመቻቸውም። መቶ ባርያ እንደ ግመል እየነዱ ተደብቀው ባሕሩ ጋር መድረስ አስቸገራቸው። ጀኔራል ሳሌታ ወሬውን ሲሰማ 'ባርያ ሲነግድ ያገኛችሁትን ተኩሳችሁ ምቱ' ሲል አዘዘ። አረቦቹ ግን እየተገደሉም፣ እየታሰሩም እዚሁ አፍንጫችን ስር ይነግዳሉ።"

"መቶ ባርያ በአንድ ጊዜ?"

ጊላጊ ሳቀ፣

"ምንድነው የምታወራው? ጥልያን ከመምጣቱ በፊት ሁለት መቶ የሚደርሱ ባርያዎች በሶስት አረቦች እየተነዱ ምጽዋ ሲገቡ በአይኔ አይቻለሁ። ያውም እንደ አጋሰስ ጭነት ነበራቸው። የነብርና የአንበሳ ቆዳ እያሸከሙ ነው የሚያመጧቸው። አንዳንዴም የዝሆን ጥርስ! የምጽዋ ዋና ንግድ ባርያ ሆኖ ነው የኖረው።"

ሲጋራውን ረጋገጠና ወሬ ቀየረ፣

"ጀኔራል ሳሌታ የሰው ልክ ያውቃል። በሰረገላ ነጂነት ከሰለጠንነው መካከል እኔን ሲመርጥ ጥቂት እንኳ አላመነታም። መረጠኝና የሰረገላውን ሉጋም ሰጠኝ። በችሎታዬ አላፈረም። ከጠበቀኝ በላይ እያገለገልኩ ነው። የኔ ጠባይ እንደ ጥልያን ነው። ንጽህናና ስራ እወዳለሁ። ፈረሶቼ ታመው አያውቁም። አንድም ቀን እግራቸው አልቆሰለም። እራሴ ነኝ የማጥባቸው።"

ኑረነቢ ራሱን ነቅንቆ ዝም ሲል ጊላጊ ቀጠለ፣

“ከጀኔራሉ ጋር የመጣችው ሴት ቱርካዊት ናት። ሃሊማ ትባላለች። እዚህ ምጽዋ ስድስት የምታከራየው ቤት አላት። ሁለቱ ባሕሩ ዳርቻ ነው። አምስት የእንግሊዝ ጀልባዎች አሏት። ጥልያን ከመምጣቱ በፊት ኢዜት ቤይ ውሽማዋ ነበር። ሳሌታ ከመርከብ ወርዶ እግሩ መሬት ሳይረግጥ አጠመደችው። ሳሌታ ተቀይሮ ሲሄድ ጀኔራል ጀኔን ይዛ ነበር። ሳሌታ ተመልሶ ሲመጣ ደ’ሞ ተቀበለችው። ግብጾችን እያባረረች ቤቶቿን ሁሉ ለኢጣልያ መኮንኖች አከራየች።!”

ኑረነቢ እንዲህ ያሉ ንግግሮችን ሰምቶ ስለማያውቅ ግር ቢለውም ቀርቦ የሚያጫውተው ማግኘቱን ወዶታል። ስለሆነም በተቻለው መጠን ከጊላጊ ጋር ለመግባባት ጥረት አደረገ። ማለትም በየመካከሉ ብድግ እያደረገ ጥያቄ ጣል አደረገ፣

“ኢዜት ማነው?”

“ኢዜት ቤይ? ማታ ማታ እዚህ ይመጣል’ኮ። አላየኸውም? የምጽዋ ምክትል አገረ ገዢ የነበረ ግብጻዊ። ውሽሞቹንና ምጽዋን ለጥልያን አስረክቦ ሲያበቃ፤ ጉዳይ አስፈጻሚያቸው ሆኗል!”

ጊላጊ ኢዜት ላይ አላግጦ በራሱ ሽሙጥ መልሶ ሲስቅ ኑረነቢ በዝምታ አስተዋለው። ለምን እንደሚስቅ እንኳ አልገባውም። ለመተባበር ያህል አብሮ ለመሳቅም አልሞከረም። የረሃብ አደጋው ባደረሰበት መጎሳቀል ምክንያት ድምጽ አውጥቶ ከሳቀ ረጅም ጊዜ አልፎታል። በቀላሉ መሳቅ የሚጀምርም አልነበረም። የፋና የተከበረ ጭቃ ሹም በነበረበት ጊዜም እንኳ አፉን ከፍቶ የሳቀበት ጊዜ ስለመኖሩ ትዝ አይለውም። ኑረነቢ ጊላጊን በሳቅ ማጀብ ባይችልም ራሱን ላይ ታች እየነቀነቀ በጨዋታው ተሳተፈ።

“...የጥልያን መርከብ ምጽዋ ስትገባ እዚሁ ነበርኩ።” ሲል ጊላጊ ወጉን ቀጠለ፣ “. . .ኢዜት ቢያንገራግር የአሳ ምሳ ያደርጉት ነበር። ሃሊማ መክራው ይሆናል።”

ጊላጊ እንደገና በረጅሙ ሳቀ።

* * *

ኦቶማን ቱርክ ከ1557 ጀምሮ ለሶስት ምእተ አመታት ምጽዋና አካባቢዋን ሲገዛ ቆይቶ ነበር። ቱርክ ሲዳከም በ1866

ምጽዋን በኪራይ ለግብጽ አሳልፎ ሰጠ። ግብጽ ራሷም ጥገኛ ብትሆንም አካባቢውን የመቆጣጠር ፍላጎቷ የበረታ ነበር። ምጽዋን ብቻ ሳይሆን፤ ሱዳንን ተቆጣጥራ ሰሜንና ምእራብ ኤርትራን ስትደንስበት ሰንብታለች። በርግጥም ላሊበላ የጉዞ አግጣጫውን ሊያስቀይረው ተንቀሳቅሶ ነበር እየተባለ የሚነገርለትን የናይል ወንዝ ከምንጩ የመቆጣጠር ፍላጎቷ እንቅልፍ ነሺ ነበር። ሆኖም አድሚራል ከይሚ ምጽዋ ደርሶ መልህቅ ሲጥል የምጽዋ ምክትል አገረገዢዎች መርከቦቹ የመጡበትን ተልዕኮ እንኳ አላወቁም ነበር።

ነገሩ ድንገት የተፈጸመ አልነበረም...

ቄስ ጁሴፔና አባ ማስያስ ታህሳስ 15 1869 አሰብ ላይ ከባሕሩ ዳርቻ የገዙት መሬት ለመርከብ ማቆሚያ በሚል ሩባቲኖ የተባለ ኩባንያን ወክለው ነበር። ጊዜው ስዊስ ካናል የተከፈተበት፣ ፈረንሳይ መርሳ አቦክን የያዘችበት፣ እንግሊዝ ዓደን ላይ የሰፈረችበት ጊዜ ነበር። ለመርከብ ማቆምያ በሚል ለቄሶቹ መሬት የሸጡት ወንድማማቾች የሸኻት ጎሳ መሪዎች ሲሆኑ፣ ሱልጣን ሃሰን እና ሱልጣን ኢብራሂም ይባላሉ። ሁለቱ ወንድማማቾች ቁራጭ መሬት በስድስት ሺህ ባጤራ ለቄሶቹ ሲሸጡ፤ ሽያጩ ጂኦ ፖለቲካዊ አላማ ሊኖረው እንደሚችል ግንዛቤ አልነበራቸውም።

በ12ኛው አመት የኢጣሊያ መንግስት መሬቱን ከቄሶቹ ላይ በ417 ሺህ ሊሬ ገዛ። ተያይዞም በ1882 በወርሃ ሃምሌ ኢጣሊያ የአሰብን ግዛት እንደመሰረተች አወጀች። ኢጣሊያ ባንዴራዋን አሰብ ላይ ስታውለበልብ ከግብጽ አቅመ ቢስ ማለቃቀስ በቀር በተቃውሞ ድምጹን ያሰማ ሌላ አገር ወይም የጎበዝ አለቃ አልነበረም።

ኢጣሊያ ምጽዋ ስትገባ ከቱርክ ተቃውሞ ሊገጥማት እንደሚችል ግምት ነበራት። ሆኖም የእንግሊዝ ድጋፍ ስለነበራት እቅዷን ገፋችበት። ምጽዋን ለመያዝ እንደ ምክንያት ያቀረበችው ጉስታቭ ቢያንኪ የተባለ ኢጣሊያዊ አሳሽ ጥቅምት 1884 ደንከል ላይ መገደሉን ነበር። ይህን ሰበብ በማድረግ ጥር 25 1885 አንድ የኢጣሊያ ባህረኛ ቡድን በይሉልን ተቆጣጠረ።

በመቀጠል አንድ የኢጣልያ መርከብ ከሲራጉዛ ወደብ ተነስታ በቅድሚያ ሱአኪን ቆመች። ከዚያም ምጽዋ ወደብ ላይ መልህቅ ጣለች። በመርከቧ ላይ በኮሎኔል ታንክሬዲት ሳሌታ

የሚመሩ 38 የጦር መኮንኖች እና 767 ወታደሮች እንዲሁም ሁለት ተራ ሰራተኞች ነበሩ። የመርከቡ አዛዥ አድሚራል ከይሚ ፒየትሮ ወታደሮቹን ምጽዋ ከማድረስ ያለፈ ተልእኮ አልነበረውም።

የምጽዋ ገዢ የነበረው እንግሊዛዊ ኮሎኔል ቸርሚሰይድ የኢጣልያ መርከብ ምጽዋ ከመድረሷ በፊት ወደ ሱአኪን ገለል አለ። ወረራው ከእንግሊዝ ጋር በተደረገ ስምምነት እንደሚፈጸም ቀድሞ ማወቁ ይገመታል። ምክትል አገረ ገዢው ኢዜት ቤይና ዋና ጸሃፊው ማርኮ ፖሎ ቀልድ አዘል ተቃውሞ እያደረጉ ኢጣሊያን አስተናገዱ። ነገሩ ያልገባቸው አንዳንዶች ከልባቸው ለመቃወም ቢሞክሩም ማርኮ ፖሎ ገሰጻቸው። የምጽዋ በኢጣልያ መያዝ በዚሁ አበቃ። እናም ከቀናት በሁዋላ የግብጽ ባንዲራ ወርዶ የኢጣልያ ተውለበለበ።

ከሳምንታት በሁዋላ ኢጣልያ ኡምኩሉና ህጥምሎን ደገመች። በተከታታይ መስፋፋቱ ቀጠለ። በሚያዝያ ወር ሚረፋይለን እና ሕርጊጎን ያዙ። ሁለት ወራት ቆይተው የዳህላክ ደሴቶችን፣ አከታትለው ከሶስት ቀናት በሁዋላ ደግሞ ሰሓጢን ተቆጣጠሩ። ኢጣሊያውያን በመስፋፋቱ ሂደት የመጀመሪያውን ቆንጣጭ ፈተና ያስተናገዱት ጥር 1887 ዶጋሊ ላይ ነበር።

ራስ አሉላ ከአስር ሺህ በላይ የሚገመት ሰራዊት ይዞ ሰሓጢ ላይ የመሸገውን በማጆር ቦረቲ የሚመራውን ሃይል ለማጥቃት ሞከረ። በርግጥ አጤ ዮሃንስ አሉላን ወደ አካባቢው የላከው ኢጣልያ መስፋፋቷን ወደ ደጋው እንዳትቀጥል ለመደራደር እንጂ ለውጊያ አልነበረም። አሉላ አራት ሰአታት በወሰደው የሰሓጢ ውጊያ በመቶዎች የሚቆጠሩ ወታደሮቹን ገብሮ ሲያበቃ፤ ከአራት ቁስለኞች በቀር በኢጣሊያ ሰራዊት ላይ ያደረሰው ጉዳት አልነበረም። ግጭቱ ሲከሰት በነጋታው ዋና አዛዡ ጀኔራል ካርሎ ጆኔ ኡምኩሉ የሚገኘውን ሰራዊት ለእርዳታ ወደ ሰሓጢ ላከው።

ዶጋሊ ከኡምኩሉ ፲፩ ኪሎሜትር ይርቃል። ኮሎኔል ቶማስ ዴ ክሪስቶፈርስ 540 ወታደሮች ይዞ ወደ ሰሓጢ ገሰገሰ። 22 መኮንኖችና ፲0 መድፎች ነበሩት። ራስ አሉላ ስለ አጋዡ ሰራዊት እንቅስቃሴ ቀድሞ መረጃ በማግኘቱ ዶጋሊ ላይ አሸምቆ ለእርዳታ ይገሰግስ የነበረውን ሃይል ገጠመው። በሌተና ኮሎኔል ዴክርስቶፈርስ ይመራ ከነበረው ሃይል ዘጠኝ ወታደሮች ሲያመልጡ ቀሪው የበረሃ፣

የጥይት እና የጎራዴ እራት ሆነ።

ከሶስት ቀናት በሁዋላ ሬሳ ለማንሳት ወደ ዶጋሊ የተላከው የኢጣልያ ቡድን አሰቃቂ ትርኢት ለማየት በቅቷል። የተገደሉት ወታደሮች ልብሳቸው ተገፎ ራቁታቸውን ነበሩ። አስከሬኖች በአሞራና በጅብ ተቦጫጭቆ አንዳንዱ ሬሳ ተበጣጥሶ ነበር። ራስ አሉላም ሳይታዘዝ በፈጸመው በዚህ ድርጊቱ ከስራው ተባርሮ በቅጣት ራስ ሓጎስ እጅ እንዲቆይ ተደረገ።

(የራስ አሉላ ማንነት ጉዳይ አከራካሪ ነው። የአባቱን ስም 'እንግዳ' ብለው የሚጽፉ ታሪክ ጸሃፊዎች አሉ። ብላቴን ጌታ ማህተመስላሴ ወልደመስቀል ጽፈውት አዲስአበባ ዩኒቨርሲቲ ያሳተመው "ቹ በለው" የተሰኘው መጽሃፍ ግን የአሉላ አባት ስም 'ቁቢ' እንደሆነ ይገልጻል። ይኸው መጽሃፍ አሉላ በትውልድ የሓማሴን ሰው መሆኑን አስፍሯል። የራስ አሉላ እናት ሃማሴናዊት ብትሆንም በአባቱ ከሳሆ ወይም ከኦሮሞ ወገን መሆኑን የጻፉም አሉ። የአሉላ ኦሮምነት የሚገመተው በአባቱ ስም ሲሆን፤ 'አሉላ' የሚለው ቃል በትግርኛ አንዳችም ትርጉም የለውም። በሳሆ ቋንቋ 'አሉሊ' ማለት 'ሃይለኛ' (አውሬ) ማለት ነው። ራስ አሉላ ለትግራይ መሳፍንት በሎሌነት በማደር ስመጥር ኮሎኔል ለመሆን የበቃ ሲሆን፤ የትግራይ ሰዎች ራስ አሉላ ከትግራይ የገበሬ ቤተሰብ የተገኘ 'ትግራዋይ' ነው ብለው ያምናሉ። ይህም 'በላይ ዘለቀ ጎጃሜ ነው' ተብሎ እንደሚታመነው፣ ናፖሊዮን ፈረንሳዊ መስሎ እንደሚታሰበው ማለት ነው።)

* * *

ጊላጊ ወጉን ቀጠለ፣

"ከጀኔራል ሳሌታ ጋር የመጣው ባልዲሴራ ይባላል። ገና ትናንት ነው ምጽዋ የደረሰው። ሳሌታ ከዚህ ይሰናበታል ይባላል። ሳሌታ ጥሩ አለቃ ነበር። ባልዲሴራ ደግሞ ይታያል እንግዲህ።"

ኑረነቢ በዝምታ ማዳመጡን ቀጠለ፣

"ሰሓጢ ካልሄድን ማታ ማታ ማምሻችን እዚሁ ነው።"

ከጥቂት ሰአታት በሁዋላ የሳሌታ ድምጽ ተሰማ። በመቀጠል ጀኔራሉ በእንግዶቹ እንደታጀበ ከሬስቶራንቱ ብቅ አለ። የጀኔራሉን ድምጽ ሲሰማ ጊላጊ ተፈናጥሮ ሲነሳና ሉጋም ሲይዝ አንድ ሆነ።

ጀኔራል መኮንኖቹ ሲጋራቸውን እያቦነኑ ተሳፈሩ።

ግዙፎቹ ፈረሶች በጥቂት ሰከንዶች ጊዜ ውስጥ ሰረገላውን እየጎተቱ ከኑረነቢ አይን ተሰወሩ። ኑረነቢ ሳይሰናበተው በድንገት ካጠገቡ በተሰወረው ሰረገላ ነጂ የፍጥነት ችሎታ በእጅጉ ተገርሞ ፈዝዞ ብዙ ቆየ። በቀሪው የህይወት ዘመኑ እንደ ጊላጊ ያለ ቅልጥፍና ሊኖረው እንደማይችል በማመን በራሱ ቀዝቃዛ ተፈጥሮ ላይ ቅሬታ ያደረበት ሲሆን፤ የከተማ ህይወት እንደማይመቸውም አሰበ።

ከዚያን ምሽት በሁዋላ ጊላጊ አለቃውን እየያዘ ደጋግሞ ወደ ሬስቶራንቱ በመመላለሱ ከኑረነቢ ጋር ቀረቤታቸው ጨመረ። ኑረነቢ በፖለቲካ ጉዳይ ላይ የመነጋገር ልምድ ባይኖረውም፤ ጊላጊ ዞሮ ዞሮ ወጎቹ ሁሉ በፖለቲካ ጉዳዮች ዙሪያ ነበሩ። ኑረነቢ በፖለቲካ ጉዳይ ላይ ፍላጎት ያጣው፤ ጊላጊ ስለሚያነሳቸው ርእሰ ጉዳዮች ቀደም ብሎ የሚያውቀው ነገር ባለመኖሩ ነበር። አልፎ አልፎ ግን በርእሰ ጉዳዮቹ ትኩረቱ ይሳባል።

አንድ ምሽት ጊላጊ የተለየ ዜና ይዞ መጣ፣

“ካፍል ጎፋር ከረንን እንደያዘ ሰምተሃል?”

“ባላምባራስ ካፍል?” ሲል በስሜት ጠየቀ።

“ሁለት ሰንበት አለፈ ከረንን ከያዘ። ከዚህ ሲሄድ ጣልያኖች 500 ጠመንጃ ጭነውለት ነበር። ይኸው ሰተት ብሎ ከረን ገባ። መቸም ከዚህ በሁዋላ ማህዲስቶችም ሆኑ ግብጾች ከረንን አያስለቅቁትም። ምናልባት ዮሃንስ ከመጣ ያሰጋዋል።”

ኑረነቢ በስሱ ፈገግ ብሎ አስተያየት ጣል አደረገ፣

“ካፍል የዶጋሊን ቁጭት ፈወሰላቸዋ?”

“አይ! የዶጋሊ መች በዚህ የሚፈወስ ሆኖ? ጥልያኖች አሉላን ማርከው በቁሙ ቆዳውን ካልገፈፉ በቀር ፈውስ አያገኙም።”

ኑረነቢ ለዘብ ብሎ ተስማማ፣

“አሉላን እንኳ እኛም ብናገኘው አንምረውም። ከሓልሓል ቦጎስ ይዘህ፣ መንሳዕ፣ ሓባብ፣ ኩናማና ባርያ ሁሉም አሉላ ላይ ቂም ይዟል። አሉላ ሙቹላ አዳም-ግን” (አሉላ ክፉ ነው።)

ኑረነቢ ስለ አሉላ አጫወተው፣

“መታሕት ለአሉላ ስለማንገብር በየአመቱ እየመጣ አሰቃይቶናል። ገበሬው አሉላ ሲመጣበት እህሉን መሬት ቆፍሮ ይቀብራል። የአሉላ ጀሌዎች ይህን ስለሚያውቁ ባቄላ እየቆሉ ትኩሱን በገበሬዎች ጆሮ ውስጥ ይጨምራሉ። እንዲህ ያለ ግፍ ሲፈጸምበት ገበሬው የደበቀውን እህል እያወጣ ይሰጣል። በዚህ ጦስ ስንቱ ንበዝ ጆሮው ተበላሽቶ ቀርቷል?”

ጊላጊ በበኩሉ የሰማውን አከለ፣

“የአሉላ ነገር የሚገርመኝ በከበሳ ጠጅ መጠጣት የሚከለክል አዋጅ ማውጣቱ ነበር። ለምን ሲባል ‘ጠጅ የመኳንንት መጠጥ ነው፤ ተራ ሰው ጠጅ ለመጠጣት ደረጃው አይደለም’ የሚል ምክንያት ሰጠ። እሱ ራሱ ግን ከገበሬ ቤተሰብ የተወለደ ነው። ደጃዝማች ሓድግ አምበስ ባልወት ልጁን ሲድር ለእንግዶቹ ጠጅ በማቅረቡ ምክንያት የአሉላ ሰዎች ሊያስሩት መጡ። ሓድግ አምበስ ግን ቀድሞ አሳባቸውን በማወቁ ወደ ሳህል ሸፈተ። ባለፈው እዚህ መጥቶ ከነተከታዮቹ ጠመንጃ ተቀብሎ ወደ ከበሳ ተመልሷል። ሲያጫውተን ምን አለ? በዚህ ዘመን የከበሳ ሰው ሶስት ጠላቶች አሉት። እነርሱም ድርቅ፣ አንበጣና አሉላ ናቸው። ከአሉላ ግን አንበጣ ይሻላል። ምክንያቱም አንበጣ ጎተራ መክፈት አይችልም።”

ጊላጊ እየሳቀ ቀጠለ፣

“ሓድግ አምበስ ሲያጫውተን አሉላ ከጦርነት በቀር ሌላ ሊሰራው የሚችለው ነገር የለውም። በሄደበት ሁሉ ገበሬውን እያስገደደ የራሱን እልፍኝና መኝታ ቤት ያስገነባል። ከዚያም ጦርነት ከሌለ አይኑን ጨፍኖ መከዳው ላይ መተኛት ነው። ረጅም ሰአት ይተኛል። እንቅልፍ ጠግቦ ሲነሳ ፍየል ወይም በግ ያሳርዳል። ደረቅ ጥብስ ከጠጅ ጋር ይቀርብለታል። ከዚያም ቡና ይፈላል። ከቡናው ጋር ቋንጣ እያኘከ የገበሬ አቤቱታ እየሰማ ይፈርዳል።”

ጊላጊ እንደ ልማዱ አለምክንያት በረጅሙ ሲስቅ፤ ኑረነቢ የዝምታ ጥልቅ ውስጥ ራሱን ቀብሮ አስተዋለ።

* * *

ዘመኑን መለስ ብሎ በሚዛን የሚፈትሽ ኑረነቢ ወይም ሓድግ አምበስ በአሉላ ላይ ያላቸውን አስተያየት መረዳት ይቻለዋል። ማለትም ኢጣልያም ሆነች የአቢሲኒያ የጎበዝ አለቆች ለአካባቢው ህዝብ በተመሳሳይ እንደ ወራሪ የሚታዩ ነበሩ። የአካባቢው ህዝብ ለራስ አሉላ ወገናዊ ሊሆን የሚችልበት በጎ ጎን አልነበረውም። በራስ አሉላ ሰራዊት ውስጥ በግለሰብ ደረጃ የኤርትራ ትግርኛ ተናጋሪዎች ተሳትፈዋል። በግልባጩ የዮሃንስና የአሉላን ተጽእኖ የተቃወሙ የመረብ ምላሽ ኤርትራውያን በኢጣሊያ ወገን ተሰልፈዋል። ባህታ ሓጎስ በራስ አሉላ እየታደነ በዓሳውርታና በሓባብ ይንቀሳቀስ ነበር። ሌሎች የመረብ ምላሽ ሰዎችም በተመሳሳይ ራስ አሉላ በምድሪ ባሕሪ በቆየባቸው ጥቂት አመታት በመከላከል ነበር ያሳለፉት። ግጭት የሚከሰተው እህል ሲገባ ነበር።

ህዳር 1886 ራስ አሉላ በናራ እና በኩናማ ህዝብ ላይ ይህ ወሰንህ የማይባል ግፍ ፈጽሞ ስለነበር ከኢጣሊያ መምጣት በፊት በተለይ የናራ ብሄር በታሪኩ አይቶት የማያውቅ ዘረፋና ግድያ አስተናግዷል። ኩናማ ከነንብረቱ የማለቅ አደጋ አጋጥሞታል። የካቲት 1886 ራስ አሉላ ሓባብ ምድር ላይ ባካሄደው ወረራ 400 ሰዎች ገድሎ፣ ንብረት ዘርፎ አገሩን አውድሟል። አጤ ዮሃንስ በጉንደትና በጉራእ ከግብጻውያን ጋር ያካሄደው ውጊያም ነዋሪውን ለሰቆቃ የዳረገ ነበር። ኩናማ እና ናራ ከኢጣልያ መምጣት በሁዋላ አንጻራዊ ሰላም ማግኘታቸውን መካድ አይቻልም። ጉልበት በተሰማቸው ቁጥር ብቅ የሚሉ የአካባቢ የጎበዝ አለቆች ያደርሱባቸው ከነበረው ግድያና ዘረፋ አረፍ ብለው ፋታ ማግኘት ችለዋል። ኢጣልያ መረብ ምላሽን እስኪቆጣጠር ድረስ በባርነት ይሸጡና ይለወጡ የነበሩ ሰዎችም ኢጣልያን እንደ ነጻ አውጪ ለመቀበል በቂ ምክንያት ነበራቸው። ኢጣልያ "ነጻ" የሚል ወረቀት እየሰጠ ከባርነት አላቋቸዋል። ከትግራይና ከማህዲስት ወራሪዎች ራሳቸውን ለመከላከል ሲሉ በገደል ላይ ጎጇቸውን ቀልሰው የዝንጀሮ ኑሮ ይኖሩ የነበሩ ጎሳዎች፤ ከኢጣሊያ መምጣት በሁዋላ ወደ ሜዳዎች መውረድ ችለዋል። እያረሱና እያረቡ አንጻራዊ ሰላም አጊኝተዋል። ዘመኑ ሁሉም በየራሱ የጎበዝ አሊቃ የሚመራበት ዘመን ስለነበር በአካባቢው አሰባሳቢ ማንነት አልነበረም።

ጊላጊ ሲጋሩን እየማገ አሳቡን ጣል አደረገ።

“ጥልያኖች ከካፍል ይልቅ በባህታ ይተማመናሉ።”

“ባህታ ለጥልያን ገበረ እንዴ?”

“300 ጠመንጃና ጥይት ከቀለብ ጋር ተጭኖለት ነው ከዚህ የሄደው። የራት ግብጥ ተደርጎለት ሲሰናበት አባ ዮሃንስ ከባህታ ጎን ተቀምጠው ተጋብዘዋል። ባህታ እዚህ በመጣ ጊዜ በሰረገላ እያዘዋወርኩ ከተማ አሳየው ነበር። መቸም ባህታ ከአጤ ዮሃንስ ነው ጠቡ። አሁን እንግዲህ በዚህም በዚያም ብሎ ደርጅቷል። የሓባብ ሰዎችንም ቢሆን ይዟል።” ፋታ ወሰደናም እንዲህ አለ፣ “በነገራችን ላይ ባህታ በእናቴ በኩል ዘመዴ ነው።”

“አባ ዮሃንስ ማናቸው?”

“የከረን ካቶሊክ? አልሰሙም ስለሳቸው?”

“አቡነ ቪካር ሲባል ነው የሰማሁት።”

“የከረን ሰው በተለምዶ አቡነ ቪካር ይላቸዋል። ስማቸው ግን አባ ዮሃንስ ነው። አባ ዮሃንስ ኩልቦ።”

ኑረነቢ ጥቂት ካሰላሰለ በሁዋላ እንዲህ አለ፣

“ባህታ አጤ ዮሃንስ ላይ ቢያምጽ እውነት አለው። ፊታውራሪ እምባየን ገድሎ አገሩ ሊቀመጥ አይችልም። ለጥልያን መገበሩ ግን ምን ሊያገኝ? የራሱ ጌታ ካልሆነ ምን ለየው?”

ጊላጊ ተጨማሪ መረጃ ደረደረ፣

“እዚህ መጥቶ ከሰነበተ፣ ስንቅና ጠመንጃ ከተቀበለ እንግዲህ ገበረ ማለት እንጂ ሌላ ምን ስም አለው? መች ባህታ ብቻ ሆኖ? አበራ ካሳም ገብሯል። ከከበሳና ከሓባብ ያልገበረ የለም። ከሓባብ ከንቲባይ ሓምድ ሃሰን፣ ከባርያ ሸኽ አረይ አገባ፣ ከቤንአምር ደግሊል አሊ ሃሰን፣ ከማርያ ሸኽ ሓምድ፣ ከመንሳዕ ብእምነት፣ ከዓሳውርታ ሸኽ ዑመር ለጥልያን ገብረው ጠመንጃ ተቀብለዋል። የለብካ ከንቲባ መሓመድ ሸኩርም መጥቶ ነበር። እሱ ብቻ እምቢ አለ። ዳሩ አገሩ ሳይደርስ ሞተ። ከዚህ ሲነሳ ጥልያኖች ከምግብ ጋር መርዝ አብልተው ነው የላኩት ይባላል።”

በዝና የሚያውቃቸው ባላባቶች እንዲህ ስማቸው ሲዘረዘር

ኑረነቢ በመደነቅ አዳመጠ። በተለይ ግን በቅርብ የሚያውቃቸው እነ ባህታ ሓነስ፣ እነ ከንቲባይ ሓምድ ሃሰን፣ የዓሳውርታው ሼኽ ዑመር ለኢጣልያ ገበሩ መባሉ የተአምር ያህል ሆነበት። ማመን ስለተቸገረም ጥርጣሬውን ጣል አደረገ፣

“ጠመንጃ ፈልገው ለመላ እንዳይሆን?”

“እሱ’ንኳ አላውቅም።” አለ ጊላጊ።

* * *

የዶጋሊ ጦርነት በአካባቢው ነዋሪዎች ብቻ ሳይሆን በአጤ ዮሃንስና በንጉስ ምኒልክ ጭምር የተደገፈ አልነበረም። በርግጥ ራስ አሉላ ዶጋሊ ላይ ያደረገውን ውጊያ ዮሃንስና ምኒልክ የኮነኑት በተመሳሳይ አመለካከት አልነበረም። ጉዳዩም አከራካሪ ነው።

የአጤ ዮሃንስ ዋና ስጋት ኢጣሊያኖች ወደ ደጋው እንዳይወጡ እንጂ በምጽዋ መከሰታቸው ላይ ሊባል አይችልም። ቀድሞውንም ምጽዋን አስተዳድረው አያውቁም። የዶጋሊ ውጊያ ከተካሄደ በሁዋላ አጤ ዮሃንስ ለራስ አሉላ በላኩት ደብዳቤ፣

“...እዚያ ሄደህ እንድትዋጋ ማን ፈቃድ ሰጠህ? ወታደሮቹ የኔ እንጂ ያንተ አይደሉም። ቀኝ እጅህን መቁረጥ ይገባኛል።” የሚል ይዘት እንደነበረው ሃጋይ ኤርሊክ ሳሊምቢኒን ጠቅሶ አሰፍሯል።

ራስ አሉላ እንዲህ ያለ ደብዳቤ ከአጤ ዮሃንስ መቀበሉን ማወቃቸውን በወቅቱ የአሉላ እስረኞች ከነበሩት ሁለቱ ፒያኖና ትራንክሬዲ ምስክርነታቸውን የሰጡ ሲሆን፤ ራስ አሉላ ደብዳቤውን ከንጉሰ ነገስቱ በተቀበለበት ምሽት አዝኖ ማየታቸውን ጽፈዋል።

በተከታታይ አጤ ዮሃንስ መጋቢት 26 1888 ምጽዋ ለነበረው የኢጣሊያ አዛዥ ለሳን ማርሳኖ በላኩት ደብዳቤ፣

“አሉላ ዶጋሊ ላይ ውጊያ ያደረገው ለኔ ሳይነግር ነው። የተፈጸመው ድርጊትም የሰይጣን ስራ ነው።” ሲሉ ገልጸዋል።

ምኒልክ ለኢጣሊያው ንጉስ ኡምቤርቶ በላኩት ደብዳቤ፣

“የጠየቅሁትን ጠመንጃና ጥይት ከላካችሁልኝ ዶጋሊ ላይ የፈሰሰውን የኢጣልያውያን ደም እኔው ራሴ እበቀልላችሁዋለሁ።”

ሲሉ ማስፈራቸውም ጠቋሚ መረጃ ነው።

ምኒልክና ዮሃንስ ይህን መሰል ደብዳቤ ለኢጣሊያ “አቻዎቻቸው” መጻፋቸውን አንዳንድ ጸሃፊዎች በትንታኔ አወንታዊ ትርጉሙን ለማብራራት ሙከራ ሲያደርጉ፤ ሌሎች ደግሞ ምናልባት በመሳቀቅ ሊሆን ይችላል አባባሎቹን ከማስፈር ተቆጥበዋል።

ከመነሻውም ግን ዮሃንስም ሆነ ምኒልክ ከኢጣልያ ጋር የነበራቸው ስምምነቶችና ግንኙነቶች አቻ ለአቻ የሚባሉ አልነበሩም። በተለይ ንጉስ ምኒልክ ኢጣልያውያን መረብን ተሻግረው አቢሲኒያን ለመውረር እስከሞከሩበት ጊዜ ድረስ፤ ከኢጣልያ ተወዳጅተው ስልጣናቸውን ለማደላደል ይጥሩ ነበር። የአጤ ዮሃንስ የጥንካሬ ምንጭም የአውሮፓውያን ድጋፍ ነበር። ስማቸው ገና “ካሳ” በነበረ ጊዜ አጤ ቴዎድሮስን ለማስወገድ እንግሊዞችን እስከ መቅደላ እየመሩ መግባታቸው አግዟቸዋል። ምኒልክም በዚህ ኦፕሬሽን ላይ በተዘዋዋሪ ተባባሪ ነበሩ። እንግሊዞች የአጤ ቴዎድሮስን ጸጉር ላጭተውና ጨቅላ ልጃቸውን ይዘው ወደ አገራቸው ሲመለሱ ተፎካካሪ መኳንንቱ ከእንግሊዞች የውጊያ መሳሪያ ስጦታ ለማግኘት ተሽቀዳድመዋል። ንጉስ ምኒልክ ራሳቸው መሄድ ስለሰጉ ራስ ጎበና ዳጪን ወክለው ወደ መቅደላ በመላካቸው የጠበቁትን ያህል አላገኙም።

ስልጣን ለመያዝ የውጭ ሃይሎችን ድጋፍ መጠቀም በአለማችን የተለመደ ነው። ንጉስ ምኒልክ በዘመኑ አጤ ዮሃንስን ለመገልበጥ ከጣልያኖች፣ ከግብጾችና ከደርቡሾች ጋር በማሴር የተቀናቃኞቻቸውን ውድቀት እንዲጣደፍ ማድረጋቸው ያልተለመደ አልነበረም። በመሆኑም የምኒልክም ሆነ የዮሃንስ ደብዳቤዎች በወቅቱ የአስተሳሰብ ደረጃ ሲመዘኑ “ሃይልን ለማጠናከር የተደረገ” ሊባል የሚችል ነው። በደብዳቤዎቹ የሰፈሩት አንዳንድ ቃላት እንደ ከሃዲ አያስገምተታቸውም። አሰባሳቢ ማንነት አልነበረም። ኦሮሞዎች ከአበሾች ሲዋጉ፤ የሐበባ ሰዎች ከአሉላ ወረራዎች አገራቸውን ሲከላከሉ ወራሪዎችም ሆኑ ተወራሪዎቹ ውጊያውን የውስጥ ጉዳይ ለማለት የሚያበቃቸው የጋራ ጀንጥላ ከላይ አልነበራቸውም። ቀመሩ ቀላል ነበር። ሃይል ያለው ድንበር አያግደውም። ኢጣልያውያን በአካባቢው ሲከሰቱ ቆዳቸው ነጭ ከመሆኑ በቀር የተለየ

የሚያደርጋቸው ልዩ ነገር አልነበረም። ባጭሩ የቆዳቸው ቀለም የተለየና ባህር ተሻግረው የመጡ ሌላ ወራሪዎች ብቻ ነበሩ።

በወቅቱ ከኢጣልያ ጋር ወዳጅነት ለመፍጠር ሽሚያ የነበረውን ያህል፤ በወዳጅነቱ የዘለቀ የአካባቢያችን ሃይል ግን አልነበረም። በየተራ የመጋጨትና የመዋጋት እጣ ገጥሟቸዋል። ኢጣልያ ከአካባቢው ሃይሎች ጋር የምታደርገው ስምምነት ለመረማመጃ እንጂ ዋና ግቧ አካባቢውን መቆጣጠር ስለነበር ስምምነቶች ሁሉ ጊዜ መግዣ ነበሩ።

በሰሜንና በደቡብ ወራሪዎች እጅግ ከተቸገሩ አውራጃዎች ዋናው የኑረነቢ አገር ሲሆን፤ የሓልሓል ቦጎስ ገበሬ ከ1875 ጀምሮ ተስፋ የመቁረጥ ደረጃ ላይ እስኪደርስ ፈተናዎችን አስተናግዷል። በዘመነ ክህደት ደግሞ በከፋ መልኩ የሚታለብ ላም ቀርቶ መሬት ማረሻ ግመል ወይም በሬ ወደ ማጣት ደረጃ ደርሱ። የህዝቡ ማህበራዊ ህይወት አደጋ ላይ ወደቀ። ስደት ተከተለ። የህዝብ ቁጥር እየሳሳ ሄደ። ከመንደራቸው ተሰደው ለዘልአለሙ ቀልጠው ከቀሩ ነባር የፋና ቤተሰቦች አንዱም ኑረነቢ በኺት ሆነ።

* * *

ጊላጊ ርእስ በመቀየር ስለ ራሱ ተረከ፤

“ሰረገላ ነጂ ከመሆኔ በፊት አስካሪ ነበርኩ። ዳህላክ ደሴት ሲያዝ ዘምቻለሁ። አሉላ ሳሆን በወረረ ጊዜ፤ ከንቲባይ ሓምድ ሃሰን እና ካፍል ጎፋር እርዳታ ፈልገው ወደዚህ ሲመጡ የተቀበልኳቸው እኔ ነኝ። ምድቤ ድንበር ጥበቃ ላይ ነበር። ለሰረገላ ነጂነት የተመረጥኩት ግን ከምጽዋ እስከ ፐሪም ደሴት የሚሄድ የባሕር ውስጥ የቴሌግራፍ መስመር በመዘርጋት ስራ ላይ ሳለን ነው። እንደ ፈረስ ስሰራ አለቃዬ አየና ፈረስ ነጂ አደረገኝ። ከጥልያን የተማርኩት ዋና ቁምነገር ‘የስራ ፍቅር’ ነው። ጥልያን ዘንድ የማይቻል የሚባል ነገር የለም። ምንም ቢሆን ሊደረግ ይችላል።”

“አድልዎ አለባቸው መባሉስ?” ሲል ጠየቀ ኑረነቢ።

“ኤህ! ወሬ ብቻ!” ብሎ እጁን አወናጨፈ።

ኢያያዘናም በስሜት ቀጠለ፤

“ከኛ የባሰ ክፉ የለም። የኛ ክፋት ከደደብነት ጋር ነው። ከእናታቸው ጉያ ልጆችን እየሰረቀ ለአረቦች የሚሸጠው ማነው? እንደውም ይሄ ጅብነት፤ አውሬነት ነው። ጥልያን ልጆችን እንደ ጨው ገበያ ላይ አይሸጥም። ለሰራኸው ስራ ደሞዝ ይከፍልሃል። ባሕር ውስጥ እንደ ዶልፊን እየዋኘን ወደ ፐሪም ደሴት የቴሌግራፍ መስመር ስንዘረጋ ጥልያኖች ልክ እንደኛው አስቸጋሪውን ስራ ይሰሩ ነበር። በርግጥ ደሞዝ ላይ ለጥቁርና ለነጭ ልዩነት ያደርጋሉ። ይሄ አድልዎ አይባልም። ጥልያን ሳይመጣ እኔ እዚህ እኔ ምን ነበርኩ? የባሪያ ፈንጋዮች ደላላ። ከዚያ የተሻለ ልሰራው የምችለው ስራ አልነበረም። ግብጾችና ቱርኮች ዋና ችሎታቸው ግብር መሰብሰብ ነው። ግሪኮችን ውሰድ። ጨርቅና ጥይት አምጥተው ይሸጡልሃል። ከዚህ ደግሞ ቅመማ ቅመም፣ የዝሆን ጥርስ፣ የነብርና የአንበሳ ቆዳ ይዘው ይሄዳሉ። የታመመ ሰው ሲያክሙ አላየንም። እውቀታቸውን ይደብቃሉ። የኛ ሰው ከአረቦችም የባሰ ነው። አሳ ማጥመድ ሰልችቶት ይራባል። አሳው ራሱን በራሱ እንዲጠብስለት ይፈልጋል። ጥልያን የስራ ሰዎች ናቸው። መምጣታቸው ለኛ እድል ነው።”

ኑረነቢ “ሸማል ሸርቅ ሬስቶራንት” ረዳት ዘበኛ ሆኖ ሶስት ወራት ከሰራ በሁዋላ ስራውን ጠላው። የዘበኝነቱን ስራ ክፉኛ ጠላው። ፋና ሳለ የነበረውን ማህበራዊ ደረጃና የማእረግ ቦታ ከአእምሮው ፍቆ፣ አሁን ያለበትን እውነት መልመድና መቀበል አልቻል አለ። በአውሮፓውያን እና በአረቦች ፊት ዝቅ ብሎ መታየቱን መልመድ ተቸገረ። ከእለት እለት መሳቀቁ ከፋው። ከሬስቶራንቱ እንግዶች ገጽታ ላይ በግልጽ የሚያነበውን የንቀት አስተያየት ተሸክሞ መቀጠል እንደማይችል ይገነዘብ ጀመር።

ርግጥ ነው፤ በሸማል ሸርቅ ስራው ላይ እንዲቆይ ካደረጉት ክስተቶች አንዱ ከባሕሩ ጋር ያደረበት አዲስ ፍቅር ነበር። አይኖቹን ከቀይ ባሕር ላይ መንቀል አልቻለም። አይቶ መጥገብ አቃተው። በምሽት የማእበሉ ዜማ በጆሮው እየተንቆረቆረ ያንሳፍፈዋል።

ባሕሩ ሰማያዊ ሆኖ ሳለ “ቀይ ባሕር” ተብሎ በመጠራቱ ግን ኑረነቢ ሳይገረም አልቀረም። “ቀይ ባሕር” ሲባል ባሕሩና ዙሪያው በቀይ ቀለም የደመቀ መስሎ ይሰማው ነበር። በባሕሩ ዙሪያ አንዳችም ቀይ ቀለም አይታይም። “ባሕሩ ለምን ቀይ ባሕር ተባለ?”

የሚል ጥያቄ መጣበት። ምክንያቱን ለማወቅ ግን አልጠየቀም።

አንድ ሌሊት ስለዚሁ ጉዳይ ሲያሰላስል፣ ባሕሩ ላይና በዳርቻው አያሌ ጦርነቶች ስለተደረጉ በፈሰሰው የደም ጎርፍ ምክንያት ባሕሩ "ቀይ" ተብሎ ተሰይሞ ሊሆን እንደሚችል ገመተ። "መሆን አለበት" ሲል ከራሱ ጋር አወጋ።

* * *

ከሁለት ሳምንታት በሁዋላ ጊላጊዮርጊስ ወደ ሬስቶራንቱ ተመልሶ መጣ። እንደተለመደው ለኑረነቢ የሞቀ ሰላምታ ካቀረበ በሁዋላ እንዲህ አለው፣

"ዛሬ ጠዋት አስደናቂ ዜና ሰማሁ።"

በአይኑ ሽንቁር ኑረነቢን ተመለከተ። እንደልማዱ ምጥጥ አድርጎ ሲጋሩን ከሳበ በሁዋላ ጭሱን እየተፋ በረጅሙ ስቆ አስደናቂውን ዜና ለኑረነቢ ነገረው፣

"አጤ ዮሃንስ መተማ ላይ በከሊፋ ሰዎች ተገደለ።"

ኑረነቢ ሳያውቀው ከተቀመጠበት ብድግ አለ። ምን እንደተሰማው ለይቶ ማወቅ ባይችልም፤ በሰማው ዜና ደምስሩን ነዘረው። ምንም አልተናገረ። ብቻ እንደገና ረጋ ብሎ ከነበረበት ቦታ ላይ ተቀመጠ። አፉን በእጆቹ ሸፍኖ አይኖቹን ወደ ባሕሩ አግጣጫ ልኮ ጥቂት ደቂቃዎች በዝምታ ቆየ።

* * *

ዘመኑ ለመረብ ምላሽ ሰው ያልተመቸ ዘመን ነበር። በአንጻሩ ኢጣሊያ መላ መረብ ምላሽን ለመቆጣጠር ምቹ ሁኔታ የተፈጠረላት ጊዜ ነበር። በዚህ ሁኔታ ላይ የአጤ ዮሃንስ መገደል ሲሰማ ኢጣልያ መረብ ምላሽን ብቻ ሳይሆን ከተቻለ ኢትዮጵያን ጨምራ ለመቆጣጠር ወደ ደጋው ገሰገሰች። በቅድሚያ የኢጣልያ ሰራዊት ምጽዋን ደጅን አድርጎ፤ ከረንና ባርካን በቀላሉ ያዘ። ወደ ሓባብ ተስፋፋ። አስመራን አልፎ ወደ መረብ ወንዝ እግሩን ዘረጋ።

ልክ በዚሁ ጊዜ ከመረብ ወዲያ ማዶ አጤ ዮሃንስ ሲገደሉ፤

አጤ ምኒልክ ራስ መንገሻን አስገብረው የንጉሰ ነገስትነት ዘውድ ለመድፋት ከኢጣሊያ ጋር ወዳጅነታቸውን ይበልጥ ለማጠናከር ተጣደፉ። ራስ አሉላ በአንጻሩ መንገሻን አስቀድሞ የአጤ ዮሃንስን ዙፋን ለማቆየት ሲል ኢጣልያን እጅ ለመንሳት ዝግጁ ሆነ።

በዚያም ተባለ በዚህ ግን ጊዜው ለኢጣልያ የተመቸ ነበር። ወደ ምጽዋ የሚጎርፈውን የመረብ ምላሽ ስደተኛ በአግባቡ ተጠቀሙበት። ረሃብ ካሳደደው ስደተኛ መካከል ከአምስት ባታሊዮን በላይ ወታደሮችን መልምለው ማሰልጠን ቻሉ። በረሃብ እየተገረፈ ምጽዋ የደረሰ ወጣትና ጎልማሳ ሁሉ የእለት ጉርሱን ለማግኘት ሲል ጉልበቱን ለኢጣልያ ሰጠ። በሌላ አነጋገር "ከመሞት ለመሰንበት" እንዲሉ አይኑን ሳያሽ ዳቦና ጠመንጃ ተቀበለ።

ዶሮቹን፣ ፍየሎቹንና እህሉን በልቶ ጨርሶ፣ ላሞቹና በሬዎቹ አልቀውበት፣ አህዮቹና ፈረሶቹ ሞተውበት፣ ድመትና ውሾች በተጋደሙበት ደርቀውበት፤ ማሳው ነጥፎ በህይወትና በሞት መካከል የተንገላታው የገበሬ ልጅ ወደ ባርካ እና ወደ ምጽዋ የተሰደደው ባንድ በኩል ህይወቱን ለማቆየት፤ በሌላ በኩል ሰላም ፍለጋ መሆኑ እውነት ነው። ከማህዲስቶች እህል ለማግኘት ተስፋ አድርገው ወደ ባርካ የተሰደዱ ብዙም አልቀናቸውም። ህይወታቸውን ለማቆየት የሚያበቃ እህል እንኳ ለማግኘት ተቸገሩ።

በትግራይ መሳፍንት ተደጋጋሚ ዘረፋና ግድያዎች፤ እንዲሁም በግብጽ ታጣቂዎች ተመሳሳይ ድርጊት የቦጎስና የአካባቢው ገበሬ በእጅጉ ተሳላችቶ ነበር። ከያቅጣጫው የሚመጣው ታጣቂ ካካባቢው ገበሬ ላይ እየነጠቀ ከዶሮ እስከ በሬ እያረደ ቅርጥፍጥፍ አድርጎ መፍጀት ልማዱ ነበር። በክተት ተሰባስቦ የሚመጣው ጀሌ ከአራት ቀናት ያለፈ ቀለብ ስለማይይዝ፤ ስንቁ ሲያልቅበት የገበሬውን ጎተራ ይበዘብዛል። በጦርነቱ ቤቶች ይቃጠላሉ። መንደሮች ጥቀርሻ ለብሰው በረሃ ይሆናሉ። ብቅ ጥልቅ ከሚለው የረሃብ አደጋ ለማገገም የሚፍገመገመው ገበሬ፤ የሚግበሰበስ ወራሪ መጥቶ እላዩ ላይ ሲሰፍርበት ለዘመናት የደከመበትን ሁሉ ባንድ ማለዳ ያጣዋል።

ከኢጣልያ ወረራ በፊት የሃይል የበላይነታቸው ይፈራረቅ የነበረው የአካባቢ ሃይሎች የሚባሉት የኤርትራ የደጋና የቆላ

ባላባቶች፣ ባህረ ነጋሲዎች ወይም ናይቦችና ሱልጣኖች ባንድ በኩል፤ ድንበር ተሻግረው የሚመጡ መሃዲስቶች፣ ቱርኮችና ግብጾች ደግሞ በሌላ በኩል ነበሩ። የትግራይ መኳንንትም ሃይል ባገኙ ጊዜ ወደ ከበሳ ወደ ሓባብ እየዘመቱ ዘረፋ የቀላቀለ ጦርነት ማካሄዳቸው አልቀረም። በ1880ዎቹ አጋማሽ ኢጣሊያ በባሕሩ ዳርቻ መከሰቱ ግን የአካባቢውን ተፎካካሪ ሃይሎች የሃይል ሚዛን ለዋወጠው።

የመረብ ምላሽ አክተሮች ድንበር ተሻግረው የሚመጡ የአካባቢ ጉልበተኞችን ለመቋቋም የኢጣልያን ድጋፍ ፈለጉ። ዘምህረት ዮሃንስ “የኢጣልያ ቅኝ አገዛዝ በኤርትራ” በተሰኘ መጽሃፉ እንደጠቀሰው የኢጣልያን ድጋፍ የመፈለጉ የወቅቱ ዝንባሌ፣ “እንደ አንድ የተቃውሞ ስልት ሊታይ የሚችል” ነበር። በወቅቱ የአካባቢው ሃይሎች የበላይነታቸውን ለማረጋገጥ ይችሉበት የነበረው ብቸኛው መንገድ የተዋጊና የጠመንጃ ብዛት አንደመሆኑ ለዚህ ደ’ሞ ከአውሮፓውያን መወዳጀትን የሚጠይቅ ነበር። የወቅቱን ሃያላን ፍላጎት መፈጸም የቻለ የጠየቀውን የማግኘት እድሉ የተሻለ ሆነ።

በርግጥ “ኤርትራውያን” ከመባላቸው በፊት የምድሪ ባሕሪ ሰዎች በከብት ርቢ፣ በእርሻና በአሳ ማጥመድ ይተዳደሩ ነበር። ደጋዎች መሬት ሲያርሱ፤ የቆላ ሰዎች ባሕሩን ያርሱ ነበር። ማለትም የደጋው አገር ሰው በሬ ሲጠምድ፤ ቆለኛው አሳ ያጠምድ ነበር። የመረብ ምላሽ ሰው የሸርካ ማንነት ከማዳበሩ በፊት በዚያው ምድርና በዚያው ባሕር ዳርቻ ረጅም ዘመን ኖሯል። በዚህ የረጅም ዘመን ጊዜ ውስጥ በተደጋጋሚ የሚካሄዱ ጦርነቶች የህዝቡን ቁጥር እንዲገታ አድርጎት ኖሯል።

መተማ ላይ ከመገደላቸው ጥቂት ወራት ቀደም ብሎ አጤ ዮሃንስ ከሶስት አግጣጫ ግንባር ተፈጥሮባቸው አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ወድቀው ነበር። በቅድሚያ ከጣልያን ጋር ለመዋጋት ቆርጠው 157 ሺህ ተዋጊ አስከትለው ወደ ሰሓጢ ወረዱ። ይህን ኢጋጣሚ አይተው መሃዲስቶች በምእራብ በኩል ጎንደር ገብተው አርባ ታቦታት አቃጠሉ። የክርስትያን ቤተመቅደሶችን ደፈሩ።

የጎጃሙ ንጉስ ተክለሃይማኖት በአጤ ዮሃንስ ትእዛዝ 100 ሺህ ወታደሮች አስከትለው ከማህዲስቶች ጋር ጦርነት ቢገጥሙም ሳይቀናቸው ቀረ። የንጉስ ተክለሃይማኖት ስምንት ሺህ ጦር ሲማረክ

ሌላው ተበታተነ። በጦርነቱ ምንትዋብ የተባለች የንጉሱ ሴት ልጅ ጭምር ተማረከች። የጎጃም ጦር ተበታትኖ አጤ ዮሃንስ አጣብቂኝ ውስጥ መግባታቸውን ሲረዱ፤ ንጉስ ምኒልክ ከደርቡሽ ተጻጽፈው፣ ተመሳጥረው ዮሃንስን ከዱ። ንጉስ ተክለሃይማኖትንም አስከዱ።

በርግጥ ሁለቱ የሸዋና የጎጃም ንጉሶች ከመክዳታቸው በፊት ከአጤ ዮሃንስ ደብዳቤ ደርሷቸው ነበር። አጤ ዮሃንስ ለጎጃሙ ንጉስ የጻፉት ደብዳቤ ላይ፣ "ፈሪ ነህ።" የሚል ስድብ ነበረበት። ለንጉስ ምኒልክ ደግሞ፣ "ለኔ ሳይሆን ለሃይማኖትህና ለአገርህ ስትል እንኳ ደርቡሾችን ተከላከል" የሚል ቅሬታ አዘል ደብዳቤ ጻፉላቸው። አጤ ዮሃንስ ይህን ደብዳቤ ለምኒልክ ሲጽፉ ምኒልክ ከደርቡሾች ጋር ተላልከው ከጀርባ እየወጓቸው መሆኑን አልጠረጠሩም። ለንጉሶቹ የላኳቸው ደብዳቤዎች ሲመዘኑ ግን አጤ ዮሃንስ ከባድ ውጥረት ውስጥ ገብተው እንደነበር ጠቋሚ ነው።

ከአጤ ዮሃንስ ፊት ሶስት ግንባሮች ተደቀኑ። ስለዚህ በቅድሚያ ማንን መውጋት እንዳለባቸው መምረጥ ቀዳሚ ስራ ሆነ። ከተከታዮቻቸው ጋር መከሩ። ከመነሻው ጣልያኖች ዘልቀው እንዳይመጡባቸው ሰጉ እንጂ ምጽዋን መያዛቸው ችግራቸው አልነበረም። ምጽዋን በተመለከተ እንግሊዝ የአይለትን ውል ባለመጠበቋ ግን ቅያሜ ነበራቸው። በዚያም ተባለ በዚህ ቀደም ሲል ራስ አሉላ ሰሓጢ ላይ የደረሰበትን ጉዳት የረሱ አይመስሉም። ማለትም የሰሓጢን ምሽግ ቢያጠቁ ድል እንደሚያገኙ ርግጠኛ አልነበሩም። ሰራዊቱና አጋሰሱም የምግብና ውሃ እጥረት ገጥሞታል። ስለዚህ ምጽዋ ለሚገኘው የኢጣሊያ አገረ ገዢ ለሌተና ጄኔራል ሳን ማርሳኖ፣ "በያለንበት እንርጋ" የሚል የተለሳለሰ ደብዳቤ ጽፈው ሲያበቁ፤ አቢሲንያን ለማዳን ወደ አገራቸው የመልስ ጉዞ ጀመሩ።

አጤ ዮሃንስ ሰሓጢ ላይ ሳይዋጉ ሰራዊታቸውን ይዘው በመመለስ ላይ ሳሉ ሞራላቸው በእጅጉ ወድቆ እንደነበር ይታመናል። ለተከተላቸው ሰራዊት በቂ ቀለብ አልነበራቸውም። ሰራዊቱ አብዛኛው ጦርና ጋሻ የያዘ ነበር። የጣልያንን ወታደር ገድሎ ባለ ጠመንጃ ለመሆን ተስፉ ያደረገው ጀሌም የውሻ መከላከያ በትሩን ይዞ ወደ አገሩ ለመመለስ በመገደዱ ደስተኛ አልነበረም።

አጤ ዮሃንስ የሚሰሙት ዜና ሁሉ አስጨናቂ ሆነባቸው።

በወቅቱ አጤ ዮሃንስን ለማዳከም ሁሉም ለየምክንያቱ ተረባርቧል። ምኒልክ ለስልጣን፤ እንግሊዝና ጣልያን የሰሓጢን ጦርነት ለማስቀረት፣ ደርቡሽ በበኩሉ አጤ ዮሃንስ በሌላ ውጊያ መያዛቸውን በማየት፣ ምናልባትም በእንግሊዞችና በጣልያኖች ግፊት፤ የበጌምድር ቀሳውስት በሙስሊም በመወረራቸው፣ ሁሉም በየራሱ ምክንያት አጤ ዮሃንስን ወጥሮ የያዘበት ጊዜ ነበር።

ለአጤ ዮሃንስ የደረሷቸው አንዳንድ ደብዳቤዎች አንጀት የሚበሉ ነበሩ። በደርቡሽ የተማረከችው የንጉስ ተክለሃይማኖት ልጅ ምንትዋብ ኡምዱርማን ደርሳ ተሰቃይታ ሞተች። ከመሞቷ በፊት ለአገሯ ሰዎች የላከችው መልእክትም ተጽፎ በገስጋሽ መልእክተኛ ለአጤ ዮሃንስ ደረሳቸው። እንጉርጉሮው እንዲህ ይላል፣

ጎጃም የምትሄዱ - እንደኔ እማትቀሩ
ድመት በልታ ሞተች - ብላችሁ ንገሩ

በሌላ በኩል ደግሞ የበጃ-ምድር ደብተሮች የሸንፈት እንጉርጉሮና ቅኔ ትግሬ አማራ ሳይል መላ ስሜንን አጥለቀለቀ፣

ሳር ውሃ ከሜዳው - የተዘራ አዝመራ
አጫጁ ደርቡሽ ነው - ሰብሳቢው አሞራ

አንድ የአበሻ ንጉስ ሴት ልጁን ለምርኮ ትቶ መሸሹ ያልተለመደ በመሆኑ የጎጃም እረኛ ተክለሃይማኖት ላይ አላገጠ።

አትከለክልም ወይ - ይዘህ አለንጋህን?
አሞራ ሲበላው - የገዛ ገላህን ?

የሸዋው ንጉስ ምኒልክ በዚህ ጦርነት አለመካፈላቸው በታሪክ ውስጥ አከራካሪ ሆኖ ዘልቋል። አጤ ዮሃንስ “ስለኔ ብለህ ሳይሆን ስለ ሃይማኖትህ ስትል” የሚል መረር ያለ ደብዳቤ በላኩላቸው ጊዜ፤ ንጉስ ምኒልክ ከደርቡሽና ከጣልያን ጋር እየተላላኩ መመሳጠራቸውን አወንታዊ ምክንያት ለመስጠት የሚሞክሩ ጸሃፊዎች አሉ። ደርቡሽ ጎንደር ዘልቆ ገብቶ አርባ ደብር አጥቅቶ አርባ ታቦት አቃጥሎ ሳለ፤ የተክለሃይማኖትን ልጅ ጨምሮ ስምንት ሺህ የጎጃም ወታደር በምርኮ ይዞ ሳለ ምኒልክ፣ “ሁመራ ላይ ወባ ስላለ መዝመት አልቻልኩም” የሚል ሰበብ መስጠታቸው ከስልጣን

ሽኩቻ ያለፈ ምክንያት ሊገኝለት አይችልም። በወርሃ ሚያዝያ ሁመራም ሆነ መተማ ላይ ወባ እንዳልነበረ ይታወቅ ነበር። ጉዳዩ አጤ ዮሃንስን የማዳከም ነገር ነበር። በተጨማሪ አጤ ዮሃንስ ጣልያንን ሳይወጉ ወደ አገራቸው እንዲመለሱ የማድረግ ሴራ ሊኖርበት ይችላል። የአጤ ምኒልክ ቀዳሚ አጀንዳ 'የተከፈለው ተከፍሎ አጤ ዮሃንስን ማስወገድ' የሚል ሆኖ ቆይቷል። እድል ተጨምሮበት በ1889 ላይ አጤ ዮሃንስን የማስወገዱ ህልም ተሳክቶላቸዋል። ማለትም የአጤ ዮሃንስ ዘመዶች የቂም መድፍ እየተኮሱ ዘልቀው ሸዋ እስኪደርሱ መግዛት ችለዋል።

በዚያን ጊዜ አጤ ዮሃንስ ዙሪያው ጨለመባቸው።

ተክለሃይማኖትና ምኒልክ መክዳታቸው ሳይበቃ አንድዬ ፈረንጅ ወዳጃቸው የእንግሊዝ ንግስት ጀርባዋን ሰጥታቸዋለች። ማህዲስቶች ለጦርነት እንደተዘጋጁ ናቸው። ጣልያን ምን ሊያደርግ እንደሚችል ገና በግልጽ አልታወቀም። አቅሙን መዝኖ ወደ ደጋው ሊገፋ ይችላል' ስጋት ነበር። በዚህ ወጣሪ ጊዜ አጤ ዮሃንስ ሁሉን እርግፍ አድርገው በመተው ለመመነን ፈልገው እንደነበር ተክለጻድቅ መኩሪያ ጽፈዋል። በሌላ ምንጭ ባይረጋገጥም ንጉሰነገስቱ የምኒና አሳባቸውን ለከበቧቸው መኳንንቶች እስከመንገር ደርሰው። እንደ ተክለጻድቅ ትረካ ቀሳውስቱ ገዝተው አሳባቸውን አስጥለዋቸዋል።

አጤ ዮሃንስ በወጣሪ ሁኔታዎች እንደተከበቡ ወደ ነባር ግዛታቸው የመልስ ጉዞ ጀመሩ። የዙሪያ ጨለማውን በከፊል ለመግፈፍም ለደርቡሽ መሪ ለሐምዳን አቡ አንጣ ለስለስ ያለ ደብዳቤ ልከው ነበር። ይዘቱ፣ "በየአገራችን፣ በየሃይማኖታችን ተከባብረን በጉርብትና በሰላም እንኑር" የሚል ነበር። ሐምዳን አቡ አንጣ ከኡምዱርማን፣ "ካንተ ጋር የምነጋገረው ሃይማኖትህን ክደህ ከሰለምክ ነው።" ሲል ትእቢተኛ ምላሽ ላከ።

ከዚህ በሁዋላ አጤ ዮሃንስ ከማህዲስቶች፣ ከጎጃምና ከሸዋ ማንን ቀድመው መውጋት እንዳለባቸው ከመምረጥ በቀር የቀራቸው ነገር አልነበረም። እና ንጉስ ተክለሃይማኖት፣ ሐምዳን አቡ አንጣና ምኒልክን በቅደም ተከተል ለመቅጣት ወስነው ሲያበቁ፣ የመጀመሪያ ዱላቸውን ጎጃም ላይ አሳረፉ። ንጉስ ተክለሃይማኖት ሸሽተው ጅበላ ዋሻ ገብተው መድፋቸውን ጠመዱ። አጤ ዮሃንስ የጎጃሙን ንጉስ

ተከለሃይማኖት መማረክ ሳይችሉ ሲቀሩ ህዝቡን ወደ ማነሳቀል ገቡ። በጥብቅ የተዋህዶ አማኝነታቸው የሚታወቁት አጤ ዮሃንስ ታቦት እንዲሰባብሩ ወታደሮቻቸውን አዘዙ። የጎጃም ሰው በደረሰበት ውድመትና መጎሳቀል ምክንያት ቅሬታውን በዝነኛ ቅኔ ገልጾታል፣

በላይኛው ጌታ - በባልንጀራዎ
በቅዱስ ሚካኤል - በጋሻ ጦግሬዎ
በጽላተ ሙሴ - በነጭ አበዛዎ
ጎጃምን ይማሩት - ፈሪም አንልዎ

የአጤ ዮሃንስ ሰብእና አከራካሪ እንደሆነ ዘልቋል። በጉዛምንና በማቻካል ታቦት ከመንበሩ እያስወጡ እንዲሰባበር ማዘዛቸው፤ ቤተክርስትያን እያስፈረሱ፣ ማገሩን እያስፈለጡ ማንደዳቸው፤ የቤተክርስትያን ሳንቃ እያስነቀሉ ለጥይት ማብረጃ እንዲሆን ማድረጋቸው ሲታሰብ አጤ ዮሃንስ ድብቅ ሰብእና እንደነበራቸው ያስጠረጥራል። በርግጥ አጤ ዮሃንስ ራሳቸውን እንደሚያቀርቡት ከሌሎቹ ነገስታት በላይ አማኝና እንደሚታወቁበት የተዋህዶ አርቶዶክስ እምነት ጠባቂ ነበሩ?

አዲስ የሚወጡ መረጃዎች እንደሚጠቁሙት አጤ ዮሃንስ ራሳቸውን "የጽዮን ንጉስ" ብለው ይጠሩ ነበር። በማህተማቸው መካከልም ዘውድ የደፋ አንበሳ ነበረ። የሸዋ መሳፍንት እንደሚያደርጉት ራሳቸውን ከሰለሞናዊ ዘር ጋር የማቆራኘት ዝንባሌ ግን አልነበራቸውም። የአጤ ዮሃንስ የዘር ግንድ በቀጥታ ከአጤ ፋሲል ጋር የተያያዘ ነው። የፋሲል (የልጅ ልጅ - አምስተኛ ትውልድ የሆነችው) መና እስራኤል አያታቸው ናት። የአጤ ዮሃንስ ማህተም ላይ በአረብኛ የሰፈረው ጽሁፍ፣ "ንጉሰነገስት ዮሃንስ፣ ንጉሰ ጽዮን ዘኢትዮጵያ፣ ዘእምነገደ እስማኤል" ይላል። "እስማኤል ማነው?" የሚል ጥያቄ ሲነሳ የመጽሃፍ ቅዱስ ታሪክ ላይ አብርሃም ኢጋር ከተባለች ገረዱ ወለደው የተባለው ልጅ ስሙ እስማኤል ነበር።

የአቡነ ተከለሃይማኖት (ተክልዬ) የስጋ ዘመድ ይኩኖ አምላክ ዘሩን ቆጥሮና ተርትሮ ንጉስ ሰለሞን ላይ ሲያደርስ፤ አጤ ዮሃንስ ደግሞ ከሸዋ ተረት ጋር ለመፎካከር በሚመስል መልኩ ከዚያም በላይ ርቀው የዘር ግንዳቸውን እስማኤል አብርሃም ላይ

አደረሱት። የአጤ ዮሃንስ ህጋዊ ሚስት ሃሊማ ሙስሊም ነበረች። አጤ ዮሃንስ ራሳቸውን ከአምላክ ጋር ለማገናኘት የእስማኤልን ሃረግ የተከተሉበት፣ ህጋዊ ሚስታቸውን ከሙስሊም ቤተሰብ የመረጡበት ስነ ልቦናዊ ምክንያት ምን እንደነበር አይታወቅም። “ዘእምነገደ እስማኤል” የሚል ጽሁፍ የያዘውን የአጤ ዮሃንስ ማህተም ምስል ለመጀመሪያ ጊዜ አስተውሎ ትርጓሜ የሰጠው ፕሮፌሰር ፍቅሬ ቶሎሳ ነበር። ፍቅሬ ቶሎሳ እውነተኛ ታሪክ ውስጥ ልቦለድ የሚቀላቅል ግዴለሽ ታሪክ ጸሃፊ ቢሆንም የማህተሙን ፎቶግራፍ ስላተመልን መረጃውን እንቀበለዋለን።

አጤ ዮሃንስ ጎጃምን ካጠፉ በሁዋላ ወደ ማህዲስቶች ዘመቱ። በመተማ ጦርነት ድል አድርገው ሳለ በመጨረሻዋ ደቂቃ በተባራሪ ጥይት ተመትተው ህይወታቸው አለፈች። ይህም አጋጣሚ ምኒልክን ከቀጣዩ የአጤ ዮሃንስ ቅጣት አዳናቸው። አጤ ዮሃንስ ወደ ሸዋ ዘምተው ቢሆን ኖሮ ንጉስ ምኒልክ እንደ አባታቸው እንደ ሃይለመለኮት በልብ ድካም ይሞቱ እንደነበር የጻፉ አሉ። እውነቱ ግን ሃይላቸው ተመጣጣኝ የነበረ መሆኑ ነው። ዞረም ቀረ አጤ ዮሃንስ መተማ በመውደቃቸው ምክንያት የአቢሲንያ ዙፋን ባልተጠበቀ ጊዜ ወደ ሸዋ ሊሸጋገር በቅቷል።

ከአጤ ዮሃንስ እረፍት በሁዋላ የትግራይ መኳንንት ወደ ምድሪ ባሕሪ ብቅ ጥልቅ ማለታቸው አበቃ። በ19ኛው ክፍለዘመን ታሪክ ውስጥ መረብን ከተሻገሩ መካከል ሊጠቀሱ የሚችሉት በዋናነት ራስ ባርያ ገብረጻድቅ እና ራስ አሉላ ናቸው። ራስ ባርያ ምድሪ ባሕሪን ለማስገበር ሰራዊት ይዞ ቤት መኻእ ኮረብታ ላይ ተቀመጠ። ደጃዝማች ወልደሚካኤል ከሃዘጋ ሲገሰግስ መጥቶ ደብረጽዮን ቅድስት ማርያም ሰፈረ። በነጋታው ቤት መኻእ ላይ ውጊያ ተደረገና በራስ ባርያው መገደል ተጠናቀቀ። በአንጻራዊነት ሲታይ መረብን ተሻግሮ ምድሪ ባሕሪ ላይ ረጅም ጊዜ የተቀመጠው ራስ አሉላ ነበር። በአስር አመታት የከበሳ ቆይታው የገጠር አስተዳደር፣ ባህልና ልማድ ውስጥ እጁን ሳያስገባ፤ እህል ከተሰበሰበ በሁዋላ አመታዊ ግብር ይሰበስብ ነበር።

የትግራይ መኳንንት በዮሃንስ ድንገተኛ ሞት የአቢሲንያን ስልጣን ከተነጠቁ በሁዋላ ቁጭት እና ብሶት ቀለባቸው ሆነ። ዙፋኑን

ለማስመለስ ያልፈነቀሉት ድንጋይ፣ ያልሸረሸሩት አሸዋ አልነበረም። መንገሻ ዮሃንስ፣ አሉላ እንግዳ፣ ሃይለማርያም ካሳ፣ ስዩም መንገሻ፣ ሃይለስላሴ ጉግሳ በተለያየ ትውልድ የተለያዩ ሙከራዎችን አድርገዋል። በተለይ ራስ መንገሻ በተደጋጋሚ ተቃውሟቸው ምክንያት ፍጻሜያቸው አንኮበር እስር ቤት ተሰቃይተው እስከመሞት አድርሷቸዋል። የመኳንንቱ የልጅ ልጆች የትግራይን ገበሬ አነሳስተው ህልማቸውን ለማሳካት፣ ቂማቸውን ለመወጣት የቻሉት ግን ከ102 አመታት በሁዋላ ነበር።

* * *

ጊላጊ ማብራራቱን ቀጠለ፣

“አጤ ዮሃንስ ከሁዋላ ገብቶ የባቡር መንገዱን እንዳይቆርጥ፣ ወይ ደግሞ የሰሓጢን ምሽግ ትቶ ዊዓን እንዳያጠቃ ጥልያኖች ስጋት ነበራቸው። ሳይዋጋ ሲመለስ ግን መልሰው ባለመዋጋታቸው ተቆጭተዋል። ብቻ አጤ ዮሃንስ ፍጻሜው አላማረም።”

ኑረነቢ ጠየቀ፣

“ለመሆኑ ዙፋኑን ለማን አወረሰ?”

“መንገሻ ለሚባል በጎን የወለደው ልጁ አውርሷል ይባላል።”

ኢያያዘናም አከለበት፣

“ባህታ ሓጎስ ቢያውቅበት ጊዜው አሁን ነበር።”

ምእራፍ 4

የነጻነት ግዳይ
በሰምሃር ደረት ላይ

አንድ ምሽት ኑረነቢ በስራ ገበታው ላይ ሳለ የሰከረ ኢጣልያዊ “ማርዮ! ፒግሮ!” ብሎ ጮኸበትና አለፈ። በርግጥ ኑረነቢ እንቅልፍ ተጫጭኖት አንገቱን ደፍቶ እያንጎላጀ ነበር። በመሆኑም በኢጣልያዊው ድምጽ ደንግጦ ከተቀመጠበት ብድግ አለ። ፈጥኖ ፊቱን በመለቃለቅም እንቅልፉን ለማባረር ሞከረ። እንቅልፉን አባርሮ ከተረጋጋ በሁዋላ ኢጣልያዊው ስለተናገራቸው ሁለት ቃላት ማሰላሰሉ አልቀረም።

ለምን ‘ማርዮ’ እንደተባለ ገብቶታል። ‘ማርዮ’ የአገልጋዮች ሁሉ የወል ስም ስለመሆኑ እህቱ የነገረችውን አልረሳም። ‘ፒግሮ’ ስለሚለው ቃል ትርጉም ግን አላወቀም። ጥርሱ ላይ ነክሷት ቆየና ለቡና ወደ ወጥቤት ሲሄድ የቃሏን ትርጉም ጠየቀ። “ሰነፍ” ማለት መሆኑን ሲነግሩት ተከፋ። በጣም ተከፋ። ብርቱ ገበሬ እንደመሆኑ እንዲህ ያለ ስድብ ሲሰደብ ኑረነቢ በመላ ህይወቱ ለመጀመሪያ ጊዜ ነበር። መሰደቡን ሲያውቅ የቡና ስኒውን አስቀምጦ መንጎራደድ ጀመረ። ከጣውቀ ጀምሮ አያቶቹ የሰሩትን ጀብዱ፤ የነበራቸውን የክብር ደረጃ እየተረከ ኩሽናውን በጠበጠ። ጣውቀ ሲገደል በተለይ ዓዲ ሃመጃይ ከዓዲ ሙሲ ጋር እንዴት እንደተዋጋ በዝርዝርና በወኔ

ተናገረ። ወጥቤቶቹና አስተናጋጆቹ መጀመሪያ ላይ ጥሩ ቀልድ ያገኙ ያህል ከልባቸው ሳቁ። በኑረነቢ ሽለላ ተዝናኑ። የኑረነቢ መንገብገብ ከአንጀትና ከልብ መሆኑን ሲረዱ፤ እየጋለ በመሄድ ላይ መሆኑን ሲያጤኑ ግን ተደናግጠው ሊያረጋጉት ተረባረቡ። በዚያ ስሜቱ ኑረነቢ አንድ ኢጣሊያዊ ላይ አደጋ ቢያደርስ ጦሱ ለሁሉም እንደሚተርፍ በመንገር ሰከን እንዲል ለመኑት። በየቀኑ ያለምክንያት ዘንቢል ሙሉ ስድብ እየተሰደቡ እንደሚውሉ የራሳቸውን ልምድ በየተራ ነገሩት። 'ፒግሮ' የሚለውን አጠራር ጥልያኖቹ ለአገሬው ሰው ሁሉ እንደሚጠቀሙበት፣ ከዚያም የከፉ ስድቦች መኖራቸውን አስረዱት። ከ"ፒግሮ" የከፉ "ቦርኮ"፣ "ሞስካ" እና "ሞስኪ" የተባሉ ስድቦችን እየተሰደቡ እንኳ በትእግስት መቻላቸውን አጫወቱት። በተለይ "ሞስካ" እና "ቦርኮ" ወደፊትም ቢሆን ሊገጥሙት ስለሚችሉ ችላ ብሎ ማለፍ እንደሚሻለው መከሩት።

ኑረነቢ እጁ እየተንቀጠቀጠ፣ በአፍንጫው እሳት እየተነፈሰ ከማዳመጥ በቀር ለጊዜው የሚናገረው ቃል ጠፋው።

በዚያን ሌሊት በስራ ገበታው ላይ ሳለ ለመጀመሪያ ጊዜ ኢጣልያውያንን በጥላቻ አይን ተመለከተ። በበቀል ስሜት አተኮረባቸው። ህይወቱን ሙሉ በአድካሚ የግብርና ስራ የኖረ ሰው እንደመሆኑ፣ የተከበረ የፋና ጭቃ ሹም ሆኖ የኖረ እንደመሆኑ "ፒግሮ" የሚለው ስድብ ፍጹም መረን የለቀቀ ክብረነክ ሆኖ ተሰማው። የስራ ባልደረቦቹ ነገሩን አቃልለው ቢያበርዱትም ከአንጀቱ ሊወጣ አልቻለም። ችላ ማለት የማይታሰብ ሆነበት። እነ ሙሲ ፍረመሃቅ፤ እነ ጨዋግ፣ እነ ናሽህ፣ እነ ሳምራ ተሰድበው ችላ ስለማለታቸው አንዳች ታሪክ አያውቅም። ለክብራቸው ሲሉ መዋጋታቸውን፣ መሞታቸውን ግን ያውቃል። እና በአባቶቹ ያልተደረገ እንዴት በሱ ጊዜ ይደረጋል?

እየረጋ ሲሄድ ማሰላሰል ጀመረ።

በርግጥ ኢጣልያዊው በሰደበው ሰአት እንቅልፍ ተጫጭኖት ከአንገቱ ቀና ደፋ እያለ ነበር።

"ቢሆንስ?" ሲል ከራሱ ጋር ሞገተ።

አያቶቹ፣ ቅድመ አያቶቹ ከጣውቀ እስከ በኺት ቀን እየሰሩ

ሌሊት ሲተኙ ኖረዋል። ምንም እንኳ በስራ ገበታው ላይ ሳለ ማንቀላፋቱ ልክ ባይሆንም አስነዋሪ ስድብ መሰደብ ግን አልነበረበትም። እና ለራሱ እንዲህ አለ።

“መሰዳደብ ለማንኛችንም ቢሆን ጥሩ አይደለም!”

አሳቡን እያኘከው መሄድ ጀመረ።

የተሰደበ የዳካ - ቦጎስ አባወራ ክብሩን ሳያስጠብቅ ዝም ሊል አይችልም። በድፍን ዳካ - ቦጎስ ስድብ ነውር ነው። “ስድብ ልብን ያቆሸሻል” ተብሎ ይታመናል። ዳካ - ቦጎስ ሰውን ቀርቶ ከብቶቹንና ግመሎቹን እንኳ አይሰድብም። ዓዲ ሙሲ ዘራቸው የጠፋው በፈጸሙት ስህተት ነበር። ጣውቀን ያህል ሰው ገድለው እንዴት በዳካ - ቦጎስ ምድር ላይ በሰላም ለመኖር አሰቡ?

ኑረነቢ እንዲህ እያሰላሰለ፤ እንዲህ እየተብከነከነ፣ እንዲህ እየተቆጨ፣ አላህን እያማረረ ሌሊቱ እንደምንም ነጋለት። እንቅልፍ ባይኑ ዝር አላለም። እንደፈጠጠ ነበር። ጠዋት ወደ እህቱ ቤት ሲመለስ ስለዚሁ ጉዳይ ለልጆቹም ሆነ ለእህቱ አንዳች አልተነፈሰም። የዳካ ምድር አባወራ እንደመሆኑ እንዲህ ያሉ የመከራ ጊዜ ፈተናዎችን ብቻውን መሸከም እንዳለበት ከራሱ ጋር ተነጋገረ።

በርግጥም የስራ ባልደረቦቹ እንደነገሩት ትንኮሳዎች ተደጋገሙ። ሞስኪ፣ ሞስካ፣ ፒግሮ፣ ቦርኮ የመሳሰሉ የስድብ ቃላት የሰላምታ ያህል እዚህም እዚያም ሲነገሩ ሰማ። እንዲህ የተሰደቡ ሰዎች ምንም ያልተፈጠረ ያህል እየሳቁ ስራቸውን ሲሰሩ በመመልከቱ መደነቅ አደረበት። ከተሰደበበት እለት ወዲህ እንዳያንቀላፋ በመጠንቀቁ የከፋ ስድብ ባይገጥመውም ንቀታቸውን ከገጻቸው ላይ ያነብ ነበር። እሱም ከአሁን አሁን “ቦርኮ” ወይም “ሞስካ” እንዳይሉት መሳቀቁ ባሰበት። ወጥቤቶቹ የሬስቶራንቷን ባለቤት በሌለችበት ሲሰድቧት ደጋግሞ ሰምቷል። ቱርካዊቷ ግን ፊት ለፊት ትሰድባቸዋለች። አንዱ ሌላውን አለምክንያት እንዳመጣለት መስደብ የከተማ ወይም የምጽዋ ልማድ መስሎ ተሰማው። የከተማ ልማድ ከሆነ እዚህ ልማድ ውስጥ መዋሃድ እንደማይችል ልቦናው አወቀ። እናም ስድብ የማይሰማበት፣ ከከተማ ራቅ ያለ፣ አድካሚም ቢሆን ሰላም ያለበት፣ የማይሳቀቅበት ስራ ለመፈለግ አሰበ። ኢጣልያውያን ከበዙበት አካባቢ ርቆ እየሰራ ልጆቹን የሚያሳድግበት

ሁኔታ እንዲፈጠር በጥብቅ ተመኘ።

በምጽዋ አካባቢ ስራ ማግኘት ችግር አልነበረም።

ኢጣልያውያን ምጽዋን ከያዙ ወዲህ የጉልበት ሰራተኛ በገፍ የሚፈለግበት ጊዜ ነበር። ሙያ ያላቸው ጥሩ ክፍያ ያገኛሉ። በተለይ የአናጢና የግንበኛ እጥረት ነበር። ኑረነቢ ልዩ ሙያ ስላልነበረው የጉልበት ስራ ማግኘት ነበር አማራጩ። ከአሳ አስጋሪዎች ጋር በጀልባ ወደ ባሕር በመሄድ አሳ ማጥመድ አንዱ አማራጭ ነበር። የውሃ ዋና ስለማይችል ተወው። ለኢጣልያ ወታደር ሆኖ የመቀጠሩን አማራጭ ማሰብም አልፈለገም። ረዳት ግንበኛ ወይም አናጢ ሆኖ የመስራት እድሎችም ነበሩ። ከሰሓጢ ወደ ማይ አጣል ለመቀጠል በተዘጋጀው የባቡር መንገድ ግንባታ ስራ ተቀጥሮ የጉልበት ስራ መስራቱን መረጠ። ቀጣዩ የባቡር መንገድ ግንባታው ስራ ገና ባይጀመርም የሰረገላ መንገዱ እየተጠረገ ስለነበር ይህን ስራ ያለማመንታት መረጠው። እናም ሞስኪ ከሚያንጥበበት፤ ቦርኮ ቃላት ከበዙበት ስራው ተሰናበተ። ለዘልአለሙ ተሰናበተ።

ከስራው ተሰናብቶ በነጋታው ማለዳ እህቱ ቤት ሲደርስ ይህንኑ አዲስ ዜና ለቤተሰቡ ተናገረ። ሰርቶ ገንዘብ ይዞ እስኪመለስ ልጆቹን እንድትጠብቅለት ለእህቱ ጥብቅ አደራ ሰጥቷት ሲያበቃ፤ በሶስተኛው ቀን ልጆቹንም እህቱንም ተሰናብቶ ምጽዋን ለቆ ወጣ።

* * *

ኑረነቢ ተሰናብቷቸው ከሄደበት እለት ጀምሮ መርየም በአደራ የተረከበቻቸውን ልጆች ይዛ ወንድሟን በተስፋ ጠበቀችው። ኑረነቢ ግን ሳይመለስ ዘገየ። አምስት ወራት እንደዋዛ ሲያልፍ ስጋት ገባት። በባቡር መንገድ ግንባታው ስራ ላይ እየሰራ ከሆነ ቢያንስ በሁለተኛው ወር መምጣት ነበረበት። ልጆቹን ትቶ ወደ አገሩ ወደ ቦጎስ ሊመለስ እንደማይችል ርግጠኛ ነበረች። ምክንያቱም የድርቁ ጊዜ ገና አላለፈም። "ምናልባት ለኢጣሊያ ቅኝ ገዢዎች በወታደርነት ተቀጥሮ ወደ ደጋ ሄዶ ይሆን?" ስትል አሰበች። ይህም ቢሆን ያለበትን ሁኔታ ለመግለጽ የሚያግደው አይሆንም።

ኑረነቢ ስላለበት ሁኔታ ወይም ስለጤንነቱ መልእክት አለመላኩ በእጅጉ አሳሰባት። ወራት አንድ ባንድ እንደዋዛ ሲያልፉ

ስለወንድሟ ደህንነት መጨነቋ እየበረታ ሄደ። “እንደ ልጆቹ እናት እሱም በረሃ ላይ ወድቆ ይሆን?” ስትል አሰበች። “ምናልባት ደግሞ ታሞ ረዳት እየፈለገ ይሆን?” የሚል ጥያቄ እረፍት ነሳት። ችግሩ የኑረነቢ ደህንነት ማሳሰቡ ብቻ አልነበረም። መርየም የወንድሞቿን ልጆች ለማሳደግ የሚያበቃ ገቢ አልነበራትም። ከመነሻውም ልጆቹን ስትረከብ አባታቸው ስራ ሰርቶ ያግዛቸዋል በሚል ተስፋ ነበር። አባታቸው በወጣበት ከቀረ በሁዋላ ግን ከልጆቹ ጋር ያሳለፈችው ጊዜ የችግርና የፈተና ጊዜ ሆነባት። የረሃቡ አደጋ እየተባባሰ ሄደ። ቁርስና እራት ቀምሰው ማደር ቢችሉም ጦም መዋል የሚያጋጥምበት ጊዜ እየበዛ ሄዶ ነበር። ልጆቹ ለአቅመ ስራ ስላልደረሱ ሊያግዟት አልቻሉም። የልጅ ስራዎችን ለመስራት የሚያበቃ አቅምም አልነበራቸውም። ገና ቆዳቸው አጥንታቸው ላይ እንደተጣበቀ ነበር።

አክስታቸው በጉዳዩ ላይ ብዙ ካሰበችበት በሁዋላ ኑረነቢ ከአቅሙ በላይ የሆነ ችግር ገጥሞት ሊሆን እንደሚችል አመነች። ሞቶም ከሆነ ቁርጡን ማወቅ ፈለገች። ታሞም ከሆነ ልትደርስለት እንደሚገባ አሰበች። ያለምክንያት ግን እንዲህ ሊሰወር አይችልም ስትል ከራሷ ጋር መከረች። እናም ልጆቹን ለአሳዳጊ ሚስዮናውያን ሰጥታ ወንድሟን ፍለጋ ለመጓዝ ቆርጣ ተነሳች።

ከምትኖርበት ቤት ብዙም ባልራቀ ርቀት አንድ የተዘጋ ሰቀላ ቤት አለ። ይህ ቤት የላዛሪስት ካቶሊካውያን ነበር። ሆኖም በቋሚነት አይቀመጡበትም። በምጽዋ በኩል ወደ ፈረንሳይ ወይም ወደ መርሳ አቦክ ለመጓዝ ሲመላለሱ ግን ቤቱን ይጠቀሙበታል። በጌጠኛ የቱርካውያን ጥበብ የተሰራውን ይህን ቪላ በ1841 የፈረንሳይ መንግስት ለቆንስል ጽህፈት ቤት ተከራይቶት ነበር። የፈረንሳይ ቆንሲል የነበረው ፍራንሷ ሶማኝ የአቢሲንያን ወኪልነት ደርቦ ይሰራ በነበረበት ጊዜም በዚሁ ቪላ ውስጥ ይኖር ነበር። ቪላው የነባር ቱርካውያን ንብረት ቢሆንም በኪራይ ከፈረንሳውያን እጅ ወጥቶ አያውቅም። ኩሬኩስ የተባለች የፈረንሳይ አሳሽ የጦር መርከብ ለጥቂት ቀናት ምጽዋ ላይ መልህቅ በጣለች ጊዜ የመርከቧ አዛዥ በዚሁ ቪላ ውስጥ ሰንብቷል። አባ ዮሃንስ ቪላውን የተረከበው ከሶማኝ ነበር። ከዚያ ወዲያ አልለቀቁትም።

በዚያን ሰሞን ጢሙን ያንዣረገገ አንድ ፈረንሳዊ ቄስ

በሰረገላ እየተመላለሰ ወደዚያች ሰቀላ ቤት ሲገባና ሲወጣ መርየም ተመልክታለች። አባ ዮሃንስ እንደሚባል፣ በጣም ደግ ሰው እንደሆነ፣ ትግርኛና ብሌን ቋንቋ እንደሚናገር፣ ከረን ላይ ወላጅ አልባ ህጻናትን እንደሚያሳድግ ሰምታለች። መርየም ለሶስት ቀናት ያህል በጉዳዩ ላይ ስታሰላስል ከሰነበተች በሁዋላ አንድ ቀን ቁሱ ወደቤት ሲገባ ጠብቃ ተከትላው በመግባት ችግሯን ዘርዝራ አዋየችው። አባ ዮሃንስ መርየምን በትህትና ተቀብሎ በጥሞና ከሰማት በሁዋላ እንዲህ አለ፣

“ከሁለት ቀናት በሁዋላ ወደ ፈረንሳይ እየሄድኩ ነው። ሶስት ወይም አራት ወራት እዚያ እቆይ ይሆናል። እዚህ ኡምኩሉ የነበረ የኛ ካምፕ በድርቁ ምክንያት ለጊዜው ሰው የለበትም። ፈረንሳይ ደርሼ እስክመጣ ልጆቹ ካንቺ ጋር መቆየት ከቻሉ ስመለስ ወደ ከረን ይዣቸው እሄዳለሁ። ካልሆነ ግን አምጪያቸውና ኡምኩሉ ከኢቫንጀሊካል ወንድሞቻችን ዘንድ አቆያቸዋለሁ።”

መርየም አባ ዮሃንስን ደግማ ደጋግማ አመሰገነች። በነጋታው ማለዳም እድሪስና አድምን ወስዳ ለአባ ዮሃንስ አስረከበች። እንባዋን እያዝረበረበች የወንድሞቿን ልጆች ስትሰናበት የምትናገረውን በትክክል አታውቅም ነበር። የጭንቀት ቃላት ከአንደበቷ እያፈተለኩ ወጡ፣

“ለእናንተው ብዬ ነው፤ እንድትማሩ ብዬ ነው፤ አባታችሁን ፈልጌ ካገኘሁት በሁዋላ ይዤው እመጣለሁ፤ አይዟችሁ። ለናንተም የሚሻላችሁ ጥሩ እየኖራችሁ መማር ነው። ከኔ ጋር ብትቆዩ ምን አደርጋችሁዋለሁ? በረሃብ ትሞታላችሁ። አላህ ከናንተ ጋር ይሁን!”

አባ ዮሃንስ በጸጥታ ሲያዳምጣት ከቆየ በሁዋላ አጭር ጸሎት በማድረግ መርየምን አሰናበታት። የልጆቹን ራስ እያሻሸም በአባትነት መንፈስ ያጫውታቸው ጀመር።

* * *

መርየም የልጆቹን ጉዳይ አባ ዮሃንስ ላይ ከተወች በሁዋላ በሳምንቱ ወንድሟን ፍለጋ ምጽዋን ለቃ ወጣች። እስከ ሰሓጢ እቃ በጫነ ባቡር ተሳፈረች። ከዚያም በእግር ቀጠለች። እናም ወደ ማይአጣል የባቡር መስመር ለመዘርጋት በሚደረገው የዝግጅት ስራ ላይ ወደ ተሰማሩት የጉልበት ሰራተኞች ሰፈር ደረሰች። የተሸከርካሪ

የአፈር መንገዱ ስራ ከባቡር መንገዱ ግንባታ ጋር ጎን ለጎን እየተስፋፋ በመሰራት ላይ ነበር። በዚህ ስራ ላይ የተሰማሩት የጉልበት ሰራተኞች ብዛታቸው የኑረነቢን እህት ክፉኛ አስደነጣት።

ሰራተኞቹ ብዙውን ጊዜ ተስያት ላይ ይተኛሉ። ዋና የስራ ሰአታቸው ሌሊትና ማለዳ ነበሩ። ለመንገድ ስራው ድንጋይ ሲፈልጡ አድረው፤ ወይ ደግሞ የባቡር መንገድ አግዳሚ ብረት ሲሸከሙ አርፍደው በድካም ነፍስና ስጋቸው ተለያይታ ተስያቱን ተዘረጋግተው በሚተኙበት ሰፈር እየሄደች ስለ ወንድሟ ጠየቀች።

ተስፋ ባለመቁረጥ ደግማ ደጋግማ አጠያየቀች።

“ኑረነቢ የሚባል ሰው ታውቃላችሁ? ከሓልሓል ቦጎስ የመጣ - የፋና ጭቃ ሹም የነበረ - የዓዲ ሙሲ፤ የሰመረጽዮን ወገን - ኑረነቢ በኺት - ታናሽ ወንድሜ ነው - ቁመቱ ዘለግ ያለ - ቀይ ነው - አታውቁትም? አላያችሁትም?”

እንደማያውቁት ከነገሯት በሁዋላ...

“..ደህንነቱን ሳይነግረኝ ብዙ ወራት አለፈና ሰጋሁ. . .” ብላ ምሬትና ብሶቷን ታስከትላለች፣ “. . . አላህ ፈቃዱ ሆኖ ካገኛችሁት ወይ ወሬ ከሰማችሁ እባካችሁ ጠይቁልኝ? ሁለት ወንድ ልጆቹ ኡምኩሉ ክርስትያኖች ዘንድ ናቸው። በአራት ወራት ጊዜ ውስጥ መልሰን ካልወሰድናቸው ሁዋላ የኛ አይሆኑም። የሰመረጽዮን የዘር ሃረግ መቋረጡ ነው። ዓዲ ሙሲ ወቀሳው በኔ ላይ እንዳይሆን ሰጋሁ። አቅም አጥቼ ነው። በረሃብ እንዳይሞቱ በማለት ነው። ኑረነቢን እንደምንም ፈልጌ ካገኘሁት ልጆቹን መልሶ እንዲወስዳቸው አደርጋለሁ። ያን ጊዜ የኔም መንፈስ ታርፋለች። ካልሆነ እንግዲህ በአላህ ፊት ሃጢአተኛ መሆኔ ነው።”

ተስፋ የሚሰጥ ወሬ ልታገኝ ግን አልቻለችም። ቢሆንም ፍለጋዋን የማቋረጥ ነገር አልታየባትም። በትጋት ማጠያየቋን ቀጠለች። ስንቅ ጎደል ሲልባት ስኳርና ሻይቅጠል ገዝታ፣ ማንቆርቆሪያ ተከራይታ ለጉልበት ሰራተኞች ሻይ የመሸጥ ስራ ጀመረች። ሰራተኞች ሻይ ፈልገው ሲመጡ ስለ ኑረነቢ ትጠይቃለች። በስራ ላይ ሳለ የታመመ፣ የሞተ ከነበረ ታጠያይቃለች። ኑረነቢ የሚል ስም ግን ልትሰማ አልቻለችም።

ከጉልበት ሰራተኞች ባሻገር በግመልና በሰረገላ የሚመላለሱ ነጋዴዎችንም ትጠይቃለች። ሻይ የመሸጡን ስራ የጀመረችው ከሰሓጢ ወደ ማይአጣል በቀጠለው የመንገድ ስራ ዳርቻ ነበር። ተሰርቶ እስካለቀው መንገድ ድረስ የሚመላለሱት በአብዛኛው በፈረሶችና በበቅሎዎች የሚጎተቱ ሰረገላዎች ነበሩ።

ከምጽዋ የመጣ ሰረገላ ሰሓጢ ወይም ማይአጣል ፈረስ ይቀይራል። የተቀየረው ፈረስ ምግብና ውሃ ተሰጥቶት ያርፋል። የአገሬው ሰው በቅሎና ፈረሶችን "ፌርሞ!" እያለ ነበር የሚጠራቸው። ኢጣሊያኖቹ ፈረሶቹን "ፌርሞ! ፌርሞ!" ሲሉ ሰምቶ ስማቸው መስሎት ነው። "ፌርሞ" ግን በኢጣሊያ ቋንቋ 'ቁም' ማለት ነበር። ፌርማታ - መቆሚያ ነው። ፈረሶቹ በየፌርማታው ሲደርሱ 'ፌርሞ! ፌርሞ!' የሚል ቃል አየሩን ይሞላዋል። አንዳንዶቹ "ፌርሞ" ማለት ሰረገላ ማለት ስለሚመስላቸው "ፌርሞ መጣ" እያሉ ፈረስ ለመቀየርና የተጫነ እቃ ለማውረድ ከወዲያ ወዲህ ይካለባሉ። ጣሊያኖች ከአውስትሬልያ ገዝተው ያመጧቸው እነዚህ ግዙፍ አጋሰሶች ከሰረገላዎች በተጨማሪ መድፎችንም ይጎትቱ ነበር።

ዘወትር ፋታ አልነበረም። ሰረገላዎች ያለማቋረጥ እቃና ሰው እየጫኑ ይመላለሳሉ። ከማይ አጣል እስከ ምጽዋ ያለው መንገድ የሰረገላዎቹ ጎማና የአጋሰሶቹ ኮቴ በሚያነሳው አቧራ ተሸፍኖ ውሎ ያድራል። ሰራተኞቹ በአብዛኛው ብረት ሲሸከሙ ይዘፍናሉ። በከፍተኛ ድምጽ ያከላላሉ። ከአገሬው ሰዎች ባሻገር እንጀራ ፍለጋ ከትግራይ፣ ከበጌምድርና ከወሎ የመጡ ሸቃዮችም በብዛት ነበሩ። አንዳንዶቹ ከጌቶቻቸው ያመለጡ ባሮች ሲሆኑ፤ የሚከፈላቸው ደሞዝ ዝቅተኛ ነበር። እየተደበደቡ በነጻ ከሚሰሩባቸው ጌቶቻቸው ነጻ የወጡ ባሮች በአነስተኛ ደሞዝ መስራቱን እንደ መልካም እድል ይቆጥሩት ነበር። ሸቃዮቹ በቋንቋ ባይግባቡም በዘፈን ይግባባሉ። ጥቂት ቃላትን በመያዝ አንዱ የሌላውን ዘፈን እየዘፈነ ድንጋይ በመፍለጥ ወደ አስመራ የሚያመራውን መንገድ ሌሊትና ቀን ያነጥፋል። ከጉልበት ሰራተኞች ዘፈንና ማከላላት ባሻገር ምንጊዜም ከፍተኛ የብረት ኳኳታ ድምጽ ይሰማል። የፈረሶች እህህታ፣ የሰረገላዎች ሿሿታ ገና ከሩቅ ይሰማል።

መርየም ሻይ ፈልገው ከሚመጡት ባሻገር፣ ፈረስ ለመቀየር

ወደሚቆሙት ሰረገላዎች ጠጋ እያለች ስለ ኑረነቢ ማጠያየቋን ቀጠለች። ሰረገላ ነጂዎች የአገሬው ሰዎች ሲሆኑ፣ ተሳፋሪዎች በአብዛኛው ኢጣልያውያን ናቸው። አልፎ አልፎ አረቦችና ጥቁሮችም በሰረገላ ተሳፍረው ሲጓዙ ይታያሉ። ተሳፋሪው ነጭ ከሆነ የኑረነቢ እህት ደፍራ ወደ ሰረገላው አትጠጋም። ኢጣልያውያኑ ተሳፋሪዎች ከሰረገላ ወርደው ለመናፈስና ወገብ ለመሞከር ራቅ ሲሉ ግን ፈረስ ወደሚቀይሩ ሰረገላ ነጂዎች ጠጋ ብላ ስለ ኑረነቢ ታነሳለች።

ብዙውን ጊዜ በደፈናው "አላውቅም" ብለው ጀርባቸውን ይሰጧታል። አንዳንዶች ግን ኑረነቢ የሚባል ሰው እንደማያውቁ ከገለጹ በሁዋላ፤ ወደ ደጋው አገር ሄዳ ብትፈልገው እንደሚሻል ይመክሯታል። ርግጥ ነው፤ አንድ ጊዜ ተስፋ አጊኝታ ነበር።

ጹናማይ የተባለ ወጣት የመጋዘን ዘበኛ ኑረነቢ የተባለ ሰው እንደሚያውቅ ነገራት። በጣም ተስፋ ስላደረገች ሻይ እና የገብስ ቂጣ ጋብዛ የሚያውቀውን በዝርዝር እንዲነግራት ለመነችው። ስኳር በዛ አድርጋ በመጨመር ሻይ ደገመችው።

ጹናማይ የታወቀ ቀልደኛ ነበር።

በእረፍት ሰአት ሰራተኞችን በቀልድና በዘፈን ያዝናናል። ሴቶች ይከቡታል። የእጃቸውን መዳፍ እያየ ስለሚያገቡት ባል ወይም ስለወደፊት ህይወታቸው ይተነብይላቸዋል። እግረመንገዱን መዳፋቸውን እያሻሻ ሲያሞቃቸው እጃቸውን እየነጠቁ ይሸሻሉ። ግን ርቀው አይሄዱም። ተመልሰው ይመጡና እጃቸውን ይሰጡታል።

መርየምን ደህና አድርጎ አጽናናት፣

"አታስቢ! በህይወት አለ። እኔ ሳገኘው ሙንጣዝ ነበር። እስካሁን እድገት አጊኝቶ ብሉቾባሽ ደርሶ ሊሆን ይችላል!"

"ጤንነቱ ብቻ ደህና ይሁን።" አለች በመሳቀቅ።

"ወፍሮ ተስማምቶታል። ቀልቶ ጥልያን መስሏል። የጥልያን ቋንቋ ሲናገር ደግሞ እንደ ኢሚሊዮ ኦሊቪየሪ ነው። በዚህ አያያዙ ለትምህርት ናፖሊ ሳይልኩት አይቀሩም። ጆሜትራ ኦሊቪየሪ ምን ይላል? Vedi Napoli, e poi muori! ይሄ ምን ማለት ነው? ናፖሊን ካየህ በሁዋላ ብትሞትም አይቆጭ።"

ከሰሉን እያርገበገበች ማዳመጧን ቀጠለች፣

“እንዴት ያለ አዋቂ ሰው! ለመሆኑ ባልሽ ነው?”

“ወንድሜ ነው። በአባቴ በኩል ወንድሜ ነው።”

“አፍረሽ እንዳይሆን ብዬ ነው?”

“ባሌ ቢሆን ለምን አፍራለሁ? ሙች ታገኘዋለህ ታዲያ?”

“እፈልገዋለሁ እስኪ። የስራ መብዛት ነው ችግሩ። ሰው ለመኝታ እንኳ ጊዜ አጥቷል። ጆሜትራ ኦሊቪየሪ ከሰሓጢ ወደ ጊንዳዕ የሚያመራ የባቡር መንገድ ለመዘርጋት ንድፍ እየሰራ ነው። ወንድምሽ ለጥበቃ ኦሊቪየሪን አጅቦ ሳይሄድ አልቀረም። ማን ነበር ያልሺኝ ስሙን? ኑሪ ነቢል?”

“ኑረነቢ ነው ያልኩህ። ኑረነቢ በኺት።”

“ያው ነው።”

“ያውማ አይደለም። ኑረነቢ ሌላ፣ ኑሪ ነቢል ሌላ።”

የቀን ሰራተኞች በሳቅ ተዝናኑ።

መርየም የጹናማይን ቀልደኛነት አላወቀችም። እንዲህ በጭንቀቷ ላይ ሳለች ይቀልዳል ብላም አልገመተችም። ስሙን ሲያሳስት ግን ጠረጠረች። እና የማረጋገጫ ጥያቄ ጣል አደረገች፣

“ደህና ከሆነ እንዴት ወደ ልጆቹ ሳይመጣ ቀረ ብዬ ነው?”

“ፈቃድ ማግኘት ችግር ነው። ይህን መንገድ ለመስራት ብዙ ገንዘብ እየፈሰሰ ነው። እረፍት፣ ፈቃድ አይታሰብም። እንግዲህ አስቢው፤ ከምጽዋ እስከ ሰሓጢ ያለውን የባቡር መንገድ ለመዘርጋት ብቻ እስካሁን ሶስት ሚሊዮን ሊሬ ወጭ ሆኗል። መንገዱን እስከ ጊንዳዕ ለመቀጠል አስር ሚሊዮንም አይበቃም። አስመራ ለመድረስ እንግዲህ ስንት ሚሊዮን ሊፈጅ ነው? ለመሆኑ ሚሊዮን ሲባል ብዛቱ ይገባሻል?”

“አይ! አላውቅም።”

“ለምሳሌ እኔ እዚህ ስንት ይከፈለኛል? በቀን አንድ ሊሬ። የሶስት ሚሊዮን ቀናት ደሞዝ ማለት ነው። ሶስት ሚሊዮን ቀናት

ሲባል ስንት አመታት ማለት ነው? እዚህ ያለው ሰው ሁሉ፣ ማለትም አስካሪው፣ ሙንጣዙ፣ ቡዝባሹ፣ ኡዝባሹ፣ ብሉቅባሹ፣ ሹምባሹ፣ አራሹ፣ ባርያው ሁሉ እድሜው ተቀጣጥሎ ቢደመር ሶስት ሚሊዮን ቀናት አይደርስም። አሁንስ ሚሊዮን ሲባል ሂሳቡ ገባሽ?"

"እንጃ ልጄ?"

"እንዴት አድርጌ ላስረዳሽ? ለምሳሌ እኔ ሶስት ሚሊዮን ሊሬ ቢኖረኝ እስክሞት ድረስ በአልጋ ላይ አስተኝተው የሚሸከሙኝን ሰዎች መቅጠር እችል ነበር። ወይም እስክሞት ድረስ በየቀኑ ጥዋት ጥዋት የባርካ ፍየል ማሳረድ በቻልኩ። ቁርስ ዱለት፣ ምሳ አልጫና ቀይ ወጥ፣ መክሰስ ቋንጣ ፍትፍት በገብስ ቂጣ፣ ራት መረቅና ገንፎ እየበላሁ አርጅቼ እስክሞት ድረስ ገንዘቡ አያልቅም።"

ጹናማይ አልጋ ላይ ስለመንፈላሰስ፣ ስለ ዱለትና መረቅ በምኞት መርቅኖ ፊቱ ጉበት ቢመስልም እንደምንም ወጉን ቀጠለ፣

"...ለማንኛውም ወንድምሽ ከጆሜትራ ኢሚሊዮ ኦሊቪየሪ ጋር በመስራቱ እድለኛ ነው። አታስቢ። ፈልጌ እዚህ መምጣትሽን እነግረዋለሁ። ማን ነበር ያልሺኝ ስምሽን? መርየም በኺት። በጣም ጥሩ። ግሩም ሻይ ጠጣሁ! ግሩም ቂጣ። የገብስ ቂጣ እወዳለሁ።"

ሌላ ቀን እንዲሁ ሻይ እየጠጣ፣ ቂጣውን እየገመሰጠ ከቀንዱም ከሸኮናውም እየደባለቀ ሲያወጋ፣

"እድሜህ ስንት ደረሰ?" ስትል ጠየቀችው።

"ሃያ አምስት አልፏል።"

"አገባህ?"

"አግብቼ ነበር። ከወለደችልኝ በሁዋላ ተፋታን።"

"ምነው ልጄ?"

"ትቀናለች። እኔ ደግሞ ጭቅጭቅ አልወድም። ዋናው ነገር ወንድ ልጅ ሰጥታኛለች። አንበሳ የመሰለ። በየወሩ ፈቃድ ሳገኝ ምጽዋ እየሄድኩ አየዋለሁ።"

"ስንት አመት ሆነው?"

"ዐናይ ልጄ የአምስት አመት ጎረምሳ ሆኗል። ከፍ ሲል

ናፖሊ ልኬ አስተምረዋለሁ። ፍላጎቴ እንደ ኢሚሊዮ ኦሊቪየሪ ጆሜትራ እንዲሆን ነው። ካልተቻለ ግን ካቫሌር ይሆናል።"

"ዑናይ ምን ማለት ነው?"

"አላውቅም። እናቱ የሰጠቸው ስም ነው።"

"ያንተስ ስም ትርጉሙ ምንድነው?"

"ምኑን አውቄው ብለሽ? ገና ልጅ ሳለሁ አባቴ ከአስመራ ወደ ጸዓዘጋ ሲጓዝ ባቡር ተገልብጦ በአደጋ ሞተብኝ። የስሜን ትርጉም ሳልጠይቀው እንዲሁ ቀረሁ። አባቴ ባቡር ነጂ ነበር። የባቡር ነጂ ልጅ ይኸው የባቡር ጣቢያ ዘበኛ ሆኗል።"

መርየም ቀና አለች፣

"ባቡር አስመራ ደርሷል እንዴ?"

በሻይና በቡናው ዙሪያ የከበቡት ሁሉ ሳቁ። ጹናማይ አይስቅም። እንደሚቀልድ በዚያን ቀን ገባት።

የጹናማይ ቀልደኛት ከገባት በሁዋላ ስለ ኑረነቢ የዘባረቀው እንዳመጣለት መሆኑን ተረዳች። እናም ሰረገላ ነጂዎች የጠቆሟትን ወደማሰላሰሉ ገባች። ማለትም ኑረነቢ ወደ ደጋው አገር ተሻግሮ ሊሆን እንደሚችል አውጠነጠነች።

በዚያው ሰሞን ግን በዊዓ እና በሕርጊጎ አካባቢ፤ በፈረስና በግመል የሚንቀሳቀሱ ሰባት ሽፍቶች መነሳታቸው ተሰማ። ወሬው ባንድ አፍታ ምጽዋን አዳረሰ። የሽፍቶቹ ማንነት አነጋገረ። እየለዩ ኢጣሊያውያንን ነበር የሚያጠቁት። የአገሬውን ሰው አይነኩም። ባንድ በኩል የሕርጊጎ ሰዎች ናቸው ሲባል፤ በሌላ በኩል ከሳህል የመጡ ናቸው ተባለ። ስለማንነታቸው በርግጠኛነት "እንዲህ ነው"" ብሎ መናገር የሚችል ግን አልተገኘም። ከኢጣሊያ ወታደሮች ጋር መታኮሳቸውና ሶስት ወይም ሁለት ማቁሰላቸው፤ ጠመንጃ ከመጋዘን መዝረፋቸው ተሰማ። ከመታሕት ገበሬዎች የሚያጋጫቸውን ድርጊት አይፈጽሙም። ፍየል ሲያሳርዱ ክፍያ ይፈጽማሉ። ያለባለቤቱ ፈቃድ ከማንም ጎጆ ገብተው አያድሩም። በርግጥ "አላማችን ይሄ ነው" ብለው ሲናገሩ የሰማቸው የለም። ከቅኝ ገዢው ቁጥጥር ነጻ ሆነው በሽፍትነት ከመኖር ያለፈ ጉዳይ አልነበራቸውም። የገበሬ ጎተራ

በርባሪ፤ ፍየል ነጣቂ ባለመሆናቸው አገሬው በክፉ አላያቸውም።

የሸፍቶቹ ወሬ በተሰማ ሰሞን መርየም ተረበሸች። በጣም ተረበሸች። ሆኖም ወደ አእምሮዋ ብቅ ጥልቅ እያለ የሚረብሻትን አሳብ ላለማመን ከራሷ ጋር ታገለች። አንድ ሰሞን የሸፍቶቹ ወሬ ጠፍቶ ይሰነብትና እንደገና ተጋኖ ይነሳል። ጋህቴላይ መታየታቸው ሲሰማ፤ የኢጣልያ የኮማንዶ ቡድን መንገድ መሪ ይዞ ወደ ጋህቴላይ ይገሰግሳል። ቴሳቸውን እንጂ ሸፍቶቹን አያገኝም።

ጥቂት ወራት እንዲያ ከተሰነበተ በሁዋላ አንድ ሌሊት ገልዓሎ አካባቢ ከአንድ ገበሬ ጎጆ ፍየል አሳርደው ራት በመመገብ ላይ ሳሉ በኢጣልያ የኮማንዶ ቡድን ተከበቡ። እጃቸውን እንዲሰጡ ሲጠየቁ ግን ፈቃደኛ ባለመሆን መተኮስ ጀመሩ። በተኩስ ልውውጡ ሶስት ኢጣልያውያን ሲቆስሉ ከሸፍቶቹ አራት ተገድለው ሶስት አመለጡ። የተማረከ ወይም ቆስሎ በህይወት የተረፈ ባለመገኘቱ ማንነታቸውን ለማወቅ አስቸጋሪ ሆነ። የሞቱትን አስከሬን በማየት ማንነታቸውን መለየት የቻለ አልተገኘም። የተገደሉት ሸፍቶች ባንድ በኩል የሰምሃር ሰዎች ስለመሆናቸው ቢነገርም፤ በሌላ በኩል ከከሓባብ ስለመምጣታቸው ተወሳ። ርግጡ ግን ሳይታወቅ ቀረ።

መርየም ኑረነቢን ፍለጋ ቀጠለች . . .

የምጽዋን የህይወት ዘይቤ በመጥላት ርቆ ወደ ከበሳ ሄዶ ሊሆን እንደሚችል ወደ ማመኑ አዘነበለች። እናም ለጉዞ የሚሆን ስንቅ ስታዘጋጅ ሰነባብታ የሰለሙና ክረምት ሊገባ አካባቢ ጉዞዋን ለመቀጠል ተነሳች። ቀናውን መንገድ እንዲመራትም አላህን አጥብቃ ተማጸነች።

ምእራፍ ፭

የኡምኩሉህላዌ
በዘመነ ክህደት – በዘመነ አርዌ

በሰምሃር ክፍለሃገር፣ ምጽዋ አቅራቢያ ኡምኩሉ የሚባል አንድ የገጠር መንደር አለ። በ19ኛው ክፍለዘመን መግቢያ በአንድ ደረቅ ወንዝ ዳርቻ በተገነባ ግቢ ውስጥ ኗሪ የነበሩ ጥቂት ሚስዮናውያን ለኡምኩሉ መንደር ማስታወሻ ለመትከል በቅተዋል። ማለትም ማተሚያ ቤት ጭምር በነበረው በዚህ የሚስዮናውያን ካምፕ ምክንያት ኡምኩሉ በመጻህፍት በተደጋጋሚ ስሟ ሊጠቀስ ችሏል። የኡምኩሉ ማተሚያ ቤት በላቲን ብቻ ሳይሆን በግእዝ ፊደል ጭምር መጽሃፍ ማተም የጀመረው ከ1885 ጀምሮ ሲሆን፤ ቀደም ብሎ ከሃያ አመታት በፊት ግን ቢያንኬሪ የተባለ ካቶሊክ ሚስዮናዊ ምጽዋ ላይ በግእዝ የሚያትም ማተሚያ ቤት ከፍቶ ነበር።

በወርሃ ግንቦት 1889 የኑረነቢ ልጆች ኡምኩሉ ሲደርሱ፤ ካምፑ በወንጌላውያን (Evangelical) እጅ የነበረ ቢሆንም፤ የኡምኩሉን ካምፕ ቀድመው በ1800 የቆረቆሩት Jacobi's ተብለው የሚታወቁ ላዛሪስት ካቶሊኮች ነበሩ። አባ ዮሃንስ ሁለቱን የሓልሓል ቦጎስ ልጆች ለስዊድን ቄሶች በአደራ ባስረከበበት እለት፤ የምሳና የቡና ግብዣ ጥያቄ ቀረበለት። በሚቀጥለው ቀን ወደ ፈረንሳይ ለመጓዝ ጓዙን በማሰናዳት ላይ የነበረ ቢሆንም ግብዣውን ተቀበለ።

በምሳ ወቅት በምግብ ጠረጴዛው ዙሪያ ጥቂት የወንጌላውያን ቄሶች ተገኙ። ከስዊድናውያን ሮዛ ማንሰን እና ኢሚሊ ሉንዳል፤ ከአፍሪቃውያን አነሲሞስ ነሲብ፣ ሃይለሚካኤል ኪዳኑ፣

ገብረጊዮርጊስ ባርያው፣ አለቃ ታዬ ገብረማርያም እና ቄስ ዘርአጽዮን ሙሴ ተገኝተው ነበር።

ምሳው አብቅቶ የቡና ስነስርአት ሲጀመር የአካባቢውን ጂአ ፖለቲካዊ ሁኔታና ስለ ሚስዮናውያኑ ተልእኮ ተጨዋወቱ። በተለይም አጤ ዮሃንስ መተማ ላይ በማህዲስቶች መገደሉ ለኢጣልያ ጥሩ አጋጣሚ እንደሆነላት ተነጋገሩ። አሉላ ዶጋሊ ላይ በፈጸመው ድርጊት ምክንያት ጣሊያን ይበልጥ ከሸዋው ምኒልክ ጋር ግንኙነት መፍጠር እንደምትፈልግ አነሱ። አሉላ ራስ መንገሻን ከፊት አስቀድሞ ለመቋቋም የሚያደርገው ሙከራ ላይ "ይሳካለታል - አይሳካለትም" የሚል ሙግት ቢጤ አካሄዱ። የድርቁ ችግር አሳሳቢ መሆኑ ላይ ደ'ሞ ይበልጥ አጽንኦት ሰጡ።

የሉንዳል መሞት የኡምኩሉን ሚስዮን ምን ያህል እንደጎዳው የውይይታቸውን ሰፊ ክፍል ያዘ። ባለፉት አምስት አመታት የኦሮሞ ልጆች ከእረኝነት ቦታቸው ላይ እየታፈኑ ወደ ምጽዋ ለሽያጭ መምጣታቸው እየቀነሰ ቢሆንም ገና አለመቆሙ፤ የአረብ ነጋዴዎች የተሰረቁ ልጆችን በጀልባ ወደ አረቢያ እንደሚያሻግሩ፤ ይህንን ለማስቆምና ባሮቹን ነጻ ለማውጣት የሚያደርጉት ጥረት በኢጣልያ እየታገዘ ስለሆነ ተስፋ ሰጪ እንደሆነ ተናገሩ። በእግረመንገድ ወደሁዋላ መለስ ብለው ዋርነር ሙንዚንገርን በበጎ ማስታወሳቸው አልቀረም።

የቡና ላይ ጨዋታቸው ሰፊ ነበር ...

አባ ዮሃንስ ከከረን የመጣ እንደመሆኑ አዲስ መረጃዎችን ለስዊድናውያኑ ሰጠ። ይህም መረጃ "ባላምባራስ ካፍል ጎፋር ለኢጣልያ አልገዛም ብሎ አፈንግጧል" የሚል ነበር። ካፍል ጎፋር ከረንን ከያዘ በሁዋላ መሳሪያ ያስታጠቁትን ኢጣልያውያን "አፍንጫችሁን ላሱ" ስለማለቱ ሲወራ መሰንበቱን ገልጾ ሲያበቃ፤ ይህን ተከትሎም ከሁለት ቀናት በፊት ባላምባራስ ካፍል ተደምስሶ ከረን እንድትያዝ ጄኔራል አንቶኒዮ ባልዲሴራ ማዘዙን ጠቆመ። በትእዛዙ መሰረትም የኢጣልያ ሰራዊት ወደ ከረን እየተጠጋ እንደሆነ መስማቱን አባ ዮሃንስ ተናገረ። የኢጣልያ ቅኝ ገዢ ከረንን መያዝ ከቻለ ወደ አስመራ ለመቀጠል አንዳች የሚያግደው ሃይል እንደማይኖር አባ ዮሃንስ የተናገረው ርግጠኛ ሆኖ ነበር። እግረ

መንገዱንም የባህታ ሓጎስን ስም ሳያነሳ አላለፈም። ኢጣልያውያን ከባህታ መስማማታቸው ከበሳውን ብቻ ሳይሆን ቆላውን ጭምር ለመቆጣጠር እንደሚያስችላቸው አስተያየቱን ሰጠ። ባህታ ሓጎስ ምጽዋ በሰነበተ ሰሞን አግኝቶት እንደነበር ጠቅሶ ሲያበቃ፤ በኢጣልያ ሞግዚትነት አከለጉዛይን ማስተዳደር እንደሚፈልግ እንደገለጸለት ተናገረ።

የቡና ላይ ጨዋታቸው ሰፊ ነበር ...

ስዊድናውያኑ ይበልጥ ትኩረታቸው በኦሮሞ ጉዳይ ላይ እንደመሆኑ፤ ልባቸውና ቀልባቸው ከመረብ ወንዝ ባሻገር ነበር። ጉስታፍ አርሃኒዩስ የሚመራው ቡድን ከስምንት አመታት በፊት በሱዳን በኩል ወደ ኦሮሞ ምድር ለመግባት ሞክሮ ሳይሳካ በመቅረቱ የደረሰውን ጉዳት ለአባ ዮሃንስ ተረኩ።

ረጅሙን ታሪክ በአጭሩ ሲተርኩለት በተመስጦ አዳመጠ...

...ለጉዞ ሲነሱ በቡድኑ ውስጥ አነሲሞስና ሃይሉ ከነሚስቶቻቸው ነበሩበት። ጋብቻ ከፈጸሙም ገና አራት ቀናቸው ብቻ ነበር። በተጨማሪ ፊሊጶስና ፓልማን የተባሉ ስዊድናውያን የቡድኑ ባልደረቦች ነበሩ። በቅድሚያ ከኡምኩሉ ተነስተው ወደ ሰሜን በመጓዝ ሱአኪን ገቡ። ከሱአኪን ግመል ተከራይተው ለአስራሁለት ቀናት በኑቢያ በረሃ ላይ ተጓዙ። በርበር እንደደረሱ ትንሽ ጀልባ ተከራይተው በሰማያዊ ናይል ላይ ቀዘፉ። ከአንድ ሳምንት የጀልባ ጉዞ በሁዋላ ካርቱም ገቡ። የጀልባ ጉዟቸውን በመቀጠል ፋምካ ሲደርሱ የኦሮሞ ምድር ተራሮችን በርቀት በማየታቸው ከፍተኛ ደስታ ሆነ።

እንዳሰቡት ግን በቀላሉ ወደ ኦሮሞ መሬት ማለፍ አልቻሉም። የቤኒሻንጉል ሼክ ወደ ኦሮሞ መሬት ለማለፍ እንደማይፈቅድላቸው በመግለጽ በመጡበት ጀልባቸው፣ በመጡበት እግራቸው ወደ ፋምካ እንዲመለሱ አዘዛቸው። ዳቡስ ወንዝ ለመድረስ የቀራቸው ስድሳ ኪሎሜትር ብቻ ነበር። ዳቡስ ወንዝን ቢሻገሩ ኦሮሞ ምድር ገቡ ማለት ነበር። በርግጥ በዚያን ጊዜ አካባቢው ሰላም አልነበረውም። ኦሮሞዎች ከግብጽና ከአቢሲንያ ገዢዎች ጋር ውጊያ ላይ ነበሩ። በአቢሲንያ በኩል ጦር የመዘዘባቸውን ንጉስ ተክለሃይማኖት እየተከላከሉ፤ በሌላ በኩል

ከባድ ግብር ከጫነባቸው የግብጽ ገዢ ላይ አምጸው ነበር።

ኦነሲሞስና ቡድኑ ወደ ኦሮሚያ መግባት እንደማይችሉ ከተነገራቸው በሁዋላ በመጡበት መንገድ ወደ ካርቱም ተመለሱ። ወደ ካርቱም በጀልባ እየተመለሱ ሳለ ጀልባው ላይ ፊሊጶስ ሞተ። ከወንዙ ዳርቻ ቀብረውት ጉዟቸውን ቀጠሉ። ካርቱም ከደረሱ በሁዋላ አሳባቸው እንደገና በመተማ በኩል ወደ ኦሮሞ ምድር ለመግባት ነበር። አብዛኞቹ የቡድኑ አባላት ታመውና ደክመው የነበረ ቢሆንም ጉዟቸውን ለመቀጠል ፍላጎት ነበራቸው። ሃይሉና ባለቤቱ ስለታመሙ ወደ ኡምኩሉ ለመመለስ ወሰኑ። ሆኖም ወደ ኡምኩሉ ለመሄድ ከፓልማን ጋር መንገድ ከጀመሩ በሁዋላ አሳባቸውን ለውጠው የግል ኑሯቸውን ለመኖር ከቡድኑ ተለዩ።

በመቀጠል ኦነሲሞስ ታመመ። አርሃኒዩስና ምህረት ግን ጤንነታቸው ደህና ነበር። ኦነሲሞስ እስኪሻለው መጠበቅ ነበረባቸው። ኦነሲሞስ ሲሻለው አርሃኒዩስ ደ'ሞ ታመመ። እንዲያገግም ጥረት ቢያደርጉም አልተቻለም።

አርሃኒዩስን ከቀበሩ በሁዋላ ኦነሲሞስና ምህረት ወደ ኡምኩሉ ለመመለስ ወሰኑ። በጉዞ ወቅት በኑቢያ በረሃ ላይ ኦነሲሞስ እንደገና ታሞ ነበር። ቢሆንም በከባድ ችግር ውስጥ ተጉዘው በሁለተኛው ወር ኡምኩሉ ደረሱ።

በዚህ መልኩ ወደ ኦሮሞ ምድር ለመግባት የታሰበው ሁለተኛው ሙከራ ከከሸፈ በሁዋላ ለሶስተኛ ጊዜ በምኒልክ ግዛት በኩል ወደ ጅማ ለመግባት ሙከራ ተደርጎ እሱም ሳይሳካ ቀረ።

አባ ዮሃንስ ሚስዮናውያኑ በደረሰባቸው እንግልትና መስዋእትነት በእጅጉ በመደነቁ ሶስተኛው ሙከራ ለምን እንደከሸፈ ለማወቅ ጓጉቶ ጠየቀ። በተለይ ስለ ንጉስ ምኒልክ ግዛት ይበልጥ መረጃ ለማግኘት ፈለገ።

ኦነሲሞስ የሶስተኛውም ያልተሳካ ጉዞ ባልደረባ ስለነበር ትእዝብትና ገጠመኞቹን ባጭሩ አብራራ፣

በ1884 በንጉስ ምኒልክ ግዛት በሸዋ በኩል ወደ ጅማ ለመግባት ፈቃድ ሲጠይቁ ንጉስ ምኒልክ ፈቃደኛነታቸውን ያሳወቁት ወዲያውኑ ነበር። በፓልማን እና የህክምና ባለሙያ በሆነው

በበርግማን መሪነት አነሲሞስና ባለቤቱ እንዲሁም ሌሎች ሁለት አሮሞዎች የተካተቱበት ቡድን ፈጥኖ ታጁራ ወደብ ደረሰ።

የምኒልክን ንብረት ከወደብ ሊያነሱ ከመጡ መልእክተኞች ጋር ጉዟቸውን ጀምረው ሸዋ ሲደርሱ ግን ምኒልክ አሳባቸውን ለውጠው ጠበቋቸው። ምኒልክ የመሻገሪያ ፈቃድ የላኩት አውሮፓውያኑ የቴክኒክ ባለሙያዎች መስለዋቸው ነበር። ሚስዮናውያን መሆናቸውን ሲረዱ በመጡበት መንገድ እንዲመለሱ አዘዟቸው። ከቡድኑ አባላት መካከል ጥቂቶች ታመው ስለነበር ግን ሁዋላ አስተያየት በማድረግ አልዩ አምባ እንዲቆዩ ፈቀዱ። የአልዩ አምባ አካባቢ ህዝብ አሮምኛ ተናጋሪ ስለነበር ለአነሲሞስ ምቹ ሆነለት። አነሲሞስ ወንጌል ሲሰብክ፤ በርግማን ደ'ሞ ህዝቡን በህክምና ማገልገል ጀመረ።

ከዘጠኝ ወራት ቆይታ በሁዋላ በአልዩ አምባ የነበሩ ካቶሊኮችም ሆኑ ኢቫንጀሊካል ሚስዮናውያን አቢሲንያን ለቀው ወደ መጡበት እንዲመለሱ በጥብቅ ተነገራቸው።

አነሲሞስ በተነካ መንፈስ ሁኔታውን እንዲህ ሲል አወጋ፣

"በምልሰት በመንገዳችን ላይ 700 የሚሆኑ ባሮች እንደ እንስሳ እየተነዱ ለሽያጭ ሲሄዱ ገጠመን። በብዛት እናቶችና ልጆች ነበሩ። ከልጆቹ ሴቶች ይበዛሉ። እድሜያቸው ከ8 እስከ 12 አመት ቢሆን ነው። በመንገድ ላይ በአለንጋ እየተመቱ ነበር የሚነዱት። ስቃይ ይደርስባቸው ነበር። እያየን ከመቆጨት በቀር ስቃያቸውን ልንቀንስላቸው ወይም ነጻ ልናወጣቸው አቅሙ አልነበረንም። ከ14 አመታት በፊት እኔም በዚሁ መንገድ እንዲሁ እንደ እንስሳ እየተነዳሁ ወደ ምጽዋ ተወስጄ ተሸጬ ነበር። በኢጋጣሚ ግን ነጻ ወጥቼ፤ ተምሬ፣ አውቄ የወንጌል መምህር ለመሆን በቅቻለሁ። ተመልሼ እናቴን፣ ወንድምና እህቶቼን ማግኘት ባልችልም፤ ቤተሰብ መስርቼ እየኖርኩ ነው። እነዚያ ከፊታችን በአሰቃቂ ሁኔታ እየተነዱ የሚጓዙት ወገኖቼ ከቤተሰባቸውና ካገራቸው ተፈናቅለው፤ እንደ እንስሳ እየተነዱ ሲወሰዱ እያየሁ ምንም ማድረግ አለመቻሌ እጅግ አሳዘነኝ። ከ14 አመታት በሁዋላም በተመሳሳይ የባርያ ሽያጩ ቀጥሏል። ቀደም ሲል ከነበረው የተሻሻለ ነገር አልነበረም።"

አነሲሞስ ፋታ ወሰደና ቀጠለ፣

“ፖለቲካውና የሃይማኖት ተቋሙ አቢስንያ ላይ እየተደጋገፉ እንደሚሄዱ ተረድተን ነበር። ምኒልክ የሚስዮናውያኑን መግባት የሚቃወሙበት ምክንያት ግልጽ ነበር። ዋናው ጉዳይ ንጉሱ ከባርያ ሽያጩ ከፍተኛ ገቢ የሚያገኙ መሆናቸው ነው። ህጻናት ከወላጆቻቸው ወደሚነጠቁበት አገር ሚስዮናውያን ከገቡ የባርያ ንግዳቸው እንቅፋት እንዳይገጥመው ፈርተዋል። ሚስዮናውያኑ ያዩትን ለአለም በመንገር እንዳያጋልጧቸው ይሰጉ ነበር። ንጉስ ምኒልክ በአውሮፓውያን ፊት መስለው እንደሚታዩት አልነበሩም። በወቅቱ የባርያ ንግድን የሚከለክል ህግ ቢያውጁም፤ አዋጁ ግን በአውሮፓውያን ፊት ምስላቸውን ለማስተካከል ያደረጉት እንጂ ዋና የገቢ ምንጫቸው የባርያ ንግድ ነበር። ከወርቅ እና ከዝሆን ጥርስ ሽያጭ የሚያገኙት ገቢ ከባርያ ንግድ ቀጥሎ የሚሰለፍ ነበር። በአመለካከት ደረጃም ከእነርሱ ባሻገር ሌላው ህዝብ ሊሸጥና ሊለወጥ የሚገባው ነው ብለው የሚያምኑ ነበሩ። በአልዩ አምባ ቆይታችን እንደተረዳነው ታክስ ከፋዮች በየአመቱ ወርቅ እና ባርያ ለምኒልክ ይገብራሉ። ምኒልክ በጦርነት የሚማርኳቸውንም በቀጥታ የግላቸው ባሮች ያደርጓቸዋል። ምኒልክና ጣይቱ በጥቅሉ 17 ሺህ ባርያዎች እንዳላቸው ሰምተን ነበር። ምኒልክ ሴት ልጃቸውን ለአጤ ዮሃንስ ወንድ ልጅ ሲድሩ አምስት ሺህ ወንዶችና ሴቶች ባሮች በስጦታ አሳልፈው እንደሰጧት ሰምተናል። ሁለቱ ሙሽሮች ለራሳቸው ጥቂት አስቀርተው በስጦታ ያገኙትን ባርያ አብዛኛውን ሸጠውታል። አቢሲንያ ዋና የገቢ ምንጯ የባርያ ሽያጭ ነው። በመሆኑም ምኒልክ ከባርያ ነጋዴዎች ጋር የመሰረቱትን የባርያ ንግድ ግንኙነት ለማቆም ይቸገራሉ። ከአረብ አገር የሚመጡት ባርያ ነጋዴዎች ለምኒልክ ጠመንጃ እያመጡ ስለሚሸጡ፤ የባርያ ንግዱ ከቆመ ጠመንጃ የማግኘት እድላቸው ስለሚቀንስ ይህ እንዲሆን አይፈልጉም። እንግዲህ ሶስተኛው ጉዟችን ያልተሳካው በዚህ ምክንያት ነበር።”

አነሲሞስ በተረጋጋ ገጽታው ላይ ዘወትር የማትጠፋ ፈገግታውን ብልጭ አድርጎ ሲያበቃ እንዲህ አለ፣

“እኛ ወደ አሮሞ ምድር መግባት ባንችል መጽሃፍ ቅዱስ ቀድሞን ወደ አሮሞ ምድር እንዲገባ ለትርጉም ስራ ሰፊ ጊዜ ሰጥተን እየሰራን ነው። የአሮምኛ የትርጉም ስራው አልቆ ከታተመ በሁዋላ

እንደገና በሌላ መንገድም ቢሆን ወደ ኦሮሞ ምድር ለመግባት ጥረታችን ይቀጥላል።"

በዚህ መልኩ እየተወያዩ የቡና ስነስርአቱ ካበቃ በሁዋላ አባ ዮሃንስ የተደረገለትን አቀባበል አድንቆ፣ የምስጋና ጸሎት አድርጎ ለመሄድ ተነሳ። ቢበዛ በአራት ወራት ጊዜ ውስጥ ተመልሶ እንደሚመጣ በማሳሰብ እድሪስና አደም በጥሩ ሁኔታ ተመግበው ለመንገድ ዝግጁ ሆነው እንዲጠብቁት ጠየቀ። ጊዜው አጭር ቢሆንም ባለው ጊዜ ውስጥ የግእዝና የላቲን ፊደሎችን ቢማሩ፣ ቁጥሮችን ቢለዩ መልካም መሆኑን አከለበት። ስዊድናውያኑም የልጆቹን ጉዳይ እንዲከታተል እዚያው አባ ዮሃንስ ፊት ሃላፊነቱን ለቄስ አነሲሞስ ነሲብ ሰጡት።

* * *

የክርስትያኖች ቅዱስ መጽሃፍ በትምህርት መልክ ይሰጥበት በነበረው በኡምኩሉ ካምፕ በታሪክ ውስጥ ሲታወሱ የሚኖሩ ጥቂት ሰዎች አሻራቸውን በመጽሃፍ መልክ ትተው አልፈዋል። በርግጥም ኡምኩሉ ስሟ ሲነሳ አብሮ ስማቸው ይነሳል። ይበልጥ ግን ከኡምኩሉ ጋር ጥብቅ ቁርኝት የነበራቸው የስዊድን ሚስዮናውያን ነበሩ። ሉንዳል ዋናው ነው። እዚያው ኡምኩሉ ተቀብሮ ነበር። ጉስታፍ አረን እና ካርል ሉንደስተሮም እንዲሁ የሚጠቀሱ ናቸው። ቄስ ዘርአጽዮን ሙሴ ከኡምኩሉ አሻራዎች መካከል ነው። የወቅቱ የጎንደር ሊቅ የነበረው ጸሃፊና ተርጓሚ አለቃ ታየ ገብረማርያምም ከኡምኩሉ መምህራንና ተርጓሚዎች አንዱ ነበር። የኑረነቢ ልጆች በአደራና በጊዜያዊነት ኡምኩሉ ገብተው አእምሯቸውን ለትምህርት ሲያዘጋጁ በጊዜው መለኪያ በካምፑ ውስጥ እጅግ አዋቂ የተባሉ ሰዎች ይኖሩ ነበር።

ቀደም ብሎ ጀምሮ ኡምኩሉ ብዙ ወዳጆች ነበሯት። አውሮፓውያን ገለል ብለው መጨዋወት ሲሹ ኡምኩሉ ተመራጭ ቦታቸው ነበረች። በወቅቱ በምጽዋ የስዊስ ቆንሱላ የነበረው ሙንዚንገር ከኡምኩሉ ቤተኞች ዋናው ነበር። በ1876 በግብጽ ሰራዊት ታጅቦ በአውሳ በኩል ወደ አቢሲንያ ሲገባ እስከተገደለበት ጊዜ ድረስ ሙንዚንገር የሚስዮናውያኑን ተልእኮ አግዟል።

በአቢሲንያ ባርያ ፈንጋዮች እየተያዙ፤ በአረቦች በኩል ለሽያጭ ምጽዋ የሚመጡትን ልጆች ነጻ በማውጣት ዝነኛ ስም አትርፎ ነበር።

በባርያ ጉዳይ ላይ ሙንዚንገር ቁርጥ አቋም ነበረው።

በቅድሚያ ዋጋ ተከራክሮ ባሮቹን እየገዛ ለማስለቀቅ ይሞክራል። በግዢ ካልተስማማ ትቶ አይሄድም። እየተታኮሰ ጭምር ባሮችን ከሻጮቻቸው እጅ ፈልቅቆ ይወስዳል። ሁዋላ የኦሮምኛን መጽሃፍ ቅዱስ ለመተርጎም የበቃው አነሲሞስ በሙንዚንገር ነጻ ከወጡ ልጆች አንዱ ነው። "አነሲሞስ" ከመባሉ በፊት ወላጆቹ የሰጡት ስም ሂካ (Hiika Awaaji) የሚል ሲሆን፤ ሙንዚንገር ሂካን ያገኘው ለዘጠነኛ ጊዜ ሽያጭ ምጽዋ ገበያ ላይ በቀረበ ጊዜ ነበር።

የ21ኛው ክፍለ ዘመን ሰው የጉስታቭ አረን እና በእዝራ ገብረመድህን አርታኢነት የታተመውን የሉንድስትሮምን መጽሃፍ አንብቦ ወደ ኡምኩሉ ለጉብኝት ቢሄድ በአእምሮው የሳለውን አያገኝም። በስእልና በፎቶግራፍ የተመለከተውን ባለ አንድ ታዛ ጌጠኛ ህንጻ በቦታው አለማግኘት ለጊዜው ቅር ቢያሰኝም በታሪክ ውስጥ ምንም ማለት አይደለም። ወደ ምጽዋ የሚያልፍ መንገደኛ በመንገዱ ዳር የቆመውን አጽመ - ግድግዳ ሲመለከት በአሳብ ወደ ሁዋላ መለስ ማለቱ ግን የማይቀር ነው። ካምፑ ከነበረበት ቦታ ላይ የሚቆም እንግዳ፣ "መጻህፍትን በግእዝ ያትም የነበረው ማሽን የተተከለው የት ነበር?" ብሎ ቢጠይቅ መልስ አያገኝም። በርግጥ የሉንዳል መቃብር ምልክቱ አለ። የማን መሆናቸው የማይታወቅ በርካታ መቃብሮችም ይታያሉ። ሜዳው ላይ ቅጠላቅጠል በቅሎበት የፍየሎች መሰማሪያ ሆኗል። ቢቆፈር የማን መሆናቸው የማይታወቅ አጥንቶች ይገኙ ይሆናል። የስዊድናውያኑን አጥንት ከሌሎች መለየት ግን አይቻልም። የሰው ልጅ በቀለም የሚለየው በህይወት ሳለ ነው። አጥንቶች ሁሉ ነጫጭ ናቸው። ጥቁር ወይ ቢጫ አጥንት የለም።

ታሪክ ለመንገር ቆሞ ከቀረው ግድግዳ ባሻገር በፍርስራሹ ላይ የቆሙት ሁለት ሃውልቶች ካቶሊክ ያዕቆባውያንና ወንጌላውያን ከመቼ እስከ መቼ በዚያ ስፍራ እንደነበሩ ይጠቁማሉ። "Beato Giustino De Jacobis 1800 - 60" ሌላው ሃውልት ደ'ሞ "Evangelical Mission Umkulu 1875" የሚል ጽሁፍ

በግእዝ ጭምር ሰፍሮበታል።

ካቶሊካውያን እና ወንጌላውያን በኡምኩሉ የገነቧቸው ህንጻዎች ምንም እንኳ ከምድረገጽ የጠፉ ቢሆንም፤ ለምልክት ያህል ከቆመው ግድግዳ ዙሪያ ከሁለት መቶ አመታት በላይ እድሜ ያላቸው የተሰባበሩ ጡቦች ሜዳው ላይ ፈሰው ይታያሉ። ትክ ብሎ ለሚያየቸው የተበታተኑ የታሪክ ፊደሎች ወይም የተገነጣጠሉ የመጽሃፍ ገጾች፤ አሊያም ብጭቅጫቂ ወረቀቶች መስለው ይታዩታል። ግን አይደሉም። ስብርባሪ ጡቦች ብቻ ናቸው።

የኑረነቢ ልጆች ኡምኩሉ ሲገቡ ፍርሃትና ጭንቀት ሰፍሮባቸው ነበር። እንደ በረዳቸው ፍየሎች የግንብ ጥግ እየፈለጉ መቀመጣቸውን ለማስተው ጥቂት ድካም ነበረበት። ርግጥ ነው፤ “ለመሆኑ ማናችሁ?” ተብለው ቢጠየቁ፣ “እኛማ የኑረነቢ ልጆች ነን” ብለው በኩራት ሊናገሩ ከሚችሉበት ነባር የህይወት ዘይቤ ወጥተው የካምፕ ልጆች ሆነዋል።

በኡምኩሉ ግቢ በቅድሚያ የተገለጸላቸው፣ “ኡምኩሉ” የሚለው የአረብኛ ቃል “የሁሉም እናት” ማለት መሆኑን ሲሆን፤ “የሁሉም እናት” ካምፕ ባልደረባ ለመሆን ቢበቁም በሰምሃር ወበቅ ውስጥ እየኖሩ መንፈሳቸው በባዶነት ብርድ መሸንቆጡ አልቀረም። በርግጥ “የሁሉም እናት” ግቢ ውስጥ ምግብና መጠለያ ማግኘታቸው ተስፋ ነበር። የጊዜው ብቸኛ ጥያቄም ምግብ እንደመሆኑ በቀን ሶስት ጊዜ መመገብ ችለው ነበር። አልፎ አልፎ የቀይ ባሕር አሳ፤ ብዙውን ጊዜ ደግሞ የህንድ ሩዝ ገበታቸው ላይ ያገኛሉ። በመሆኑም በኑረነቢ ልጆች የልጅነት ህይወት ላይ የተከሰተው የረሃብ ገጠመኝ ትቶት ያለፈው ጠባሳ ከባድ ቢሆንም፤ ሰው ናቸውና እየገሰገሰ ከፊታቸው የሚመጣውን መጪ ዘመን መመልከታቸው አልቀረም።

የኡምኩሉ ቄሶች ማንኛውንም ስራ ተከፋፍለው ይሰራሉ። በየተራ ስደተኞችን ማገዝ እለታዊና መንፈሳዊ ተግባራቸው ነበር። ድርጊቱ ህይወታቸውን እየነጠቃቸው እንኳ አላፈገፈጉም። የካምፑ አለቃ ስዊድናዊው ሉንድሃል በ45 አመት እድሜው ህይወቱን ያጣው በፈንጣጣ በሽታ ምክንያት ነበር። በመደጋገፍና በቅን ልቡና፣ በማገዝ መንፈስ ስራቸውን ይሰራሉ። ከፊሉ ቁርስ ሲያድል፤ ሌላው ሞተው ያደሩትን ይቀብራል። የታመሙትን እየለየ ህክምና የሚሰጥ

ደ'ሞ አለ። የትሮፒካል በሽታዎች በስደተኞቹ ላይ ከነጓዙ ሰፍሯል። ኮሌራ፣ ፈንጣጣ እና ታይፈስ የተለመዱ በሽታዎች ነበሩ። በቆዳ በሽታ የሚሰቃዩ ይበዛሉ።

ኦነሲሞስ የአደራ ልጆቹን በህይወት አቆይቶ ለአባ ዮሃንስ መልሶ ለማስረከብ ብርቱ ጥንቃቄ አደረገ። የኑረነቢ ልጆች ግንብ ስር እንደ ጥንቸል ተጠጋጋግተው ከመቀመጥ ፍርሃት ተላቀው ግቢውን ከለመዱት በሁዋላ ደጃፉ ላይ የፈሰሱትን ስደተኞች ለመርዳት ፍላጎት አደረባቸው። የኦነሲሞስን ክልከላ እየጣሱ በተለይ ቁርስ በማደሉ ስራ ይሳተፋሉ። ኦነሲሞስ ሊያስቆማቸው አልቻለም።

ከስደተኞቹ ደህና አቅም ያላቸው ለመቃብር የሚሆን ጉድጓድ የመቆፈር ስራ ይሰራሉ። አቅም የሌላቸው ጭምር በስራ ለማገዝ ፍላጎት ያሳያሉ። ግን አይችሉም። ዶማውን ማንሳት እንኳ እያቃታቸው በአፍጢማቸው ይደፋሉ። ወርቅ ይዘው እህል ለመግዛት ወደ ምጽዋ የሚመጡ ነበሩ። የኢጣልያ ቅኝ ገዢዎች ከህንድ እየገዙ ለሽያጭ ከሚያቀርቡት የእህል ገበያ ከመድረሳቸው በፊት ግን ብዙዎቹ በረሃብና በበሽታ አለቁ። በመሆኑም አንድ ሰው ሲሞት ከመቀበሩ በፊት ፍተሻ ይደረጋል። በኩታቸው የተቋጠረ ወርቅና ገንዘብ ማግኘት የተለመደ ነበር።

ስደተኞች ወደ ምጽዋ በሚያደርጉት ጉዞ ብዙ ፈተናዎች ይገጥማቸው ነበር። ጅቦችና ነብሮች ዋና ፈተና ነበሩ። በእነዚህ አውሬዎች ላለመጠቃት ሌሊት መጓዙን የሚደፍር አልነበረም። ነብሮችና ጅቦች ግን ሌሊት ሰው ሲያጡ ቀን እየወጡ ማደን ጀመሩ። ከአውሬዎች ባሻገር ዘራፊዎችም በየጉድባው አድፍጠው ይጠብቃሉ። ጥራጥሬ ለመቀማት ሲሉ ሰው ይገድላሉ። ከአውሬዎች እና ከዘራፊዎች አምልጠው ምጽዋ የሚደርሱ ባብዛኛው በምግብ እጥረት የተጎዱ እንደመሆናቸው፤ እድለኞች በጥቂት እርዳታ አገግመው ስራ ለመስራት ይዘጋጃሉ። ወደ ምጽዋ ከተማ ዘልቀው በመግባት የአናጢና የግንበኛ ረዳትነት ስራ አያጡም።

አንድ ማለዳ ቄስ ኦነሲሞስና ቄስ ዘርአጽዮን ሙሴ እንደተለመደው ቁርስ በማደል ስራ ላይ ነበሩ። የኑረነቢ ልጅ አድም በስራው ብዙ ባያግዝም ዘወትር ማለዳ እንደሚያደርገው ሁለቱን ቄሶች ተከትሎ ሱክ ሱክ ይላል። ቂጣና ውሃ በማደል ላይ ሳሉ

ታፋዋን ጅብ የነከሳት ሴት አገኙ።

እያቃሰተች ታሪኳን ነገረቻቸው...

ወደ ኡምኩሉ በመጓዝ ላይ ሳሉ ደክሟት የአንድ አመት ልጇን እንዳቀፈች አረፍ ብላ ነበር። በጠራራ የማለዳ ጸሃይ ሁለት ጅቦች መጡባት። አንዱ ከመቅጽበት ልጇን ከእጇ ነጥቆ ጎረሰውና ሮጠ። ልጇን ለማስጣል ስትከተል ሌላው ጅብ ታፋዋ ላይ በጥርሶቹ ያዛት። ድንጋይ አንስታ ጭንቅላቱን ስትመታው ለቋት ሸሸ።

ዘርአጽዮን ሙሴ እንባዋን በማፍሰስ ላይ ላለችው ሴት ቂጣና ውሃ ከሰጣት በሁዋላ ህክምና እንድታገኝ ወደ ግቢው እንድትሄድ ነገራት። አመስግና ከተጋደመችበት ተነሳች።

እንዲህ ያለ ገጠመኝ እየሰሙ ቁርስ ማደላቸውን ሲቀጥሉ ግራር ስር ከተኛ አንድ ጎልማሳ ሰው ዘንድ ደረሱ። ሰውየው ጎልማሳ ቢሆንም ያረጀ ይመስላል። ታሞ ነበር። በከባዱ ይስላል። ህይወት ያለው አይመስልም። ከስቶና ጠውልጎ ስንጥር አክሏል። ቂጣና ውሃ ለመቀበል ቀና ሲል ከአድም ጋር አይን ለአይን ተጋጩ። ሰውየው እንደ እብድ በድንገት ጮኸ!

“አድም ልጄ!”

አድም አላወቀውም። ሓርቤ መሆኑን ሲነግረው ግን ማመን ተቸገረ። ተቃቅፈው ተሳሳሙ። ሁለቱ የሓልሓል ሰዎች በሰቀቀን ተሳስመው ሲያበቁ ሓርቤ ጥያቄ ደረደረ፣

“ወንድምህ እድሪስ የታለ? ዛህራ የት ናት? አባታችሁስ?”

አድም የሚያውቀውን ያህል ስለ እናትና አባቱ ተናገረ። አድም የእናቱን መሞት ሲናገር እንባ እየተናነቀው ነበር። ሓርቤ በኩታው ጫፍ አይኑን አባበሰ። አይኖቹን እያባባሰ እሱም ሚስትና ሁለት ልጆቹን ቀብሮ ብቻውን መቅረቱን ለአድም አጫወተው። አድም እንደ ጥንቸል ጆሮውን አቁሞ ከማዳመጥ በቀር የሚናገረው ጠፋው። ሓርቤ ግን መጠየቁን አላቋረጠም፣

“ኑረነቢ መሸፈቱን ሰምተን ነበር። እውነት አይደለም?”

አድም በድንጋጤ ኩምትር አለ፣

“አልሰማንም። ስራ አጊኝቶ ከሄደ በሁዋላ ስለ አባታችንም ሆነ ስለ አክስታችን ምንም ወሬ የለንም።”

“ከሼኽ ሳልሕ ጋር ምራራ መታየታቸውን ሰምተን ነበር።”

“ማነው ሼኽ ሳልሕ?”

“ሼኽ ሳልሕ አሕመድ! የመንሳዕ ሰው ነው። ከሸፈተ ቆየ።”

“መቼ ሰማህ ይህን?”

“ቆየ። ከረን ነበርኩ። ዋናው ነገር እናንተን እንኳን አላህ አተረፋችሁ። እኔ ልጆቼን ቀበርኩ። ሚስቴን ቀበርኩ። እነሱ ተርፈው እኔ ብሞት ይሻለኝ ነበር። አላህ በሃጢአቴ እየቀጣኝ ነው።”

ሓርቤ በኩታው ፊቱን ሸፍኖ ማልቀስ ቀጠለ። አድም የሚያደርገው ጠፍቶት በጸጥታ ጥቂት ከቆየ በሁዋላ ከእድሪስ ጋር ተመልሰው እንደሚመጡ ነግሮት ወደ አነሲሞስ በመሄድ ቂጣና ውሃ ማደሉን ማገዝ ቀጠለ። እንባ ቢተናነቀውም አላለቀሰም። መራራ ነገር ብቻ ጉሮሮውን ይከረክረዋል። ልቡ ላይ ድንጋይ የተጫነበት ያህል መተንፈስ አቃተው። በርግጥ “መሸፈት” ምን ማለት እንደሆነ ያውቃል። ሰዎች ለምን እንደሚሸፍቱ ግን አያውቅም።

በዚያን እለት ማታ በመኝታቸው ሰአት አድም ቀን የገጠመውን ዝርዝር አድርጎ ለታላቅ ወንድሙ ነገረው። እድሪስ ጉዳዩን በጉጉት ከሰማ በሁዋላ በነጋታው ሓርቤን አጊኝተው ስለ አባታቸው በዝርዝር ለመጠየቅ ተስማሙ።

በነጋታው ማለዳ ግን ሓርቤን አላገኙትም። አጠገቡ የነበሩ ስደተኞች ሓርቤ ማምሻው ላይ ሞቶ መቀበሩን ነገሯቸው። በየቀኑ ከሰላሳ እስከ አርባ ሰዎች ይሞቱ ስለነበር የሓርቤ መሞት ልዩ ክስተት አልሆነባቸውም። የረሃቡ ጊዜ እየተራዘመ በሄደ መጠን በኡምኩሉ ካምፕ ዙሪያ በቀን የሚሞተው ሰው ቁጥር ከመቶ በላይ ደርሶ ነበር። ስደተኞች ይጎርፋሉ። በየእለቱ ኦዳዴስ ፊቶች ይታያሉ። ከትግራይና ከጎንደር ጭምር ይመጡ የነበረ ሲሆን፤ ምጽዋ ከመድረሳቸው በፊት መንገድ ላይ የሚቀሩ ይበዙ ነበር።

* * *

በኡምኩሉ ግቢ አስራ ዘጠኝ ያህል ልጆች ነበሩ። የኑረነቢ ልጆች ሲታከሉ ሃያ አንድ ሆኑ። ልጆቹ በተለያዩ መምህራን ትምህርት ያገኛሉ። መጽሃፍ ቅዱስ ይነበብላቸዋል። አለቃ ታዬ የግዕዝ ፊደልና ንባብ ያስተምራል። ኦነሲሞስ፣ ሃይለሚካኤል ኪዳኑ፣ ገብረጊዮርጊስ ባርያው፣ ቄስ ዘርአጽዮን ሙሴ እንዲሁ በፕሮግራም የቋንቋ፣ የቁጥርና የመጽሃፍ ቅዱስ ትምህርት ይሰጣሉ። በኡምኩሉ አማርኛ ቋንቋ ልዩ ትኩረት አግኝቶ ነበር። ምክንያቱ መጽሃፍ ቅዱስ በአማርኛ ቋንቋ ታትሞ ስለነበር ሲሆን፤ በጣና ሃይቅ ዙሪያና በአቢሲንያ ባለስልጣናት ዘንድም አማርኛ መጠቀሚያ ቋንቋ በመሆኑ ምክንያት ነበር።

ምንጊዜም ማለዳ ለስደተኞች ቁርስ ያድላሉ። ከዚያም ተማሪዎች ይማራሉ። ሰኞና ማክሰኞ ከምሳ በሁዋላ የመጽሃፍ ቅዱስ የጥናት ክፍለጊዜ ነው። አርብ ከሰአት በሁዋላ ወደ ምጽዋ ገበያ ይሄዳሉ። በገበያውም የወንጌል ሰበካ ይደረጋል። አዳዲስ ሰዎችን ማነጋገር፤ መረጃዎችን የማወቅ ስራዎች ይሰራሉ። እሁድ በጸሎትና በመዘመር አምላክን ያመሰግናሉ።

አንድ ማለዳ ኦነሲሞስ የልጅነት ህይወቱን ለተማሪዎቹ አወጋ። ታሪኩን የተረከበት መነሻ “የአምላክ መንገድ” በሚል ርእስ ነበር። ፈጣሪ ከህይወት ለማስተማር ሲል የሰው ልጆች በከባድ ችግርና መከራ ውስጥ እንዲያልፉ ሊያደርግ እንደሚችል የዮሴፍን ታሪክ ጠቅሶ ሲያስተምር ቆየና በእግረመንገዱ ሂካ አዋጂ በነበረበት ጊዜ የራሱን ረጅም የልጅነት ታሪክ ባጭሩ ተረከላቸው።

...ሂካ በ1856 ሁሩሙ፣ ኢሉ-አባ-ቦራ ተወለደ። ሁሩሙ ከመቱ 17 ኪሎሜትር ይርቃል። ሂካ የተወለደባት መንደር ልዩ ስሟ አጌ ነው። ከዋራቆ ጎሳ ነበሩ። አባቱ በህይወት እስካለ ጊዜ ድረስ ጥሩ የገጠር ህይወት ነበራቸው። የሂካ አባት የሞተው ሂካ የአራት አመት ልጅ ሳለ ነበር። ሂካ የመጨረሻ ልጅ ሲሆን፤ ታላቅ እህትና ወንድም ነበሩት። ከአባታቸው ሞት በሁዋላ ጎጇቸው ተደፈረ።

የሆነው እንዲህ ነው ...

ጊዜው የበጋ ወቅት ነበር። ሳሮች ደርቀዋል። በመሆኑም ከብቶችን ለማሰማራት ሳር ፍለጋ ከመንደራቸው ርቀው ለመሄድ

ተገደዱ። ርቀው ሄደው ከብቶቻቸውን አሰማርተው ሳለ አንድ ሰው ይመጣና ባሪያ ፈንጋዮች ልጆቿን ሰርቀው ወስደው ሊሸጡ፤ ከብቶቹንም ለመውሰድ ማሰባቸውን ይነግራታል።

ይህን ሲሰሙ ወንዝ ተሻግረው ተደበቁ።

ጥቂት ቆይተው ባሪያ ፈንጋዮቹ ሄደው ይሆናል በሚል ግምት ወደ ከብቶቻቸው ተመለሱ። ወዲያው ግን ባሪያ ፈንጋዮቹ ከበቧቸው። ጦርና ጋሻ የያዙትን ገደሉና ሂካንና ወንድሞቹን ያዙ። እናት ግን የትንሹ ልጇን የሂካን እጅ ይዛ አሳልፋ ላለመስጠት ታገለች። ከባሪያ ፈንጋዮቹ አንዱ፣ ልጇን የማትለቅ ከሆነ ልጇንም እሷንም እንደሚገድል ነገራት። ጦሩንም ሰበቀ። የሂካ እናት ልጇን እንደማታድነው ስትረዳ፤ ከሚሞት ባሪያ ሆኖ በህይወት ቢቆይ ይሻላል በሚል ተወችላቸው። ሂካ ከዚያን ቀን በሁዋላ የባርነት ህይወቱን ጀመረ። ወንድምና እህቶቹ ምን እንደደረሰባቸው ግን አልታወቀም። የተሸጠ ባርያ ጌታውን እንደ አህያና በሬ ማገልገል ይጠበቅበታል። ጌታውም እንደፈለገው ያደርገዋል። ተጠቅሞበት ሲያበቃ አሳልፎ ለሌላ ሊሸጠው ይችላል።

ሂካን የያዘው ሰው ወደ ቤቱ ወሰደው። ሚስቱና ልጆቹም ባርያ በማግኘታቸው በጣም ተደሰቱ። ሂካ በዚያኑ ቀን ስራ ጀመረ። ሁሉም በየፊናቸው ያዝዙታል። ሊሰራው ከሚችለው በላይ ስራ ይጭኑበታል። እያለቀሰ ስራውን ይሰራ ነበር።

የሂካ ጌታ ከጥቂት ጊዜ በሁዋላ ለሌላ ጌታ ሸጠው። ገዢው ጥቂት ጊዜ ከተጠቀመበት በሁዋላ ደግሞ ለሌላ ሸጠው። ከአንዱ ጌታ ወደ ሌላው ጌታ፣ አንድ ጊዜ በአንድ ፈረስ፤ ሌላ ጊዜ በአራት ላሞች ተሸጠ ወይም ተለወጠ። በአራት ላሞች የገዛው አዲሱ ጌታ አሳልፎ እንደማይሸጠውና እንደ ልጁ እንደሚይዘው ~~ቃል ገብቶለት ነበር። ሁለት አመታት ከተጠቀመበት በሁዋላ ግን~~ ቃሉን ሳይጠብቅ ለሌላ ሁለት ጌቶች ሸጠው። ሁለቱ ጌቶች ርስበርስ ተጣልተው አንዱ ሌላውን ገደለው። ገዳዩም ሂካን ለዘመዶቹ ሰጥቶ ተሰደደ። ሂካ እነዚህኑ አዲስ ጌቶች ማገልገል ጀመረ።

ከእለታት አንድ ቀን ውሃ እየቀዳ ሳለ አንድ ሰው መጥቶ አስገድዶ ይዞት ከሄደ በሁዋላ በ200 ጣሳ አሞሌ ጨው ለአንድ አበሻ ሸጠው። አበሻው ደ'ሞ ሂካን በጥሩ ዋጋ ለመሸጥ ወደ ምጽዋ

ይዞት ሄደ። በጥቅሉ ሂካ ምጽዋ ከመድረሱ በፊት ስምንት ጊዜ የመሸጥ እጣ ገጥሞታል። ጌቶቹ በጣም ጨካኞች ነበሩ። “ሰው ለሚበሉ እንሸጥሃለን” እያሉ ያስፈራሩት ነበር። ለስምንተኛ ጊዜ ሂካን የገዛው አበሻ ምጽዋ ይዞት ሲገባ ሂካ ነጭ ሰዎች ሲያይ “ሰው ይበላሉ” የተባሉት እነዚህ ነጫጭ ሰዎች መስለውት ክፉኛ ደነገጠ። አርደው እስኪበሉት ከመጠበቅ በቀር ግን ምንም ማድረግ አልቻለም። በመካከሉ ሙንዚንገር የሚባል ነጭ ሰው በደላሎች በኩል መጥቶ ከባሪያ ነጋዴዎች ገዝቶ ወደ ቤቱ ወሰደው። ሂካ ይህን ነጭ ሰው በጣም ፈራው።

የሂካን ፍርሃት የተረዳው ነጭ ሊያረጋጋው ሞከረ፣

“አትፍራ! ከዚህ በሁዋላ እንደ ባርያ አትሸጥም። ነጻ ነህ።”

ሂካ ግን የሙንዚንገርን ንግግር አላመነም። ከዚህ ቀደም የገዙትም እንዲህ ያለ የማታለል ቃል ይናገሩ ስለነበር ይህም በተመሳሳይ እያታለለው መሰለው። እንዳሰበው ግን አልነበረም። ሙንዚንገር ሂካን ወደ ኡምኩሉ ወስዶ ለሉንዳል ሲያስረክበው፣ “Make a good man out of this boy” አለው።

በርግጥ ሉንዳል ማድረግ ቻለ።

ከሂካ ነፍስ ውስጥ ኦነሲሞስ ወጣ። ማለትም ከአምስት አመታት በሁዋላ ሂካ ኡምኩሉ ላይ የወንጌል አስተማሪ ሆነ። ከአስር አመታት በሁዋላ ስዊድን አገር ሄዶ ትምህርቱን አጠናቆ ተመለሰ። ከአስራ አምስት አመታት በሁዋላ ደ’ሞ መጽሃፍ ቅዱስን ወደ ኦሮምኛ ቋንቋ መተርጎም ቻለ። ከሃያ አመታት በሁዋላ ሌቃ ዱለቻና ሌቃ ለቀምት የኦነሲሞስን ድምጽ ሰሙ። ወንጌልን በኦሮምኛ ማንበብ ጀመሩ። ሙንዚንገር ግን ይህን አላየም። በ1875 ዓሳውርታ ላይ ተገደለ።

ኦነሲሞስ የባርነት ታሪኩን ተርኮ ሲያበቃ እንዲህ አለ፣

“ተወልዳችሁ ወደዚህች ምድር መጥታችሁዋል። ሰው ናችሁ። የሰው ልጅ ፍላጎት ምግብና መጠለያ በማግኘት ብቻ አያበቃም። የሰው ልጅ በተፈጥሮው አይረካም። ለስጋው ካሰበ፣ በስጋው ከታዘዘ እስከ ህይወት ፍጻሜው ርካታ አያገኝም። አይጠግብም። የሰው ልጅ ለመርካት ህሊናውን ማነልበት አለበት።

መንፈሱን ማዳመጥ ይገባዋል ...”

የረኑረነቢ ልጆች በኡምኩሉ ቆይታቸው ዋና እለታዊ ተግባራቸው መማር ነበር። ግዕዝ፣ ትግርኛ፣ አማርኛና የስዊድሽ ቋንቋዎችን ይማራሉ። ቁጥሮችን መለየት ቻሉ። አራቱን የሂሳብ ስሌቶች በአጭር ጊዜ አወቋቸው። ከመጽሃፍ ቅዱስ ትምህርት ቀጥሎ በኡምኩሉ ልዩ ትኩረት የሚሰጠው የንጽህና አጠባበቅ ጉዳይ ነበር። በቅድሚያ ልብሳቸውን ማለቅለቅ ተማሩ። ጥርሶቻቸውን ምንጊዜም ማለዳ በእርጥብ እንጨት ማጽዳት ግዴታ ነበር። ወደ ገበታ ከመቅረባቸው በፊት እጆቻቸውን ጥሩ አድርገው ይታጠባሉ። የኑረነቢ ልጆች ፋና በነበሩ ጊዜም ወደ ገበታ ከመቅረባቸው በፊት እጆቻቸውን ይታጠቡ ነበር። የኡምኩሉ የተለየ የሆነው እዚያው ግቢ ውስጥ የሚሰራ ሳሙና ከመታጠቢያው አጠገብ መቅረቡ ነበር።

(በኡምኩሉ ቆይታቸው የኑረነቢ ልጆች ከኦነሲምስ ነሲብና ከዘርአጽዮን ሙሴ አባታዊ ፍቅር ማግኘት ችለዋል። ኦነሲምስና ዘርአጽዮን ሙሴ ኡምኩሉ ላይ ረጅም ጊዜ አብረው የመድሃኒየለምን ቤተክርስትያን ያገለገሉ ሲሆን የቅርብ ወዳጆችም ነበሩ።

ኦነሲምስ የመጀመሪያ ባለቤቱ ምህረት ሃይሉ ካረፈች በሁዋላ ዲምቦ ጋርባን አገባ። ዲምቦ ሰዮ - ወለጋ ነበር አገሯ። አከስቷን ለመጠየቅ ሰትሄድ ፈንጋዮች ይዘው ሸጧት። ፈንጋዮቹ ከመጽዋ ወደ አረቢያ ሊያሻግሯት ሲሉ ግን ኢጣልያውያን ነጻ አወጧት። ሁዋላ ኦነሲምስ ኩዲምቦ አራት ልጆች ለማፍራት በቅቷል።

ከ55 አመታት በሁዋላ ከኢድም ልጆች አንዱ የኢትዮጵያ መንግስት ባለስልጣን ለመሆን በመብቃቱ ወለጋ ሄዶ ኦነሲምስን ለማግኘት ችሏል። በዚያን ጊዜ ኦነሲምስ ሸምግሎ ነበር። ሆኖም አባ ዮሃንስ ኡምኩሉ ያመጣቸውን ሁለት ልጆች አልረሳም። ገብርኤል 'የኢድም ልጅ ነኝ' ብሎ ሲነግረው ኦነሲምስ የደመቀ ፈገግታና እንባ ተቀላቀሉበት። እጁን ከገብርኤል ግንባር ላይ በመጫንም በእየሱስ ስም ጸሎት አደረገለት።

ሁለቱ ቄሶች ኡምኩሉ በአንድ ግቢ ውስጥ ይኖሩ ከነበረበት ጊዜ ከ120 አመታት በሁዋላ የልጅ ልጆቻቸው ፕሮፌሰር አስመሮም ለገሰ እና ፕሮፌሰር ህዝቅኤል ጋቢሳ አሜሪካ ላይ ተገናኝተው ስለ አያቶቻቸው አውግተዋል።)

ምእራፍ ፮

መሬቱ ደግ ነበር
ቅዱስ መንፈሱን - ከተቻለ መድፈር

ከስድስት ወራት በሁዋላ አባ ዮሃንስ ከፈረንሳይ ተመልሶ ምጽዋ ደረሰ። በዚያ ጊዜ ውስጥ በአካባቢው ከጥቂት በላይ አዳዲስ ነገሮች ተከስተው ነበር። የኢጣልያ ሰራዊት አስመራን ብቻ ሳይሆን መረብ ምላሽን ተቆጣጥሮ፤ ጀኔራል ባልዲሴራ ኦሬሮ ኤርትራ የኢጣልያ ቅኝ ግዛት መሆኗን ጥር 1890 አውጆ ነበር። ይህም ንጉስ ምኒልክ እንጦጦ ላይ ዘውድ በደፉ በሶስተኛው ወር ማለት ነበር። አጤ ምኒልክ ዘውድ ከመድፋታቸው በፊት ውጫሌ ላይ "የሰላምና የወዳጅነት" የሚል ውል ከኢጣልያ ጋር ተፈራርመው ነበር። የዚህ ውል ዋና አጀንዳ ኤርትራ የኢጣልያ ግዛት መሆኗን ህጋዊ ማድረግ ቢሆንም ሁዋላ አንቀጽ 17 ቀጣዩን ጸብ ለማቀጣጠያ አገልግሏል።

በርግጥም አጤ ዮሃንስ መተማ ላይ በደርቡሽ ከተገደሉ በሁዋላ የኢጣሊያ ሰራዊት የሚያሰጋው ሃይል ባካባቢው አልነበረም። ያለምንም ውጊያ በቅድሚያ ከረንን ተቆጣጥሮ ባላምባራስ ካፍል ጎፉርን አስሮ ወደ አሰብ እስር ቤት ከላከ በሁዋላ፤ ልክ በወሩ ጉዞውን ወደ አስመራ ቀጠለ። የኢጣልያ ሰራዊት ወደ አስመራ ሲገሰግስ እንቅፋት አልገጠመውም። በኤጤ ቴዎድሮስ ዘመን የእንግሊዝ ሰራዊት ያለምንም ውጊያ ከዙላ ወደብ ተነስቶ መቅደላ እንደ ደረሰው ሁሉ የኢጣሊያ ሰራዊትም እንዲሁ ሰተት ብሎ እያፉዋጨ ነሃሴ 3 1889 አስመራ ገባ። አምላክ ወረራውን የባረከለት እስኪመስል የኢጣሊያ ሰራዊት አስመራ ከተማ ሲገባ ከባድ ዝናብ

ይረግጥ ነበር። ይህም ዝናብ የከበሳን ድርቅ ገፈፈው።

ከህዳር 1889 እስከ ጥር 1890 ባሉት የሁለት ወራት ጊዜያት ውስጥ ምኒልክና ኢጣልያ ባደረጉት ስምምነት በየፊናቸው ያልተናነሰ ጥቅም አጊኝተውበታል። ምኒልክ ወደ ደቡብና ወደ ኦሮሞ ምድር ጀምረውት ለነበረው መስፋፋት በቂ ጠመንጃ በማግኘት ጡንቻቸውን አፈርጥመው ዘውድ ደፉ። ኢጣልያ በበኩሏ ወደፊት ኢትዮጵያን ጠቅልላ ለመያዝ እንዲያመቻት ኤርትራን እንደ አስተማማኝ ቀዳሚ መምሪያ አደላድላ ያዘች።

አጤ ምኒልክ መረብ ምላሽ የኢጣልያ ግዛት መሆኗን ለማወቅ አምስት ሺህ ጠመንጃ በስጦታ፤ አምስት ሚሊዮን ሊሬ በብድር አገኙ። በገፍ ጠመንጃ ካገኙ በሁዋላም የኦሮሞን ምድርና ጋሞን ለመቆጣጠር ዘመቻቸውን ወይም ወረራቸውን አስፋፉ።

ቢትወደድ አስፍሃ ወልደሚካኤል፣ "ምኒልክ ኤርትራን በጠመንጃና በገንዘብ ለኢጣሊያ ሸጠ" ብሎ ሲኮንን፤ ዘምህረት ዮሃንስ በበኩሉ፣ ኢጣልያና ምኒልክን "የኤርትራ ግዛት እና የኢትዮጵያ ኤምፓየር ፈጣሪዎች" ሲል ይገልጻቸዋል። ይህም ስሌት የኢጣልያ "ኤርትራ" እና የምኒልክ "ኢትዮጵያ" በተመሳሳይ ጊዜ በ1890 የተመሰረቱ ወይም እንደ አገር የቆሙ በእድሜያቸውም እኩል የሆኑ አገራት ያደርጋቸዋል። አዲስ አበባና አስመራም በተመሳሳይ ጊዜ እንደ ዋና ከተማ መገንባት ጀመሩ። አጤ ምኒልክ በኤርትራ ጉዳይ ላይ ከተፈራረሙ በሁዋላ ከአዲሲቷ ጎረቤት አገር ጋር በሰላም መቆየት የቻሉት ግን ለጥቂት ወራት ብቻ ነበር።

አባ ዮሃንስ ከፈረንሳይ እንደተመለሰ ምጽዋ ብዙ አልቆየም። በሶስት ቀናት ጊዜ ውስጥ ጓዙን ወደ ከረን ልኮ ሲያበቃ፣ በሚቀጥለው ቀን ማለዳ ጀርባውን ለባሕሩ ፊቱን ለአስመራ ሰጠ። መንገዱን እንዲቀይር ካደረጉት ምክንያቶች አንዱ የሮማን ካቶሊክ ቤተክርስትያን አስመራ ላይ ሰፊ መሬት ወስዳ ግንባታ የመጀመሯን ወሬ በመስማቱ ሲሆን፤ ዜናው ትኩረቱን ስቦት ሰንብቷል። የኢጣልያ ቅኝ ገዢ አስመራን መቆጣጠሩ ከተሰማ ወዲህ ሃይማኖት ነክ ማህበራትና ተቋማት ቁልፍ መሬት ለመያዝ ሽሚያ ጀምረው ነበር። አባ ዮሃንስ ወደ አስመራ የሚያስኬድ ሌላ ጉዳይም ነበረው። ከባህታ

ሓጎስ ጋር ለመገናኘት ቀንና ቦታ የቆረጡት ፈረንሳይ ሳይሄድ ነበር።

የአባ ዮሃንስ የጉዞ ቡድን በመንገዱ ላይ ከግመል ጠያሮች ጋር በብዛት ተላለፈ። ተመላላሽ መንገደኞች ማቋረጫ አልነበራቸውም። ገና ሳይነጋ ከምጽዋ ጉዞ የጀመሩ መንገደኞች የቁርስ እረፍታቸው ጋህቴላይ ሲሆን፤ ከአስመራ የተነሱ በበኩላቸው እምባትካላ ወይ ደብረ ቢዘን ግርጌ ቆይታ ያደርጋሉ።

አባ ዮሃንስ በጉዞ ወቅት እረፍት በተደረገበት ቦታ ሁሉ የአካባቢውን ህዝብ የማነጋገር ልማድ አዳብሯል። አብዛኛውን የአገሬውን ቋንቋዎች መናገርና መስማት መቻሉም ከህብረተሰቡ ጋር ቀርቦ ለመነጋገር በእጅጉ አግዞት ነበር።

የኢጣልያ ቅኝ አገዛዝ መረብ ምላሽን መያዙ በህዝቡ ዘንድ በአወንታ መታየቱ አባ ዮሃንስን በጣም ያስደነቀ ጉዳይ ነበር። ህዝቡ በተመሳሳይ ስሜት በደፈናው ጣልያንን እንደ ነጻ አውጪ መመልከቱን መገንዘብ ቻለ። ለዚህ አመለካከት ግን አሳማኝ ምክንያት የሚሰጠው አላገኘም። ካነጋገራቸው የአገሬው ሰዎች የጣሊያኖችን መምጣት 'ወረራ' ብሎ የገለጸ አላጋጠመውም። አለያ ጣልያን መረብ ምላሽን በመያዟ ያገኙትን ጥቅም አይናገሩም። ቀድመው "ሰላም ስለማግኘት" ይናገራሉ።

ለቁርስ ጋህቴላይ ባረፉ ጊዜ አባ ዮሃንስ ከኑረነቢ ልጆች ጋር ጥቂት ተጨዋወተ። ስለ ልጅነታቸው፣ ስለ ወላጆቻቸው፣ ስለማንነታቸው እያነሳ ጠየቃቸው። ከሚሰጡት ምላሽ ልጆቹ በተለይ ስለ ማንነታቸው ያላቸው እውቀት ዝቅተኛ መሆኑን ተረዳ። ልጆቹ ከወላጅ ግንባታ ተለያይተው፤ ከህብረተሰብና ~~ክዘመድ አዝማድ ስለተነጠሉ በጊዜ ሂደት በልጅነት እድሜያቸው ያወቋትንም ሊረሱ እንደሚችሉ አሰላሰለ። ከወላጆቻቸው ሊያገኙ ይችሉት የነበረውን ጎዶሎ መሙላት እንደማይችል ቢረዳም እንደዋዛ እያደረገ ሊገባቸው በሚችል ቀላል አቀራረብ~~ በከረን ቆይታው ከብሌን ታሪክ አዋቂዎችና ሽማግሌዎች የሰማውን ላይ ላዩን አወጋቸው።

"...ጣውቀ ከየት እንደመጣ፣ ማን ማንን እንደወለደ በዝርዝር ማወቃችሁ ጥሩ ነው። እንዳይረሳ በወረቀት ላይ እንዴት እንደሚመዘገብ ከረን ስንደርስ አሳያችሁዋለሁ። ስለ እናታችሁም እንዲሁ በዝርዝር ማወቅ ይገባል። ከምራራ ወገን መሆኗን ማወቅ

ብቻውን በቂ አይደለም። ከፍ ስትሉ ወደ ትውልድ አገራችሁ ተመልሳችሁ በህይወት የተረፈ ዘመድ ከተገኘ መጠየቅና መመዝገብ ይገባል። የእግዚአብሄር ፈቃድ ከተጨመረበት አባታችሁን ዳግም ለማየት ትበቃላችሁ። ርግጥ ነው በሽፍትነት ያለ ሰው ለአደጋ የተጋለጠ ነው። የኢጣልያ ኮሎኒ ለሸፈቱት ምህረት ከሰጠ አባታችሁ ተመልሶ ሊመጣ ይችላል። አክስታችሁንም አስመራ እንፈልጋታለን።

"...እናታችሁ 'የምራራ ወገን ነኝ' ማለቷ እንግዲህ የዘር ሃረጓ ከምራራ ተከለሃይማኖት ቢሆን ነው። በተለምዶ ግን መራ ተኽለሃይማኖት ይሉታል። ምራራን ለማሳጠር ሲባል የተሰጠ ስያሜ ሊሆን ይችላል። የምራራ ሰዎች ተሰደው ያመጡት ከሳዑዲ አረቢያ ሳይሆን አይቀርም። በመካከለኛው ምስራቅ የምራር ልጆች ነን የሚሉ አሉ። ምራር እና ምራራ ልዩነቱ ምን እንደሆነ አላውቅም። የምራር ልጆች ከሳዑዲ አረቢያ በጦርነት ምክንያት መሰደዳቸውን ይገልጻሉ። ወንድሞቻቸው የኤርትራን ባሕር እንደተሻገሩም አፈታሪክ አላቸው።

"...ምራራ ተከለሃይማኖት ሰፊ ታሪክ ያለው ሰው ነው። ከፍ ስትሉ ሁሉን ታውቃላችሁ። ከምራራ ወደ አክሱም ሄዶ የዛጉየን መንግስት የመሰረተ ነበር። የምራራ ተከለሃይማኖት ወደ ስልጣን አመጣጥ እንዲህ ነው። ድግና ጎን የሚባል የአክሱም ንጉስ ነበር። ምራራ ተከለሃይማኖት ጀግና ተዋጊ ስለነበር ንጉሱ ሴት ልጁን ዳረለት። ምራራ ተከለሃይማኖት አቅሙን ገምቶ ሲያበቃ፤ የአማቹን ስልጣን ነጥቆ የአክሱምን መኳንንት አሳደዳቸው። ዛጉየ የሚለው ቃል ዘአጓየየ (ያሯሯጠ) ከሚለው የመጣ ነው ይባላል። የአክሱም መኳንንት ሸሽተው ሸዋ ገቡ። ያን ጊዜ እንኳ ሸዋ የሚባል አልነበረም። የምራራ ልጆች ምን ያህል አመታት እንደነገሱ አይታወቅም። ከ133 እስከ 300 አመታት መሆኑን የሚገልጹ ጥንታዊ ድሁፎች አሉ። የምራራ ተኽለሃይማኖት መነሻው ከረን በኩ ወንዝ አካባቢ ነው። በኋላቸው በጉና - ቡግና የሚባል አገር ሮሃ አካባቢ ነበረ። ዘራቸው አገው ነው። ይህም ዘር አግአዝያንና አረቦች ወዲህ ከመምጣታቸው በፊት የነበረ ዘር ነው።

"...ከምራራ ጋር ወደ ላስታና ወደ አክሱም የተጓዘው ጎሳ ከፊሉ በዘመነ ያእቆብ እንደገና ተመልሶ ወደዚህ ወደ መረብ ምላሽ መጥቷል። የምራራ ልጆች በላስታ ዘመን ቆይታቸው ተራራ ላይ

ወጥተው በየአመቱ ብሌንካ አገራቸውን፤ ብሌንካ ንጉሳቸውን የማስታወስና የመዘከር ልማድ ነበራቸው። ድግስ ተደግሶ ይበላል፣ ይጠጣል። ሲጠጣና ሲበላ ምራራ እና ብሌንካ በመንፈስ ይነግሳሉ። ቀይ ባሕርን አሻግረው የሚመለከቱ የሰንሒት ሰዎች ደቂ ብሌንካ፤ አንዳንዴም ደቂ ምራራ ተብለው ይጠሩ ነበር። ብሌንካ እና ምራራ የነገሱበት ቦታ እና ህዝብ ዛሬም በስማቸው ይጠራል።

“....በ1270 አካባቢ አባ ተክለሃይማኖት የተባለ የሳይንት ቄስ የአክሱም ነገስታት ወደ ዙፋኑ ይመለሱ ዘንድ ማደራጀት ቻለ። የዘር ሃረጋቸውንም ከእስራኤል ንጉስ ሰለሞን ጋር አገናኝቶ ጻፈላቸው። በዚህም ‘ሰለሞናዊ’ የተባለ ስርወ መንግስት መመስረት ቻሉ። የምራራ ልጆች በላስታ ቆይታቸው ባህልና ቋንቋቸውን ሳያጠፉ ይዘው መቆየት ችለዋል። የዛጉየ ስርአት ከፈረሰ በሁዋላ ወደ መረብ ምላሽ ተመልሰው የገቡት ብሌን ሆነው ቀጠሉ።

“...የሓልሓልን ትርጉም አላውቅም። አባቶቻችሁ ግን ሓልሓልን ‘ዳካ’ ይሉታል። በኩሽቲክ ቋንቋ ዳካ ‘መሬት’ ማለት ነው። ሓልሓል ቀደም ብሎ ‘ዓዲ ሊባን’ ይባል ነበር። ‘ሊበን’ ማለት በኩሽቲክ ቋንቋ ‘እጣን’ ማለት ነው። በሰራዬ ሓልሓለ የሚባል ቦታ አለ። በሓልሓልና በሓልሓለ መካከል ያለውን ልዩነት ግን አላውቅም።

“....ሽማግሌዎች ዘር ሲቆጥሩ ‘ንጉስ ምራራ ተክለሃይማኖት ጠጠው ውድምን ወለደ።’ ይላሉ። ጠጠው ውድም ጃን ስዩምን ወለደ። ጃን ስዩም ምራራ ገብረማርያምን ወለደ እያሉ ሲቀጥሉ በሰንሰለቱ ውስጥ እነ ቅዱስ ላሊበላ፣ እነ አቤቶ ሐርቦይ፣ ይመጣሉ። ዝርዝር ምዝገባው ቢቀጥል ምናልባት ሄዶ ሄዶ ከእናታችሁ ዘንድ መድረሱ ይረጋገጥ ነበር። ካልተመዘገበ ግን ማወቅ አይቻልም። እንዲህ ያለ ነገር ማወቅ ከፈለጋችሁ ወደፊት ጠለቅ ብላችሁ መቆፈር ይገባል። ያለፈውን ማወቅ ተገቢ ነው። ያለፈው ከሌለ መቆሚያ አይኖራችሁም። ያለፈው የሌለው ነገ አይኖረውም።”

በጋህቴላይ የቁርስ እረፍት ቆይታቸው ከጊላጊዮርጊስ ጋር ተገናኙ። ጠመንጃና ጥይት የጫኑ 600 ግመሎችን እየመራ ወደ አስመራ በመጓዝ ላይ ነበር። ከሃምሳ ያላነሱ አጃቢዎች ነበሩት።

በጊላጊዮርጊስ ህይወት ላይ ብዙ ለውጥ ነበር። ከሰረገላ ነጂነት እድገት አጊኝቶ፣ ብሉቾባሽ ለብሷል።–በአውስትሬሊያ ፈረስ ላይ ተቀምጦ ሲንጎማለል ለሚያይ የከበደ ግርማ፤ የደመቀ ሞገስ ነበረው። ጊላጊዮርጊስ በፈረሱ ሶምሶማ እየጋለበ አባ ዮሃንስ ካረፉበት ጥላ ስር ደርሶ ለአንድ የሃይማኖት መሪ የሚገባውን ሰላምታ አቀረበ። ቀደም ሲል ምጽዋ ይተዋወቁ ነበር። በተለይም ጀኔራል ሳሌታ አባ ዮሃንስን ለማነጋገር በፈለገ ጊዜ በተደጋጋሚ ወደ ቄሱ ቪላ በመመላለሱ እውቂያቸው የቀረበ ነበር።

ጊላጊ እንደተለመደው ደስተኛ ነበር።

ቡና እየጠጡ ስለ ወቅታዊው የፖለቲካ ሁኔታ ተጨዋወቱ። በወግ መካከል አባ ዮሃንስ የከነከነውን ጉዳይ አንስቶ ጠየቀ። ማለትም ህዝቡ የኢጣልያን ሰራዊት እንደ ነጻ አውጪ ለማየት የቻለበት ምክንያት ምን እንደሆነ አሳቡን ጠየቀው።

ጊላጊ እያመነታ ምላሽ ሰጠ፣

“ምናልባት በጦርነት መሰላቸቱ አንድ ምክንያት ሊሆን ይችላል። ብዙ ቦታ ገበሬው፣ ‘ኢጣልያ ሰላም ያመጣል’ የሚል ነገር በተስፋ ይናገራል። አስመራ ሲያዝ ተቃውሞ አልገጠመም።”

አባ ዮሃንስ በትኩረት ሲያዳምጥ ጊላጊዮርጊስ ቀጠለ፣

“...ገበሬው ብዙ ችግር አሳልፏል። ከሁሉም በላይ ለጉልበተኛ የጎበዝ አለቆች በፈረቃ በመገበር ተማሮ ነበር። እኔ ስለ ራሴ ስናገር ግን የኢጣልያን መምጣት መደገፌ ከግብጽ ጋር በማወዳደር ነው። ሌላ አይደለም። የባርያ ንግድ ማገዳቸው ትልቁ ጉዳይ ነው። የከበሳና የመታሕት ገበሬ ልጆቹ በባርያ ፈንጋይ እየተወሰዱበት ብዙ ስቃይ አሳልፏል።”

“ህዝቡን የፈታው ድርቁ እንዳይሆን?” ሲል ቄሱ ጠየቀ።

“ዋናው ጉዳይ የሰላም ፍላጎት ይመስለኛል። ባለፉት ሃያ አመታት ውስጥ እኔ የማውቀው ብቻ እንኳ እዚህ አካባቢ ከአስራ ሶስት በላይ ውጊያዎች ተካሂደዋል። ጎጆ መቃጠል፣ በሬና ላም መነጠቅ እንዲህ ያለ ነገር ሲደጋገምበት ህዝቡ መኖር ተቸግሮ ነበር። በሬውን ሲያርሱበት በሚቀጥለው በምን ያርሳል? ክረምት አልፎ ምርት ከተሰበሰበ በሁዋላ ወራሪ አይጠፋም። ልጆቹን ያጣል።”

ጊላጊ አከለበት።

“...በሌላ መልኩ የኢጣልያ ሰራዊት እስካሁን ህዝቡን አላስቀየመም። በየደረሱበት ለሚሰጣቸው አገልግሎት በአይነት ወይም በኢጣልያ ገንዘብ ክፍያ ይፈጽማሉ። በባርነት የተያዙ ሰዎች ሲገጥሟቸው ነጻ መሆናቸውን የሚገልጽ ወረቀት ይሰጣሉ። ፍትህ አላቸው። ሰው ሲያስሩ ጉዳዩን መርምረው ይፈርዳሉ። በዚህ ክፉ ጊዜ ደግሞ በእርዳታም በሽያጭም እህል እያቀረቡ ነው።”

“መኳንንቱ ከኢጣልያ ጋር መተባበራቸውስ?”

“ጠመንጃ ፈልገው እንዳይሆን? ምናልባት!”

እያወጉ ጉዟቸውን ወደ አስመራ ቀጠሉ።

አባ ዮሃንስ ለማወቅ በሚጓጓ ሰው መንፈስ የጊላጊዮርጊስን ስሜትና አመለካከት ለመረዳት ከቀላል እስከ ውስብስብ ጥያቄዎች እንደዋዛ ጣል ሲያደርግ ጊላጊ እንዳመጣለት መለሰ፣

“ይሄ የሚሰጧችሁ ማእረግ የቱርክ ነው ይባላል። ምነው የራሳቸውን ማእረግ ሳይሰጧችሁ ቀሩ? ሰርጀንትና ሌፍተናንት ምን እንዳይላችሁ ነው? የደንብ ልብሳችሁም የቱርክ ይመስላል። ለኢጣልያ እየሰራችሁ ለምን የቱርክ ያለብሷችሁዋል?”

ጊላጊ እየሳቀ ምላሽ ሰጠ፣

“እኩል የመሆን ስሜት እንዳያድርብን ይሆናላ።”

በጊላጊዮርጊስ ምላሽ ቁሱ መደነቅ አደረበት፣

“እንደዚህ ትገነዘባለህ ብዬ ያልጠበቅሁት ነው።”

“አባ ዮሃንስ! የዚህ አገር- ሰው ምንም አያውቅም ብለው በማሰብዎ አይገርመኝም። ጣልያኖችም ምንም የማናውቅ ያደርጉናል። ቁጥራችን ትንሽ ነው። ምን ማድረግ እንችላለን? በዚህ ክፉ ዘመን ከድርቅ፣ ከባርያ ንግድና ከጦርነት በቀር ሌላ የሚታይ ነገር የለንም። እንዳዩት ህይወቱን ለማትረፍ ገበሬው እየተሰደደ ነው። እስኪ ልጠይቅዎ? በረሃብ ጊዜ ስለ ክብር ማሰብ ይቻላል?”

“ክብርን ከማጣት በፊት መሞትን መምረጥ መፍትሄ የሚሆንበት ጊዜ አለ። የእነዚህ አብረውኝ ያሉ ሁለት ልጆች አባት

በተራበበት ጊዜ ለክብሩ ሲል መሸፈቱን ሰምቼ ተደንቄያለሁ።"

ጊላጊ በነቃ መንፈስ ስለ ልጆቹ ማንነት ጠየቀ። አባ ዮሃንስ የኑረነቢን ስም ሲጠቅስለት ጊላጊዮርጊስ በዚያው ቅጽበት ኑረነቢ የተባለውን የሸማል ሽርቅ ዘበኛ አስታወሰ፣

"ሸማል ሽርቅ ሬስቶራንት በዘበኛነት ይሰራ የነበረው ሰው ከሆነ አውቀዋለሁ። አንድ ጥልያን 'ፒግሮ' ስላለው ተቀይሞ ስራ እንደተወ ሰምቻለሁ። ሸፈተ ነው የሚሉኝ? የዋህ ነው።"

በጊላጊ አነጋገር አባ ዮሃንስ ቅር ተሰኘ፣

"ፒግሮ ሲሉት ኑረነቢ መበሳጨቱ ተፈጥሯዊ ነው። ስህተት የሚሆነው ስድቡን ቢለማመደው ነበር።"

ጊላጊ አባባሉን ለማብራራት ሞከረ፣

"ጥልያኖች ቢሳደቡ ለክፋት አይመስለኝም። በስንፍንናችን እየተበሳጩ ነው። ፒግሮ አለመሆናችንን በስራ ማሳየት እንችላለን። እኔ ስራዬን አክብሬ በርትቼ ስለምሰራ እስካሁን የሰደበኝ ጥልያን የለም። ኑረነቢ ችላ ማለት ይሻለው ነበር ለማለት ነው።"

"የሰውን ልጅ በማዋረድ ማስተማር አይቻልም። አምላክ የሰውን ልጅ ሲፈጥረው እኩል አድርጎ ነው የፈጠረው። እኔ በኑረነቢ ቦታ ብሆን ኖሮ በትክክል ኑረነቢ ያደረገውን ነበር የማደርገው።"

ብሉቐባሽ ጊላጊዮርጊስ ሙግቱን ቀጠለ፣

"አንድ ሰካራም ጥልያን ንቀት ስላሳየ መሸፈት ይገባል?"

"ነገሩ የአንድ ተራ ሰካራም ብቻ ከሆነ እንዳልከው ችግር አይደለም። ጉዳዩ የአንድ ተራ ሰካራም ብቻ ካልሆነ ማለቴ ነው።"

ጊላጊ የቄሱን የአግቦ አነጋገር ተረዳና አባባሉን አረመ፣

"ቅድም ስለ ማእረግና ስለዚህ የቱርክ ልብስ የተናገሩት ነገር አለ። እሱም ብቻ አይደለም። እያየን እንዳላየን የምናልፋቸው ደስ የማይሉ ነገሮች አሉ። ፒግሮ ብቻ ሳይሆን ሌሎች ጸያፍ ስድቦችንም እንሰማለን። ማርዮ እያሉ ይጠሩናል። በመረብ ምላሽ በአባቶቻችን ህግ መሳደብ ያስቀጣል። በቀጥታ መሳደብ ብቻ ሳይሆን በዶሮና በውሻ እያስመሰሉ በአሽሙር መሳደብ እንኳ ያስቀጣል። አባቶቻችን

ምንም እንኳ ለአውሮፓ ስልጣኔ የራቁ ቢሆኑም ፈሪሃ እግዚአብሄር ያላቸው፣ ባህል ያላቸው፣ ግብረገብና ሞራል ለልጆቻቸው ማውረስ የቻሉ ናቸው። ስድብ ~~ባህላችን አይደለም። እንግዲህ ጥልያኖች መጥተው ባንድ ጎኑ ጥሩ እየሰሩ ነው። የሚሳደቡትን ነገር ችላ ማለቱ ይሻላል መቸም? ችላ ማለት ባንችልስ ምን ማድረግ ይቻላል?~~”

~~“እንቱን ማርዮ ቢሉህ ምን~~ ታደርጋለህ?”

“አባ ዮሃንስ! መቸም የምሸፍት አይመስለኝም። እኔ ከርሶ ባላውቅም በዚህ ክፉ ጊዜ በጥቃቅን ~~ነገሮች መበሳጨት አይገባንም። በጥልያን መምጣት ከሁሉም በላይ ሰላም እያገኘን ነው~~። ስድብ ጥሩ አይደለም። ፒግሮ ቢሉን ግን እውነት ነው። ስንፍና አለብን። ውሃ ዳር ተኝተን ይጠማናል። ባሕሩ አጥር የለውም። አሳው ባለቤት የለውም። አሳ ሞልቶ በተረፈው ባሕር ዳርቻ እየኖርን ይርበናል። ጥልያን ይህን አይቶ ሰነፎች ቢለን ውሸት አይደለም።”

አባ ዮሃንስ ፈገግ ብሎ መልስ ሰጠ፣

“ጣልያኖች እንዳንተ አይነት አርቆ አሳቢ ብልህ ሰው በማግኘታቸው እድለኞች ናቸው።”

የአባ ዮሃንስ አነጋገር ከልብ ይሁን የለበጣ በትክክል ሊገነዘብ ባለመቻሉ ጊላጊዮርጊስ መንታ ልብ ሆኖ ዝምታን መረጠ። ጊንዳዕ እስኪደርሱም ጨዋታቸው ስለ መልከአ ምድሩ ነበር።

አባ ዮሃንስ ጀስዊታዊው አባ ፍራንቸስኮ አልቫሬዝ በ1620 ስለጻፈው መጽሃፍ ለጊላጊዮርጊስ አወጋ። በመጽሃፉ የተገለጸው ዱር በአእምሮው ሲስለው ከነበረው ጋር አልተጣጣመለትም። በተለይ ፍሬ ያንዣረገጉ የተምር ዛፎችን ጫካ ለማየት ~~ጓጉቶ ነበር።~~

~~አባ ዮሃንስ በቅሬታ እንዲህ አለ፣~~

~~“በርግጥ አልቫሬዝ በዚህ መንገድ ከተጓዘ ከ~~200 አመታት በላይ አልፏል። ለማውደም በቂ ጊዜ ነው።”

አባ ዮሃንስ እያመነታ አከለበት፣

“እዚህ የምናየው አልቫሬዝ ከጠቀሰው በብዙ መልኩ

የተለያየ መሆን አልነበረበትም። ምናልባት አልቫሬዝ ሲጽፍ ሳያጋንን አልቀረም። ቀደም ባለው ጊዜ እንዲህ ያለ ነገር ብዙ አጋጥሟል።"

ርእሰ ወሬው ለጊላጊዮርጊስ ትርጉም ስላልሰጠው መልስ አልሰጠም። አባ ዮሃንስ በሌላ መልክ ውይይቱን አስቀጠለ፣

"ወደ ደብረ ቢዘን ስንጠጋ ጫካው እየበረታ ይሄድ ይሆን?"

"ከሁለት ሰአት መንገድ በሁዋላ ጫካ ነው።"

"አራዊቶች አሉ?"

"አንበሶችና ነብሮች አሉ። የአንበሳ ምግብ አጋዘን ነው። ነብር በአብዛኛው ጦጣና ዝንጀሮ ይለቃቅማል። ዝሆኖች እንደ ቀድሞው አይደሉም። አባቶች ሲነግሩን ይርመሰመሱ ነበር። ወደ ደጋው እየወጡ የማሽላ ማሳ ያበላሹ ነበር። አምላክ ይመስገን፤ አሁን ቁጥራቸው ቀንሷል። ጥርሳቸው ዋጋ ስለሚያወጣ ጠላት በዛባቸውና እየተገደሉና እየሞቱ ጠፉ። አስቸግረው ነበር።"

አልቫሬዝ በመጽሃፉ የጠቀሰው ለእግረኛ የሚያስቸግር ጫካ ተመንጥሮ ስለ መሳሳቱ ግምት ወሰደ። አልቫሬዝ ያያቸውን አውሬዎች አንበሳ፣ ዝሆን፣ ነብር፣ ጥንቸል፣ ድብ፣ በቃቃን፣ ኩኩ ብሎ ሲጠቅስ፤ በመንገዳቸው ላይ የብርቱካን፣ የሎሚ፣ የትርንጎ፣ የፐረ፣ የበለስ፣ የኮክ ተክሎችን፣ የወይራ ዛፍ ጫካዎችን አልፎ ተጉዟል። ገበሬዎች የዘሩትን ካውሎና ኮረሪማ ያየ ሲሆን፤ ጥሩ ሽታ ያላቸው ቅጠሎችም ነበሩ። ፍራንቸስኮ አልቫሬዝ በ1526 ወደ አገሩ ከተመለሰ በሁዋላ The Prester John of the Indies በሚል ርእስ የጻፋቸውን ሁለት ቅጽ መጽሃፍት አባ ዮሃንስ በሻንጣው ይዟቸው ነበር።

አልቫሬዝ የጠቀሳቸው "ሰውነታቸውን የሚሸፍን ልብስ ያልነበራቸው" ሰዎች ግን በመንገዳቸው ላይ አልታዩም። "ሙራውያን" ሲል ገልጿል። ሙስሊሞች ማለት ነው። 'እነዚህ ርቃናቸውን የሚኖሩ የተባሉት ሰዎች አለመታየታቸው ጨርቅ መደረብ ስለለመዱ ይሆናል?' ሲል አሰበ። ጨርቅ መልበሱን ለመልመድ 200 አመታት ከበቂ በላይ መሆኑን አባ ዮሃንስ አሰላሰለ። የማወቅ ጉጉት ስላደረበት ቆም እያለ የአካባቢውን ሰዎች ስለ "ሙራውያን" ጠየቀ። ቃሉን የሚያውቅ አላገኘም። "ሱመራውያን" ማለቱ እንዳይሆን ሲጠይቁት ግን ግራ ተጋባ። እና ቃሉን መዘገበ።

በጥንታዊ ጽሁፎች እውነት ያልሆኑ ወጎች መታተማቸውን አስታወሰና ይህንኑ ለጊላጊ አጫወተው፣

“ስሙን ረሳሁት፤ አንድ ጀብደኛ አውሮፓዊ አሳሽ ‘አፍሪቃውያን ግንባራቸው ላይ አይን አላቸው’ ብሎ መጽሃፍ ጽፎ ታምኖ ነበር። ደረታቸው ላይ አይን ስላላቸው ፍጡራንም ተጽፎ በጉጉት የተነበበበት ዘመን ነበር። እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ አፍሪቃውያን ጥቁሮች ከሌላ አለም እንደመጡ ፍጡራን ነበር የሚታወቁት። ‘ዱባ የሚያክል ድንች አየሁ’ ብሎ የጻፈ ነበረ። ድንች ስለሚያክል ለውዝ ጭምር ተጽፎ ነበር። ሁዋላ ምድር እየጠበበች ስትመጣ እውነት ያልሆኑ ነገሮች እየተለዩ፣ እየጠሩ ሄዱ።”

ጊላጊ በግዴለሽነት አስተያየት ሰጠ፣

“ግንባሩ ላይ አንድ አይን ያለው ሰው መተተኞች የደገሙበት ሰው ሊሆን ይችላል። ጠንቋዮች ስንት ክፉ ጉድ ይሰራሉ። ቅዱስ ተአምራትም አሉ። አንድ ምሳሌ ልስጥዎ። ዓንሰባ አካባቢ አንዲት ሴት በአንድ ወር እርግዝና ጤነኛ ልጅ ወልዳለች።”

አባ ዮሃንስ የሞቀ ፈገግታ አሳየ፣

“እውነት መሆኑ እንዴት ታወቀ?”

“አገር ሁሉ የሚያውቀው ነው። ሰርግ ተደግሶ በተጋቡ ልክ በወሩ ወንድ ልጅ ወለደች። የፈጣሪን ተአምር ሰው ሁሉ አደነቀ።”

“ቀደም ብላ አርግዛ ቆይታ እንዳይሆን?”

“በፍጹም። ወንድ ቀርቧት አያውቅም።”

“አይ! ይህን እንኳ ለማመን ይከብዳል።”

“ድፍን ከበሳ ግን ይህን አምኗል። አገሩም በዚሁ ተአምር ‘ዓዲ ወርሂ ሰብ’ ተብሎ ይጠራል።”

አባ ዮሃንስ በጊላጊ እርግጠኛነት ተገርሞ እንዲህ አለ፣

“ፍየል ለመውለድ ስድስት ወራት ይፈጅባታል። ዶሮ እንቁላሎቿን ለመፈልፈል ሶስት ሳምንት ይፈጅባታል። አህያ ውርጭላዋን ለመውለድ አንድ አመት ያስፈልጋታል። ሰው ደግሞ ተረግዞ ለመወለድ ዘጠኝ ወራት ያስፈልገዋል። በህመም ምክንያት

ወይም በአንዳንድ ችግር በሰባት ወራት የሚወልዱ ሴቶች አሉ። በአንድ ወር እርግዝና ስለተወለደ የሰው ልጅ ግን በአለማችን ተሰምቶ አይታወቅም። ይህን ማመን የዋህነት ነው።"

ጊላጊ ግን አልተበገረም። ሞገተ፣

"ቅድስት ማርያም በድንግልናዋ ጌታን ወልዳ የለም እንዴ?"

"እሱ የእግዚአብሄር ተአምር ነው።"

"ይሄንንም የአምላክ ተአምር ብሎ ነው ሰው የሚያምን።"

እዚህ ላይ አባ ዮሃንስ ልጓም ያዘ። ሙግቱን መቀጠል ሳይችል ቀረ። በሙግቱ መሸነፉን ሲያውቅ ከፍተኛ መደነቅ አደረበት። 'ለምን አይሆንም?' ሲል ራሱን አጥብቆ ጠየቀ። ዓንሰባ በምትገኝ አንዲት የገጠር መንደር ውስጥ አምላክ ተአምር ሰርቶ ከሆነስ? ለምን አይሆንም?

"ብሉቾባሽ ጊላጊዮርጊስ፤ የተማርኩ እና ለእውነት የቆምኩ ሰው እንደመሆኔ መረታቴን ማመን አለብኝ።"

የመደነቁ ተራ ወደ ጊላጊዮርጊስ ዞረ። እና በተፈነቀለ ስሜት እንዲህ ሲል አባ ዮሃንስን አመሰገነ፣

"እንዲህ ያለ ሙግት የፈጸምኩት ከአገሬ ባላባት ጋር ቢሆን ተደፈርኩ ብሎ ጉድጓድ በቆፈረብኝ ነበር። አመሰግናለሁ።"

* * *

ጊንዳዕ አዳር ሆነ።

እሳት አንድደው ፍየሎችን አርደው እየጠበሱ በመመገብ አመሹ። ጊላጊዮርጊስ ለተከታዮቹ ላም አሳርዶ ሲያበቃ እሱ ወደ አባ ዮሃንስ ተመለሰ። የአካባቢው ሰዎችም የሚጠጣና የሚበላ በማምጣት በሚነደው እሳት ዙሪያ የሰፈሩ እንግዶችን አስተናገዱ።

በእሳት ዳር ወግ ላይ አንድ የጊንዳዕ የአገር ሽማግሌ ኢጣልያ ለምድሪ ባሕሪ መጠሪያ "ኤርትራ" የሚል ስም መስጠቷንና ማወጇን እንደሰሙ ጠቅሰው የቃሉን ትርጉም ጠየቁ።

ጊላጊዮርጊስ "ኤርትራ" የሚለው ቃል የባሕሩ መጠሪያ

መሆኑን፤ በግሪክ ቋንቋ ትርጉሙ “ቀይ” ማለት መሆኑ፤ ባሕሩ በዚህ ስም ለመጠራት የበቃው ባሕሩ ውስጥ በሚገኙ ቀያይ እጽዋት ምክንያት እንደሆነ የኢጣልያ አለቆቹን ምንጭ ጠቅሶ ተናገረ። እንግዶቹን በማስተናገድ ላይ ያሉት የአካባቢው ሰዎች ግን፤ የጊላጊን ማብራሪያ ችላ ብለው ስለ ቃሉ ከአባ ዮሃንስ ለመስማት ፈለጉ።

- አባ ዮሃንስ ረጋ ብሎ ተናገረ፣

“ብሉቾባሽ ጊላጊዮርጊስ ከገለጸው የተለየ ነገር እንኳ አላውቅም።” ዘግየት ብሎ አከለበት፣ “...ቀይ ባሕር ላይ ከሚገኙት ደሴቶች በአንዱ ይኖር የነበረ አንድ ፐርሺያዊ ስሙ Eruthras እንደነበር አንብቤአለሁ። ኤርትራ የሚለውን ስም በቅድሚያ የተጠቀሙት ሃብት አዳኞች፣ አዲስ አገር አሳሾችና ባሕር አቋራጭ ነጋዴዎች ሊሆኑ ይችላሉ። Erythreum Mare ብለው ደጋግመው ጽፈዋል። እንግዲህ እንደ ቃል ኤርትራ የሚለው ቃል በግሪክ ቋንቋ ‘ቀይ’ ማለት ከሆነ ይህን ባሕር ‘ቀይ’ ለማለት ያበቃቸው አንድ ምክንያት አለ ማለት ነው። ባሕሩ ውስጥ ቀያይ ቀለም ያላቸው የአሳ ዝርያዎች በብዛት መኖራቸው እውነት ነው። ቀይ ቅጠሎች ያሉት እጽዋት ባሕሩ ውስጥ መኖሩም ይነገራል። ባሕሩ ‘ቀይ’ የሚለውን ስም ያገኘው በርግጥ ከእነዚህ ምክንያቶች በአንዱ ወይም በሁለቱም ሊሆን ይችላል። በተጨማሪ ግን ፐርሺያዊው Eruthras የሚል ስም ከየት እንዳገኘ ማወቅ ይገባል።”

አባ ዮሃንስ እንደተለመደው ጢሙን እየነተተ ጠየቀ፣

“ለምሳሌ የእኔ አገር ስሟ ፈረንሳይ ይባላል። በመሆኑም እኔ ፈረንሳዊ ነኝ እላለሁ። ከዚህ አንጻር ብሉቾባሽ ጊላጊዮርጊስ እስከዛሬ እራስህን እንዴት ስትገልጽ ነበር? አገርህ ስሟ ማንበር?”

~~ጊላጊ አላመነታም፣~~

“ይሄ አገር ‘ምድሪ ባሕሪ’ ነው ስሙ። ከዚያ ቀደም ብሎ ደግሞ ሽማግሌዎች እንደነገሩን፣ ‘ብሄረ አግአዚት’ የሚባልበት ዘመን ነበር። ዐትግረ ቋንቋ በተስፋፋበት ዘመን አገሩ ‘ትግረ’ ተብሎ ይጠራ ነበር ይባላል። የደጋው ህዝብ ግእዝን በመተው ትግርኛ ቋንቋ መናገረ ሲጀምር ደ’ሞ ‘ትግረ - ትግርኛ’ የሚል አጠራር ተለምዶ ነበር። ‘መረብ ምላሽ’፣ ‘ምድረ ሓማሴን’ እየተባለም ተጠርቷል።

ስሙ በየጊዜው ሲለዋወጥ ነበር።”

“ማንነትህን ስትጠየቅ ምን ትላለህ?”

“ሓማሴን ነኝ እላለሁ።”

አባ ዮሃንስ ሌሎቹንም በተመሳሳይ ሲጠይቅ የተለያዩ ምላሾች መጡ። አንደኛው “ሃበሻ ነኝ” ሲል፤ ሌላው “ዓፋር” አንዱ “መንሳዕ ነኝ” ሲል ሌላው “ሓባብ” አለ። ከመንገደኞች መካከል አንዱ ጥያቄውን በቅጡ ባለመረዳት “ተዋህዶ ነኝ” ሲል ደመደመ። ማንነትና እምነት ላይ ለያይተው ቢያስረዱትም “ተዋህዶ” ከሚለው ሊነቃነቅ አልቻለም። በተንኮል ሃይማኖቱን ሊያስቱት ስለመሰለው አባ ዮሃንስን በጥርጣሬ አጤነ።

“እኔ ቡር ነኝ” አለ ሌላው; “በገድለ ጻድቃንም ቢሆን ቡር ተብለን ነው የምንታወቅ። ’ካዕበ ሶበ ሀለው ሰብአ ቡር ወረስዕም ለእግዚአብሄር ወውእቶሙስ ሰብአ ሀገር ግዙፋነ ክሳድ’ ይላል መጽሃፉ። ቡር የሚለው እኛን ነው።”

ሌላው ተቃወመ።

“ትክክለኛ የመጠሪያ ስማችን ‘ትግረ ትግርኛ’ ነው። ይህም የትግረ እና የከበሳን ሰዎች፣ የባርካን፣ የሰምሃርን ሁሉ ይጠቀልላል።”

ሌላው ደግሞ “በለው ነን። ዋና ከተማችን ስዋኪን ነበረች።” ሲል ሞገተ። “ቡር የሚባል አናውቅም።”

“እኔ አከለ ጉዛይ ነኝ።”

“አከለ ጉዛይ ከመባልህ በፊት ቡር ነበርክ። አከለና ታከለ የሚለው ቃል የመጣው ትናንት ነው። መቶ አመት አይሞላም። ሱባጋዲሽ፣ ማርየና ውብየን ስንመክት ቡሮች ተብለን ነበር የምንታወቅ። ታሪካችንን ማወቅ ያስፈልጋል።”

ሌላው ደግሞ ድምጹን ከፍ አድርጎ ተናገረ፣

“በለው ነን። ከለው መረብን ተሻግሮ ሲሄድ እዚህ በለው ቀረን። ረሳሁት እንጂ አያቴ ዘርዝሮ ነግሮኝ ነበር። እኛ በለው ነን።”

ሸምገል ያለ ሰው ይህንን አባባል ተቃወመ፣

“መሮኒያን ነን። አባቶቻችን እንደነገሩን ፋሉቾ፣ ማሉቅ እና

ጫሉቅ ከተባሉ ጎሳዎች ነው የመጣነው።”

“መሮኒ የት ነው?” ሲል አባ ዮሃንስ ጠየቀ።

“ሓማሴን፣ ባርካ፣ አከለጉዛይ፣ ሳሕል።”

ውይይቱ እየሞቀ ሄደ፣

ግርማቸው የከበደ አንድ ቄስ መናገር ጀመሩ፣

“አባታችን አዳም ሲፈጠር እድሜው ሰላሳ ነበር።” ሲሉ ሁሉም በጸጥታ ማዳመጥ ጀመሩ። አስታራቂ ነገር ካመጡ በሚል ትኩረት አገኙ። እና ቄሱ ቀጠሉ፣ “....እናታችን ሔዋን ደግሞ የአስራ አምስት አመት ኮረዳ ነበረች። አምላክ የደነገልን ህግ ባልና ሚስት በአስራ አምስት አመታት እንዲበላለጡ ነው። ለምሳሌ ልጅ ሲወለድ ወንድ በአርባ ቀኑ ይጠመቃል። ሴት ከሆነች ደግሞ በሰማንያ። ይሄ ለምን ሆነ ካላችሁ?”

ሌላ ሰው ጣልቃ ገብቶ አቋረጣቸው፣

“አባ! እኛ የምናወራው ሌላ ጉዳይ ነው። የኛ አገር ‘ኤርትራ’ ተብሏል። እና እኛ ደግሞ፣ ’ኤርትራውያን’ እየተባልን ነው። ዋናው ነገር ‘እኛ ማነን?’ የሚል ነው።”

ቄሱ መገረም አደረባቸው፣

“ማነው ኤርትራ ያለን?” ሲሉ ጠየቁ።

“ጥልያን።”

“ጥልያን ስለኛ ምናገባው?”

“ገዢያችን ሆኖ የለም እንዴ?”

“አስመራ ገባ ሲባል ሰምቻለሁ። ወደኛ ግን አልመጣም።”

“እርስዎ ከየት ነዎት?”

“ደቀምሓረ።”

“ጥልያን ደቀምሓረን አልፎ ሰገነይቲ ደርሶ የለምንዴ?”

“የሓማሴን ደቀምሓረ ማለቴ ነው።”

“ሓማሴን ላይ ደቀምሓረ የሚባል አገር አለ እንዴ?”

“ከየት የመጣህ ነህ!? የሓማሴን ደቀምሓረ የታወቀ ጥንታዊ አገር ነው። ዓዲተከሌዛን አጠገብ ይገኛል። የታላላቅ ሰዎች መፍለቂያ ነው። ሌላው ቀርቶ ንጉስ ሰምብሩጠስ ተቀምጦባታል።”

“ማነው ሰምብሩጠስ?” ሲል አንዱ ጠየቀ።

“ከየት የመጣህ ነህ!? ሰምቡሩጠስ 24 አመታት አክሱም የነገሰ ነዋ። እንዴት ይህን አታውቅ? የሰምብሩጠስ ሰራዊት ከአክሱም አዱሊስ ሲመላለስ ደቀምሓረ ማረፊያቸው ነበረች። በጽርዕ ቋንቋ የተጻፈ ድንጋይ ተገኝቶባታል። የአገራችን ሰው ሁሉ ተባብሮ ድንጋዩን አጥቦ ልጆች እንዳይጫወቱበት አሳጥሮታል።”

“መቼ የነገሰ ነው ይሄ የሚሉት ሰው?”

“ቀኑን እንኳ እንጃ። ክርስቶስ ከተሰቀለ በሁዋላ ነው።”

“አሁን ወዴት እየሄዱ ነው አባ?”

“ልጄ አግብታ ምጽዋ ነበረች። ወንድ ልጅ በሰላም ተገላገለች። ልጠይቃት መሄዴ ነው። እና ዋናው ጉዳይ ምንድነው? ልጄ ሃያ አመቷ ነው። ባሏ ደግሞ ሰላሳ አምስት። ልክ እንደ አዳምና ሄዋን። ይህን ለማለት ነው። ጥልያን ምን አደረገ ነበር ያልከኝ?”

“ኤርትራ ብሎ ጠራን።”

“ማንን?”

“እኛን ነዋ። አልሰሙኝም እንዴ? ከበሳና መታሕትን።”

“ጥልያን ስለኛ ምናገባው?”

በዚህ ጊዜ ከፍተኛ ሳቅ ሆነ። ሽማግሌው ወዲያው ወዲያው እንደሚረሱ ታወቀ። አባ ዮሃንስ ሳይቀር ድምጽ አውጥቶ ሳቀ።

ውይይቱ እየሞቀ ሄደ።

ሌላው ሌላ ተናገረ።

እያንዳንዱ የየራሱን፣ ከአያቶቹ የሰማውን ገለጸ፣

“የኔ አያቶች የዘር ግንድ ወርዶ ወርዶ - ዘልቆ ዘልቆ ድሩይ ፍጋግ ዘንድ ይደርሳል። ‘ማነው ድሩይ?’ ካላችሁ ባህረ ነጋሲ የነበረ፣ የተከበረ ሊቅ ታላቅ ሰው የነበረ ነው። ከሱ በሁዋላ ቡላ ነግሷል።

ከዚያም ነቢያት፣ ከዚያም አምሓ፣ ከዚያም ቴዎድሮስ ወዲ ቶምቦሳ፣ ከዚያም ይስሃቅ፣ ከዚያም ዑቅባሚካኤል ጠቋሬ፣ ከዚያም ዮሃንስ ሃካይ እነዚህ ተከታትለው ነገሱ። የኔ ዘር ከድሩይ ይጣበቃል።"

የዘር ግንድ ትንተናው ማለቂያ አጣ።

አንዱ ሓማሴን ነኝ ብሎ ሲያበቃ ዘሩን ከአስበሮም ጋር ወስዶ አጣበቀ። "ማነው አስበሮም?" ተብሎ ሲጠየቅ "የአርዓዶም ታናሽ ወንድም" ሲል መለሰ። "ማነው አርዓዶም?" ሲባል ግን ከመመለስ ፈንታ በመደነቅ ሳቀ። እና በኩራት እንዲህ አለ፣

"አርዓዶምን የማያውቅ ታሪክ አያውቅም። አርዓዶም ሓማሴናይ ነው። ከዚህ ሄደው እንደርታን የመሰረቱ አርዓዶምና አስበሮም ናቸው። እምባ አርዓዶም የሚባለው ተራራ ታዲያ በማን ነው የሚጠራው? በቅድመ-ቅድመ አያቴ ስም ነው።"

ሌላው ሌላ አለ፣

"....የማታውቁ ካላችሁ ልንገራችሁ። በምድሪ ባሕሪ አምስት ያህል የአካባቢ ግዛቶች ነበሩ። እነርሱም ታንክሽ፣ በልጅን፣ ባዘን፣ ያርን፣ ቅጣእ ይባላሉ። ታንክሽ ከአስዋን እስከ ባርካ የተዘረጋ ነበር። የበልጅን ማእከል ሳህል የነበረ ሲሆን፤ ሁለት የፊት ጥርሶቻቸውን በማውለቅ ያጌጡ ነበር። በጥንቆላ የሚያምኑ ነበሩ። ያርን እና ቅጣእ በምጽዋ አካባቢ የነበሩ አስተዳደሮች ሲሆኑ፤ ባዘን ከበልጅን ጋር ይዋሰናሉ። በመቀጠል በለው ከለው ከኑቢያ ወደ ኤርትራ በመግባት ነባር አስተዳደሮችን እየዋጠ አጠፏቸው። ከለው መረብን ተሻግሮ ሲሄድ፤ በለው ምድሪ ባሕሪ ቀረ።"

"ቡር ነን" ባዩ አቋረጠው፣ "...ሁላችንም ቡር ነን። ወርስና እዝጊ ይመራን ነበር። ባርካም በለው ነው። ጀዓሊ አሸነፉችሁና ገዛ። አግአዚ ትግረ ይናገሩ ነበር። የተለየ ታሪክ አልነገርከንም። እኔ ያልኩትን ነው የደገምከው።"

"አግዓዚና ትግረን ምናገናኘው?" ሲል አንዱ ተቃወመ።

"ይገናኛል። ለምሳሌ አስመራ ማለት ምንድነው? አስመራ ዓዲ ሳምራ ናቸው። ቡር ነው መነሻው። ዓዲ ሳምራ የሚለውን አሳምራ አሉት። ከጊዜ በሁዋላ አስመራ ሆነ። 'ሴቶች ተሰብስበው መስመር አሰመሩና አስመራ ተባለ የሚባለው ሃቅ አይደለም። እንኳን

በዚያን ጊዜ ዛሬ እንኳ ሴቶች ብቻቸውን ተሰብስበው አይመክሩም።"

ሁሉም የሚያውቀውን እንዳመጣለት ተናገረ፣

"....አስመራ ላይ እነማን ነበሩ? ገዛ አስመኣ፣ ገዛ ጎረቶም፣ ገዛ ሸለለ፣ ገዛ ስርስር የሚባሉ ነበሩ። እጣ ተጣጥለው በአራት አግጣጫ ሰፈሩ። ደብረ ጽዮን ቅድስት ማርያምን በሳር ህድሞ ገንብተው ሲያበቁ የጸሎት ቦታቸው አደረጓት። ደብሩ ላይ 'ዘታቦተ አርባዕተ አስመራ ምስለ አህጉራ' የሚል አሰፈሩ።"

አንድ አዛውንት በቀሰስተኛ ድምጽ አብራሩ፣

"ስለ አርባዕተ አስመራ ታሪኩ እንዲህ ነው። አራቱ መንደሮች ልጆቻቸውን ለመጠበቅ ውል ፈጸሙ። ወደ አንዱ መንደር ባርያ ፈንጋይ ብቅ ካለ ወይም አንድ ችግር ከመጣ ሴቶች ጩኸት ያሰማሉ። ለአቅመ ውጊያ የደረሱ የሶስቱ መንደር ወንዶች ድምጹን ወደሰሙበት መንደር በመገስገስ የመጣውን ጠላት ያሳድዳሉ። 'አርባዕተ አስመራ' የሚለው ቃል ከዚህ ጊዜ ነው የጀመረው,..."

"ጉዳዩ መች እሱ ሆኖ" ሲል ሌላ አዛውንት ጣልቃ ገባ፣ "...ሓዮ ሕረት፣ ሰምዓሰም፣ ዳምባ ምጭ፣ ዓዲ ግረቶም፣ ዓዲ መንጎቲ፣ ዓዲ ሰረንታይ፣ ዓዲ ሓብሽ፣ ዓዲ ባሮ፣ ደቐ ሸመር..."

በዚህ ጊዜ ሌላው አቋረጠ፣

"ሸመር ኣድግ የእናቴ አገር ነው። እወለድበታለሁ። ደቐ ሸመር ስትል ሸመር ዓድግ ማለትህ ነው ወይስ ሌላ?" ሲል ጠየቀ።

አንዳንድ ሰዎች በጣም ሳቁ።

የሳቁበት ምክንያት በትግረ ቋንቋ "ሸመር ኣድግ" ማለት "የአህያ ብልት" ማለት ስለነበር ነው። የገባው ላልገባው እየነገረ ሳቁ ሲተረተር ከቆየ በሁዋላ፤ ተናጋሪው ለጥያቄው መልስ ሳይሰጥ እንዳጀማመሩ ወጉን ቀጠለ፣

"...ዓዲ ቐ ተኹላ፣ ዓዲ ጋውል፣ ሃዘጋ፣ ጸዓዘጋ፣ ዓዲ ሹም አንዱ፣ ዓዲ ኢታይ፣ አዶሌ፣ አዱሊስ ምንጩ አዶ-ሌ ነው። በሳሆ ቋንቋ 'ነጭ ውሃ' ማለት ነው። ተለውጦ አዱሊስ ተባለ።"

ድብልቅልቅ እያለ ሄደና መግባባት ተቸገሩ።

ከመሮኒ ማሉቅ፣ ፋሉቾ፣ ጫሉቾ እስከ በለው ከለው፣ ከቆላው እስከ ደጋ፣ ከዳንከልያ እስከ ሳህል ሲነጋገሩ ልዩነትም አንድነትም ነበራቸው። ሁሉን አጣምሮ የሚይዝ ማንነት ግን አልነበራቸውም። የነሳቸው ስም ሲነሳ አጥብቀው ይሞግታሉ። ከማዳመጥ ይልቅ ከአባት ከአያት የሰሙትን አንቀው ይዘው ይሞግታሉ። ሙግታቸውን ጥቂት ከቀጠሉ ጎራዴ ለመምዘዝ የተቃረቡ እስኪመስሉ ደም ስራቸው ይገታተራል። ይቆጣሉ። ንዴታቸው አፍንጫቸው ጫፍ ላይ ተንጠልጥላ እንደ ተለኮሰ ክብሪት ስትነድ ትታያለች።

አባ ዮሃንስ አንድ ግልጽ የሆነለት ጉዳይ የመረብ ምላሽ ሰዎች “ምድሪ ባሕሪ” ከሚለው የወል ማንነት ስማቸው ይልቅ ከበቀሉበት “ዓዲ” ወይ “ነሳ” ጋር ይበልጥ የተቆራኙ መሆናቸውን ነበር። ማስታወሻው ላይም ይህንኑ አሰፈረ።

አባ ዮሃንስ ከሃይማኖት አባትነቱ ይልቅ ፍልስፍና እና የፖለቲካ ጉዳዮች ይስቡታል። ከዚህ ባሻገር በውስጡ የተደበቀ ፍላጎቱ ወደ ሩቅ ቦታዎች መጓዝ ነበር። ቄስ እሆናለሁ ብሎ ያሰበበት ጊዜ አልነበረም። ቄስ የሚሆኑ ልጆች የሚያሳዩት አይነት ዝንባሌም አልነበረውም። መለስ ብሎ የህይወት መንገዱን ባሰበ ቁጥር በደረሰበት ደረጃ በጣም ይደነቃል። በአንድ አጋጣሚ ይህን መንገድ ያዘ። በአንድ ቀን ድንገተኛ ውሳኔ ሰማያዊው ሰረገላው ላይ ተሳፈረ። የመጨረሻውን ቃለ መሃላ እስኪፈጽም ድረስ ግን የጀመረውን ስለመቀጠሉ እርግጠኛ አልነበረም። ያም ሆኖ የሚቆጭበት ነገር የለም። አዲስ ነገር የማወቅ ዝንባሌውን፤ በተለይም በአፍሪቃ ቀንድ እየፈጸመ ያለው አሰሳ የውስጥ ፍላጎቱን ያረካለታል። ቀዳሚ ፍላጎቱ የነበረው ፖለቲካና ፍልስፍና በመንገዱ ላይ ጣልቃ እየገባ ከመስመሩ ቢያስወጣውም፤ የእምነት አባትነቱን ከአለማዊ ህይወት ጋር እያዋሃደ መጓዝ ችሏል። በተለይ በንግግሮቹ መካከል ጣልቃ እየገቡ ለሚያስቸግሩት አሳቦች ቅዱስ የማሰሪያ ቃል እያበጀ ተጉዟል።

በጊንዳዕ አዳራቸውም እንዲሁ የአካባቢው ሰው ሊገነዘበው ስለመቻሉ ብዙም ሳያስብበት ይናገር ነበር። እንዲህ አለ፣

“ዘመን ያመጣው ነው። አምላካችን ሲፈጥረን ድንበር አላበጀም። ለምሳሌ ከአዳምና ከሄዋን ቀጥሎ የተፈጠረውና ህይወት

የዘራው እባብ ነበር። አባታችን አዳም ተመን ብሎ ጠራው። እባብ ግን ስሙ ‘ተመን’ እንደተባለ አላወቀም። በምድር ላይ በህይወት ለመኖር የመጠሪያ ስም አያስፈልግም። የሰው ልጆች ግን ስለ መጠሪያ ስም አጥብቀው ይጨነቃሉ። በዚህ ምክንያት አለማችን በጦርነት ተሰቃየች። ወደ ጦርነት መግባት ቅዱስ አይደለም።”

ዝግ ብሎ ቀጠለ፣

“ሰዎች በምድር ሲኖሩ ቡድን አቋቋሙ። በሃይማኖት፣ በዘር፣ በቀለም ተባደኑ። ለአሰልቺው ረጅም እድሜያቸውም ማጣፈጫ ፈጠሩ። በቀድሞ ጊዜ የሰው ልጅ የዱር አራዊት ቁርስ ከመሆን ለማምለጥ ሲሮጥ ስለሚውል ህይወቱ ማጣፈጫ ነበራት። ሲሮጥ የዋለ ሰው ሲመሽለት ተዘረጋግቶ ከመተኛት በቀር የማሰቢያ ጊዜ አልነበረውም። የዱር አራዊትን መቋቋም ከቻለ በሁዋላ ግን የሰው ልጅ ርስበርሱ በመጋጨት ማጣፈጫውን ቀየረ። ጦርነት መጣ። የጦርነት ምሬቱ ሲበዛበት ‘ጨዋታ’ የሚባል ስሜት ማርኪያ ፈጠረ። ሁለት ሰዎች ሲፋለሙ እያየ የማሸነፍ ጥሙን ያረካ ጀመር። ይሄ ‘ጨዋታ’ ሲሰለቸው ግን ወደ ጥንታዊ ማጣፈጫው መለስ ቀለስ ማለቱ አልቀረም። ይህ የአምላክን ጸጋ ያለማወቅ ነው።“

እስኪተኙ ድረስ ብዙ ተጨዋወቱ።

በተለይም የማንነት ጉዳይ ላይ ውይይታቸው ደመቅ አለ። አቢሲንያውያን ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ‘ኢትዮጵያ’ የሚለውን የማንነት ስም እንደ መጠሪያቸው እየለመዱት መሄዳቸውን አባ ዮሃንስ አነሳ። የተዋህዶ እምነት ተከታዮች በአብዛኛው ‘አበሻ ነኝ’ እንደሚሉ ገለጸ። የመረብ ምላሽ ከበሳም በተመሳሳይ እንደ አቢሲንያውያን ‘ሃበሻ ነኝ’ ይላል። ሃበሻ የሚለው ቃል ራሱ ግን የሌላ ነው። ስለተለመደ ግን የማንነት መገለጫ ሆነ።

የማንነት መታወቂያ ለመሆን የሚበቁ ስሞች በአጋጣሚ የሚፈጠሩ እንጂ በስምምነት የሚገኙ አለመሆናቸውን አባ ዮሃንስ አጫወታቸው። ፈረንሳይ የቀድሞ ስሟ Gaul እንደነበር፤ France የሚለው ቃል ከላቲን እንደመጣ ጠቀሰ። ኢንግላንድ Angle Land የሚለው ቃል “የመላእክት አገር” ማለት መሆኑን፤ እንግሊዞች በመካከለኛው ዘመን ከአንጀሊን ወሸመጥ ከባልቲክ ባሕር አካባቢ

ተነስተው ወደ ደሴቷ እንደሄዱ አጫወታቸው። አባ ዮሃንስ የተለያዩ የአውሮፓ አገራትን ስም እየጠቀሰ እንዴት ስማቸውን ለማግኘት እንደበቁ በሰፊው አወጋ።

... እንዲህ ያሉ ወጎችን እያወጉ አመሹ።

አባ ዮሃንስ ከመተኛቱ በፊት ማስታወሻ የመያዝ ልምድ ነበረው። ውሎውን ያሰፍራል። በሃይማኖት አባትነቱ ምክንያት ከአንደበቱ ሊያወጣቸው ያልቻላቸውን አሳቦች ለማስታወሻ ደብተሩ ይመግባታል። በዚያን ቀን ለከበቡት ሰዎች ሊናገር አስቦ የተወውን በማስታወሻ ጥራዙ ላይ እንዲህ ሲል አሰፈረ፣

“ከምድር እንስሳት መካከል ሰዎች ከሌሎች እንስሳት በተሻለ መልኩ ማሰብ ስለቻሉ ከሌሎች ፍጥረታት የተለዩ መሆናቸውን አመኑ። የአገር ስምና የመጠሪያ ስም ያልነበራቸው ሰዎች የትም ቦታ በምድር ላይ ይኖሩ እንደነበር ረስተው ልዩ መጠሪያ አስፈለጋቸው። እና የሰው ልጆች በጊዜ ሂደት ቃል መፍጠር ቻሉ። ‘ቃል ይቀድማል ወይስ ፍጡር?’ የሚለው በርግጥ ያከራክራል። ከዚህ ሁሉ በሁዋላ ግን እንደገና በጊዜ ሂደት ከሰዎች መካከል ‘የተሻልን ሰዎች ነን’ የሚሉ ሰዎች ብቅ ማለት ጀመሩ።

“...የሰው ልጅ የማሸነፍ ፍላጎት ለአለም ጥፋት ሆኖ ኖረ። የሰው ልጅ ሲርበው ሞትን ለማሸነፍ ይታገላል። ሲጠግብ የሌላውን ህይወት ለማጥፋት ይተጋል። በርግጥ ይህን የሚያደርገው የሰው ልጅ ብቻ አይደለም። ዛፍ እንኳ በስሩ የሚበቅሉትን ተመሳሳይ እጽዋት እየበላ ያጠፋል። የተፈጥሮ ህግ ነው። ራሱን ለመተካት ሲል ህይወት ሌላውን እየበላ ራሱን እየተካ ይጓዛል።”

ምእራፍ 7

የአስመራ ፖለቲካ
የምስጢር ቀጠሮ - ዘመኑን ተሻግሮ

ከምጽዋ የመጡ ሶስት እንግዶች በጫካና በወንዞች መካከል እያቆራረጡ ማይጮኾት ከተባለ መንደር ሲደርሱ ከሚፍለቀለቅ ምንጭ ዳርቻ የተተከለ ግዙፍ ሰማያዊ ድንኳን ጠበቃቸው። ዓርበረቡዕ ላይ ተቀብለዋቸው ሲያበቁ፤ እየገሰገሱ የመጡት ፈረሰኞች ድንኳኑ ደጃፍ ላይ ቆሙ። በዚህ ጊዜ ከሰማያዊው ድንኳን ውስጥ ትከሻው ላይ አንፋሮ የደፋ ሰው ብቅ ብሎ እንግዶቹን በሞቀ ፈገግታ ተቀበላቸው። ይህ ሰው ደጃዝማች ባህታ ሓጎስ ሲሆን፤ እንግዶቹ ደግሞ አንድ ፈረንሳዊ የካቶሊክ ቄስ እና ሁለት ወላጅ አልባ የሓልሓል ቦጎስ ማቲዎች ነበሩ።

በአሸከሮች ሽርጉድ ከድንኳኑ ደጃፍ ላይ በተዘጋጀላቸው መከዳ ላይ አርፈው ፊታቸውንና እግሮቻቸውን ታጠቡ። በኬሻ አሸዋ ውስጥ ተቀብሮ የቀዘቀዘ ውሃ ተጎነጩ። በማከታተል የፍየል ጥብስና የአጃ ሾርባ ቀረበላቸው። ገና ተመግበው ሳያበቁ የጀበና ቡና ተጀመረ። ማለትም በተጉተረከከው የምድጃ ከሰል ላይ ቡና ይቆላ ጀመር። ምርጥ የኢጣሊያ ቪኖ ወረደ። የቆላ ንቦች ከግራዋ አበባ ከቀመሙት ማር የተዘጋጀ ጠጅ ቀረበ። ከቄሱ ጋር በእንግድነት የመጡት ሁለት ማቲዎች ግን ከአካባቢው ልጆች ጋር ይጫወቱ ዘንድ በሰርዶ በተሸለመው መስክ ላይ ተለቀቁ።

እንዲህ ተበልቶና ተጠጥቶ እንዳበቃ፤ ደጃች ባህታና አባ

የሃንስ ኩልቦ በግል ቆይታ ለማድረግ ወደ ደንኳኑ ውስጥ ዘለቁ።

ከጥቂት ጸጥታ በሁዋላ አባ የሃንስ መናገር ጀመረ፣

“አንድ ጉዳይ ልነግርህ እፈልጋለሁ።”

ቄሱ ፉታ ወስዶ ቀጠለ፣

“በቅድሚያ ግን ከፈረንሳይ አገር ስጦታ አምጥቼልሃለሁ።”

የእጅ ቦርሳውን በመክፈት የተጠቀለለ እቃ አውጥቶ ሰጠው። ባህታ ከፍቶ ሲያየው የሩቅ መመልከቻ ወታደራዊ መነጽር አይኑ ላይ አብረቀረቀበት። ባህታ በመደነቅ አገላበጠው። የሩቁን አቅርቦ ስለሚያሳይ መነጽር ቢያውቅም የራሱ ኖሮት አያውቅም።

አባ የሃንስ ፈገግ ብሎ ቀለደ፣

“እንደኔ ካለ ሰው የሚጠበቀው ስጦታ መስቀልና መጽሃፍ ቅዱስ ነበር። እንዲህ ያለ ስጦታ መስጠት የተለመደ አይደለም። እቃው ግን ላንተ ጠቃሚ ነው። የሩቁን መመልከት ላለበት ራሱን ለሚያከብር ሰው ይገባል። እንድትጠቀምበት ነው ያመጣሁልህ።”

ደጃች ባህታ በቄሱ ቅኔያዊ አነጋገር እየሳቀ ስጦታውን በከፍተኛ አክብሮትና በማመስገን ተቀበለ። እና ስጦታውን መልሶ በመጠቅለል መከዳው ላይ አስቀመጠው። ከዚያም ግንባሩን ቅጭም እንዳደረገ ቄሱ ሊነግረው የፈለገውን ጉዳይ ለመስማት ጠበቀ፣

አባ የሃንስ የረዘመ ጢሙን እየነተተ ጥቂት ከተከዘ በሁዋላ በደከመ ድምጽ መናገር ጀመረ፣

“ጉዳዩ ከበድ ሊልብህ ይችላል። ባልነግረው ይሻላል ብዬ አስቤ ነበር። ውሎ አድሮ ማወቅህ ስለማይቀር ግን ከወዲሁ ለሚሆነው ነገር ራስህን ብታዘጋጅ ይሻላል በሚል በመጨረሻ ልነግርህ ወስኛለሁ። የአምላክ አገልጋይ እንደመሆኔም እውነትን መናገር ግዴታዬ ነው።”

አባ የሃንስ አቀርቅሮ ጥቂት ካሰላሰለ በሁዋላ ቀና አለ፣

“ኢጣልያውያን በሁለት ትውልድ ጊዜ ሁለት ሚሊዮን ዜጎቻቸውን እዚህ አገር ለማስፈር ወስነዋል። ይህንን አጥንቶ ያቀረበላቸው ፍራንኬቲ የተባለ ዜጋቸው ነው። እዚህ አገር ሲመላለስ

ሰንብቷል፤ ሳታውቀው አትቀርም። የደጋውን መሬት ሁሉ እየዞረ አጥንቷል። ከወዲሁ ግለሰቦች የእርሻ መሬት በየቦታው እየያዙ ነው። ዋና አሳባቸው ግን ማስፈር ነው። የመጀመሪያዎቹ የሙከራ ሰፋሪዎች ከልጆቻቸው ጋር በቅርቡ መግባት ይጀምሩ ይሆናል። የታሰበላቸው ቀዳሚ የሰፈራ ቦታ ኩዶፈላሲ መሆኑን ሰምቻለሁ።"

ባህታ ሓነስ ፈገግ ሲል ጥርሶቹ የሙብረቅ ብልጭታ መሰሉ። መደነቁና መደንገጡ እየታየ ሳያስበው እጁን ጎራዴው ላይ አሳረፈ። ለጥቂት ሰከንዶች ዝምታ ሆነ። ባህታ ትክ ብሎ አባ ዮሃንስን ያስተውል ገባ። ከቁሱ አንደበት የሰማው ጉዳይ ምን ማለት እንደሆነ ለመረዳት ጊዜ አልወሰደበትም። የሚንቀጠቀጥ እጁን ከጎራዴው ላይ አነሳና በረጅሙ ተነፈሰ። እና የተሰማውን ስሜት አምቆ ጥያቄ ጣለ፣

"እነሱ መሬታችንን ሲይዙ ለኛ ምን አስበውልናል?"

አባ ዮሃንስ በቀልድ መልክ መለሰለት፣

"አይገድሏችሁም። በዚህ የሚያሰጋ ነገር የለባችሁም። ሰላማዊ እስከሆናችሁ ድረስ ይፈልጓችሁዋል። ቁጥራችሁ እንዲበዛም ይፈልጋሉ። የኢጣልያን Nationals አምጥተው እዚህ ሲያሰፍሩ፤ በእጥፍ የሚሆን አገልጋይ Indigenous መፈለጋቸው አይቀርም። የመረብ ምላሽ ሰው ቁጥሩ ትንሽ ነው። 200 ሺህ አትሞሉም። ሁለት ሚልዮን የኢጣልያ Nationals እዚህ መጥተው የሚሰፍሩ ከሆነ እናንተ ቢያንስ ቁጥራችሁ አሁን ካለው በአራት በአምስት እጥፍ እንዲጨምር ይፈልጋሉ። ወንዶቹን ለወታደርነትና ለጉልበት ስራ፤ ሴቶቹን ደግሞ ለጽዳት ስራ እና ለፋብሪካ ቀላል ስራዎች ይፈልጓቸዋል። ስለዚህ እንድትባዙ ያደርጋሉ እንጂ አያጠፏችሁም። በቀጥታ ለመናገር አንድ ገበሬ ስጋ ለማምረት ሲል በጎች እንደሚያረባው፤ እናንተም ለኢጣልያ ጥቅም ሲባል መራባታችሁ አስፈላጊ ይሆናል።"

ባህታ ድምጽ አውጥቶ ሳቀ። ሳቁ ተኩስ መሰለ።

አባ ዮሃንስ ቀጠለ፣

"ህዝቡ እንዳያምጽባቸው ግን አንተን የመሰለውን እየለቀሙ ያስወግዳሉ። አንተና የአንተ አይነት ሰዎች ከመንገድ ጠራጊነት ያለፈ

ሚና አይኖራችሁም። በካፍል ጎፋር ጀምረውታል። አንድ ባንድ እያነቁ ናኹራ ይልኳችሁዋል። መጪው እውነት ይሄ ነው።"

ድምጹን ዝቅ አድርጎም እንዲህ አለ፣

".....ዛሬ እኔና አንተ እዚህ ምን እንደተነጋገርን ጣልያኖች ለማወቅ መፈለጋቸው አይቀርም። ዋናው የተነጋገርንበት ጉዳይ ዓዲ ቀይሕ ላይ ለቤተክርስትያን መስሪያ የሚሆን ውሃ ገብ መሬት እንድታፈላልግልኝ መማጸኔ ነው። ይህንኑ ሳይጠይቁህ ቀድመህ ራስህ ንገራቸው። ለነገሩ መሬት ማግኘቱንም እፈልገዋለሁ። እንግዲህ የሰማኸውን ሰምተሃል። ማድረግ ያለብህን አንተ ታውቃለህ። ልጄ ነህና ወደ ናኹራ ደሴት መላክህን መስማት አልችልም። ጠባይህን ሳትቀይር ማድረግ ያለብህን በርጋታ አስብ። ከምታምናቸው የአገርህ ሰዎች ጋር ጊዜ ወስደህ ምክርበት። የሚደረገውንም በንቃትና በእውቀት ተከታተል።"

የብፆ ውይይታቸው አበቃ።

እንደገና ደጁ ላይ ግብዣው ቀጠለ። ልጆቹ ከአባ ዮሃንስ አጠገብ እንዲቀመጡ ከተደረገ በሁዋላ እርጎ ቀረበላቸው። በወግ መሃል ባህታ ስለ ልጆቹ ማንነት መጠየቁ አልቀረም። አባ ዮሃንስ ልጆቹን ከየት እንዳገኛቸው ከነገረው በሁዋላ እንዲህ አለ፣

"አባታቸው ሳይሸፍት አልቀረም። የቦጎስ ሰው ነው። ብፆ ያልተረጋገጠ ወሬ ነው። ምናልባት ስለዚሁ ሰው ወሬ ከሰማህ አሳውቀኝ። ኑረነቢ በኺት ይባላል። የፋና ጭቃ ሹም የነበረ፤ ብሌን ከጣውቀ ወገን ነው።"

ኢጣልያውያን እንግዶች የመጠጥ ጠርሙሶች ይዘው በመምጣታቸው የባህታ ድንኳን ሞቃ ደምቃ አመሸች። እኩለ ሌሊት አልፎ ጭምር በሚዥመለመል የግንዲላ እሳት ዙሪያ ከበው "ኤርትራ" የሚል ስያሜ ስለተሰጣት አዲስ አገር፣ እንዲሁም የአውሮፓን የወቅቱ ትኩስ አጀንዳዎች እያነሱ ተጨዋወቱ።

በነጋታው አባ ዮሃንስ ባህታን ተሰናብቶ ካምፖ ቺታቶ በመሄድ ለመሰንበቻው ድንኳን ተከራየ። አስመራ የመቆየታቸው ዋና አላማ ለካቶሊክ ቤተክርስትያን መስሪያ የሚሆን መሬት መምረጥ ሲሆን፤ እግረመንገዳቸውን ደግሞ ወንድሟን ፍለጋ ከምጽዋ ከወጣች

በሁዋላ እንደወጣች የቀረች የልጆቹን አክስት ማፈላለግ ሲሆን፤ ጥቂት ሳምንታት አስመራ መቆየታቸው ግድ ነበር።

* * *

ከጥቂት ወራት በፊት ኢጣልያ አስመራን ስትቆጣጠር አስመራ "ከተማ" ተብላ ለመጠራት የምትበቃ አልነበረችም። ሶስት መቶ ህድሞዎች የቆሙባት የገጠር መንደር ነበረች። በርግጥ ለአካባቢው ገጠሮች የገበያ ማእከል መሆኗን አረጋግጣ ነበር። በተጨማሪ በደረጃው ከፍ ያለ የማርያም ደብር መትከል ችላለች። ጣልያን ኤርትራን ሲቆጣጠር በከተማ ደረጃ ያገኛት ምጽዋን ብቻ ሲሆን፤ ሌሎቹ መንደሮች ዘመናዊ ቤቶች ያልነበራቸው፤ መንገድ ያልተቀየሰላቸው የገጠር ከተሞች ነበሩ።

በ15ኛው ክፍለዘመን በጀስዊታዊው አልቫሬዝ የተነበኘችውና ስሟ በየመጽሃፉ ተደጋግሞ የምትጠቀሰው፤ አብርሃም ሃኒባል የተሸጠባት ድባርዋ እንኳ ተራ የገጠር መንደር ነበረች። ከድባርዋ ቀጥሎ በወቅቱ ገናና ስም የነበራቸው እነ ዓዲ ተክላይ፣ እነ ሃዘጋ እነ ጸዓዘጋ በድንጋይ ተገንብተው ውስጣቸው በእበት በተለቀለቀ ህድሞዎች የተሰሩ ነበሩ። የተሻለ የስነህንጻ ጥበብ የሚታይባቸው እንደ ደብረዳሞ ያሉ ገዳማት፤ ከደመና በላይ የተንሳፈፉ የሰማይ ላይ ደሴቶች ነበሩ።

የአስመራ መስክ ለአይን እስኪታክት በሳር ተሸፍኗል። በሳር ውስጥ የሚሸሎኮሎኩ ጥንቸሎች ማለቂያ የላቸውም። ወደ ምጽዋና ወደ ከረን መሄጃው በአንጻሩ የተጠቀጠቀ ዱር ነበር። አነስተኛ ወንዞች እየተሰባጠሩ ይፈሱባታል። ማይ ተመናይ፣ ማይጮኾት፣ ማይ በላ፣ የምንፈጭቹ መፍለቂያ ናቸው። በአስመራ ዙሪያ ያሉ ኮረብቶች በአበቦች የተሸፈኑ ነበሩ። ሽታቸው የሚያውድ ቅጠሎች በኮረብቶቹ ላይ ሞልተዋል። መድሃኒት ቀማሚዎች በአስመራ ኮረብቶች ላይ ውለው ያድራሉ። በተለይም አገር ጎብኚዎች ወደ አስመራ ብቅ ሲሉ ኮረብቶቹን ሳይጎበኙ አይመለሱም።

ጣልያን አስመራን እስኪቆጣጠር ድረስ በዱር የተሸፈነው የአስመራ ዙሪያ ለነዋሪዎች የስጋት ምንጭ ሆኖ ኖሯል። ከጫካው እየተመዘዙ የሚመጡ አውሬዎችን መቋቋም ቢችሉም ባርያ

ፈንጋዮች ግን ከቁጥጥር ውጭ ነበሩ። ከባሕር አግጣጫ እየመጡ በእረኝነት ላይ ያሉ ልጆችን አፍነው ወደ ጫካው ይሸሻሉ። ከዚያ በሁዋላ የሚያገኛቸው የለም። ሲጓዙ አድረው ሲነጋ ጀልባቸው ላይ ይደርሳሉ። በመሆኑም የአስመራ አባወራዎች ልጆቻቸውን ከሁለት ነጣቂዎች የመጠበቅ ሃላፊነት ነበረባቸው።

በርግጥም አስመራ በአቀማመጧ ለመረብ ምላሽ ማእከላዊና ምቹ የመገናኛ ቦታ ነበረች። የገበያ ቦታ ሆና ለማደግ ጊዜ አልወሰደባትም። ከያቅጣጫው የሚመጣ ሁሉ ማረፊያው አርባዕተ አስመራ ሆነ።: ውሃ እንደልብ ነው። አገሩ ከአመት አመት ለምለም ሲሆን፤ ለፈረሶች ምቹ ነው። ባለ በቅሎች፣ ባለ ግመሎች፣ ባለ አህዮች አስመራ ለመሰንበት አይቸገሩም። መተላለፊያና መገበያያ ቦታነቷ እውቅና እያገኘ ፖለቲከኞችና ሰላዮች ወደ አስመራ ብቅ ማለት ጀምረዋል። እምብርትነቷ ገና መንደር ሳለች ታወቀ።

የኢጣሊያ ሰራዊት አስመራ እንደገባ ቦታ እየመረጠ ሰፈረ። በቤት መኻእና በጸጸራት እንዲሁም በሌሎች ቦታዎች ተበታትኖ ሰፈሩን ተከለ። ገና ከመድረሱም በአፈርና በኮረት ሁለት መንገዶችን ቀይሶ ገነባ። በፈረስና በበቅሎ የሚጎተቱ ሰረገላዎች በአዲሶቹ መንገዶች ላይ መታየት ጀመሩ። አስመራ ላይ አዳዲስ መንደሮችና ስሞች መሰማታቸው በፍጥነት ቀጠለ።

ጆንዮ የተባለ የኢጣልያ የሰራዊት መሪ ያረፈበት ቦታ ገና ድሮ “ቪላጆ ጆንዮ” እየተባለ መጠራት ጀምሯል። ቪላጆ “መንደር” ማለት ነበር። ፈረሰኞች የሰፈሩበት ዓዲ ተለሪያ ሲባል፤ ፓራዲዞ ዝነኛ ሰፈር ለመሆን ጊዜ አልወሰደበትም። “ፓራዲዞ” በኢጣሊያ ቋንቋ “ገነት” ማለት ነው። እምባ ጋልያኖ ሌላ ሰፈር ሆነ። ጋልዮኖ የጣሊያን የጦር መሪ ነው። የኢጣልያ 77ኛ ክፍለ ሰራዊት የሰፈረበት “ሰታንታ ሰተ” ሲባል፤ 78ኛው ክፍለሰራዊት ያረፈበት ደግሞ ሰታንታ ኦቶ ተሰኘ። የሮማን ካቶሊክ ዋና ቤተክርስትያኗን ለመገንባት የወሰደችውን መሬት ተከትሎ አንድ ሰፊ ጥርጊያ ተቀደደ። በመንገዱ ዳርቻ ዋና ዋና ተቋማት መሬት ተሻሙ። ዙሪያው ታጠረ። ጄኔራል ባልዲሴራ ያሳጠረው ይህ ቦታ በግንብ የታጠረ ካምፕ (ካምፖ ቺታቶ) ተባለ። ሁዋላ “ኮምቢሽታቶ።”

ኢጣሊያ መረብ ምላሽን ይዞ “ኤርትራ” የሚል ስያሜ

ከሰጣት በሁዋላ በአውራጃዎች ከፋፍሎ ያስተዳድራት ጀመረ። ሰባት የኤርትራ ከተሞች ማለትም አስመራ፣ ከረን፣ ደቀምሃረ፣ መንደፈራ፣ ዓዲቀይሕ፣ ምጽዋና አሰብ በመዘጋጃ ቤት እንዲተዳደሩ አደረገ። እነዚህን ከተሞች የሚያስተዳድሩ ፖሊስታ እየተባሉ የሚጠሩ ከንቲባዎች ተሾሙላቸው። ግብር የመሰብሰቡን ስራ ግን በአንዳንድ መሳንፍቶች ያሰራሉ። ምስለኔ፣ ጭቃ፣ ደግሊል፣ ናይብ ናዚር እያሉ በመሾም ተጠቀሙባቸው። የኤርትራ ዋና ከተማ ለመሆን የበቃችው አስመራም በጥቂት ወራት ውስጥ ማበብ ጀመረች።

* * *

በዚያው ሰሞን አባ ዮሃንስ ኮምቢሽታቶ ከተከራየው ድንኳን ደጃፍ ላይ ከሁለቱ የአደራ ልጆቹ ጋር ቁርስ በመመገብ ላይ ሳለ አንድ ደንዳና ወጣት፤ ሰርዶውን እያስተኛ በከፍተኛ ፍጥነት በፈረስ እየጋለበ ሲመጣ በሩቅ ተመለከተው። ማንነቱን ለመለየት በማይቻልበት ርቀት ላይ ቢሆንም ፈረሰኛው ጊላጊዮርጊስ እንደሆነ አባ ዮሃንስ አልተጠራጠረም። በርግጥም አንድ ደቂቃ ሳይሞላ ጊላጊዮርጊስ ፈረሱን ከአንድ የወይራ ዛፍ ላይ አስሮ በፍጥነት ወደ ቄሱ አመራ። እና ተጣድፎ የመጣበትን ምክንያት አበሰረ፣

“አባ ዮሃንስ! መልካም ዜና አለኝ። መርያም ተገኝታለች።”

የአባ ዮሃንስ በጢም የተሸፈነ ፊት በፈገግታ ደመቀ። ሁለቱ ልጆችም እንዲሁ በተመሳሳይ ፈረሰኛው ላይ በጉጉት አተኮሩ።

“የት ተገኘች?”

“አቦይ ተወልደ ከሚባሉ ሃብታም ገበሬ ቤት እያገለገለች ነው። ሰምበል አካባቢ ከብቶች፣ ፍየሎችና ዶሮዎች ያረባሉ። አቦይ ተወልደ ሃይማኖት ለውጠው የሰንበት ጸሎታቸው ከስዊድናውያኑ ጋር በለዛ ነው ይባላል። ሌላው ደግሞ....”

አባ ዮሃንስ አቋረጠው፣

“በትክክል እሷ መሆኗን አረጋግጠሃል?”

“እንደነገሩኝ ከሆነ ራሷ ናት። አብረን ብንሄድ ይሻላል ብዬ በቀጥታ ወደዚህ መጣሁ። አሁኑኑ መሄድ እንችላለን።”

ቁርሳቸውን በልተው እንዳበቁ አባ ዮሃንስ ፈረሶቹ እንዲጫኑ አዘዘ። የቄሱ አገልጋይ ፈረሶቹን ለመጫን በሚጣደፍበት ደቂቃ ጊላጊዮርጊስ መርየምን እንዴት ሊያገኛት እንደቻለ በስሜት እያጋነነ በመተረክ ላይ ነበር። አቦይ ተወልደን በተመለከተም በአንድ ቀን ጊዜ ውስጥ የቃረመውን እንዲህ ሲል አወጋ፣

“አቦይ ተወልደ ከሃዘሞ ናቸው። የባህረ ነጋሲ ጭሩም ጻዕዱ የታላቅ ወንድማቸው ልጅ ናቸው። ባለቤታቸው ጽገወይኒ ትባላለች። ሁለት ልጆች ወልደዋል። የበኩር ልጃቸው ያዕቆብ 14 አመቱ ነው። ሰገን ተወልደ ገና ስምንት ነበረች። ሌላ አልወለዱም። ይህን ሁሉ ሃብት ይዘው አምላክ ልጅ በደላቸው። የውጭ አገር ሰዎች አስመራ ሲመጡ የአቦይ ተወልደ ቤት ማረፊያቸው ሆኗል። ሪሶ አንቶኒ እና ሉዊጂ ቶርቴሊ አቦይ ተወልደ ቤት ነበር ያረፉት። ዋና ወዳጃቸው ሙንዚንገር ነበር አሉ። የጓሮ አትክልት ማልማት ያሳያቸው ሙንዚንገር ነው። የተለያዩ የጓሮ አትክልቶች ያበቅላሉ። ካሮት፣ ቲማቲም፣ ጥቅል ጎመን፣ ዝርግ ጎመን፣ ድንች፣ ነጭ ሽንኩርት፣ ቀይ ሽንኩርት፣ ቃሪያ . . .”

ግማሽ ሰአት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ሶስት ፈረሶች በሰርዶ የተሸፈነውን ሜዳ እየሰነጠቁ ወደ ሰምበል አግጣጫ ገሰገሱ። ጊላጊዮርጊስና አገልጋዩ ልጆቹን አፈናጠጧቸው።

በመንገዳቸው ላይ አባ ዮሃንስ እንዲህ አለ፣

“ለመሞከር ያህል እንጂ ተስፋ አላደረግሁም ነበር። መገኘቷ ጠቃሚ ነው። ምናልባት ስለአባታቸው የሰማችው ነገር ይኖራል።”

እኩል ሰአት ያህል በዝግታ እንደተጓዙ ከሁለተኛው የአስመራ የገበያ ማእከል ደረሱ። በሶስት ግዙፍ ዋርካዎች መካከል ከሚገኘው ገበያ ላይ ብዙ ህዝብ ተሰብስቦ በማየታቸው አባ ዮሃንስ ሉጋም ያዘ። እና ከፈረሶቻቸው ወርደው ወደ ገበያተኛው ተጠጉ።

የታወቁ የመረብ ምላሽ ባላባቶች ህዝቡን ሰብስበው እየሰበኩ ነበር። ባህታ ሓጎስ በመናገር ላይ ነበር። ባህታ ከአባ ዮሃንስ በስጦታ ያገኘውን ባይነኩላር አንገቱ ላይ በማንጠልጠል አጊጦበታል። በግራ ደጃዝማች ሓድነ አምበስ ባልወት ቆመዋል። በቀኝ በኩል የጸዓዘጋው ባላባት የደጃዝማች ሃይሉ ተወልደመድህን

የልጅ ልጅ ደጃዝማች አበራ ካሳ ቆመዋል። አባ ዮሃንስ የትግርኛ ችሎታው ጥሩ ነበር። የባህታ ድምጽ ስለራቀ ግን ለመስማት ጣረ፣

- ስያሜው የባእድ አይደለም። - ሲል ሰማው።

ይዘቱን ለመረዳት ጆሮውን ይበልጥ ተከለ፣

- አባቶቻችን መረብ ምላሽን ምድሪ ባሕሪ ብለው ይጠሩት ነበር። ኤርትራ የባህራችን ስም ነው። ምድሪ ባሕሪ ማለት 'የባሕሩ ምድር' ማለት እንደመሆኑ ልዩነት የለውም። የኤርትራ ባሕር ከደጋውና ከቆላው ጋር የተቆራኘ ነው። ባሕሩ ለመረብ ምላሽ ሰዎች በር ነው። 'ኤርትራ' የሚለው ቃል እኛ ስለራሳችን ከምንለው የራቀ አይደለም። እስላም፣ ክርስትያን፣ ከበሳ፣ መታሕት እጣችንና አዱኛችን፣ ደጃፋችንና በራችን ባሕሩ ነው። ደቂ ባሕሪ ኢና፤ ሽም ባሕሪ ሽምና እዩ። የባሕር ልጆች ነን። የባሕሩ ስም ስማችን ነው። -

ደጃች ባህታ ትንፋሹን ሰብስቦ ቀጠለ፣

- ሌላው ጉዳይ እንግዲህ የባርያ ንግድ ነው። አዋጁን መረዳት ይገባል። የሰው ልጅ በአምላክ አምሳል የተፈጠረ እኩል ሰው ነው። ሰው አይሸጥም፤ አይለወጥም። በቱርክ ቅኝ አገዛዝ ምን አየን? አጤ ዮሃንስ አሉላን ከላኩበን ወዲህ ሰላም አልነበረንም። በሓባብ፣ በሰምሃር፣ በሰንሒት፣ በዓሳውርታ፣ በሓልሓል፣ በከበሳ ሁሉ ጦርነት ነበር። በግብር መሰብሰብ፣ በግብጽ መምጣት ጦርነት ነበረብን። አሁን ጥልያን እንደ አውሮፓ ያለ መንግስት በአገራችን መስርቶ ሰላምና እውቀት ሊሰጠን፤ ሊገነባና ሊያለማ ቃል ገብቷል። ጥልያን የአባቶቻችንን ሃይማኖትና ህግ ያከብራል። ከአባት ከአያት የወረስነውን መሬት ይዘን እያረስን፤ ለእውቀት መትጋት ነው። አንድነት ያስፈልገናል። ህብረት ያስፈልገናል። የተሰነጠቀ እንቁላል የዝንቦች መጫወቻ ይሆናል' እንዲሉ፤ እኛም .... -

አባ ዮሃንስ ጉዞው እንዲቀጥል ምልክት ሰጠ።

በመንገዳቸው ላይ ጥርጊያ ከሚቀይሱ ጣልያኖች ተላለፉ። ኢጣልያውያን መኮንኖች፣ ቀያሾች፣ ቄሶች በፈረስና በበቅሎ ከአንዱ ቦታ ወደ ሌላው ሲጣደፉ አዩ። ፖስተኞችም እንዲሁ ወደ ተለያየ አግጣጫ በፈረስ ሽምጥ እየጋለቡ ውልብ ውልብ ይላሉ። ከማለዳ እስከ ምሽት እረፍት የላቸውም። በመቶዎች የሚገመቱ የግመል

ጠያሮች ከደቡብ አግጣጫ የእህልና የፍራፍሬ ኮረብታ ጭነው ወደ አስመራ ይገባሉ። የጫኑትን አራግፈው ሲያበቁ ባዷቸውን ወደመጡበት አግጣጫ ይመለሳሉ። ከምጽዋ ወደብ አግጣጫ እቃ ጭነው ወደ አስመራ የሚገቡ ግመሎች በሺህዎች ናቸው። ከከረን አግጣጫም እንዲሁ ፍየልና በግ የሚነዱ፣ ዶሮና እንቁላል የተሸከሙ የገበሬዎች ጎርፍ ማቋረጫ የለውም። መረብን ተሻግረው የመጡ የጎንደርና የትግራይ ስራ ፈላጊዎች አስመራን አጨናንቀዋታል። ከአወሮፓውያን በመቀጠል ደረጃቸው እንዲታወቅላቸው የሚፈልጉ አረቦችና ህንዶች የንግዱን መስክ ቀድመው ለመያዝ ይፎካከራሉ።

የአስመራ መሬት እሳት ሆኗል።

በአንድ ሌሊት ሱቅ ተከፍቶ ያድራል። አራት ቋሚ እንጨቶችን በመትከል፤ ዙሪያውን በኬሻ በመክበብ፣ አንድ ጠረጴዛ በማጋደም የዶሮ እና የእንቁላል፣ የቅመማ ቅመምና የቁሳቁስ ገበያውን ማጧጧፍ ለህንዶችና ለአረቦች ቀላል ተግባር ነበር። ድምጻቸው ገና ከሩቅ የሚሰማ ኢጣልያውያን ካራቢኔሪዎች እየጮሁ መጥተው ሲያፈርሱባቸው ምንም አይመስላቸው። ዘወር ሲሉ ግማሽ ሰአት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ሱቃቸውን መልሰው ይተክላሉ። እናም እንቁላላቸውን ደርድረው ሲያበቁ በየቋንቋቸው ማስታወቂያቸውን ያምበለብላሉ። የጋራ መግባቢያ ቋንቋ ባይኖራቸውም ቃላት እየደባለቁ ይግባባሉ።

ጊላጊ ስለ ኑረነቢ ልጆች አስተያየት ጣል አደረገ፣

“ምናልባት መርየም የወንድሞቿን ልጆች ለማስቀረት ትፈልግ ይሆናል። አቦይ ተወልደ ከተጠየቁ ሊስማሙ ይችላሉ።”

አባ ዮሃንስ ፈገግ አለ፣

“አይ! ከኔ ጋር ይሻላቸዋል። ከረን ትምህርት ቤት ይገባሉ።”

አባ ዮሃንስ “በርግጥ መርየም አባብላ ታስቀራቸው ይሆን?” የሚል ጥያቄ ሸው አለበት። ልጆቹ መማር እንደሚሻላቸው ቢያምንም ፍላጎታቸውን መፈጸም እንደሚገባ ከልቡ ጋር መከረ።

የተተራመሰውን የአስመራ አዳዲስ መንደሮች እያቆራረጡ ግማሽ ሰአት ያህል ከገሰገሱ በሁዋላ በፍራፍሬ ዛፎች እና የጓሮ አትክልቶች መካከል ጉብ ካሉ ሶስት ህድሞዎች ደጃፍ ላይ ደረሱ።

በዚህ ጊዜ ጊላጊዮርጊስ ድምጹን ከፍ አድርጎ ተናገረ፣

“በምልክት የተነገረኝ ቤት በትክክል ይሄ ነው።”

በቅርብ ርቀት ከፈረሶቻቸው ላይ ወረዱ።

አንዲት ሴት ከቀዳሚው ህድሞ ብቅ አለች። አባ ዮሃንስና የወንድሞቿን ልጆች እንደተመለከተች በእጇ ይዛው የነበረውን ሙሬ ወርውራ ሁለት እጆቿን ዘረጋግታ፤ የልጆቹን ስም እየጠራች በረረች። ልጆቹም እየተሸቀዳደሙ ሮጠው ተጠመጠሙባት።

* * *

የኑረነቢ ልጆች ሰምበል ሄደው አክስታቸው መርየምን አይተው ከተመለሱ በሁዋላ ደስተኛ ሆነው ታዩ። ባልተመደ ሁኔታ ሳቅና ጨዋታቸው ጨመረ። አክስታቸው የወንድሟን ልጇች መልሳ ለመውሰድ ፈልጋ ነበር። ልጆቹ ፈቃዳቸው አልሆነም። በተለይ አቦይ ተወልደ ደጋግሞ ልጆቹን ለማስቀረት አባ ዮሃንስን ጠየቀ። አባ ዮሃንስ የልጆቹን ፍላጎት በመረዳቱ ሃላፊነቱን ለልጆቹ ለራሳቸው ሰጠ። የመርየም ፍላጎት ግን ሳይሳካ ቀረ። የኑረነቢ ልጆች ከአባ ዮሃንስ ጋር ወደ ከረን ሄደው መማር እንደሚፈልጉ በማያወላውል ሁኔታ ፍላጎታቸውን ገለጹ። ጉዳዩም በዚሁ ተዘጋ።

መርየም በአቦይ ተወልደ ቤት በአገልጋይ ደረጃ ሳይሆን ኑሮዋ እንደ ቤተሰብ ነበር። ያዕቆብና ሰገን ከእናታቸው በላይ መርየምን ይታዘዙና ይቀርቡ ነበር። መርየም ጉልበቷን አትቆጥብም። ለነገ አታውቀም። ላም ማለቡን፣ እንቁላል መልቀሙን፣ የቤት ስራውን ሁሉንም ትሰራለች። አቦይ ተወልደ እና ባለቤታቸውም የስራ ሰዎች ነበሩ። መርየም ከፋና የተፈናቀለችበት ዋናው ምክንያት በመካንነቷ ምክንያት ስለነበር ሌላ የህይወት ምኞትና ህልም አልነበራትም። ሆኖም በአደራ የተረከበቻቸውን የወንድሟን ልጇች ዳግም መልሳ ለማግኘት ባለመቻሏ ቅሬታዋ በግልጽ ታየ። ለብቻ ወስዳ ብታባብላቸውም አልሆነላትም። ልጆቹ ተምረው የተሻለ ህይወት ሊኖራቸው እንደሚችል በማሰብ ግን ተጽናናች።

አባ ዮሃንስ ከመርየም ጋር ባደረገው ቆይታ ስለ ኑረነቢ አንስተው መጨዋወታቸው አልቀረም። ስለ መሸፈቱም አንስተዋል።

በህይወት ስለ መኖር አለመኖሩ ግን እርግጠኛ ሆነው መነጋገር አልቻሉም። በየፊናቸው ወሬ ለማጠያየቅ ተነጋገሩ። ስለ ኑረነቢ ፍንጭ ከሰማች ፈጥና እንድታሳውቀውም አባ ዮሃንስ አሳሰባት።

አቦይ ተወልደ ጠቦት አረዱላቸው። ምሳ በልተው ቡና ጠጥተው እስኪመሽ እዚያው ቆዩ። አድምና እድሪስ ከያዕቆብ ጋር ተጫወቱ። ያዕቆብ ፈረሱ ላይ አፈናጦ እየጋለበ ወደ ደብረ አውሊዕ ተራራ ወሰዳቸው። ፈረሱን የወይራ ዛፍ ላይ አስረው ሲያበቁ በወይራ ዛፎች ወደ ተሸፈነው ተራራ እስከወገቡ ድረስ ወጡ። የኑረነቢ ልጆች ደስታቸው ወሰን አጣ። ያዕቆብ ጥቁሩን ተራራ አባቱ በስጦታ እንደሰጠውና የራሱ እንደሆነ ሲነግራቸው አመኑት። ያዕቆብ በርግጥ እምባ አውሊዕ ተራራ የራሱ ንብረት ይመስለው ነበር።

* * *

አባ ዮሃንስ ከኑረነቢ ልጆች ጋር ሁለት ሳምንታት አስመራ ቆየ። በዚህ ቆይታው በማለዳ እየተነሳ በበቅሎ እየሰገረ አስመራን ከዳር እዳር ማሰስ እለታዊ ተግባሩ ነበር። ተስያት ላይ እረፍት ያደርጋል። ወይም በድንኳኑ ደጃፍ ካለችው የወይራ ዛፍ ስር እንግዶችን እየተቀበለ ያነጋግራል። በበቅሎ እየተዘዋወረ አስመራን በሚጎበኝበት ጊዜ አልፎ አልፎ የኑረነቢ ልጆች አብረውት ይሄዳሉ። ካልሄዱ ደግሞ ከአካባቢው ካሉ ልጆች ጋር ይጫወታሉ። ወይም ደግሞ ፊደል መቁጠርና ማንበብ ይለማመዳሉ። እንዲህ ከሰነበተ በሁዋላ አባ ዮሃንስ ወደ አገረገቢው በመሄድ አይኑ ያረፈበትን መሬት ጠየቀ። በጥቂት ሳምንታት ውስጥ መልስ እንደሚሰጠው ተነገረው። በዚህም የአስመራ ቆይታው አበቃ።

በሚቀጥለው ቀን ወደ ከረን ለመጓዝ ጓዛቸውን አሰሩ። በዚያን ሌሊት አባ ዮሃንስ በማስታወሻው እንዲህ ሲል አስፍሮ ነበር፣

“የመረብ ምላሽ ሰዎች በኢጣልያ መምጣት ገና አልተከፉም። ሰላም ማግኘታቸውን ደጋግመው ይገልጻሉ። ለመጀመሪያ ጊዜ ያገኙትን ፍጹም የሚመስል አስተማማኝ ሰላም ገና ሊጠግቡት አልቻሉም። ከአውሬና ከባርያ ፈንጋዮች በላይ፤ ከርስበርስ ጦርነታቸው በላይ፣ ከትግራይ መኳንንት ዘረፋ በላይ፣ ልጆቻቸውን እየነጠቀ የሚወስድ ከባድ ጦርነት ከፊታቸው እየገሰገሰ

በመምጣት ላይ መሆኑን አሁን ሊያዩት አይችሉም። አይናቸውን በከፈቱ ጊዜ ደግሞ ጊዜው አልፎ ይጠብቃቸው ይሆናል። ከፈረንሳይና ከእንግሊዝን የኮሎኒ ታሪክ የምንገነዘበው ይህንኑ ነው።"

ከረን እንደደረሱ የኑረነቢ ልጆች በካቶሊክ የክርስትና እምነት ተጠመቁ። ሚስዮናውያኑ በደንባቸው መሰረት በጥምቀቱ ጊዜ የልጆቹን ስም ቀየሩ። ለእድሪስ "ኤድዋር" የሚል ስም ሲገኝለት፤ አድም ደግሞ "ኤድሞ" ተባለ። ኑረነቢ የተባለው የአባታቸው ስም "ገብረመድህን" በሚል የክርስትያን ስም ተተካ።

በሰው ልጅ ህይወት ውስጥ ልጅነትና ወላጅ ምንጊዜም በትዝታ ውስጥ ነግሰው ይኖራሉ። በመሆኑም የኑረነቢ ልጆች ወላጆቻቸውን ማሰባቸው ተፈጥሯዊ ነበር። ወላጆችም እንዲሁ በህይወት እስካሉ ድረስ ስለ ልጆቻቸው ይጨነቃሉ። የኑረነቢ ልጆች ስማቸውም ሆነ የአባታቸው ስም ለምን እንደተቀየረ አላወቁም። በተለይ የአባታቸው ስም "ገብረመድህን" በሚል ስም ለምን እንደተተካ ሊገባቸው አልቻለም። ገብረመድህን ማን እንደሆነ አልጠየቁም። በከረን የላዛሪስት ካቶሊክ ካምፕ ውስጥ ገብረመድህን በሚል ስም የሚጠራ ሰው አልነበረም። ሁዋላ ነፍስ አውቀው ገብረመድህን ማንም እንዳልሆነ ቢረዱም እስከ ህይወታቸው ፍጻሜ ሁለተኛ ስማቸው ሆኖ ዘልቋል።

አባታቸው ኑረነቢ እንደወጣ ቀልጦ የመቅረቱ ነገር ግን በአእምሮ ውስጥ የተሸነቆረ እንጥልጥል ስቃይ ሆነባቸው። ዳሩ ህይወት ወደፊት መመልከት የተፈጥሮ ግዴታዋ ነውና በጊዜ ሂደት የሁዋላውን እየረሱ ትኩረታቸው በአዲሱና በመጪው ላይ ሆነ። ይህ በቀላሉ ይሆን ዘንድም ልጅነታቸው አገዛቸው።

ምእራፍ 8

ሰንጋል ወንድሜ!

ለነጭ መርዝ ፈውሱ - ጎራዴ ነው ምሱ

በወርሃ መስከረም 1894 አንድ ወጣት የከበሳ ባላገር የአንድ ቀን መንገድ ተጉዞ ከፍሸይ ምራራ ሸለቆ ደረሰ። እናም በምስጢር በተጠቆመው መሰረት የቦጎስ ሽፍቶች ይገኙበታል ወደተባለው ዱር አቀበቱን ተያያዘው።

ሸለቆው ጥቅጥቅ ባለ ጫካ የተሞላ ነበር። አቀበቱም እንዲሁ ርስበራሱ በተገማመዱ ዛፎች ተጠቅጥቆ መተላለፊያ የለውም። ወጣቱ የተላከበትን ብርቱ ጉዳይ ከመፈጸሙ በፊት የአውሬ እራት እንዳይሆን ክፉኛ ስጋት ቢያድርበትም የተነገረውን አግጣጫ ተከትሎ ወደፊት ከመገስገስ በቀር አማራጭ አልነበረውም። ተንሸራቶ እንዳይወድቅ የወይራ ቅርንጫፍ እየያዘ አቀበቱን አጋመሰ።

ወጥቶ ጫፍ ከመድረሱ በፊት ግን የሰው ድምጽ የሰማ ስለመሰለው ባለበት ቆመ። ጥቂት ጠበቀ። ድምጹ አልተደገመም። እንደገና በዝግታ ጉዞውን ቀጠለ። አሁን በትክክል የእህህታ ድምጽ ሰማ። እና ድምጹን ወደ ሰማበት አግጣጫ በዝግታ አዘገመ። የሰማው ድምጽ ከሸፍቶቹ መንደር መድረሱን ስለጠቆመው ተስፋ አደረገ። ምንም እንኳ ድምጽ ቢሰማም ሰው ሊታየው አልቻለም።

እርስበራስ የተቆላለፈው ዛፍና ሃረግ ምንም አያሳይም። የሰማው ድምጽ በቅርብ ርቀት መሆኑን ቢረዳም ቦታውን ለመለየት አልቻለም። ስለዚህ በበኩሉ ምልክት ሰጠ፣

“ጤና ይስጥልኝ! እንግዳ ነኝ!”

እንደገና የእህህታ ድምጽ ተሰማ። በዚህ ጊዜ ግን ድምጹ ከበላዩ የሚመጣ መሆኑን በመረዳቱ ከአጠገቡ ወደነበረው የወይራ ዛፍ ቅርንጫፎች አንጋጠጠ። ከዛፉ ቀለም ጋር የሚመሳሰል ደበሎ የለበሰ ሰው ጠመንጃ አነጣጥሮበት ተመለከተ።

“ምን ፈልገህ መጣህ?”

“መልእክት ይዣለሁ - ለኑረነቢ?”

“ማነው የላከህ?”

“አይ! ለራሱ ነው የምነግረው። ኑረነቢን አገናኘኝ እባክህ?”

“ኑረነቢ የሚባል ሰው እዚህ አናውቅም። ወደዚህ የመጣህበትን ጉዳይ አሁኑኑ ተናገር። አለዚያ ወላሂልዓዚም እተኩስብሃለሁ። በል አውቀህ ግባበት?”

“ወንድሜ! ለኑረነቢ ለራሱ ካልሆነ ለሌላ ለማንም እንዳልነግር በአደይ ማርያም ስም መሃላ ፈጽሜያለሁ። ‘ኑረነቢ እዚህ የለም’ ካልከ ግን አሰናብተኝና ተመልሼ ልሂድ።”

“ተከትሎህ የመጣ ሰው አለ?”

“ማንም የለም። ብቻዬን ነኝ።”

“ካራቢኔሪ ተከትሎህ አልመጣም?”

“በስመአብ ወልደ መንፈስ ቅዱስ!” ደረቱ ላይ አማተበ።

በዚህ ጊዜ ሽፍታው ከዛፉ ላይ ወረደ። እንግዳውን ሳይቀርበው በቅጡ አጤነው። ከዚያም ጆሮውን ተክሎ ድምጽ ለመስማት ጥረት አደረገ። ድምጽ ለመስማት ለደቂቃዎች ያህል ጆሮውን ተክሎ ቆየ። በመቀጠል በተለያየ ዘዴ እንግዳውን በጥያቄ አጣደፈው። የጣልያን ሰላይ ሊሆን ይችላል በሚል ግንባሩ ላይ ጠመንጃውን በመደቀን አስፈራራው። በዚህም ቢለው በዚያ ግን “ወደ ኑረነቢ ተልኬ ነው የመጣሁት” ከማለት በቀር ትንፍሽ ሊል

አልቻለም። ብብቱን ሳይቀር በረበረው። ከዱላ በቀር ሌላ አልያዘም።

የእንግዳውን ጽናትና በራስ መተማመን ከመዘነ በሁዋላ፣

“ሳትንቀሳቀስ እዚሁ ጠብቀኝ።” ብሎት አቀበቱን ወጣ።

ከግማሽ ሰአት በሁዋላ ተመልሶ ሲመጣ ጠጉሩን ያሳደገ፣ ጢሙን ያንጀረገገ ቀይ ጎልማሳ አብሮት ነበር። ረጅም ሲሆን፤ ግንባሩ የተኮፋተረ፣ የነብር የሚመስሉ አይኖቹ ውስጥ ጭካኔ የሚነበብበት፣ ከፈገግታ ጋር የማይተዋወቅ አይነት ነበር። ጠመንጃውን እንደ በትር ይዞታል። ዝናር ወገቡ ላይ ጠምጥሟል። ጥልፍልፍ ከቆዳ የተሰራ ሸበጥ ተጫምቷል።

“ኣሰላም ዓለይኹም!” አለ እንደደረሰ።

“አምላክ ይመስገን።”

“ኑረነቢ እኔ ነኝ።” ብሎ ጨበጠው።

ከዚያም አስከትሎት ወደ አቀበቱ ከወጡ በሁዋላ በአንድ ዋሻ መሳይ ጎሬ ውስጥ ገቡ። በዋሻው ደጃፍ ላይ የነበረ ሌላ ጎፈሬያም ሽፍታ ኩርሲ አቀረበለትና እንግዳው አረፍ አለ። ውሃ ቀርቦለት ተጎነጨ። የገበስ ቂጣ እና ቋንጣ፣ እንዲሁም የተቆላ ጥራጥሬ አቀረቡለት። እንግዳው በውሃው እያራሰ ቂጣውን ገመጠ። ቋንጣውን አኘከ። ከቆሎው ዘግኖ ቃመ። ተርቦ ስለዋለ ልቡ መለስ አለችለት። ይህ ሁሉ ሲሆን ኑረነቢ አንዳች ቃል ሳይተነፍስ ቆየ። በመጨረሻ ግን ጥያቄውን ጣል አደረገ።

“ማነው ወደኔ የላከህ?”

“ብቻችንን ብንነጋገር...”

“ግዴለም! ከሱ ከወንድሜ የሚደበቅ ነገር የለኝም።”

መልእክተኛው ጥቂት ከአቅማማ በሁዋላ፣

“ደጃዝማች ባህታ ሓጎስ ነው የላኩኝ።” አለ።

ኑረነቢ በዚያችው ቅጽበት ገጽታው ተለወጠ፣

“ባህታ ከኔ ምን አለው? ምህረት ሊለምንልኝ ፈለገ?”

ይህን ብሎ መራር ፈገግታ አሳየ። ያን ከመሰለ ጨፍጋጋ

ገጽታ ተፈልቅቆ የወጣው ፈገግታ ገጽታውን ይበልጥ ጨካኝ አስመሰለው። ፈገግታው ግን ፊቱ ላይ አልቆየም። እንደ ሰምሃር ጥላ ብልጭ ብሎ ወዲያው እልም አለ።

እንግዳው በቅሬታ መንፈስ መልስ ሰጠ፣

“አይ! ቸኩለው ያልሆነ ነገር ባይናገሩ ይሻላል። ባህታ ከጥልያን ጋር ስምምነት የለውም። ሊወጋቸው ቀን ቆርጧል። ርስዎም ሰዎችዎን ይዘው ወደ ሰገነይቲ እንዲያልፉ ንገር ብሎኛል።”

ኑረነቢ ለአፍታ በጸጥታ ተዋጠ።

ወደ ባልደረባው መለስ ብሎ በአይን ተነጋገሩ። ከጥቂት ሰከንዶች በሁዋላም እንዲህ አለ፣

“የተናገርከው ሃቅ መሆኑ በምን ይታወቃል?”

“አደይ ማርያም!” ሲል ማለ።

ኑረነቢ እንደገና ጥቂት አሰላሰለ።

“የተናገርከው እውነት ከሆነ ደግ ነው። ቀድሞውንም ባህታ ለጥልያን ማደሩ አስገርሞን ነበር። ባህታ ዓንሰባ ወንዝ ላይ አሉላን ሲመክት በፈጸመው የጀግንነት ሙያ የመታሕት ሰው አክብሮት ነበረው። ሁዋላ የጥልያን ቀኝ እጅ ሆነ መባሉ የሚያስቆጭ ሆነ። ባህታ እንደ ካፍል እሱም ናኹራ ለመጋዝ ተራውን ይጠብቃል ብለን እያማነው ነበር። የነገርከን እውነት ከሆነ መቸም በመጨረሻ እንኳን ለዚህ አበቃው። የላከውን መልእክት በተመለከተ እስኪ አስበንበት ስናበቃ እንነግራችሁዋለን።”

“አይ! ከወሰኑ አሁኑኑ ይንገሩኝ። ጊዜ የለንም። ጥልያንን ተጋግዘን ከዚህ ካላጠፋነው ሁዋላ ስር ከሰደደ መንፈሳችን በጸጸት እረፍት ያጣል። ‘ለልጆቻችን ስንል ክርስትያን እስላም ሳንባባል አንድ ሆነን እነዚህ ባሕር ያመጣቸውን ተንኮለኞች መልሰን ከባሕር እንጨምራቸው’ ብለህ አጥብቀህ ንገረው ብሎኛል።”

ኑረነቢ እንደገና ፈገግ አለ፣

“ለመሆኑ እንዴት ነው የገመትከኝ? አደይ ማርያም ስላልክ ብቻ እንዲያው ብድግ ብዬ የማምንህ ይመስልሃል? ካፍል ጎፋርን ያየ

ጥልያንን አያምንም። ሃቅ መናገርህን እስኪ በሌላ አረጋግጥ?”

በእንግዳው ገጽታ ላይ ቅሬታው በግልጽ ታየ።

“በሃሰት የአደይ ማርያምን ስም እንዴት እጠራለሁ? በአባቶቼም በአያቶቼም ቃልና መሃላ ተበልቶ አያውቅም። እንዲህ የተጠራጠሩት ባያውቁኝ ነው። ስሜን እንኳ ሳይጠይቁኝ ሰተት ብለው ወደ ነገር ገቡ። ባይጠይቁኝም እንዲያውቁኝ ያህል ልንገርዎ። የደጃዝማች ባህታ ሓጎስ የበኩር ልጅ ነኝ።“

ኑረነቢ ከተቀመጠበት ብድግ አለ።

“ገብረመድህን አንተ ነህ?”

“ልክ ነው። እኔ ነኝ።”

ኑረነቢ ስለ ባህታ ወንድሞችና ልጆች ዝርዝር ነገር ያውቅ ነበርና ይህ አጠገቡ የተቀመጠ ጎረምሳ በዝና ከሚያውቃቸው ሰዎች አንዱ መሆኑ ያልጠበቀው ሆነበት። በእንግዳው ሰው ላይ የነበረው ጥርጣሬም በእጅጉ ቀነሰ። ይበልጥ ለማረጋገጥ በመፈለግ ግን ባህታ በዓሳውርታና በሓባብ በነበረ ጊዜ የተፈጸሙ አንዳንድ ነገሮችን እያነሳ ጠያየቀው። ያላንዳች መደናገር ተግባብተው ተጨዋወቱ። በዚህ ጊዜ ኑረነቢ በረጅሙ ተነሰፈና ወደ ዋናው ጉዳይ ተመለሰ።

“የሆነው ሆኖ ባህታ መቼ ሊወጋቸው አሰበ?”

“እንግዲህ ቆርጦ ተዘጋጅቷል። እህል ተወቅቶ ጎተራ እስኪገባ ነው የሚጠብቀው። ከሚታመኑ ጋር እንዲህ በምስጢር እየተላላከ፤ የጥልያንን ክፉ ተንኮል እየነገረ ከተት እያለ ነው።”

“ሌላ ወደ ማን ተላከ?”

“ሰንጋል ወደ ዓሳውርታ ሄዷል። ካሕሱ ወደ ሰራዬና ወደ ሽመዛና። እንዲህ እንደርስዎ በባዳ እና በሌላ አካባቢ ለሸፈቱ ሁሉ ተልኮባቸዋል። አባቴ እኔን ወደርሶ መላኩ የርስዎን የልብ ኩራትና የጀግንነት ሙያ ከአባ ዮሃንስ ቢሰማ ነው። በኔ ስር 200 ታጣቂ አለ። የእርስዎን ሰዎች ጨምረን እኔና እርስዎ አንድ ግንባር እንይዛለን። የጥልያንን የልብ ተንኮል ከሁላችን ቀድመው በማወቅዎ ደጃች ባህታ ለርስዎ ትልቅ ግምት አላቸው።”

የኑረነቢ አይኖች ወጣቱ እንግዳ ላይ ይበልጥ አተኮሩ። የአባ ዮሃንስ ስም ሲነሳ አንድ ነገር ሊናገር ከጀመረ በሁዋላ ከመቅጽበት አሳቡን በመለወጥ ማለት የፈለገውን ከምላሱ መለሰው። እንደገና ዝምታ ሆነ። እና ኑረነቢ እንዲህ አለ፣

“የምንሄድ ከሆነ እንግዲህ በቅድሚያ እዚህ አብረውኝ ያሉ ጓደኞቼን ማማከር አለብኝ። ባንድነት ወደ ሰገነይቲ ማለፍ ሳያስቸግረን አይቀርም። ተነጣጥለን፣ ጨለማ ለብሰን፣ ጠመንጃችንን ይዘን መሄድ ስለመቻሉ ማወቅ ይገባል። ጥልያን አሸምቆ እንዳያጠቃን ዘዴውን፣ መንገዱን መፈለግ ይገባል።”

ገብረመድህን ፋታ አልሰጠውም፣

“ርስዎ ከወሰኑ ደጃች ባህታ የመንገዳችሁን ጉዳይ ያስተካክላሉ። ሳትነጣጠሉ ሰገነይቲ እንድትገቡ ይደረጋል። የኛ ሰዎች ወደዚህ አካባቢ ቀርበው ትገናኙና እናንተን መሃላቸው ቀላቅለው ሰገነይቲ ያደርሷችሁዋል። እርስዎ ብቻ ቃልዎን ይስጡኝ።”

ኑረነቢ ግን ቃሉን መስጠት አልቻለም፣

“እዚህ እደርና ጠዋት ውሳኔዬን እነግርሃለሁ።” አለው።

ገብረመድህን ራሱን በመነቅነቅ ከተስማማ በሁዋላ፣

“ደጃች ባህታ ከሁለቱ ልጆች ጋር ተገናኝተው ነበር። በጥሩ ሁኔታ ላይ መሆናቸውን፣ ደህንነታቸውንም እንደሚከታተሉ ንገር ብለውኛል።” ሲል እንደዋዛ ጣል አደረገ።

የኑረነቢ አይኖች ፈጠጡ፣

“የማን ልጆች?”

“እድሪስና አድም ማለቴ ነው።”

ኑረነቢ አቀረቀረ። እና በጸጥታ ጥቂት ቆየ፣

“ባህታ የት አገኛቸው?”

“ወደ ከረን ሲያልፉ አስመራ አጊኝቷቸው ነበር።”

ኑረነቢ አይኖቹን ከዋሻው ማዶ እሩቅ አሻግሮ ሲመለከት ቆየ። ባንድ አፍታ የሃዘን ድባብ ፊቱን ሸፈነው። እናም በረጅሙ

ተንፍሶ ፍጹም በተለወጠ ደካማ ድምጽ ተናገረ፣

“ልጆቹ ያሉበትን ሁኔታ አውቃለሁ። ሁሉንም አውቃለሁ። እኔ ስላለሁበት ሁኔታ ግን ለጊዜው እንዲያውቁ አልፈለግሁም። ማሳቀቅ ይሆናል ብዬ ተውኩት። አንድ ቀን በረሃ ላይ መውደቄ ለማይቀር ተስፋ ማድረጉ አይበጃቸውም ብዬ ነው። ቢረሱኝ ይሻላል ብዬ ተውኳቸው። ለመሆኑ እኔ ስላለሁበት ሁኔታ ሰምተዋል?”

“አይ! እሱን እንኳ አላውቅም።” አለ ገብረመድህን።

አንዲት ሴት የቡና ማፊያ እቃዎችን ይዛ ወደ ዋሻው ደጃፍ ቀረበች። የገል ምድጃ ላይ በተንተረከከው የከሰል ፍም ላይ ቡናው መቆላት ጀመረ። ከደጅ ሌላ ድምጽ አይሰማም። አእዋፍት ብቻ ይዘምራሉ። በየጣልቃው ቆቅ ድምጽዋ ይሰማል። በተቀረ በማረር ላይ ያለው የቡና መቆላት ድምጽ ብቸኛ መሰለ። እና ዝንጅብል የገባበትን የቡኖ ቡና እየጠጡ ስለ ኢጣልያ የቅኝ አገዛዝ ጠባይ፤ በተለይም ኢጣልያውያን እንደ ድመት ተለሳልሰው ገብተው ሲያበቁ፤ እንዴት ጥፍራቸውን እንደዘረጉ አንስተው ተጨዋወቱ። የሚፈጽሙትን አስጸያፊ የዘረኛነት ተግባራትም በዝርዝር አወጉ።

በተለይም የኢጣሊያን ቅኝ አገዛዝ የተቃወሙ አንድ ባንድ እየተለቀሙ በመጥፋት ላይ መሆናቸውን ተጨዋወቱ።

ደጃዝማች መስፍን ወልደሚካኤል ወደ ኢጣሊያ ከተወሰደ በሁዋላ በዚያው ቀልጦ ቀርቷል። ልጅ አበራ ካሳ የባላምባራስ ካፍል ጎፋር እጣ እንደሚገጥመው ቀድሞ በማወቁ የጀግንነት ሙያ ፈጽሞ መረብን ተሻገረ። እንዲህ እያወጉ አመሹ።

ገብረመድህን በጨዋታ መሃል አጎቱ ሰንጋል ጣልያኖችን በየዋህነት እንደሚያምናቸው ጠቀሰ። “ከጥሩ ዘር የሚወለዱ ቆነጃጅት ምረጡልን?” ብለው በጠየቁ ጊዜ ግን ሰንጋል እንደደነገጠና ከጣልያኖች ጋር የነበረው ጥሩ ግንኙነት ጨርሶ እንደተቆረጠ አጫወተው። ቀደም ብሎ ባህታ የጣልያኖችን ተንኮል ተረድቶ ስለነበር ለአጎቱና ለራሱ ጭምር ያቀነቀነላቸውን ቅኔ አዜመለት፣

ባጽዕ እግሩ ዓሰም መተርኣሱ
ገመድ ኣሎ ቅሩብ ተፋሒሱ

ዝጠዓመ እንተጠዓመ ጓና ነይምሹ
ኣንታ ሰንጋል ሓወይ እምብዛ ኣይትዓሹ
ወደይ ገብረመድህን እምብዛ ኣይትዓሹ
ጻዕዳ ተመን ድሕሪ ነኺሱ...
ደላሊኻ ኣይርከብን ፈውሱ።
- - -

ምጽዋ ግርጌው - ኣሰብ ላይ ትራሱ
የገመድ ሸምቀቆ - ዝግጁ ለነብሱ
ልቡ ተንኮል ቋጥሮ - ጣፋጭ ነው ምላሱ
ሰንጋል ወንድሜ - ኣትሁን ተላላ
ገብረመድህን ልጂ ኣትሁን ተላላ
ነጭ እባብ ሲነድፍ - ፈውስ የለውም መላ።

የኤርትራ ሰዎች የኢጣልያን ኣገዛዝ መቃወም የጀመሩት ውለው ሳይድሩ ነበር። ኣስተዳደሩ በኣስመራና በኣካባቢው የነባሩን ነዋሪ መሬት ለከተማ ግንባታ መንጠቅ ሲጀምር ቅሬታ ጀመረ። የኣገሩን ገበሬዎች ከኢጣልያ ኣምጥቶ ምርጡ መሬት ላይ ማስፈር ሲጀምር የገበሬው ቀልብ ይበልጥ ተሳበ። ይህ ወሬ በተስፋፋበት ሰሞን የኣስመራ ኣውሎኛ ነጠላ ግጥም ለቀቀ፣

ሕጂ ድዩ ዋይ! ዋይ!
ቀደም እዩ ዝነበረ . . .
ኣብ ዓርበሮቡዕ ኮንካ ...
ሓደ ሓደ እምኒ ምድርባይ
- - -
ኣሁን ምን ያደርጋል ዋይ ዋይ?
ቀድሞ ነበር እንጂ . . .
ዓርበሮቡዕ ሆኖ . . .
መወርወር ኣንዳንድ ድንጋይ

ይህን ግጥም ተርጉመው ሲነግሩት የኣስመራ ከንቲባ እንዲህ ሲል ኣሸሚጠጠ ኣሉ። “A chi dai il dito si prende anche il braccio.” ማለትም “ኣንድ ጣት የሰጠ - ሙሉ ክንዱን ያጣል።” ሲል የልቡን ብቻ ሳይሆን እውነቱን ተናገረ። በግመል ሃብቱ የሚታወቀው የኤርትራ ኣካባቢ ከግመል ጋር የተያያዙ ወጎችን ያውቃል። ከእነዚህ ወጎች መካከል፣ “ለኣንገቴ ማስገቢያ ብቻ

ስጡኝ?" ብላ የለመነችው ግመል ታሪክ አንዱ ነበር። ለአንገቷ ማስገቢያ ከሰጧት በሁዋላ ግመሏ ለሌላው አካሏ መለመን አላስፈለጋትም። ጥሳ ገባች።

የኢጣልያ ቅኝ አገዛዝ መላ ኤርትራን ሲቆጣጠር በአገሬው ሰው ዘንድ የነበረው አንዳንድ አወንታዊ ስሜት ብዙም አልዘለቀ። ከረሃብ አደጋው ማለፍ ጋር የተሰደዱት ገበሬዎች ወደ መንደራቸው ተመለሱ። ህይወት እንደነበረው ሲቀጥል፤ ዜጎች አርሰውና አርብተው ራሳቸውን መመገብ ሲጀምሩ የተፈጸመውን ማስተዋልና ጥያቄዎች ማንሳታቸው አልቀረም።

ጥያቄያቸው፣ "ሰላም ከነጻነት ጋር" ወደሚል አደገ። ለአሸሙርና ለስድብ እንኳ የቅጣት ህግ ደንግጎ ተከባብሮ ሲኖር የነበረው ህብረተሰብ በገዛ አደባባዩ ላይ "ጥቁርና ነጮችን በአንድ ክፍል ውስጥ መቀላቀል አንፈልግም" የሚል መፈክራዊ መመሪያ ሲለጠፍበት አይኖቹን ማመን ተቸገረ። "Non vogliamo bianchi e neri mischiati in una camera" የሚሉት ቃላት የመረብ ምላሽ ሰዎች ለመጀመሪያ ጊዜ የኢጣልያን ቋንቋ የተማሩባቸው ቃላት ሳይሆኑ አልቀሩም።

በ20ኛው ክፍለዘመን አጋማሽ በርግጥም "የነጭና የጥቁር" ልዩነት በቀጥታ ስራ ላይ ውሎ ነበር። የአገሬው ሰዎች ነጭ ኢጣልያውያን በሚገቡባቸው ሲኒማ ቤቶች፣ ሬስቶራንቶች፣ ባሮችና ሆቴሎች ገብተው እንደ ነጮች መስተናገድ እንደማይችሉ ተነገራቸው። ቆይቶም የከተማ አውቶብሶች ለሁለት ተከፍለው ለኤርትራውያን ከሁዋላ መቀመጫ ተለየላቸው። ወደ ባር ሄዶ ቡና ወይም ሻይ የሚጠይቅ ኤርትራዊ በጓሮ በኩል ይስተናገዳል። በብርጭቆ ወይም በስኒ አይፈቀድለትም። ሻይና ቡናው ሳልሳ ታሸንበት በሚመጣ የቆርቆሮ ጣሳ ይሰጠዋል። የሚከፍለው ዋጋ ግን በብርጭቆ የሚጠቀሙ ኢጣልያውያን ከሚከፍሉት ጋር ተመሳሳይ ነበር። በትምህርት ቤቶችና በሆስፒታሎች አድልዎ በግልጽ ታየ። የጥቁርና የነጭ መንደሮች ተለዩ።

ርግጥ ነው፤ ዘመኑ የተምታታበት ነበር።

የአጤ ምኒልክ ሰራዊት ወደ ደቡብ ዘምቶ መሬታቸውን

በእጅ ካደረገ በሁዋላ ነባር ነዋሪውን ጭሰኛ አደረገ። አውሮፓውያን ቅኝ ግዛታቸውን ሲያስፋፉ የአገሬውን ነዋሪ ለጥይት ማብረጃ ከፊት ማጋፈጥ ልማዳቸው ነበር። እንግሊዝ ህንዶችንና ናይጂሪያውያንን፣ ጣልያን ኤርትራውያንና ሶማሌዎችን፣ ፈረንሳይ የሰሜን አፍሪቃ አረቦችን ከፊት እንደሚያሰልፉት ሁሉ አጤ ምኒልክ ወደ ደቡብ ባደረጉት መስፋፋት ጎንደሬዎችን ለጥይት ማብረጃ እንደተጠቀመባቸው አፈወርቅ ገብረእየሱስ ጽፏል። የአጤ ምኒልክ ስርአት አስቀያሚ ገጽታ ይበልጥ የሚገለጸው ግን በወረራ ያስገበሩትን ህዝብ ወቅቱ በሚፈቅደው መጠን እንኳ እንደ ሰው የማየት አቅምና ፍላጎት በማጣታቸው ነበር።

ኢጣልያውያን ኤርትራ ላይ ትምህርት እስከ አራተኛ ክፍል ብቻ መፍቀዳቸው በሚያስወቅሳቸው ዘመን፤ አጤ ምኒልክ ከደቡብና ከኦሮሞ ምድር የባርያ ንግድ እያጧጧፉ ነበር። ሁዋላ ፕሮፌሰር መሓመድ ሃሰን በጥናት እንዳረጋገጠው በአጤ ሚኒልክ ዘመን ነ.3 ሚሊዮን ኦሮሞዎች ተሸጠዋል። በዚያን ዘመን በመንገድ ስራ ላይ የተሰማሩ ኤርትራውያን በሚከፈላቸው ደሞዝ ማነስ ሲያጉረመርሙ፣ ኢጣልያ 800 ኤርትራውያንን በድብቅ ስለመግደሏ ዜናው በአውሮፓ አነጋጋሪ በነበረበት ዘመን፤ አጤ ምኒልክ በመቶ ሺህዎች ኦሮሞዎችን ለባርያ ነጋዴዎች አሳልፈው እየሰጡ ነበር።

ንጉስ ኡምቤርቶ ኤርትራ የኢጣሊያ ግዛት መሆኗን ከማወጁ በፊትም ሆነ በሁዋላ የኤርትራውያን ተቃውሞዎች በያቅጣጫው ይታዩ ነበር። ተቃውሟቸው ግን በተደራጀ የትጥቅ ትግል ደረጃ አልነበረም። በተናጠል ነበር። ኢጣሊያኖች ዘለግ ብሎ የሚታየውን የኤርትራውያን አንገት አንድ ባንድ እየቀነጠሱ፤ ህዝብ ሊመራና ሊያንቀሳቅስ የሚችለውን ግለሰብ ከአገር ለማጽዳት ሞከሩ። ጎን ለጎንም ለኢጣሊያ ታማኝ ሊሆኑ የሚችሉ ኤርትራውያንን ኮትኩተው ለማሳደግ ተጉ።

የካቲት 1892 ኢጣልያውያን አዝማሚያው ደስ ያላላቸውን ደጃዝማች አበራን ለማሰር ተንቀሰቀቀሱ። አበራ ካሳ ኢጣልያውያን ምን እንዳሰቡለት ቀድሞ በማወቁ ሸፈተ። የኢጣሊያ አስተዳዳሪዎች ደጃዝማች አበራን አሳዶ እንዲይዝ ካፒቴን በቲኒ በተባለ መኮንን የሚመራ መቶ ታጣቂዎችን የያዘ ቡድን አሰማሩ። ካፒቴን በቲኒ

መመረጡ ቀደም ሲል ከአበራ ጋር እውቂያ ስለነበራቸው ቢቻል በማግባባት፤ ካልተቻለ በማስገደድ ሊይዘው ይችላል በሚል ነበር።

እንደታሰበው ግን አልሆነም።

ቡድኑ ዓንሰባ - ደቂ ሸሃይ ዋልታ መድሃኒአለም በተባለ ቦታ ከደጃች አበራ ጋር ባደረገው ውጊያ ኢጣሊያዊው አዛዥ ተገደለ። ኢጣሊያ ኤርትራን በቅኝ ግዛት መያዟን ካወጀች በሁዋላ በአገሬው ሰዎች የተገደለ የመጀመሪያው ኢጣሊያዊ በመሆኑ ዜናው ትኩረት ሳበ። በዚህ የተደናገጡት ቅኝ ገዢዎች ለመቀጣጫ በሚል በተባባሪነት ስም በጅምላ ብዙ ሰላማዊ ሰው ገደሉ። ህድሞዎችን አፈረሱ። "ለልጅ አበራ መሸሸጊያ ሆናችሁ፤ ምግብ አበላችሁ፣ መጠጥ አጠጣችሁ" በሚል ገበሬዎችን ዘረፉ። በደጃች አበራ አመጽ ምክንያት ከፍተኛ ውድመት ከደረሰባቸው መንደሮች መካከል ዓዲ ንአምን፣ ዓዲ ዕጀል እና በከፊል ደግሞ ጸዓዘጋ ይጠቀሳሉ።

ያም ሆኖ ኢጣልያኖች ደጃዝማች አበራን ለመያዝ ያደረጉት ሙከራ አልተሳካላቸውም። እየተከታተሉ ሲወጉት፤ እየተዋጋ ወደ ኢትዮጵያ ድንበር አግጣጫ አፈገፈገ። እየበረቱበት ሲሄዱ ከታጠቁ 70 ተከታዮቹ ጋር በአከለጉዛይ በኩል ወደ ዓጋመ ተሻገረ። በዚያው ኮብልሎ አልቀረም። ከትግራይ ድንበር እየተነሳ፤ ድንበር ተሻግሮ ኤርትራ እየገባ የኢጣሊያን ሃይል በሽምቅ ውጊያ ማጥቃቱን ቀጠለ። ሆኖም ኢጣሊያ በጠየቀችው መሰረት አበራ ትጥቁን ፈትቶ ወደ ሸዋ እንዲሄድ በአጤ ምኒልክ ታዘዘ። በወቅቱ ምርጫ አልነበረውም። ወደ እንጦጦ ሄደ። ምኒልክ ደጃዝማች አበራን በቤተመንግስታቸው ተቀብለው የፈጸመውን ጀብዱ ከራሱ አንደበት የሰሙ ሲሆን፤ ሰምተው ሲያበቁ፣ "ከሺህ አማራ - አንድ አበራ" ሲሉ መተረታቸውን ስዊድናዊው ዮሃንስ ኮልመዲን በመጽሃፉ ጠቅሷል። ከዚያ በሁዋላ ደጃዝማች አበራ ወደ ኤርትራ አልተመለሰም። ከምባታ - አንጋቻ ግዛት ላይ ተሹሞ እስከ እለተ ሞቱ እዚያው ቆየ።

ርግጥ ነው በኤርትራ መኳንንት መካከል የነበረው የርስበርስ ሽኩቻ ኢጣልያን በእጅጉ ጠቅሟል። ለአብነት ኢጣልያኖች አበራን እንዲጠረጥሩ የገፋፉት ሌሎች የደጋ ባላባቶች መሆናቸው ይታመናል። አንዱ ጠንክሮ እንዳይወጣ በተዘዋዋሪ ማጥቃት በመኳንንቱ መካከል የነበረ ልማድ ነው። ይህ ከጀርባ ጠልፎ

የመጣሉ የፖለቲካ ሽኩቻ፣ እንደ አንድ የትግል ስልት ይታይ የነበረ ሲሆን፤ የወቅቱ መሳፍንትና መኳንንት ከወላጆቻቸው በውርስ የሚያገኙት “ተንኮል” ሊባል የሚችል ነው።

በመጨረሻ ከኢጣሊያ ጋር ስምምነት የፈጸሙ የከበሳና የመታሕት ባላባቶች አንድ ባንድ እየተለቀሙ ተወግደዋል። አንዳንዶቹ ተዋግተው ተሰው። ሌሎቹ ወደ ናኹራ እና አሰብ እስር ቤቶች ተላኩ። ጥቂቶቹ ወደ ኢጣልያ ተወስደው በዚያው ቀልጠው ቀሩ። ከኢጣልያ ዱላና ሰንሰለት ማምለጥ የቻሉ መረብን ተሻግረው ወደ ኢትዮጵያ ገቡ። ከኢጣሊያ ጋር ሳይጋጭ ጥቂት ጊዜያት እንኳ በስምምነት መቆየት የቻለ አንድም አልነበረም። ባህታ ሐጎስ ተመሳሳይ እጣ የገጠመው ቢሆንም በአይነቱ የተለየ ሆኖ ሊታይ የሚችለው ተቃውሞውን በተደራጀ መልኩ ማካሄድ በመቻሉ ነው።

ዘምህረት ዮሃንስ እንደተረከው፣

“ባህታ በ1839 ከሃብታም ቤተሰብ ሰገነይቲ ተወለደ። እድገቱ እዚያው ሰገነይቲ ነበር። በ1875 ህይወቱን የሚቀይር ክስተት አጋጠመው። የትግራይ መኳንንቶች በወቅቱ ሰገነይቲን ያስገብሩ ነበር። የራስ አርአያ ልጅ ፊታውራሪ እምባየ አርአያ አመታዊ ግብር ሊሰበስብ እንደ ወትሮው ሰገነይቲ ብቅ አለ። ህዝቡ ግን በግብርና በንበዝ አለቆች ዝርፊያ ተሰላችቶ ነበርና አንገራገረ። ባህታ ሐጎስ ልክ በዚህ ጊዜ ታሪክ መስራት ጀመረ። የአመጻውን ህዝብ ወክሎ ፊታውራሪ እምባየን እዚያው ሰገነይቲ ላይ ገደለው። የተደራጀ ሃይል ስላልነበረው ግን ከሚከተለው አደጋ ራሱንና ቤተሰቡን መከላከል አይችልም ነበርና ሸፈተ።”

ባህታን በተመለከተ አያሌ ትረካዎች በተለያዩ ቋንቋዎች ለንባብ በቅተዋል። እንደትረካዎቹ፣ ባህታ ካሕሱ እና ሰንጋል ከተባሉ ወንድሞቹ ጋር ወደ ዓሳውርታ ሸፈተ። የራስ አርአያ ወገኖችም እንደሚጠበቀው ለብቀላ ሰገነይቲ መጡ። የፈለጓቸውን ባያገኙም የባህታ ሐጎስን መኖሪያ ቤት አቃጥለው ንብረቱን ዘርፈው ወደ መጡበት ተመለሱ። በቀጣዮቹ አመታት ራስ አሉላ ወደ መረብ ምላሽ ሲመጣ እንደ ባህታ ሐጎስ ያሉ ሽፍቶችን ማደን ከተልእኮዎቹ መካከል ነበሩ። አሉላ ባህታን ለማደን ወደ ዓሳውርታ ሲወርድ ባህታ ወደ ሓባብ ገለል አለ። በዚያን ጊዜ የሓባብ መሪ ከንቲባይ ሓምድ

ነበር። ከአሉላ ጋር የማያቋርጥ ግጭት ስለነበራቸው ባህታን ሾሞ ሸልሞ ተጠቀመበት። ባህታ ሓጎስ በሓባብ ቆይታው ከአሉላ ሰራዊት ጋር ተዋግቶ አዋግቷል። ጥቅምት 1880 ባህታ ሓጎስ ከግብጾች ጋር ቅንጅት በመፍጠርም ዓንሰባ ወንዝ ላይ ከአሉላ ተዋግቷል።

በዚህ ወቅት ኢጣልያ ምጽዋን ያዘ።

የዶጋሊ ውጊያ ከተደረገ በሁዋላ ባህታ ወደ ምጽዋ ወርዶ ከኢጣልያውያን ጋር ስምምነት ፈረመ። በ1888 ባህታ ሓጎስ 300 የታጠቁ ጀሌዎችን ይዞ በመረብ ምላሽ መንቀሳቀስ ጀመረ። አቆርዳትን ለመያዝ ኢጣልያኖች ከመሃዲስቶች ጋር ባደረጉት ውጊያ ባህታ ሓጎስ የአንበሳውን ድርሻ ይዞ ነበር።

አጤ ዮሃንስ መተማ ላይ ሲገደል የባህታ እና የኢጣልያውያን ስምረት አደገ። ባህታም ቢሆን ታማኝ የኢጣልያ አገልጋይ መሆን በመቻሉ፤ የካቶሊክን እምነት በመቀበሉ ጀኔራል ባልዲሴራ ማእረግ አልብሶ፤ አከለጉዛይን ሾመው። ኢጣልያ መረብ ምላሽን ይቆጣጠር ዘንድ የባህታ ሚና ከፍተኛ ስለነበር ሹመቱ የሚጠበቅ ነበር። ስሙ እየገነነ መሄድ በመቻሉም ሃይሉና ሃብቱ ደረጀ። በርግጥም እያደር የኢጣልያን መሬት የመያዝ ፍላጎት እስኪገነዘብ ድረስ ባህታ ከኢጣልያ ጋር እየሰራ ቆይቷል። ከጊዜ ጋር አባ ዮሃንስ ኩልቦ የነገረውን በተጨባጭ ማየትና ማረጋገጥ ቻለ።

መሬት የመያዝ ሽሚያው ፈጣን ነበር።

ከ200 በላይ ኢጣልያውያን እና ሌሎች የውጭ አገር ሰዎች ምርጥ ምርጡን የቆላ መሬት እየመነተፉ በቆሎ፣ ባቄላና ቲማቲም ማምረት ጀመሩ። ከ1893 እስከ 1895 ባለው ጊዜ ውስጥ መሬት ነጠቃው የጦፈበት ጊዜ ሆነ። ከ520 ሄክታር በላይ መሬት በውጭ አገር ሰዎች ተያዘ። አስመራ ዙሪያ፣ ጸዓዘጋ፣ ድባርዋ፣ ዓዲ ባሪ፣ ገለብ፣ ዓንሰባ፣ ሕርጊጎና ሰሓጢ ሰፈሩ። እዚህም እዚያም የመሬት ነጠቃ ወሬ ሲሰማ ባህታ ሓጎስ የአባ ዮሃንስን ማስጠንቀቂያ ማስታወሱ አልቀረም። በድርቁ ምክንያት ጎጆውን ዘጋግቶ የሄደውን የአባወራ መሬት ጠቀለሉ። ድርቁ አልፎ ክረምቱ ሲመለስ ከተሰደዱበት የሚመለሱ ገበሬዎች መሬታቸው ተይዞ ጠበቃቸው።

ይህ ጊዜ ለባህታ ወሳኝ ጊዜ ለመሆን በቃ።

ኩዶፈላሲ ላይ የኢጣልያ ገበሬዎች ከነቤተሰባቸው መስፈራቸው ሲሰማ ባህታ ተቀማጭነቱ መንደፈራ ለነበረው ጊላጊዮርጊስ ደብዳቤ ላከለት። የደብዳቤው ይዘት ባጭሩ ኩዶፈላሲ ሄዶ ስለሚነገረው የሰፈራ ወሬ እንዲያጣራለት የሚጠይቅ ነበር። በሁለት ሳምንት ጊዜ ውስጥ ጊላጊዮርጊስ ለደጃች ባህታ ምላሽ ላከ። ደብዳቤው ዝርዝር ነገሮች ጭምር አስፍሮ ነበር።

"ኩዶፈላሲ መሄድ ሳያስፈልገኝ ነገሩን አውቀዋለሁ። አባቴና ወንድሞቼ ከመሬታቸው ተፈናቅለዋል። ማንበብና መጻፍ የማይችሉ፣ በአገራቸው በደህነት ላይ የነበሩ 61 ኢጣልያውያን ገበሬዎች ኩዶፈላሲ ገብተው መሬት፣ በሬ፣ ላሞች፣ በጎችና አጋሰሶች ተሰጥቷቸዋል። ሰፋሪዎቹ ሴቶችና ህጻናት ጭምር ሲሆኑ፤ ፓሌርሞ ከተባለ ቦታ የመጡ መሆናቸውን ራሳቸው ይናገራሉ። ለሚቀጥለው ክረምት ለእርሻ እንዲደርሱ ለእያንዳንዱ ሰፋሪ እስከ ሃያ ሄክታር መሬት ተሰጥቷል። በኢጣልያ የሚኖሩ አይሁዳውያንም በብዛት እንደሚመጡ እየተሰማ ነው። አባቴና ወንድሞቼ መሬታቸውን በመነጠቃቸው አገልጋይነት ተቀጥረው ለሰፋሪዎቹ እያረሱ ነው።"

ጊላጊ ደብዳቤውን ሲቋጭ እንዲህ አለ፣

"አቤቱታ ለማቅረብ ወደ አስመራ እሄዳለሁ።"

(ለኢጣልያ ታማኝ የነበረው ጊላጊ በሐላይ ጦርነት ማግስት በካራቢኔሪዎች ተገደለ። የክብር አሟሟት ነበር የሞተ። የማጭቱ መንስኤ የአባቱ መሬት ነበር። በርስታቸው ላይ ኢጣልያውያን ገበሬዎችን ለማስፈር አባቱና ወንድሞቹ ሲፈናቀሉ ይህን የመሬት ጉዳይ ለሚከታተለው ቢሮ ለማመልከት አስመራ ሄደ። የሚመለከታቸውን አነጋግሮ መፍትሄ ማግኘት አልቻለም። ተሰፋ ባለመቁረጥ ወደ ኤርትራ አገረ ገዢ ቢሮ ሄደ። ደጃፍ ላይ የቆሙ ተራ ጥበቃዎች መግባት ከለከሉት። ተራ ዘበኞች ጉዳዩ ምን እንደሆነ እንዲነግራቸው ከንቀት ጋር ሲጠይቁት ጊላጊዮርጊሰ ራሱን መቆጣጠር አስኪያቅተው ቁጣውን ገለጸ። በጊላጊ ድፍረት የተናደደ አንድ ካራቢኔሪ ክብረ ነክ ቃል ካንደበቱ አፈለቀ። ጊላጊዮርጊስ ሽጉጥ ታጥቂል ብለው አልገመቱም። ቢታጠቅም ይጠቀምበታል ብለው ሊያስቡ አይችሉም ነበር። ይህን ያወቁት ጊላጊዮርጊስ ሽጉጥ መዞ ቃታ ስቦ የሰደበውን ዘበኛ ከገደለ በሁዋላ ነበር። በተደረገው የተኩስ ልውውጥም ሌላ ሁለት አቁሰሎ ጊላጊ ህይወቱን ከፈለ።)

* * *

ገብረመድህን ወደ ኑረነቢ ከመላኩ ቀደም ብሎ ባህታ ሓጎስ ለትግራዩ ራስ መንገሻ መልእክት ልኮ ነበር። የመልእክቱ ይዘት፣ “ጣልያን ስር ሳይሰድ ሊወገድ ይገባል። እኛን ማንበርከክ ከቻሉ በቀጣይ መረብን ተሻግረው ወደናንተ መምጣታቸው አይቀርም። ተባብረን ወደ መጡበት እንመልሳቸው።” የሚል ነበር።

ራስ መንገሻ ለደጃች ባህታ ስለ ሰጠው ምላሽ የሚገልጽ የጽሁፍ መረጃ የለም። ራስ መንገሻ ጉዳዩን ወደ አጤ ምኒልክ ማሳለፉ ግን ተረጋግጧል። አጤ ምኒልክ ከኢጣልያ ጋር ስምምነት ስለነበራቸው “ይቆይ” ሲሉ የባህታን አሳብ ሳይቀበሉ ቀርተዋል።

ደጃዝማች ባህታ የራስ መንገሻንና የአጤ ምኒልክን አለመተባበር እንደተረዳ “ኤርትራ ላይ በተበታተነ መልኩ ጸረ ኢጣልያ ትግል ወደ ሚያካሂዱ ሽፍቶች መልእክተኛ መላክ ጀመረ። ገና ተቃውሞ ወዳላሰሙት ጭምር ጥሪ ሰደደ። የመልእክቱ ይዘት በጸረ ኢጣልያ አቋም ከጎኑ እንዲሰለፉ የሚጠይቅ ሲሆን፤ “መብታችንን የገፈፈ፣ መሬታችንን የነጠቀ፣ እርሻ እንዳናርስ ከከለከለን ከባሕር የመጣ መንግስት ነጻ አወጣችሁዋለሁ።” የሚል ቃል ነበረበት። የደጃዝማች ባህታ ሓጎስን ጥሪ ተቀብለው ሰገነይቲ ከደረሱት መከካል ብሌናይ የምራራ ሽፍቶች ቀዳሚዎቹ ነበሩ።

ታህሳስ 14 1894 ባህታ ሓጎስ በይፋ ክተት አወጀ። ጸረ ኢጣልያ ቅኝ አገዛዝ እንቅስቃሴውን በተግባር ጀመረ። በቅድሚያ ሰገነይቲ ወደሚገኘው የኢጣልያ ቅኝ ገዢ ጽህፈት ቤት በመሄድ ጆቫኒ ሴንጉኔቲ የተባለውን የመገናኛ ክፍል ሹም አሰረው። መሬት ላይ ጥለው እጅና እግሩን ሲያስሩት ጆቫኒ “ቪቫ ኢታልያ” ሲል መፈክር ማሰማቱ ይነገርለታል።

በመቀጠል ባህታ ሓጎስ የቴሌግራፍ መስመሮችን ቆራረጠ። ጆቫኒ ሴንጉኒቲ መታሰሩና የቴሌግራፍ መስመር መቋረጡ እንደተሰማ ከረን የነበረው ጀኔራል ኦሬስቴ ባራትዬሪ አስመራ ወደነበረው ማጆር ፒየትሮ ቶዘሊ መልእክት ላከ። ሰራዊቱን ይዞ ሰገነይቲ እንዲገባ አዘዘው። ቶዘሊ ከአንድ ቀን በሁዋላ ማዕረባ ደረሰ። ቶዘሊ በቀጥታ ወደ ግጭት አልገባም። ጊዜ ለመግዛት ከባህታ ጋር ድርድር ጀመረ። በሁለት ቀናት ውስጥ የሚጠብቀው ተጨማሪ ሃይል ሲደርስለት ግን ንግግሩን አቋርጦ ሰገነይቲ ገባ።

ሓላይ በተባለ ቦታ የኢጣልያ ወታደሮች ሰፍረው ነበር። ጉብጣን ካስተለዚ በተባለ መኮንን የሚታዘዙ 250 ወታደሮች ነበሩ። ቶዘሌ ከማዕረባ ወደ ሰገነይቲ ሲያመራ፤ ባህታ ሓላይ ላይ የሰፈሩትን ኢጣልያውያን ቀድሞ ለመምታት ገሰገሰ። ሁለት ሺህ የሚገመት ሃይል የነበረው የባህታ ጦር በካስተሌዚ የሚመሩትን ወታደሮች ላይ የበላይነት ይዞ ሶስት ሰአት ያህል ተዋጋ።

የካስተሌዚ ምሽግ መፍረስ ሲጀምር ማጆር ቶዘሊ አራት መድፎችና ሶስት ሺህ ተዋጊ ይዞ ከጀርባ ተኩስ ከፈተበት።

በተደረገው ውጊያ ሚዛኑ ተገለበጠ። ባህታ ሓጎስ በመትረየስ የእሩምታ ተኩስ ተመትቶ ወደቀ። የባህታ ሰራዊት ለመቋቋም ቢሞክርም ከጀርባ የመጣበትን ሃይል ሊመክት አልቻሉም። በብዛቱም ሆነ በመሳሪያ ብቃቱ ከአቅማቸው በላይ ሲሆንባቸው ወደ ደቡብ አግጣጫ አፈገፈጉ። በወቅቱ እስከ መሬት በወረደው ጉም ተሸሽገው ገለል ማለት ቻሉ።

* * *

ከሓላይ ውጊያ በሁዋላ የኢጣልያ ቅኝ ገዢ ጣቱን ወደ አባ ዮሃንስ ቀሰረ። ካራቢኔሪዎች የላዛሪስት ካቶሊካውያንን ጽህፈት ቤትና ቤተ አምልኮ ወረሩ። ሰነዶቻቸውን ሰብስበው አቃጠሉ። የፈረንሳይ ደናግል ይሰሩት የነበረውን ስራና የሚያሳድጓቸውን ልጆች ንኡሳን አሕዋት ካፑቺነ (Capuchins) ተረከቧቸው። እናም ኤርትራን ለቆ እንዲወጣ ለአባ ዮሃንስ የጊዜ ገደብ ተሰጠው።

አባ ዮሃንስ አማንያኑን ሰብስቦ በመሰናበት ለጉዞ ተነሳ። የከረን ካቶሊክ አማንያን የመንፈስ መሪያቸው ላይ በደረሰው ሁኔታ እጅግ ቢያዝኑም አጅበው ከመሸኘት በቀር ሌላ አቅም አልነበራቸውም። መንፈሳዊ አባታቸውን እስከ ዓዲተከሌዛን ድረስ ለመሸኘት ተነሱ። በመንገዳቸው ላይ አባ ዮሃንስ ወደ ዝርዝር ነገሮች ውስጥ ሳይገባ ስለ ሰው ልጆች ክብር አንስቶ ሰበከ። በባህታ ሓጎስ አመጽ ምክንያት አገር ለቆ እንዲሄድ መታዘዙንም አጫወታቸው፣

“የሰው ልጅ አብቅሎ የሚመግበውን የአባቶቹን የእናቶቹን መሬቱን ካጣ በዚህች አለም ላይ ሌላ ምን የሚቀረው ነገር ይኖረዋል? መሬት አገር ነው። አገር ሰው ነው። ሰው መሬት ነው።

የሚለያዩ አይደሉም። መሬት የሌለው ሰው ምንም የለውም።”

አድም አሳዳጊና መንፈሳዊ አባቱን እስከ ዓዲተከሌዛን ለመሸኘት ከወጣው ህዝብ ጋር አብሮ ነበር። አረፍ ባሉበት ጊዜ አድም ከአባ ዮሃንስ ጋር ጥቂት አወጋ፣

“ኤድዋር አልመጣም እንዴ?” ሲል ጠየቀ አባ ዮሃንስ።

“አልመጣም።”

“ምነው?”

“ከረን የለም።” አለ ስቅቅ ብሎ።

አባ ዮሃንስ ደንገጥ ብሎ ጠየቀ፣

“ኤድዋር ልጇ የት ሄደ?”

“ወደ ጥልያኖች ሄዷል። አስካሪ ሆኗል።”

አባ ዮሃንስ በረጅሙ ተነፈሰ። ገጽታው ላይ መራር መከፋት ተስተዋለ። ሊደብቀው የማይችል ሃዘን ፊቱን ሸፈነው። በተሰላቸ ስሜትም ቀጣዮቹን ጥያቄዎች ጠየቀ፣

“መቼ ሄደ?”

“አንድ ሳምንት ይሆናል።”

“ምነው ሳይነግረኝ?”

“እንዳይከለከል ሰግቶ ይሆናል።”

አከታትሎ አድም ሲያስጨንቀው የነበረ አንድ ጉዳይ አነሳ፣

“ስለ አባታችን የተሰማ ወሬ ይኖር ይሆን?”

አባ ዮሃንስ ጢሙን ጎተተ።

የሚያውቀውን ለአድም መንገር እንደሚገባው አሰበ። ምናልባት ከዚህ በሁዋላ ስለማይገናኙ ሁሉን ለመንገር ጊዜው መሆኑን በመረዳት ረጋ ብሎ በአጭሩ አጫወተው፣

ኑረነቢ የሸፈተበት ምክንያት በግልጽ እንደማይታወቅ፤ ምጽዋ በዘበኛነት ስራ ላይ በነበረ ጊዜ ግን አንድ ኢጣልያዊ ክብር የሚነካ ቃል ተናግሮት በዚያ ተቀይሞ እንደነበር ጠቀሰ። በጥቅሉ

የባእድ ገዢዎች እየተፈራረቁ በሚፈጽሙት ግፍና ጭቆና ተከፍቶ ሸፍቶ ሊሆን እንደሚችል ግምቱን አኖረ።

ኑረነቢ በሸፍትነት ዘመኑ ገልዓሎ አካባቢ ከኢጣልያ ወታደሮች ጋር በተደረገ የተኩስ ልውውጥ ከመገደል ለጥቂት ተርፎ ማምለጡንም አብራራ። ከዚያም አሕመድ ሳልሕ ወደ ተባለ ሸፍታ ገባ። አሕመድ ሳልሕ ሸፍትነቱን በመተው ወደ ሳዑዲ አረቢያ ሲሻገር ኑረነቢ ጥቂት የቦገስ ሰዎችን ይዞ በፍሽይ ምራራ ሸለቆ ውስጥ መንቀሳቀስ ጀመረ።

አባ ዮሃንስ እንደልማዱ ጢሙን እየነተተ እንዲህ አለ፣

“ስለ አባታችሁ በመጨረሻ የሰማሁት ከነሰዎቹ ወደ ደጃዝማች ባህታ ገብቶ ሓላይ ላይ በተደረገው ጦርነት መካፈሉን ነው። ባህታ ሲገደል የባህታ ወንድሞች መረብ ወንዝን ተሻግረው ወደ ትግራይ አፈግፍገዋል። ገብረመድህን የተባለው የባህታ ሓጎስ የበኩር ልጅ ግን መረብን አልተሻገረም። ሳሆ ምድር ላይ ከነተከታዮቹ ቀርቷል። ኑረነቢ ከገብረመድህን ጋር መኖሩን አረጋግጫለሁ። ስለ አባታችሁ የማውቀው ይህን ያህል ነው።”

አድም በተመስጦ አዳምጦ ሲያበቃ፣ ቁና አየር ተነፈሰ፣

“አባታችን ስላለንበት ሁኔታ ያውቃል?”

“ያውቃል። ባህታ በደብዳቤ ይህን አረጋግጦልኛል። ኑረነቢ መጥቶ ሊያያችሁ ያልቻለው ገና ልጆች ስለነበራችሁ እንዳትሳቀቁ በሚል ነው። አሁን ነፍስ አውቃችሁዋል። ሁሉን ብታውቁ ጉዳት የለውም። ዋናው ነገር እናንተ ደህና መሆናችሁ ነው። በመጪው ጊዜ አባታችሁን በህይወት ለማየት ከቻላችሁ መልካም እድል ይሆናል።”

አድም ቅጭም ብሎ ብዙ ቆየ። አባ ዮሃንስ ጥቂት አከለ፣

“ልጆች ምንጊዜም ከወላጆቻቸው ጋር ቢያድጉ ይመረጣል። ቢያንስ ከአባት ወይም ከእናታቸው አንዱን ማግኘት አለባቸው። ሁለቱንም ባንድ ጊዜ ማጣት ክፉ እድል ነው። ያላለቀ ፍቅርና ፍላጎት ልብ ውስጥ ይቀርና ሙሉ ህይወትን ይበጠብጣል። ቢሆንም አምላክ በጥበቡ እንዲህ ያለውን ጎደሎ ይሞላዋል።”

ዓዲተከሌዛን ደርሰው እረፍት ካደረጉ በሁዋላ የከረን

ሸኚዎች ተመለሱ። አባ ዮሃንስን እስከ ምጽዋ የሚያጅቡ የዓዲተከሌዛን ሰዎች ተረከቡት። አድም እስከ ምጽዋ ለመሸኘት ፍላጎት ቢያሳይም ከለከለው። ቢሆንም ወደ ምጽዋ እስኪነሳ ድረስ በአባ ዮሃንስ ፍላጎት አድም ዓዲተከሌዛን ቆየ።

በዚያን ቀን ምሽት አባ ዮሃንስ አድምን ለብቻ አናገረው፣

“ጣልያኖች አንዳንድ ሰነዶቻችንን ወስደውብናል።”

እንደገና በጥልቅ ሲያስብ ቆየና፣

“በየእለቱ ማስታወሻ የምይዝበትን ጥራዝ አላገኙትም። ሻንጣዬን የበረበሩት፤ መኝታ ቤቴን ገለባብጠው የፈተሹት ያንን ጥራዝ ለማግኘት ነበር። በአምላክ ፈቃድ ተሰወረባቸው። እንግዲህ ለአንተ አንድ ምስጢር እነግርሃለሁ።”

አባ ዮሃንስ የአድምን ራስ አሻሸ፣

“ዋናው ቅጂ እጄ ላይ አለ። ምጽዋ ላይ ወይም መንገድ ላይ ከፈተሹኝ ግን ሊወስዱብኝ ይችላሉ። ቅጂው ከእርግቦች ጎጆ ጀርባ በአንድ የእንጨት ሳጥን ውስጥ ተቀምጧል። ካምፑ እንግዲህ ለካፑቺነ ተሰጥቷል ተብሏል። እነርሱ ናቸው የሚረከቧችሁ። አባ ኩልፕ ባራትዬሪ በተገኘበት በቅርብ ጊዜ ውስጥ የንብረት ርክክብ ለማድረግ ቀጠሮ ይዘዋል። የተመቸ ጊዜ አይተህ፤ ሰው በማይኖርበት ጊዜ ጠብቀህ እርግቦቹን የምትመግብ በመምሰል ያቺን ጥራዝ ትወስዳለህ። ጥራዙን ከረን ከሚገኙ የአባትህ ዘመዶች ለአንዱ በአደራ ስጥ። እኔ ወደዚህ ተመልሼ እንድመጣ አይፈቅዱልኝም። በማንኛውም ጊዜ ግን እኔ የምልከው ሰው ወደ አንተ ይመጣል። ሰው ካልላክሁ ግን ዋናውን ቅጂ አልነኩብኝም ማለት ነው። ላንተው ማስታወሻ ትሁንህ። ለሌላ ሰው ግን አሳልፈህ መስጠት የለብህም።”

አባ ዮሃንስ ደጋግሞ ይህንኑ ለአድም አስጠናው።

ዓዲተከሌዛን ላይ አባ ዮሃንስን የተቀበሉ ወገኖች መላልሰው የሚጠይቁት ጉዳይ የባህታ ሓጎስ አመጽን በተመለከተ ነበር። አባ ዮሃንስ በተመሳሳይ የመሬት ጉዳይ ላይ እያነሳ ተናገረ። የኢጣልያን አስተሳሰብ ባህታ የመገንዘብ እድል እንደነበረው አወጋ፣

“ባህታ ጊዜ ወስዶ የጣልያኖቹን አስተሳሰብ መገንዘብ

ችሏል። ከመሬት ነጠቃው ባሻገር ክፉኛ ያስቆጡት አንዳንድ ጥቃቅን ነገሮችም ነበሩ። ባህታ በጽሁፍ እንደገለጸልኝ ጣልያኖቹ ለፍትወተ ስጋ የሚጠቀሙባቸውን ደም ግባታቸውና አጥንታቸው ማለፊያ የሆኑ ሴቶችን እንዲሰበስብላቸው በመጠየቁ በጣም አዝኖ ነበር። ጣልያኖች ወንዶቹን ለጦርነት እየወሰዱ ነው። ልጃገረዶቹን ደግሞ ለስሜት ማርኪያ ፈለጓቸው። እንዲህ ያለውን ተግባር እግዚአብሄር አይወደውም። ይህን የመሰለ አሳባቸው በመጨረሻ ደጃዝማች ባህታን ተስፋ ሳያስቆርጠው አልቀረም። ጠርጎ ባሕር ሊጨምራቸው አስቦ ነበር። አልሆነለትም።"

አባ ዮሃንስ ረጋ ብሎ ምክሩን ቀጠለ፣

"እኔ ቄስ ነኝ። ተዋጉ ብዬ አልመክራችሁም። ምን ማድረግ እንዳለባችሁ የምታውቁት እናንተው ናችሁ። እግዚአብሄር ከጎናችሁ ይሆን ዘንድ እጸልይላችሁዋለሁ። የሰው ልጆች ሁሉ በአምላክ አምሳል የተፈጠሩ እኩል ሰዎች ናቸው። ልጆቻችሁ የሚኮሩባችሁ አባቶች ሁኑ! ዘራችሁ ይብዛ! ዘራችሁ ይባረክ! ሳትለያዩ አንድ ሁኑ!"

(አባ ዮሃንስ ግን አልተመለሰም። መልእክተኛም ወደ ኢድም አልላከም። አባ ዮሃንስ ኩልቦ በኤርትራ ቆይታው ያጠናውን መጽሃፍ ጽፎ ሲያበቃ፤ በ1921 በ78 አመት እድሜው ፓሪስ ላይ አረፈ።)

ምእራፍ ፱

ዓዲ ቀይሕ ታየ!
ባራትዬሪ አፍሮ - ሲገሰግስ አድሮ

ባህታ ሓጎስ ሓላይ በተባለ ቦታ ከተገደለ በሁዋላ ተከታዮቹ እስከ ምድር በወረደው የተሰያት ጉም ውስጥ ተሸሽገው ማፈግፈግ ቻሉ። ኑረነቢ እግሩ ላይ ቆስሎ መራመድ ባለመቻሉ በወሳንሳ ተሸክመውት ሲጓዙ ከጀርባ የኢጣልያ ተኩስ ዘነበባቸው።

ተደጋግሞ የተተኮሰው መድፍ አላገኛቸውም።

የባህታ ተከታዮች ወፍራም ጉም እስከ ምድር ያወረደላቸውን አምላክ እያመሰገኑ ነጎዱ። በመንገዳቸው የተሰዋ መሪያቸውን ስም በቁጭት እያነሱ፤ ወደ ኢትዮጵያ ድንበር አግጣጫ አፈገፈጉ። ተስፋ የመቁረጥ ነገር ግን አልታየባቸውም። ባሕር ወለዱን ገዢ የመበቀል ብርቱ ቂም ቋጥረው ነበር። ሲጓዙ አምሸተው እኩለ ሌሊት ላይ በአንድ ኮረብታ ግርጌ አረፍ አሉ። እረፍታቸው አጭር ነበር። በዚያች አጭር እረፍት ወቅት ወዴት መሄድ እንዳለባቸው አንስተው ሲወያዩ መግባባት አልቻሉም። ልዩነቱ በሰንጋልና በገብረመድህን መካከል ነበር።

ሰንጋል፣ "ትግራይ እንግባ።" ሲል ገብረመድህን ተቃወመ። "ከሳሆ መንደሮች ተሸሽገን፣ እዚሁ አካባቢ ሆነን ሃይላችንን

እናጠናክር።" አለ። ኑረነቢ የቆሰለ ቢሆንም የገብረመድህንን አሳብ በመደገፍ "እንደገና ተጠናክረን ማጥቃት አለብን" አለ።

በዚህ ልዩነት ሊግባቡ ባለመቻላቸው የባህታ ሓጎስ ሰራዊት ለሁለት ተከፈለ። ሰንጋል 500 የሰው ሃይል ይዞ ወደ ትግራይ ሲያቀና ገብረመድህንና ኑረነቢ ከነተከታዮቻቸው ከ300 የሰው ሃይል ጋር ወደ ሳሆ ኮረብቶች አግጣጫ ተጓዙ። ሌሊቱን የሳሆ መድሃኒት አዋቂዎች መጥተው ኑረነቢን አከሙት። ዳሩ ጥቂት ሳምንታት ተሸሽገው መቆየት ቢችሉም፤ ጣልያን መረጃ አጊኝቶ አሳሽ ሃይል ላከባቸው። የመጣውን ሃይል ሊቋቋሙት እንደማይችሉ ሲያውቁ አፈገፈጉ። ጣልያን እየተከታተለ ሲያጠቃቸው አንድ ኮረብታ ላይ የደፈጣ ቡድን አስቀምጠው ጥቂት አደጋ ካደረሱ በሁዋላ እንደገና አፈገፈጉ። በማፈግፈግ ላይ ሳሉ ታዲያ የሰንጋል ውሳኔ ልክ እንደነበር አንስተው መጨዋወታቸው አልቀረም። እናም ግራዝማች ገብረመድህንና የኑረነቢ ተከታዮች በጥቅሉ ከመቶ ሃምሳ በላይ ጠመንጃ ጋር ታህሳስ 1894 መረብን ተሻግረው ኢትዮጵያ ገቡ።

ራስ መንገሻ የባህታን መገደል ሲሰማ "እንኳን ደስ ያላችሁ" የሚል መልእክት ወደ አስመራ መላኩ ይነገራል። ጣልያኖች ግን ይህንን እንደ ሽንገላ ወሰዱት። የባህታ ወንድም ሰንጋል፤ የባህታ ልጅ ገብረመድህን ትግራይ መመሸጋቸውን ምክንያት በማድረግ መረብን ተሻግረው እስከ አድዋ ድረስ አሰሳ አካሂደው ተመለሱ። ራስ መንገሻ በበኩሉ ኢጣልያ ድንበር ተሻግራ ለፈጸመችው ውጊያ አጸፋ ለመመለስ በሚል ወደ ኤርትራ ገብቶ ጣልያንን አጠቃ። ግን አልተሳካለትም። መከላከያ መሸገው በመጠበቅ ክፉኛ መቱት።

ራስ መንገሻ ከሰገነይቲ ሲሸሽ እቃዎቹን መሰብሰብ አልቻለም ነበር። ሌሊቱን ጣልያን ይማርከኛል ብሎ ስለሰጋ ጥሎ ሸሸ። በነጋታው ጣልያን ወደ ራስ መንገሻ ሰፈር ሲደርስ ብዙ ጠቃሚ ደብዳቤዎች አገኘ። ራስ መንገሻ ይጠቀምባቸው የነበሩ ሽቶ፣ የወርቅ ሰአት፣ በብረት የተለበጠ ሽፋን ያለው መጽሃፍ ቅዱስ ጭምር ተዝረክርከው ወድቀው ተገኝተዋል። ከደብዳቤዎቹ መካከል አንዱ አባ ዮሃንስ ለራስ መንገሻ የጻፈው ይገኝበታል። ይህም ባህታ ሓጎስን እንዲረዱ የሚመክር ደብዳቤ ነበር። የአባ ዮሃንስ ደብዳቤ በኢጣልያኖች እጅ መግባቱ ግን ፋይዳነቱ ለታሪክ ብቻ ነበር።

ምክንያቱም አባ ዮሃንስ ጥር 22 1895 ከኤርትራ ተባርሮ ነበር።

ጣልያን ራስ መንገሻን ተከታትሎ ተመልሶ መረብን ተሻገረ። ማሳደዱን በመቀጠልም ዓዲግራትና አድዋን ያዘ። በዚህም አጤ ምኒልክ ክተት አውጀው ከፊኒፊኔ ነቀሉ። ቀዳሚ ዘማቹ ራስ መኮንን አምባላጌ ላይ ማጆር ቶሴሊን በቀላሉ ድል አድርጎ ወደ መቐለ ጉዞውን ቀጠለ። አስከትሎም መቐለ የመሸገው የኢጣልያ ጦር ሳይዋጋ በውሃ ጥም ብቻ ተፈትቶ ወደ አድዋ በማፈግፈጉ፤ ታሪካዊው የአድዋ ጦርነት ሊካሄድ ቀኑን ይጠብቅ ጀመር።

በዚህ ጊዜ ከሓላይ ውጊያ የተረፈው የባህታ ተከታይ ከአጤ ምኒልክ ጦር ጋር ለመቀላቀል ችሏል። አጤ ምኒልክም በክብር ተቀብሎ በተገቢው ደረጃ ካስተናገዳቸው በሁዋላ ገብረመድህንና ኑረነቢ የሚመሩትን ሃይል በልዩ ሁኔታ ጀኔራል ባራትዬሪን ለመማረክ ከተደራጀው የፈረሰኛ ቡድን ጋር ቀላቀሏቸው።

* * *

ጀኔራል ኦሬስቴ ባራትዬሪ በማፈግፈግና በመዋጋት መካከል እያመነታ ሲጨነቅ ቆይቶ ነበር። ልቡ እሁለት ተከፈለበት። የቀረው ቀለብ ለሁለት ወይም ለሶስት ቀናት የሚበቃ ብቻ ነበር። ቀደም ሲል የምግብ እደላው ለነጭ ወታደሮች ዳቦ፣ ለኤርትራውያን ዱቄት ነበር። ለነጭ ወታደሮች ወይን ጠጅ ጭምር ይታደል ነበር። ጦርነቱ ከመጀመሩ ጥቂት ቀናት በፊት ጀምሮ ግን የወይን ጠጅ እደላው ተቋረጠ። ለነጮቹ ወታደሮች የተጋገረ ዳቦ ማደል ባለመቻሉ ለኤርትራውያን እንደሚሰጠው የስንዴ ዱቄት ይሰጣቸው ጀመር። ኢጣልያውያኑ የተሰጣቸውን ዳቦ እንዴት ጋግረው መመገብ እንዳለባቸው አላወቁም። ስለዚህ ኤርትራውያን እንዲያስለምዷቸው ታዘዙ። በኤርትራውያን የተዋቀረው ስምንት ባታሊዮን ሰራዊት ሲሆን፤ ከጦርነቱ የፊት መስመር እንዲሰለፉ ተገደው ነበር።

መጋቢት 1 1896 ማለዳ የአድዋ ጦርነት ተጀመረ።

እዚህች ቀን ላይ ለመድረስ ግን ብዙ ችግሮች ታልፈዋል። ጦርነቱ ከመጀመሩ ጥቂት ቀናት በፊትም በተመሳሳይ አጤ ምኒልክም በጣም ተጨንቆ ነበር። የያዘው ቀለብ ሰራዊቱን ከሶስት ቀናት በላይ እንደማይመግብ ተነግሮታል። እና ጦርነቱ በኢጣሊያ በኩል

እንዲጀመር ከፍተኛ ፍላጎት ነበረው።

የካቲት ማብቂያ 1896 ባራትዬሪ ከበታቹ የሚገኙ አራት የጦር አዛዥ ጄኔራሎችን ሰበሰበ። አንድ ውሳኔ የግድ መወሰን ነበረበት። ይህም ውሳኔ ከመዋጋት ወይም ከማፈግፈግ አንዱ መሆን ነበረበት። ባራትዬሪ ስብሰባውን ሲከፍት፤ ትግራይን ሙሉ በሙሉ በመተው በቅድሚያ ወደ ሰንዓፈ፤ በመቀጠል ወደ አስመራ ለማፈግፈግ ማሰቡን፤ ዳሩ ግን ገና ውሳኔ ላይ አለመድረሱን ገለጸ።

ጄኔራሎቹ ግን ይህን አሳብ አልተቀበሉም። ከተሰብሳቢ ጄኔራሎች አንዱ ዳቦርሚዳ ይባላል። በኢጣሊያ ህዝብ ጥሩ ስም የነበረው ዝነኛ መኮንን ሲሆን፤ በዚህ ጦርነት ጀብዱ ይፈጽማሉ ተብለው ከሚጠበቁት የጦር መሪ ጄኔራሎች መካከል አንዱ ነበር።

የባራትዬሪን የማፈግፈግ አሳብ በሶስት ምክንያቶች ተቃወመው። በቅድሚያ "የኢጣልያ ህዝብ ከምናፈገፍግ ተዋግተን ብንሰዋ ይመርጣል" ሲል ተንደረደረ። "ብናፈገፍግ ወታደሮቻችን የመዋጋት ሞራላቸውን ያጣሉ" ሲል ቀጠለ። በመጨረሻ፣ "የአቢሲንያ ወታደሮች የመጓዝ ፍጥነታቸው ከኛ የላቀ ስለሆነ በማፈግፈግ ወቅት ደርሰው ሊያጠቁን ይችላሉ። ስለዚህ ከምሽጋችን ወጥተን ማጥቃቱ ይመረጣል።" ሲል አጽንኦት ሰጥቶ አሳቡን ገለጸ። ሌሎቹ ተሰብሳቢዎችም የዳቦርሚዳን አሳብ ተቀብለው ሲያበቁ፤ ተጨማሪ መረጃ አከሉ። ይህም የአጤ ምኒልክ ሰራዊት ምግብ ፍለጋ በመበታተን ላይ መሆኑን፤ አብዛኛቹ መሪዎቻቸውን በመተው ወደ አገራቸው በመመለስ ላይ መሆናቸውን፤ ጠቅላላ በግንባር ያለው የአቢሲኒያ ሰራዊት ከአስራአምስት ሺህ እንደማይበልጥ በመጥቀስ የተሻለው አማራጭ ማጥቃት መሆኑን ገለጹ።

የመጨረሻው ውሳኔ የባራትዬሪ ነበር።

በስብሰባው ማብቂያ ላይ፣

"ዛሬ ሌሊት ከአንድ ሰላይ አስፈላጊ መረጃ በመጠባበቅ ላይ ነኝ። መረጃውን ከሰማሁ በሁዋላ ውሳኔዬን አሳውቃችሁዋለሁ።" በማለት ስብሰባውን ዘጋ። ባራትዬሪ የመጨረሻውን ውሳኔ ለመወሰን የሚጠብቀው አውዓሎም ሓረጎት የተባለ ሰው ነበር።

ባራትዬሪ በአውዓሎም ሓረጎት ላይ ሙሉ እምነት ነበረው።

በግልባጩ ለኢትዮጵያ እየሰራ ሊሆን ይችላል የሚል ጥርጣሬ አልነበረውም። አውዓሎም ከአጤ ምኒልክ ሰፈር እየዋለ የሚያቀርብለትን መረጃ ለመጠራጠር የሚያበቃ ፍንጭም አላገኘም።

የካቲት ማብቂያ ላይ በተደረገው ስብሰባ ባራትዬሪ "አንድ ሰላይ እየጠበቅሁ ነው።" እንዳለው በርግጥም አውዓሎምን በጉጉት ጠበቀ። በዚያን እለት ምሽት አውዓሎም ከአጤ ምኒልክ ሰፈር ሰንብቶ ወደ ባራትዬሪ ሲመለስ ለባራትዬሪ የነገረው የተሳሳተ መረጃ በኢጣሊያ ታሪክ ውስጥ በቁጭት ሲወሳ ይኖራል።

ተክለጻድቅ መኩሪያ አጤ ምኒልክ በተባለ መጽሃፉ እንደተረከው፣ አጤ ምኒልክ ጭንቀት ላይ ነበሩ። ለሰራዊቱ ቀለብ እየጨረሱ ነበር። ፈረሶቹም የሚበሉትን ጨርሰዋል። የሚጠጣ ውሃ ለፈረስ ቀርቶ ለሰው የሚሆንም እጥረት ማጋጠም ጀመረ። የአካባቢው ህዝብ ተራቆተ። የአቅርቦት አቅም አልነበረውም።

በኩረጽዮን ሃይሌ እንደተረከው ደግሞ፤ በዚህ ጊዜ አጤ ምኒልክ ትግራይን ለኢጣልያ ለመተው፤ ራስ መንገሻ በኢጣልያ ስርም ቢሆን ትግራይን መምራቱን እንዲቀጥል ለመደራደር በማሰባቸው የካቲት 28 መኳንንቱን ሰብስበው መከረው ነበር።

ራስ መንገሻ የአጤ ምኒልክን አሳብ ለመቀበል ተቸገረ። ሁለት ምርጫ ነበረው። ከአጤ ምኒልክ ጋር ወደ ሸዋ መሄድ ወይም ትግራይ ላይ በኢጣልያ ስር መቅረት? የአጤ ምኒልክ አሳብ ጠቅልሎ ከመጥፋት መሰንበትን የመምረጥ አማራጭ ነበር።

መንገሻ በዚህ አሳብ ላይ ለመምከር የሁለት ቀናት ጊዜ እንዲሰጠው ጠየቀና ወደ ሰፈራቸው ተመለሱ። በምክክራቸው ጊዜ ራስ መንገሻ "ጣልያን ትግራይን እንዳስተዳድር ይፈቅዳል ወይ?" ሲል ጠየቀ። ከአማካሪዎቹ አንዱ ጆን - የአጤ ዮሃንስ የእህት ልጅ ነበር።

በምክክሩ ወቅት ጆን ራስ መንገሻን አበረታታ። ጣልያኖች ራስ ገዙን ሊፈቅዱ ስለሚችሉ የንጉሱን አሳብ መቀበል እንደሚገባ አሳብ ሰጠ። ራስ አሉላ ግን አሳቡን ስላላመነበት ማምሻውን ከአውዓሎም ጋር መከረበት። እለቱ አውዓሎም ከአጤ ምኒልክ ሰፈር ሰንብቶ ወደ ባራትዬሪ የመመለሻው ቀን ነበር። አሉላ የአውዓሎምን ምክር ይዞ ተስያት ላይ ወደ ባራትዬሪ ሰፈር ገሰገሰ።

አውሳሎም ከመምሸቱ በፊት ባራትዬሪ ዘንድ ደረሰ። በአበሻ መሪዎች የተመከረውን ለባራትዬሪ እውነት አስመስሎ ገለጸ። የአጤ ምኒልክ ሰራዊት ምግብ ፍለጋ ሰፈሩን ጥሎ መበታተኑን፤ ንጉሱ ወደ ሸዋ ለመመለስ መዘጋጀቱን ባራትዬሪን ማሳመን ቻለ። መጋቢት ፣ 1896 ጣልያን ማጥቃት ቢሰነዝር አንድ ጥይት ሳይተኮስ አጤ ምኒልክን ብቻውን አጊኝቶ እንደሚማርከው ለባራትዬሪ አጥብቆ ነገረው። በርግጥ ጄኔራል ባራትዬሪ በመጨረሻ ሌሎች ግፊቶችም ተጨምረውበት ጦርነቱን ለመጀመር ወሰነ።

አውሳሎም ባራትዬሪን ካሳመነ በሁዋላ እንደገና ሹልክ ብሎ ወደ አጤ ምኒልክ ሰራዊት ለመመለስ ችሏል። በቅድሚያ የሄደው ራስ አሉላ ዘንድ ነበር። ባራትዬሪ ለበነገታው ማጥቃት መዘጋጀቱን ገለጸለት። አሉላ ይህን ዜና ይዞ ወደ አጤ ምኒልክ በረረ። አጤ ምኒልክም ለማለዳ ጦርነት እንዲዘጋጁ ለራሶቹ መልእክት ላኩ።

በርግጥ የአጤ ምኒልክ ሰራዊት በምግብ እጥረት ምክንያት በመፍረስ ላይ መሆኑ በኢጣሊያውያን የጦር ሰፈር በተለያየ አግጣጫ ወደ ባራትዬሪ እንዲደርስ ጥረት ሲደረግ ሰንብቷል። ሰራዊቱ ግንባሩን እየተወ በመመለስ ላይ የሚያስመስል የማሳሳቻ እንቅስቃሴ ጭምር ተደርጓል። ይህን አውሳሎም ያውቅ ነበር። አሉላና ምኒልክ ባንድ በኩል የማሳሳቻ ድራማ ቢሰሩም በሌላ በኩል የምር ተቸግረው ነበር። አውሳሎም ለባራትዬሪ እውነተኛውን ሁኔታ ነግሮ ቢሆን ኖሮ፤ ባራትዬሪ ያቺን ታሪካዊ ውሳኔ ባልወሰነ ነበር።

ባራትዬሪ ከአውሳሎም የሰማውን መረጃ እንዲያምን ተጨማሪ ድራማዎች መሰራታቸው በኢትዮጵያውያን ጸሃፊዎች ይጠቀሳሉ። ከድራማዎቹ መካከል ንጉስ ተክለሃይማኖት፣ ራስ ሚካኤልና ራስ መኮንን “ጦርነቱ ሲጀመር አጤ ምኒልክን እንከዳለን፤ ከእናንተው ጋር ነን” የሚል ደብዳቤ በምስጢር መላካቸው ነው። ባራትዬሪ ይህን መሰል ደብዳቤ ሙሉ በሙሉ አምኖ ተቀብሏል ማለት ግን አይቻልም። ቀደም ሲል በተመሳሳይ የከዱ ስለነበሩ ደግሞ ግማሽ ልብ ሊሆን ይችላል። በተለይ ራስ መኮንን ወልደሚካኤል ደጋግሞ ደብዳቤ እየጻፈ፣ “ጦርነቱን ይጀምሩ ከርሶ ጋር ነኝ” እያለ ባራትዬሪን መወትወቱ ተጽእኖ አድርጎበት ሊሆን እንደሚችል ይታመናል።

አውዓሎም ባመጣለት መረጃ መሰረት የንጉሱ ድንኳን ሲነቀል ባራትዬሪ በባይነኩላር ተመልክቷል። የአጤ ምኒልክ ጦር ምግብ ለመሰብሰብ በመበታተን ላይ ስለመሆኑ ለኢጣልያ ጄኔራሎች በተለያዩ መንገዶች እንዲደርስ የተደረገው የማታለያ እቅድም ወደ ባራትዬሪ እየመጣ በጆሮው ተንቆርቁሯል።

አውዓሎም እንደተጫወተበት ባራቲየሬ የጠረጠረው ውጊያው በተጀመረበት እለት ረፋዱ ላይ ነበር። አውዓሎምን እንዲያቀርቡለት የስራ ባልደረቦቹን ቢያዝም አውዓሎም የትም አልነበረም። ባራትዬሪ በድጋሚ "አውዓሎምን ፈልጉት" ብሎ ቢያዝም አውዓሎም ከአጤ ምኒልክ ሰፈር ደርሶ ነበር። አውዓሎም በአባቱ ኤርትራ ዓዲ ቆንጺ ሲሆን፤ በእናቱ ትግራይ እንትጮ ነበር።

* * *

በርክሌይ እንደጻፈው ጀኔራል ባራትዬሪ መጋቢት ፣ የአቢሲኒያ ጦር ላይ ማጥቃት እንዲካሄድ ውሳኔ ባይሰጥና ለሰባት ቀናት ያህል በምሽጉ ለመቆየት ችሎ ቢሆን ኖሮ አጤ ምኒልክ ጦሩን በትኖ ወደ ሸዋ ለመመለስ ይገደድ ነበር። ሳይሆን ቀረና ባራትዬሪ ቅዳሜ ለእሁድ አጥቢያ ሊነጋጋ ሲል ውጊያው እንዲጀመር አዘዘ።

በነጋታው እሁድ ነበር።

የአጤ ምኒልክ ወታደሮች ቤተክርስትያን ለመሳለም ይሄዳሉ ብሎ ርግጠኛ በመሆኑ፤ አጤ ምኒልክም ድንኳን ነቅሏል ብሎ በማመኑ፤ ባራትዬሪ ተስፋ ያደረገው ሰፈር የቀረውን እያተራመሰ ለመፍጀት ነበር። ባራትዬሪ ከጥቂት በላይ ደካማ ጎኖች ነበሩት።

የአበሻን ጦር ለማጥቃት የተላከው የኢጣልያ ወታደር ጓዘ ብዙ ነበር። በጀርባው ኮሮጆ አዝሏል። ጠመንጃ ተሸክሟል። የውሃ ኩዳና የጥይት ቦርሳ በግራና ቀኝ ጎኑ ታጥቋል። እስከ ጉልበቱ የሚደርስ ከቆዳ የተሰራ ጫማ። በጥቅሉ 25 ኪሎ የተሸከመ ወታደር ሌሊቱን ሲጓዝ አድሮ አባገሪማ ደረሰና መድፉን ጠመደ።

ሲነጋ ግን ጨዋታው ሌላ ሆኖ ተገኘ። ቋንጣው አበሻ እንደ ጦጣ እየዘለለ ጓዘ ብዙው የነጭ ወታደር ላይ ሰፈረበት። ጀኔራል ዳቦርሚዳና ጀኔራል አሪሞንዲ ሲገደሉ፤ ጀኔራል አልቤርቶኒ

ተማረከ። ጀኔራል ኤሊና ቆሰለ። ስድስት ሺህ ያህል ኢጣሊያውያን የሃበሻ ጎራዴ ቁርስ ሆኑ። ዋናው አዛዥ ጀኔራል ባራትዬሪ የሶስቱን ቀን መንገድ ባንድ ቀን ጨርሶ ዓዲቀይሕ እንደገባ ይነገርለታል።

በርግጥ ይህ አባባል ለማናናቅ የተነገረ ሊሆን ይችላል። ባራትዬሪ ከአድዋ እስክ ዓዲቀይሕ ባደረገው የሸሸት ጉዞ የፈረሰበትን ሰራዊት መልሶ ለመገንባት ብዙ ጥሯል። ግራ ተጋብቶ የሚሸሸውን ሰራዊት ለማስቆም የተቻለውን ዘዴ ሁሉ ተጠቅሟል። ሙከራው ግን ውጤት አላስገኘለትም። የወታደሩ ሸሽት መልክ ያለው አልነበረም። እንደደነበረ እንስሳ ከፊቱ ያለውን እየጣሰ የሚጋልብ ጎርፍ ነበር። "ከሞቱ አሟሟቱ" እንዲሉ የአበሻ ጎራዴና ጦር የፈጠረበት ቅዥት የማሰቢያ የሰውነት ክፍሉን አናውጾበት፤ ለማስቆምና ለማረጋጋት በማይቻልበት ሁኔታ ላይ ነበር።

ፈረሰኛው የአበሻ ተዋጊ ሜዳ ሜዳውን እየጋለበ ባራትዬሪን ለመቅደም መገስገሱን ቀጥሎ ነበር። በዚህ ሂደት የባህታ ተከታዮች የመረብ ምላሽን ሰው መስለው ተደባልቀው በመግባት ጣልያኖችን በማሳሳት ጎራዴያቸውን ተጠቀሙበት። በመልክ የሚለዩ ስላልሆኑ ኢጣልያኖች ግራ ተጋቡ። ተራሮቹ በአቢሲንያውያን ተዋጊዎች ተሞልተዋል። ከተራራ ወደ ተራራ እየዘለሉ በፍጥነት ይጓዛሉ። ጥቁሩም ነጩም ተቀላቅሏል። በዚህ መካከል ባራትዬሪ በጥቂት ዛብጥያዎች ታጅቦ ከመሸሽ በቀር አማራጭ አልነበረውም።

ባራትዬሪ ከንርኣዮ ተራራ በታች ከረቢ አርእየኒ ባሻገር በተዳፋቱ ላይ ብዙ ህዝብ ሰፍሮ አየ። ኮረብታው ላይ አናውን የቀረ አንድ ደብር ይታይ ነበር። ባራትዬሪ ወደ ቤተክርስትያኑ ቅጽር ግቢ ገብቶ አጥሩን ከለላ በማድረግ የሚከተሏቸውን አበሾች ለማስቆም ተኩስ ጀመረ።"ቪቫ ኢታሊያ" (ኢጣልያ ትኑር) እያለ ጮኸ። ደጋግሞ "ሶቮያ" ሲልም ተሰማ። ሶቮያ የንጉሳውያኑ ትውልድ ቦታ ነበር። "ኢጣልያ ትኑር!" የሚል መፈክር እያሰማ መተኮስ ሲቀጥል ሞራላቸው ወድቆ የነበሩ ኢጣልያውያን ወታደሮች ተነቃቅተው መፈክሩን ተቀብለው እያሰሙ ሊዋጉ ሞከሩ።

ብዙም ግን አላዘለቃቸውም። አበሾች የሸጉጥ የተኩስ ርቀት ውስጥ ጭምር እየገቡ ይዋጋሉ። ይህ ሁኔታ ለኢጣልያ ወታደሮች አስፈሪ ሆነባቸው። ማሰብ ከሚችል የሰው ፍጡር ጋር ሳይሆን

በደመነፍስ ከሚያጠቃ የተቆጣ አውሬ ጋር ጦርነት የገጠሙ መስሎ እየተሰማቸው በፍርሃት ራዱ። የአበሻው ጦር እንደማይገታ ሲገነዘቡም የቀራቸው ነገር ሽሽቱ ላይ መበርታት ሆነ።

ረቢ አርአየኒ ሲደርሱ ከባራትዬሪ ጋር የቀሩት አምስት ወታደሮች ብቻ ነበሩ። በመሸሽ ላይ ካሉት ኢጣልያውያን መቶ ያህል ወታደሮች ሰብስቦ እንደገና ለመከላከል ሞከረ። እንደ ጎርፍ በላይ በላይ እየገነፈለ የሚመጣው የአቢስንያ ጦር ግን ሊገታ የሚችል አልነበረም። ግድብ የሰበረ ጎርፍ መሰለ።

ፈረሰኞች ወደ ሶልዋ ማምራታቸው ለባራትዬሪ ሲነገረው አሳባቸው ቁልጭ ብሎ ገባው። ቀድመውት መንገድ ለመዝጋት መሆኑን ተገነዘበ። ባራትዬሪ ፈረሰኞቹ ካሰቡት በተለየ መንገድ ወደ ሰሜን በመታጠፍ ሽሽቱን ቀጠለ።

ሁዋላ ባራትዬሪ ሁኔታውን እንዳሰፈረው፣

“የኢጣልያ ወታደሮቹ ህሊናቸውን ስተዋል። በዙሪያቸው ምን እየተደረገ እንዳለ አያውቁም። ስለምንም ነገር አያስቡም። የሚያደርጉት የግል ህይወታቸውን ለማዳን መጣር ብቻ ነበር። የጦር መኮንኖች ወታደሩን ማዘዝ አልቻሉም። ለማዘዝ የሚሞክረውን መኮንን እንደ ጅላጅል ቆጠሩት። የኢጣልያ ወታደሮች የነፍስ ወከፍ ጓዛቸውን ጣሉ። የከበዳቸውን ነገር እየወረወሩ ህይወታቸውን ማዳን ብቻ ቀዳሚ ጉዳይ አደረጉ። ‘ኢታልያ ለዘልአለም ትኑር!’ የሚለው የአዛዥ የመኮንኖች ድምጽ እንኳ ሊያቆማቸው አልቻለም።”

ባራትዬሪ ተግቶ በመሸሽ ላይ ሳለ መነጽሩ እንደ ወደቀበት ይነገራል። በመረበሹ ግን መነጽሩን እንኳ ለማንሳት መቆም አልቻለም። በዚህም ምክንያት የዛፍ ቅርንጫፎች ከፈረሱ ላይ እንዳይጥሉት አጃቢዎቹ መንገድ እየመሩ ዓዲቀይሕ አድርሰውታል። ባሪየቴሪ ዓዲቀይሕ ቀድሞ መግባቱ የሚያስወቅሰው አልነበረም። በአዛዥነቱም የሚታማ አልነበረም። ቀደም ሲል በጦር ሜዳ የተፈተነ ነበር። በሱዳን የወታደራዊ ጥበብ ችሎታውን ማሳየቱ የሚነገርለት ነበር። በአድዋ ጦርነት ራሱን ከምርኮ ከማትረፍ በቀር ሌላ አማራጭ እንዳልነበረውም ሁዋላ ተረጋግጦለታል።

(ባራትዬሪ አስመራ ላይ በተቋቋመ የጦር ፍርድ ቤት ቀርቦ

ጉዳዩ በዝርዝር ከታየ በሁዋላ ጥፋት አልተገኘበትም። በመሆኑም ከሰራዊት አዛዥነቱ ተሰናብቶ በግሉ ኑሮውን እንዲቀጥል ተወሰነበት። ወደ አገሩ ከተመለሰ በሁዋላ የጦርነት ማስታወሻውን መጽሃፍ ጽፎ በ1901 በስድሳ አመት እድሜው አርፏል።)

በራስ አሉላ እቅድ መሰረት ባራትዬሪን ለመያዝ ሙከራ ያደረገው ቡድንም ሳይሳካለት ቀርቷል። ገብረመድህንና ኑረነቢ የተሳተፉበት የአሮሞ ፈረሰኞች ቡድን ባራትዬሪን መማረክ ባይችልም መሳሪያውን እየጣለ በድካምና በውሃ ጥም በየዛፍ ጥላው ስር የወደቀውን የኢጣልያ ወታደር እየሰበሰቡ በአንድ ኮረብታ ላይ አከማቹት። በዚያን ሌሊት የባህታ ተከታዮች የነበሩት ሌሊቱን በድል ደስታ ሰክረው ችቦ እያበሩ ከሰፈሩበት ኮረብታ ባሻገር "ምድሪ ባሕሪ"ን ወይም "ኤርትራ"ን በሩቁ እየተመለከቱ አነጉ።

አድዋ በደም ተጨማልቃ ነጋች።

ማለትም ሁለተኛው ሌሊት ነጋላት።

የአጤ ምኒልክ አጋፋሪዎች ነጋሪት እየመቱ፤ ቱልቱላ እየነፉ ገና በማለዳው የንጉሰነገስቱን ሰፈር ቀወጡት። የአጤ ምኒልክ ድንኳን ከተተከለበት ኮረብታ ፊት ከሚገኘው ገላጣ ሜዳ ዙሪያ ድል አድራጊው ሰራዊት በቱልቱላውና በነጋሪቱ ድምጽ እየተሳበ ተሰበሰበ። ሰራዊቱ ምን እየተካሄደ እንዳለ ባያውቅም አጤ ምኒልክና ጣይቱ ዙፋናቸውን ወዳኖሩበት ገላጣ ሜዳ ጎረፈ። እንደተለመደው ግዳይ የማቅረብና የሸለላ በአል ሊሆን እንደሚችል እያሰበ ጀሌው፣ መደበኛው፣ ጦረኛው፣ ዱለኛው፣ ወሬኛው፣ ፈረሰኛው፣ እግረኛው ወደ ጥሪው ቦታ ገሰገሰ።

ገላጣው ሜዳ ላይ አምስት ትልልቅ ግንዲላዎች ተጋድመው ይታያሉ። የሰሉ መጥረቢያዎችና የሰሉ ጎራዴዎች በእያንዳንዱ ግንዲላ ላይ ተቀምጠዋል። ከእያንዳንዱ ግንዲላ አጠገብ በሶስት ጉልቻ ላይ ትልቅ የብረት ድስት ተጥዷል። የሚሹመለመለው እሳት በብረት ድስቱ ውስጥ የተሞላውን ቅቤ ያንተከትከው ይዟል። ይህ ሁሉ ሲሆን፣ ምን እንደታሰበ የጠረጠረ ነበር ማለት አይቻልም። ከአንድ ቀን በፊት በነበረው ጦርነት በድል የሰከረው ሰራዊት

በያቅጣጫው ቀረርቶውን ያሰማል። ረገዳውን አጡፎታል። ሽለላው ማቋረጫ የለውም። ሆታው፣ ዱታው፣ ጀሎታው. . .

ከሜዳው ዳርቻ ላይ የንጉሰ ነገስቱ ዙፋኑ በአጀብ ወጣ። ግራና ቀኝ እንዲሁ አነስተኛ ግልገል ዙፋኖች ቦታቸውን ያዙ። በመቀጠል ራስ መንገሻ ከዙፋኑ በግራ በኩል፤ እቴጌ ጣይቱ ብጡል ከዙፋኑ በቀኝ በኩል ተቀመጡ። እንደ ደረጃቸው ራሶች ቦታቸውን ያዙ። በአብዛኛው ግን የሸዋ መኳንንት ነበሩ። አጃቢዎች እንዲሁ ዙፋኑን በግማሽ ጨረቃ ቅርጽ ከበው ተኮለኮሉ። በቱልቱላና በነጋሪት ጥሪ እየተሳበ ወደ ገላጣው ሜዳ የገሰገሰው ሰራዊት ሜዳውን ከቦ የማለዳውን ትርኢት ለማየት በጉጉት ጠበቀ።

ድንገት ጸጥታ ሆነ።

የተማረኩ የኢጣልያ መኮንኖችና የበታች ሹሞች በሰልፍ ሲመጡ ድንገት ጸጥታ ሆነ። ወዲያው ግን "ሊገደሉ ነው" የሚል ወሬ ካንዱ ጫፍ ወደ ሌላው እየተተረተረ ጫጫታ ሆነ። ዳሩ ይህ ጫጫታ ብዙም አልዘለቀ። ጣልያኖቹ መኮንኖች ከንጉሰ ነገስቱ ግራና ቀኝ የክብር ቦታ ተሰጥታቸው መሬቱ ላይ እንዲቀመጡ ተደረገ።

እናም የእለቱ ትርኢት ተጀመረ።

ከኢጣልያ ጋር ተሰልፈው የነበሩና የተማረኩ የምድሪ ባሕሪ ዜጎች በአምስቱ ግንዲላዎች ትይዩ በአምስት ረድፍ እንዲሰለፉ ተደረገ። ብዛታቸው ከአምስት መቶ በላይ ነበር።

ሁለት የአጤ ምኒልክ አሽከሮች የመጀመሪያውን ኤርትራዊ ግራና ቀኝ እጁን ያዙት። እድሜው ከሃያ አይበልጥም። ጠጉሩ ግንባሩ ላይ የተደፋ አይኖቹ የጉጉት የመሰሉ፣ ቀጭን ጠይም ልጅ እግር ባላገር ነበር። ምን እንዳሰቡ ገና ባለመረዳቱ ነው መሰል ግራና ቀኝ የያዙትን በፈገግታ ይመለከታል። እንደ ባርካ በግ እየንተቱ በመውሰድ እግሩን ግንዲላው ላይ ሲያጋድሙት ጭምር ያለማንገራገር ፍላጎታቸውን ፈጸመላቸው። መጥረቢያውን እያየ እንኳ እግሩን ሊቆርጡት እንደሆነ ሊጠረጥር አልቻለም።

በዚያቸው ቅጽበት ሌላው ጀሌ መጥረቢያ ሲያነሳ ግን አሳባቸውን በማወቁ ጩኸቱን ለቀቀው። ለማምለጥ ታገለ። ጊዜ ግን አልሰጡትም። የተምዘገዘገው የሰላ መጥረቢያ ከቁርጭምጭሚቱ

ከፍ ብሎ ጎመደው። መልሰው ግራ እጁን ግንዲላው ላይ በማስደገፍ በጎራዴ ቀንጠሱት። ከእግርና ከእጁ የሚንፈቀፈቀውን ደም ለማቆም የሚንተከተከው ቅቤ ውስጥ ነክረው አወጡት። አንድ ደቂቃ ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ሞኝ ገጽታ ያለው ወጣት እግርና እጅ አልባ ሆኖ ታየ። በሌሎች ግንዲላዎችም ላይም እንዲሁ ተመሳሳይ ድርጊት መፈጸም ቀጠለ። መስኩ በሰቆቃ ጩኸት ተናወጠ።

ሜዳውን የከበበው የአጤ ምኒልክ ሰራዊት አንዳችም ድምጽ አላሰማም። ጸጥታ ነበር። እግርና እጃቸው እየተቆረጠ፤ የፈላ ቅቤ ውስጥ የሚነከሩት የምድሪ ባሕሪ ወጣቶች የስቃይ ድምጽ ጸጥታውን ከማደፍረስ በቀር አልፎ አልፎ ይሰሙ የነበሩ ሽለላዎች እየረገቡ ሄደው በመጨረሻ ፍጹም ጸጥታ ሆነ። የወጣቶችን የስቃይ ድምጽ መስማት ያልቻሉ፤ ፊታቸውን በኩታቸው ሸፈን እያደረጉ ገለል ማለት ጀመሩ። እጅ እግራቸው የተቆረጡ ወጣቶች ቁጥር መቶ ሲያልፍ የትርኢቱ ተመልካቾች ቁጥርም እየቀነሰ ሄደ።

የአጤ ምኒልክ አሽከሮች መላ ሰውነታቸው በደም ተበክሎ አውሬ እንጂ የሰው ፍጡር አልመሰሉም። የደም ፍንጣሪው ተጠራቅሞ አበሰበሳቸው። እግራቸውና እጃቸው ተቆርጦ፤ በፈላ ቅቤ ደሙ እንዲቆም ተደርጎ፤ ከዘራ እየተሰጣቸው የሚሰናበቱ የምድሪ ባሕሪ ዜጎች፤ በሌሎች ምርኮኞች እየተደገፉ የእግርና የእጅ አጨዳ ከሚካሄድበት ቀለበት ይወጣሉ። በቱልቱላ እና በነጋሪት ጥሪ ለትርኢት ከመጡት መካከል የገጠማቸውን አሰቃቂ ትርኢት ማየት ባለመቻላቸው ገለል የሚሉ እየበረከቱ ሄዱ።

ሰቆቃው እየበረታ ሲሄድ እጅና እግር ያጡትን ወጣቶች የሚያግዙ ኢትዮጵያውያን መታየት ጀመሩ። ውሃ ሰጧቸው። በአንድ እግራቸው እያነከሱ፤ በብትር እየተደገፉ ወደ አገራቸው አግጣጫ ጉዞ የጀመሩትን እያጽናኑ፤ ከገዛ ስንቃቸው ላይ ምግብ ቀንሰው ሲሰጡ ታዩ። ደግ ቃላት እየደረደሩ፣ በአጤ ምኒልክ መጥረቢያ እጅና እግራቸውን ያጡ የምድሪ ባሕሪ ሰዎችን አጽናኑ።

የአቦይ ተወልደ የበኩር ልጅ ያዕቆብ ግራ እጅና ቀኝ እግሩን ለማስቆረጥ በሁለተኛው ረድፍ ላይ ተሰልፎ ነበር። አእምሮው ደንዝዟል። እንደ አብዛኞቹ ደንዝዟል። እየተነዳ ወደ ግንዲላው በመጠጋት ላይ ሳለ የሚያየው ነገር በውኑ ስለመሆኑ እንኳ ርግጠኛ

አልነበረም። የህልም አለም ውስጥ ያለ ያህል ነበር። እንዴት እዚህ ቦታ ሊገኝ እንደቻለ እንደ ቅዠት ሆኖ መላልሶ አእምሮውን እያቋረጠ አለፈ። ከራሱ በቀር የሚወቅሰው ሌላ ሰው አልነበረም።

ጣልያን አስመራ ሲገባ አባቱ አቦይ ተወልደ ለኮምቢሽታቶ ዋና የጓሮ አትክልትና እንቁላል አቅራቢ ለመሆን ቻሉ። ስራቸው በጥሩ ሁኔታ ተስፋፋ። ያዕቆብ ዋና ስራው በአገልጋይነት ከተቀጠሩት ሁለት ጎልማሶች ጋር ሰርክ በማለዳ በሰረገላ እየገሰገሰ እንቁላልና የጓሮ አትክልቶችን ኮምቢሽታቶ ማድረስ ነበር። ያዕቆብ ኮምቢሽታቶ ብቅ ሲል ወጣትነቱን የሚማርኩ ነገሮች ፈተና ላይ ጣሉት። የሰልፍ ትርኢት፣ አለባበሳቸው፣ ንጽህናቸው፣ ቀልቡን ተቆጣጠረው።

አንድ ማለዳ እንደተለመደው እንቁላል እና አትክልት ኮምቢሽታቶ ካደረሰ በሁዋላ ሰረገላውን ለአገልጋዮቹ ሰጥቶ፣ ከጣልያኖች ካምፕ መግባቱን ለአባቱ መልእክት ልኮ ተሰናበተ። ይህ ከሆነ ገና አራተኛ ወሩ ነው። በዚህ አጭር ጊዜ ውስጥ ጠመንጃ መተኮስ አስለመዱት። እና አንድ ጠመንጃ ተሸክሞ ራሱን አድዋ አገኘው። ከሞቀ ቤቱ የወጣበትን እለት ለመርገም ግን ጊዜ አላገኘም። ምን እየተካሄደ እንዳለ ግንዛቤ አልነበረውም።

አድዋ ደርሶ ምሽግ ይዞ ብዙም ሳይቆይ ጦርነቱ ተጀመረ። እስከ ረፋዱ በእሩምታ ጥይት ይተኩሱ ነበር። ቀትር ላይ ኢጣልያ መሸነፏ ግልጽ ሆነ። አድዋ ላይ ቀኑን ሙሉ በተደረገው ውጊያ ስድስት ሺህ ያህል ኢጣሊያውያን ሲሞቱ፤ 2261 ኤርትራውያን ሞተው፤ 958 ቆሰሉ። 2500 ኢጣሊያውያን ቁስለኛ ሲሆኑ፤ 1900 ደግሞ ተማረኩ። አብረውት እንደነበሩት የምድሪ ባሕሪ ሰዎችና ኢጣልያውያን ወጣቶች ያዕቆብም በምኒልክ ወታደሮች ተማረከ።

እና ይኸው አሁን እጅና እግሩን ሊቆርጡት ነው።

አንድ እጅና አንድ እግራቸውን በመጥረቢያና በገጀራ የተቆረጡ ወጣቶች ቁጥር ሁለት መቶ አለፈ። ያዕቆብ ተራው እየደረሰ ነበር። በደም ወደ ጨቀየው ግንዲላ እየተጠጋ ሲመጣ እጅና እግሩን ከሚቆርጡት ቢገድሉት እንደሚመርጥ ማሰቡ አልቀረም። እንዲገድሉት ምን ማድረግ እንደሚገባው ግን ማሰብ አልቻለም። ደንዝዟል። ከፊቱ እየተወሰዱ እጅ እግራቸው የሚታጨድ ወጣቶች የሰቆቃ ድምጽ አደንቁሮታል። በደም ተለውሰው እንደ ማገዶ

የተከመሩ ቁራጭ እጅና እግሮች በግንዲላው ዙሪያ ይታያሉ። ብዙዎቹ እድሜያቸው ገና ለጋ በመሆኑ የአባት፣ የእናታቸውን ስም ይጠራሉ። የመላእክትን ስም እየጠሩ የሚማጸኑ ይበዛሉ። በተለይ አደይ ማርያም እና ቅዱስ ጊዮርጊስ ስማቸው በተደጋጋሚ ተነሳ። ያዕቆብ የሚያየውንና የሚሰማውን ማመን እንዳቃተው፤ ምን ማድረግ እንዳለበት ሳይወስን ተራው ደረሰ።

አስተናባሪዎቹ መንጭቀው ሲወስዱት አንደኛው "ከሃዲ!" ብሎ አጉረጠረጠበት። እጅና እግራቸው የሚቆረጡትን ሁሉ፣ ይህንኑ ስለሚሏቸው ትርጉሙን አውቆታል። ያዕቆብ በረድፉ እየተገፋ ወደ ግንዲላው ሲያዘግም ይህንኑ ቃል እያሰላሰለው ነበር።

መቼ እና የት ማንን እንደከዳ ሊገነዘብ አልቻለም። ሰውን ከድቶ ከሆነ በርግጥ አባቱን ነው የከዳው። እነዚህ ሰዎች በምን ምክንያት "ከሃዲ" እንደሚሉት ሊረዳ አልቻለም። ማንን እንደ ከዳ፤ ከህደቱን መቼና እንዴት እንደፈጸመ ሳያውቅ ግራ እግሩን ወሰዱና ግንዲላው ላይ አጋደሙት። መጥረቢያው ተምዘግዝጎ እግሩ ላይ ሲያርፍ ፈዝዞ ይመለከት ነበር። ግራ እጁን ደገሙት። በመቀጠል አንከብክበው በማንሳት ፈልቶ የሚንተከተክ ቅቤ ውስጥ እግርና እጁን ሲነክሩት የስቃይ ኡኡታውን አቀለጠው። ከመጥረቢያው ይልቅ የፈላው ቅቤ ቃጠሎ የበለጠ አሳበደው። በርግጥ የተቆረጠ እጅና እግርን በፈላ ቅቤ ደሙን ማቆም እንደ ህክምና ዘዴ የሚጠቀሙበተት ነበር። የገዛ ወታደሮቻቸው ሲቆስሉም በዚሁ ዘዴ ነበር የሚጠቀሙት።

ፈጻሚዎቹ ከኤርትራውያን እግርና እጅ በሚፈናጠረው ደም ተጨማልቀው የሰው ፍጡር አይመስሉም። ጭንቅላቱን የአህያ ሆድ ውስጥ ከትቶ ስጋ ሲበላ ያደረ ስግብግብ ጅብ መስለዋል። በሰው ደም ሰክረው አንዳች ነገር ያለማቋረጥ ይለፈልፋሉ።

ያዕቆብ በአምስት ደቂቃ ጊዜ ውስጥ እጅ እግሩን አጥቶ ከትርኢቱ ቀለበት ገለል እንዲል ተደረገ። በርከት ብለው በአጋጮች እየተረዱ ከማረጃ ቦታው ገለል እንዳሉ አንድ ወጣት ባላባት በጋሻ ጎግሬዎች እንደታጀበ ከፊታቸው መጣና አስቆማቸው። ፈረሱን ዳንጋላሳ እያስደነሰ ቁስለኞቹን እየተዘዋወረ ከተመለከተ በሁዋላ፤ በደማቅ ድምጽ ስቆ ሲያበቃ፣

“ለከሃዲ የሚገባው ቅጣት ይሄ ነው።” ሲል ተናገረ።

ከቁስለኞች አንዱ አማርኛ ይችል ኖሯል፣

“ማንን ከዳን?” ሲል ጠየቀ።

“ከጣልያን ጋር ሆናችሁ ወጋችሁን? እናንተን ከጎኑ ባያደርግ ጣልያን ሃይል አጊኝቶ ባልተቋቋመን። በዚህ ጦርነት ስንት የጨዋ ዘር ጨረሳችሁ? ከጥልያን እናንተ የገደላችሁን ይበዛል።”

ቁስለኛው በተንገፈገፈ ድምጽ ተናገረ፣

“የጥልያን ወታደሮች ነን። ምን ነበር የምትጠብቀው?”

ጋሻ ጦግሬዎች ጌታቸው በመደፈሩ አላስችል ብሏቸው ጎራዴ እያወዛወዙ አንገቱን ሊቀነጥሱት ሲጋበዙ ፈረሰኛው እጁን አንስቶ አገዳቸው። እናም እንዲህ አለ፣

“አትንኩት። እየተሰቃየ እንዲኖር ፈርጀበታለሁ። መኖር ካልቻለ ከፈለገ ራሱን በራሱ ይግደል። አትንኩት!”

ፈረሰኛውና ጋሻጦግሬዎቹ መንገዳቸውን ቀጠሉ። በዚህ ጊዜ ይህ ወጣት ባላባት “ደጃዝማች ካሳ” እንደሚባል ቁስለኞቹ አወቁ። ቁስለኞቹ ከማረጃው ሜዳ ገለል ካሉ በሁዋላ ልባቸው እንደተሰበረ የአገራቸውን አግጣጫ ይዘው ተጓዙ። ያዕቆብ በዚያች ቅጽበት እነዚህን ሰዎች ተበቅሎ ቢሞት ይወድ ነበር። ቢገድሉትም ይመርጥ ነበር። ግን እንዲገድሉት ማድረግ ሳይችል ቀረ። መጥረቢያቸውን ለመንጠቅ ቢሞክር ይገድሉት ነበር። ባለመሞከሩ ጸጸት እና ቁጭት፤ ቂም እና በቀል ልቡን በዶማው ቆፈረው። በሰዎቹ ላይ ያደረበት ጥላቻ መልሶ እሳት ሆኖ ፈጀው። የሰው ልጅ አምሳያው በሆነው ፍጡር ላይ እንዲህ ያለ አሰቃቂ ግፍ ሊፈጽም እንደሚችል እውቀት አልነበረውም። በዚያን ቀን ግን አወቀ።

እጅና እግራቸው እየተቆረጠ የፈላ ቅቤ ውስጥ እየተነከሩ ወደ ምድሪ ባሕሪ ከተላኩት 461 ወጣቶች መካከል አብዛኞቹ አገራቸው ሳይደርሱ መንገድ ላይ ሞቱ። ያዕቆብ በህይወት ተርፈው መረብ ወንዝን ከተሻገሩት እድለኞች አንዱ ለመሆን በቃ።

የኤርትራን ድንበር ከመሻገራቸው በፊት የኢጣልያ የህክምና ቡድን ደርሶ ቁስለኞችን ተረከባቸው። ሰረገላዎችን ሳይቀር ለዚሁ

ተግባር መድበው በፍጥነት ህክምና ወደሚያገኙበት ቦታዎች አጓጓዟቸው። ደም ፈሷቸው የደከሙትን ለመርዳት ቅድሚያ ሰጡ። ያዕቆብን የተረከበችው ሴት ኢጣልያዊት የካፑቺኒ ማህበር አባል ነበረች። በተኛበት የሸራ አልጋ ላይ ቁስሉን ስታክመው ታለቅስ ነበር። እንባዋ ሲንጠባጠብ ለምን እንደምታለቅስ አልገባውም።

ቁስሉ አገግሞ ብዙ ሳምንታት ካለፈ በሁዋላም እንኳ ያዕቆብ የተፈጸመው ነገር እውን ሊመስለው አልቻለም። አገግሞ ወደ ቤቱ እስኪመለስ ድረስም አንዳች ቃል አልተነፈሰም። ዝምታው ማቋረጫ ሲያጣ በድንጋጤ ምክንያት ዲዳ እንደሆነ ታወቀ። ያዕቆብ ደጋግሞ ለመናገር ቢሞክርም ቃል ከአንደበቱ ማፍለቅ አልቻለም። በመሆኑም የሚፈልገውን በጽሁፍ መጠየቅ ጀመረ።

ያዕቆብ እንደገና የመናገር ችሎታው የተመለሰለት ሰምበል ወደሚገኝ የአባቱ ቤቱ ከተመለሰ ከሁለት ወራት በሁዋላ ነበር። በዚያን ጊዜ ግን እናቱ ጽጌወይኒ ልጇ ላይ በደረሰው አደጋ ምክንያት በድንጋጤ ህይወቷ አልፎ ነበር። አባቱ አቦይ ተወልደ በቁጭት የአልጋ ቁራኛ ሆኖ ነበር።

ያዕቆብ አንደበቱ ተከፍቶለት መናገር ሲጀምር መጀመሪያ የተነፈሰው ቃል፣ “አቦይ ይቅር በለኝ!” የሚል ነበር። አባቱ ይህን ሲሰማ በደስታ እንባ ታጠበ። መርየም የምታደርገው ጠፍቷት ደጅ ወጥታ ጉሮሮዋ እስከቻለ ድረስ እልልታዋን ለቀቀችው። የደስታ እንባዋ ጉንጯን እያጠበ ወረደ። ከሰምበል ወዲያ ማዶ ዝንተአለም ቆሞ የኖረው ተራራ የመርየምን ድምጽ ተቀብሎ አስተጋባ።

* * *

አጤ ምኒልክ ይህን አይነት አሰቃቂና አውሬአዊ የቅጣት ዘዴ “ፍትሃ ነገስት ላይ የሰፈረ ቅጣት ህግ” ቢሉትም ድርጊቱን የተማሩት ግን ከአጤ ቴዎድሮስ መሆኑ ይታመናል። አጤ ቴዎድሮስ ሸዋ በዘመቱ ጊዜ የሸዋን መኳንንት ሁለት እጆቻቸውን እየጎመዱ፤ አንገታቸው ላይ እንደ ሜዳሊያ እያንጠለጠሉ ሸኝተዋቸዋል። ያን ጊዜ አጤ ምኒልክ ሙጫ ልጅ ነበሩ። የልጅነታቸው የመጀመሪያ መራር ልምድ ወላጅ አባታቸው፣ “ቴዎድሮስ መጣ!” ተብሎ ሲነገራቸው በልብ ድካም መሞታቸውና ዘመዶቻቸው ሁለት እጆቻቸውን

ማጣታቸው ነበር።

አጤ ቴዎድሮስ የእጅ ቆረጣ ትርኢት ባካሄዱበት መንደር የምትኖር ስንቄ ከበደ የምትባል መንዜ ነበረች። ቆረጣው ሲካሄድ በቦታው ተገኝታ እልልታ አሰማች። የበኩር ልጇ በሃይለመለኮት ጋሻ ጣግሬዎች ተገድሎባት ፍትህ ተነፍጋ ነበር። በአጤ ቴዎድሮስ የእጅ ቆረጣ ድርጊት ይህች ሴት ቂሟ ሻረላት። እጅ ቆረጣው ካበቃ በሁዋላም ገበያ ወርዳ እንዲህ ስትል ዘመን የተሻገረ ቅኔ ተቀኘች፣

አባ ታጠቅ ካሳ - እጅግ ተዋረዱ
የሸዋን መኳንንት - እጅ ነስተው ሄዱ

አባ ታጠቅ ካሳ - ይስሙኝ አቤቱታ
ዘር እንዳይባዛ - እንዳይሆን በሽታ
መቁረጦ ካልቀረ - ነበር ሌላ ቦታ

የስንቄ ከበደ ትንቢት ደርሶ የሸዋ መኳንንት ከአጤ ቴዎድሮስ በሁዋላ እንደገና አንሰራርተው ዘራቸውና ስርአታቸው ለ84 አመታት ሊቀጥል ችሏል። ሻለቃ መንግስቱ ሃይለማርያም ወደ ስልጣን ሲመጣ ከአጤ ቴዎድሮስ ስህተት መማር የፈለገ ይመስል እጅ፣ እግር፣ ብልት ሳይል አንገታቸውን በመቀንጠስ የሸዋን መኳንንት አጠፋቸው። ከመንግስቱ ጨካኝ ርምጃ በሁዋላ መኳንንቱ ዘራቸው እንደ ዋልያ ተመናምኖ ቢጠፋም፤ እነርሱ የተከሉት ስርአት ግን ቀጥሎ ነበር። በመለስ ዜናዊ ዘመን የሸዋ መኳንንት የተከሉት ስርአትም ለዘልአለሙ ወደ መቃብር ወረደ ወይም ተረት ሆነ።

ምእራፍ 10

የኑረነቢ ማህደር!
ነጻነት ፍለጋ - የጦርነት መንገድ

የአድዋ ድል በተገኘ በሰባተኛው ቀን ማለትም መጋቢት 8 1896 የሚኒልክ ጦር “ፈረስ ማይ” ከተባለ ቦታ በመስፈር ወደ ኤርትራ ለመሻገር ያቀደ መስሎ ነበር። ይህም ዝንባሌ እና ወሬ እንደተሰማ ለኑረነቢና ለምራራ ሸፍቶች፣ እንዲሁም ለባህታ ሓጎስ ተከታዮች መልካም ዜና ሆኖ ነበር። ዳሩ ጉዳዩ ሌላ ሆነ። አጤ ምኒልክና ራስ መኮንን ከኢጣልያ ወኪሎች ጋር በእርቅ ጉዳይ ላይ ተነጋግረው በስምምነት ቋጩት። የምድሪ ባሕሪ ሰዎች ምኞትና ተስፋም የህልም አምባሻ ሆኖ ቀረ።

የመረብ ምላሽ ሰዎች በወቅቱ የህዝባቸው ቁጥር በጣም ጥቂት እንደመሆኑ እላያቸው ላይ መጥቶ የሰፈረባቸውን አውሮፓዊ ሃይል ለመንቀል አቅሙ እንደሌላቸው በግልጽ ተረድተውት ነበር። የባህታ ሓጎስ መጨፍለቅም የአቅም ማነስ ጉዳይ ነበር። መሬታቸውን እየነጠቀ ወደ ጭሰኛነት እየለወጣቸው ያለውን ወራሪ ሃይል ነቅሎ ለመጣል ያላቸው አማራጭ ይኸው የአጤ ምኒልክን ጦር መጠቀም ነበር። እና አጤ ምኒልክ ወደ ኤርትራ ዘልቆ ለመግባት ያሳየው አዝማሚያ የመረብ ምላሽ ሰዎች ላይ ተስፋ አጭሮ ነበር።

አጤ ምኒልክ ፈረስ ማይ በሰፈረ በሳምንቱ የተገመተው እውነት እንዳልሆነ ታወቀ። የባህታ ተከታዮችን ያሳቀቀ ክስተት ተፈጠረ። ማምሻውን የአጤ ምኒልክ ሰራዊት ጓዙን እንዲያስር በቱልቱላ ተነገረው። ይህም ወደ ሸዋ ለመመለስ መሆኑ ታወቀ።

ውድቅት ላይ በጠራ ጨረቃ የአጤ ምኒልክ ሰራዊት ጓዙን ጠቅልሎ ወደ ሸዋ ለመመለስ ይዋከብ ጀመረ። በዚህ ጊዜ ኑረነቢ ፈረስ ማይ ኮረብታ ላይ ከጥቂት ተከታዮቹ ጋር ነበር። ኑረነቢና አንድ ባልደረባው ከአንድ ግዙፍ አለት ላይ ደገፍ ብለው ትርምሱን በርቀት አስተዋሉ።

አቡዋራ እያነሳ የሚግተለተለው የሰራዊት ጎርፍ እንደ አሸዋ የበዛ ነበር። የፈረሰኞች ጎርፍ ማቋረጫ የለውም። የቱልቱላው ድምጽ የአቧራ መጋረጃውን ሰነጠቀው። የሸዋ ሰው ደስተኛ ነበር። ወደ አገሩ የመልስ ጉዞ በመታወጁ፤ ጦርነቱ በማለቁ፣ በድል አድራጊነት ወደ ትዳሩ መመለሱ በመረጋገጡ በርግጥም ከፍተኛ የደስታ ስሜት ላይ ነበር። ሆታው ነጎድጓድ መሰለ። የድል ዜማ ተሰማ።

ኑረነቢ በሩቁ በዝምታ አስተዋለ።

ይህ ተዋጊ ህዝብ ጥልያንን እየነዳ እስከ ቀይባሕር እንዲቀጥል ፍላጎት ነበረው። የሸዋ ሰዎች ግን ድንበራቸውን ካስከበሩ በሁዋላ ወደ ቀያቸው ለመመለስ ወሰኑ።

ኑረነቢ ሃዘን ቢጤ ውስጡን ቦረቦረው።

ልክ እንደ አንድ ግዙፍ አካል ፈረስ ማይን ለቆ ከነ ግርማ ሞገሱ ጀርባውን ለኤርትራ ከሰጠው ሰራዊት ላይ አይኑን መንቀል አልቻለም። ፍሽይ ምራራ ከሸፈቱ ባልደረቦቹ አሁን አብረውት የቀሩት በትክክል አስር ነበሩ። የአጤ ምኒልክን ሰራዊት ሲቀላቀሉ ግን ኑረነቢን የተከተሉት የሓልሓል ሽፍቶች 53 ነበሩ። ቀሪዎቹ የት እንደደረሱ አያውቅም። በጦርነቱ ተሰውተው ይሆናል። ወይም ኤርትራን ከኢጣልያ ማላቀቅ እንደማይቻል በማመን ተስፋ ቆርጠው ከአጤ ምኒልክ ጦር ጋር ወደ ሸዋ ለመሰደድ ወስነው ይሆናል።

ኑረነቢ ከተዋጠበት እንዲህ ያለ አሳብ ያነቃው አጠገቡ አለት ተደግፎ በጸጥታ የቆየው ሽፍታ ባልደረባው ሲናገር ነበር። ፈካክ አሊ በስሜትና በበረታ ድምጽ እንዲህ አለው፣

“ኑረነቢ! መሄድ ነው የሚሻለን?”

በፍጥነት ዘወር ብሎ ጓደኛውን አየው፣

“ወዴት ነው የምንሄደው፣ ፈካከ?”

“ከምኒልክ ጋር ወደ ሸዋ!”

ኑረነቢ ስቅቅ አለ። ፈካከ ንግግሩን ቀጠለ፣

“ምኒልክ ይህን ሁሉ ሰራዊት ይዞ ያልደፈረውን እኛ ምን ልናደርግ እንችላለን? በአገርህ ከመገዛት ስደት ይሻላል። አሁን ተከትለነው ከሄድን ምኒልክ ርስት ሊሰጠን ቃል ገብቷል።”

ኑረነቢ መልስ ሳይሰጠው ዝም አለ፣

“ኑረነቢ! እንግዲህ እኔ መሄዴ ነው!”

“አላህ ካንተ ጋር ይሁን!” ሲል ተነፈሰ።

ፈካከ አሊ ፈረሱ ላይ ዘሎ ከወጣ በሁዋላ ኮረብታውን በዝግታ ወረደ። ሜዳው ላይ ሲደርስ ከረኮረውና ሽምጥ ጋለበ። የፈረሱ ኮቴ የሚያነሳው አቡዋራ ድንክዬ አውሎ ነፋስ ፈጠረ። ኑረነቢ እንደተደገፈበት አለት ልቡም ደረቀበት።

ከሽፍታ ባልደረቦቹ አንዱ መጥቶ አናገረው፣

“ፈካከ ሄደ?” ሲል ጠየቀው።

ኑረነቢ በአወንታ ራሱን ናጠ።

“በረሃቡ ጊዜ የቀበራቸውን ልጆቹን ስደት ሄዶ ቢረሳቸው ይሻለዋል። እዚህ ቢቆይ ስቃዩን አይችለውም።”

ኣያያዘና አከለበት፣

“ከልብ ጀግና ነበር። ደረቱን ሰጥቶ ነው የተዋጋው። የልጆቹን ፊት መርሳት ግን አልቻለም። መሞት ይፈልግ ነበር። አልሆነለትም። ሞት ራቀው። መሄዱ ጥሩ ነው።”

ኑረነቢ አሁንም አልመለሰም።

ሌሎቹም የምራራ ሽፍቶች ወገብ ለመሞከር ከየሄዱበት ጢሻ እና ገደል እየተመለሱ በኑረነቢ ዙሪያ ከበቡ። ስንቁን እየጫነ

ጀርባውን ለኤርትራ የሰጠውን የአጤ ምኒልክ ሰራዊት በርቀት ተመለከቱ። የሚዥመለመለውን የአቡዋራ ጎርፍ በርቀት እያዩ ጥቂት ተጨዋወቱ። አድም ዑስማን አሕመድ በሃዘን ስሜት ተናገረ፣

“ጥልያንን ባሕር መጨመር ይገባ ነበር። ምኒልክ ተሳሳተ።”

ሌላው ደሞ እንዲህ አለ፣

“‘ምኒልክ መረብ ላይ ድንበር ለይቶ በልዋጩ ገንዘብና ጠመንጃ ወስዷል ነው የሚባለው። መረብን ሊሻገር አይችልም።”

“የውል ነገር ከሆነ እነሱስ መረብን ተሻግረው የለም እንዴ?”

ሌላው ተቀብሎ አብራራ፣

“የውል ጉዳይ ሳይሆን ምኒልክ የሚያዋጣውን እያደረገ ነው። ውጊያው ከቀጠለ የሚሆነው አይታወቅም።”

“ምኒልክ ትንሽ ቢጨክን ጥልያንን ባሕር መጨመር በተቻለ ነበር። ያቆሰልከውን አውሬ ካልጨረስከው አገግሞ መመለሱ አይቀርም። እንዲህ ከተዋረደ በሁዋላ ጥልያን ተኝቶ አያድርም።”

ኑረነቢ በመጨረሻ ተናገረ፣

“ምኒልክ ብዙ ሰው አልቆበታል። ቀለብም ጨርሷል ይባላል። ለራሱም ቢሆን ችግር ላይ ነው። እዚህ ድረስ መጥተው መዋጋታቸውም ጥልያን እየገፋ እንዳይመጣባቸው ይሆናል።”

ፈገግ ብሎ ቀጠለ፣

“...ምኒልክ አገሩንና ድንበሩን አስከብሯል። በታሪክ ፊትም ሲከበር ይኖራል። እንግዲህ የኛ ጉዳይ ሸክሙ እኛው ላይ ነው።”

ዑስማን ጣል አደረገ፣

“በምን አቅማችን?”

“እስካለን በሸፍትነት መኖር ነው። ሸፍትነቱን ካልቻልነው ደግሞ ለጥልያን መገበር ወይ ደግሞ አገር ለቆ መሰደድ ነው።”

የአጤ ምኒልክ የሰራዊት ጎርፍ ጓዙን ይዞ ለቆ ሊያልቅ ከአንድ ሰአት በላይ ወሰደበት። ቀስበቀስ አቧራው እየጠራ የጫጫታው ድምጽ እየራቀ ሄደ። ጨርሶ ሲነጋ በአካባቢው አንዳች

ያልነበረ ያህል አካባቢው ባንድ አፍታ በጸጥታ ተመታ።

ኑረነቢ እንደገና ከእንቅልፍ የባነነ መሰለ፣

“ስለ ገብረመድህን ወሬ አልተሰማም?”

አማሮ ምላሽ ሰጠ፣

“ምንም አላገኘሁም።”

ጥቂት ደቂቃዎች አለፉ።

ኑረነቢ ከሕርጊነ ጀምሮ በሰምሃር ደረት ላይ በሽፍትነት ካልተለየው፣ እንደ ታናሽ ወንድም ወደሚያየው ወዳጁ ዘወር አለ።

“መሓመድ ወንድሜ?”

“ኑረነቢ ወንድሜ?”

“ምን ቀረን እንግዲህ?”

“ምን ማድረግ አለብን ትላለህ?”

“ሓልሓልን ትተን የት እንሄዳለን?”

ኑረነቢ እየጋለ በሚሄድ ድምጽ ቀጠለ፣

“...አያቶቻችን የቆረቆሩትን፣ የኖሩበትን አገር ትተን፤ ከአባቶቻችን መንፈስ ርቀን መሄድ እንችላለን እንዴ መሓመድ? ወደነበርንበት ሸለቆ ብንመለስ ይበጃል። መቸም ከጥልያን ምህረት አንጠይቅም። ምን ትላለህ መሓመድ?”

“አላህከሪም ኑረነቢ።”

* * *

በርግጥ ኑረነቢና ተከታዮቹ እጃቸውን ለኢጣልያ መንግስት የመስጠት አሳብ አልነበራቸውም። ከአስር አመታት በፊት ጀምሮ ከኢጣልያ ጋር ለመተባበር የሞከሩ ሁሉ በመጨረሻ የደረሰባቸውን አይተዋል። የኢጣልያን ልብና አካሄድ ተገንዝበውት ነበር።

ኢጣልያ መረብ ምላሽን ሲቆጣጠር ለህዝቡ ሲሰጥ የከረመውን ተስፋ አላሟላም። በተለይ የሰላም ጉዳይ የህልም እንጀራ ሆነ። ተገላቢጦሽ ተፈጸመ። ኢጣልያ ሰላምን ሳይሆን

ጦርነትን ከነጓዙ ኤርትራ ላይ ማራገፏ ከተረጋገጠ በሁዋላ መላቀቂያው አልተገኘም። የተሻለውና ተስፋ የነበረው ተቃውሞ የደጃች ባህታ ሓጎስ ነበር። ከባህታ ሙከራ በሁዋላ የተደራጀ ቀርቶ፣ የግለሰቦች ተቃውሞ እንኳ እየቀነሰ ሄደ። ሊቃወሙ የሚችሉና የተቃወሙ አንድ ባንድ ተመቱ። ከባላምባራስ ካፍል ጎፋር እስከ ብላታ ገብረእግዚአብሄር ጥርግ ብለው ከምድሪ ባሕሪ ጠፉ።

በ1890 ካውንት አንቶኔሊ ከአጤ ምኒልክ ጋር የተፈራረመው የውጫሌ ውል አንቀጽ 13 "ድንበር የሚሻገሩ አማጽያንን አሳልፎ ስለመስጠት" የሚገልጽ ነበር። ይህ አንቀጽ ኤርትራውያን ጸረ ኢጣልያ እንቅስቃሴ እንዳያደርጉ ሲባል የተካተተ ነበር። በተቀረ በወቅቱ አጤ ምኒልክን ተቃውሞ ወደ ኤርትራ ግዛት የሚገባ ስላልነበር አንቀጹ ለኢትዮጵያ ፋይዳ አልነበረውም። ኤርትራውያን የኢጣልያን ኮሎኒ ተቃውመው መንቀሳቀስ በማይችሉበት ደረጃ ዙሪያቸውን ተከበው መፈናፈኛ አጡ።

ከአድዋ ጦርነት በፊት ባራትዬሪን ለማስደሰት ሲባል ታስረው ለኢጣልያን ከተላለፉት ኤርትራውያን መካከል ልጅ በየነ ይጠቀሳል። ልጅ በየነ ተጠልሎበት ከነበረው የራስ አሉላ ካምፕ ተይዞ ህዳር 18 1892 ለኢጣልያ ከተሰጠ በሁዋላ የገጠመው እጣ በናኹራ ደሴት ቀልጦ መቅረት ነበር።

የኢጣልያን ዘረኛ ቅኝ አገዛዝና የመሬት ፖሊሲ የተቃወሙ አንድ ባንድ ተለቅመው ተወገዱ። ናኹራ የገባ ማምለጫ የለውም። ምጽዋ ላይ ለሚሰሩ ህንጻዎች የሚሆን ድንጋይ እየፈለጠ ይኖራል። ናኹራ ከምጽዋ ሃምሳ ኪሎሜትር ርቀት ላይ የሚገኝ ደሴት ሲሆን፤ ዳህላክ ከቢር አይደርስም። በናኹራ ደሴት የእስር ቤት ታሪክ አንድ ጊዜ ብቻ ጥቂት እስረኞች በዋና አምልጠው ወደ ኤርትራ መሬት ከተመለሱ በሁዋላ፤ ሳይያዙ ትግራይ መድረስ ችለዋል። ከእነዚህ አንዱ ብላታ ገብረእግዚአብሄር ሲሆን ይህ ሰው የኢትዮጵያ የመጀመሪያውን ጋዜጣ የመሰረተ ሲሆን፤ "የኢትዮጵያ የፕሬስ አባት" ተብሎ ይታወቃል።

የኢጣልያ ቅኝ ገዢ ካጠፋቸው የምድሪ ባሕሪ ዜጎች አንዱ ዘማት ወድ እኩድ ነው። ይህ የባርካ አርበኛ ተዋጊ መሪ ብቻ ሳይሆን ድንቅ ገጣሚም ነበር። የዘማት ወዲ እኩድ ፍጻሜ አሳዛኝ

ነበር። ባርካ ላዕላይ፣ ከዓዲ ዓሊ በኺት ናብታይ ወገን ነበር። በጎሳውና በማህበረሰቡ ተወዳጅ ነበር። ህዝቡ በትግራይ የጎበዝ አለቆች እንዳይዘረፍ መከላከል ችሎ ነበር። መሃዲስቶችን የመቋቋም ችሎታም ነበረው። ኢጣልያውያን ሲመጡም በተመሳሳይ ተቃወመ።

ያም ሆኖ ዘማት የተደራጀ አልነበረም። ጣልያን በቀላሉ አጠቃው። ለጎሳው አባላት መልእክት ላከ። ጎሳው ሁሉ ከሚጠፋ ዘማት ወዲ እኩድን አሳልፈው እንዲሰጡት ጠየቀ። ጎሳው ከሚጠፋ በሚል የገዛ ዘመዶቹና ተከታዮቹ ይዘው አስረከቡት። ወዲ እኩድ በአሰብ እስር ቤት ቀልጦ ቀረ።

ከዘማት ወዲ እኩድ ቀስቃሽ ግጥሞች ውስጥ የሚከተሉት ስንኞች በዘምህረት ዮሃንስ መጽሃፍ ላይ ተመዝግበዋል፣

መን ደቅ መን እዮም - እዞም ካብ ስግር ዝመጹና
አብ መሬት አቦታትና - በራዩ ኩኑ ዝብሉና
ካብ'ቲ ማል ሓላልና - ግብሪ ዘክፍሉና
ሰብ እኳ ኢና ከምአቶም - ጽቡቕ ጌሮም ይፍለጡና
ኢድና እውን ዓጸፋ እያ እትመልስ - ትንዕ ንዝብለና
- - -
ማን የማን ልጅ ናቸው - ድንበር ተሻግረው የመጡ
ባባታችን መሬት ላይ - ሊገዙን የቋመጡ
ከገዛ ሃብታችን እምብርት ላይ - የደም ግብር የቃጡ
ደህና አድርገው ይወቁን - እኛም ሰው ነን እንደነርሱ
እጥፍ ምላሽ እንሰጣለን - መዘዝ ይወልዳል ጦሱ

የጣልያን ቅኝ ገዢ መንግስት የኤርትራ ተቃዋሚዎቹን በዚህ መንገድ አጥፍቶ ሲያበቃ ሙሉ ልቡን እና ሙሉ ሃይሉን ወደ ኢትዮጵያ አዙሮ ነበር። አልቀናውም። ውጤቱ የአድዋ ጦርነት ሆነ። ጣልያን በአድዋ የደረሰበት ውርደትና ሽንፈት ለጊዜው ኢትዮጵያን እንዳያልም ጋብ አድርጎታል።

እና ኢጣልያ ኤርትራን ይዛ ቆየች።

ኤርትራን ይዛ በመቆየቱ ርግጠኛ አልነበረችም። ኢጣልያ የምግብና የጥሬ እቃ ፍላጎቷን ከኤርትራ ማግኘት ስለመቻሏ ርግጠኛ አልሆነችም። እና "ኤርትራ ኪሳራዋ በዛብኝ" በሚል በጥሩ ዋጋ

ለቤልጅየም ለመሸጥ ተደራድራ ስታበቃ አልገፋችበትም።

ከአድዋ ሽንፈት በሁዋላ ፈረንሳይና እንግሊዝ ለአድዋ ውርደቱ ማካካሻ ይሆንለት ዘንድ ቱርክን ወግቶ ሊቢያን እንዲወስድ ፈቀዱለት።፡ ኤርትራም የወታደር መመልመያ እና ማሰልጠኛ ሆና አገለገለች። ይህ ዘመን በኤርትራውያን ዘንድ "የጨለማው ዘመን" ተብሎ ይታወቃል።

* * *

አጤ ምኒልክ ከአድዋ ጦርነት በሁዋላ ተከታትሎ ጣልያንን ያልመታበት ምክንያት በታሪክ ጸሃፊዎች ዘንድ አወዛጋቢ እንደሆነ ዘልቋል። ልዩ ልዩ ምክንያትም ይሰጠዋል።

አጤ ምኒልክ በወቅቱ ለአንድ ቄስ ገለጹ የሚባለው፣ "ለሰራዊቱ በቂ ውሃ ማግኘት አለመቻል እና የኢጣልያ ጦር ብዛት ያለው ርዳታ እየመጣለት ስለነበር የሰው ደም በከንቱ እንዳይፈስ" የሚል ሲሆን፤ ከዚህ ባሻገር ሌሎች መላ ምቶችም አሉ። እነሱም አጤ ምኒልክ የኤርትራ ምድርና ባሕር ግዛቴ ነው ብሎ ባለማመኑ፣ መረብ ምላሽ የኢጣልያ ግዛት ስለመሆኑ ውል በመፈረሙ፤ ትኩረቱ ወደ ደቡብ መሆኑ ጦርነቱን እንዳይቀጥል እንዳገደው ይጠቀሳል።

የአድዋን ጦርነት ያስከተለው የባህታ ሐጎስ አመጽ ነበር። የአድዋ ሽንፈትም የኢጣልያ መንግስት በኤርትራ የእርሻ መሬት የሰፈራ ፕሮግራም ላይ ያለውን ፖሊሲ እንዲመረምር አስገደደው። የደጃች ባህታ ሐጎስ አመጽ ስለ መጪው ዘመን ምልክት ሰጪ ሆነ። "ገበሬውን ከመሬቱ ማፈናቀል ይቻላል" የሚለው የፍራንኬቲ ቀዳሚ አሳብ ጥያቄ ውስጥ ገባ።

በመሆኑም ኢጣልያ ሌላ ዘዴ ቀየሰች።

ይህም የቅኝ አገዛዝ ስልት ገበሬው በራሱ ፍላጎት መሬቱን እየተወ በከተማ የፋብሪካ ስራዎች እና በውትድርና ላይ እንዲሰራ የማድረግ ስልት ነበር። ይህ ስልት በተገመተው ፍጥነት ባይሄድላቸውም ውጤት አስገኝቶላቸዋል። በጥቂት አመታት ውስጥ ኤርትራ የፋብሪካ ሰራተኞች አገር ሆነች።

አጤ ምኒልክ ከአድዋ ድል በሁዋላ እንደገና መረብ ምላሽ

የኢጣልያ ግዛት መሆኗን እውቅና ሰጥተው ከኢጣልያ ጋር ተፈራረሙ። ለዚህም አስር ሚሊዮን ሊሬ ተከፈላቸው። ይህ ክፍያ ለሁለተኛ ጊዜ መሆኑ ነበር። ከውጫሌ ውል በሁዋላ የተደረገው ይህ ስምምነት በምስጢር እንዲሆን አጤ ምኒልክ ጠይቀው ስምምነት ላይ ተደርሶ የነበረ ቢሆንም፤ ፊርማው ሳይደርቅ ውሉ የአውሮፓ ዜና ለመሆን በቅቶ ነበር።

ኤርትራን በማከራየት ወይም በመሸጥ ገቢ የማግኘት ነገር በተደጋጋሚ ተፈጽሟል። አጤ ምኒልክ ሁለት ጊዜ (25 ሚሊዮን ሊሬ)፤ አጤ ሃይለስላሴ የቃኘውን መሬት በማከራየት (287.3 ሚሊዮን ዶላር)፤ ወስደዋል። አጤ ምኒልክ ባገኙት ሊሬ ጠመንጃ ገዝተው የደቡብ ኢትዮጵያ ግዛት አስገበሩበት። አጤ ሃይለስላሴ በበኩላቸው ከቃኘው ባገኙት የዶላር ገቢ የጎንደር ጤና ሳይንስ ኮሌጅ እና የአለማያ የእርሻ ኮሌጅን ገነቡበት። የጎጥ ወገኖቻቸውን እየለዩ አሜሪካ በመላክ የሰው ሃይላቸውን አጠናከሩበት።

* * *

እነሆ! የኑረነቢ ፍጻሜ በትክክል ሳይታወቅ ቀረ።

በርግጥ ከአድዋ ጦርነት በሁዋላ ከጥቂት ታማኝ ተከታዮቹ ጋር ወደ ምራራ ሸለቆ መድረስ ችሎ ነበር። ኢጣልያውያን በምራራ ሸለቆ የሸፈቱ ዘጠኝ የቦጎስ ሰዎችን አድኖ ለመያዝ አሰሳ ማድረጋቸውን የሚጠቁሙ መረጃዎች በምጽዋ የፖሊስ ሰነዶች ላይ ተገኝተዋል። በወቅቱ በሓልሓል አካባቢ አንዳንድ ያልተጣሩ ወሬዎች ተናፍሰው ነበር። ከእነዚህ ወሬዎች አንዱ 'ኑረነቢ በደዊዎች ረድተውት ከነተከታዮቹ የኤርትራን ባሕር ተሻግሮ ሳዑዲ አረቢያ ገብቷል' የሚል ነበር። የምራራ ሸለቆ ሸፍቶች ከኢጣልያ ጋር ባደረጉት ግጭት ኑረነቢ ቆስሎ እንደነበር የሚናገሩም አልታጡም።

ወሬው መልከ ብዙ ነበር።

ኑረነቢ ከምራራ ወደ ሰገነይቲ ተሻግሮ መሓመድ ኑሪ ከተባለ ሸፍታ ጋር መታየቱ ደግሞ አንድ ሰሞን በሰፊው ተወራ። ሌሎች ደግሞ "ስሙን ለውጦ ነው'ንጂ መሓመድ ኑሪ ራሱ ኑረነቢ ነው።" ሲሉ በርግጠኝነት ተናገሩ። በተለይ የባህታ ልጅ ደጃዝማች ገብረመድህን ከዚሁ መሓመድ ኑሪ በሚል ስም ከሚታወቀው ሸፍታ

ጋር መታየቱ ሲሰማ ወሬው የበለጠ ታምኖ ነበር።

ዞረም ቀረ የኑረነቢ ነገር ርግጡ አልታወቀም።

እንዲህ ያሉ ወሬዎች በሚወሩበት ሰሞን ግን በድፍን ሓልሓል የኑረነቢ ስም ተጋንኖ ይነሳ ነበር። በተለይም ቅዳሜ ዞሮ ሲመጣ ገበያተኞች ከግላስ፣ ከፋና፣ ከሮራ መንሳዕ፣ ከአሸራ፣ ከሰንሒት እየመጡ ሓጋዝ ሲገናኙ ቀዳሚ አጀንዳቸው ኑረነቢ በኺት ሆነ። የፈጸመውን ጀብዱ እያነሱ ተረኩ። የኑረነቢን ጀብዱ አንዱ ወደ ሌላው ሲያስተላልፍ እየተጨማመረበት መልኩን ለወጠ። ኩራት በቀላቀለ መንፈስ የኑረነቢን ስም ማንሳትም ተለመደ።

ኑረነቢ ይኖርበት የነበረው ጎጆ ከጊዜ መርዘም ጋር አና ሆኖ ፈራረሰ። ኗሪዎች ከፍርስራሹ ላይ አንዳንድ እንጨቶችን እየመዘዙ ለማገዶ ወሰዱ። የእርሻ ርስቱን በጭቃ ሹሙ ዳኝነት ከኑረነቢ ጋር የቀረበ ዝምድና ያላቸው በአደራ ተረክበው ያርሱት ጀመር።

ለተወሰኑ አመታት ያህል የኑረነቢ ስም በወሬ መሃል መነሳቱ የማይቀር ሆኖ ነበር። በሰርግ ላይ ወይም በሃዘን ወቅት፤ የሓልሓል ሰዎች ተሰባስበው ሲጨዋወቱ፤ ተያያዥ ባልሆነ ምክንያት ጭምር የኑረነቢን ስም ደብለቅ ያደርጋሉ። አንድ ጊዜ ስሙ ከተነሳ በሁዋላ ማቆምያ አይኖረውም። ሽማግሎች ስለ ኑረነቢ የልብ ኩራት ሲተርኩ ብዙውን ጊዜ ወጣት ሴቶች ስሜታቸውን መቆጣጠር አይችሉም። ፊታቸውን በልውየታቸው ሸፈን ያደርጋሉ።

ከ1900 በሁዋላ ግን ኑረነቢ ጨርሶ ተረሳ።


የኑረነቢ የልጅ ልጆችም በስሙ ስለማይጠሩ በኤርትራ የዜጎች መዝገብ ላይ የኑረነቢ በኺት ስም ሳይመዘገብ ቀረ። የኑረነቢ ልጆችና የልጅ ልጆች "ገብረመድህን" የሚለውን ስም ስለሚጠቀሙ ኑረነቢ ስሙ የሚነሳበት አጋጣሚም አልነበረም። ይህ ታሪክ በተፈጸመ በ35ኛው አመት ግን የኑረነቢን ስም ከመቃብር የሚቀሰቅስ አጋጣሚ ተፈጠረ።



አስመራ - ኮምቢሽታዶ - ካቴድራል



ቴሌፍሪካ - የአየር ላይ የእቃ ባቡር - ከአስመራ ምጽዋ




የአጤ ምኒልክ መስፋፋት ወደ ደቡብ






ከላይ - አጼ ምኒልክ በአድዋ ጦርነት ማግስት እግርና እጃቸውን የቆረጧቸው የኢጣልያ ወታደሮች (ኤርትራውያን) በከፊል።


ከታች - ኡምኩሉ የስዊድናውያን ካምፕ 1890






- አጤ ምኒልክ ሃ/መለኮት
- ፊርዲናንዶ ማርቲኒ
- ራስ አሉላ ቁቢ
- ጀኔራል አሬስቶ ባራትዬሪ
- ባሻይ አውዓሎም ሓረጎት
- ደጃዝማች ባህታ ሓጎስ
- ቀኛዝማች ሰንጋል ሓጎስ
- አጤ ዮሃንስ ምርጫ









ደራሲው - ከ1800 ጀምሮ ተገንቡቶ በፈራረሰው የኡምኩሉ የላዛሪስት ካቶሊክ ሚስዮናውያን ማእከል



ደበሳይ ገብርኤል በጥንታዊው የኡምኩሉ ወንጌላውያን ማእከል - 2016

ክፍል ሁለት

ምእራፍ 1

በታሪክ ጎዳና - ለታሪክ ሰሪ ሰው
ነገ ሌላ ቀን ነው

በ20ኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ የአውሮፓ አገራት በራሳቸው ጉዳይ ስለተጠመዱ ኢትዮጵያን የረሱበት ጊዜ ነበር። በ1906 አጤ ምኒልክ ታመሙ። ራስ መኮንን እና ራስ መንገሻ ሞቱ። አጤ ምኒልክም ከታመሙበት ከ1906 በሁዋላ ኢትዮጵያም አለምን ረስታ ሰነበተች። ንጉሰነገስቱ መሞታቸው ከታወቀ በሁዋላ ኢትዮጵያ በተዳከመ የሽግግር ጊዜ ተያዘች።

"አጤ ምኒልክ ኤርትራን ለኢጣልያ ሸጠ።" የሚል አባባል ሲነገር ኖሯል። ተቀባይነት ያለው እውነት ግን አጤ ምኒልክ 'ኢትዮጵያ" የተባለች አገር ይመሰርቱ ዘንድ በአውሮፓውያን መመከራቸውና ያንን በተግባር መፈጸም መቻላቸው ነው። በወቅቱ አጤ ምኒልክ የኢትዮጵያን ኤምፓየር ለመመስረት ወደ ደቡብ ከመስፋፋት ያለፈ ስለ ኤርትራ ስታራቴጂያዊ ጠቀሜታ የመገንዘብ ደረጃ ላይ አልነበሩም።

በርግጥ አጤ ምኒልክ በደቡብና በምስራቅ የተሳካ ወረራ ማካሄድ ችለው ነበር። ለእነዚህ የደቡብ እና የምስራቅ ዜጎች ዘመኑ የጨለማ ዘመን ነበር። የአጤ ምኒልክ አዲስ ገዢ ስርአት መሬታቸውን ነጥቆ ሲያበቃ፤ ነዋሪዎችን ለባርያ ፈንጋዮች አሳልፎ ሰጠ። የጅማው አባ ጅፋር እና የወለጋው ጅቴ ጁሉ ያለውጊያ ስለገበሩ የገጠማቸው አደጋ አነስተኛ ነበር። አርሲ፣ ባሌ፣ ወላይታ፣

ከፋ አሰቃቂ ግፍ አስተናገዱ። ጋኪ ሻረቾ በእስርቤት ሞተ።

ራስ ሉል ሰገድ የኮሬን ህዝብ ፈጅ። ራስ መኮንን የሃረርጌን መስጊዶች እያፈረሰ ቤተክርስትያን ተከለባቸው። ራስ ጎበና ወለጋ፣ ከፋ፣ ጅማ፣ ሊሙ፣ ጌራ እና ጉማን ቀጥቅጦ አስገበረ። ራስ ዳርጌ በአርሲ ተመሳሳይ ተልእኮ ፈጸመ። አሚር አብዱላሂ ተሸንፎ ጁገልን ከመልቀቁ በፊት የመላ ወጣቶቹን ህይወት ለነፍጠኛ መገበር ነበረበት። ኢሉ-አባ-ቦራ እና ጉራጌ ተያዙ። ኮንታ እና ኩሉ በራስ ወልደጊዮርጊስ ቁጥጥር ስር ገቡ። ከንባታ፣ ኦጋዴን፣ ባሌ ሲዳሞ ለጠቁ። ራስ ወልደጊዮርጊስ ጎፋን አንበረከከ። በመቀጠል ቦረና ገበረ። ሃብተጊዮርጊስ ወደ ኮንሶ ዘመተ። ቤኒሻንጉል ከተያዘ በሁዋላ ወልደ ጊዮርጊስ ማጂን አልፎ ሩዶልፍ ሃይቅ ደረሰ። ራስ ተሰማ ጊሚራን ያዘ። እናም ኢትዮጵያ የምትባል አገር ተመሰረተች። አጤ ምኒልክ ኢትዮጵያን የመመስረት ተልእኳቸውን ከፈጸሙ በሁዋላ ታመው አልጋ ላይ ለአመታት ቆይተው ነበር። ሻል ሲላቸው ዙፋናቸውንም ለልጅ እያሱ ተናዘዙ።

የአጤ ምኒልክ አልጋ ወራሽ ልጅ እያሱ ከቱርክ አገዛዝ ጋር የድብቅ ስምምነት ስለማድረጉ በሰፊው ታማ። ዝንባሌው ወደ ጀርመኖች መሆኑ ተነገረ። የእያሱ አካሄድ ያላማራቸው እንግሊዝ፣ ፈረንሳይና ጣልያን በኢትዮጵያ ጉዳይ ላይ ስምምነት አደረጉ። ከአጤ ምኒልክ መሞት እና ከእያሱ አዲስ ዝንባሌ ጋር የአውሮፓ ሃያላን አገራት እንደገና አይናቸውን ኢትዮጵያ ላይ ጣሉ። ጀርመን ቀድማ ኢትዮጵያን እንዳትቆጣጠር ኢጣልያ ነቅታ መጠበቅ ያዘች።

የልጅ እያሱ ስልጣን አልዘለቀም። የኢትዮጵያን ህብረተሰብ በእኩል አይን የማስተዳደር ዝንባሌው የሸዋን መኳንንት አስደነገጠ። ለዘመናት "የክርስትያን ደሴት" ስትባል በኖረችው ኢትዮጵያ ላይ ሙስሊሙ እኩል መብት ማግኘቱን የሸዋ መሳፍንት ሊቀበሉት የሚችሉት አልነበረም። እና ተፈሪን አስቀድመው ዙፋን ፈነቀሉ።

ልጅ እያሱን ማስወገድ አስቸጋሪ አልነበረም። በቅድሚያ የሃሰት ወሬ ለቀቁበት። "እያሱ የእስላም ልብስ ለበሰ!"፣ "የማድ ሙላህን ልጅ ሊያገባ ሽማግሌ ላከ!"፣ "የኢትዮጵያ ባንዴራ ላይ ኮከብና ጨረቃ ለጠፈ!"፣ "ከኮከብና ጨረቃው ስር፣ 'አላህ እንጂ እግዚአብሄር የለም' የሚል ጽሁፍ አሰፈረ!"፣ "ኢትዮጵያን በቱርክ

ህግ ለማስተዳደር ወሰነ!" የሚል ወሬ አስወሩበት። በአርመናውያን አስፈጻሚነት እያሱ ጀለቢያ ለብሶ የሚያሳይ ፎቶ ግብጽ ላይ ተባዝቶ ለሸዋ መኳንንት ተበተነ። ከዚህ በሁዋላ ራሶች እያሱን አውርደው ዘውዲቱን በንግስትነት ለማስቀመጥ አልተቸገሩም።

እያሱ ከአያቱ በውርስ ያገኘውን ዙፋን ለማስከበር መሞከሩ አልቀረም። አልቀናውም። ስለዚህ ወደ ደንከሊያ ሸሸ። በ1921 ተይዞ ፍቼ በራስ ሃይሉ ተከለሃይማኖት እጅ እንዲታሰር ተፈረደት። ራስ ሃይሉ ከኢጣልያውያን ጋር ባደረገው ስምምነት እያሱ ከእስር ቤት አምልጦ ነበር። ዳሩ እያሱን ወደ ኤርትራ የማሻገሩ እቅድ አልተሳካም። ልጅ እያሱም ራስ ሃይሉም ተይዘው ታሰሩ።

የሸዋ መኳንንት እያሱን ከስልጣን አውርደው ዘውዲቱን ካነገሱ በሁዋላና በፊት ጥቂት መተራመሶችና ጦርነቶች ተካሂደዋል። ከእነዚህ መተራመሶች አንዱ የደጃዝማች ባልቻ ሳፎ (አባ ነፍሶ) አመጽ አንዱ ነበር። ተፈሪ በተንኮል በልጦ ተገኘ። ባልቻ ተፈሪን መናቁ ከታወቀ በሁዋላ ወደ አዲሳባ ተጠራ። ሊያስሩት እንደሆነ በመጠርጠሩ አስር ሺህ ሰራዊት ይዞ መጣባቸው። ከቤተመንግስቱ አስራ ሁለት ኪሎሜትር ላይ ሰራዊቱን አስፍሮ ሲያበቃ፤ 600 ታማኝ ታጣቂዎች ይዞ ወደ ቤተመንግስቱ ግብጣ ሄደ። በግብጣው አዝማሪዎች ባልቻን አሞገሱ። ባልቻ እየተዘፈነለት ሳለ ግን የተፈሪ ወታደሮች የአዲሳባ ደጃፍ ላይ የሰፈሩትን የባልቻ ወታደሮች ገንዘብ እየሰጡ ጠመንጃቸውን በመግዛት ላይ ነበሩ። ያንገራገረውን ገደሉት። ደጃች ባልቻ ግብጣውን ጨርሶ ወደ ሰራዊቱ ሲመለስ አይኑን ማመን አቃተው። ሰፈሩ ተቃጥሎ ጠበቀው። 600 ተከታዮቹን ይዞ ለማምለጥ ያደረገው ሙከራም አልተሳካ። ተከቦ ነበር። እጁን ሰጠ። ደጃች ባልቻ የተከበረ ስም ስለነበረው አልገደሉትም። ገዳም እንዲገባ አስገደዱት። ኢጣልያ ኢትዮጵያን እስኪወርም በገዳም በብቸኛነት ቆየ። ተፈሪ ወደ እንግሊዝ ሲሸሽ ባልቻ ከገዳም ወጥቶ ወራሪ ኢጣልያን እየተዋጋ ህይወቱን ሰጠ።

ተፈሪ መኮንን ከልጅ እያሱ አባት ከራስ ሚካኤል ጋርም ግጭት ማድረጉ ግድ ነበር። ራስ ሚካኤል አልቀናቸውም። ከሃብተጊዮርጊስ ዲነግዴ ጋር ተዋግተው ሰገሌ - ሸኖ ላይ ተማረኩ።

የንግስተ ነገስት ዘውዲቱ ባል ራስ ጉግሳ ወሌ የጣይቱ

ብጡል የወንድም ልጅ ነበር። ዘውዲቱን ሲያነግሱ ንጉስነትን እንዳይመኝ በሚል ጋብቻው እንዲፈርስ አደረጉ። የጉግሳ ቅሬታ የጀመረው በዚህ ነባር የሸዋ ተንኮል ነበር። የዘውዲቱን ጋብቻ በግዴታ አፍርሰው ለይስሙላ ካነገሷት በሁዋላ ራስ ጉግሳን በጌምድር ሾሙት። ራስ ጉግሳ ጊዜ ጠብቆ ለመበቀል ያደረገው ሙከራ አልተሳካም። "ተፈሪ ሃይማኖቱን ወደ ካቶሊክነት ለውጦ ኢትዮጵያን ለኢጣልያ ሊሸጣት ነው።" የሚለውን ቅስቀሳ በቀላሉ አከሸፉበት። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስትያን በራስ ጉግሳ ወሌ ሰራዊት ውስጥ የበተነችው፣ "ራስ ተፈሪ ታምኝ የኦርቶዶክስ አማኝ ናቸው" የሚለው ማስተባበያ የራስ ጉግሳን ሰራዊት እሁለት ከፈለው። እና ከራስ ሙሉጌታ ጋር በተደረገው ጦርነት ራስ ጉግሳ ወሌ ተገደለና ሰራዊቱም ተፈታ። የባለቤታቸውን መሸነፍና መገደል ሲሰሙ ንግስተ ነገስት ዘውዲቱ በሶስተኛው ቀን ባልታወቀ ሁኔታ ሞተው አደሩ። የአሟሟታቸው ምክንያት ርግጡ አልታወቀም። እና ተፈሪ መኮንን ጊዜውን ተጠቀመበት። ታሪክ የአሸናፊዎች ነው።

ራስ ተፈሪ በፖለቲካ ተንኮል ችሎታው ተወዳዳሪ አልነበረውም። ዋና ተቀናቃኞቹ የነበሩትን ዘውዲቱና ባልቻን በረቀቀ ዘዴና ጥበብ ካስወገደ በሁዋላ ለሁለቱም በስማቸው ሆስፒታል ሰይሞላቸዋል። ደጃች ባልቻ እና ንግስተነገስት ዘውዲቱ ግን በኢትዮጵያ ምድር ላይ የሚጠሉት ቀዳሚ ሰው ቢኖር ራስ ተፈሪ ነበር። ሮበርት ግሪን ራስ ተፈሪ ደጃች ባልቻ እና ራስ ጉግሳን እንዴት በጥበብ አስወግዶ ስልጣኑን ማስቀጠል እንደቻለ ተንትኖ ጽፏል።

(ሁዋላ አጤ ሃይለስላሴ በማይጨው ውጊያ ተሸንፈው ወደ ጅቡቲ ሲሸሹ ጣልያን እያሱን እንዳይጠቀምበት እንዲገደል አደረጉ። ልጅ እያሱ ቢገደልም ልጆቹ ብዙ ነበሩ። ልጅ እያሱ 'ከኢትዮጵያ የተለያዩ ብሄረሰቦች እና ሃይማኖቶች ልጆችን በመውለድ የኢትዮጵያን አንድነት አስከብራለሁ።' የሚል መዝናኛ አዘል ፖለቲካ ነበረው። ለልጆቹ የሰጣቸው ሰም ቴዎድሮስ - ዮሃንስ - ምኒልክ - ግርማ - መልዐከጸሃይ - መስፍን የሚል ነበር። በየጊዜው "የእያሱ ልጆች ነን" እያሉ ብቅ የሚሉ ማለቂያ አልነበራቸውም። ልጅ እያሱ በአጭር ጊዜ የስልጣን ዘመኑ የፈጸመው የተሳካ ተግባር ቢኖር ከደርዘን በላይ ልጆች ማፍራት መቻሉ ነበር።)

ምእራፍ 2

በእነዚያ አመታት

የኢጣልያን “ልብ” አየናት!

በኑረነቢ ልጆች ቤተሰብ ውስጥ ጥቂት ለውጦች ተከሰቱ። ርግጥ ነው፤ በልዩ ሁኔታ ሊወሳ የሚችል ክስተት ላይሆን ይችላል። ሆኖም ህይወት ያለ ለውጥ አትጓዝምና። ከመብላትና ከመጠጣት፣ ከመተኛትና ከመነሳት ባሻገር የሰው ልጅ በህይወት መንገድ ላይ አያሌ ተግዳሮቶች ይገጥሙታል።

የኑረነቢ ልጆች ከከረን ሚስዮን ከተሰናበቱ በሁዋላ ህይወታቸው ለየቅል ሆኖ ነበር። እድሪስ ከቱርክ ጋር ለመዋጋት ወደ ሊቢያ ከዘመቱት የመጀመሪያዎቹ ወታደሮች አንዱ ሆነ። አድም አስመራ ፖስታ ቤት ተቀጥሮ ሲቪል ሰራተኛ ሆነ። ሁለቱም አግብተው ልጆች ወልደዋል። “ኤድዋር” እና “ኤድሞ” የነበረ የፈረንሳይኛ ቅላጼ የያዘ ስማቸው ከጊዜው ጋር ተለውጦ “ኤድዋርዶ” እና “ኤድሞንዶ” ሆኗል። የተመዘገበ ስማቸው እንዲያ ቢሆንም ርስበርስ ግን በልጅነት ስማቸው መጠቀሙን ይመርጣሉ።

ኤድሞንዶ ዋናው ፖስታ ቤት ከተቀጠረ በሁዋላ ስራ አልቀየረም። ከታላቅ ወንድሙ ጋር ሲነጻጸር ህይወቱ የተረጋጋ ነበር። ሁለት ልጆቹ ሚካኤል እና ገብርኤል ለአገሬው ዜጋ ከተፈቀደው

በላይ ከረን እየተማሩ ነበር። የካቶሊክ እምነት ተከታዮች መሆናቸው፣ የፈረንሳይኛ እና የኢጣልያንኛ ቋንቋ ችሎታቸው፣ ያስገኘላቸው ጥቅም ነበር። ገብርኤልና ሚካኤልም እንዲሁ የኢጣልያ ቋንቋ ችሎታቸው የተመሰገነ ለመሆን ቻለ። ሁለቱም በትርፍ ጊዜ ከረን የፖለቲካ ጽህፈት ቤት በአስተርጓሚነት እየሰሩ ይማሩ ነበር። የወደፊት እድላቸው አስካሪ ከመሆን ያመለጠ ቢሆንም፤ ኤድዋርዶ ለልጆቹ የሚመኘው ተራ አስተርጓሚነትን ወይም ተራ የመኪና ጸሃፊነትን አልነበረም። ወደ ኢጣልያ ሄደው በከፍተኛ ደረጃ እንዲማሩለት አለቆቹን ከመወትወት ቦዝኖ አያውቅም። ባለቤቱ ተዋበሽ ገብራይ ትንሽ የጤና ችግር ነበረባት። ሁለት ሳምንት አልጋ ይዛ ከታከመች በሁዋላ ግን መሻሻል አሳየች። ምግብ በቀመሰች ቁጥር ጨጓራውን ያነዳት የነበረው ሁሉ ድራሹ ጠፋ። የፈለገችውን እያማረጠች መመገብ ቻለች። በተለይ ግን የግመል ወተት ፈዋሽ ምግቧ ሆነ።

በወርሃ ነሃሴ 1920 አንድ ሰንበት ማለዳ በካቫሌር አዝማች ኤድዋርዶ መኖሪያ ቤት ትልቅ ግብዣ ተደረገ። በርግጥም ሁለት ሙክት በአንድ ጊዜ ማረድ ትንሽ ግብዣ አልነበረም። የግብዣው ምክንያት ኤድዋርዶ ረጅም ጊዜ ከሰራበት የትሪፖሊታኒያ፣ የሲሪናይከ እና የፊዘን ዘመቻዎች ወታደራዊ አገልግሎቱን ጨርሶ በሰላም ወደ ኤርትራ በመመለሱ ነበር።

በዚያን ሰሞን የአስመራ አዝማሪዎች በአባ ሻውል፣ በገዛ ታኒካ፣ በገዛ ብርሃኑ፣ በማይተመናይ እየተዘዋወሩ ባለቤታቸው ያልታወቁ ዜማዎችን ያዜሙ ነበር።

ሊቢያ ውረድ - ተሰገር እምኒ
እንተሞትካ - ዕዳካ ትስኒ
እንተለኻ - መዳልያ ተግኒ
- - -
ሊቢያ ዝመት - ተሻገር በረሃ
ከሞትከ - ዕዳ ቀረልሃ
ካለህ - ሜዳልያ ታገኛለሃ
* * *

በዓል አደይ - ልበን ቀሊል
ጓል"ንተ ወለዳ - ዝብላ ጽልል
ወድ"ንተወለዳ - ዝብላ ዕልል
ወላ ዓዋን ይኹን - ዋላ ጀሊል
ትሩቡሊ ከይዱ - ዝብል ሸብልል
- - -
እናቶቻችን - ልበ የዋህ
ሴት ሲወልዱ - ኡኡታ
ወንድ ሲወልዱ - ዕልልታ
ሞኝም ሆነ ብልህ - ቅሉ
ትሪፖሊ መሞት ዕድሉ

ወደ ሊቢያ የዘመተ የመመለስ እድሉ ጠባብ ስለነበር፤ ኤድዋርዶ ከአካላቱ አንድም ሳይጎድል፤ ማእረግ ተጨምሮለት፣ አንደኛ ደረጃ የጀግና ሜዳይ ተሸልሞ ወደ አገሩ በሰላም መመለሱ ለቤተሰቡ እጅግ አስደሳች ዜና ነበር።

በጥንት ዘመን በምድሪ ባሕሪ ዜጎች እምነት ወንድ ልጅ መውለድ ልዩ ዋጋ ነበረው። ማቋረጫ ባልነበረው የሊቢያ ዘመቻ ምክንያት ግን ባንድ ወቅት ወንድ መውለድ፤ ሴት ከመውለድ በላይ ለማሳቀቅ በቅቶ ነበር። በርግጥ ለወንድ ልጆች ልዩ ግምት መስጠት በ21ኛው ክፍለዘመን እንኳ ቀጥሏል። ይህን የሚያስረዳ በ20ኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ላይ የተፈጸመ ወግ አለ፣

ግደ አንደስላሴ (ወዲ አንደ) የተባለ በስራው፣ በጠባዩ፣ በብልህነቱ የተከበረ ሰው ደቂሸሃይ ይኖር ነበር። አንዲት ሴት በቂም ተነሳስታ መርዛ ገደለችው። ወዲ አንደ ምብራቅ እና አባዲት የተባሉ ሴቶች ልጆች እንጂ ወንድ ልጅ አልነበረውም። ቀብሩ ከተፈጸመ በሁዋላ የግደ ገዳይ ያለ ችግር ኑሮዋን በመቀጠሏ የተቆጨው ወዲ ዑቕቢት (የደቂ ሸሓይ አውሎኛ) እንዲህ አቀነቀነ፣

ወዲ አንደ - አዋልድ ወሊዱ - ወሊዱ
ደሙ ብላሽ ተሪፉ - ወይ ጉዱ - ወይ ጉዱ

ወዲ አንደ - ሴቶች ወልዶ - ወልዶ
ደሙ መና ቀረ - ወይ ነዶ - ወይ ነዶ

* * *

ወደ ኤድዋርዶ መኖሪያ እንግዶች መምጣታቸው ቀጠለ፣

በኤድዋርዶ መመለስ ዘመድ አዝማድና ጎረቤቶች የደስታው ተካፋይ ሆኑ። በዚህ ግብጣ ላይ ለመገኘት ከቦጎስ - ፋና ጭምር ጥቂት የሩቅ ዘመዶች መጥተዋል። ከቅርብም ከሩቅም የሚመጡ እንግዶች የተጠቀለለ ስጦታ ይይዛሉ። ልጆቻቸውን አስከትለው የመጡ ባልና ሚስት ጎረቤቶች ገና ደጃፉ ላይ ስደርሱ እልልታ አሰሙ። ወደ ውስጥ ሲዘልቁም ኤድዋርዶን አገላብጠው ሳሙት፣

"እንኳን ከሼኽ ዑመር ኢል ሙኽታር ጎራዴ አተረፈህ። እንኳን ከትሩቡሊ የበረሃ ምላስ አምላክ አወጣህ!"

የኑረነቢ ልጆች ምርጥ ልብሶቻቸውን ለብሰው እንግዶቻቸውን በደስተኛ መንፈስ አስተናገዱ። ግብጣው የደመቀ ሆነ። በዚህም በዚያም ያለፉትን ጊዜያት በየፊናቸው እያነሱ ተጨዋወቱ። የወጎች ማእከል ግን ኤድዋርዶ ነበር። ዳሩ ኤድዋርዶ በተፈጥሮው ብዙ መናገር የሚሆንለት አልነበረም። ቢሆንም የእንግዶቹን ፍላጎት ለማርካት ያህል አንዳንድ ገጠመኞቹን እያነሳ አጫወታቸው። በሳኑሲ ተዋጊዎች ጎራዴ እየታረዱ በየበረሃው ስለወደቁ ኤርትራውያን ግን አላነሳም። እንዲሁ ብቻ የእንግዶቹን ጥያቄ ለመመለስ ያህል ነገሩን ነካ ነካ እያደረገ ተወው። እንግዶቹ ግን የመስማት ፍላጎታቸው በጣም በመበርታቱ አስጨንቀው ያዙት። በተለይም ታናሽ ወንድሙ ኤድሞንዶ ጥያቄ እያነሳ ወተወተው።

በ1912 ቁጥራቸው 112 የሚደርስ የመጀመሪያው ዙር ወታደሮች የሊቢያን ምድረበዳ ሲረግጡ ኤድዋርዶ ሙንጣዝ ማእረግ ለብሶ ከዘመቱት አንዱ ነበር። ኤርትራውያንን ለማጓጓዝ በተደጋጋሚ ወደ አስመራ ለመመላለስ እድል በማግኘቱ ግን እድለኛ ሆነ። ቤተሰቡን ለማየት፤ በአገር ልማድ መሰረት ጊዜውን ጠብቆ በተከታታይ ልጆች ለመውለድ ቻለ። በልጅ ረገድ ከአድም ተሻለ። ልጆቹ በረከቱለት። ባለቤቱ አምስተኛውን ልጅ ነፍሰጡር ነበረች።

በዚያን ቀን ግብጣው ላይ የተገኙ እንግዶች ኤድዋርዶ ከሊቢያ ጠቅልሎ በመመለሱ ደስታቸውን ገልጸው ሲያበቁ ስለ ሊቢያ ቆይታው በነገራቸው ባለመርካት በጥያቄ አጣደፉት። ሊቢያ

የዘመተ ዘመድ የሌለው የለም። እና የሁሉም ጥያቄ በሰቀቀን የተዋጠ ነበር። ኤድዋርዶ ይህን ተረድቶ በጎ በጎውን እያነሳ መናገሩን ሲቀጥል በየጣልቃው እየገቡ በወሬ የሰሙትን እያነሱ አዋከቡት፣

“ሼኽ ዑመር መተት አለው መባሉ እንዴት ነው?”

“ከ7ኛው ባታሊዮን አንድም ሰው አልተረፈ?”

“ኢለና ረጂና ጉድ ሰራችን! ወይኔ ወንድሞቻችን!”

“ምን ገጥሟት ሰጠመች ባክህ?”

“የትኛው ባታልዮን ነው በበረሃ የተበላው?”

ኤድዋርዶ ያየውንና የሰማውን እየቀላቀለ አወጋ።

7ኛው ባታሊዮን በመርከብ ወደ ሊቢያ በመጓዝ ላይ ሳለ ሜዲትራንያን ባሕር ላይ መርከቧ የመስመጧ አሰቃቂ ዜና በመላ ኤርትራ ለአያሌ ወራት ያለማቋረጥ የተነገረ ነበር። ወሬውና ሰቆቃው ሊረሳ አልቻልም። ኢለና ረጂና ላይ ተሳፍረው የነበሩ 500 ኤርትራውያን ወጣቶች መርከቧ በመስጠም ላይ ሳለች “አድኑን” የሚል ጥሪ ያሰሙ ነበር። የሚደርስላቸው አጋዥ ግን በአካባቢው አልነበረም። ጥቂቶች በመንሳፈፊያና በዋና መትረፍ ቻሉ። የሜዲትራንያን ባሕር አሳዎች ለመጀመሪያ ጊዜ ኤርትራውያንን ቀለብ ማድረግ የጀመሩት ኢለና በሰጠመች ጊዜ ነበር። ማን በባሕር አሳ ተቆረጠመ? ማን በሼኽ ዑመር ጎራዴ ተቀላ? ማን በሊቢያ አሸዋ ተጋጠ? አይታወቅም። መጽናኛቸው እንጉርጉሮ ሆነ፣

ትሩቡሊ ጸላኢና ይኺዶ
ከይትሃድም ቀላይ ዝጋረዶ
ከይትጠርዕ ንጉስ ዝፈረዶ
አብኡ ዘሎ ኩናት መሓመዶ
ብካራ ገዲፎም ብጋለዶ
- - -
ትሪፖሊ ለጠላትም አያስመኝም
በባሕር ተከቦ ማምለጫ የለም
እንዳትከስ ንጉስ ወስኗል
የእነ መሓመድ ጦርነት
ከሳንጃ አልፎ በጎራዴ

* * *
ከም ሰቲም ዝረከበዶሎ
ቀያሕቶም መሲሎም ጸለሎ
ኣንቲ ኤሌና ወይ ኤሌና
ለኪምክዮም ከይድኪ ጀጋኑ ኣሕዋትና
- - -
ክፉ ገጠመው ሰባተኛ?
ጎበዝ ቀያዮች ጥቀርሻ ለበሱ
ኤሊና ኤሊና ጦሰኛ
ጀግና ይዘሽ ጠፉሽ መጋኛ

ከአርባ ሺህ በላይ ኤርትራውያን ወደ ሊቢያ ተወስደው በጦርነት ውስጥ አልፈዋል። አንዱ ሲሄድ ሌላው እየመጣ ተፈራርቋል። ከሊቢያ ተመላሾች የሰፈሩበትን ሰፈር ጣልያኖች "ላርጎ ሊቢያ" ብለው ሲጠሩት አበሾች "ደባልቆ" የሚል ስም ሰጡት። ብዙ አይነት ሰው ተደባልቆ የሚታይበት መንደር ነበር። ከመረብ ምላሽ ብቻ ሳይሆን ከመረብ ወዲያ ማዶ ከጎንደርና ከትግራይ መጥተው ለጣልያን ወታደርነት ተቀጥረው ሊቢያ የዘመቱ ዜጎች ጭምር ከጥቂት በላይ ነበሩ።

የላርጎ ሊቢያ ሰፋሪዎች በሳር እንደነገሩ በተሰሩ ጎጆዎች ውስጥ ይኖራሉ። አምባጓሮ እና የእሳት አደጋ በደባልቆ አይጠፋም። በመሸታ ቤቶች የሊቢያ ጀብዱ እየተነሳ ይተረካል። አውሎ አውሎ ይባላል፤ መሰንቆ የያዘ አዝማሪ ግጥም እየተቀበለ ያዜማል፣

ራብዓይ ቦጦሎኒ - በዓል ስረ
ሓዊ ሓዊ ዝጨንው - አሰር ዓረ
ፈሽራ ሼኽ ዑመር - ገበርናዮ ወረ
ብሳላና ጅግንነት - ጥልያን ኸበረ
- - -
አራተኛ ባታልዮን - ልበ ጀግና
እሳት የሸተተው - የባሩድ ፋና
የሼኽ ዑመርን ፉከራ - በወሬ ያስቀረ
በኛ ጀግንነት - ጣልያን ተከበረ

ከመላ ኤርትራ ለወሬ ፍለጋ ወደ ላርጎ ሊቢያ የማይመጣ የለም። ወደ ሊቢያ ስለዘመተ ልጁ ወሬ ለማግኘት የሚመጣው

ባላገር ማቋረጫ የለውም። በርግጥ ማንም መንገደኛ ላርጎ ሊቢያ ዘው ማለት አይችልም። መዘረፍ እና መደብደብ ያጋጥማል። ይህን የሚያስፈጽሙ ደላሎች ግን አሉ።

ወዲ ባጽዕ የላርጎ ሊቢያ አውደልዳይ ነው። ድለላ ዋና ስራው ቢሆንም፤ በትርፍ ጊዜው ጨለማ ለብሶ ማጅራት በመምታት ገቢ ያገኛል። ካጋጠመው ኪስ አውላቂነትም ቢሆን ይሰራል። ወዲ ባጽዕ ቀን ቀን የሊቢያ ወሬ ፈልገው የሚመጡ ባላገር እንግዶችን በመቀበል በደባልቆ ጎጆዎች እየዞረ ወሬ ያጠያይቃል። ለተባባሪ ማጅራት መቺዎች በማመቻቸትም ደምበኞቹን ያስዘርፋል። በዚህም ተባለ በዚያ ላርጎ ሊቢያ የገባ ባዶ እጁን መመለሱ ግድ ነበር።

ልጁ በሰላም የተመለሰለት ቤተሰብ ደስታው ዳርቻ ሲያጣ፤ መርዶ የሰማ በአንጻሩ ሃዘኑ ቅጥ ያጣል። ከምድብ ባታሊዮናቸው ተነጥለው ያልተመለሱ በህይወት እንደሌሉ ይቆጠራል። የሳህል በረሃ፣ የሜዲትራንያን ባሕርና የሳኑሲ ተዋጊዎች ጎራዴ ራት ሆነው መቅረታቸውን ቤተሰብ በመርዶ ሳይሆን በደመነፍስ ያውቃል። እና በዚያን ዘመን ልጁ ቱሩቡሊ የሄደበት ወላጅ፣ አባቱ የዘመተበት ጨቅላ ያለማቋረጥ ስለ ሊቢያ ያንጎራጉራል። ልቡ መሪር እጣውን ቢነግረውም ከዛሬ ነገ ቤተሰቡን መልሶ ለማግኘት ተስፋ ማድረጉ አይቀርም። ላርጎ ሊቢያ ፈርሶ ወደ ገዛ ታኒካ እስኪጋዙ ድረስ የገጠር ገጣሚዎች “አውሎ - አውሎ” ሲሉ የሚያመሹት በዚሁ በደባልቆ መሸታ ቤቶች ነበር። ከሊቢያ የሞት ከርስ ተርፈው እንደ ኤድዋርዶ ወደ አስመራ ብቅ የሚሉ ሲገኙ ቀሪ ቤተሰብ አምላኩን ያመሰግናል። ሌላውም በጎ ዜና ለመስማት እየተመኘ ከሊቢያ ስላልተመለሱ ልጆቹ ያለማቋረጥ ያጠያይቃል።

(ሊቢያ ላይ ለነጻነቱ ይዋጋ የነበረው ሳኑሲ የተባለው እስላማዊ ቡድን ቁጥሩ በሺህዎች ብቻ የሚገመት አነስተኛ ቢሆንም የኢጣልያን ቅኝ አገዛዝ አስጨንቆ መያዝና መመከት ችሎ ነበር። አማጽያኑ ከግብጽና ከቱርክ ድጋፍ ቢያገኙም መሰረታቸው ዘላኑ ህዝብ ነበር። ኢጣልያ 20ሺህ ወታደር ይዛ ሳኑሲን መቋቋም እስክትቸገር ድረስ በረቱባት። ሁዋላ ጀኔራል ግራዝያኒ ሳኑሲን መደምሰስ ቢችግረው የጅምላ እልቂት ወደ መፈጸም ገብቷል። የሳኑሲ መሪ ሼሽ ዑመር ተይዞ በስቅላት እስኪቀጣ ድረስም ኢጣልያ ተረጋግታ የሊቢያን የከርሰ ምድር ሃብት ለመፈተሽ አልቻለችም።)

* * *

በኤድዋርዶ መኖሪያ ቤት ግብዣው ቀጠለ፣

ደጃፉ ላይ በኢጣልያ ቋንቋ እየዘፈኑ የሚጫወቱ የልጆች ድምጽ ይሰማል። የልጆቹ ዘፈን የካቫሌር ኤድዋርዶን ትኩረት ለመሳብ በቃ። ጆሮውን ተክሎ ሲያዳምጥ ከቆየ በሁዋላ ከሚዘፍኑት ልጆች አንዷን ጠርቶ እንድትደግምለት ጠየቃት። ትምህርት ቤት የተማረችውን ዘፈን በሞቀ ኮልታፋ ኢጣልያንኛ ቋንቋ ደገመችለት፣

ከሰለጠኑት የአውሮፓ አገራት - ኢጣሊያ አንዲ ናት
አፈቅርሻለሁ ኢጣልያ - ላንቺ ረጅም እድሜ!
ለኢጣሊያ ንጉስ - ረጅም እድሜ!
በኢጣልያ ስር በመገዛቴ ደስተኛ ነኝ
ዳግማዊ አገሬን - ለዘልአለሙ እንዳከብር...
አምላኬ ሆይ አግዘኝ - አምላኬ ሆይ እርዳኝ

ኤድዋርዶ አፉን በርግዶ ሳቀ። እና ባርኔጣውን አውልቆ ጠረጴዛው ላይ አስቀመጠ። እንዲያ የሳቀበትን ምክንያት ይነግራቸው ዘንድ በጉጉት ቢጠብቁትም ህጻናቱን አሰናብቶ ወደ ሌላ ወሬ ገባ።

ኢጣልያ ምድሪ ባሕሪን በተቆጣጠረች ጊዜ ወደ ኤርትራ ከሚመጡት የኢጣልያ ወታደሮች አብዛኞቹ ማንበብና መጻፍ እንኳ በቅጡ የማይችሉ እንደነበሩ ኤድዋርዶ ያውቅ ነበር። ለቤተሰባቸው ደብዳቤ ለመላክ ለምነው ያስጽፉ ነበር። በተለይ ከ1915 በሁዋላ ኤርትራ ላይ "ነጭ ሰው ሁሉ አዋቂ ነው" የሚለው አባባል ተቀይሮ "የተማረ አዋቂ ነው" በሚል መተካት የጀመረበት ጊዜ ነበር። በተለይ ወደ ኢጣልያ ሄደው የተማሩ ኤርትራውያን ወጣቶች በኢጣልያንኛ የተጻፉ መጻህፍትን እያፈላለጉ ማንበብ በመጀመራቸው ሰበካውን ከእውነቱ መለየት እየቻሉ ነበር።

ገና ከመነሻው ኢጣልያ በአውሮፓ ውስጥ ያለችበትን ደረጃ ለማወቅ ለኤርትራውያን የተዘጋ አልነበረም። ተገደው ወታደር ሆነው ኤርትራ የሚመጡ የኢጣልያ ገበሬ ልጆች ስለ አገራቸው ሁኔታ ሲያወጉ የመደባበቅ ነገር አልነበራቸውም። በኢጣሊያ ስራ አጥነቱ በከፍተኛ ሁኔታ ማሻቀቡን ይናገራሉ። ለወታደርነት በግዳጅ

መመልመላቸውን አይደብቁም። የተጣለበትን የመሬት ግብር መክፈል ስለከበደው እርሻውን ትቶ ያልፍልኛል በሚል ወደ ኤርትራ የመጣም ገጠመኙን ያወጋል። ወደ አሜሪካ፣ አርጀንቲናና ብራዚል ስለተሰደዱ ዘመዶቻቸው በስሜትና በናፍቆት ይናገራሉ። ደብዳቤ ይጻጻፋሉ። ከኤርትራ ወደ ብራዚል ለመሄድ መንገድ ያፈላልጋሉ። ሳይሳካላቸው ሲቀር ያማርራሉ። ለህንጻ ስራ ወደ ኤርትራ የመጡ ኢጣልያውያን፣ "ወደ አገራችን መልሱን" የሚል ጥያቄ ይዘው የተቃውሞ ሰልፍ ያደርጋሉ። ከጦርነት ለማምለጥ ይጥራሉ። ወላጆቻቸው የሚጽፉላቸው ደብዳቤዎችም ይህንኑ ያንጸባርቃል። ከኤርትራ እንደምንም ብሎ ወደ አርጀንቲና እንዲሻገር በአባቱ የተመከረ ወጣት ይህንኑ አብረውት ለሚሰሩት ኤርትራውያን ያጫውታል። ኢጣልያ ኢትዮጵያን ለመውረር በተዘጋጀችበት ጊዜ በተለይ ኢጣልያውያኑም ሆነ ኤርትራውያኑ ወጣቶች ራሳቸውን ከጦርነቱ የማግለል ፍላጎታቸው የበረታ ነበር።

"ከሰለጠኑት የአውሮፓ አገራት - ኢጣልያ አንዷ ናት" የሚለው ስንኝ በተለይ ግማሽ እድሜውን ሊቢያ ላሳለፈው እና ፓሌርሞን ደጋግሞ ለጎበኘው ኤድዋርዶ ተረት ነበር የሆነበት።

* * *

ርግጥ ነው፤ የኢጣልያ ኮሎኒ ኤርትራውያንን በረጅም ርቀት በድንቁርና እያስከተለ ለመግዛት ያደረገው ጥረት ግዛቱን አስጠብቆ ለመቆየት አግዞታል። አንድ ኤርትራዊ ተማሪ ትምህርቱን አራተኛ ክፍል ላይ ሲያጠናቅቅ ሊያውቃቸው የሚገቡ የሚባሉት እውቀቶች በጣም ውሱን ነበሩ። በአራት ነጥቦች ይጠቃለላሉ።

እነርሱም፣ "ጥሩ የኢጣሊያ ቋንቋ ችሎታ፣ መሰረታዊ የሂሳብ እውቀት፣ የንጽህና አጠባበቅና ኢጣሊያን ታላቅ ያደረጓትን ጀግኖች ታሪክ ማወቅ" ነበሩ። ኤርትራውያን ከዚህ ያለፈ እንዳያውቁ ቁጥጥር ይደረግ ነበር። በጠብቅ የተከለከለም ነበር።

አንድ ኤርትራዊ እነዚህንም እንዲያውቅ የተፈቀደው ለኢጣሊያውያን ምቾት አገልግሎት ይሰጥ ዘንድ ብቻ እንጂ ለራሱ ጥቅም አልነበረም። በታሪክ ትምህርት ላይ በኢጣሊያ ስለተከሰተው ቀደም ያለ የህዝብ አመጽ እንኳ አይነገራቸውም። ወጣቶች ስለ

ተደራጀ ህዝባዊ አመጽ ካወቁ በአርአያነት ሊወስዱት ይችላሉ የሚል ስጋት ነበር። በኢጣሊያና በአለም ታሪክ ውስጥ በቀላሉ የሚታወቁት የነሎምባርዲያ የአመጽ እንቅቃሴ እንኳ አይነሳም። ደራሲው ጆሴፍ ማዚኒና የማዚኒ ተከታይ የነበረው ዝነኛው ተዋጊ ጆሴፍ ጋሪባልዲ በታሪክ ትምህርት ላይ ስማቸው እንዳይጠቀስ ተለይቶ ታግዷል። ደራሲው ማዚኒ የኢጣሊያ ገበሬዎች ስለ "ብሄራዊ መብት" ማወቅ እንዳለባቸው ማስተማሩ ለኢጣልያን ተማሪዎች በሰፊው ይብራራል። ማዚኒ በኤርትራውያን ተማሪዎች ፊት ስሙ አይነሳም። በርግጥ የባለ ቀዩ ሸሚዝ የጋሪባልዲ የጀግንነት ታሪክ በተለያየ አጋጣሚ ይጠቀሳል። በዚህ ጊዜ ኤርትራውያን እንደ ጋሪባልዲ ለኢጣልያ የጀግንነት ተግባር እንዲፈጽሙ ይሰበካሉ። የአእምሮ አጠባ ስራ የሚፈጸመው ፍጹም የኢጣልያ አገልጋዮች ሆነው እንዲያድጉ ነበር።

ተማሪዎች ትምህርት ቤት ሄደው ክፍል ውስጥ ከሚማሩት ይልቅ በስፖርት የሚያሳልፉት ጊዜ ይበዛል። የመጪው ዘመን ወታደሮች ስለሚሆኑ የበለጠ የሚያስፈልጋቸው የአካል ጥንካሬ ነው ተብሎ ይታሰብ ነበር። ከዚያ ባሻገር ከተማሪዎቹ የሚጠበቀው ዋናው ነገር ዲሲፕሊን ማክበር ነው። ይህም ለነገው ውትድርና የሚደረግ ዝግጅት አካል ነው። ትምህርት በኢጣሊያ ቋንቋ ይሰጣል። አራተኛ ክፍል ላይ ትምህርታቸውን ጨርሰው ይመረቃሉ። በእነዚህ ትምህርት ቤቶች ለመግባትም የመሳፍንት ልጅ አሊያም የታዋቂ ሰው ልጅ መሆንን ይጠይቅ ነበር። የኤድሞንዶና የኤድዋርዶ ልጆች እስከ አራተኛ ክፍል ለመማር ከእድለኞች መካከል ነበሩ። ከዚያ በላይ ጥቂት መቀጠላቸው ደ'ሞ ከእድለኞች መካከል እድለኞች አድርጓቸዋል። አባቶቻቸው ግን የአባ ዮሃንስ ግርፍ ስለነበሩ ልጆቻቸው ያገኙትን ትምህርት እንደ ልዩ እድል ሊቆጥሩት አልቻሉም። ከህብረተሰብ ተነጥለው "ልዩ" የተባለው እድል ተጠቃሚ መሆናቸውም ምኞት የሚሰጥ አልነበረም። ይህም ቀስበቀስ ከስርአቱ ጋር ቅራኔ ውስጥ የሚከታቸው ሆነ።

* * *

በኤድዋርዶ ቤት ግብጣው ቀጠለ።

አዋቂዎች ባንድ ላይ ለገበታ ሲቀርቡ ልጆች ለብቻ በመሶብ ዙሪያ ከበቡ። ቪኖ ተከፈተ። አረቄና ጠላም በገፍ ቀረበ።

ያዕቆብ ከልጆቹ ጋር መጥቷል። ዋና እንግዶች ነበሩ። ልጆቹ አድገውለታል። እያሱ ከአንድ ወር በፊት በኢጣልያ ሚሊተሪ ኢንተሊጀንስ ውስጥ ሰልጥኖ ተመርቋል። ምድብ ቦታው ሞቅዲሾ መሆኑ ተነግሮት ለጉዞ የሚቀጥለውን መርከብ እየጠበቀ ነበር። የኑረነቢ እህት መርየም ካረፈች ሰባት አመታት ቢያልፍም ከአቦይ ተወልደ ቤተሰብ ጋር የፈጠረችው ግንኙነት ግን መቀጠል ችሏል።

በአጤ ምኒልክ ትእዛዝ የአድዋ ጦርነት ላይ አንድ እግር እና አንድ እጁን ያጣው ያዕቆብ ከኤድሞንዶ ጋር የገንፎ ማህበር መስርተው በወር አንድ ጊዜ በቀጣይነት በየተራ በየቤታቸው እየተገናኙ አብረው ይውላሉ። ያዕቆብ ሲያገባ ኤድሞንዶ ሚዜ ሆኗል። በእድሜ እኩያሞች የሆኑት ልጆቻቸው እያሱና ገብርኤል ልጅነታቸውን ተካፍለዋል። እያሱ በበለዛ ወንጌላውያን፤ ገብርኤል በከረን ካቶሊክ ሚስዮን በመማራቸው በእውቀትም ይቀራረባሉ።

ያዕቆብ በአካሉ መጉደል ምክንያት ከአባቱ የወረሰውን የግብርና ስራ ለማካሄድ መጀመሪያ ላይ በእጅጉ ተቸግሮ ነበር። መርየም የጎደለውን እየሞላች ሞራሉን እንዳይጥል የከፈለችውን መስዋእትነት ያዕቆብ ምንጊዜም አይረሳውም። ሙሉ አካል ካለው ሰው እኩል መስራት ይችል ዘንድ የኮሎኒው መንግስት ያደረገለት እንክብካቤም በህይወቱ ተስፋ እንዳይቆርጥ በእጅጉ አግዞታል። እርሻውን በዘመናዊ መንገድ እንዲያደራጅ ስልጠና እና የማስፋፊያ የብድር ገንዘብ ሰጥተውታል። የጓሮ አትክልት ምርቶችን ወደ ኢጣልያ እንዲልክና የተሻለ ገቢ አጊኝቶ እዳውን በአጭር ጊዜ ከፍሎ እንዲጨርስ አድርገውታል። ልጆቹ ከአራተኛ ክፍል በላይ እንዲማሩም ልዩ ፈቃድ ተሰጥቶታል። እያሱ በለዛ ከኢቫንጀሊካል ሚሽን ትምህርት ቤት ሲገባ ታናሾቹ የኮሎኒው መንግስት የሰጣቸውን እድል ተጠቀሙበት። እያሱ ትምህርቱን ከጨረሰ በሁዋላ ከኢንተሊጀንስ ክፍል በመመደቡ፤ ሮማ ሄዶ የስድስት ወራት ስልጠና ለማግኘት ችሏል።

ያዕቆብ እግርና እጁን እንዴት እንዳጣ ዝርዝሩን ለልጆቹ በተደጋጋሚ አውግቷል። እግርና እጁን ስለ ቆረጡበት ሰዎች

ጭራቂው ገጽታና ጭካኔ፣ አንድም ሳያስቀር ሁሉን ለልጆቹ ዘርዝሮ ከመናገር አልተቆጠበም። በቀሪ ሕይወቱም በንግግሮቹ መሃል የሸዋን ሰው መርገም እንደ ልማድ ያዘው። ግማሽ ቀን በፈጀው እጅና እግር የመቁረጥ ሂደት የሸዋ መሳፍንት እንደ መዝናኛ ትርኢት ቆመው ይመለከቱ እንደነበር፤ እጅና እግራቸው የሚቆረጡ ሰዎች በሚያሰሙት የስቃይ ድምጽ የሚስቁ ሰዎች እንደነበሩ ጭምር ለልጆቹ ተረከላቸው። እያሱ ከወተት ቀጥሎ በገፍ እየተመገበ ያደገው ይህንኑ የአባቱን የቁጭት ትረካ ነበር። በእግርና በእጅ ቆረጣው ወቅት አዝነው ስላገዟቸው የሸዋ ሰዎች ግን ያዕቆብ ለልጆቹ ነግሮ አያውቅም። ያዕቆብ የአድዋ ጦርነት ማግስት ትዝታውን አውግቶ ሲያበቃ ሸዋን በመርገም ንግግሩን ይቋጫል።

የኤድዋርዶ የምሳ ግብዣ ካበቃ በሁዋላ እንግዶቻቸውን አሰናብተው ሲያበቁ ሁለቱ የኑረነቢ ልጆች ወደ ያዕቆብ መኖሪያ ቤት ሄደው ለማምሸት ተስማሙ።

ያዕቆብ አትክልትና ፍራፍሬ እየጫነ ወደ ኮምቢሽታቶ የሚያመላልስባት ፊያት የመከካለኛ ጭነት መኪና ነበረችው። በሾፌር ይጠቀማል። በዚያን ምሽት በያዕቆብ አሮጌ መኪና ተሳፍረው ወደ ሰምበል ጉዞ ሆነ።

ከተማው በሰው በመጨናነቁ መንዳት አስቸጋሪ ነበር።

የቆርቆሮ አገልግል ያንጠለጠሉ የፋብሪካ ሰራተኞች ወደ ማደሪያቸው ይጣደፋሉ።፡ መኪኖች በሁለት ረድፍ ይፈሳሉ። ኮምቢሽታቶ መግባት አይቻልም። በዙሪያው የሚታየው የሰው አይነት ጉራማይሌ ነው። ጣልያኖች፣ ክልሶች፣ ጥቁሮች፣ ጠይሞች፣ አረብ ነጋዴዎች፣ ግሪኮችና አርመኖች፣ በተለያየ አለባበስ ይርመሰመሳሉ። የሚሰማው ቋንቋ እንደ ሰው መልክ ጉራማይሌ ነው። ከባቡር ጣቢያው አግጣጫ የሚነርፈው ሰው መንገዱን ሞልቶታል። ከከረን ወይም ከምጽዋ የተራገፉ ናቸው። ድብልቅ ነው። ለእረፍት የሚመለሱ ወታደሮችም ይታያሉ። ሸኚዎችና ተጓጉች ወደ ባቡር ጣቢያው ይገባሉ ይወጣሉ።

ኤድዋርዶ ብዙ አዳዲስ ነገሮች አየ።

በአምስት አመታት ውስጥ አስመራ ብዙ ተለወጠችበት።

የተጀመረው ህንጻ ማለቂያ የለውም። የሰው ብዛት በእጥፍ ጨምሯል። የምድር ባቡር፣ የአየር ባቡር፣ የመኪና ጎዳና፣ የእርሻ፣ የማእድን ፍለጋ እና ኢንዱስትሪ ግንባታዎች በስፋት ይጣደፋል። ከ1885 ከምጽዋ የጀመረው የባቡር መንገድ ግንባታ ስራ በፍጥነት እየገሰገሰ ወደ ምእራብ አቅንቷል። የብረት አገዳዎች ያለማቋረጥ ይገባሉ። ባቡሩ አስመራ መድረስ የቻለው በ1911 ነበር። ከምጽዋ ሲለካ 125 ኪሎ ሜትር ርዝመት ነበረው። ጊዜ ሳይሰጡ እያጣደፉ ቀጠሉት። አስመራን ከከረን የሚያገናኘው 104 ኪሊሜትር የባቡር ሃዲድ ዝርጋታ በ1922 ተጠናቀቀ። የአስመራ ከረን አቆርዳት መስመር በ1928 ይጠናቀቃል እየተባለ ነበር። ወደ ጋሽ ባርካ ስለሚዘረጋ የባቡር መስመር ቢወራም ገና አልተጀመረም። የባቡር መንገዱ ወደ ከሰላ ያመራል ተብሎም እየተጠበቀ ነበር።

ከሶርያ፣ ከሱዳን፣ ከየመን፣ ከኢትዮጵያ የጉልበት ሰራተኞች ወደ ኤርትራ እየጎረፉ ነበር። የተሰባጠሩ መንገዶች ማቋረጫ የላቸውም። ኤርትራ በጉልበት ሰራተኞች ተወራለች። ባቡር የሚቆምባቸው መንደሮች ወደ ከተማነት ተለወጡ። ነፋሲትና እምባትካላ የተባሉ መንደሮች ተወለዱ። ከጎዳይፍ እየተነሳ ወደ ምጽዋ የሚምዘገዘገው የአየር ላይ ባቡር እንደ ምድር ባቡሩ ጭስ የለውም። የሸቦ ገመድ ላይ ተንጠልጥሎ አስመራ ምጽዋ ይመላለሳል። በአለም ላይ ረጅሙ ቴሌፍሪካ ነበር። በባቡር ሲሆን 121 ኪሎሜትር የሚፈጀውን መንገድ ቴሊፍሪካ በ71 ኪሎሜትር ያጠናቅቀዋል። ከጎዳይፍ ተነስቶ ምጽዋ እስኪደርስ ሶስት ዋና ዋና ፌርማታዎች ነበሩት። እነርሱም ዓርበረቡዕ፣ እምባትካላ እና ሰሓጢ ነበሩ። በርግጥ ነፋሲት፣ ጊንዳዕ፣ ሰባርጉማ፣ ማይአጣል፣ ዶጋሊ፣ ኡምኩሉ፣ የተባሉትን መንደሮች ሲያቋርጥ ቴሌፍሪካ ለጥገና ወይም ለእረፍት ለአጭር ጊዜ መቆሙ አይቀርም።

ከተማና ከተማን የሚያገናኙ መንገዶችም እየተሰሩ ነበር። በዚህ የመንገድ ግንባታ ለመሳተፍ በሺህዎች ኢጣልያውያን የጉልበት ሰራተኞች በመርከብ ተጭነው ገብተው ኤርትራን አጨናንቀዋል። የቀን ሰራተኞች ቁጥር ከመቶ ሺህ በላይ አሻቅቧል። ከጎንደርና ከትግራይ የመጡ ኢትዮጵያውያንም ቁጥራቸው ትንሽ አልነበረም። የየመናውያን እና የሱዳናውያን ቁጥር ብቻ ከአስር ሺህ በላይ ነበር። በጥቅሉ ኢጣልያ ኢትዮጵያን ከመውረሯ በፊት የህንጻ ስራዎችን

ጨምሮ የግንባታ ስራ ለመስራት ኤርትራ የገቡ ኢጣልያውያን ቁጥራቸው ሃምሳ ሺህ ደርሶ ነበር። ኢጣልያውያን ኤርትራ ሲመጡ የሚከፈላቸው ደሞዝ የተሻለ ስለሚሆን ለገንዘቡ ሲሉ አንድ ቀላል ሻንጣ እያንጠለጠሉ ወደ ኤርትራ ለመጓዝ ሞተር የቀሰቀሰችው መርከብ ላይ እየተጋፉ የሚሳፈሩበት ዘመን ነበር።

መገናኛዎች የሰለጠነ ደረጃ ላይ ደረሱ። ከ500 ማይልስ በላይ የቴሌግራፍ መስመሮች ነበሩ። ፖስታ በየቤቱ ይታደላል። 25 ፖስታ ቤቶች፣ 67 የቴሌግራፍና 17 የቴሌፎን ጣቢያዎች ነበሩ። መደበኛ የአውሮፕላን በረራ አይቋረጥም። የአውሮፕላን ማረፊያዎችም ከአስመራ ሌላ ምጽዋ፣ አሰብ፣ ተሰነይና ጉራእ ላይ ተገንብተው አገልግሎት መስጠት ከጀመሩ ሰነበቱ። ደቀምሃረ ላይ በአንድ ጊዜ ሶስት ሺህ ከባድ መኪኖችን መጠገን የሚችል ጋራጅ ተገነባ። አስር ሺህ የጭነት መኪኖች፣ ዘጠና አውቶብሶች፣ 3500 ትናንሽ መኪኖች እና 350 ሞተር ብስክሌቶች ኤርትራን አጨናነቁ። በ1921 ነሓሴ 14 ምጽዋ በከባድ መሬት መንቀጥቀጥ ፈራርሳ ነበር። ኢጣልያውያን በጥቅሉ 50.9 ሚሊዮን ሊሬ ወጪ በማድረግ እንደገና ገነቧት። እድሳትም አካሄዱ። በርግጥ በዚህ ጊዜ አሰብ ተኝታ ነበር። ከወደብነት ይልቅ በእስር ቤትነት ነበር የምትታወቅ።

በጥቅሉ ኤርትራ ላይ የሚካሄደው የጥድፊያ ግንባታ ኢትዮጵያን ለመውረር የሚደረግ ዝግጅት አንድ አካል እንደነበር ለማንም ቢሆን ግልጽ ነበር።

በዚያን ቀን የኑረነቢ ልጆች ሰንበል ከያዕቆብ ጎጆ ሄደው በጀበና ቡና ዙሪያ ቁጭ አሉ። ቪኖ ተከፈተ። እና ኤርትራውያን በኢጣልያ የቅኝ ገዢ አስተዳደር የሚደርስባቸውን በደል እያነሱ መጨዋወት ጀመሩ። ቡናቸውን፣ ሃሜታቸውን፣ ቪኗቸውን አጣጥመው ሲያበቁም ያዕቆብ ወደ የቤታቸው ሸኛቸው። በርግጥ ከተማውን ሰንጥቀው ሲያልፉ በእግረመንገድ ፎቶ ለመነሳት ወደ አንድ ግሪካዊ ፎቶ ቤት ጎራ ብለው ነበር።

* * *

የኑረነቢ ልጆች እንደገና በአስመራ መሰባሰባቸው ቢያስደስታቸውም፤ ደስታቸው ብዙም አልዘለቀ። በጸጥታው ክፍል ክትትል ስር መውደቃቸውን ተገነዘቡ። አይን ውስጥ ለመግባት

የበቁት የገንፎ ማህበራቸውን በማስፋታቸው ብቻ ሳይሆን፤ በወርሃዊ ግንኙነታቸው ወቅት በተለይ ከትምህርት ጋር በተያያዘ የኢጣልያን የትምህርት ፖሊሲ እያነሱ በመወያየታቸው ምክንያት ሊሆን እንደሚችል ጠርጥረዋል።

እና ያልጠበቁት ዱብ እዳ መጣ።

ወንድማማቾቹ ከነ ቤተሰባቸው በጄኔራል ሮዶልፎ ግራዝያኒ አስተዳደር ስር ወደ ነበረችው ሶማሊያ - ኢጣልያ መቀየራቸውን የሚገልጽ ደብዳቤ ደረሳቸው። ዝውውሩ በግዞት እና በእስር መልክ እንዳይመስል አለቆቻቸው ተጠንቅቀው ነበር። በአመት አንድ ጊዜ ለእረፍት ወደ ኤርትራ መምጣት እንደሚችሉ ተነግሯቸዋል። የህክምና ጉዳይ ከገጠማቸውም በማንኛውም ጊዜ ወደ ኤርትራ መመለስ እንደሚችሉ በጽሁፍ ተገለጸላቸው ነበር።

ምእራፍ 3

ጊዜ እንደ ጎራዴ

ቀድሞ ይበላሃል - ካልያዝከው በዘዴ

ግንቦት 2 1935 ጀኔራል ግራዝያኒ ሮማ ከሚገኘው የበላይ አካል ጽህፈት ቤት አንድ ጥቅል አስቸኳይ ደብዳቤ ደረሰው። የደረሰውን ፖስታ መርምሮ ሲያበቃ ከመናደድ ይልቅ ተገረመ። በሚያየው ነገር በእጅጉ ተደነቀ።

አዲስ አበባ የሚገኘው የኢጣልያ ቆንስላ ከአጤ ሃይለስላሴ ቢሮ በስለላ ጥበብ መንትፎ በእጁ ያስገባው ጥብቅ ምስጢርና መረጃ ይሽው ሞቅዲሾ ከሚገኘው የጀኔራል ግራዝያኒ ጠረጴዛ ላይ ቁጭ ብሏል። አይኑን አፍጥጦ ሶስት ጊዜ አነበበው። ሮማ የሚገኙት አለቆቹ ከላኩለት ሰነድ ጋር የተያያዘው ማስታወሻ ብጥቱ ውስጥ የተሸሸጉ የአቢሲንያ ሰላዮችን እንዲፈትሽ ያሳስባል።

እንደ ጀኔራል ግራዝያኒ ላለ በራሱ የሚተማመን ከፍተኛ የጦር ጀኔራል እንዲህ ያለ ነገር ሲገጥመው ከሁሉም በላይ በሚንቃቸው አገልጋዮች መበለጡ አስገረመው። ኢጣልያ ያሳደገቻቸው ልጆች ጉያው ውስጥ ሆነው የኢጣልያን ምስጢሮች እየቀዱ ወደ አጤ ሃይለስላሴ ለመላክ ያስባሉ ብሎ መገመት ይቀርና ቢያስቡ እንኳ ያን ለመፈጸም አቅሙና ችሎታው ይኖራቸዋል ብሎ አይገምትም ነበር።

በተጨባጭ ግን ጠረጴዛው ላይ የተቀመጠው ሰነድ የኢጣልያን ምስጢሮች ሁሉ ዘክዝኮታል። ጽሁፉ ኢጣልያ ኢትዮጵያን ለመውረር ዝግጅት በማድረግ ላይ መሆኗን በዝርዝር ይተነትናል። በካርታ ጭምር የተደገፈው መረጃ ኢጣልያ በሶማሊያ ግንባር በሁለት አግጣጫዎች ምን ያህል ወታደሮችና ከባድ መሳሪያዎች እንዳከማቸች ያስረዳል። ካርታው ላይ በትክክል የኢጣልያ ጦር አቀማመጥ ምን እንደሚመስል ተመልክቷል። የጽሁፍ መረጃውም እንዲሁ ሁሉን በዝርዝር ይተነትናል። የሞቅዲሾን ብቻ አልነበረም። ኢጣልያ በአምስት አግጣጫዎች የወጊያ መሳሪያና ወታደሮችን እያከማቸች ስለሆነ ወረራውም በእነዚህ አምስት አግጣጫዎች ሊሆን እንደሚችል ግምቱን ያስቀምጣል። እነዚህም በሶማሊያ በሁለት ግንባር፤ በአሰብ አንድ ግንባር፤ በትግራይ ሁለት ግንባር ነበሩ። ይህም ካርታው ላይ በምልክት ጭምር ሰፍሯል።

ሰነዱ ብዙ ምክሮችን ለንጉሱ ሰርአት ልኳል።

ከእነዚህ መካከል፣ እንደ አድዋ ጦርነት በቀጥታ ኢጣልያን በወጊያ መግጠም ለኢትዮጵያ እንደማያዋጣት አሳብ ሰጥቷል። እንደ ጽሁፉ ትንተና ከሆነ የኢትዮጵያ ጦር የኢጣልያን ታንኮችና አይሮፕላኖች መቋቋም አይችልም። ኢትዮጵያን ለመውረር ዝግጅቱን ያጠናቀቀውን ግዙፍ ሃይል መቋቋም የሚቻለው በኮንቬንሽናል ውጊያ ሳይሆን በሽምቅ ውጊያ ሊሆን ይችላል። ሰላዩ ይህን አስተያየት የሰማው ከኢጣልያውያን የስራ ባልደረቦቹ መሆኑንም ሰነዱ ይጠቁማል። ኢትዮጵያ ሽምቅ ውጊያን እንደአማራጭ ከተጠቀመች ኢጣልያ አስቸጋሪ ፈተና ሊገጥማት እንደሚቸል የኢጣልያ የጦር አለቆች ስጋት እንዳላቸው ሰነዱ ያብራራል።

ኢጣልያ ፕሊን ጋዝ ልትጠቀም እንደምትችልም ሰነዱ ይጠቅሳል። ይህን የመርዝ ጋዝ ኢትዮጵያ ለመከላከል አቅሙ እንደሌላትም ያሳስባል። ስለ መርዝ ጋዙ ጠባይም ይተነትናል። ቆዳን ገሸላልጦ፣ መላ ሰውነትን አቁስሎ ለሞት እንደሚዳርግ መስማቱን ያብራራል። የመርዝ ጋዙ በመስታወት ቱቦ ውስጥ የታሸገ ፈሳሽ ሲሆን፤ ከአውሮፕላን ተወርውሮ መሬት ሲያርፍ መስታወቱ ይሰባበራል። ከውስጡም ቢጫ ቀለም ያለው የሚያቅለሸልሽ ሽታ አየሩ ውስጥ እንደ ጉም ይበተናል። የመርዝ ጋዙ በጠባዩ ወደ

ዝቅተኛ ቦታ እንደሚሄድ ጽሁፉ ያብራራል። ኢትዮጵያ የጎሪላ ታክቲክ ካልተጠቀመች በቀር እንዲህ ያለ ዝግጅት ካለው የኢጣልያ ሰራዊት ጋር ፊትለፊት መጋፈጥ እንደማያዋጣት በዝቅተኛ ደረጃ ላይ ያሉ የኢጣልያ ሹሞች ሲነጋገሩ መስማቱን ይገልጻል። በመደበኛው ውጊያ ኢትዮጵያ ከኢጣልያ ፊት ከአንድ ወር በላይ መቆም እንደማትችል እንደሚናገሩም የሰማውን ተንትኖ ጽፏል።

ለአጤ ሃይለስላሴ በተላከው በዚህ ሰነድ ላይ ከጀኔራል ግራዝያኒ ጀምሮ የዋና ዋና አዛዦች ስምና ማእረግ ሰፍሯል። በኤርትራውያን የተገነቡ ብርጌድና ባታሊዮኖች ብዛትና አሰላለፋቸውን ያሳያል። ኤርትራውያኑ ከኢትዮጵያ ጋር በሚደረገው ውጊያ የመሳተፍ ፍላጎታቸው ዝቅተኛ መሆኑን በመጠቆም፤ በታችኛው ማእረግ ላይ ከሚገኙ ኤርትራውያን የጦር መሪዎች ጋር ግንኙነት እንዲደረግ ሰነዱ ንጉሰነገስቱን ይመክራል።

ጀኔራል ግራዝያኒ አንብቦ ጨርሶ፤ የጻረ ስለላ ሹሞችን ሰብስቦ ጥብቅ መመሪያ ሲሰጥ ስሜታዊ አልነበረም። አጤ ሃይለስላሴ ጓዳው ውስጥ የተከለበትን ሰላይ ማነንነት ለማወቅ ግን ጓጓ። የሰላዩን አንገት ለማነቅ ብዙም እንደማይቸገር ግራዝያኒ አውቋል። ምክንያቱም የአጤ ሃይለስላሴ ሰላይ ምንም አንኳ ጠቃሚ የጽሁፍ መረጃ መላክ የቻለ ቢሆንም የዋህነት አጥቅቶታል። ከላከው ጽሁፍ መጨረሻ ላይ የስሙንና የአባቱን ስም የመጀመሪያ ፊደሎች በግእዝ አስቀምጧል። የስሙ የመጀመሪያ ፊደል “ገ” የሚል ሲሆን፤ ሁለተኛው ፊደል የተሞነጫጨረ ስለነበር የሚለይ አልነበረም።

የስሙ መጠሪያ “ገ” በሚል የሚጀምር አንድ ኤርትራዊ ሰላይ ጓዳቸው ውስጥ የሚገኝ ከሆነ ይህን ለማግኘት በቅድሚያ መደረግ የነበረበት ስማቸው በዚህ ፊደል የሚጀምረውን ሁሉ ከስም መዝገቦች ላይ መልቀም ነበር። የጻረ ስለላ ባልደረቦች ስማቸው በዚህ ፊደል የሚጀምረውን ለቅመው ለመጨረስ አንድ ሰአት እንኳ አልወሰደባቸውም።

ከተሰበሰቡት 23 ስሞች መካከል ማራገፍ ጀመሩ።

በመጀመሪያው ዙር ማጣሪያ ትምህርታቸው ዝቅተኛ ደረጃ ላይ ያሉትን ሰረዙ። መረጃ የማግኘት እድል የሌላቸውን ቀነሱ። እንዲህ እያጠበቡ በመጨረሻ ሁለት ሰዎች ላይ ቆሙ። ሁለቱም

ወጣቶች ናቸው። ከሁለቱ ወጣቶች የአንዱን አንገት ለማነቅ አጭር የጠባይና የእንቅስቃሴ ጥናት እንዲያደርጉለት አዝዞ ጀኔራል ግራዝያኒ ስብሰባውን በተነ።

የጸረ ስለላ ስራ ባልደረቦች የታዘዙትን አጥንተው ሲያበቁ፤ የመጀመሪያው ተጠርጣሪ ገብረማርያም ቴዎድሮስ ሆኖ ተገኘ። በሁለተኛ ደረጃ ገብርኤል ኤድሞንዶን በተጠርጣሪነት አስቀመጡ። በርግጥ የሁለቱን ወጣቶች ፋይል ሲመረምሩ አንዱን ለመምረጥ ተቸግረው ነበር። ገብረማርያም ቴዎድሮስን የመጀመሪያ ተጠርጣሪ ለማድረግ የወሰኑት በአመለካከቱ ከገብርኤል ይበልጥ የሚያስጠረጥረው ነገር አጊኝተው ሳይሆን፤ ገብርኤል ኤድሞንዶ በትሁት ጠባዩ ምክንያት ታማኝ የመሆን እድሉ ስላመዘነባቸው ነበር። በአንጻሩ ገብረማርያም አፈንጋጭ በመሆኑ የእርሳሳቸውን ጫፍ ቀሰሩበት።

ጀኔራል ግራዝያኒ የቀረበለትን ሪፖርት ካነበበ በሁዋላ ገብረማርያም ተይዞ በጥብቅ እንዲመረመር፤ ገብርኤል በአይነቁራኛ እንዲጠበቅ አዘዘ። በተያያዘም የሁለቱ ግለሰቦች የሁዋላ ታሪካቸው እንዲፈተሽ መመሪያ ሰጠ።

በሶስተኛው እለት አርብ ምሽት አምስት ካራቢኔሪዎች ገብረማርያምን በቁጥጥር ስር ለማዋል ወደ መኖሪያ ቤቱ ገሰገሱ። ቤቱ ግን አላገኙትም። ሁለት ካራቢኔሪዎችን ከመኖሪያ ቤቱ አስቀምጠው ሶስቱ ሞቅዲሾን ለማሰስ ወደ ከተማው ተሰማሩ። በቅድሚያ ያመሩት ወደ ኤርትራውያን ማምሻ ክለቦች ነበር። ከአንዱ ክለብ ወደ ሌላው እየተዘዋወሩ ገብረማርያምን መፈለግ ቀጠሉ።

* * *

ገብረማርያም በዚያን ምሽት ከእስጢፋኖስ መኖሪያ ቤት ነበር ያመሸው። የተለመደ የሙዚቃ፣ የመጠጥና የውይይት ሳምንታዊ ፕሮግራም ነበራቸው። በምሽቱ ፕሮግራም ላይ ከእስጢፋኖስና ከገብረማርያም ሌላ መሐመድ አሕመድ፣ ዘርኢ መብርሃቱ፣ መዝገበ መኮንን፣ ፍካሬ መኮንን እና ፍጡር አብርሃም ተገኝተው ነበር። ቪኖ፣ ኮኛክና ቬርሙጥ የምግብ ጠረጴዛው ላይ ወርዷል። የእለቱ የመወያያ ርእሰ ጉዳያቸው ኢጣልያ ኢትዮጵያን ለመውረር

የምታደርገው ዝግጅት ጉዳይ ነበር።

እስጢፋኖስ አንድ የካርቱን ስእል አውጥቶ አሳያቸው። አንበሳ አሞራን በጥፍሩ ይዞ በጥርሱ ሲቦጫጭቀው የሚያሳይ ነበር። በአንበሳ የተመሰለው ኢትዮጵያ ሲሆን፤ በአሞራ የተመሰለው ኢጣልያ ነበር። ኢትዮጵያ በአንበሳ የተመሰለችው ንጉሰነገስቱ ራሱን ሞአ አንበሳ ስለሚል አልነበረም። በአድዋ ጦርነት ኢትዮጵያ በኢጣልያ ላይ ያገኘችውን ድል በማስታወስ ነበር። ኢጣልያ በአሞራ መመሰሉ የመንግስቱ አርማ አሞራ በመሆኑና በዚያን ወቅት ኢጣልያ የውጊያ አይሮፕላኖች በመታጠቋ ምክንያት የበላይነት ይሰማት ስለነበር ነበር። ፍጡር ዘወትር እንደሚያደርገው ብሶቱን ተነፈሰ፣

“ዋናው ጥያቄ ‘አሞራውና አንበሳው ሲጋጩ እኛ በመካከሉ ምንድነን?’ የሚለው ነው። ቁራ ወይስ ቀበሮ? ድምቢጥ ወይስ ሸለምጥማጥ? ምን እንባላለን? ምን ማድረግ አለብን? ምን ማድረግ እንችላለን? ምን ማድረግ አንችልም? ዋናው ጥያቄ ይሄ ነው። መሰዋት ካለብን ለማን ጥቅም ነው መሰዋት ያለብን?”

የሞቀ ውይይት ቀጠለ።

“አንበሳው አሞራውን በጥፍሩ ለመያዝ ከበቃ እንደሚቦጫጭቀው አያጠራጥርም።” ፍካሬ መኮንን ተፈላሰፈ፣ “....ዳሩ ግን አሞራው አንበሳው ጥፍር ውስጥ ምን ሊሆን ይገባል? ከሰማይ እያንጣበበ አናት አናቱን በመንቆሩ መኮርኮም ይበቃዋል። ምሳሌ ልስጣችሁ። ቢንቢ የአንበሳን አይን ታስለቅሳለች።”

መዝገበ መኮንን የወንድሙን አሳብ ተቃወመ፣

“በአድዋ ጦርነት ኢትዮጵያና ጣልያን ተመሳሳይ ትጥቅ ነበራቸው። 25 አመታት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ልዩነታቸውን ተመልከቱ። ኢትዮጵያ ያረጀች አንበሳ። ኢጣልያ ወጣት ጭልፊት። አቢሲንያ የኢጣልያን ታንኮች እንዴት ትከላከላለች?”

“ስለእኛ እንነጋገር?” ሲል ገብረማርያም አቋረጠ፣ “...ፍጡር የጠየቀው ተገቢ ጥያቄ ነው። እኛ ምንድነን? ቁራ ነን ወይስ አይጥ? የት ላይ ነው የቆምነው? እውቀትና ጀግንነት ሳያንሰን የጦር መኮንን ደረጃ ያልተፈቀደልን አስካሪዎች? ኢጣልያ ስትሰቅ የምንሰቅ፤ የራሳችንን ሳቅ፤ የራሳችንን ንዴት የተነጠቅን! እኛ ምንድነን? ማነን?

ጥይት ማብረጃ? ኢጣልያኖችስ? ከአምላክ በታች - ገዢዎቻችን?"

ያደጉበት እንደመሆኑ ብዙውን ጊዜ ግራማፎኑን ከፍተው በኢጣልያ የወቅቱ ዘመናዊ ሙዚቃዎች ነበር የሚዝናኑት። አልፎ አልፎ ግን ክራር እያነሱ የትግርኛና የሱዳን አረብኛ ሙዚቃዎችን በመጫወት በትዝታ ወደ ኤርትራ ይነጉዳሉ። ኢጣልያ ኢትዮጵያን ለመውረር ማሰቧ ከታወቀ ወዲህ ግን ጠቅላላውን የኢጣልያ ሽክላዎቻቸውን አስወግደው ነበር።

* * *

ገብረማርያም ቴዎድሮስ ከእስጢፋኖስ መኖሪያ ቤት አምሽቶ ሲያበቃ፤ Duke of Abruzzi,s ወደሚገኝ መኖሪያ ቤቱ የሄደው ከእኩለ ሌሊት በፊት ነበር። ከቤቱ ደጃፍ ደርሶ የበሩን ቁልፍ ሊከፍት ሲል ከጀርባው ጥላ ከበደው። ዞሮ ሲመለከት ካራቢነሪዎች መሆናቸውን በጨለማው ውስጥ ለያቸው። ቢደነግጥም በቅጽበት ራሱን አረጋጋ፣

"ጓደኞች! ችግር አለ?" ሲል ጠየቀ።

ሁለት እጆቹን በሰንሰለት ካሰሩ በሁዋላ የቤቱን በር በርግደው በመግባት ፍተሻ ጀመሩ። ሳጥኖቹን፣ ሻንጣዎቹን ፈተሹ። መጽሃፍቶቹን ሰበሰቡ። የተጠራቀሙ ደብዳቤዎችን ወሰዱ። ፍተሻው በዚህ መልኩ ከተከናወነ በሁዋላ የያዙትን ይዘው ገብረማርያምን አስረው ወደ ልዩ የምርመራ ቢሮ ከነፉ።

በዚያኑ ሌሊት የገብርኤል የጀርባ ታሪክ ሲፈተሽ አጠራጣሪ ነገሮች ተገኙ። በነጋታው ቅዳሜ ማለዳ ገብርኤል ኤድሞንዶን በተመለከተ ለጄኔራል ግራዝያኒ ሪፖርት ቀረበለት።

- በሪፖርቱ የኑረነቢና የአባ ዮሃንስ ስም ተጠቅሷል። አያቱ ኑረነቢ በኺት በኢጣልያ ቅኝ ገዢ መንግስት ላይ ለአስር አመታት ሸፍቶ ነበር። አባቱና አጎቱ በአባ ዮሃንስ እጅ ያደጉ ናቸው። ሁለቱ ወንድማማቾች "ኤድሞ" እና "አድዋር" የሚል ስም የተሰጣቸው በላዛሪስት ካቶሊክ ሚስዮናውያን ሲሆን፤ ሁዋላ በስራ አለም ከገቡ በሁዋላ ስማቸው "ኤድሞንዶ" እና "ኤድዋርዶ" ተብሎ ተመዝግቧል። የገብርኤል አጎት ኤድዋርዶ በሊቢያ መልካም ስምና

ዝና አትርፏል። አባቱ ወደ ሞቅዲሾ ከመምጣቱ በፊት በኢጣልያ የፖስታ አገልግሎት ሰርቷል። ወንድማማቾቹ ወደ ሞቅዲሾ የተዛወሩት የተቃውሞ ዝንባሌ በማሳየታቸው በቅጣት መልክ ነው -

ሪፖርቱ ሲቀጥል እንዲህ ይላል።

- ወንድማማቾቹ የፖለቲካ ዝንባሌ ያሳያሉ። ምንም እንኳ ለኮሎኒው መንግስት ታማኝ ቢሆኑም በኮሎኒው ፖሊሲ ላይ ያላቸውን ቅሬታ ይናገራሉ። ሁለቱ ወንድማማቾች በሊቢያም ሆነ በአስመራ ቆይታቸው ህግ በመጣስ ወንጀል ተከሰው አያውቁም። ለህብረተሰቡ መጥፎ አርአያ ሊሆን የሚችል አመለካከት ግን ነበራቸው። በስራ አለም ሳሉ ያደረጉት ጥሩ አስተዋጽኦ ታይቶላቸው ቅጣት መሆኑ ሳይገለጽላቸው ወደ ሞቅዲሾ እንዲዛወሩ በጸጥታው ክፍል ተወሰኗል። ገብርኤል ኤድሞንዶ ወደ ሞቅዲሾ ከመምጣቱ በፊት በፖለቲካው ክፍል አስተርጓሚነት አገልግሏል። በሞቅዲሾ በአውቶግሩፖ መስሪያ ቤት ቆይታው በስራው የተመሰገነ ነው። ባለትዳር ነው። ባለቤቱ ሉላ እዮስአብ የተባለች የአዶምዘማት ሴት ናት። እድገቷ ግን ድባርዋ ነው። ወንድ ልጅ ወልደው ነበር። በህጻንነቱ በህመም ሞቷል -

ጀኔራል ግራዝያኒ ሪፖርቱን አንብቦ ሲያበቃ "የኑረነቢ ማህደር" ከኤርትራ ባስቸኳይ ወደ ሞቅዲሾ እንዲመጣ፤ ገብርኤል ኤድሞንዶም ተይዞ በጥብቅ እንዲመረመር አዘዘ።

* * *

ቅዳሜ ምሽት በአብዛኛው ኤርትራውያን ሲቪል ሰራተኞች አስመሮም ሰለሙን በተባለ ሰው ሰርግ ላይ ነበሩ። ከገብረማርያም ቴዎድሮስ በቀር ሰርጉ ላይ ያልተገኘ ኤርትራዊ አልነበረም። ከአንድ ቀን በፊት ካራቢኔሪዎች ገብረማርያምን ከመኖሪያ ቤቱ አፍነው እንደወሰዱት የሰማ አልነበረም። በሰርጉ ላይ አለመገኘቱንም ቢሆን ማንም አላስተዋለ።

በዚያን ቀን የገብርኤል ሚስት ሉላ እዮስአብ ደስተኛ ነበረች። ሞቅዲሾ ከመጣች ወዲህ ሰርግ ላይ ስትገኝ ይህ ሶስተኛዋ ነበር። አምሮባታል። እጅና እግሯ በሂና አጊጧል። ጠጉሯን ተሰርታለች። ከሳምንት በፊት ከአስመራ በተላከላት ጥበብ ልብስ

አጊጣለች። የወተት አረፋ በሚመስለው ጥበብ ላይ በቀይ የተነደፈው ጌጥ የልጃገረድ ፈገግታ ይመስላል።

ገብርኤል ኤድሞንዶ እና እያሱ ያዕቆብ ገና ከመገናኘታቸው በአሳብና በአመለካከት መጋጨት ጀመሩ። ገብርኤል ትከሻውን ይዞ ትህትና ሳያጎድል፤ ግን ደ'ሞ አጠንክሮ እንዲህ አለው፣

"በወንድምነቴ ልምከርህ! ምኒልክ አባትህ ላይ በፈጸመው የግፍ ድርጊት ሸዋ ላይ ቂም ይዘሃል። ሌላ ምክንያት ያለህ አይመስለኝም። ለዚህ የበቀል ፍላጎትህ ፖለቲካዊ ሽፋን እየሰጠኸው ይመስለኛል። ቂምና በቀል ግን መልሶ አንተኑ ይጎዳሃል።"

በዚህ ንግግር እያሱ አውሬ ሆነ።

"ሰርግ ቤት ባንሆን በቡጢ ላይንህን አጠፋው ነበር። ሲበዛ ደፋር ነህ። እንኳን አንተ እኔ እንኳ ስለራሴ በትክክል አላውቅም። ስለኔ የልብ አሳብ ለመናገር እንዴት እንዲህ ደፈርክ?"

ገብርኤል ሳቀ።

ስለለመደው በእያሱ አነጋገር አልተደነቀም። አብሮ አደግ ናቸው። የስጋ ዝምድና ባይኖራቸውም የቤተሰብ ያህል ናቸው። በአመለካከት ግን አንድም ቀን ተግባብተው አያውቁም። አንድም ቀን ሳይጣሉ በሰላም ተለያይተው አያውቁም። ችግሩ የገብርኤል ነው። ሲናገር ለነገ አይልም። እንደ ፊጋ በሬ ጠብ ለሚያምረው እያሱ ደግሞ የገብርኤል ንግግር ከሚሸከመው በላይ ይሆንበታል።

ገብርኤል ረገብ ብሎ እንዲህ አለው፣

"ለቃላቶቼ ይቅርታ። ወንድሜ ስለሆንክ የሚሰማኝን ብነግርህ ይሻላል ብዬ ነው። ታውቀኛለህ ብዬ ነው። ለማንኛውም ግራዝያኒን ተጠንቀቀው።"

"ምን እንዳያደርገኝ ነው የምጠነቀቀው?"

"ላንተ ያለው አድናቆት የተለመደ አይደለም።"

"ምን ማለትህ ነው?"

"የኢጣልያ አለቆች ሲያደንቁህ ለጥቅማቸው ነው።"

"ፑፍ!" አለና ሲጋራ ለኮሰ።

የሰርግ ዘፈን በከበሮና በማሲንቆ እየቀለጠ ነበር።

እያሱ በስሜት መናገሩን ቀጠለ፣

“ጣልያን ኢትዮጵያን የመውረር አሳቧን ብትተው የኛ እጣ ምን የሚሆን ይመስልሃል? አርጅተን እንደ ውሻ እስከምንጣል የኢጣልያ አሽከር ሆኖ መቀጠል። ሌላ ምን ማድረግ እንችላለን? ከቁጥራችን ማነስ አንጻር ምንም ልናደርግ አንችልም። ሰባ ሺህ ኢጣልያውያን ጀርባችን ላይ ሰፍረዋል። ኢኮኖሚው የነሱ ነው። አልተማርንም። ጣልያን ኢትዮጵያን ከያዘች ግን ነጻነት የማግኘት ተስፋ እንደሚኖረን እንዴት ማየት አትችልም?”

ገብርኤል መደነቅ አደረበት፣

“በኢትዮጵያ ኪሳራ ነጻነት እየተመኘህ ነው?”

“አቢሲንያ በነጻነት የቆየችው በኤርትራ ኪሳራ ነው።”

“አትሳሳት። ምኒልክ በወቅቱ ኤርትራን ለኢጣልያ የመሸጥ አቅም አልነበረውም። ባለቀ ነገር ላይ ነው የፈረመው። መረብ ምላሽን እንደ ራሱ ግዛት አስቦም አያውቅም። ምኒልክ ምድሪ ባሕሪ ግዛቴ ነው ብሎ ቢያስብ ኖሮ አይፈርምም ነበር። አክሱም መነሻችን ነው ብለው ስለሚያምኑ አይደራደሩም። በተቀረ አክሱምን እስካልነኩበት ድረስ የምኒልክ ልብ ወደ ምእራብና ወደ ደቡብ ነበር። ሳንማርኮ አሁን አንተ የምትናገረውን አይነት ነገር ለኤርትራውያን እንደሚናገር ሰምቻለሁ። በሱ አመለካከት ታጥበሃል። ተራ ብልጠት ነው። እውነት አይደለም። ይህን መቀበል የዋህነት ነው። ለአነጋገሬ ይቅርታ፤ ላታልልህ አልፈልግም። አሁንም ቢሆን በቂም እየተነዳህ ይመስለኛል።”

የአባቱ ጉዳይ በድጋሚ ሲነሳበት እያሱ እንደገና ነደደ፣

“መነሻዬ እሱ አይደለም ብዬሃለሁ። አትድገምብኝ። እሱም ቢሆን ግን ተራ ነገር አይደለም። በደልን መመለስ ባህላችን ነው።”

“ምኒልክና መንገሻ በህይወት የሉም። ማን ላይ ነው ዱላ የምታሳርፈው? ዱላ ካለህ ማለቴ ነው?”

“ምኒልክ የተከለው ስርአት አለ።”

“አንተ ምንም የምትጨምረውና የምትቀንሰው ነገር የለም። ኢጣልያ የመርዝ ጋዝ አከማችታለች። ይህን ታውቃለህ። ኢትዮጵያውያንን ጨርሰው ሊፈጁ ተዘጋጅተዋል። እንደ አንተ አባት ያሉ ንጹህ ገበሬዎችን ሊፈጁ ወስነዋል። እኛ አገልጋይ ብቻ ነን። ራስህን አታታልል። ከተቻለ የሚሻለው ገለል ማለት ነው።”

“ወዴት ነው ገለል የምለው?”

“እሱን አላውቅም። ብቻ ጥላቻህ መልሶ አንተኑ ነው የሚጎዳህ። አሳብህ ብቀላ ከሆነ ደግሜ የምነግርህ አባትህ ላይ ያን የመሰለ ጭካኔ እንዲፈጸም ያዘዙት ሰዎች አሁን በህይወት አለመኖራቸውን ነው። ስርአቱ ላልከው ሙሶሊኒ ከተሳካለት ያስወግዳቸዋል። የኛ ሚና ከአጫፋሪነት አያልፍም።”

እያሱ አከርሮ ተቃወመ፣

“ብቀላ የለብኝም። ከአባቴ ጋር የሚያያዝ ነገር አይደለም። ሰብአዊነት የሌለው ስርአት መፍረስ አለበት። አላማዬ ሰው መግደል አይደለም። የኔ ጸብ ከግለሰብ ጋር አይደለም፤ ከስርአቱ ጋር ነው።”

“ለኢትዮጵያ ህዝብ በጎ እየተመኘህ ነው?” ብሎ ሳቀ።

በገብርኤል ሽሙጥ እያሱ እንደገና ተናደደ።

“ምኒልክ ምናባቱ አግብቶት ስለኛ ፈረመ?”

“ምኒልክ እኛን ለመሸጥ አልፈረመም።” አለ አከርሮ፣ “.... ወደ ሸዋ እንዳይመጡበት አጥር አጠረ። በቃ። ሌላ የሆነ ነገር የለም። የሆነው ሆኖ ግራዝያኒ ሰብአዊነትን ወደ ኢትዮጵያ ጭኖ እንደሚጓዝ እየነገርከኝ ነው?”

“ከባሪያ ፈንጋይ ስርአት ለህዝቡ ጣልያን ይሻለዋል።”

“ያንተ ነገር አይገባኝም።” አለ ገብርኤል በመንገፍገፍ፣ “...አቋምህ ምን እንደሆነ እንኳ መረዳት አልቻልኩም።”

እያሱ ሲናገረው የቆየውን መልሶ በሌላ ቃላት ሊያስረዳው ጥረት አደረገ። በተቻለው መጠንም ረጋ ሊል ሞከረ፣

“እኛ ብቻችንን ኢጣልያን ከኤርትራ ለማስወገድ ለጊዜው አንችልም። ረጅም ጊዜ ይፈጅብናል። ኢትዮጵያውያን በኢጣልያ ስር

ከገቡ ግን ሃይል እናገኛለን። ስለዚህ ኢጣሊያ ኢትዮጵያን እንድትቆጣጠር እደግፋለሁ። በመጨረሻ ከእለታት አንድ ማለዳ ትልቅ አገር ሆነን ጣልያንን በቀላሉ እናባርራለን።"

ገብርኤል በመደነቅ ሲያየው፣ እያሱ ቀጠለ፣

"የአቢሲንያ ደደብ ፊውዳላዊ ስርአት መደምሰስ አለበት። በአካባቢያችን ስልጣኔ በግድ ደማችን ውስጥ መግባት አለበት። የሸዋ መኳንንት እኛን ሰውተው በሰላም ለመኖር ተመኝተው ነበር። ሊሆን አይችልም። ያልሰለጠነ ደደብ ስርአት ቀርቶ ..."

ገብርኤል እንደገና አይኖቹን ጎልጉሎ አፈጠጠበት፣

"ሁዋላ የምትጸጸትበትን ተግባር እንዳትፈጽም ተጠንቀቅ። የቅኝ ገዢ አገልጋይ ሆነህ ሳለ የራስህ አቋም ሊኖርህ አይችልም። እነዚህ ሰዎች ተጫውተውብሃል። አእምሮህን ማርከውታል። የአንተ አቋም ኢጣልያን ስለሚጠቅም ከማንም በላይ አቅርበውሃል። ከመነሻው መኳንንቱ እኛን ለመሸጥና ለመለወጥ አቅሙ እንዳልነበራቸው ነግሬሃለሁ። ለህልውናቸው ሲታገሉ ነው የኖሩት።"

እያሱ አተኩሮ ገብርኤልን እያጤነ እንዲህ አለ፣

"ግራዝያኒን እየተጠቀምኩበት ከሆነስ?"

ገብርኤል ለመጀመሪያ ጊዜ በጣም ተናደደ።

"እባክህ ራስህን አታታልል። ተራ ግለሰብ ነህ። ግራዝያኒን ልትጠቀምበት የሚያስችል ብቃትና ድርጅት የለህም።"

እያሱ ከገብርኤል በላይ በጣም ተናደደ። ለመናደድ የሚፎከካሩ መሰሉ። አፍንጫቸው እንደ ክብሪት ጨሰች።

"ድርጅት ባይኖረኝስ? ዋጋ ያለው አሳብ ማሰብ አልችልም? አርቆ ማየት የሚችል አንጎል አለኝ። አፍንጫህ ስር የምታስበው አንተ ነህ። አስተሳሰብህ ለረጅም ጊዜ የኢጣልያ አሽከር ሆነን እንድንቆይ የሚያደርግ ነው።"

ገብርኤል ቀዝቀዝ አለና አሰበ።

ረጋ ብሎ ሲያስብ የእያሱ እምነት ባዶ ሆኖ አልታየውም፣

"በርግጥ ኢትዮጵያውያን መወረራቸው የኛን ነጻነት

ያቃርበዋል ማለትህ እውነት ሊሆን ይችላል። በዚህ መንገድ አስቤው አላውቅም። ምናልባት የኢትዮጵያ መወረር ለኢጣልያውያን አካባቢያዊ ውድቀት የሚያስከትል ከሆነ ማለት ነው። የኢጣልያን ወረራ መደገፍ ግን መፍትሄ አይደለም።"

እያሱ ቡጢ ጨብጦ ተናገረ፣

"አካባቢው ሁሉ መደፍረስ አለበት። ስለ መደራጀት የገለጽከው ነገር አለ። አሁን ባይኖረኝም፤ ወደፊት ድርጅት ይኖረኛል፤ አትጠራጠር። ብዙ ባንሆንም የኔን አስተሳሰብ የሚጋሩ ጓደኞች አሉኝ። የመጀመሪያ ግባችን ኢጣሊያ ኢትዮጵያን እንድትቆጣጠር ማገዝ ነው። አንጎል ካለህ ከኛ ጋር ተባበር።"

ገብርኤል ግብጣውን ችላ ብሎ ጥያቄውን ቀጠለ፣

"እንዳሰባችሁት ካልሆነስ?"

"ይሆናል። ኢጣልያ ኢትዮጵያን መቆጣጠር ትችላለች። አገሩን አንዴ ከያዘች ሃያ ወይም ሰላሳ አመታት ይዛ ትቆያለች። በዚህ ጊዜ ውስጥ የአቢሲንያን ፊውዳሎች ጠርጋ ታጠፋለች። በሂደት የአካባቢው ህዝቦች አንድ አካባቢያዊ ማንነት ፈጥረን ለነጻነት መቋቋም አያቅተንም። ያን ጊዜ ኢጣልያ ራሷ ባንዴራዋን ነቅላ በመጣችበት መርከብ ተመልሳ ወደ አገሯ ትሄዳለች።"

ገብርኤል እንደ ተኮረኮረ ሰው ሳቀ፣

"ከፋፍሎ ይገዛሃል እንጂ ምን ይሁን ብሎ ነው አንድ አካባቢያዊ ማንነት እንዲፈጠር እድል የሚሰጥህ?"

"ኤርትራን ለምን አልከፋፈሏትም?"

"ግማሽ ሚሊዮን የማንሞላ ህዝብ አናሰጋውም ነበር። ሳይከፋፍሉን በቀላሉ ሊቆጣጠሩን እንደሚችሉ ያውቁ ነበር። ያም ሆኖ በሃይማኖት አልከፋፈሉንም ማለት አትችልም። አቢሲንያ ላይ ተመሳሳይ ቀመር ሊጠቀሙ አይችሉም። የኢጣልያን መርዛማ ተንኮል የተረዳኸው አይመስለኝም።"

እያሱ በትእዝብት መልክ እንዲህ አለ፣

"እኔን ቂመኛ ትላለህ። አንተ ራስህ ጣልያን ላይ ቂም

ይዘሃል። የአያቶችህን መንገድ እየተከተልክ ነው። ጣልያን ከነሙሉ ችግሮቹ ለኛ መጥፎ አይደለም። የሁላችንም ቅሬታ የታወቀ ነው። የትምህርት ፖሊሲው መቀየር አለበት። የነጭና የጥቁር ጋብቻ በመከልከላቸው ግን ደግ አደረጉ። በዚህ አዋጅ ተጠቃሚዎቹ እኛ ነን። ክልስ የሚባል አንድ አስቸጋሪ ማንነት ኤርትራ ላይ እንዲፈጠር ማናችንም አንፈልግም።"

"ቆንጽለህ አትሞግተኝ። ተቃውሟችን በአጠቃላይ ዘረኛ ፖሊሲያቸው ላይ ነው። ዋናው ጥያቄ የነጻነት...."

በድንገት ወደ ሰርጉ ድንኳን ሁለት ኢጣልያውያን ካራቢኔሪዎች ገቡ። በአይናቸው ሰው ሲፈልጉ ታዩ። እድምተኛውን በአይናቸው እየፈተሹ ጥቂት ከቆዩ በሁዋላ ከዳሱ ሁዋላ አካባቢ ከተቀመጡ እንግዶች መካከል የሚፈልጉትን ሰው አገኙ። አንደኛው ካራቢኔሪ በቀጥታ ሄደና ከሁዋላ በኩል የገብርኤል ትከሻ ነካ አደረገ።

ገብርኤል ዘወር ብሎ ሲመለከት ካራቢኔሪው "ተከተለኝ!?" ሲል በምልክት ነገረው። ገብርኤል ገጽታው ላይ ድንጋጤ እየታየበት ወደ ባለቤቱ ጆሮ ጠጋ ብሎ፣ "በካራቢኔሪዎች መወሰዴን ዛሬውኑ ለጳጋይ ንጉሴ ንገሪው።" ሲል ሹክ አላት። ከዚያም ቆሞ በጥንቃቄ በአይኑ የሚቆጣጠረውን ፖሊስ ተከትሎ ከዳሱ ወጣ። እያሱም ገብርኤልን ተከትሎ ወጣ።

"ምን ችግር ተፈጠረ?" ሲል ገብርኤል ጠየቀ።

"አናውቅም።" አሉት።

እያሱም ካራቢኔሪዎቹን ተመሳሳይ ጥያቄ ጠየቀ። እነርሱም ምንም እንደማያውቁ ተመሳሳይ ምላሽ ሰጡት። እያሱ ወደ ገብርኤል ዞሮ አጥብቆ ጠየቀው፣

"የምታውቀው ጉዳይ አለ?"

"እንጃ! አላውቅም።" ሲል በተረበሸ ሁኔታ መለሰለት።

ደጃፉ ላይ የፖሊስ መኪና ቆማ ነበር። መኪና ውስጥ ካስገቡት በሁዋላ እጁን በሰንሰለት አሰሩት። እና መኪናዋ ወደ ገብርኤል መኖሪያ ቤት ገሰገሰች።

ምእራፍ 4

ፋሺስት ኢጣልያ – ብዙ አትደነቂ
እኔም ወገን አለኝ – ባራኪ መራቂ

በግርማዊ ንጉስ ቪቶሪዮ አማኑኤል ሶስተኛ፤ በእግዚአብሄር ቸርነት በህዝቡ ፍላጎት፤ በኢጣልያ ንጉስ ስም፤ በሞቅዲሾ የኢጣልያ ቅኝ ግዛት የጦር ፍርድ ቤት 14 ኤርትራውያንን በስለላ ወንጀል ከስሶ ፍርድ ቤት አቀረበ። ደንቡ በሚያዘው መሰረትም አምስት ዳኞች ተሰየሙ።

ኮሎኔል ማርቶረሌ ኮማንዳቶረ ፋቢዮ ፕሬዚዳንት ሲሆን፤ አራቱ ሌሎች ፈራጆች ካፒቴን ቺያንቶ አቮካት ፊድሪኮ፣ ሌተና ኮሎኔል ማንዶ ካቫሌር አሪጎ፣ ሜጀር ፋቨዘ ካቫሊዬር ቪንቸንሶ እና ካፒቴን ሎ ኩዎኮ ሳንማርኮ ነበሩ።

ቀዳሚው ተከሳሽ ስሙ ተጠራ።

Gabriele Edmondo Gabramdin fu Edmondo, nato ad Asmara il 27 Dicemeber 1910 …..domiciliato a Mogadiscio ….. impiegato presso 1’ Autogruppo della Somalia Italiana……

ገብርኤል ኤድሞንዶ ገብረመድህን ከአባቱ ከኤድሞንዶ ገብረመድህንና ከእናቱ ከተዋበሽ ገብራይ ታህሳስ 27 በ1910 አስመራ ከተማ ተወለደ። በአባቱ ሓልሓል ቦጎስ፤ በእናቱ ድባርዋ ነው።

አድራሻው ሞቅዲሾ ሲሆን፤ በኢጣልያ ሚሊታሪ ውስጥ የአውቶግሩፖ ክፍል ሰራተኛ። (እስረኛ።)

ሁለተኛ ተከሳሽ፡

መስፍን በጋሸት። እድሜው 24። የተወለደበት አገር ኤርትራ። ነዋሪነቱ ዓደን። (ያልተያዘ።)

ሶስተኛ ተከሳሽ፡ ገብረማርያም ቴዎድሮስ። ከረን አካባቢ ሳላለ በተባለ ቦታ በ1916 የተወለደ። (እስረኛ።)

አራተኛ ተከሳሽ፡ ፊታውራሪ ኤድዋርዶ፤ እድሜው 50፤ የተወለደበት ቦታ ከረን ሓልሓል፣ ስራው በሞቅዲሾ የመንግስት ጽህፈት ቤት፤ በወታደራዊ ጀብዱ ሜዳይ የተሸለመ። (እስረኛ)

አምስተኛ ተከሳሽ፡ እስጢፋኖስ ኤድዋርዶ፣ የእናቱ ስም ለተብርሃን ሓጎስ፣ በ1917 አስመራ የተወለደ። ስራው በሞቅዲሾ በመንግስት ጽህፈት ቤት መኪና ጸሃፊ። (እስረኛ)

የ14 ተከሳሾች ስም በዚህ መልኩ ተዘርዝሮ ካበቃ በሁዋላ የፈጸሙት ወንጀል አንድ ባንድ ተዘረዘረ።

በተለይ የመጀመሪያዎቹ ሶስት ተከሳሾች፤ ርስበርስ ባደረጉት ስምምነት በፈጸሙት ወታደራዊ የስለላ ስራ ተከሰዋል። የስለላ ስራው ዋና መሪ ገብርኤል ኤድሞንዶ ወንጀሉን እንደፈጸመ በምርመራው ወቅት አምኗል። የኢጣልያን ጦር ቁጥር፣ ቦታና አቀማመጡን፣ ያለውን የመሳሪያ ብዛትና አይነት ለአቢሲንያ መንግስት ምስጢሩን አሳልፎ መስጠቱን አምኗል።

በመጨረሻ ገብርኤል እና ጓደኞቹ የኢጣልያን ምስጢራዊ እንቅስቃሴ ለአቢሲንያ መንግስት የመላክ ወንጀል በመፈጸማቸው ኢጣልያን አደጋ ላይ ጥለዋል። በዚህም ጥፋተኛ ሆነዋል።

* * *

ተጠርጣሪዎችን የመከታተሉ ሂደት ፈጣን ነበር።

አንዱ ሌላውን መራ። ከማስፈራራት፤ እስከ መቀጥቀጥ፣ ከዚያም አልፎ በሽጉጥ ተኩሶ እስከማቁሰል የደረሱ ምርመራዎች ተካሄዱ። ሰነዶች ሲፈተሹ ፍንጭ አገኙ። ምርመራው ሌት ተቀን

ተካሄደ። ሁለት ሳምንት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ 14 ኤርትራውያን ተይዘው በጥብቅ ምርመራ ስር ዋሉ። በመጀመሪያ ፍተሻቸው ከገብረማርያም መኖሪያ ቤት ወደ ኢትዮጵያ ስለገቡ የውጊያ መሳሪያዎች ብዛት የሚገልጽ ዝርዝር በማግኘታቸውን እንደ ትልቅ ፍንጭ ቆጥረውት ነበር። በምርመራው ወቅት ከየት እንዳገኘ ሲጠየቅ ግን፣ ገብረማርያም "ሶማሊያ ፋሺስታ" ከሚለው ጋዜጣ ላይ ታትሞ የወጣ መረጃ መሆኑን ገለጸ፣

"ምን ሊያደርግልህ ገለበጥከው?" ሲሉ አፋጠው ያዙት።

"ለጊዜ ማሳለፊያ ነው እንጂ ምንም አያደርግልኝም።"

"ከመስፍን በጋሽት ጋር ያለህ ግንኙነት ምንድነው?"

"በስም እንጂ መስፍንን አላውቀውም።"

መርማሪው "ገ" በሚል ፊርማ ለመስፍን የተላኩትን ሰነዶች አወጣና አሳየው። ገብረማርያም ሰነዶቹን ለአፍታ ተመለከተ፣

"ይህን ለመስፍን የላክኸው አንተ አይደለህም? ይኸው ከነ ስምህ ማስረጃው ሰፍሯል።"

ገብረማርያም ሰነዱን በመደነቅ አገላብጦ አየ፣

"እኔ አይደለሁም። ይህ የኔ የእጅ ጽህፈት አይደለም። የእጅ ጽህፈቴን በባለሙያ ማስተያየት ትችላለህ። ከመስፍን ግንኙነት የለኝም። አላውቀውም።"

መርማሪው ካራቢኔሪዎችን ጠርቶ ሲያበቃ ገብረማርያምን ለሁለት ሰአታት ያህል ሁለተኛ ደረጃ ዱላ እንዲያቀምሱት ትእዛዝ ሰጠ። ከሁለት ሰአታት በሁዋላ ካራቢኔሪዎች ገብረማርያምን ይዘውት ሲመጡ አይኖቹን መግለጥ እስኪያቅተው ድረስ በደም ተጨማልቆና ደክሞ ነበር። መርማሪው መልሶ ሰነዱን ወደ አይኖቹ ስር አስጠግቶ ጠየቀው፣

"ይህን ወረቀት ለመስፍን የላከው ማነው?"

"እኔ አይደለሁም። እኔ አለመሆኔን ስታውቅ ትጸጸታለህ።"

መርማሪው ገብረማርያምን ለማመን ጫፍ ላይ ደረሰ። እውነት የተናገረ መስሎ ተሰማው። እና ካራቢነሪዎችን ጠርቶ

ሲያበቃ፤ ገብረማርያምን ወደ ህክምና እንዲልኩት፣ ገብርኤልን ደ'ሞ በአስቸኳይ እንዲያመጡ አዘዘ።

* * *

የገብርኤልን መኖሪያ ቤት ሲፈትሹ በወቅቱ አስመራ ከነበረ አጎቱ የተላከለትን ደብዳቤ አግኝተው ነበር። ይዘቱን ሲመረምሩ ትኩረታቸውን የሳበ አባባል አገኙ። ደብዳቤው ገብርኤል "ታምሜያለሁ" የሚል ምክንያት ፈጥሮ ወደ አስመራ ዝውውር እንዲጠይቅ የሚመክር ነበር። ኤድዋርዶ ተይዞ እንዲመረመር ወደ አስመራ ቴሌግራም ተላከ። ቴሌግራሙ በደረሰ በጥቂት ሰአታት ውስጥ ኤድዋርዶ ካራቢኔሪዎች እጅ ወደቀ። በዚያኑ እለት ደግሞ ገብርኤል በአሰቃቂ ምርመራ ስር ነበር።

መርማሪው ገብርኤልን በቀጥታ ጠየቀው፣

"ይህን ወረቀት ለመስፍን የላክህለት በማን በኩል ነበር?"

"ማነው መስፍን?" ሲል ጠየቀ ገብርኤል።

መርማሪው የሞቀ ሳቅ ሳቀ። እና ካራቢኔሪ ጠራ።

"አስገባው። አንደኛ ደረጃ ምርመራ ተጠቀም።"

በሚቀጥለው ቀን ማለዳ ገብርኤል ወደ መርማሪው ሲቀርብ መራመድ እንኳ አይችልም። እግሩን አንስቶ መሬት በረገጠ ቁጥር የስቃይ ድምጽ ያሰማል። በመዶሻና በሚስማር የተበሳሳ የእግሩ መዳፍ አብጦ ሊፈነዳ ደርሷል።

ገብርኤል በምርመራው ወቅት ላለማመን የተቻለውን ያህል ጥሮ ነበር። ሽጉጥ ተኩሰው እግሩን ሲቦድሱት እንኳ አልደነገጠም። መካዱን ቀጠለ። በብረት ቡጢ አይንና አፍንጫውን ነረቱት። ደም እስኪተፋ ቀጠቀጡት። አላመነም። ገለበጡትና በምስማር ኩቴውን በመዶሻ ሲቀጠቅጡት ነፍሱ ልትወጣ ጥቂት ቀራት። ስቃዩን አልቻለውም። ያን ጊዜ ተሸነፈ። መስፍንን እንደሚያውቀው አመነ። ሰነዱ የሱ መሆኑን ተናገረ። "ገ" የሚለው ፊደል "ገብርኤል" መሆኑን አመነ። የሚያውቀውን ሁሉ ለመናገር ቃል ገባ። ኢጣሊያውያን መርማሪዎቹ ከተሰቀለበት አወረዱት። ደሙ አንዲቆም የመጀመሪያ

የህክምና እርዳታ ከተደረገለት በሁዋላ በነጋታው ወደ ምርመራው ቢሮ አመጡት። ለምርመራ ጠረጴዛ ተደግፎ ወንበር ላይ ቁጭ ብሎ ሳለ እንኳ ሰውነቱ ከመንቀጥቀጥ ገና አላረፈም ነበር።

መርማሪው በፈገግታ ተመለከተው፣

“የግርማዊ ንጉስ ቪቶሪዮ አማኑኤል ሶስተኛ መንግስት እንዲህ ያለ የምርመራ ባህል የለውም። ከሃዲዎች ግን የስራ ጊዜዬን እንዲያቃጥሉብኝ አልፈልግም። አሁን ወደ ስራችን እንገባለን። አንድ ትንሽ መረጃ ለመደበቅ መሞከርህን ከጠረጠርኩ መልሼ ወደዚያ ክፍል አልልክህም። እዚሁ አሰናብትሃለሁ። እጠይቅሃለሁ፤ በቀጥታ መልስልኝ። የቀረ ትእግስት የለኝም።ተጠንቀቅ!”

ምርመራው ቀጠለ።

“ማነው የመለመለህ? መቼ? ዘርዝረህ ንገረኝ?”

“ከመስፍን ጋር ስንነጋገር ኢትዮጵያ ላይ የታሰበው ጦርነት ተገቢ እንዳልሆነ፤ በዚህም በአቅማችን መጠን ኢትዮጵያን ለመርዳት እንደሚገባ ነገረኝና ተስማማሁ።”

“መስፍን ማነው? የት ነው የምታውቀው?”

“መስፍን በጋሸት አብሮ አደግ ነን። አስመራ ተወልዶ ያደገ፤ አሁን የዓደን ነዋሪ ነው። ወደ አስመራ በመጓዝ ላይ ሳለሁ መርከቧ ዓደን ስትቆም ተገናኘንና ተነጋገርን።”

“ማን አገናኛችሁ? እንዴት ተገናኛችሁ?”

“ቀደም ሲል አስመራ ሄጄ ሳለ አስገዶም ሃይሉ ከሚባል ሰው ጋር ስንነጋገር መስፍን ዓደን እንደሚኖር ነገሮኝ ሲያበቃ ሰላምታ እንዳደርስለት ለመነኝ። በዚያ መሰረት ከመስፍን ጋር ለመገናኘት ቻን።”

“አስገዶም ከመስፍን ጋር አገናኘህ?”

“የታቀደ አይደለም።”

መርማሪው ከምርመራ ክፍሉ ወጥቶ አስገዶም ሃይሉ በአስቸኳይ ከአስመራ ተይዞ ሞቅዲሾ እንዲመጣ ወደ አስመራ ቴሌግራፍ እንዲላክ ካዘዘ በሁዋላ ተመልሶ ምርመራውን ቀጠለ።

“መስፍንን ለማግኘት ብለህ ዓደን ወረድክ?”

“መርከቧ ዓደን ስትቆም መስፍን መርከቧ ላይ ወጣ። እና አገኘሁት? መርከቦች ሲመጡ መስፍን አንዳንድ ጊዜ ወደ ወደብ እየመጣ ተመላላሽ ኤርትራውያንን ያገኛል። በዚያ መሰረት የተገናኘን ይመስለኛል። አስገዶም እስኪነግረኝ ግን መስፍን ዓደን መኖሩን አላውቅም ነበር።”

“መርከብ ላይ ሆናችሁ ተነጋገራችሁ?”

“የለም። እሱ ወደ መርከቡ ላይ ወጣና ተያይዘን ወረድን። ከዚያም አንድ ቡና ቤት ውስጥ ቁጭ ብለን ተነጋገርን።”

“ብቻችሁን ነበራችሁ?”

“ሌሎች ሁለት አረቦች ነበሩ።”

“መስፍን ካቶሊክ ነው?”

“አይደለም። የኢቫንጀሊካል ሃይማኖት ተከታይ ነው።”

“ስትገናኙ እንግሊዛውያን አብረዋችሁ ነበሩ?”

“አልነበሩም።”

“መስፍን ምን ጠየቀህ?”

“የኢጣልያን የሞቅዲሾ ወታደራዊ ሁኔታ የሚገልጽ የካርታ ንድፍ እንዳዘጋጅ፤ ሌሎች ወታደራዊ መረጃዎችንም ለሱ እንድልክና እሱ ለኢትዮጵያ ንጉስ እንደሚያደርስ ነገረኝ። እና በተጨማሪ የሶማሊያና የኢትዮጵያን ድንበር የሚያመለክት ካርታ ሰጠኝ። ካርታውን እንዳጠናው ነገረኝ።”

“ለሃይለስላሴ በላክኸው ጽሁፍ ላይ ብዙ ዝርዝር ነገሮች ገልጸሃል። ከየት አገኘሃቸው?”

“በስራ ኢጋጣሚ ያወቅሁት ነው። አውቶግሩፖ ስለምሰራ ብዙ ሰዎችን አገኛለሁ። የተሸከርካሪ እንቅስቃሴዎችን አውቃለሁ። ወደ ባለስልጣናት የሚላኩ ሪፖርቶችን እኔ ስለምጽፍ በስራ ኢጋጣሚ ያወቅሁዋቸው ናቸው። ሆን ብሎ መረጃ የነገረኝ ሰው የለም።”

ከገብርኤል መኖሪያ ቤት የተገኘውን በእጅ የተሰራ

የሞቅዲሾ ካርታ ዘርግቶ ሲመለከት ቆየና ጠየቀው።

“ይህን ካርታ እንዴት አዘጋጀኸው? ተጠንቅቀህ ስማኝ? አንተ የካርታ ስራ ባለሙያ አይደለህም። ማን አዘጋጀልህ?”

ጥቂት ሲያቅማማ ቆየና ተናገረ፣

“የስራ ባልደረባዬ ነው ያዘጋጀልኝ። ለምን አላማ እንደሆነ ግን አያውቅም። በሞቅዲሾ የሚገኙ የኤርትራውያን ክለቦችንና ባሮችን ለማወቅ እንዲረዳኝ ካርታ እንዲያዘጋጅልኝ ጠይቄው አዘጋጅቶ ሰጠኝ። አልጠረጠረም። አምኖኝ ሰራልኝ።”

“ማነው የስራ ባልደረባህ?”

“ዛኖኒ ፒየትሮ።”

“አሁን ሞቅዲሾ አለ?”

“ይኖራል። በአውቶግሩፖ የእቃ ግምጃ ቤት ጸሃፊ ነው።”

መርማሪው ምርመራውን አቋርጦ ዛኒኖ ፒየትሮ የሚባል ኢጣልያዊ ከአውቶግሩፖ ይዘው እንዲያመጡለት በእስቸኳይ ካዘዘ በሁዋላ ምርመራውን ለሻይ እረፍት አቋረጠ።

በአንድ ሰአት ጊዜ ውስጥ ፒየትሮ ከምርመራው ቢሮ ደረሰ። መርማሪው እንደገና ስራ ጀመረ። ፒየትሮ ገብርኤልን ሲያይ ስሜታዊ ሆኖ መለፍለፍ ጀመረ፣

“ገብርኤል! እንኳን አገኘሁህ። ምን ገጠመህ? ለአቢሲንያ የስለላ ስራ ሲሰራ ተያዘ ብለው ሲነግሩኝ አላመንኳቸውም። ውሸታሞች አልኩ። አንተ ለአቢሲንያ ልትሰልል? የማይሆን ነገር። በፍጹም የማይሆን። አንተ መች ኢጣልያን ተቃውመህ ታውቃለህ?”

ወደ መርማሪው ዞሮ እንደገና በስሜት መናገሩን ቀጠለ፣

“ተሳስታችሁዋል። ገብርኤል የአቢሲንያ ሰላይ ሊሆን አይችልም። ገብርኤል የኢጣልያ ታማኝ ልጅ ነው።”

መርማሪው ሲጋሩን እየማገ በትእግስት አዳምጦ ሲያበቃ፣

“ጨርሰሃል?” ሲል ጠየቀው።

“አልጨረስኩም።” ካለ በሁዋላ እንደገና በስሜት ቀጠለ፣

“ሰላይ ማን እንደሆን ልንገርህ? ፍጡር አብርሃም ነው። ኢጣልያ አቢሲንያን ልትይዝ ችላለች የሚል ወሬ ሲነሳ ሁልጊዜ የሚቃወመው ፍጡር ነው። በኢጣልያ ላይ ያለውን ጥላቻ ደጋግሞ ይገልጻል። የኢጣልያ ጠላት ፍጡር እንጂ ገብርኤል አይደለም።”

“አሁንስ ጨርሰሃል?” ሲል መልሶ ጠየቀው።

“ጨርሻለሁ።” ብሎ አይኖቹን አቁለጨለጨ።

መርማሪው ብእሩን ወረቀት ላይ ቀስሮ ጠየቀው፣

“ሙሉ ስምህን፣ እድሜ፣ የትውልድ ቦታና ስራህን ተናገር?”

“ዛኖኒ ፒዮትሮ ኪሪስቶፎር። እድሜዬ 21። በርጋሞ ሎምባርዲያ ተወለድኩ። የአውቶግሩፖ የእቃ ቤት ሹም ነኝ።”

መርማሪው መዝግቦ ሲያበቃ በእጅ የተሰራውን የሞቃዲሾ ከተማን ካርታ አወጣና ከፊቱ አስቀመጠለት። ዛኖኒ ፒየትሮ ካርታውን በቅጡ አስተዋለና ወደ ገብርኤል መለስ አለ። አይን ለአይን ተገጣጠሙ። መርማሪው ጥያቄውን ቀጠለ፣

“ይህን ካርታ የሰራው ማን ነው?”

“እኔ ነኝ የሰራሁት። የሞቅዶሾ ኤርትራውያን ኮማሪዎች የሚገኙበትን ቦታ ማወቅ ፈልጎ በካርታ እንድሰራለት ሲጠይቀኝ ሰርቼለታለሁ።” አያያዘናም ጠየቀ፣ “በዚህ ካርታ ምክንያት ነው ያሰራችሁት? በዚህ ተራ ነገር?”

መርማሪው ጥያቄውን ቀጠለ፣

“ከዚህ ሌላ የሰራህለት ካርታ አለ?”

“የለም። ይህንኑ ነው የሰራሁለት።”

“ጨርሰናል። ወደ ስራህ ሂድ።”

ዛኖኒ ፒየትሮ ከመቀመጫው ሊነሳ አልቻለም።

“ሽርሞጦች የሚገኙበትን ሰፈር የሚያመለክት ካርታ ስለተገኘበት ነው ገብርኤል የታሰረው? ጉዳዩ ይሄ ከሆነ እሱን ፍቱትና እኔን እሰሩኝ። ገብርኤል የኢጣልያ ታማኝ ልጅ ነው። ህይወቴን እንኳ ቢሆን አሳልፌ እሰጥለታለሁ። ከኔ እኩል ኢጣልያን

ይወዳል። እንዳውም አንዳንድ ጊዜ ከኔ በላይ ኢጣልያን ይወዳል...”

መርማሪው በብእሩ እየጠቆመ ገሰጸው፣

“ወደ ስራህ መሄድ ትችላለህ። ሌላ ንግግር ተው።”

ፒየትሮ ከመቀመጫው ተነስቶ ከምርመራው ክፍል ከወጣ በሁዋላ ደጁ ላይ ቆሞ በጩኸት መናገሩን ቀጠለ፣

“ሽርሙጦች የሚገኙበትን ካርታ ስለያዘ እንዴት ይታሰራል? እዚህ ምን እየተሰራ እንዳለ ለጀኔራል ግራዝያኒ አሁኑኑ ሄጀ እነግረዋለሁ። እንዲያውም አሁኑኑ ካልፈታችሁት ስራዬን ለቅቄ ወደ ሎምባርዲያ እመለሳለሁ።”

መርማሪው ወደ ደጅ ወጣና ካራቢኔሪዎች ዛኖኒን ከግቢው እንዲያስወጡት አዘዘ። ሁለት ፖሊሶች ግራና ቀኝ ብብቱ ላይ ይዘውት ሲወጡ ድምጹን ከፍ አድርጎ መርማሪውን ሰደበ። በዚያም አላበቃም። ያንጠለጠሉትን ፖሊሶች ሲሳደብ ገብርኤል ሰማ።

መርማሪው ሲጋራውን ለኮሰና፣

“እንዲህ ያሉ ጓደኞችህን ነው የከዳሃቸው።” ሲል ተነፈሰ።

“ፒየትሮን አልከዳሁትም።” አለ ደፈር ብሎ።

በዚህ ጊዜ መርማሪው ፈገግ አለና እንዲህ አለው፣

“ኢጣልያውያን ሁሉ እንደ ፒየትሮ የዋህ ቢሆኑ እናንተም ከባርያ ፈንጋዮች ዘመን ሳትላቀቁ እንደ አቢስንያ ጎሳዎች በጨለማ ውስጥ በኖራችሁ ነበር። ለክህደትህ ዋጋ የተከበረው ፍርድ ቤት በጥቂት ቀናት ውስጥ ተገቢውን ሽልማት ይሰጥሃል።”

ወረቀቶችን እያገላበጠ ጥያቄውን ቀጠለ፣

“ለሃይለስላሴ በላክኸው ሰነድ ላይ ምጽዋ ስለ ተከማቹ ታንኮች ገልጸሃል። ብዛታቸውን እንዴት አወቅህ? የውጊያ መሳሪያ መከማቻው ዓዲኳላ መሆኑን የጠቀስከው ከየት አጊኘተህ ነው?”

ምርመራው ለሰአታት በዚህ መልኩ ከቀጠለ በሁዋላ፤ መርማሪው ጥያቄውን ወደ መረጃ አላላኩ ቀየረው፣

“መረጃውን አንዴት ወደ መስፍን ላክኸው?”

ኮቴው ላይ የቀረቀሩበትን መስማር እያስታወሰ ምላሽ ሰጠ። ሌሎችን አደጋ ላይ እስካልጣለ ድረስ ራሱ የፈጸመውን በዝርዝር ለመንገር ወስኖ ያልተጠየቀውን ጭምር ይናገር ገባ፣

"መረጃዎቹን በፕላስቲክ ከጠቀለልኩ በሁዋላ በተልባ መያዣዢያ ጠርሙስ ውስጥ አሸጌ፤ ጠርሙሱን ዓደን ላይ ለመስፍን እንዲሰጥልኝ ነግሬ ለአባቴ ሰጠሁት። አባቴ ለህክምና ወደ አስመራ በመሄድ ላይ ነበር። በእግረ መንገዱ አደረሰልኝ። አባቴ በዚህ ስራ ተባባሪ አልነበረም። በጠርሙሱ ውስጥ ስለነበረው ነገር የሚያውቀው ነገር አልነበረም።"

"አባትህ የት አለ አሁን?"

"ከጥቂት ወራት በፊት አርፎ፤ እዚሁ ሞቅዲሾ ተቀብሯል።"

"መስፍን መረጃውን ለሃይለስላሴ እንዴት ይልካል?"

"አላውቅም።"

መርማሪው ቱግ ብሎ ከመቀመጫው ተነሳ። ሽጉጡን መዘዘና ግንባሩ ላይ ደቀነበት። ገብርኤል ተንቀጠቀጠ። አላበው። መርማሪው እንደገና በጩኸት ጠየቀው፣

"መስፍን መረጃውን ለሃይለስላሴ እንዴት ይልካል?"

"በኪዳነ በኩል።"

"ኪዳነ የት ይገኛል? የአባቱ ስም ማነው?"

"ኪዳነ አድነይ። ከጅቡቲ አዲሳባ የሚመላለስ ነጋዴ ነው።"

መርማሪው ተመልሶ ወንበሩ ላይ ተቀመጠ። ቁጭ ከማለቱ አንድ ነገር ጭንቅላቱን መታው። የገብርኤል መኖሪያ ቤት ሲፈተሽ ገብረማርያም ለገብርኤል የጻፈለት ማስታወሻ ተገኝቶ ነበር። ገብረማርያም በማስታወሻው የኪዳነ አድነይን አድራሻ እንዲልክለት ነበር የጠየቀው። መርማሪው ከአንድ ቀን በፊት ከገብረማርያም ጋር ያደረገውን የምርመራ ምልልስ አስታወሰ።

- ኪዳነ ማነው? - ይለዋል።

- ማነው'ሱ? አላውቀውም።-

- የኪዳነ አድኃይን አድራሻ እንዲሰጥህ ለገብርኤል የጻፍከው ደብዳቤ እጇ ላይ አለ። -

- አ! ኪዳነ አድኃይ! ነጋዴ ነው። ከጅቡቲ ወደ አዲስ አበባ እንደሚመላለስ ስለሰማሁ አድራሻውን እንዲሰጠኝ ወረቀት ጽፌ ገብርኤልን ጠይቄ አድራሻውን ሰጥቶኛል። ኪዳነ አድኃይን የፈለግሁት አዲስ አበባ ስለሚገኝ አንድ ዘመዴ ለማወቅ እንዲረዳኝ ነበር። አድራሻውን ካገኘሁ በሁዋላ ለኪዳነ ደብዳቤ ጽፌለት ነበር። መልስ ግን አልሰጠኝም። -

መርማሪው ገብረማርያም ቴዎድሮስን የሚያጠምድበት ተጨማሪ ቁልፍ መረጃ ማግኘቱን አወቀ።

ኪዳነ አድኃይ!

ገብርማርያም የኪዳነ አድኃይን አድራሻ የፈለገበት እውነተኛ ምክንያት አሁን ግልጽ ሆነለት። ገብረማርያም የኪዳነ አድኃይን አድራሻ የፈለገው ስለ ዘመዱ ለማወቅ መልእክት ለመላክ እንደሆነ የተናገረው ማታለያ መሆኑን ተረዳ። እና በርግጥ ገብረማርያምም በኪዳነ በኩል ለአጤ ሃይለስላሴ መረጃ ይልክ እንደነበር መገመት ቻለ። መርማሪው ገብርኤልን አሰናበተና ባስቸኳይ ገብረማርያምን እንዲያመጡለት አዘዘ። ትንፋሹ ነበልባል ሆኖ ነበር። ገብረማርያም እስኪመጣለት ትእግስት አጣ።

* * *

ምርመራው በሰፊውና በፍጥነት ቀጠለ፣

የካቫሌር ኤድዋርዶ መያዝ የልጁ የእስጢፋኖስን መያዝ አስከተለ። ሃምሌ 1935 የእስጢፋኖስ መኖሪያ ቤት ሲፈተሽ የተገኙት ሰነዶች የሞቅዲሾን የኤርትራ ወጣቶችን ህቡእ ማህበር አጋለጠ። የፖለቲካ ይዘት ያላቸው በራሪ ወረቀቶች ማግኘት ቻሉ። መዝገበ መኮንን ለእስጢፋኖስ የላከው በራሪ ወረቀት “ሪቪስታ ዴላ ኮሎኒያ ኢታልያና” ከሚል የመጽሄት ቅጂ ጋር “ሚዮቤሎ አሚኮ” (ቆንጆ ጓዴ) የሚል ርእስ የነበረው በራሪ ወረቀት ተገኘ። በዚያኑ ቀን መዝገበን ይዘው ቤቱን ሲፈትሹ ለፍጡር አብርሃም ለመላክ ያዘጋጀው “ውድ ጓደኞቼ” የሚል በራሪ ወረቀት ተገኘ።

ወረቀቶቹ የኢጣልያን ዘረኛ ቅኝ አገዛዝ የሚኮንኑ፤ ከኢትዮጵያ ጋር በሚደረገው ጦርነት መካፈል እንደሌለባቸው የሚመክሩ ነበሩ። አንዱ ፍንጭ ሌላውን እየመራ ፍጡር አብርሃም ላይ ደረሱ። በ1911 ሰገነይቲ የተወለደው ፍጡር በሞቅዲሾ ጉምሩክ ጸሃፊ ነበር። ቤቱን ሲፈትሹ "ኢትያጵያውያን ወንድሞቻችን ላይ በታሰበው ጦርነት መሳተፍ ሃጢአት ነው።" በሚል ርእስ በኢጣልያንኛ ቋንቋ የተላከለትን በራሪ ወረቀት አገኙ። ላኪው ገብርኤል ኤድሞንዶ ሆኖ ተገኘ። በዚህም የገብርኤል ተግባር የስለላ ስራ ብቻ አለመሆኑን መርማሪው አወቀ።

ወጣቶቹ በኢጣልያ ዘመን የተወለዱ፤ ቋንቋቸው ኢጣልያንኛ ባህላቸው በአብዛኛው የኢጣልያ የነበረ ቢሆንም በመርህ ላይ ተግባብተው የኢጣልያን ቅኝ ገዢ በአንድ ልብ መቃወም የቻሉበት ጊዜ ነበር።

ባልጠበቁት ደረጃ የተደራጀ ወጣት ተቃዋሚ ሃይል ብቅታቸው ውስጥ ያገኙት የኢጣልያ የሞቅዲሾ ሹማምንት ምርመራቸውን ሌት ተቀን በጥብቅ ቀጠሉ። በተከታታይ ወንድማማቾቹ መዝገበ መኮንንና ፍካሬ መኮንን ተያዙ። በመቀጠል ፍጡር አብርሃምና እና መሐመድ ከስራ ቦታቸው ላይ በቁጥጥር ስር ዋሉ። እስጢፋኖስ እጅ ላይ የተገኙት ሰነዶች "በሞቅዲሾ የኤርትራ ወጣቶች ማህበር"ን ህቡእ ድርጅት መራቸው። ይህ የወጣቶቹ ህቡእ ማህበር በስራዊቱ ውስጥ ከሚገኙ ኤርትራውያን ጋር ግንኙነት እንዳይኖረው እንዲፈትሹ ጀኔራል ግራዝያኒ አዘዘ።

* * *

ካቫሌር ኤድዋርዶ መርማሪው ፊት ሲቀርብ የሃዘን ድባብ አጥልቶበት ነበር። በህይወቱ እስር ቤት ሲገባ የመጀመሪያ ጊዜው ነበር። መርማሪው ኤድዋርዶን ለምርመራ ከመጥራቱ በፊት ታሪኩን አንብቦ ስለነበር በትህትና ቀረበው፣

"ካቫሌር ፊታውራሪ ኤድዋርዶ ታሪክህን እንዳየሁት የአንደኛ ደረጃ የጀብዱ ኒሻን ተሸላሚ ነህ። በሊቢያ የነበረህን ቦታ ተረድቻለሁ። በሊቢያ ቆይታህ ከሸኽ ዑመር ኣል ሙክታር ጋር ባደረግነው ውጊያዎች የፈጸምከውን ጀብዱ በዝርዝር በማወቄ

ላከብርህ እገደዳለሁ። አንተ የኢጣልያ አርበኛ ሆነህ ሳለ ልጅህ እንዴት የኢጣልያ ጠላት ሊሆን ቻለ?”

“ልጄ ለምን የኢጣልያ ጠላት እንደሆነ አላውቅም።”

“ለወንድምህ ልጅ ለገብርኤል እና ለልጅህ ለእስጢፋኖስ የጻፍከላቸውን ደብዳቤዎች አጊኝተናል። ገብርኤል በህመም አሳብቦ አስመራ እንዲመጣ የጠራኸው ለምንድነው?”

“ቤተሰባችንን ባገራችን ለማሰባሰብ ከመፈለግ እንጂ በሌላ አይደለም። በተለይም ገብርኤል እናቱም አባቱም ስለሞቱ አጠገቤ እንዲሆን በመፈለጌ ነው።”

“ልጅህ እስጢፋኖስ ኢጣልያን በጥንቸልና በአሞራ፤ አቢስንያን በአንበሳ እየመሰለ ካርቱን ስዕል እያዘጋጀ ሲበትን እንደነበር ታውቃለህ? የካርቱን ስእሉ አንተ ጋር አልደረሰም?”

“በፍጹም አላውቅም። ይህ ዋጋ ቢስ አስተሳሰብ ነው። ልጄ ጭንቅላት ውስጥ እንዲህ ያለ አሳብ መግባቱን ባውቅ ኖሮ ድርጊቱ ተገቢ እንዳልሆነ በነገርኩትና በመከርኩት ነበር።”

“ምን ብለህ ትመክረው ነበር?”

“ቅሬታችንን እዚሁ መጠየቅ እንጂ የያዝነውን ማጣት እንደማይገባ በነገርኩት ነበር።”

“ካቫሌር! በኢጣልያ ስርአት ላይ ቅሬታችሁ ምንድነው?”

“የትምህርት ገደብ ማድረጋችሁ ያሳዝነናል። ‘ኤርትራውያን ከተማሩ ለኢጣልያ መንግስት አይታዘዙም’ ብላችሁ እንደምትሰጉ በወሬ እሰማለሁ። ይህ እውነት ከሆነ ያስከፋኛል። እኔ ለኢጣልያ ታማኝ የሆንኩት በእውቀት ማነስ ምክንያት አይደለም።”

“ልጆችህም ሆኑ የወንድምህ ልጅ የተሻለ ትምህርት አጊኝተዋል። ጥሩ ስራ አላቸው። ከዚያ በላይ ምን ፈለግህ?”

“ቅሬታዬ ከቤተሰቤ ጋር የተያያዘ አይደለም። ስለ አገሬ ሰዎች ነው ስናገር የነበረው። ምግብ፣ ጤና እና ትምህርት - ሶስቱን መለያየት አይቻልም። ሓልሓል ቦጎስ - ፋና ደርሼ ስመጣ ኮማንዳቶረ ኮሎኔል ሳንማርኮን አጊንቼ ያየሁትን ችግር ነግሬዋለሁ። በጽሁፍ

አቅርብ ብሎኝ በጽሁፍ አቅርቤያለሁ።”

“ወጣቶች ወደ ሊቢያ በመዝመታቸው እርሻ የሚያርስ ጠፍቶ ሰው ተርቧል’ የሚለው ቅሬታ ነው?”

“አይደለም። በምግብ ጉዳይ ቅሬታ አልሰማሁም። ዋናው የጤና ጉዳይ ነው። በፋና ህጻናት በተቅማጥና ውሃ በሚያመጣው ህመም እንደሚሞቱ አይቻለሁ። በከተማ የትምህርት ጥያቄ አለ። እንዲህ ያሉ ቅሬታዎቻችንን በግልጽ እየተናገርን ነው። የኢጣልያን ኮሎኒ በሃይል ለማስወገድ ከኢትዮጵያ ጋር የመተባበር ነገር ግን በአሳቤም የሌለ ነገር ነው።”

መርማሪው በመገረም ፈገግ ብሎ እንዲህ አለው፣

“አሁን የተናገርከው ሁሉ አመጽ ነው!”

“ለኢጣልያ ህይወቴን የሰጠሁ ነኝ። አነጋገርህ ያስከፋኛል።”

“በዚህ ጉዳይ ከልጆቹ ጋር ተነጋግራችሁ ነበር?”

“እንዲህ ያለውን ነገር ከልጆቹ ጋር ተነጋግሬ አላውቅም። የወጣት ልብ ችኩል እንደመሆኑ ስህተት ላይ እንዲወድቁ አልፈልግም። እንዳልኩህ ለኮማንዳቶረ ሳንማርኮ ይህን ነገር ደጋግሜ ነግሬዋለሁ። በጽሁፍም አቅርቤያለሁ። ከእንግሊዝ ኮሎኒዎች ባነሰ ደረጃ ላይ መገኘታችን ልክ እንዳልሆነ ነግሬዋለሁ።”

“የኢጣልያ መንግስት የአቢሲንያን ነሳዎች ከባርነት አገዛዝ ነጻ ሊያወጣ እንደተዘጋጀ ሰምተሃል?”

“በወሬ ሰምቻለሁ።”

“አስተያየትህ ምንድነው?”

“የሚያስጨንቀኝ የኢትዮጵያ መያዝ ሳይሆን፤ ኢጣልያ በምታደርገው ጦርነቶች ሁሉ ግንባር ቀደም ሟቾች መሆናችን ነው። ሞት በዝቶብናል። የምንሞተውን ያህል ከክብሩና ከጥቅሙ ተካፋይ አይደለንም። እንዲህ ሊቀጥል አይችልም።”

“እንዲህ ያለ አሳብህን ኮሎኔል ሳንማርኮ ያውቃል?”

“ሁሉንም ያውቃል። የግርማዊ ቪቶርዮ አማኑኤል መንግስት ፍትህ እንዲሰጠን እየጠየቅን ነው።”

* * *

መሰብሰቢያቸውን ከእስጢፋኖስ መኖሪያ ቤት ያደረጉት ወጣቶች እየተገናኙ ውይይት እንደሚያካሂዱ በምርመራው ወቅት አመኑ። የተያዙት ሁሉ ጠበቅ ያለ ምርምራ ሲገጥማቸው በጸረ ኢጣልያ ቅኝ አገዛዝ መሰባሰባቸውን ቢያምኑም፤ ከገብርኤል ኤድሞንዶ ጋር ግን "ግንኙነት የለንም" ሲሉ ካዱ። መርማሪዎቹ ግን ቀሲታቸውን ትውልዳቸው ከብሌን ከሆኑት ከገብርኤልና ከገብረማርያም ሳይነቅሉ ምርመራቸውን ቀጠሉ።

አስገዶም ሃይሉ አስመራ ላይ ተይዞ ሃምሌ 16 1935 ሞቅዲሾ ከመርማሪው ክፍል ቀረበ።

"ከገብርኤል ጋር ግንኙነታችሁ ምን ነበር?"

"አብሮ አደግ ነን። ረጅም እውቂያ አለን።"

"ከመስፍን በጋሽት ጋርስ?"

"እውቂያ የለንም። ከሞቅድሾ በህመም ምክንያት ወደ አስመራ በመመለስ ላይ ሳለሁ ዓደን ላይ ተገናኝተን ነበር። ጥቂት ተጨዋወትንና እኔ መንገዴን ቀጠልኩ።"

"ምን ተጨዋወታችሁ?"

"ስለ ወልወል ግጭት ጠየቀኝ። ምንም የማውቀው ነገር ስላልነበር አስተያየት መስጠት አልቻልኩም። ከዚያም አስመራ የምትገኝ እናቱን እንዳይለት አደራ አለኝ። ይኸው ነው።"

"ገብርኤልና መስፍንን ያገናኘሃቸው አንተ ነህ?"

"እኔ አላገናኘሁዋቸውም። ገብርኤል አስመራ ቆይቶ ወደ ሞቅዲሾ ሲመለስ ባቡር ጣቢያ ድረስ ሸኝቸው ነበር። ዓደን ላይ መስፍንን ካገኘው ሰላምታ እንዲያቀርብልኝ ነገርኩት። መስፍንና ገብርኤል እንደሚተዋወቁ አውቃለሁ።"

"መስፍን የአቢሲንያ ሰላይ መሆኑን አታውቅም ነበር?"

"ሁዋላ ወሬ ሰምቻለሁ። ዓደን ላይ ሳገኘው ግን መስፍን የኢትዮጵያ ሰላይ እንደሆነ አላውቅም ነበር። ሆስፒታል ታምሜ

ተኝቼ ሳለ መስፍን ከአቢሲንያ ጋር እንደሚሰራ ሰማሁ። ወሬውን ከሰማሁ በሁዋላ ስለፈራሁ ወደ እናቱ ቤትም አልሄድኩም።"

ሃምሌ 28 ብሉቾባሽ ነጋሽ አበራ፣ ተክለ አውግስቲኖ እና ዘርኡ መብራህቱ የመጨረሻዎቹ በቁጥጥር ስር የዋሉ ኤርትራውያን ነበሩ። በርግጥም አንዱ ፍንጭ ወደ ሌላው እየመራ በገብርኤልና በገብረማርያም ስር የተደራጀውን የወጣቶች ኤርትራውያን የተቃውሞ ህብእ ቡድን በቁጥጥር ስር አዋሉት። በዚህ እንቅስቃሴ ተጠርጥረው የተያዙት እድሜያቸው ከ14 አመት እስከ 29 ያሉ ሲሆን፤ ንጉሰ አበራ እና ካቫሌር ኤድዋርዶ ገብረመድህን እድሜያቸው 36 እና 50 ነበሩ።

* * *

በግርማዊ ንጉስ ቪቶሪዮ አማኑኤል ሶስተኛ፤ በእግዚአብሄር ቸርነት በህዝቡ ፍላጎት፤ በኢጣልያ ንጉስ ስም፤ በሞቅዲሾ የኢጣልያ ቅኝ ግዛት የጦር ፍርድ ቤት የ14 ኤርትራውያንን ጉዳይ ሲመረምር ከቆየ በሁዋላ ፍርድ ሰጠ።

ችሎቱ የግራ-ቀኝ ሙግቶችን ሰምቶ ሲያበቃ ህጉ በሚያዘው መሰረት ጠበቆቻቸው አቮካቶ ካታንዮ ቪንቸንሰን፣ አቮካቶ ዳመዚን ጀርጀን፣ አቮካቶ ካጥራ ፈርዲናንዶን፣ ዶስካኖ ዶክቶር አርካጀሎ በተገኙበት ጥቅምት 30 1935 ፍርድ ቤቱ ውሳኔ ሰጠ።

ገብርኤል ኤድሞንዶና ገብረማርያም ቴዎድሮስ የስለላ ስራ መስራታቸው የተረጋገጠ በመሆኑ በ1930 በወጣው የወንጀለኛ መቅጫ ህግ አንቀጽ 257 መሰረት በሞት እንዲቀጡ ፍርድ ቤቱ ወሰነ። መስፍን በጋሽትና ኪዳኔ አድነይ በተመሳሳይ በሌሉበት ሞት ተፈረደባቸው። ካቬሌር ፊታውራሪ ኤድዋርዶ ገብረመድህን ምንም ጥፋት ስላልተገኘበት በነጻ ተሰናበተ። በእነ እስጢፋኖስ ኤድዋርዶ መዝገብ የተያዙ ሌሎቹ አስር ተከሳሾች በስለላ ወንጀል ማስረጃ ባይገኝባቸውም ኢጣልያን የሚጎዳ የፖለቲካ ስብሰባ በማድረጋቸው ከ6 አመታት እስር ጀምሮ በነጻ እስከመሰናበት ድረስ ፍርድ ተሰጥቶ ችሎቱ ተጠናቀቀ። በምርመራ ወቅት ገብርኤልን በጥይት እግሩ ላይ የመታው መርማሪ ጥፋተኛነቱ በመረጋገጡ በቅጣት ወደ ኢጣልያ እንዲመለስ ፍርድ ቤቱ ወሰነ።

ምእራፍ ፭

ከ ት - ከ ት ብ ሎ ሳ ቀ

መንፈሱ ተሳቆ - መከዳቱን አውቆ!

ባልተለመደ ሁኔታ ከመሸ በሁዋላ ካራቢኔሪዎች መጥተው ልብሱን እንዲቀይር፤ ጠጉሩን ተበጣጥሮ እንዲዘጋጅ ነገሩት። ገብርኤል ከዛሬ ነገ እለተ ሞቱን እየጠበቀ ነበር። የሚገድሉት ከሆነ ግን ልብሱን እንዲቀይር ለምን ያደርጋሉ? ምናልባት ባለቤቱን እንዲሰናበታት ለማድረግ ሊሆን እንደሚችል አሰበ። ተስፋ ባጣ ስሜት ልብሱን ቀያይሮ ጨረሰ። ጠጉሩን እንደነገሩ አበጣጠረ።

ግራና ቀኝ አጅበው መኪና ውስጥ አስገቡት። ከእስር ክፍሉ ሲወጣ ዘወትር እንደሚያደርጉት እጆቹን በሰንሰለት አለማሰራቸው ልዩ ነገር ሆነበት። በዚያችው ቅጽበት ከእጃቸው አፈትልኮ ስለማምለጥ አሰበ። ካራቢነሪዎቹ የታጠቁ እንደመሆናቸው ግን የትም ሊያመልጥ እንደማይችል ግምት ወሰደ። ቢያመልጥ እንኳ ከሞቅዲሾ መውጣት እንደማይችል ያውቃል። አንድ ቀን ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ይይዙታል። ግን ደግሞ ከመገደሉ በፊት ባለቤቱን እንዲያይ ከፈቀዱለት አንድ እድል መሆኑን አሰበ።

ሌላ አሳብ ደግሞ መጣበት።

የሞት ፍርድ እንዴት ነው የሚፈጸመው?

መጻህፍት ሲያነብ የሞት ፍርድ በተለያየ መንገድ እንደሚፈጸም ተረድቷል። በገመድ የሚንጠለጠሉ አሉ። በጠመንጃ የሚረሸኑም አሉ። የመርዝ ክኒን በመስጠትና ከኤሌክትሪክ ጋር

የተያያዘ ወንበር ላይ አስቀምጠው ስለሚገድሉም ሰምቷል። ወደ አረብ አገራት ደግሞ ሞት የተፈረደባቸውን አንገቱን በጎራዴ ቆርጠው በመጣል ያሰናብቱታል። መርማሪው እንደነገረው በኢጣልያ ወታደራዊ ፍርድ ቤት ደንብ መሰረት "ከሃዲዎች እና ሰላዮች" ተንበርክከው ማጅራታቸውን በጥይት ይደበደባሉ።

ገብርኤል በአሳብ ነጎደ።

አጤ ምኒልክ የእያሱን አባት፣ አቦይ ያዕቆብን "ከሃዲ" ብሎ እጅ እና እግሩን ቆረጠው። ኢጣልያ ደግሞ ገብርኤል ኤድሞንዶን "ከሃዲ" ብላ ማጅራቱን በጥይት በመደብደብ አዋርዳ ልትገድለው ፈርዳለች። ገብርኤል ይህን ጉዳይ በትእዝብት አሰበው።

በመቀጠል ስለ ሞት አሰበ።

"ጎራዴ፣ ገመድ ወይም ጥይት ምንም ልዩነት የላቸውም። ስለዚህ መጨነቅ የለብኝም።" ሲል ራሱን አበረታታ። ቀጠለና ደግሞ፣ "ሞት ያው ሞት ነው! የአንድ ሰከንድ ጉዳይ ናት! እና እረፍት። እና ሰላም። እና ለዘልአለሙ ዝምታ።" ሲል ተፈላሰፈ።

ወዲያው ግን አእምሮው ወደ ሌላ ጉዳይ ዘለለ።

ከመሞቱ በፊት በጥብቅ ማወቅ የፈለገውን ጉዳይ አስታወሰ። ይህም እሱ ወደ አጤ ሃይለስላሴ የላከውን መረጃ "ኢጣልያውያን እንዴት ሊያገኙት ቻሉ?" የሚለው ጥያቄ ነበር።

አባቱ ኤድሞንዶ ተልባ የያዘችውን ጠርሙስ ለመስፍን በጋሸት በእጁ መስጠቱን አረጋግጦለታል። መስፍን በጋሸትም ራሱ ወደ ጅቡቲ በመሄድ መረጃውን ለኪዳነ ኢድጎይ አስረክቧል። ኪዳኔ ተመላላሽ ነጋዴ እንደመሆኑ ወደ አዲስ አበባ ገስግሶ በመሄድ መረጃውን ለአጤ ሃይለስላሴ ያለችግር ከቤተመንግስት አድርሷል። ይህንንም መስፍን አረጋግጦለታል። እና ምስጢሩ የት ሾለከ?

ኢጣልያኖች ከንጉሱ ቤተመንግስት ሰላይ ተከለው ይሆን? ሊሆን አይችልም። ካልሆነ ታዲያ መረጃው እንዴት ኢጣልያኖች እጅ ሊገባ ቻለ? ሊሆን የሚችለውን መገመት ተቸገረ።

ዛሬ የሚገድሉት ከሆነ ሰነዱ እንዴት ከእጃቸው ሊገባ እንደቻለ ሊጠይቃቸው ወሰነ። ግን ማወቁ ምን ይጠቅመዋል?

“በእገሌ በኩል የተገኘ ነው” ብለው ከነገሩት ከአንድ ደቂቃ በሁዋላ የሚሞት ከሆነ ማወቁ ምን ጥቅም አለው? ለነገሩ የሞት ፍርዱን የሚያስፈጽሙት ተራ ካራቢኔሪዎች እንጂ የጸጥታው ስራ ባለስልጣናት ሊሆኑ አይችሉም። ስለዚህ ሰነዱ እንዴት እንደተገኘ ሊያውቁ አይችሉም። ምናልባትም ለምን እንደሚገደል እንኳ ላያውቁ ይችላሉ። ዋጋ ቢስ አሳብ!!

ገብርኤል ሳያስበው በድንገት ከት ብሎ ሳቀ።

መኪናዋን ያሽከረክር የነበረው ፖሊስ ደንግጦ ፍሬን ያዘ፣

“ደህና ነህ?”

“Mi dispiace! ወዴት ነው የምትወስዱኝ?”

“ኮማንዳቶረ ሳንማርኮ ሊያነጋገርህ ይፈልጋል።”

ገብርኤል በጣም ተገርሞ ጠየቀ፣

“ኮማንዳቶረ ሳንማርኮ ወደ ሞቅዲሾ መቼ መጣ?”

“ሰነበተ።”

ባንድ አፍታ ወደ ሌላ የአሳብ ባሕር ውስጥ ዘልሎ ገባ።

ኮማንዳቶረ ሳንማርኮ በኤርትራ የፖለቲካ ሃላፊ ሲሆን፤ በዜጎችም ሆነ በአገሬው ሰዎች ዘንድ ተወዳጅ ነበር። የአገሬው ሰው ሳንማርኮን የሚወደው ትሁት ስለሆነ ብቻ አይደለም። ኤርትራውያንን በክብር በቢሮው እየተቀበለ ማነጋገሩ ብቻ ሳይሆን ለችግሮች መፍትሄ ይሰጣል። የኤርትራውያንን ፍላጎት ለማወቅና ለመረዳት ይጥራል። ገዛ ባንዳ ሃበሻ እየሄደ ወደ ግሮሰሪዎች ገብቶ ከተራ ሰዎች ጋር ይጨዋወታል። ሳንማርኮ ከአጎቱ ኤድዋርዶ ጋር ወዳጅ መሆናቸውንም ገብርኤል ያውቃል።

መኪናዋ ኢጣልያውያን ወደሚኖሩበት ሰፈር ከገባች በሁዋላ ከአንድ ሬስቶራንት ደጃፍ ላይ ቆመች። ካራቢኔሪዎቹ እንደገና ግራና ቀኝ አጅበውት ወደ ውስጥ ይዘውት ገቡ። የቆሰለ የእግሩ መዳፍ የዳነ ቢሆንም በመጠኑ ያነክስ ነበር። ዋናውን የማስተናገጃ ክፍል ካለፉ በሁዋላ በአንዲት አነስተኛ የልዩ እንግዶች ማስተናጋጃ ክፍል ውስጥ አስገብተው አስቀመጡት። ክፍሉ በምቹ

ሶፋዎች የተሞላ ነበር። ከሁለት ወንበሮችና ከአንድ ጠረጴዛ በቀር ሌላ አልነበረም። ገብርኤል የክፍሉን ዙሪያ ቃኘ። በግድግዳው ላይ የኢጣልያ የምስራቅ አፍሪቃ ግዛት ካርታ ተሰቅሏል።

ሲቪል የለበሰ አንድ አጭር ባለ ነጭ ሙስታቹ ሰው ገባ። በእድሜ የገፋ ነው። ወደ ሰባ ይጠጋል። ይህ ሽማግሌ ኮሎኔል ኮማንዳቶረ ሳንማርኮ መሆኑን ገብርኤል አሳምሮ ያውቃል። እንዲህ ተገናኝተው ባያውቁም፤ ደጋግሞ ምስሉን ጋዜጣ ላይ አይቶታል። የሞቀ ሰላምታ ከሰጠው በሁዋላ ወንበር ስቦ ተቀመጠ። አስተናጋጆች ቀልጠፍ ብለው ታዘቧቸው።

“ታውቀኛለህ?” ሲል ጠየቀው።

“አውቅሃለሁ። አጎቴ ኤድዋርዶ ላንተ ልዩ ግምት አለው። ስለ መልካም አስተሳሰብህ ብዙ ጊዜ ይናገራል።”

ኮሎኔሉ ፈገግታውን ብልጭ አደረገ፣

“ልክ ነው። ፊታውራሪ ኤድዋርዶ ወዳጄ ነው። በቀጥታ በመናገር ችሎታውና ለራሱ ባለው ክብር አደንቀዋለሁ።”

አስተናጋጆች ራት አቀረቡ። ቀላል ሳንዱች ነበር። ኮሎኔል ሳንማርኮ በተዝናና መንፈስ ጨዋታ ጀመረ፣

“ዛሬ ካንተ ጋር እየጠጣሁ አመሻለሁ፤ ፈቃድህ ቢሆን?”

ገብርኤል ተመሳሳይ የመዝናናት ስሜት አደረበት፣

ሳንማርኮ እንዲህ አለ፣

“ኤድዋርዶን ከረጅም ጊዜ በፊት ጀምሮ አውቀዋለሁ። ሲሪናይከ እና ፊዘን አብረን ሰርተናል። ብዙ ቀረቤታ አልነበረንም እንጂ አባትህንም አውቀዋለሁ። በርግጥ ወደ ሞቅዲሾ የመጣሁት ለሌላ የስራ ጉዳይ ነበር። እዚህ ከመጣሁ በሁዋላ ችግር ላይ መውደቃችሁን ሰማሁ። ኤድዋርዶን አጊንቼው ነበር። ነጻ ሆኖ መገኘቱ መልካም ዜና ነው። በልጁ በእስጢፋኖስና በአንተ ላይ የተከበረው ፍርድ ቤት ትክክለኛ ፍርድ መስጠቱን አምናለሁ። እንደ ኤድዋርዶ ያሉ ሰዎች በኢጣልያ ላይ ሲያዝኑ ማየት ደግሞ ያሳዝነኛል። ዳሩ ምንም ማድረግ አይቻልም። ፍትህ መሰጠት ስላለበት መቀጣታችሁ ግዴታ ሆኗል።”

ገብርኤል በፈግታ ምላሽ ሰጠ፣

“ስለቤተሰባችን ላደረብህ መልካም ግምትና ልትጠይቀኝ ስለመጣህ አመሰግናለሁ። በተቀረ ፍርድ ቤቱና ህጉ የባለ-አገሩን እውነት የመዘነ አይደለም። ጠበቃዬም ይህን ያምናል። የምርመራ ሂደቱም በጣም ጭካኔ የተሞላበት አስከፊ ነበር።”

ኮማንዳቶረ ሳንማርኮ የሃዘን ስሜት አሳየ፣

“በምርመራ ወቅት ጉዳት እንዳደረሱብህ ሰምቻለሁ። በተፈጸመው ድርጊት አዝናሁ። እንዴት ነህ ለመሆኑ?”

“ሞት ተፈርዶብኛል። የደህንነቴ ጉዳይ አያሳስብም።”

“ፍርዱ እስኪፈጸም መብት አለህ።”

“በኔ ላይ እስኪደርስ ድረስ በኢጣልያ ቅኝ ግዛት ውስጥ እንዲህ ባለ ሁዋላቀር መንገድ ምርመራ እንደሚደረግ አላውቅም ነበር። በማወቄ ደንግጫለሁ።”

አያያዘናም ገብርኤል በምርመራ ወቅት የተደበቀ ምስጢር ለማውጣት በሚል እንዴት እንዳሰቃዩት በዝርዝር ተረከለት። ኮሎኔል ሳንማርኮ በሰማው ነገር በድጋሚ የማዘን ነገር ያደረበት መሰለ። ያም ሆኖ በርእሰ ጉዳዩ ላይ አስተያየት ከመስጠት ተቆጠበ። በዚህም የምርመራ መንገዱ የተለመደ እንደሆነ ገብርኤል ገመተ።

የቀረበላቸውን ራት አጣጥመው ከጨረሱ በሁዋላ እንደየፍላጎታቸው መጠጥ አዘዙ። ይህን ጊዜ ኮሎኔሉ ወደመጣበት ዋና ጉዳይ ለመዝለቅ በመፈለግ እንዲህ አለ፣

“የተፈረደብህ የሞት ፍርድ እንዳይጸና ጥረት እየተደረገ ነው። የግርማዊ ንጉስ ቪቶሪዮ አማኑኤል ወኪል ለአንተና ለገብረማርያም ምህረት እንዲሰጥ ተጠይቋል። እድለኛ ከሆናችሁ ፍርዱ ወደ እድሜ ልክ እስራት ዝቅ ይልላችሁዋል። ዛሬ ላነጋግርህ የመጣሁት ጉዳይ ግን ከዚህ ጋር በተያያዘ አይደለም። አንተ የምትናገረው የፍርድ ቤት ውሳኔውን ለማሻሻል አይጠቅምም።”

ሳንማርኮ በተረጋጋ መንፈስ ሲጋሩን ለኮሰ።

“የህይወት ታሪክህን ለማወቅ ሞክሬያለሁ። ገና ወጣት ነህ።

በስራ አለም ብዙ ልምድ የለህም። በኢጣልያ የኤርትራ ኮሎኒ ላይ የተቃውሞ ክስ የለብህም። በአንጻራዊነት የተሻለ የትምህርት እድል አጊኝተሃል። ኢጣልያ ከተንከባከበቻቸው ወጣቶች አንዱ ነበርክ።"

ፋታ ወስዶ ቀጠለ፣

"ከመሰረቱ እንጨዋወት። ምናልባት ከአያትህ ታሪክ መጀመር ይሻል ይሆናል። ስለ ኑረነቢ ያለህ እውቀት ምንድነው?"

"ዝርዝር ነገር አላውቅም። ክብሩን የሚነካ ነገር ሲናገሩት ተቀይሞ መሸፈቱንና መገደሉን ነው የሰማሁት።"

"አባትህ ስለኑረነቢ አሟሟት እንዴት እንደገለጸልህ ማወቅ ነው የፈለግሁት? በቅድሚያ እኔ ያገኘሁትን ላንብብልህ?"

ወረቀት እየገላለጠ ማየት ጀመረ፣

"ኑረነቢ በኺት ከ1889 ጀምሮ እስከ 1899 ለአስር አመታት በገልዓሎ አካባቢ፣ በዊዓ፣ በፍሽይ ምራራ ሸለቆ እና በሌሎችም ቦታዎች ሸፍቶ አንዳንድ ጉዳት አድርሷል። በ1899 አጋማሽ ግን የኑረነቢን ድርጊት ባልወደዱ ባልደረቦቹ ጥቆማ ተከቦ እጁን እንዲሰጥ ተጠየቀ። ምህረት እንደሚያገኝ መልእክት ተልኮበት ነበር። ፈቃደኛ ባለመሆኑ በተደረገው የተኩስ ልውውጥ ህይወቱን አጥቷል።" ሳንማርኮ ወረቀቱን አስቀመጠና ጠየቀው፣

"ከዚህ የተለየ የምታውቀው ታሪክ አለ?"

"መሸፈቱንና መገደሉን ብቻ ነው የማውቀው። እሱንም ቢሆን ዘመዶቼ ሲያወሩ እንጂ በቀጥታ አልተነገረኝም።"

"ኑረነቢ ለአንተ አርበኛ ነው?"

"በውነቱ አስቤበት አላውቅም።"

"የግድ አስበሃል።"

"አያቴ አቅሙን አለመገመቱን እረዳ ነበር። አንድ ግለሰብ 'ፒግሮ' የሚል ነገር ስለተናገረው አምርሮ መቀየሙ ይገርመኝ ነበር።"

ሳንማርኮ ትኩረት አደረገ፣

"ክብረነክ የተባለው ቃል 'ፒግሮ' የሚል ነበር?"

“የሰማሁት እንደሱ የሚል ነው።”

“አያትህ በፋና ጭቃ ሹም የነበረ ሰው ነበር። ምጽዋ ከሄደ በሁዋላ ከከተማው ጋር ራሱን ማዋሃድ የተቸገረ ይመስለኛል።”

“ሊሆን ይችላል።” አለ ገብርኤል።

እና ተስፋ ባጣ ድምጽ አከለበት፣

“እኛ ስድቦችን እንደ ሰላምታ ለምደናቸዋል።”

የገብርኤል ሁኔታ ደስ አላለውም። የመረረ ስሜት ላይ መሆኑን ገመገመ፡ና ሳንማርኮ ለማቅለል ሞከረ፣

“አንዳንድ ግለሰቦች ክብረነክ የሆነ ቃላት ካንደበታቸው ሊያወጡ ይችላሉ። እኔ የመንግስትን ስራ ወክዬ በመስራት ላይ ሳለሁ ክብረነክ ቃላት ተጠቅሜ አላውቅም። ከስራ ውጭ ባሉ ሁኔታዎች ግን ሊያጋጥም ይችላል። በርግጥ ገዢው አካል ሲሳደብ ወይም ጉዳዩ የዘረኛነት መልክ ሲይዝ የሚፈጥረውን ስሜት አውቃለሁ።” ለሰከንድ ያህል ፋታ ወስዶ ሲያበቃ አጠንክሮ ጠየቀው፣ “እንዲህ ያሉ አጋጣሚዎች ተጽእኖ አሳድረውብሃል?”

“እኔን በግል የሰደበኝ ሰው አላጋጠመኝም።”

“አንድም ጊዜ?”

“የወል ስድቦችን መጋራቴ አልቀረም። የናሽናሌና የኢንዲጅኔ አለመደባለቅ የመንግስት ፖሊሲ ነው። ይህ የታወጀ ስድብ ነው።”

ሳንማርኮ እየተጎነጨ ፋታ ወሰደና ቀጠለ፣

“በእናትህ በኩል ስለ ወንድ አያትህ ታሪክም ሰምቻለሁ። በኢጣልያ ኮሎኒ ላይ ሽፍቶ ህይወቱን አጥቷል። የወላጆችህ ጋብቻ በታሪክ መመሳሰል ምክንያት የተፈጸመ ሊሆን ይችላል?”

“አይመስለኝም። ሁለቱም በካፑቺኒ ማህበር ስር ስላደጉ እዚያ የተገናኙ ይመስለኛል። እናትና አባቴ በኢጣልያ ኮሎኒ ላይ ያላቸውን ቅሬታ በልጆቻቸው ፊት አይናገሩም። የአባቴ ቅሬታ ይታወቃል። እናቴ የፖለቲካ ዝንባሌ አልነበራትም።”

ሳንማርኮ ወረቀቶቹ ላይ አቀርቅሮ ቆየ፣

“ወንድምህ ሚካኤል በህመም ምክንያት ህይወቱ ማለፏን ሰምቻለሁ። የበኩር ልጅህን ሞት እንደነጠቀህም ተረድቻለሁ። በህክምና ወቅት ተገቢ እርዳታ አጊኝተው ነበር?”

“ተገቢ ህክምና አግኝተዋል። ቅሬታ የለንም።”

ኮሎኔል ሳንማርኮ ቀና አለ፣

“እንግዲህ በቤተሰብህ ዙሪያ ከዚህ ያለፈ የምንነጋገረው ነገር ያለ አይመስለኝም። ምናልባት ግን አባ ዮሃንስ ስለሚባል ፈረንሳዊ ቄስ ሰምተህ እንደሆን መጠየቅ እፈልጋለሁ።”

“በወሬ ሰምቻለሁ። ብዙም አላውቅም።”

“የሰማኸውን ልትነግረኝ ፈቃደኛ ነህ?”

“የላዛሪስት ሚስዮን በካፑቺነ መተካታቸውን አውቃለሁ።”

“አባ ዮሃንስ ለምን እንደተባረረ ተረድተሃል?”

“ፈረንሳይና ኢጣልያ ካላቸው የፖለቲካ ጉዳይ ጋር የተያያዘ ይመስለኛል። ጉዳዩን በጥልቀት ለማወቅ አልሞከርኩም።”

“እንደምትነግረኝ ከሆነ ከአባት ወይም ከአያት የወረስከው ቂም የለም። ከሌለ ጉዳዩ ካንተው ነው?”

“ልክ ነው። የተወረሰ አመለካከት የለኝም።”

ሳንማርኮ ሲጋሩን አወጣና አቀጣጠለ፣

“በቀጥታ እጠይቅሃለሁ። የልብህን፣ ቃላት ሳትመርጥና ሳትቆጥብ ምላሽ ስጠኝ። የምታውቀኝ ከሆነ ሽንገላ አልወድም። መርማሪም አይደለሁም። ተግባብተናል?”

ገብርኤል ራሱን ላይ ታች ናጠ።

እና ሳንማርኮ ምርመራውን ቀጠለ፣

“የአቢሲንያ ስርአት ሁዋላ ቀር፤ ፊውዳላዊ ነው። ኤርትራውያን በቅኝ ግዛት ስር ብትሆኑም በማንኛውም መለኪያ ከአቢሲንያውያን በተሻለ የስልጣኔ ደረጃ ላይ ናችሁ። የፊውዳሉ ስርአት የጥቂት ቤተሰቦች መጠቀሚያ ነው። ሌላው ጎሳ በአሰቃቂ ባርነት ውስጥ ይገኛል። ጤነኛ አእምሮ ያለው ሰው እንዲህ ያለው

ስርአት ተለውጦ ህዝብ በስልጣኔ ስር እንዲኖር ይመኛል። ይህ የሰው ልጅ ሁሉ የሚመኘው ነው። አንተ እንዴት የመሰልጠን ተስፋ ከሌለው ስርአት ጋር ለመስራት ወሰንክ? Non capisco."

ገብርኤል ለምላሽ በመዘግየቱ ሳንማርኮ ቀጠለ፣

"ሃይለስላሴ ገና የባርያ ንግድ እንኳ ማስቆም አልቻለም። እናንተ ያገኛችሁትን ስልጣኔ ሌሎች አቢስንያውያን ማግኘት ይፈልጋሉ። ኤርትራን በመገንባቱ ሂደት ምን ያህል አቢሲንያውያን ስራ ፈልገው ወደ ኤርትራ እንደሚመጡ ታውቃለህ። አቢሲንያውያን የኢጣልያን ስልጣኔ መጋራት ስለሚፈልጉ እኛን በጉጉት እንደሚጠብቁን በቂ መረጃ አለን። ይኸው ገና ጦርነቱ ከመጀመሩ የተረዳነው እውነት ይህንኑ ነው። ሃይለስላሴ ጉግሳ ወደኛ ገብቷል። አንተ ለማን ነው ያገለገልከው? ለንጉሱ ቤተሰብ?"

ገብርኤል ጥያቄ ጣል አደረገ፣

"የኢጣልያ ፍላጎት አቢሲንያን ማስልጠን ከሆነ አገሩን በጦርነት መያዝ ለምን ያስፈልጋል? ጦርነት ሳይደረግ ስልጣኔውን ማስተላለፍ አይቻልም?"

ሳንማርኮ ፈገግ አለ፣

"የብስለት ደረጃ ላይ መድረስ የማይችል ጭንቅላት የስልጣኔ መሪ ሊሆን አይችልም።"

ገብርኤል ሳይመልስ ጥቂት ከቆየ በሁዋላ፣

"የብስለት ደረጃ ላይ መድረስ የማይችል ጭንቅላት የሚለው አባባል አልገባኝም።" ሲል ጠየቀው።

"የተናገርኩት ስለ ፊውዳሉ የአቢስንያ ስርአት ነው።"

"በብስለት ደረጃ ላይ የማይደርስ አእምሮ የሚለው አባባል ለእኛም ሲነገር ከዚህ ቀደም ስለሰማሁ ነው።"

"ሰምተህ ከሆነ የተሳሳተ አባባል ነው። አንድ አፍሪቃዊ አውሮፓውያን ሊደርሱበት ከሚችሉበት የእውቀት ደረጃ ላይ ሊደርስ ይችላል። በዚህ ዘመን ይህን መካድ አይቻልም። በቅርቡ አውሮፕላን አብራሪ ለመሆን ስለበቃው ኤርትራዊ ሰምተህ ይሆናል።

ችሎታችሁን ብንጠራጠር አይሮፕላን ባልሰጠናችሁ። የተናገርኩት ስለ አቢስንያ ፊውዳል ቤተሰብ ነው።"

አያያዘናም ቀጠለ፣

"የአቢሲንያን የፊውዳል ስርአት ለማስወገድ ኢጣልያ ሃላፊነቱን ወስዳለች። አቢስንያን ከእንቅልፏ ለመቀስቀስ መወሰኗ ለአቢሲንያና ለህዝቦቿ የምስራች ነው። በዚህ አንድ ወር ባልሞላ ጊዜ ውስጥ የኢጣልያ ሰራዊት በድል እየተጓዘ ነው።"

ገብርኤል ለምላሽ ሲዘገይ ሳንማርኮ ቀጠለ፣

"ለመሆኑ የአቢሲንያ መንግስት ዜጎቹን እንዴት እንደሚያስተዳድር በትክክል ታውቃለህ? ምንድነው ለዚህ ያበቃህ?"

ገብርኤል ቢራውን አንስቶ ተጎነጨ፣

"ማርቲኒ ለባለ-አገሩ ትምህርት ቤት መከፈቱን ይቃወም ነበር። ሞሪኖ የከፋ ሆነ። *L'Italia farà da sè.* የሚል አነጋገር ካፉ አይጠፋም። እኛ ቦታ የለንም። ኤርትራ አገራችን ናት። ሌላ አገር የለንም። በገዛ አገራችን እንደ ሁለተኛ ዜጋ ስንታይ ብንከፋ ለምን ይደንቅሃል? *L'Eritrea farà da sè* ለማለት አልበቃንም።"

ሳንማርኮ በጋለ ድምጽ ምላሽ ሰጠ፣

"የሞሪኖን አስተሳሰብ አውቀዋለሁ። በኢጣልያ መንግስት ተቀባይነት የለውም። የግሉ ነው።"

"ሞሪኖ የመንግስት ባለስልጣን ነው።"

"አይ! አሁን በሃላፊነት ላይ አይደለም። በኦሮሞ ጉዳይ መጽሃፍ እየጻፈ ነው። ቀደም ባለው ጊዜ አሳቡን ለመሸጥ መሞከሩ ግን አልቀረም። ከሞሪኖና ከማርቲኒ የከፋ አመለካከት ያላቸውም ነበሩ። ፍራንኬቲን አንተ አታውቀውም። የነደፈው ፖሊሲ ስህተት መሆኑ ታውቆ ተሰርዟል። ግለሰቦች የተለያየ አመለካከት ሊኖራቸው ይችላል። ሞሪኖ ወይም ማርቲኒን እንተዋቸውና በቀጥታ ወዳንተ ጉዳይ እንመለስ። አንተ ህይወትህን የከፈልክለት ንጉሳዊ ቤተሰብ ከራሱ የቤተሰብና የዘር ቀለበት ባሻገር ያለውን ህዝብ ከሚያይበትና ከሚያስተዳድርበት ዘይቤ አንጻር መልስ ስጠኝ?"

“አቢስንያ ሁዋላቀር ሁኔታ ውስጥ እንዳለች የታወቀ ነው።” ሲል መልስ ሰጠ። “...ዋናው ነጥብ ምንድነው? እኛ ኤርትራውያን ከአቢሲንያ በተሻለ የስልጣኔ ሁኔታ ላይ ነን ወይ? በጦርነት ወቅት ግንባር ላይ እየተሰለፍን የመጀመሪያውን ጥይት የምናስተናግደው በምን ምክንያት ነው? እኛን ለእናንተ በሚጠቅሙ ሙያዎች ላይ አስተምራችሁናል። ጠበቃና ሃኪም እንድንሆን ግን አትፈቅዱም። ሙንጣዝ፣ ብሉቹባሽ፣ ቡዝባሽ፣ ሹምባሽ ካልሆነ የጦር መኮንን ደረጃ ላይ እንድንደርስ አትፈቅዱም። የትምህርት ገደብ ተጥሎብናል። የአገልግሎት ስራዎችን ብቻ እንድንሰራ ትፈልጋላችሁ። በእንግሊዝ ቅኝ ግዛት አስተዳደር ስር ያሉ ግን የተሻለ ደረጃ ላይ እንዳሉ እናውቃለን። ለከፍተኛ ትምህርት ጭምር ወደ ለንደን ይላካሉ።”

ሳንማርኮ የትምህርቱ ጉዳይ ላይ አተኮረ፣

“የትምህርት ገደብ መጣሉ የበጀት ጉዳይ ነው።” ሲል ሞገተ። ሊያሳምነውም ሞከረ። “...ጄኔራል ጋስፓሪኒ ሲያስተዳድር እስከ 7ኛ ክፍል ፈቅዶ ትምህርት እየተሰጠ እንደነበር ታውቃለህ። ጋስፓሪኒ ተነስቶ በቦታው ጎቨርናቶረ ዳውዲያቺ ሲተካ ገደቡን እስከ አራተኛ ክፍል አደረገው። ከግለሰቦች አመለካከትና ከበጀት ጋር የተያያዘ እንደሆነ ይሄ ያመለክታል። ጎቨርናቶረ ጋስፓሪኒ የሃይማኖት አባቶችን ሁሉ አግባብቶና አስፈርሞ ትምህርት ቤት ገንብቶ ለሁሉም እኩል ትምህርት እንዲሰጥ ለማድረግ ሲጥር የከለከለው አልነበረም። ዳውዲያቺ ሄዶ አስቱቶ ሲመጣ ደግሞ ገደቡን ወደ ሶስተኛ ክፍል አወረደው። ሁለቱም አስተዳዳሪዎች የተጠና ምክንያት አልነበራቸውም። ዳውዲያቺን ተቃውመነው ነበር። አስቱቶም እንዲሁ ያልተጠና ውሳኔ እንደወሰነ በጽሁፍ ነግረነዋል። የፖለቲካ ክፍሉ ጋስፓሪኒ የተከለው መሰረት እንዲቀጥል ፍላጎት አለው። ከዚህ አንጻር የእናንተንም ግፊት አንጠላውም።”

ሳንማርኮ ፋታ ወሰደና ቀጠለ፣

“ማወቅ ያለብህ እኛ መላ ኤርትራን ከያዝን 38 አመታት ነው የሆነው። በዚህ ጊዜ ውስጥ የተሰራውን መርምር። በየትኛውም የአፍሪቃ ኮሎኒ ግዛት የኤርትራን ያህል አልተሰራም። የመገናኛ አውታሮችን ለምሳሌ ውሰድ...”

ገብርኤል አቋረጠው፣

“ከህንጻና ከመንገድ ግንባታው ባሻገር የሰው ግንባታ ላይ ትኩረት ቢደረግ እንመርጣለን ማለቴ ነው።”

“ጎን ለጎን የሚሰራ ነው። ለያይተህ የምታየው አይደለም። ኤርትራን ስንረከብ ያልተማሩ 180 ሺህ ገበሬዎች ብቻ ነው ያገኘነው። ለጉልበት ስራ እንኳ በቂ አልነበራቸሁም። አናጢና ግንበኛ ከኢጣልያ አምጥተን ነው መስራት የጀመርነው። እኛ ስንመጣ እዚህ አገር ምንም ነገር አልነበረም። ዘመናዊ ትምህርት ቤት አልነበረም። መንገድ አልነበረም። አሁን ለባለ-አገሩ የተፈቀደው የሆስፒታል አልጋ 800 ብቻ ነው የሚል ቅሬታ ይሰማል። እኛ ስንመጣ ግን ሆስፒታል ቆርቶ ክሊኒክ አልነበረም። እኛ ከመጣን በሁዋላ ነው ዘመናዊ ትምህርት ቤቶች የከፈትነው። ኢጣልያ እየላክን ያስተማርናቸው ጥቂት አይደሉም።”

ገብርኤል እንደገና አጥብቆ ሞገተ፣

“ለግለሰቦች የተሰጡ ስጦታዎች መኖራቸውን አውቃለሁ። ቅሬታዬ በፖሊሲ ደረጃ ‘ኤርትራውያን ምሁራን እንዲፈጠሩ አትፈልጉም።’ የሚል ነው። የቅሬታችን ማእከል ይሄ ነው። መማራችን ለምን ስጋት ይሆንባችሁዋል?”

“አመለካከቱ መኖሩን አልክድም። ሊሻሻል ይችላል።”

“መቼ ነው የሚሻሻለው?”

አያያዘና ቀጠለ፣

“ከነሙሉ ችግሯና ሁዋላቀርነቷ ለኛ የነጻነት ምሳሌ የሆነችው አቢስንያ ስትወረር ቢከፋን ምኑ ነው ስህተቱ?”

“ኢትዮጵያን በአርአያነት ማየት ወደሁዋላ መመለስ ነው።”

“አርአያነቷ በቴክኖሎጂ ወይ በትምህርት አይደለም። የነጻነት ጉዳይ ነው። አፍሪቃውያን በአብዛኛው በቅኝ ግዛት ስር ነን። ጥቁር ህዝቦች እንደ ኢትዮጵያ ነጻ መንግስት መመስረት ይፈልጋሉ። የአፍሪቃውያን እንቅስቃሴዎች አሉ። የወቅቱ ጥያቄ ሆኗል።”

ሳንማርኮ ስሜታዊ ሆነ፣

“አገሩን ብንሰጣችሁ ወደሁዋላ ነው የምትመልሱት። እኛ

በ38 አመታት የገነባነውን ያህል በ200 አመታትም አትሰሩትም። ነጻነት እውቀት አይደለም። አቢሲንያ ጠመንጃ መስራት ስላልቻለች በአንድ ባርያ አንድ ጠመንጃ ስትለውጥ ኖራለች። ምኑ ላይ ነው የአቢሲንያ ነጻነት? አቅምህ ባልሆነ ጉዳይ እየተናገርክ ነው።"

"አሳቤን ስለ ጠየቅኸኝ ነገርኩህ።"

ረጋ ብሎም እንዲህ አለው፣

"ለኢትዮጵያ መረጃ በማቀበሌ መጸጸቴን እንድነግርህ ጠብቀህ ከነበረ ጸጸት የለብኝም። ምህረት አገኛለሁ ብዬም አልጓጓም። ተወልጄ ያደግሁት 'ኤርትራ' በተባለች ትልቅ እስር ቤት ውስጥ ነበር። አሁን ወደ ጠባብ እስር ቤት ተዛውሬያለሁ። ልዩነት የለውም። መኖር የሚያጓጓው ከክብር ጋር መኖር ሲቻል ነው።"

ገብርኤል እንዲህ መናገሩ ልቡን ለማጀገን እንጂ በትክክል እንዲያ እንደሚያስብና እንደሚሰማው ርግጠኛ አልነበረም። በአንጻሩ ገብርኤል የመረረ ጫፍ ላይ እንደደረሰ ሳንማርኮ የበለጠ ተረዳ።

ገብርኤል ቀጠለ፣

"ኮሎኔል ሳንማርኮ! በአከብሮት ልነግርህ የምፈልገው አያቴ የሸፈተው አንድ ቀላል ስድብ ተሰደብኩ ብሎ ብቻ ከሆነ ኩራቱን አደንቃለሁ። የአያቴን ግማሽ ያህል ክብር እንኳ ለራሴ ስለሌለኝ በራሴ አፍራለሁ።"

ሳንማርኮ ጥቂት ቃላት ጣል አደረገ፣

"በዚህ ደረጃ የተማረርክበት ምክንያት ሊገባኝ አልቻለም።"

ገብርኤል እየጋለ ቀጠለ፣

"እኔ ጥሩ ኑሮና ጥሩ ስራ እንደነበረኝ ነግረኸኛል። ኤርትራውያን እለት በእለት ከሚያስተናግዱት ዘረኛ ገጽታ ይልቅ የቀድሞ ሁዋላ ቀርነታቸውን የማይመርጡ ይመስልሃል? ከኢጣልያ ስልጣኔ ምን አገኘን? ከአቢሲንያውያን ቀድመን መኪና ስለነዳን? አህያቸንን እየነዳን ከነጻነታችን ጋር ብንቀር ይሻለን ነበር። ምን እንድልህ ነው የምትፈልገው? ሞት ከፈረዳችሁበት ሰው ምን ትጠብቃለህ? ኤርትራዊው በኢጣልያውያን ግቢ ከሚደርስበት ውርደት ይልቅ ከሁዋላ ቀርነቱ ጋር በኢትዮጵያ ነጻነት የማይቀና

ይመስልሃል?”

“ስለ አቢሲንያ ምንም አታውቅም። ኤርትራውያን ከኢትዮጵያ በተሻለ የኑሮ ደረጃ ላይ ናችሁ። ሊገባህ ግን አልቻለም። ይህን ማወቅ የምትችለው ስታጣው ነው።”

ገብርኤል ይበልጥ ጋለ፣

“ህዝቡ ምንም ይሁን ምን ነጻነቱን ቢያገኝ ይመርጣል። እናንተ ከመምጣታችሁ በፊት የነበረው ህይወት ይናፍቀዋል። ይህን አውቃለሁ። እናንተ ስትመጡ ሰላም የሚያገኝ መስሎት ደግፏችሁ ነበር። ያገኘው ግን ጦርነት እና ሞት ሆነ። የማያቋርጥ ጦርነት ህይወቱ ሆነ። ሊቢያ ሄደው በጠፉት ወንድሞቻችን ስናዝን፤ አሁን ደግሞ ከኢትዮጵያ ጋር ሌላ የሞት ሰርግ ተሰረገልን። በዚህ ጦርነት ስንት ኤርትራውያን ሊያልቁ ነው? መስዋእትነቱ ምናቸው ነው? አይጠቀሙበት፣ አይከበሩበት። በታሪክ ፊትም አያኮራቸውም። ይሄን ነው ተጠቀማችሁ፣ ሰለጠናችሁ የምትለኝ? ደግሜ የማረጋግጥልህ የኛ መገዛት ሳያንስ አቢሲንያውያን ላይ የኛ እጣ እንዲደርስ ተባባሪ መሆን አልፈለግሁም። ሌላ ምክንያት የለኝም።”

ሳንማርኮ መልሶ ያንኑ ጣል አደረገ፣

“ለሚሞት ስርአት ለማገልገል የፈለግህበት ምክንያት አሁንም ቢሆን ግልጽ አይደለም። ለገዛ አገሩ ህዝብ ብሩህ ራእይ ለሌለው፤ የማሰቢያ አእምሮው ዝቅተኛ ለሆነ ፊውዳላዊ ስርአት መስራትህ አስገርሞኛል። ምን ለማግኘት? ድንቁርናና ባርነት?”

ገብርኤል ተበሳጨ፣

“መጽሃፍ ለመጻፍ ስሜቴን እያጠናህ ከሆነ ተገቢ አይደለም። ስላንተ ያለኝን በጎ አመለካከት እንደነበረ ይዤ እንድሞት ፍቀድልኝ! አታሰቃየኝ! Per favore!”

በመካከላቸው ዝምታ ሰፈነ።

ፍጹም ዝምታ።

ከጥቂት ደቂቃዎች በሁዋላ ሳንማርኮ ከተቀመጠበት ተነሳ። ወደ ከተማው መሃል ይሄዱ ዘንድ ገብርኤልን ጠየቀው። ገብርኤል ቃል ሳይተነፍስ ከተቀመጠበት ተነሳ። የሳንማርኮን አጃቢዎች

አስከትለው በእግር አዘገሙ። በመንገዳቸው ላይ ስለ ባለቤቱ አንስቶ ጠየቀው። ሉላ እንደምትባል ነገረው። ቴዎድሮስ የተባለ ወንድ ልጅ ወልደው እንደነበር፣ ገና በህጻንነቱ አምላክ እንደወሰደው ነገረው። ሳንማርኮም ስለራሱ አንስቶ የት እንደተወለደ፣ ወላጆቹ ጭሰኞች እንደነበሩ፣ ስለ ልጅነት ህይወቱ፣ ስለ አስተዳደጉ፣ ስለ ቤተሰቡ አጫወተው። አያያዘናም በጥቅሉ ስለኢጣልያ ታሪክና ፖለቲካ ተናገረ። ከአንደኛው የአለም ጦርነት በሁዋላ ስለተከሰቱ የሃይል ሚዛን መለዋወጦች አነሳ። ነምሳ ኢጣልያውያን ላይ የፈጸሙትን የግፍ ቅኝ አገዛዝ፣ ኢጣልያ ከቡርቦንና ከነምሳ አገዛዝ ተላቃ በአንድ ባንዴራ ስር እንደ አገር ከቆመችበት ከ1870 ጀምሮ ያገጠሟትን ችግሮች፤ ፈተናዎቿን ተቋቁማ ራሷን ከሰለጠኑት የአውሮፓ አገራት ተርታ ማሰለፍ ስለመቻሏ፣ ስለ ባልካን አገሮች እየዘረዘረ አወጋ።

ከአንድ የኤርትራውያን ባር ደጃፍ ላይ ደረሱ።

ደጁ ላይ ወንበሮች ተደርድረዋል። ቁጭ ብለው ቢራ አዘዙ። እየጠጡ ሳለ ሳንማርኮ ሲጋራ ለኮሰ። ለመናገር እየፈለገ መልሶ ስሜቱን ሲቆጣጠር ገብርኤል ይታዘበው ነበር። ሶስተኛውን ቢራ አዝዘው በመጠጣት ላይ ሳሉ ግን ሳንማርኮ ተነፈሰ፣

“ፈቃድህ ከሆነ ውይይታችንን ነገ እንቀጥላለን።”

ገብርኤል በቢራው ሃይል ዘና ብሎ ነበር።

* * *

በነጋታውም እንዲሁ በተመሳሳይ ሰአትና ቦታ ተገናኙ። ምግብ አዘዙ። ሳንማርኮ ኮኛክ ሲያዝ ገብርኤል ቢራ መረጠ።

“ትናንት ካቆምንበት መቀጠል እፈልጋለሁ።”

ሳንማርኮ ሲጋራውን ለኮሰና በስሱ ማገው፣

“ስለ አድዋ ጦርነት ያለህን ግንዛቤ ንገረኝ?”

ገብርኤል እንደዋዛ መናገሩን ቀጠለ፣

“ምኒልክ ራሱን ለመጠበቅ ቅድሚያ ሰጥቷል። አንተ እንዳልከው የማያውቃትን ኤርትራ ከነህዝቧ ሸጦም ቢሆን እናንተ እንዳትመጡበት ማዘግየት ችሏል። ምኒልክ ስጋት ነበረው። ኤርትራ

ላይ እንደማትቆሙ ተረድቶ ነበር። ኢጣልያ በአቢሲንያ ዙሪያ ባሉ በረሃዎች ረክታ እንደማትቆም ያውቅ ነበር። እና አድዋ ላይ ባገኙት ድል ምክንያት ነጻነታቸውን ጠብቀው መቆየት ችለዋል።"

ሳንማርኮ አክርሮ ተቃወመ፣

"ህዝቡ ነጻ አይደለም። የፊውዳሎች ባርያ ነው። በምኒልክ አስተዳደር ስር በባርነት የሚሸጡ ጎሳዎች አሉ። አንተ የሰለሞን ዝርያ ነን ስለሚሉ ጥቂት መኳንንቶች ነው የምትናገረው።"

እዚህ ላይ ገብርኤል ሉጋም ያዘ። የሳንማርኮ አባባል እውነት ሊሆን እንደሚችል አሰበ። ሆኖም ሙግቱን ቀጠለ፣

"አቢስንያ ውስጥ የጎሳዎች ጭቆና ሊኖር ይችላል። በዝርዝር አላውቅም። የውስጥ ችግራቸው ግን የራሳቸው ነው። ኢጣልያ ለምን ጣልቃ ትገባለች?"

ሳንማርኮ በመደነቅ ተናገረ፣

"ኢጣልያ ኤርትራን በሃይል ያዘች። ምኒልክ የኦሮሞንና የደቡቡን መሬት በሃይል ያዘ። ምንድነው ልዩነቱ? ሃይለስላሴ ጥቁር ስለሆነ በወረራ የተያዘውን ህዝብ እንደፈለገ ሊበዘብዝ ይችላል?"

ሳንማርኮ ቀጠለ፣

"በኢጣልያ ላይ ያለህ ጥላቻ ከኑረነቢ ጋር ስላለመያያዙ አላሳመንከኝም። በስሜት ነው የተገፋኸው። ለአቢሲንያ ፊውዳሎች ስታገለግል በስሜት እንጂ ማን መሆናቸውን አላወቅህም። ብታውቃቸው ለነሱ በመስራትህ ባፈርክ ነበር።"

"አፍሪቃ በጥቅሉ..."

"እሱን እርሳው። ስለ አፍሪቃ ነጻነት የሚለፈፈው ዘመናዊ ወሬ ባዶና ከንቱ ነው። አፍሪቃውያን ስልጣኑን ቢይዙ በገዛ ህዝባቸው ላይ ከኮሎኔ ግዛቶች የከፉ ጨካኞች ሊሆኑ እንደሚችሉ በአቢሲንያ ማየት ትችላለህ። ፊውዳሎቹ ምንም መስራት አይችሉም። በእግራቸው ስር የረገጡት ህዝብ ሁለት በደል ይሸከማል። ዘረኝነትና ሁዋላቀርነት በጥምረት ይጫንበታል።"

"ኤርትራውያን ፍትህ አጊኝተዋል ብለህ ታምናለህ?"

“አላልኩም። ትናንት ተነጋግረንበታል። ኢጣልያ በኤርትራ ላይ የዘረኛነት ፖሊሲ እንደምታራምድ በከፊል አምናለሁ። እንዲሻሻል ከሚታገሉት አንዱ ነኝ። የኤርትራውያን መብቶች እንዲከበሩ አጥብቀው የሚታገሉ ኢጣልያውያን መኖራቸውን ማመን አለብህ። በተመሳሳይ በመሳፍንቱ ጫማ ስር የወደቁት የደቡብ ሰዎች ምን ሁኔታ ላይ እንዳሉ መረዳት አለብህ። መሬታቸውን ተነጥቀዋል። ልጆቻቸው እየታፈኑ ይሸጣሉ። በአስተዳደር ውስጥ የሉበትም። ስርአቱ ራሱ ስላልሰለጠነ እነርሱም ከሰልጣኔ ጋር የመተዋወቅ እድል አላገኙም። ኢጣልያ አቢሲንያን ነጻ ስታወጣ የህዝብ ወኪሎች ስልጣን እንዲካፈሉ፣ ፍትህ እንዲያገኙና ማህበራዊ አገልግሎት እንዲሻሻል ይደረጋል።”

ሳንማርኮ ቀጠለ፣

“ከአቢሲንያውያን ጋር ሲነጻጸር በተሻለ ሁኔታ ሰብአዊ መብታችሁ ተከብሮ በመኖር ላይ ናችሁ። በፍርድ ቤት ጠበቃ ቆሞልህ፣ ተሟግተሃል። አቢስንያ ላይ እንዲህ ያለ ነገር ገና አይታወቅም። ኢጣልያ በኤርትራ ላይ ያላት ፖሊሲ ችግር እንዳለበት ደግሜ ላረጋግጥልህ እችላለሁ። እንዲሻሻል መታገል አለባችሁ። የትምህርት ገደብ መደረጉ ልክ አይደለም። ግፊት መፍጠር የናንተ ፈንታ ነው። ከጎናችሁ ሆነን ልንረዳችሁ የምንችል ኢጣልያውያንም አለን። ችግርን ለመፍታት ወደ ሌላ ችግር መግባት ግን ስህተትን በስህተት ማረም ማለት ነው።”

ገብርኤል ስሜቱ ባልታወቀ ሁኔታ ዝምታን መረጠ። ሳንማርኮም የመጣበትን ጉዳይ ወደ ማጠናቀቁ ገባ።

““...በአንተ እና በገብረማርያም ላይ የሞት ፍርዱ እንዳይጸና የግርማዊ ቪቶርዮ አማኑኤል ወኪል ተጠይቋል። እንደሚሳካ ተስፋ አደርጋለሁ። ከመሄዴ በፊት ምላሽ ካገኘሁ በድጋሚ አገኝሃለሁ።”

ሳንማርኮ ሲሰናበተው እንዲህ አለው።

“ባጭር ጊዜ ውስጥ አዲስ አበባን እንይዛታለን።”

እየሳቀና እያላገጠም ጨመረበት፣

“ደብረ ማርቆስ የነበረው የራስ ካሳ ጦር ሶስት ቀናት ‘ግራ-ቀኝ’ ስልጠና አካሂዶ ሲያበቃ ወደ ግንባር ጉዞ ላይ ነው። ይህን

ስልጠና መጀመር የነበረባቸው ከአንድ አመት በፊት ነበር። ሊግ ኦፍ ኔሽን የሚያድናቸው መስሏቸው ነበር። ነጭ ሁሉ ደግሞ አዋቂ ይመስላቸዋል። ያገኙትን ጀብደኛና የተቀበረ ሃብትና ጅል ንጉስ ካገኘሁ በሚል የተሰደደውን አውሮፓዊ ሁሉ የጦር አማካሪ ሹመት እየሰጡ ሰብስበዋል። ጥይት የሌለው የመድፍ ብረታብረት ተሸክመው ለጦርነት ተነስተዋል። ተስፋ የሚያደርጉት ጥይት ከኛ ማርከው መልሰው ሊተኩሱብን ነው። ቴክኖሎጂው እንደተለወጠ እንኳ መረጃ የላቸውም። ከእውቀት በጣም ሩቅ ናቸው።"

ገብርኤል ትንፋሹን ውጦ ማዳመጡን ቀጠለ፣

"ወዳንተ ጉዳይ ስንመለስ አንተ ወጣት ነህ። አንተን በገመድ አንጠልጥላ ሊጣልያ ምንም ጥቅም አታገኝም። በጊዜ ሂደት መሳሳትህን እንድትረዳ እንመኛለን። በቅርቡ የአዲሳባ ህዝብ ሊጣልያን በእልልታ መቀበሉን በዜና ትሰማለህ። ህይወትህን የከፈልክለት ሁዋላቀር ፊውዳላዊ ስርአት ማን እንደሆነ በቅርብ ቀን ትገነዘባለህ። ያን ጊዜ ሽማግሌውን ሳንማርኮ አስታውስ።"

ገብርኤል በረጅሙ ተነፈሰና እንዲህ አለ፣

"እባክህ ተጨማሪ መጠጥ እዘዝልኝ?"

* * *

ኮማንዳቶሬ ሳንማርኮ ወደ አስመራ ከመመለሱ በፊት ለመጨረሻ ጊዜ ገብርኤልን በተመሳሳይ ቦታ አስጠርቶ ለአጭር ጊዜ አነጋጋገረው። ቡና እና ቀላል ቁርስ አዝዘው ጥቂት አወጉ። ማለትም ገብርኤል በመጪው የህይወት ዘመኑ በፍጹም ሊረሳቸው የማይችላቸውን ቃላት ከሳንማርኮ አንደበት ሰማ፣

"ዛሬ መልካም ዜና አለኝ።" ሲል ጀምሮ እንዲህ ሲል አስከተለ፣ "...ከትናንት በስቲያ በአንተ እና በገብረማርያም ላይ የሞት ፍርዱ እንዳይጸና የግርማዊ ቪቶርዮ አማኑኤል ወኪል ፈርሟል። በአንቀጽ 556 መሰረት በውዝፍ የቆየው የሞት ፍርድ ውሳኔ ወደ እድሜ ልክ እስራት ተቀይሮላችሁዋል። ይህንኑ የሚገልጽ ደብዳቤ በቅርብ ጊዜ ውስጥ ይደርሳችሁዋል። እንኳን ደስ ያለህ!"

ገብርኤል ድርቅ ብሎ ቀረ።

በድንገተኛ የመኖር ተስፋ ውስጥ ገብቶ አይኖቹ በሩ። የልብ ምቱ ዜማውን ቀየረ። የሰራ አካላቱ ህይወት ተረጨበት። በእስር ቤት ውስጥም ቢሆን በህይወት መቆየቱ ተስፋ አሳደረበት። ጸሃይ ማየት፤ መተኛትና መነሳት፤ ጋዜጣ ማንበብ፤ ለሚቀጥሉት ብዙ አመታት በህይወት መቆየት በራሱ ትልቅ እድል መሆኑን አወቀ።

ገብርኤል ለሰማው በጎ ዜና በቃላት ምላሽ ባይሰጥም ደስታውና ተስፋው ገጽታው ላይ ይነበብ ነበርና ሳንማርኮ ቀጠለ፣

“በወር አንድ ቀን ቅዳሜ ሌሊት ከባለቤትህ ጋር አድረህ ወደ እስር ቤት እንድትመለስ ከአስተዳደሩ ጋር ስምምነት ላይ ደርሰናል። ቤትህ በምታድርበት ጊዜ ጥበቃ ይደረጋል። ወደ እስር ቤቱ የምትመለሰው ከመንጋቱ በፊት ይሆናል። ከዚህ በሁዋላ አስር ወይም አስራ አምስት አመታት እስር ቤት ልትቆይ ትችላለህ። እዚህ ሆነህ የምትሰራው ስራ የሚኖር ከሆነ የሞቅዲሾ አስተዳደር ቀስ ብሎ ያያል። ልጆች መውለድ ትችላለህ። ባለቤትህ የንግድ ስራ እየሰራች ልጆችህን ማሳደግ አይቸግራትም።”

አሁንም ገብርኤል ቃል አልተነፈሰም። የህልም አለም ውስጥ ያለ መስሎ ተሰማው። በወር አንድ ጊዜ ከባለቤቱ ጋር በመኖሪያ ቤቱ ማደር? ህልም ነው ወይስ እውነት? ልጅ መውለድ? ቀልድ ነው ድራማ? በዚያችው ቅጽበት ኮማንዳቶሬ ሳንማርኮ ከሰማይ የተላከ መልአክ መስሎ ተሰማው። ከታሰረ ወዲህ ለመጀመሪያ ጊዜ ህይወት ያለው ፈገግታ አፈለቀ።

ሳንማርኮ በትሁት ቃላት ገብርኤልን ተሰናበተው፣

“የሞት ፍርዱ እንዳይጸና በቁርጠኛነት የታገለልህ ጠበቃህ ካታንዮ ነው። ካቫሌር እያሱ የተባለ ዘመድህም ግራዝያኒ ባንተ ላይ ያሳደረውን ቁጣ ያለዝብ ዘንድ አግዟል። ግራዝያኒን ሳነጋግረው ይህንኑ አንስቶልኛል። ግራዝያኒ ለእያሱ ጥሩ አመለካከት እንዳለው ተረድቻለሁ። ዋናው ነገር እንግዲህ አንተ በህይወት እንድትቆይ ማድረግ ነበር። በዋናነት በጠበቃህ ጥረት ተሳክቷል። እኔ ያደረግሁልህ ነገር የለም። የምስጋና ቃላቶች ካሉህ ለካታንዮ ስጠው። እኔና አንተ ከዚህ በሁዋላ የምንገናኝ አይመስለኝም። አስመራ ከሄድኩ በሁዋላ በቀጥታ ወደ ኢጣልያ እመለሳለሁ። የጡረታ ጊዜዬን በመጻፍ ነው የማሳልፈው። ሁኔታዎች ከፈቀዱልኝ

ስላለህበት ሁኔታ መጠየቁ ግን አይቀርም። ደህና ሁን።"

ሳንማርኮ ከተቀመጠበት ተነሳና እጁን ዘርግቶ አቀፈው። ገብርኤልም አቅፎ በእጆቹ ጀርባውን ጠበጠበ።

* * *

ህዳር 21 ገብርኤል ሌላ ጠያቂ አገኘ።

ካቫሌር እያሱ ነበር።

በወታደራዊ ዩኒፎርም ደምቆቋል። እንደተለመደው የጉራ መንፈስ ገጽታውን አጥለቅልቆታል።

ገብርኤል በካቫሌር እያሱ ጠባይ ምንጊዜም እንደተደነቀ ነው። ሊገነዘበው ያልቻለው ነገርም አለ። ኢጣልያን አይወድም። ኤርትራ በቅኝ ግዛት ስር በመውደቋ ይቆጫል። የቅኝ ገዢዎቹ ታማኝ አገልጋይ ሆኖ ግን ይሰራል። ብዙ ኤርትራውያን እያሱን አያምኑትም። 'ሊሰልለን ነው' ይሉታል። ማስመሰል እንደሌለበት ግን ገብርኤል ያውቃል። የሚጋጩ አመለካከቶችን አንዴት በአንድ የአእምሮ ከረጢት ውስጥ ማስተናገድ እንደቻለ ግን መግለጫ አላገኘለትም።

ካቫሌር እያሱ ገብርኤልን ለመጠየቅ ሲመጣ ለአንድ አስረኛ የሚያስፈልጉ በርከት ያሉ ነገሮችን ይዞለት ነበር። ሳሙና፣ ምላጭ፣ በኢጣልያንኛ ቋንቋ የተጻፉ መጻህፍት፣ እንዲህ ያሉ ነገሮችን በወረቀት ከረጢት ሞልቶ ሰጠው። ስለ ቤተሰብ ሁኔታ አንስተው ሲጨዋወቱ ከቆዩ በሁዋላ እንዲህ አለ፣

"ነገ ወደ ኤርትራ መሄዴ ነው። ካልተገናኘን ደህና ሁን። ከኔ ይልቅ አንተ በህይወት የመቆየት እድል አለህ። በዚህ አስከፊ የጦርነት ወቅት በቤተ መንግስት ውስጥ እየተጠበቅህ ለማሳለፍ መቻልህ እድለኛ ብትሆን ነው።" ሲል ቀለደበት።

በራሱ ቀልድ ሳቀናም እንዲህ አለ፣

"እኔ እንኳ የሸዋ ዘመዶቼን መጎብኘት የቆየ ምኞቴ ነበር።"

የአነጋገሩ አሽሙር ስለገባው ገብርኤል ተከዘ።

እንዲህ ከተጨዋወቱ በሁዋላ የመሰነባበቻቸው ሰአት ደረሰ። ሲሰነባበቱ ገብርኤል፣

“አመሰግናለሁ።” አለው።

“ለምኑ?”

“መጥተህ ስለጠየቅኸኝና ግራዝያኒን ለማለዘብ በመቻልህ።”

እያሱ በመደነቅ አስተዋለው፣

“ስለዚህ ጉዳይ ማን ነገረህ?”

“ሳንማርኮ አንተንና ጠበቃዬን እንዳመሰግን ነገረኝ።”

እያሱ ጢም አልባ አገጩን አሸ።

“ያደረግሁትን ባትሰማ እመርጥ ነበር። ከሰማህ ላይቀር ግን በትክክል እውነተኛ ስሜቴን ማወቅ አለብህ። ባጭሩ ለአቢሲንያ መረጃ በማቀበልህ በጣም አዝኛለሁ። መርማሪህ እኔ ብሆን ኖሮ ጣልያኖች ከቀጠቀጡህ በላይ በነዳሁህ ነበር። ቢሆንም ግን ወንድሜ ነህ። እንድትሞት አልፈልግም። ስለዚህ ግራዝያኒን በአካል አጊንቼ ለምኜዋለሁ። የሞት ፍርዱ የተቀየረላችሁ በኔ ልመና ነው ማለት ግን አይቻልም። የጠበቃህ ጥረት ዋናው ነው። ግራዝያኒ ከተለያየ አግጣጫ ግፊት ነበረበት። ሳንማርኮ ራሱ ግራዝያኒን አነጋግሮታል። ‘ገብርኤልና ገብረማርያም ከተገደሉ ሰማእት ይሆናሉ፤ ድርጊታቸው ተጋንኖ ተከታዮች ሊያፈሩ ይችላሉ’ በሚል ዘዴ አስፈራርቶታል። ማስፈራሪያ ብቻ ሳይሆን ምናልባት ሊሆን የሚችል ስጋት ነበር። ለማንኛውም በዚያም ሆነ በዚህ መንገድ ፍላጎታችን በመሳካቱ ደስ ብሎናል። አንተም መሳሳትህን ለማወቅ እድል ታገኛለህ።”

ገብርኤል ስሜታዊ ሆኖ ተናገረ፣

“አንተም ሆንክ ሳንማርኮ ያልገባችሁ ነገር፤ የኢትዮጵያ መኳንንት ድክመት የእናንተን ወረራ ቅዱስ ሊያደርገው እንደማይችል ነው። የሳንማርኮ ይገባኛል። ያንተ ግን በጣም ያበሽቃል። ለጥቅም ስትል ብታደርገው ምንም አልነበረም። ተገደህ ቢሆንም ባልደነቀኝ። አምነህበት የምታደርገው መሆኑ ያሳዝነኛል።”

እያሱ ፈገግ አለ።

ከገብርኤል ጋር መቸም ቢሆን ሊግባቡ እንደማይችሉ የበለጠ ግልጽ ሆነለት። “መቼም ቢሆን።” ሲል አሰበ። እና ከተቀመጠበት ተነስቶ ለስንብት ተዘጋጀ፣

“እንዳልኩህ እኔ ነገ ወደ አስመራ እየሄድኩ ነው። ሶስተኛ ክፍለ ሰራዊት ተመድቤያለሁ። ከአማራ ጎራዴ ተርፌ አዲስ አበባ ከደረስኩ ደብዳቤ እጽፍልሃለሁ። ደህና ሁን!!”

ተቃቅፈው ሲሰነበባቱ ገብርኤል እንዲህ አለ፣

“እግዚአብሄር አንተንም ከአደጋ ይጠብቅህ። ሁዋላ የምትጸጸትበትን ስህተት እንዳትሰራ እጸልይልሃለሁ።”

* * *

በገብርኤልና በገብረማርያም ቴዎድሮስ ላይ ተሰጥቶ የነበረው የሞት ቅጣት ውሳኔ በንጉሱ ወኪል በጀኔራል ሩዶልፎ ግራዝያኒ ፊርማ ወደ እድሜ ይፍታህ ተለውጦ ከሞቅዲሾ ወታደራዊ ፍርድ ቤት ለሁለቱም ፍርደኞች ተላከ። ደብዳቤው የተላከው ፍርዱ ከተሰጠ ከሶስት ወራት በሁዋላ የካቲት 3 1936 ነበር።

በ1939 ታህሳስ ወር ገብርኤል ወንድ ልጅ አገኘ። ስሙንም ደበሳይ ሲል ሰየመው። ይህን ስም የመረጠው በበኩር ልጁ መሞት፤ ከዚያም ከሞት ፍርዱ የመፈጸም አደጋ አምልጦ እንደገና ልጅ ማግኘት በመቻሉ ነበር። “ደበሳይ” የሚለው የትግርኛ ቃል ትርጉሙ “አጽናኝ፣ የሃዘን መርሻ” እንደማለት ሲሆን፤ በከበሳ ኤርትራውያን ልማድ ከባድ ችግር ካለፈ በሁዋላ የሚወለድ ልጅ ብዙውን ጊዜ ይህን ስም ያገኛል።

ምእራፍ ፮

Facetta Nera - Bella Abissinia

ባለ ጥቁር ፊት - የአቢሲንያ ቆንጆ

ይዘን ስልጣኔ - መጥተናል ከአውሮፓ

ሳሊኒ ያኮና - ማርዮና ጆርጆ

ጥቅምት 2 1935 ዱቼ ሙሶሊኒ ከሮማ አደባባይ በፓላሶ ቬኒሲያ መስኮት ብቅ ብሎ የተናገረውን ገብርኤል ኤድሞንዶ እስር ቤት ሆኖ በወሬ ሰማ። ሙሶሊኒ እንዲህ ሲል ደነፋ፣

“አርባ አመታት ጠብቀናል!! ጊዜው ደረሰ።”

ንግግሩን ሲቀጥል ኢጣልያ ኢትዮጵያን ለመቆጣጠር ልትጠቀም ያዘጋጀቸውን የቅኝ አገዛዝ ዘዴ በጨረፍታ ነካ አደረገ፣

“....በይሁዳው አንበሳ መንግስት ስር ያሉ ልዩ ልዩ ጎሳዎች በኢጣልያ ባንዴራ ስር ሆነው ለመሰልጠን የሚፈቅዱ መሆናቸውን በግልጽ አመልክተዋል።”

ማርሻል ኢሚሊዮ ደ ቦኖ የመጨረሻውን ትእዛዝ ከሙሶሊኒ እየጠበቀ ነበር። 300 ሺህ ኢጣልያውያን ወታደሮች በእጁ ይዟል። በመቶዎች የሚቆጠሩ ታንኮች በተጠንቀቅ ቆመዋል። ተመሳሳይ ቁጥር ያላቸው ቦምብ ጣይ አይሮፕላኖች ለሰማይ ላይ ተልእኮ ዝግጁ ሆነዋል። ጥቅምት ሶስት 1935 ጦርነቱን ለመጀመር የቀረ ነገር አልነበረም። ጦርነቱ አድዋን ከአየር በመደብደብ

እንዲጀመር የተወሰነ ሲሆን፤ ይህም ከአርባ አመታት በፊት በሽንፈታቸው የተደመደመውን የአድዋ ጦርነት ለማስታወስ ነበር።

ሙሶሊኒ ከሮማ ፓላሶ አደባባይ በእብሪት ተነፋፍቶ የጦርነት አዋጅ ባወጀ ማግስት ካፒቴን ቻፕ አድዋን ደበደበ። በዚያችው ደቂቃ መቶ አለቃ ሞርጋንቲኒ መረብን ተሻግሮ የኢትዮጵያን መሬት ረገጠ። በዚህም የጦርነቱ መጀመር ይፋ ሆነ።

በርግጥ ሙሶሊኒ ኢጣልያ ታላቅ ጸሃያማ ኢምፓየር በአፍሪቃ ቀንድ እንደሚኖራት ለህዝቡ የገባውን ቃል በተግባር ለመተርጎም በቂ ዝግጅት አድርጎ ነበር። የአድዋን ሽንፈት በመበቀል በታሪክ ፊት የኢጣልያን ውርደት የማጠብ ፍላጎትም ቢሆን በሁለተኛ ደረጃ የሚታይ አልነበረም።

ጥቅምት 4 ዓዲግራት ተያዘች። ጥቅምት 6 አድዋ ተደገሙች። አከታትሎ የንጉሰነገስቱ አማች ደጃዝማች ሃይለስላሴ ጉግሳ ከነ ሙሉ ሰራዊቱ አጤ ሃይለስላሴን "ቻዎ!" እንኳ ሳይል ከኢጣልያ ጎን በመሰለፉ ህዳር 8 መቐለ በኢጣልያ ስር ወደቀች። የኢጣልያ ሰራዊት አንድ ጥይት ሳይተኮስበት አብዛኛውን የትግራይ ግዛት ተቆጣጠረ። ራስ እምሩ ከደብረ ማርቆስ ተነስተው፤ ዳንግላና ጎንደርን አቋርጠው ተከዜ አፋፍ ሲደርሱ 50 ሺህ ያህል ተከታይ ነበራቸው። በራስ እምሩ አንጻር የነበረው ማርሻል ፒየትሮ ባዶሊዮ በደንብ የታጠቀ፣ በደንብ የሰለጠነ፣ በደንብ የተመገበ ምሽግ ቆፍሮ የተዘጋጀ ዘጠና ሺህ ወታደሮች ነበሩት። ራስ እምሩ የማርሻል ባዶሊዮን ይዞታ ቀርቶ የራሳቸውን ተከታይ እንኳ ቁጥሩን በግምት ነበር የሚያውቁት። በጉዟቸው ላይ እህል ጭኖ ወደ ገበያ በመሄድ ላይ የነበረ ባላገር ሳይቀር፤ አሳቡን ቀይሮ ዱላ ብቻ እንደያዘ ከሰራዊቱ ጋር ተቀላቅሏል። አብዛኛው ገበሬ የዋህ ነበር። በአንድ ቀን ጣልያንን ፈጅቶ ሲያበቃ፤ ጥሩ ጠመንጃ ማርኮ ማምሻውን ወደ ቤቱ መመለስ የሚፈልገው ከጥቂት በላይ ነበር። ለዚህም ይመስላል፤ በመጀመሪያው ቀን ብቅ ያሉት የኢጣልያ የጦር አይሮፕላኖች ከሰማይ በለቀቁት ቦምብ ብዙ ሰውና አጋሰስ ሲገድሉ፤ በነጋታው ተስፋ ቆርጠው ወደቤታቸው የመልስ ጉዞ የጀመሩ ታዩ። ከተመላሾች መካከል ሹማምንት ጭምር ነበሩበት። ሃዲስ አለማየሁ "ትዝታ" በሚል ርእስ ባሳተሙት መጽሃፍ ደጃዝማች ገሰሰ በለው

በመጀመሪያው ቀን የአየር ድብደባ ተስፋ ከቆረጡት መካከል አንዱ መሆኑን ጠቁመዋል። ተስፋ ያስቆረጣቸው አይሮፕላኖችን በጠመንጃ ጥይት ለመምታት ሞክረው ሳይሆንላቸው ሲቀር ነበር።

የኢትዮ - ኢጣልያ ጦርነት በተጀመረ ማግስት ጅቡቲ የሚታተም ጋዜጣ በርእስ አንቀጹ፣ "ኢጣልያ ጊዜ ወስዳ ለጦርነት ተዘጋጅታለች። ኢትዮጵያ ግን ከአድዋ ጦርነት አቅሟ ያሻሻለችው ነገር የለም።" ሲል አስተያየት ሰጠ። አያይዞም ኢትዮጵያ ለጦርነቱ ያዘጋጀችው የሰለጠነ መደበኛ ወታደር ሰባት ሺህ ብቻ መሆኑን፤ ሌላው ያልሰለጠነ፣ የገበሬ ሰራዊት መሆኑን በመግለጽ ተቸ። ምንም እንኳ ይህ ጀሌ ሰራዊት ከአርባ አመታት በፊት አድዋ ላይ ድል የቀናው ቢሆንም፤ በዚያን ጊዜ ኢጣልያ ታንኮችና የጦር አይሮፕላኖች እንዳልነበራት በመግለጽ የጊዜውን ልዩነት ተነተነ።

ሩስያ የኢጣልያን የወረራ እቅድ ብትቃወምም እንግሊዝና ፈረንሳይ ወረራውን መርቀው ሸኝተዋታል። መስጠትና መቀበል ነበር። ኢጣልያ ከናዚ ጀርመን ጋር ተሰልፋ የጠላታቸውን ጎራ እንዳታጠናክር ለማባበል ኢትዮጵያን እንደ ስጦታ መረቁላት።

ጦርነቱ እንደተጀመረ በተከታታይ የተሰሙ ዜናዎች የጅቡቲን የጋዜጣ አስተያየት የሚያጠናክር ነበር። በተለይም ኢትዮጵያ ለጦርነቱ ምንም እንዳልተዘጋጀች መረጃዎች ይወጡ ቀጠሉ። የሃይለስላሴ ጓዳ በኢጣልያ ሰላዮች ቁጥጥር ስር መውደቁን ጉብርኤል ከጅቡቲ ጋዜጦች ሲያነብ ጥረቱ መና የቀረበትን ምክንያት ገመተ። ኢትዮጵያ በጦርነቱ ልትሸነፍ እንደምትችልም ጠረጠረ።

የኢጣልያ ከፍተኛ የጦር መኮንኖች የጦር ፕላናቸውን የነደፉት ከአመታት በፊት አገር ጎብኚ፣ ሃኪም፣ ቆንስላ፣ ቄስ እየተመሰሉ ወደ ኢትዮጵያ በመግባት ነበር። በኢትዮጵያ ዋና ዋና ከተሞች የቆንስላ ቢሮ የከፈተችው ኢጣልያ መንደሮችን ሳይቀር አውቃለች። ጦርነቱ ከመጀመሩ ከወራት በፊት ጀምሮ አዲስ አበባ በውጭ አገር ሰዎች መጥለቅለቋም አለምክንያት አልነበረም።

ኤርትራ የነበረው ሞሪሞ የኦሮሞ ተረቶችና ግጥሞችን አጠናለሁ በሚል የኦሮሞ ክፍለሃገሮችን (ኦሮሚያን) ሲያስስ ሰንብቶ ነበር። ጦርነቱ እንደተጀመረ ከ200 በላይ ጋዜጠኞች አዲስ አበባ ገቡ። እቴጌ ሆቴል የፖለቲካ መሰለቂያቸው ሆነ። አጤ ሃይለስላሴ

ምንም ማድረግ በማይችሉበት ደረጃ እጃቸውን አጣምረው ቁጭ ብለዋል። እንደ ብላታ ታከለ ወልደሃዋርያት ያሉ የወቅቱ የቅርብ አማካሪዎች የሚሰጡትን ምክርም መስማት አልቻሉም። ንጉሰነገስቱ ኢጣልያን መቋቋም እንደማይችሉ ቀድመው ሳይገነዘቡ አልቀሩም። ሆኖም ለታሪክ ፍጆታ ሲባል የተቻለውን ያህል ሞክረዋል።

በክተት ለዘመቻ የተነሳው ገበሬ የታጠቀው መሳሪያ እጅግ ሁዋላ ቀር ነበር። እነዚህም ናስማስር፣ ውጅግራ፣ ወጨፎ፣ ስናዲርና መስኩብ ናቸው። አንዳንዶቹ ጠመንጃዎች የሚጎርሱት ጥይት በአገር ውስጥ የለም። መውዜርና ዲሞትፎር የታጠቁት በአብዛኛው አለቆች ሲሆኑ፤ ለጌጥ አንጂ አይጠቀሙበትም። እንደ አድዋ ጦርነት ጎራዴና ጦር ውጤታማ ይሆናሉ ተብሎ የሚታሰብ አልነበረም።

ገብርኤል በእስር ቤት ወሬ ከማነፍነፍ በቀር ሌላ ስራ አልነበረውም። አልፎ አልፎ ብቻ እግዚአብሄር ኢትዮጵያን እንዲጠብቃት ጸሎት ያደርጋል። የእስር ቤት ጓደኞቹ ሁሉም አይነት ዜጎች ነበሩ። ኤርትራውያን፣ ሶማሊያውያን፣ ኢትዮጵያውያን፣ በእንግሊዝ ሰላይነት የተያዙ ሱዳናውያን፣ ኬንያውያን፣ የመናውያን፤ እና ሌሎችም አፍሪቃውያን ነበሩ።

የኢትዮጵያ በኢጣልያ መወረር የአፍሪቃውያን ጥቁር ህዝቦችን ትኩረት ከመሳቡም መጠነኛ ቁጣ መቀስቀስ ቻለ። ለንደን ላይ ጥቁሮች የኢትዮጵያን መወረር በመቃወም ጎዳናዎችን በሰልፍ አጥለቀለቁ። የድጋፍ ማህበር ጭምር አቆሙ። በወቅቱ በለንደን በኩል ወደ አሜሪካ በመሄድ ላይ የነበረ አፍሪቃዊ ታጋይ ኩዋሜ ንኩሩማ የኢትዮጵያን መወረር አስመልክቶ ሲናገር፣ "የአርበኛነት ስሜቴ ገነፈለ። የቅኝ አገዛዝ ስርአትን ለመዋጋት ሁሉን ለመክፈል፤ ሲኦልን እንኳ ልቋቋም ቆረጥሁ" ሲል ተናገረ።

ኤርትራውያን በየአግጣጫው ወገናዊነታቸውን ለኢትዮጵያ ገለጹ። ሁዋላ የኤርትራ መሪ ለመሆን የበቃው ኢብራሂም ሱልጣን አቆርዳት ላይ፣ "ፋሺስት ኢጣሊያ አንዲት ነጻ የነበረች አፍሪቃዊት ሃገር ወረረ።" ብሎ ሲቀሰቅስ ስለተሰማ ታስሮ ለፍርድ ቀረበ። በኢጣልያ ዘረኛነትና አድልዎ ሲሰቃይ አንድ ትውልድ ያሳለፈ ኤርትራዊ ለተወረረችው ኢትዮጵያ ወገናዊነት አሳየ። ከወረራው በፊት በኢትዮጵያ በስደተኛነት ተጠልለው የነበሩ ኤርትራውያን

በአርበኛነት ከኢትዮጵያውያን ጎን ተሰለፉ። የተሻለ የትምህርት እድል ያገኙ ኤርትራውያን ከጥቂት በላይ ስለነበሩ በዲፕሎማሲው ስራ ጭምር ንጉሰነገስቱን ያግዙ ጀመር። በዚህ መስክ ሎሬንዞ ታእዛዝና ኤፍሬም ተወልደመድህን ግንባር ቀደም ሆኑ።

አጤ ሃይለስላሴ በስደት ላይ ሳሉ ሎሬንዞ ታእዛዝ በተለይም ለሊግ ኦፍ ኔሽን የሚቀርቡ ጽሁፎችን የማዘጋጀቱን ስራ በሃላፊነት ወስዶ የሰራ ሲሆን፤ የአርበኞችን እንቅስቃሴ ለአለም ዜና በማብቃትም አብይ ድርሻ ነበረው። በአውሮፓ ብቻ ሳይሆን ወደ ኢትዮጵያ ጫካዎች በመመላለስ አርበኞች በቅንጅት እንዲታገሉ ለማድረግ ጥረት አድርጓል። ኢትዮጵያ ነጻነቷ ከተመለሰላት በሁዋላ ሎሬንዞ ታእዛዝ የኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ሆኖ ሰርቷል።

በወቅቱ ኤርትራውያን ወደ ኢትዮጵያ በብዛት ተሰደው ነበር። የተሰደዱት በአብዛኛው የትግል ሜዳ ፍለጋ ሲሆን፤ በኢጣሊያ ቅኝ አገዛዝ ዘመን ወደ ኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን ወደ ሱዳንም ይሰደዱ ነበር። ሱዳን ግን በእንግሊዝ ቁጥጥር ስር ስለነበር ለኤርትራውያን ኢትዮጵያ የበለጠ ተመራጭ አገር ነበረች።

በኢትዮ - ኢጣልያ ጦርነት የተካፈሉ ኤርትራውያንን በሁለት መክፈል ይቻላል። የኢጣልያን ወረራ በመቃወም ጠመንጃቸውን መልሰው ኢጣልያ ላይ ያዞሩ በአንድ በኩል ነበሩ። ወታደርነትን እንደ ስራ በመቁጠር እስከ መጨረሻዋ ደቂቃ ኢጣልያን በታማኝነት ያገለገሉም አሉ። ኢትዮጵያን በመውረሩ ሂደት ከኤርትራውያን ሌላ፤ ሊብያውያን፣ ሶማሊያውያን እና ኢትዮጵያውን ጭምር በኢጣልያ ሰራዊት ውስጥ ተካተው ነበር።

በኢትዮጵያ የጦርነት ታሪክ ውስጥ “የአገር ክህደት” የሚባለው ቃል ብዙውን ጊዜ አለቦታው ይገባል። ከመነሻው በወቅቱ በአፍሪቃ ቀንድ አገራዊ ማንነት ወይም ስሜት መገንባት የቻለ “አገር” ነበረ ማለት አይቻልም። ጎሳዎች የተማከለ አመለካከት አልነበራቸውም። የአንድ ደጃዝማች ወታደሮች ቀዳሚ ታማኝነታቸው ለደጃዝማቹ እንጂ “ለአገር” አልነበረም። ሃይለስላሴ ጉግሳ ከጣልያን ጋር ተስማምቶ አጤ ሃይለስላሴን ለመውጋት ሲወስን፤ ተከታዮቹ ጌታቸውን መከተላቸው ከአገር ይልቅ ታማኝነታቸው ለጌታቸው ስለነበር ነው። መኳንንቱና መሳፍንቱም

ቢሆኑ ሃገራዊ ስሜት የሚያንጸባርቁት ሲነግሱ እንጂ፤ ከመንገሳቸው በፊት ንጉሱን ለመገልበጥ ከውጭ ጠላት ጋር በቀላሉ ይተባበሩ ነበር። ከመንገሳቸው በፊት ቴዎድሮስ ከሱዳን፣ ዮሃንስ ከእንግሊዝ፣ ምኒልክ ከኢጣልያና ከደርቡሽ እየተመሳጠሩ የገዛ አገራቸውን ሲወጉ፤ የወቅቱ አስተሳሰብ ድርጊቱን "ክህደት" አላለውም።

ኢጣልያ ኢትዮጵያን እንድትቆጣጠር የተባበሩ ኢትዮጵያውያን ድርጊቱን የፈጸሙት በተራ ቅጥረኛነት ብቻ አልነበረም። የፊውዳሉን ስርአት አስተዳደር በመቃወም ጭምር ነበር። "'ኢትዮጵያ ከፊውዳሉ ስርአት ተላቃ በጣልያን ብትገዛ በተሻለ መንገድ ትሰለጥናለች፤ የኢትዮጵያ ህዝቦችም የተሻለ ፍትህና አስተዳደር ያገኛሉ' የሚል እምነት ነበራቸው። ለዚህ አመለካከት እንደ አብነት ሊጠቀሱ ከሚችሉ ኢትዮጵያውያን መካከል፣ ራስ ሃይሉ ተክለሃይማኖትና ፕሮፌሰር (ደራሲ) አፈወርቅ ገብረእየሱስ ይጠቀሳሉ። በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ እነዚህን ሁለት ግለሰቦችና መሰሎቻቸውን በክህደት የሚወነጅሉ ሲሆን፤ ውግዘቱ ሚዛን ያጣ የመሆኑ ጉዳይ ማከራከሩ አልቀረም። ተሳክቶላቸው ቢሆን ምናልባት ታሪክ በተለየ መንገድ ባስታወሳቸው። ደጃች ውቤ ደጃች ካሳን ተቋቁሞ ቢሆን ኖሮ በአጤ ቴዎድሮስ ምትክ የደጃች ውቤ ታሪክ በደመቀ ነበር። ታሪክ ምንጊዜም የአሸናፊዎች ነው። የተሻለ ራእይ የነበራቸው ተሸናፊዎች በታሪክ ውስጥ ቦታ የላቸውም።

ጦርነቱ ከመጀመሩ በፊትም ሆነ በሁዋላ ኤርትራውያን ከተለያዩ አግጣጫዎች ጀርባቸውን ለኢጣልያ እየሰጡ ኮብልለዋል። ቀኛዝማች ሰለባ ወልደስላሴ ቀዳሚው ሲሆን፤ ከጦርነቱ መጀመር ሁለት ወራት ቀደም ብሎ ከ29 ወታደሮች ጋር ከነትጥቁ ኢትዮጵያ መግባት ቻለ። ሃይለስላሴ አዲስ አበባ ላይ የክብር አቀባበል ካደረገለት በሁዋላ ሾሞ ሸለመው። አጤ ሃይለስላሴ ወደ እንግሊዝ ከሸሹ በሁዋላ እንኳ ሰለባ ወልደስላሴ በአርበኛነት ቀጥሎ ደቡብ ኢትዮጵያ ላይ እስኪገደል ድረስ የአርበኛነትን ሙያ ፈጽሟል።

ጦርነቱ ከመጀመሩ በፊት በኢጣልያ ሶማሊያ በ4000 ኤርትራውያን የተገነባ የሰለጠነ ሰራዊት ነበር። በዚያ ግንባር በጦርነቱ ዋዜማ ግራዝማች ገብራይ 12 ኤርትራውያንን ይዞ ወደ ኢትዮጵያ ሰራዊት በመቀላቀል የመጀመሪያው ሆነ። ከዚያው

ከደቡብ ግንባር ጸጋይ ንጉሴ ከ40 ቀላልና ከባድ መድፎች ጋር በርካታ ወታደሮችን ይዞ ወደ ራስ ደስታ ጦር ሲያመሩ የኢጣልያ ሞተረኛ ብርጌድ ተከታትሎ ሊያጠቃቸው ሞከረ። በተደረገው የተኩስ ልውውጥ ሞተረኞቹን አጥቅተው መለሷቸው። የተወሰኑትንም ከነትጥቃቸው ማረኩ። ኢጣልያን ለመውጋትም ከራስ ደስታ ሰራዊት ጋር ተቀላቀሉ። አብዛኞቹም በጦር ሜዳ በአርበኛነት ወድቀዋል።

ጸጋይ ንጉሴ ከገብርኤል ኤድሞንዶ ጋር ግንኙነት ከመሰረቱ ሰዎች አንዱ የነበረ ሲሆን፤ በተከታታይ ኤርትራውያን ኢትዮጵያን እንዳይወጉ የማንቃት ስራ ያካሂዱ ነበር። በዚህ በገብርኤልና በጸጋይ ንጉሴ የግንኙነት መስመር በመቶዎች የሚቆጠሩ ኤርትራውያን ከነ ትጥቃቸው ኮብልለዋል። 600 ያህል ኤርትራውያን መንገድ ስተው ኬንያ ቢገቡም በመጨረሻው ኢጣልያን የመደምሰስ ዘመቻ ላይ በእንግሊዝ ሰራዊት ውስጥ ከደቡብ አፍሪቃውያን ተዋጊዎች ጎን ተሰልፈው አዲስ አበባን ነጻ አውጥተዋል።

አንዶም ተስፋጽዮን ከመቶ በላይ የሰለጠኑና የታጠቁ ኤርትራውያን ይዞ ኢጣልያን መልሶ የወጋው ከማይጨው ውጊያ በፊት ነበር። ተንቤን ላይ ውጊያ ገጠሙ። የኢጣልያ ወታደሮች ሃይላቸውን አጠናክረው ወደ ከበባ ሊያስገቡት ሲሞክሩ አንዶም አፈገፈገ። የአንዶም ተስፋጽዮን አመጽ ለኢጣልያ መጥፎ ምልክት ነበር። መቀጣጫ ለማድረግ በማሰብ ቢከታተሉትም አልደረሱበትም። ሰሜን አርማጭሆ ላይ ሸፈተ። ሁዋላ "ስመ-ጥሩ ሓማሴን" የተባለ ማእረግ ተሸልመው ሻሸመኔ ላይ የሰፈሩት ኤርትራውያን "ኢትዮጵያን አንወጋም" ብለው ጠመንጃቸውን ኢጣልያ ላይ ያዞሩ የኢጣልያ ወታደሮች ነበሩ። ከማይጨው ጦርነት በፊት የኤርትራውያን ተቃውሞና አመጽ በዓዲግራትና በተምቤን በተናጠልና በቡድን ተስፋፋ።

በመቀጠል በገብረአብ ሓጎስ የሚመሩ ሃምሳ ኤርትራውያን ራስ እምሩን ተቀላቀሉ። ራስ እምሩ እነዚህን የሰለጠኑ ኤርትራውያን ያገኘው የገበሬ ሰራዊቱ ሽሬ ላይ ተመቶበት በተዳከመበት ወሳኝ ጊዜ ላይ ነበር። የገብረአብ 50 የሰለጠኑ ወታደሮች ሲመጡለት ራስ እምሩ ጥቂት ማንሰራራት ቻለ። በቀጥታ ወደ ስልጠና ተግባርም

አሰማራቸው። ተከታትለው ገረንከኤልና ሃይሉ የተባሉ የሌፍተናንት ማእረግ የነበራቸው ሁለት ኤርትራውያን ብዛት ያለው ጥይትና 50 አልፓይን ይዘው ወደ ራስ እምሩ መጡ። እነዚህም በቀጥታ የኢትዮጵያን የገበሬ ሰራዊት የማሰልጠን ስራ ላይ ተመደቡ።

ከማይጨው ጦርነት በሁዋላ በተለይ በርካታ ኤርትራውያን በቡድን እና በተናጠል ኢጣልያን በመተው ከአርበኞች ጋር መቀላቀላቸው እየጨመረ ሄደ። የኢጣልያ መሪዎች ኩብለላው ስላሳሰባቸው ኤርትራውያንን በጥርጣሬ ይከታተሉ ዘንድ ተገደዱ። የስለላ ስራቸውን አጠናከሩ። የስለላው መጠናከር ግን ኩብለላውን ሊቀንሰው አልቻለም። የሚከዱ ኤርትራውያን የቤተሰባቸው ንብረት እንዲወረስ፣ ሲያዙ እንዲረሽኑ ቢደረግም ቅጣቱ ሊያቆማቸው አልቻለም። በተለይ የኢጣልያ ሰራዊት የኢትዮጵያን ሃይል አሸንፎ አዲስ አበባን እንደሚቆጣጠር በታወቀበት ጊዜ ኩብለላው እየጨመረ መሄዱ ኢጣልያውያንን ያስገረመ እንቆቅልሽ ነበር።

ጦርነቱ እየገፋ ዋግ ሲደርስ አርባ ኤርትራውያን ከደጃዝማች ሃይሉ ከበደ ጦር ጋር ተደባለቁ። በተደረገው ውጊያም ሁሉም ህይወታቸውን ከፈሉ። ኢጣልያ ላይ ቆንጣጭ ጉዳት ስላደረሱ ጣልያኖች ደጃዝማች ሃይሉን በመግደል ብቻ አልረኩም። ጭንቅላቱን ቆርጠው ፎቶ ተነሱበት። ኤርትራውያን በውጊያ ወቅት በቆራጥነት እስከመጨረሻው ይፋለሙ ነበር። እጅ መስጠት ከሞት ተለይቶ ስለማይታይ ማመንታት አልነበረባቸውም።

የአጤ ሃይለስላሴ የጦር አዛጦች አራት ነበሩ። ራስ እምሩ ሃይለስላሴ፣ ራስ ሙሉጌታ፤ ራስ ካሳ ሃይሉና ራስ ስዩም መንገሻ ሲሆኑ፤ ጦርነቱን ከመሩት አራት ራሶች በተለይ የራስ ካሳ ሚና ላቅ ብሎ የታየ ነበር።

ራስ ካሳ ሶስት ወንዶች ልጆቹን ይዞ፤ እጅግ ግዙፍ ጦር እየመራ ወደ ሰሜን ሲያቀና ከፍተኛ ግምት ተሰጥቶት ነበር። በርግጥም ተምቤን ላይ በተደረገው ውጊያ ኢጣልያን የመቋቋም ብቃት አሳይቶ ነበር። ከራስ እምሩ ጦር የተሻለ ብቃት ነበረው። ራስ እምሩ በእንዳስላሴ በኩል ወደ ዓዲኳላ ሲገሰግስ በመርዝ ጋዝ ሲቀበሉት ሰራዊቱ ወዲያውኑ ተፈታ። የራስ እምሩ ዋና ተከታይ የነበረው፤ ይበልጥ በገጣሚነት የሚታወቀው የጎጃም ገበሬ ወፍ

ከሰማይ የሚያወርዱ ቅኔዎችን በዜማ እየደረደረ ወደየአገሩ ተበታተነ። የጎጃም ጦር በንጉስ ተክለሃይማኖት መሪነት ከደርቡሽ ጋር ሲዋጋም እንዲህ ያለ አደጋ ገጥሞታል። "አማራ ሲዋጋ በጀግንነቱ አይታማም። አንድ ጊዜ መፈታት ከጀመረ ደግሞ ማንም አያቆመውም።" ይባልለታል። ራስ ካሳ ሃይሉ አማካሪያቸው ለነበረው አዶልፍ ፓርለሳክ ይህንኑ ነግረውታል።

* * *

ራስ ካሳ ይተማመንባቸው ከነበሩ ተዋጊ ክንፎች መካከል በደጃዝማች በየነ የሚመራው ጦር አንዱ ነበር። የደጃዝማች በየነ ሰራዊት በኢጣልያው ሶስተኛ ክፍለጦር ከተደመሰሰ በሁዋላ የራስ ካሳ ውድቀት ግልጽ ሆነ። ማለትም የመጨረሻው መጀመሪያ ሆነ።

የኤርትራውያንን መኮብለል ለመግታት የኢጣልያ የሰራዊት አዛዦች አንድ "ድንቅ" ሊባል የሚችል መላ ዘየዱ። ካቫሌር እያሱ ያዕቆብን መሪ በማድረግ 325 ኤርትራውያንን ከሰራዊቱ በመለየት ልዩ ስልጠና ሰጧቸው። ዘዴው አደገኛ ቢሆንም ሊሳካላቸው በቅቷል። የደጃዝማች በየነን ሰራዊት በቀላሉ ለመምታት አስችሏቸዋል። የደጃች በየነ ሰራዊት መመታት የራስ ካሳን የሃይል ሚዛን እንደሚያዛባው ደግሞ ኢጣልያውያን የሰራዊት አዛዦች ቀመራቸውን ሰርተው ጨርሰው ነበር። ይህ ታሪክ የተፈጸመው ወርቅአምባ ላይ ሲሆን ነገሩ ወዲህ ነው።

እያሱ የሚመራቸው ኤርትራውያን ከደጃዝማች በየነ ሰራዊት ጋር ውጊያ ከመግጠማቸው በፊት መልእክተኛ ለደጃች በየነ ላኩበት። "እንዳትተኩሱብን፤ አንተኩስባችሁም።" የሚል ነበር። ኤርትራውያን ያለማቋረጥ ይኮበልሉ ስለነበር ደጃዝማች በየነ ይህንን መልእክት አመነ። ሊጠራጠር የሚችልበት ምክንያትም አልነበረውም።

በርግጥም ጦርነቱ ሲጀመር በእያሱ የተመራው ልዩ ቡድን የአጤ ምኒልክን ስም እየጠራ ወደፊት ገሰገሰ። የደጃች በየነ ተዋጊዎች መልእክቱ ደርሷቸው ስለነበር አልተኮሱም። በሰላም ተቀብለው ወደሁዋላ አሳለፏቸው። እናም ከኤርትራውያኑ ጀርባ ከነበሩት ኢጣልያውያን ጋር ውጊያ ገጠሙ።

የእያሱ ቡድን በዚያችው ቅጽበት ከጀርባ ተኩስ ከፈተ። ሊታመን በማይችል ፍጥነት የደጃች በየነ ሰራዊት ቀለበት ውስጥ ገባ። ከጀርባው ሲተኮስበት መረጋጋት ባለመቻሉ ይፈታ ጀመር። የዚህ ውጊያ ፍጻሜ ባጭር ጊዜ ውስጥ ታወቀ። የደጃዝማች በየነ ሰራዊት ተበታትኖ ሸሸ። ከወርቅ አምባ ያልተገመተ ፍጻሜ በሁዋላ ራስ ካሳ ድንኳን ነቅሎ ለማፈግፈግ ተገደደ።

* * *

የራስ ሙሉጌታ ሰራዊት አምባላጌ ላይ ተመትቶ ሲበተን፤ ራስ ሙሉጌታም እዚያው አምባላጌ ላይ በጀግንነት እየተዋጉ ተሰው። በመጨረሻ ተስፋ የተደረገበት የአጤ ሃይለስላሴ ሰራዊት ደሴ ገባ።

እና መጋቢት 31 የማይጨው ውጊያ ተጀመረ። በተመሳሳይ አልተሳካም። አጤ ሃይለስላሴ መድፍ እየተኮሱ ጥቂት ፎቶግራፎችን ለታሪክ ፍጆታ ካስቀሩ በሁዋላ፤ በትራሶች መካከል ደሴ ተጋድሞ የከረመውን አልጋወራሽ ከፊት አስቀድመው ንጉሰነገስቱ በፍቼ ተራሮች በኩል ተጉዘው ሚያዝያ 30 አዲስ አበባ ገቡ። በዚያኑ ቀን ሌሊት በባቡር ወደ ጅቡቲ ገሰገሱ። በመርከብ ወደ እየሩሳሌም አምርተው ሲያበቁ፤ ብዙም ሳይቆይ የብርድ ካፖርትና የቡሽ ባርኔጣ ደፍተው ለንደን ላይ ታዩ። ነባሩ የአበሻ ብሂል፣ "ተከተል አለቃህን" የሚል ነውና አብዛኞቹ መኳንንቶች የንጉሰነገስቱን መንገድ ተከተሉ።

ኢጆሌ ኤጀርሳ ጎሮ፤ የጀሚላ የመጨረሻ ልጅ፣ የጉዲና የልጅ ልጅ ልጅ፣ የይሁዳው አንበሳ፣ የእቴጌ መነን አራተኛ ባል ተፈሪ መኮንን በባቡር ጅቡቲ መግባቱ ከተሰማበት ጊዜ ጀምሮ የኩበለላው መንገድ ለሁሉም ክፍት ሆነ።

ግራዚያኒ በቆራጌ በኩል ዘልቆ ገባ። ከአጤ ሃይለስላሴ የጦር አበጋዞች ግራዝማች አፈወርቅ በጦርነቱ ሲገደል፤ ሌሎች ከደርዘን በላይ ግራዝማቾች እንደ አጤ ሃይለስላሴ በባቡር ወደ ጅቡቱ አመለጡ። ግራዝማቾቹ ነገሌ በቀላሉ ተያዘች። በመቀጠል ግንቦት 8 ሃረር በግራዚያኒ እጅ ላይ ወደቀች።

አጋዴን የነበሩት መኳንንት በባቡር ተጠቅጥቀው ጅቡቲ ገቡ። የአጤ ሃይለስላሴ ደጃዝማቾች ለውጊያ የሰበሰቡትን ገበሬ እንኳ በወግ አላሰናበቱም። ደጃዝማች ነሲቡ፣ ደጃዝማች

ሃብተሚካኤል፣ ደጃዝማች አበበ፣ ደጃዝማች አምዴ፣ ጅቡቲ ሲደርሱ አጤ ሃይለስላሴን የያዘችው መርከብ ፊቷን ወደ ሰሜን ተክላ ቀይ ባሕር ላይ እየተንሳፈፈች ነበር።

ጅቡቲ በሚሸሹ መኳንንት ተጨናነቀች።

መኮንን ሃብተወልድ፣ ፊታውራሪ ሺፈራው፣ ፊታውራሪ ታፈሰ፣ ፊታውራሪ ተሰማ በንቲ በመጨረሻው ባቡር ጅቡቲ ደረሱ። ኢትዮጵያ በጦርነት ሜዳ መሸነፏ ይፋ ሆኖ ነበር። የኢጣልያ ሰራዊት መንገድ እየጠረገ ወደ አዲስ አበባ ከመገስገስ በቀር የሚያቆመው ሃይል አልነበረም። በርግጥ ነባር ባለ አገሮች "ተሸንፈናል" ብለው አላመኑም። "ባህር ወለድ ነጭ አይገዛንም" ወይም "ኢትዮጵያ ለዘልአለም ትኖራለች" የሚል ዜማ እያንጎራጎሩ ወደ ጫካው አማተሩ። ወደ ሸለቆው፣ ወደ ዱሩ፣ ወደ በረሃው...

አጤ ሃይለስላሴ አዲስ አበባ አንድ ሌሊት ሳያድሩ ገስግሰው ጅቡቲ መግባታቸው ከተሰማ በሁዋላ ጣልያንን ለመመከት ገና ተስፋ የነበረው ገበሬም ከያቅጣጫው ጠመንጃውን ዘቅዝቆ ወደ አገሩ የሚያቀናውን መንገድ ያዘ። 400 ያህል የገነት ጦር ትምህርት ቤት እጩ መኮንኖች አዲስ አበባን ለመከላከል ደብረብርሃን ተከማችተው ነበር። ንጉሱ መሸሹን ሲሰሙ ጣልያንን ለመግታት የያዙትን ምሽግ በመተው ገለል አሉ። ስለዚህ የኢጣልያ ሰራዊት ግንቦት 5 1936 ሰተት ብሎ አዲስ አበባ ገባ።

ርግጥ ነው፤ አብዛኞቹ መኳንንትና መሳፍንት ንጉሱን ተከተለው ጅቡቲ የገቡ ቢሆንም ጥቂቶች ግን አገራቸውን ትተው ለመሰደድ መንፈሳቸው እምቢ አላቸው። ከእነዚህ መካከል ራስ እምሩ ሃይለስላሴ፣ ራስ አበበ አረጋይ፣ ደጃዝማች አበራ ካሳ፣ ደጃዝማች ባልቻ ሳፎ፣ ደጃዝማች ዘውዴ አስፋው፣ ራስ ደስታ፣ ብላታ ታከለ ወልደሃዋርያት ዋና ዋናዎቹ ነበሩ።

* * *

እያሱ ከድል አድራጊው የኢጣልያ ሰራዊት ጋር አዲስ አበባ ገባ። ከዋና ከተማዋ አዲስ አበባ ሲገቡ በእያሱ የሚመራ የኤርትራውያን ቡድን በወታደራዊ የጭነት መኪና ላይ ሆኖ አዲስ አበባን ቀወጣት። ምናልባት ከጥቂቶች በቀር ትርጉሙን

የማያውቁትን ዜማ እያዜሙ አዲሳባን ዞሩ። መሪው እያሱ ቢሆንም፤ የግጥሙ አፍላቂዎች በኢጣልያ ሰራዊት ውስጥ ተቀጥረው እስከ ሊቢያ በመዝመት ያገለገሉ አማሮች ነበሩ። ግርማቸው ተክለሃዋርያት "አርአያ" በተባለ መጽሃፉ እንደተረከው እንዲህ አዜሙ፣

የሸዋን ባንዴራ - ፈታው አሞራ
ፈታው አሞራ - ሸዌን ባንዴራ

የሸዋ ደብተራ ከጎንደር ጋር በመፎካከር ኢጣልያን የሚያወድስ ዜማ ማፍለቅ የጀመረው በዚያኑ ቀን ነበር። ፕሮፌሰር መስፍን ወልደማርያም "አዳፍኔ" በተባለ መጽሃፋቸው ላይ እንደጠቀሱት የሸዋ ደብተሮች ባንዳ ወይም አስካሪ ለመሆን ኢጣልያን በሚያወድሱ አሳፋሪ ስንኞች ተፎካክረዋል፣

በሰማይ ሲበሩ - ነፋስ አይነካቸው
በመንገድ ሲሄዱ - እንቅፋት የላቸው
በባሕር ቢሄዱ - ማዕበል አይነካቸው
ከክርስቶስ በታች - ከኛ በላይ ናቸው
እንዲህ አድርጎ ነው - አምላክ የሰራቸው

* * *

ራስ ሃይሉ ተክለሃይማኖት በፈረስ ተቀምጠ፤ በኩራት ተኮፍሶ፣ በፈገግታ ተውጦ ማርሻል ባዶልዮን አጅቦ ከአዲስ አበባ አደባባይ ብቅ አለ። ቀደም ብለው ጀምሮ በምስጢር ከኢጣልያ ጋር ግንኙነት የነበራቸው፤ ወይም ኢጣልያ ድል ካደረገ በሁዋላ የገበሩ መኳንንት ምርጥ ልብሳቸውን ለብሰው ድል አድራጊውን አጀቡ።

ከአሕመድ ኢብራሂም (ግራኝ) ዘመን ጀምሮ እንዲሁ ነበር። መኳንንቱ በአሕመድ ሲማረኩ፤ በነፋስ ፍጥነት ሃይማኖታቸውን እየለወጡ የአሕመድ ኢብራሂም ዋና ዋና የሰራዊት አበጋዞች ሆነው አገልግለዋል። ለአሸናፊው መገበር የመኳንንቱ ጥንታዊ ልማድ ሆኖ እንደመኖሩ ተራው ጀሌም ባላባቶቹን ተከትሎ ለኢጣልያ ገባ። በባርነት ስር የነበሩ ተራ ዜጎች ለኢጣልያ በወታደርነት አደሩ። የሹማምንት አሽከር የነበረ ሸዌም የራሱችን አርአያነት ተከትሎ

ለኢጣልያ በአስካሪነት ተቀጠረ። መንፈሱ ያልፈቀደለት ደግሞ ጨለማ ለብሶ ወደ ጫካ በመሄድ ከአርበኞች ጋር ተቀላቀለ። በአምስት አመቱ የኢጣልያ ቅኝ አገዛዝ ዘመን የአርበኞች ቁጥር በዛ በተባለበት ጊዜ መቶ ሺህ ደርሶ እንደነበር ይገመታ። የተማከለ አመራር ግን አልነበረውም። በጎበዝ አለቆች የሚመራ፣ ዲሲፕሊን ያልነበረው፣ ወታደራዊ ስልጠና ያላገኘ ነበር።

* * *

እያሱ በጎዳናው ዳርቻ ወጥቶ በፍርሃት፣ በመገረም፣ አልፎ አልፎም በድጋፍ ስሜት የሚመለከተው የአዲስ አበባ ህዝብ ላይ የኢጣልያን ባንዴራ አውለበለበ። ከቤቱ መውጣት ፈርቶ፤ በመስኮት አጮልቆ ጨፋሪዎቹን የሚመለከትም ይታይ ነበር። ቀስበቀስ ግን ወጣቶቹ ፍርሃታቸው እየለቀቃቸው ጨፋሪዎችን መቀላቀል ጀመሩ።

ሆታውን ተከትሎ ነጭ ፈረስ ላይ የተቀመጠ ሸማግሌ ኢጣልያዊ ብቅ አለ። ማርሻል ባዶሊዮ ነበር። የሸዋ ባለቅኔ ማርሻል ባዶልዮን እየተከተለ ውዳሴውን አዥጎደጎደ። ሁዋላ ይህ ቅኔ "የሮማ ብርሃን" ላይ ታትሟል፣

ድምጹ ሲያስተጋባ - ከሩቅ የሚሰማው
የአማኑኤል መድፉ - ወልደ ነጎድጓድ ነው
ሁለት ጊዜ ንጉስ - ሶስተኛ ቄሳር
ማን አግኝቶ ያውቃል - ያንተን ያህል ክብር?
እግዜር ላነገሰው - ለሾመው ቀብቶ
መገዛት ይገባል - ህሊናን አቅንቶ

በግጥሙ ውስጥ "አማኑኤል" የሚል መግባቱ የኢጣልያን ንጉስ አማኑኤል ቪቶርዮን ለማሞገስ ነበር። የማርሻል ባዶሊዮ አጃቢዎች የማርያ ቴሬዛን ገንዘብ ግራና ቀኝ መርጨት ሲጀምሩ በፍርሃት በር ዘግቶ የነበረው አዲሳበቤ ወደ ጎዳናው መጉረፍ ጀመረ። ከልጆች አልፈው አዋቂዎች ጭምር የሚበተነውን ማሪያ ቴሬዛ ለማግኘት ተሻሙ።

በ1936 መጨረሻ የኢትዮጵያ ከተሞች ሙሉ በሙሉ በኢጣልያ ቁጥጥር ስር ገቡ። ገጠሮች፣ በረሃዎችና ጫካዎች ግን

በአርበኞች ተሞሉ። ራስ እምሩ የአርበኞች መሪ ሆኖ ብቅ ብሎ ነበር። በተደራጀና ባልተደራጀ መልኩ አርበኞች ኢጣልያን ለመቋቋም በተለያዩ አግጣጫዎች ተሰማሩ።

ደጃች ባልቻ ሳፎ ወደ ጉራጌ ሄደ። ብላታ ታከለ ወልደሃዋርያት ሊሙ ገባ። አበበ አረጋይ ወደ ጌድዎን መረጠ። ዘውዴ ወደ ሙሎ ሲያቀና ራስ እምሩ ሃይለስላሴ ወለጋ ገባ። ራስ ደስታ ዳምጠው ሲዳሞን ሲይዝ፤ ደጃዝማች አበራ ካሳ ሸዋ ቀረ።

እንዲህ ተከፋፍለው ጣልያንን ማበሳጨት ቀጠሉ። በሁሉም ዘንድ ኤርትራውያን ነበሩ። ጎንደር አካባቢ ብቻ የኢጣልያን ወረራ በመቃወም የኢትዮጵያን አርበኞች የተቀላቀሉ ኤርትራውያን ቁጥራቸው 650 ደርሶ ነበር። በወቅቱ የኢትዮጵያ አርበኞች ዘመናዊ የነበሩትን የኢጣልያ ጠመንጃዎችና መድፎች የመጠቀም ችግር ነበረባቸው። ኤርትራውያን በየግንባሩ አርበኞችን ማሰልጠን ዋና ስራቸው ሆነ። ሊቢያ የዘመቱ ኤርትራውያን አረብኛ ቋንቋ ያውቃሉ። አብዛኞቹ ደግሞ ጣልያንኛ ይናገራሉ፤ ያነባሉ። ዜናዎችን እየሰሙ አርበኞችን ከወቅታዊው ሁኔታ ጋር ማሳወቅና ማንቃት የስራ ድርሻቸው ሆነ።

ታህሳስ 1936 ራስ እምሩ ተያዙና ወደ ጣልያን ተላኩ። ራስ እምሩ ከተያዙ በሁዋላ ለጥቂት ጊዜ ሰብሳቢ መሪ አልነበራቸውም። ሁዋላ ግን አርበኞች የራስ ካሳን ልጆች አበራ፣ አስፋወሰንና ወንደሰንን በማስቀደም ማንሰራራት ጀመሩ። በላይ ዘለቀ፣ ጃጋማ ኬሎ፣ ገረሱ ዱኪ፣ ራስ አበበ አረጋይና ራስ መስፍን ስለሺም የአርበኝነት ትግሎ የወለዳቸው መሪዎች ሆነው ብቅ አሉ።

(ከ1936 እስከ 1941 ባለው ጊዜ አርበኞች የልጅ እያሱን ልጆች በመጠቀም የተለያየ እንቅስቃሴዎችን ለማድረግ ሞክረዋል። ዮሃንስ እያሱ በጌምድር ላይ ንጉሰነገስት ተባለ። ግርማ እያሱ ኬንያ ስደተኛ ጣቢያ ነበር። በምግብ ተመርዞ ተገደለ። አበበ አረጋይ መልዐከጸሃይ የተባለውን አንግሶ ሲያበቃ፣ መልአከ ጸሃይ መልሶ ለአበበ "ራስ" የሚል ማእረግ እንዲሰጠው አደረገ። ምኒልክ እያሱ በፈረንሳይ ጥበቃ ስር ታጁራ ነበር። ፊታውራሪ ተክለሃዋርያት ተክለማርያም ምኒልክን ሊጠቀምበት ሞክሮ አልተሳካለትም። ከኢጣልያ መወገድ በሁዋላ መኢሶ ላይ የእርሻ ስራ እንዲሰራ ተፈቀደለት። ቴዎድሮስ እያሱ በ1941 ጋምቤላ ሆኖ ንጉሰነገስት የሚል ማእረግ ጭኖ ነበር።

በአካባቢው ጸረ ኢጣልያ እንቅስቃሴ ያደርጉ በነበሩ ቤልጂማውያን ተመዶ ተማረከ። ከዚያ በሁዋላ የእሥሱ ልጅ የደረሰበት አልታወቀም።)

አርበኞች የመጀመሪያው ጠንካራ ሊባል የሚችል የማጥቃት ሙከራ ያደረጉት አዲስ አበባ ላይ ነበር። አሳባቸው በአምስት አግጣጫ አዲስ አባባን ማጥቃት ነበር። ማለትም አበበ አረጋይ በአምቦ፣ አበራ ካሳ በሰላሌ፣ ዘውዱ እና ባልቻ ሳፎ በልደታ፣ ፍቅረማርያም በኡራኤል፣ ሊያጠቁ እና አዲስ አበባን በቁጥጥር ስር ለማዋል ነበር እቅዱ።

ሃምሌ ወር 1936 ነበር።

አዲስ አበባን ከበው ለማደር በወሰኑበት ሌሊት ግን ከባድ ዝናብ ሲዘንብ አደረ። በጎርፍ ምክንያት በቀጠሯቸው መድረስ አልቻሉም። ወንዞች ሞልተው ለመሻገር የሚቻል አልነበረም። በርግጥ ደጃዝማች ባልቻ እና ደጃዝማች መስፍን በቀጠሯቸው መድረስ ችለው ነበር። ደጃች አበራም በቀጠሮው ቦታ ደርሶ ነበር። ለማጥቃት እንደ ምልክት እንዲሆን አስቀድመው የተነጋገሩበት ተኩስ ባለመሰማቱ ግን እቅዱ ከሸፈ።

ምእራፍ 7

በሸለቆ ጋራ - በበረሃ በዱሩ
ገድለው እየሞቱ - በእሩምታ ዘመሩ

አዲስ አበባ ላይ የተሞከረው የከበባ ማጥቃት ከከሸፈ በሁዋላ ማርሻል ሩዶልፎ ግራዝያኒ ሶስቱን የራስ ካሳ ልጆች መማረክ የመጀመሪያ ኢላማው በማድረግ በጥበብ ተንቀሳቀሰ። ለዚህም የጎጃሙ ራስ ሃይሉና የትግራዩ ራስ ስዩም መንገሻ ተባበሩት። አስገራሚው ነገር በተለይ ሁለቱ ራሶች ከራስ ካሳ ልጆች ጋር በጋብቻ የተዛመዱ መሆናቸው ነበር። ዳሩ ግን ከፍተኛ ደሞዝ እየተከፈላቸው በኢጣልያ ጓዳ የቅምጥል ህይወት ስለቀጠሉ ለመታዘዝ ዝግጁ ነበሩ።

ደጃዝማች አበራ ካሳ በተምቤን ጦርነት ኢጣልያን ክፉኛ ተፋልሟል። የኢትዮጵያ ሰራዊት ከተሸነፈ በሁዋላም በአርበኛነት ቀጥለዋል። አባታቸው ራስ ካሳ አጤ ሃይለስላሴን ተከትለው ሲሸሹ፤ አራት ወንድ ልጆቻቸውን ይዘው ለመሄድ ቢፈልጉም አልተሳካላቸውም ነበር። ሁለቱ ልጆች መጨረሻቸው ባያምርም ታሪክ ለመስራት ሞክረዋል። የግራዝያኒን አስተሳሰብ አለማወቃቸው ለአሳዛኝ እድላቸው አስተዋጽኦ አድርጓል። ማርሻል አዶልፎ ግራዝያኒ የሚታወቅባት አንድ አባባል ነበረችው። ይቅርታ ያደረግህለት ጠላት፤ ከሺህዎች ጠላቶችህ በላይ አደገኛ ነው። (An Enemy for-

given is more dangerous than a thousand foes)

ግራዝያኒ በሁለቱ ራሶች በኩል ከራስ ካሳ ልጆች ጋር ግንኙነቱን ቀጥሎ ሰነበተ። ደጃዝማች አበራ ካሳ በተለይ የማረካቸውን ስድስት ኢጣልያውያን ለኢጣልያ መልሶ እስከ መላክ ደረሰ። በዚህ ድርጊቱ የተከታዮቹን እምነት ቢያሳጣውም፤ ድርጊቱ ከግራዝያኒ እንደሚያስታርቀው ገምቶ ነበር።

ጥር 21 1936 የግራዝያኒ ሰራዊት መርሃቤቴ አካባቢ ደጃች አበራና ደጃች አስፋወሰንን መክበብ ቻለ። ከከበባው በሁዋላም የማግባባት ስራ መስራት ጀመሩ። ደብዳቤዎች ተላላኩ። ግራዝያኒ ለደጃዝማች አበራ ካሳ በጻፈው ደብዳቤ እንዲህ አለ፣

“በራስ ሃይሉና በደጃች አመዴ በኩል የጻፍክልኝን ደብዳቤ አይቼዋለሁ። እንደምታውቀኝ አውቃለሁ። ከዚህ በሁዋላ በደንብ እንደምታውቀኝም አምናለሁ። ቃሌን የማላጥፍ ሰው መሆኔን የዚህ አገር ሰዎችም በደንብ ያውቃሉ። እጅህን ስጥ። በዚህም ባንተ ላይ የሚደርስ ምንም ጉዳት እንደማይኖር አረጋግጥልሃለሁ።

“...የተዋጋኸው ለሃገርህ ነው። በዚህ ደግሞ የሚወቅስህ የለም። እግዚአብሄር የፈቀደው ሆኗል። ይህም ለኢትዮጵያ መልካም እድል ነው። ለማይረባ ነገር ለምን ትሞታለህ? ወንድምህ ወንደሰንም እንዲመጣ ደብዳቤ ጽፌለታለሁ። ከተከበበበት ከላሊበላ እጁን ሰጥቶ ወደዚህ ይመጣል። ስለዚህ አንተም ያለመዘግየት ወደ አዲስ አበባ መምጣት አለብህ።”

ደጃዝማች አበራ ከሁለት አግጣጫ ምክሮች መካከል ተቀረቀረ። ራስ ሃይሉ ከአዲስ አበባ እጁን እንዲሰጥ ወተወቱት። መስፍን ስለሺ ግን ሁለቱ ወንድማማቾች ማለትም አበራና አስፋወሰን እጃቸውን እንዳይሰጡ መከራቸው። ሲያወላውል ከሰነበተ በሁዋላ ደጃች አበራ ወደ ራስ ሃይሉ ምክር አዘነበለ። እና ታህሳስ 21 1936 ከወንድሙ ጋር እጃቸውን ሰጡ።

አበራ እና አስፋወሰን እጃቸውን ለመስጠት መስማማታቸው ለማርሻል ግራዝያኒ መልካም ዜና ነበር። በዚያኑ እለት ተስያት ካቫሌር እያሱ የሚገኝበትን ቡድን ወደ መርሃቤቴ ላከ። በነጋታው እያሱ የራስ ካሳን ደጃዝማቾች ተረከበ።

በትእዛዙ መሰረት ወደ ፍቼ ተወሰዱ።

በጉዞ ላይ ከአንድ ጫካማ ስፍራ ሲደርሱ መኪኖቹ ቆሙና የራስ ካሳ ልጆች እጆቻቸውን የፊጥኝ ታሰሩ። ከማርሻል ግራዝያኒ ተገናኝተው የክብር ግብኣ እንደሚደረግላቸው ሲጠብቁ ለነበሩት ልጆች ይህ እርምጃ ፍጹም ያልጠበቁት ሆነባቸው።

እያሱ ደጃዝማቾቹን ካሰረ በሁዋላ ወደ ፍቼ እንዲገባ የታዘዘበትን ሰአት እየጠበቀ ቆየ።

ደጃዝማች አበራ ካሳ ምን እየተደረገ እንዳለ ለማወቅ እያሱን መወትወት የጀመረው ገና እጁን ጠምዝዘው አስረውት ሳያበቁ ነበር። አንድ ስህተት እየተሰራ መሆኑን በመገመቱ፣

“በፈቃዳችን ነው እጃችንን የሰጠነው። ማርሻል ግራዝያኒ በገቡልን ቃል መሰረት ነው እጃችንን የሰጠነው።” ሲል ወተወተ፣ “... ማርሻል ግራዝያኒ ሳያውቁ እኛ ላይ ጉዳት ብታደርሱ ትጠየቁበታላችሁ። ማርሻል ግራዝያኒ የላኩልንን ደብዳቤ ይዘናል!”

እያሱ በሃዘን አስተዋላቸው። አስፋወሰን በተለይ ተጨነቀ።

“ወገናችሁ ነን፤ ወንድሞቻችሁ ነን? አትግደሉን” አለ።

እያሱ ምላሽ ሰጠ፣

“ምህረት ማድረግ የኔ ስልጣን አይደለም። የማርሻል ግራዝያኒን ትእዛዝ በመፈጸም ላይ ነኝ።”

ደጃዝማች አበራ ለዘብ ብሎ ተናገረ፣

“አታለውናል ማለት ነው?”

“ይመስለኛል።”

ደጃች አበራ በቁጭትና በእልህ አጓራ። እና እንዲህ አለ፣

“እንድናመልጥ ከረዳኸን መንግስታችን ሲመለስ ሹመት ታገኛለህ። ንጉሱና አባቴ ውለታህን ይመልሳሉ።”

እያሱ በመደነቅ ጠየቀ፣

“በርግጥ ግራዝያኒን አምናችሁ ነው የመጣችሁት?“

“ራስ ሃይሉ ናቸው ያግባቡን።” አለ አበራ።

አስፋወሰን የስቃይ ድምጽ አወጣ፣

“የሰላሌ ጦርም እየከዳን ነበር። ጣልያን የቋንቋ ጉዳይ ሲያነሳ ልባቸው እሁለት ተከፈለና ከኛ አፈገፉ።”

“እንደ ንጉሱ ወደ ስደት መሄድ አይሻላችሁም ነበር?”

“ተከበን ነበር። ሱዳን መድረስ የሚቻል አልነበረም። መሞከር እንኳ ይቻል ነበር። ተሞኝተናል። ፈቃድህ ቢሆን ግን አንተ ህይወታችንን ማዳን ይቻልሃል።”

“አልችልም።” ሲል ቁርጡን ነገራቸው፣ “...ተጻጽፋችሁ እጅ ከሰጣችሁ ወዲያ እኔ ምንም ላደርግ አልችልም።”

እያሱ እንደማያግዛቸው ሲያውቁ የሚደርስላቸው ቢገኝ በሚል ይመስላል ጫካውን በአይናቸው አሰሱ። በእሩቅ ሆኖ የሚያቅራራ የአውሬ መንጋ እንጂ፤ ሌላ ድምጽ አልነበረም። የሚታይም የለም። የኦሮሞ መሬትና አገር ጸጥ እንዳለ ነበር።

ደጃዝማች አበራ እንደገና ለዘብ ብሎ ተናገረ፣

“ስለ ነገ ከአምላክ በቀር የሚያውቅ የለም። እኛን ካዳንክ ለኢትዮጵያ ህዝብ ውለታ እንደዋልክ ይቆጠራል።”

እያሱ ዘወር ብሎ በመገረም አበራን አጤነው።

ምንም መልስ ሳይሰጥ ዝም አለ።

ደጃዝማች አበራ እንደገና ተናገረ፣

“ምን ልታደርጉን ነው?”

“አላውቅም።”

“ራስ ሃይሉና ራስ ስዩም ከዱን።” አለ አስፋ ወሰን።

እያሱ በቁምነገር እርማት ሰጠ፣

“ራስ ሃይሉና ራስ ስዩም የከዷችሁ አይመስለኝም። ምናልባት ሊቀበሏችሁ ሙከት አርደው እየጠበቋችሁ ይሆናል።”

እና እያሱ በቁምነገር እንዲህ አለ፣

“ይልቁን ተምቤን ላይ ያደረጋችሁት ውጊያ የሚደነቅ ነበር። ግን ለምን ሳትቀጥሉት ቀራችሁ? በርትታችሁብን ነበርኮ?”

“አጤ ሃይለስላሴ ፍላጎታቸው በእርቅ መጨረስ ነበር።”

“እንግሊዞች ከናንተ ወገን ይመስሏችሁ ነበር?”

“እንደሱንኳ አላሰብንም። አቅማችንን በመገመት ነው። ንጉሱ የእርቅ መንገድ ይፈልጉ ነበር መሰለኝ።”

“ምን አይነት እርቅ?”

“ትግራይና ኣጋዴንን ለጣልያን ለመተው ነበር የታሰበው።”

እያሱ በረጅሙ ሳቀ።

“ሙሶሊኒ ‘በረሃ አግበስባሽ አይደለሁም’ ስለ ማለቱ አልሰማችሁም? ሙሶሊኒ ልቡ ከኦሮሞ መሬት ላይ ነው። ኢጣልያ በህዝብ ብዛት ልትፈነዳ ደርሳለች። እህል የሚያመርት ገበሬ የሚያሳርፍበት ቦታ ነው የቸገረው። ትግራይና ኣጋዴን ምን ያደርግለታል? አክሱም የሚያስፈልጋችሁ ለእናንተ ነው።”

ደጃዝማች አበራ ትእግስቱ አለቀ፣

“ስላለፈ ነገር መናገር ምን ያደርጋል? ህይወታችንን የምታድን ከሆነ ታሪክ ስራ። ታሪክ ሰሪ መሆን የሚቻለው እንዲህ ባለ ጊዜ ነው። ይሄ ላንተ ጥሩ ኣጋጣሚ ነው። ስምህ ለዘልአለሙ ህያው ሆኖ ተከብሮ ይኖራል።”

እያሱ እንደገና ሳቀ፣

“እናንተን በማዳን ታሪክ ሰሪ የመሆን አሳብ የለኝም። ገበታችን አንድ ላይ አይደለም።”

“ምን ማለትህ ነው?” አለው አበራ።

በአድዋ ጦርነት ጊዜ ደጃዝማች ካሳ ስለሚባል ወጣት ባላባት ክፉ አነጋገርና የጭካኔ ልብ አባቱ የነገረውን ፈጽሞ የሚረሳው አልነበረም። በርግጥ የእነዚህ ሁለት ደጃዝማቾች አባት በአድዋ ጦርነት ስለመካፈሉ፤ በወቅቱ ወጣት የነበረው ደጃዝማች የእነዚህ ወጣቶች አባት ስለመሆኑ ርግጠኛ አልነበረም። ሊጠይቃቸው ካሰበ በሁዋላ ካፉ መለሰው።

አስፋወሰን ተስፋ ባለመቁረጥ እንደገና ሞከረ፣

“ከዚህ ሞት ብታድነን ኢትዮጵያ ውለታህን ትመልሳለች።”

እያሱ መልስ አልሰጠም። ሰአቱን አየ። ወደ ፍቼ እንዲገባ የታዘዘበት ሰአት ደረሰ። እናም ሶማሊያዊውን ሹፌር ወደ ፍቼ እንዲነዳ አዘዘው። ከጥቂት ደቂቃዎች በሁዋላ የራስ ካሳን ልጆች የያዘችው መኪና በታጣቂዎች እንደታጀበች ፍቼ አደባባይ ደረሰች።

በፍቼ ገበያ ከቆሙት ሶስት የመስቀያ ማማዎች አጠገብ ሲደርሱ አበራ እና አስፋወሰን ምን እየተካሄደ ለመረዳት እንኳ ጊዜ አላገኙም። አንድ ተጨማሪ ሰው ታክሎ ገመዱ በአንገታቸው ገባላቸው። የአካባቢው ኦሮሞ ተሰብስቦ እየጠበቀ ነበር። የራስ ካሳ ልጆች እንደሚሰቀሉ ወሬው በመሰማቱ ገበያው ሞቋል፤ ደምቋል። የሶስተኛው ሰው ማንነት አከራከረ። ወንድ በወሰን የተባለው የራስ ካሳ የመጀመሪያ ልጅ መሆኑን አንዳንድ ሰዎች ተናገሩ። እውነት ግን አልነበረም። ወንድ በወሰን ከሁለት ቀናት በፊት ላስታ ላሊበላ ላይ ከኢጣልያ ጋር ሲዋጋ ተገድሎ ነበር። ስለ ሶስተኛው ሰው ማንነት ርግጡን የሚያውቅ አልነበረም። የገበያተኞች ትኩረትም በቅርብ ከሚያውቋቸው አበራና አስፋወሰን ላይ ነበር።

ገበያተኛው ስቅላቱን ለማየት ተጋፋ።

አንዳንድ ሴቶች ሲያለቃቅሱ ታዩ። አብዛኛው ግን በድጋፍ እየጨፈረ ነበር። የሚቆጭ አልታየም። የተቆጨ አንድ የታጠቀ ሰው ባአካባቢው ቢኖር ችግር ለመፍጠር እድል ባገኘ ነበር። መሬታቸውን ነጥቀው በጭቆና ሲገዟቸው የነበሩ ባላባቶች ሲሰቀሉ ለማየት የፍቼ ኦሮሞች መጓጓታቸው የሚጠበቅ ነበር።

በአንድ ኢጣሊያዊ የመቶ አለቃ መሪነት የስቅላት ስነስርአቱ ያለምንም እንቅፋት ተከናወነ። ወታደሮች ገመዱን በሶስቱ አርበኞች አንገት ካስገቡ በሁዋላ ካቫሌር እያሱ ጠመንጃውን እንደታጠቀ ተጠግቶ የኑዛዜ ቃል ይኖረው እንደሆን ደጃዝማች አበራን ጠየቀው። ገጽታው እንደጠቆረ ጥቂት ቃላት ተናገረ፣

“እጅ መስጠታችን ህዝብ እንዳናስጨርስ ብለን እንጂ በፍርሃት አይደለም። በኛ ሞት ህዝብ ከተረፈ ታሪክ ያስታውሰናል።”

እያሱ፣ “ይህንኑ ለራስ ሃይሉ እነግራለሁ።” አላቸው።

እያሱ በቀጥታ ወደ ኢጣልያዊ አለቃው ሄዶ የኑዛዜውን ቃል ነገረው። ከዚህ በሁዋላ የቀረው የቆሙበትን ጠረጴዛ ማንሳት ነበር። ዳሩ ግን ጠረጴዛውን በማንሳት ፈንታ በእሩምታ ተኩስ እግሮቻቸውን በጥይት አደቀቁት። መቆም ሲያቅታቸው ተንጠለጠሉ። ሸምቀቆው በአንገታቸው ጠበቀ።

ከዳር እዳር የህዝብ ጫጫታ ተሰማ።

የራስ ካሳ ልጆች መንፈራገጣቸው አብቅቶ ሲዝለፈለፉ እያሱ የእጆቻቸውን ደም ስር በመንካት መሞታቸውን አረጋገጠ። ከዚያም ስቅላት ለመመልከት የተሰበሰበውን የፍቼ ገቢያተኛ ሰንጥቀው ወደ አዲስ አበባ የመልስ ጉዞ ሆነ። ጫንቃው ላይ የተጫኑበት መሳፍንት በመወገዳቸው የፍቼን ገቢያ የከበበው ኦሮሞ ገበሬ ደስታውን በጭፈራና በሆታ መገለጽ የጀመረው የፋሺስቱ ቡድን ገና አካባቢውን ሳይለቅ ነበር።

(ሁዋላ እንደታየው ግን የማርሻል ግራዝያኒ እርምጃ የአርበኞችን ትግል የሚያዳክመው አልሆነም። የግራዝያኒ የማታለል ተግባር እነ ጃጋማ ኬሎ፣ እነ ሃይለማርያም ማሞ እና ራስ አበበ አረጋይ ጸንተው ትግላቸውን እንዲቀጥሉ አደረጋቸው። በዚያው ሰሞን ግራዝያኒ ከአብርሃ ደቦጭሙና ከሞገስ አስገዶም የመግደል ሙከራ አምልጦ በግዕዝ የዘመን አቆጣጠር የካቲት 12 የአዲስ አበባ ነዋሪ ላይ ጅምላ ጭፍጨፋ ካካሄደ በሁዋላ ደግሞ አርበኞች ከከተማ በጎረፈ የሰው ሃይል ተጥለቀለቁ። የደጃዝማች አበራ ካሳ ባለቤት ከበደች ስዩም የበረኸኞች መሪ ሆና ብቅ አለች። ይህች ሴት የአጼ ዮሃንስ ዘር፣ የትግራዩ የራስ ስዩም መንገሻ ልጅ ነበረች። ታሪኳ ግን ብዙም ሳይነገር ተቀብሮ ቀርቷል።)

ምእራፍ 8

እንዴት ነህ ወገኔ?

ከጥቂት ተስፋ ጋር - ደናኔ አለሁ እኔ !

ገብርኤል ኤድሞንዶ የኢጣልያን ወረራ እና የአርበኞችን ትግል በመከታተል ጊዜውን ከማሳለፍ በቀር ሌላ ሊሰራው የሚችለው ነገር አልነበረውም። ወደ ደናኔ እስር ቤት ከሚመጡት እስረኞች ጋር እየተገናኙ ስለ ወደፊት እጣቸው፤ ስለ አካባቢያቸው፣ ያወጋሉ። ሲመቸው ባጭር ባጭሩ ማስታወሻ ይይዛል።

ኤርትራውያን እየኮበለሉ ወደ ይርጋአለም በመጠጋት ላይ ወደነበረው የራስ ደስታ ሰራዊት እየተቀላቀሉ ነበር። ግራዝማች ገብራይ ከ12 ኤርትራውያን ጋር ኮበለለ። ገናሌ ላይ ውጊያ ይደረጋል ተብሎ እየተጠበቀ ነበር። በአንድ ሌሊት ብቻ 904 ኤርትራውያን ኮብልለው አደሩ። በኮሎኔል ሞራማርቾዮ የሚመራው አራተኛው ብርጌድ ባዶውን ቀረ። ብርጌዱም ወደተለያዩ ክፍሎች እንዲበተን ግራዝያኒ አዘዘ። ኩበለላውን የመሩት ጸጋይ ንጉሴ እና ገብራይ ከገብርኤል ኤድሞንዶ እና ከገብረማርያም ቴዎድሮስ ጋር ግንኙነት ይኖራቸው እንደሆን እንዲፈተሽ አዘዘ። በኩበለላ የሳሳው የሰራዊቱ ክፍልም በሊቢያውያን እንዲተካለት ጠየቀ።

ገብርኤል ወር በገባ በመጀመሪያው ቅዳሜ ወደ ባለቤቱ ሄዶ አንድ ሌሊት ያሳልፋል። ይህም በጉጉት የሚጠበቅ ወርሃዊ

ቀጠሮ ነው። ጦርነቱን በተመለከተ ለገብርኤል ወሬ መንገር የሚፈልጉ ወደ ሉላ ኪዮስክ ብቅ ይላሉ። በተለይ የቢራና የሻይ ደምበኞቿ ከጥቂት በላይ ነበሩ። እነዚህ ደምበኞች የሰሙትን ዘርገፈው ይሄዳሉ። ሉላ የሰማችውን ሁሉ በአእምሮዋ ልቅም አድርጋ በመያዝ ገብርኤል ሲመጣ አንድ ባንድ ትነግረዋለች። ጸጋይ ንጉሴ ኤርትራውያን ወታደሮችን ይዞ ኢትዮጵያ መግባቱን የነገረችው ሉላ ነበረች። በዚህም ገብርኤል በጣም ተስፋ አደረገ። ያለ ኤርትራውያን ተሳትፎ ኢትዮጵያ በጦርነቱ መሸነፏ የማይቀር ቢሆንም እንኳ፤ ኤርትራውያን ኢትዮጵያን በሚጎዳ ተግባር እጃቸውን መክተት እንደሌለባቸው በጥብቅ ያምን ነበር። ጣልያን አንድ ቀን ወደ አገሩ እንደሚመለስ፤ ኢትዮጵያ እና ኤርትራ ግን ምንጊዜም በጉርብትና የሚኖሩ ህዝቦች ናቸው ብሎ ስለሚያምን በጊዜያዊ ነገር ህዝቡ ደም መቃባቱን እንዳይቀጥል ይጨነቅ ነበር።

ገብርኤል በእስር ቤት በርካታ መረጃ የሚያገኝባቸው መንገዶች ነበሩት። አዳዲስ እስረኞች ሲመጡ፤ እስከተያዙባት እለት ድረስ የተፈጸመውን ለነባር እስረኞች ይተርኩላቸዋል። በተለይም ኢትዮጵያውያን በብዛት መምጣት ሲጀምሩ ገብርኤል አማርኛ ቋንቋ ለመስማት ጥረት ማድረግ ጀመረ። ጅቡቲ የሚታተሙ ጋዜጦች እየዘገዩም ቢሆን ይደርሳሉ። ከእንግሊዝ ሶማሌ ላንድ የሚመጡ ጋዜጦችም አሉ። ከደናኔ ማጎሪያ ካምፕ የጥበቃ ሰራተኞችም እንዲሁ ወሬ ያገኛል። ሁዋላ የሶማሊያ ፕሬዚዳንት ለመሆን የበቃው ዚያድ ባሬ ከደናኔ እስር ቤት ካቦዎች አንዱ ነበር።

* * *

የገብርኤልን ትኩረት ከሳቡት ወሬዎች መካከል አንዱ ጅማ በሚገኙ የኢጣልያ ኤርትራውያን የተፈጸመ ድርጊት ነበር። ገብርኤል ዜናውን ያገኘው ከJibouti Correspondent ሲሆን፤ ነገረ ወሬው እንዲህ የሚል ነበር።

ጅማ ላይ በኤርትራውያን የተገነባ ባታሊዮን ነበር። በእነዚህ ባታሊዮን ጥቂት ሊቢያውያን እና ኢጣልያውያን ነበሩበት። ኤርትራውያን ወታደሮች አለቆቻቸው የሆኑትን ጣልያኖች በቁጥጥር ስር አውለው ሲያበቁ በሞት ቀጧቸው። ከዚያም የጠመንጃ እና

የጥይት ክምችቱን ለኢትዮጵያ አርበኞች አከፋፍለው ሲያበቁ እነርሱም ከአርበኞች ተቀላቀሉ።

እንዲህ ያሉ ብጥስጣሽ ዜናዎች የገብርኤልን ትኩረት በከፍተኛ ደረጃ የሚስቡ ነበሩ። ሞንፍሬድ የተባለ ፈረንሳዊ ጋዜጠኛ በተከታታይ የሚጽፋቸው ጽሁፎች በድብቅ ገቡለት። የእንግሊዝኛ፣ የፈረንሳይኛ፣ የኢጣልያንኛ ጋዜጦች ሲያገኙ እንደየቋንቋ ችሎታቸው እየተረዳዱ መረጃዎችን ይለዋወጣሉ። በኢጣልያንኛ ቋንቋ የተጻፉ መጻህፍትና መጽሄቶችን በተለይ በተከታታይ ይገኙ ነበር። መጋቢት 12 1938 የታተመ jibouti correspondent ጋዜጣ “Italia lose Dessie” የሚል ርእስ ከመጀመሪያው ገጽ ላይ አስፍሮ መጣ።

ገብርኤል እንደ ጊዜ ማሳለፊያ ከሚጠቀምባቸው ነገሮች አንዱ በአርበኛነት የተሰለፉ ኤርትራውያንን ስም መመዝገብ ነበር። ይህንንም ያለማቋረጥ ከሚመጡት እስረኞች ያገኝ ነበር። የሚጽፈውንም ወር ዞሮ ሲመጣ ለሉላ ያስረክባታል።

ማስታወሻውን የሚይዘው ባጭር ባጭሩ ነበር፣

- ሹምባሽ አንዶም ተስፋጽዮን የጀግንነት ተግባር ፈጽሞ ተሰዋ። በተምቤን ውጊያ በጦርነቱ የሞቱ ኢጣልያውያን ተቀብረው ኤርትራውያን እንዳይቀበሩ ሲከለከል ነበር አንዶም ያመጸው። 135 ኤርትራውያንን ይዞ ጣልያንን መልሶ ወጋ። ድጋፍ በማግኘቱ የተከታዮቹ ቁጥር አንድ ሺህ ደረሰ። ከዚያም አርማጭሆ ሸፍተ። ሚያዝያ 15 1939 እስኪገደል ድረስም በአርበኛነት እየተዋጋ ቆየ።

- ድራር ተክላይ ሰንአፈ ተይዞ አስመራ ተገደለ። ገብረእግዚእ ስብሃት ተሰዋ። ሰለባ ወልደስላሴ ደቡብ ኢትዮጵያ ላይ ተገደለ። ገብራይ ገብረማርያም፣ ሰረቀ ብርሃን ገብረእግዚእ፣ ጸጋይ ንጉሴ፣ አሰፋ ባህታ አርበኞችን እየመሩ ነው።

አንድ ቀን ገብርኤል እንዲህ ሲል አሰፈረ...

- ኢጣልያ ኢትዮጵያን መውረሯን ምንጊዜም አወግዛለሁ። ሆኖም ኢትዮጵያ በመወረሯ ምክንያት ኤርትራውያን ለነጻነታቸው መዋጋት ችለዋል። በሰፊው የኢትዮጵያ ጫካ ውስጥ እንደ ልብ እየተዘዋወሩ ኢጣልያን በጥይት ማነጋገር ችለዋል። ይህ አጋጣሚ ለኛ ጠቃሚ ነው።

- ፍስሃ ተክሌ መሰዋቱን ዛሬ ሰማሁ። ከራስ እምሩ ጋር ነበር። ጌራ ላይ ተገደለ። ይህን የነገረኝ ጳውሎስ ብርሃኔ ነው። ጳውሎስ የካርኒሽም በለዛ ተወላጅ ሲሆን ጉለልቻ ወራን እና ገንቦ ላይ በተደረገው ጦርነት ተካፍሎ በጣሊያን ተማርኮ ከአንድ ሳምንት በፊት እዚህ ደናኔ አመጡት። ወደ ደናኔ እስረኞች በብዛት እየገቡ ነው። ከስድስት ሺህ በላይ መድረሳችንን ሰምቻለሁ። በብዛት ኢትዮጵያውን ናቸው። እስረኞችን በፈረቃ ወደ ጀናሌ የሙዝ እርሻ ስራ ይወስዷቸዋል።

ከሶስት አመታት በሁዋላ መልሶ ስለ ጳውሎስ ጻፈ,፣

- ያሳዝናል። ደናኔ ተጎልቻለሁ። ያለምንም ስራ የወጣትነት ዘመኔ እየባከነ ነው። ብቻ ከሞት ፍርድ የተረፍኩ መሆኔን በማሰብ እጽናናለሁ። ጳውሎስ እድለኛ ነው። ከእስር ተለቆ እንደገና ወደ ትግል ገባ። ዛሬ የመጣ አዲስ እስረኛ እንደነገረኝ ጳውሎስ ብርሃኔ ባሌ ጎባ ከሚገኙ አርበኞች ጋር ተቀላቅሏል።

ሌላ ቀን ደሞ እንዲህ ሲል አሰፈረ፣

- ቀናሁ! በጣም ቀናሁ!! ሌተና ኮሎኔል በላይ ሃብተአብን ከአውሮፕላን ላይ ቁልቁል ፈጥፍጠው ገደሉት። መሞት ካልቀረ እንዲህ ነው። የሚያስቀና አሟሟት ሞተ። ኢጣልያ ይህን ፈጽማም ቢሆን በበላይ ሃብተአብ ላይ ያደረባት ቁጭት ሊሽርላት አይችልም።

- የዘርአይ ደረስ ወሬ መጣ። አዲስ አበባ የተያዘችበትን አንደኛ አመት ለማክበር ግንቦት 5 1937 ሮማ አደባባይ ተሰብስበው ነበር። ጥቁር ህዝብ ላይ ሲያላግጡ ማየት አልቻለም። በቅርስነት ተይዞ የነበረ ጎራዴ እጁ ላይ ስለነበር ተጠቀመበት። መካከላቸው ገብቶ ደነሰ። አምስት አቁስሎ እሱም ተወግቶ ተያዘ። ሮማ አደባባይ ፒያሳ ቺንኮ ቼንቶ ላይ ለጥቂት ደቂቃዎች ነገሰ።

- ዘርአይ ደረስ! እንኳን ደስ ያለህ። ምን አይነት ህዝብ እንደሆንን አሳየኻቸው። ሙሶሊኒ “ዘልአለም በግ ከመሆን፤ አንድ ቀን አንበሳ ሆኖ መሞት ይሻላል” ያለውን እዚያው ሮማ ላይ አሳየኻቸው። በጎች እንዳልሆንን በማይረሳ መንገድ ነግረሃቸዋል። ትውልድ ለዘልአለም ሲያስታውስህ ይኖራል።

- የአብርሃ ደቦጭና የሞገስ አስገዶምን ገድል ዛሬ ሰማሁ። በእድሜ እኩዮቼ ናቸው። የመግደል ሙከራውን ተከትሎ ማርሻል ግራዝያኒ የከተማውን ሰላማዊ ህዝብ እንደፈጀ ይነገራል። ቸር እና ስልጡን ጣልያን 'ሁዋላቀር' እያለች ለምታብጠለጥለው ህዝብ ስጦታዋ ይሄ ሆነ? ሳንማርኮን ባገኘው በጅምላ እየተገደሉ ያሉት ኢትዮጵያውያን በየትኛው አንቀጽ እንደተፈረደባቸው በጠየቅሁት።

* * *

የሆነው እንዲህ ነበር።

አብርሃ ደቦጭ ስራ ውሎ ወደ ቤቱ ሲገባ ባለቤቱ ታደሰች እስጢፋኖስ አልጋ ላይ ተደፍታ ስታለቅስ አገኛት። በዚህም አሳዛኙን ዜና እንደሰማች ተረዳና አንስቶ አቅፎ ደረቱ ላይ ለጠፋት።

"ገደሏቸው እኮ! ሁለቱንም ገደሏቸው!" አለችው።

አንዳችም ቃል ሳይተነፍስ ደረቱ ላይ አጣብቆ እንደያዛት ጥቂት ቆየ። እሱም ወሬውን ሰምቶ ነበር የመጣው። አበራ ካሳ እና ወንድምየው አስፋወሰን ካሳ ፍቼ ገበያ ላይ መሰቀላቸው በአዲስ አበባ ከተማ እየተወራ ውሏል። የአብርሃ ደቦጭ ሚስት የእነዚህ ሁለት ወጣቶች ዘመድ ነበረች። ማለትም በቀጥታ የስጋ ዝምድና ባይኖራትም የራስ ካሳ ሃይሉ ሚስት አክስቷ ነበረች። አብርሃ ደቦጭ የሚኖርበት ቤትም የራስ ካሳ ሃይሉ ንብረት ነበር።

የአብርሃ ሚስት እየተነፋረቀች መናገሯን ቀጠለች፣

"ምንም አትሆኑም ብሎ ደብዳቤ ጽፎላቸው ሲያበቃ እንዴት እንደዚህ ያደርጋል? ራስ ሃይሉ ዋስ ሆነዋል አልተባለም እንዴ? ግራዝያኒ እንዴት እንዲህ ያደርጋል? ትልቅ ሰው አይደለም እንዴ? ቃል እንዴት እንዲህ ይበላል? ክርስትያን አይደለም እንዴ? አሸንፈው አገሩን ይዘዋል። ሌላ ምን ይፈልጋሉ? አንደኛውን ሁላችንንም ፈጅተው ብቻቸውን ለምን አይኖሩም?"

አብርሃ ደቦጭ አንዳች ቃል አልተነፈሰም። ደረቱ ላይ ተጋድማ የምትነፋረቅ ሚስቱን ማባበል እንኳ አልቻለበትም። እንደ ሚስቱም እንባ አላፈለቀም። ከተጋቡ ስድስት ወራት ሆኗቸዋል። ያፈቅራታል። በጣም ያፈቅራታል። እሷም ነፍሷ እስኪወጣ

ትወደዋለች። ልጆች ለመውለድ የነበራትን ጉጉት ግን አዘገየባት። “በዚህ ዘመን ልጅ አይወለድም።” ይላት ነበር ስትጨቀጭቀው።

አበራና አስፋወሰን እጃቸውን እንዲሰጡ ማርሻል ግራዝያኒ ደብዳቤ መጻፉን፤ በደብዳቤውም ለህይወታቸው ዋስትና እንደተሰጣቸው፣ ለአገራቸው ሲዋጉ ባደረሱት ጉዳት ተጠያቂ እንደማይሆኑ፤ ቃሉን የሚያከብር ሰው ስለመሆኑ ጠቅሶ ደብዳቤ መጻፉን አብርሃ ደቦጭ ሰምቶ ነበር። ይህንንም በማመን የሚስቱ ዘመዶች አዲስ አበባ ሲመጡ እንዴት እንደሚቀበሏቸው ከባለቤቱ ጋር ሲነጋገርበት ሰንብቷል። ወሬውን ሲሰማ ማርሻል ግራዝያኒ ቃሉን አጥፎ ሁለቱ ወጣቶች እንዲገደሉ አዟል ብሎ ለማመን ተቸግሮ ነበር። በግራዝያኒ በራሱ ትእዛዝ መገደላቸውን የሚያውቅ የስራ ባልደረባው አረጋገጠለት።

በነጋታው አብርሃ ስራ አልገባም።

ቀጥታ ወደ ጓደኛው ወደ ሞገስ አስገዶም ሄደ። ሞገስ ጀርመን ኤምባሲ ከሚሰራ ስብሃቱ ከተባለ ዘመዱ ጋር ይኖር ነበር። በጉዳዩ ላይ ሲወያዩበት አረፈዱ። ከዚያም በነጋታው በድጋሚ ለመገናኘት በቀጠሮ ተለያዩ። ለሶስት ቀናት ያህል በየእለቱ እየተገናኙ ከተወያዩ በሁዋላ በመጨረሻ ቁርጠኛ ውሳኔ ላይ ደረሱ። ርግጥ ነው፤ አብርሃ ማርሻል ግራዝያኒን ለመግደል ቁርጠኛ ውሳኔ ላይ የደረሰው በባለቤቱ እንባ ተገፋፍቶ ነው ማለት አይቻልም። ኢጣልያ በኢትዮጵያውያን ላይ በምታሳየው ንቀት ሲያዝን ቆይቷል። በዚህ ጉዳይ ላይም ከሞገስ ጋር በተደጋጋሚ ተነጋግረውበታል።

የሚደረገውን በቅርብ መከታተል እንደመቻሉ መጠን የኢጣልያ ንቀት፤ የባርያ ንግድን እየተቃወመች ኢትዮጵያውያንን በባርነት ስር ለመግዛት የምታሳየው አዝማሚያ ሲያሳስበው ቆይቷል። የሁለቱ ወጣቶች መታለልና መገደል ግን በጣም አሳዘነው። ግራዝያኒን ለመቅጣት መነሻ ሆነው።

ካምፕቤል 2010 ላይ ስለ ግድያ ሙከራውና ስለ አብርሃ ደቦጭ የተለየ ታሪክ ጽፏል። ከመነሻው በባዶሊዮና በግራዝያኒ መካከል የስልጣንና የአለመላከት ሽኩቻ እንደነበር ይገልጻል።

ሽኩቻቸው “ኢትዮጵያን በምን መንገድ ማስተዳደር አለብን?” ከሚለው ጥያቄ ይነሳል። ባዶሊዮና ጓደኞቹ ለኢትዮጵያውያን ሹማምንትን ስልጣን በማካፈል ተቀራርቦ መስራትን ሲመርጡ፤ የሙሶሊኒ አስተዳደርና ግራዝያኒ ግን ይህን አይቀበሉም። ግራዝያኒ ላይ የተደረገውን የግድያ ሙከራ ከዚሁ የፖለቲካ ሽኩቻቸው ጋር ያያይዙታል። በግራዝያኒ አስተዳደር ስር የፖለቲካ ጉዳይ ሃላፊው ፓላቪሲኖ የባዶሊዮ አሳብ ደጋፊ ሲሆን፤ አብርሃ ደቦጭ ደግሞ የፓላቪሲኖ አስተርጓሚና አማካሪም ነበር።

ሁለቱ ኤርትራውያን ቦምብ ከመወርወራቸው ጥቂት ደቂቃዎች በፊት ፓላቪሲኖ በአሉ ከሚካሄድበት ቦታ ዘወር ማለቱን ሁዋላ ግራዝያኒ በጻፈው ሪፖርት ላይ ጠቅሷል። ቦምብ ተወርውሮ ግራዝያኒ በቆሰለበት ደቂቃ ፓላቪሲኖ ቢሮው ውስጥ ያልታወቁ ኢትዮጵያውያንን እያነጋገረ ነበር። በርግጥ እንደ ካምፕቤል ትረካ ፓላቪሲኖን በግድያው ሊያስጠረጥረው የሚችለው ቦምብ ከመወርወሩ በፊት ስፍራውን መልቀቁ ብቻ ሳይሆን፤ ከእንግሊዛዊት እናት የተወለደ፣ እንግሊዛዊት ያገባ፣ አብዛኛውን ጊዜውን አዲስ አበባ በሚገኘው የእንግሊዝ ኤምባሲ ማሳለፉ ጭምር ለጥርጣሬ እንደሚያበቃ ጠቁሟል። ካምፕቤል ፍንጮችን ተንትኖ የሁለቱ ኤርትራውያንን ተግባር ለእንግሊዝ ሲሸልም፤ አንዳንድ ሃበሻ ጸሃፊዎች ደግሞ ካምፕቤል ከእንግሊዝ ጋር ያቆራኘውን ትንተና ከአጤ ሃይለስላሴ ጋር በቀጭን ክር ለማገናኘት ይሞክራሉ።

የተፈጸመው ወዲህ ነው።

ሁለቱ ወጣቶች ማርሻል ግራዝያኒን ለመግደል ቁርጠኛ ውሳኔ ላይ ከደረሱ በሁዋላ የእግር ጉዞ ልምምድ ማድረግ ጀመሩ። እንጦጦ በመሄድ ተራራ መውጣትና መውረድ ተለማመዱ። በባዶ እግር የመራመድ ልምምድ አደረጉ። ዝግጅቱ ካበቃ በሁዋላ አብርሃ እቃውን ሸጠ። ሚስቱን ደብረሊባኖስ ወስዶ አስቀመጣት። እዚያው ደብረሊባኖስ ገዳም በመሰንበትም ተጨማሪ የቦምብ ውርወራ ልምምድ አደረገ።

በዚህ መካከል ጥሩ አጋጣሚ ተገኘ።

የፕየሞንቴው መስፍን፤ የኢጣልያ አልጋ ወራሽ ባለቤት በሰላም ወንድ ልጅ በመውለዷ ምክንያት ማርሻል ግራዝያኒ አዲስ

አበባ ላይ የደስታ በአል ለማክበር ተዘጋጀ።

እለቱ የካቲት 20 1937 ነበር። በግእዝ የካቲት 12።

ማርሻል ግራዝያኒ ስድስት ኪሎ ከሚገኘው ከገነተ ልዑል ቤተመንግስት ለተሰበሰበው ህዝብ ንግግር ማሰማት ጀመረ። ለጣልያን በገቡሩ መካንንት ታጅቦ ነበር። እነዚህም ደጃዝማች ወልደአማኑኤል፣ በጅሮንድ ለጥ ይበሉ ገብሬ፣ ቀኛዝማች ወልደዮሃንስ እና ሌሎችም ነበሩ። ማርሻል ግራዝያኒ ዲስኩሩን እያሰማ ሳለ ሁለቱ ኤርትራውያን ወጣቶች አከታትለው የእጅ ቦምብ ወደ ግራዝያኒ ወረወሩ።

ግራዝያኒ፣ አቡነ ቄርሎስና በርካታ እንግዶች ቆሰሉ። ደጃዝማች ወልደአማኑኤልና ሌሎች ሁለት ኢጣልያውያን መኮንኖች ወዲያውኑ ሞቱ። በዚህ ድርጊት የበገነው ግራዝያኒ ማምሻውን ጉይዶ ኮርቴዜ የተባለውን የጥቁር ሸሚዝ ለባሾችን አዛዥ ጠርቶ የበቀል እርምጃ እንዲወስድ ትእዛዝ ሰጠው። የማርሻል ግራዝያኒን የጅምላ ጭፍጨፋ ትእዛዝ የጄኔራል ባዶሊዮ ደጋፊ የሆኑት ዴላ ፖርታ እና ፓላቪሲኖ ሊያስቆሙት ሞክረው አልተሳካላቸውም።

ጉይዶ ኮርቴዜ በዚያችው ደቂቃ አዲስ አበባን ከአለም ለያያት። ስልኮች ተቆረጡ፤ ፖስታ ቤቶች ስራ አቆሙ፤ ሱቆች ተዘጉ፣ ከተማዋ አና ሆነች። መንገዶች ባዶ ሆኑ። ከዚያም ምሽቱን ባለ ጥቁር ሸሚዝ ወታደሮች ሰላማዊው ህዝብ ላይ ዘመቱበት። ጉሮሮዎችን በሳንጃ በጠሱ። መላ ቤተሰብ በጎጆው ውስጥ እንዳለ እሳት ተለቀቀበት። ከእሳት ለማምለጥ ጎጆ በርግደው ሲወጡ በጥይት ተቀበሏቸው። በዚህ መንገድ የጅምላ ግድያው ለሁለት ቀናት ቀጠለ። በሺህዎች ህይወታቸውን አጡ። መግደሉ ሲደክማቸው ተጠርጣሪዎችን እያነቁ ወደ ናኹራና ደናኔ እስር ቤቶች ላኳቸው። ወደ ደሴቶቹ ከመላካቸው በፊትም ቃሊቲ አከማቿቸው።

ሁለቱ ኤርትራውያን ወጣቶች ግራዝያኒ ላይ የመግደል ሙከራ ካደረጉ በሁዋላ ከአዲስ አበባ ሾልከው ወጡ። ቀደም ብለው ያዘጋጁት ሰው በመኪና ደብረሊባኖስ አደረሳቸው። ከዚያም ወደ ራስ አበበ አረጋይ የአርበኞች ቡድን ያለ ችግር መድረስ ችለው ነበር። መስፍን ስለሺና አበበ አረጋይ ግን እነዚህን ወጣቶች ይዘው መቆየት አልቻሉም። ጣልያንን ሰግተዋል ወይም አላመኗቸውም። ከሁለት

ባንዱ ምክንያት አባረሯቸው። ማርሻል ግራዝያኒ ሁለቱን ወጣቶች ይዞ ላስረከበ አስር ሺህ ማርያ ቴሬዛ ብር እንደሚሰጥ አውጆ ስለነበር ወጣቶቹ የጥቃት ኢላማ ሆኑ። እና ጉዟቸውን የእንግሊዝ ግዛት ወደ ሆነው ሱዳን ቀጠሉ። ዳሩ አልተሳካላቸውም። ድንበር በመሻገር ላይ ሳሉ በጎጃም ሰዎች ተያዙ። እነዚህ የጎጃም ባላገሮች ሁለቱን ወጣቶች ይዘው ለጣልያን አስረከቧቸው። በማስታወቂያ የተገለጸውን የማርያ ቴሬዛ አስር ሺህ ከጣሊያን ስለመቀበላቸው ግን መረጃ የለም። አብርሃና ሞገስ ወዲያውኑ በተያዙበት እለት በስቅላት ተገደሉ። ሲሞቱ ሁለቱም እድሜያቸው በሃያዎቹ አጋማሽ ላይ ነበር።

ከዚህ ሁሉ በሁዋላ የግራዝያኒ አስተዳደር ባደረገው ምርመራ ድርጊቱ ከመፈጸሙ በፊት የአብርሃ ደቦጭ ሚስት ቀደም ብላ ወደ ደብረሊባኖስ ገዳም መሄዷን ደረሱበት። በዚህም የደብረሊባኖስ ገዳም ቀሳውስትን በግድያ ሙከራው እንዲጠረጠሩ አደረገ። ልክ በወሩ ፒየትሮ ማለቲ በተባለ ኢጣልያዊ ጀኔራል የተመሩ ሶማሊያውያን ወደ ደብረሊባኖስ ተላኩ። ዘ9 ደናግልና መነኮሳትንም በአሰቃቂ ሁኔታ ፈጇቸው።

* * *

ዳሩ የግራዝያኒ ድንጋጤና ቁጣ የወለደው እልቂት ህዝቡን በፍርሃት ለመግዛት አላስቻለም። በሺህዎች ወደ ጫካ እንዲወጡ ስላደረገ የአርበኞች ትግል ይበልጥ ተፋፋመ። ስልታቸውን እየቀያየሩ ማጥቃታቸው በረታ። አጥቅቶ የመሸሸን ስልት ተጠቀሙ። መንገድ ላይ አሸምቀው አደጋ መጣል ፍቱን ጥበብ ሆነ። የመገናኛ መስመሮችን መቆራረጥ ዋና ተግባራቸው አደረጉት። እረፍት በሚነሳ ስልት የኢጣልያ የአዲስ አበባ ኮሎኒ እንዳይረጋጋ ማድረግ መቻል ጀመሩ። በተለይ የመገናኛ መስመሮች ሲቆረጡ የኢጣልያ ሰራዊት የተቀናጀ ተግባር መፈጸም ይቸገርና ሞራሉ ይወድቃል።

የአፍሪቃ ቀንድ ሰው በጦርነት ውስጥ የኖረ እንደመሆኑ የበረሃና የዱር ህይወትን ለመልመድ የሚቸገር አልነበረም። ፈረስና ጠመንጃ የያዘ አንድ ወጣት አሮሞ አንድ ጊዜ መጋለብ ከጀመረ የእሳት እራት ከመሆን አይመለስም። ሉጋም ለቆ ከሚጋልብ የሰላሌ ፈረሰኛ ጋር መፋለም ለኢጣልያ ፈተና ነበር። አፈወርቅ ገብረእየሱስ

“የሰሜን ቋንጣ” እያለ የሚጠራቸው የትግራይ ልጆችም ቀኑን ሙሉ ሳይበሉና ሳይጠጡ ረጅም ተጉዞ የመዋጋት ችሎታ ነበራቸው።

አርበኞች ቀላል ተንቀሳቃሽ መሆናቸውና የአገሪቱ መልክዐ ምድር አገዛቸው። ተራሮቹ፣ ጫካዎቹ፣ ገደላገደሎቹ ወንዞቹ ይበልጥ ለአገሬው አርበኛ የተመቹ ነበሩ። ለመሸሸጊያ ምቹ ሆኑላቸው። ከፍተኛ ዝናብ ሲጥል የሚወርደው ጎርፍ የኢጣልያን ሰራዊት እንቅስቃሴ ያግዳል። በኤርትራ እንደተሞከረው ኢትዮጵያ ላይ ኢጣልያውያን ገበሬዎችን ለማስፈር እንቅስቃሴ ላይ ነበሩ። ኢትዮጵያ ሰፊ ያልተነካ ለም መሬት ያለው አገር እንደመሆኑ ነባሩ ገበሬ ብዙም ሳይጎዳ ኢጣልያውያንን ማስፈር እንደሚቻል ያጠኑት ገና ኢትዮጵያን ከመያዛቸው ከአመታት በፊት ነበር።

አጤ ምኒልክን ተከትሎ በደቡብና በኦሮሞ ምድር የሰፈረ ነፍጠኛ ከኢጣልያ ጋር ፉክክር ቢገባም የመሬት ጥበት አልነበረም። ያም ሆኖ የሰፈራ ፕሮግራሙን ባሰቡት ፍጥነት መጀመር አልቻሉም።

ይህ በእንዲህ እንዳለ ለአፍሪቃ ቀንድ ህዝቦች አንድ የምስራች ተሰማ። ኢጣልያ በአውሮፓ ሽኩቻ ውስጥ ከጀርመን ጎራ ሆነች። በመሆኑም እንግሊዝና ኢጣልያ ተወነጃጅለው ሲያበቁ፤ በይፋ ወደ ጦርነት ገቡ። ጣልያን እና እንግሊዝ አፍሪቃ ቀንድ ላይ ጦርነት ጀመሩ። ይህም የአፍሪቃ ቀንድ አገራት ከኢጣልያ ቅኝ አገዛዝ የሚላቀቁበትን መንገድ ከፈተ።

* * *

ገብርኤል ማስታወሻ ከመያዝ የተሻለ የሚያዝናናው ተግባር አልነበረም። አረብኛ፣ ሶማሊኛ፣ ጣልያንኛ እና ትግርኛ ቋንቋዎችን ስለሚችል በደናኔ እስር ቤት ሰፊ ማህበራዊ ግንኙነት ይኖረው ዘንድ፤ መረጃ ከያቅጣጫው ያገኝ ዘንድ ሊያግዘው ችሏል።

ጅቡቲ ኮሮስፖንዳንት የሚያወጣቸው ዘገባዎች በተከታታይ ገብርኤል ዘንድ ይደርሳሉ። “Will Addis Ababa Fall” በሚል ርእስ በመጋቢት ወር 1938 የዘገበውን ገብርኤል ሲያነብ የደስታ ስሜቱን ከእስር ባልደረቦቹ መደበቅ አቅቶት ነበር።

በዚያን ምሽት ስለ ሶማሊያ ጻፈ፣

- ፋራህ ሁሴን የኢጣልያን ቅኝ አገዛዝ በመቃወምና በህቡእ በማደራጀት ተከሶ የ15 አመታት እስራት ተፈርዶበት ደናኔ ገብቷል። ሌሊት ሲዘፍን ያድራል። ዘፈኖቹ ነጻነትን የሚጠሩ ናቸው። ሶማሊያን መንታ መንታ በምትወልድ ሴት ግመል ይመስላታል። በፋራህ እንጉርጉሮ "ማንዴቅ" የግመሏ ስም ነው። በመጪው ዘመን ግመሏ መንታ ስትወልድ ወተት እንደልብ ይገኛል። ማንዴቅ በነጻነት የተመሰለች ሴት ግመል ነበረች።

- ፋራህ አንድ ማለዳ ስንገናኝ በእንግሊዝና በኢጣልያ ቅኝ አገዛዝ ምክንያት የተከፋፈሉ ሶማሊያውያን መቀላቀላቸው የማይቀር መሆኑን ነገረኝ። ኢትዮጵያ ኦጋዴንን ወርራ ሶማሊያን ከፋፍላለች በሚል "የጎረቤት አውሬ ጅብ" እያለ ይጠራታል። ሊገለጽ በማይችል ደረጃ ኢትዮጵያ የሶማሊያ ጠላት መሆኗን ይናገራል። ኢትዮጵያ ራሷ በኢጣልያ ስር ወድቃ ሳለ እንኳ ለሶማሊያ ስጋት መሆኗን ነገረኝ።

- ሶማሊያ የግመል አገር ነው። በዘፈኖችና በአባባሎች ላይ ሴት ግመል የግድ ስሟ ይጠቀሳል። ሶማሊያን ያለግመል ማሰብ አይቻልም። ስጋና ወተቱም የግመል ነው። የተከበረ እንግዳ ሲመጣ የግመል ወተት ይቀርብለታል። የፍየልና የላም ወተት ርካሽና የተናቀ ነው። የተከበረ እንግዳ ሲመጣ የግመል ወተት ይቀርባል።

- ሶማሊያውያን አሳ የማጥመድ ባህላቸው በጣም ዝቅተኛ ነው። በቤት እንስሳት ርቢ ላይ ያተኩራሉ። በመላ ሶማሊያ ከአምስት ሚሊዮን በላይ ግመል እንደሚኖሩ ይነገራል። በጎችና ፍየሎች 26 ሚሊዮን ሲገመቱ፤ ከብቶች 13 ሚሊዮን ናቸው።

- ጁባ እና ሸበሌ ወንዞች የተመሰገነ የውሃ ይዞታ ቢኖራቸውም የህዝቡ የእርሻ ስራ ፍላጎት ዝቅተኛ ነው። የቤት እንስሳት ገበያ ምንጊዜም የደራ ነው። በገንዘብ ብቻ ሳይሆን በመለወጥም መገበያየት ይቻላል። አንድ ግመል በአምስት ከብት ይለወጣል። አንድ ግመል በ30 በጎችና ፍየሎች ይቀየራል። ግመል ሞቃታማውን የአየር ጠባይ በመቋቋም ችሎታው ተፈላጊ ነበር።

- አብደላ ሃሰን "እናት" ሲል ግመልን አወድሶ ተቀኝቷል። "ሶማሊያውያን ተነሱ" በተባለው የነጻነትን ጥያቄ በሚያነሳው ዜማ፣ "ግመላችሁ ሲሰረቅ ህይወታችሁን ለመሰዋት የማትሳሱ፤ ለአገራችሁ ነጻነት አንድ ድንጋይ እንዴት መወርወር አቃታችሁ?" ሲል

ይጠይቃል። ሁሴን አሊ ደግሞ ኢጣልያን በጅብ መስሎ ሲያበቃ፤ ሶማሊያውያንን በግመል መሰለ። ይህ ዜማ እስረኛ ሶማሊያውያንን አነቃንቆ ሰነበተ። ግጥሙን በቃላቸው አንበለበሉት። ይህን ግጥም ሲያዜም የሚሰማ ሶማሊያዊ ደናኔ እስር ቤት ውስጥ ወደሚገኘው ልዩ እና አሰቃቂ እስር ቤት ይላካል። ያም ሆኖ ግን ሶማሊያውያን ፍርሃት የሚባል አይጠጋቸውም።

በነጋታው ደግሞ ኤርትራን በተመለከተ ጻፈ፣

- ቅሬታዎች መልከ ብዙ ናቸው። የጭቆናና የዘረኛነት ሸክሙ ከብዶናል። የግድ ሁኔታዎች መለወጥ አለባቸው። በማንኛውም መንገድ ቢሆን ለውጥ መምጣት አለበት። ራሷን ችላ ለኛም አጋዥ ትሆናለች ብለን ተስፋ ያደርግንባት ኢትዮጵያ እንዲህ በኢጣልያ እግር ስር ወድቃ ማየቱ አሳዛኝ ነው። ለረጅም አመታት በባርነት ስር ነበርን። አያቶቻችን ቀንበሩን ለማውለቅ ሞክረው አልቻሉም። አባቶቻችን ላይ ቀንበሩ ጠበቀ። እኛ በኢጣልያ ቅኝ አገዛዝ ስር ተወልደን አደግን። በዘረኛ ገጽታዎች እየተሳቀቅን አደግን። የኛ መኖር አስፈላጊነት የመጨዎችን ምኞት ለመጠበቅ መሆኑን አወቅን። ከዚህ ለመላቀቅ መንገዱን የሚያሳየን አልነበረም። አሁንም የለም። እንደ እውር ፈረስ አውላላ ሜዳ ላይ ተገትረናል።

ምእራፍ ፱

ደህና ሁኚ ሮማ!
Ciao! Ciao! - ባንቺው ዜማ
አባቶች እንዲሉ - ቦ! ጊዜ ለኩሉ

ኢጣልያ ጎራዋን ወደ ናዚ ጀርመን በመደባለቋ የአፍሪቃ ቀንድ ፖለቲካ ባጭር ጊዜ ውስጥ ተለዋወጠ። ኢጣሊያ በተለይ ለአምሳ አመታት የገነባቸውን የኤርትራ ስትራቴጂያዊ ግዛት ላለማጣት ሙሉ አቅሟን ተጠቅማ ነበር። ከመጠቃቷ በፊት የእንግሊዝ ግዛት የነበረችውን ከሰላን ያዘች።

ቀደም ብለው ከተት በማወጅ ከጥቂት በላይ ባታሊዮን ወደ ሊቢያና ወደ ሞቃድሾ ልከው ስለነበር እንግሊዝ ትኩረቷን ወደ ኢትዮጵያና ኤርትራ ስታደርግ የሰው ሃይል እጥረት ገጠማቸው። የሰው ሃይል እጥረታቸውን ለማቃለል ለአቅመ ጠመንጃ ያልደረሱ ኤርትራውያንን በጥሪና በግዳጅ እያፈሱ ወደ ማሰልጠኛ ካምፖች ጨመሩ። ስልጠና የጨረሱትን ከአስመራ በባቡር ወደ ከረን ልከው ሲያበቁ መንደሮችን እያሰሱ እንደገና ማሰልጠኛዎችን ሞሉ።

ወላጅ በባቡር ጣቢያ እየተገኘ በእንባ ከመሰናበት በቀር አንዳች ለማድረግ የሚያበቃ ድርጅት አልነበረውም። ቅሬታውን በጠባብ ክልል ከመነጋገር አልፎ፤ ለአምላክ ብሶቱን ከማሰማት ባሻገር እንዴት ተደራጅቶ፣ እንዴት መብቱን ማስከበር እንዳለበት አግጣጫ የሚያሳየው አመራር አልነበረውም። የኤርትራ ህዝብ፣

“መጪው ሰይጣን የተሻለ ሊሆን ይችላል።” በሚለው ነባር የተስፋ ብሂል መሰረት የእንግሊዞችን መምጣት በጉጉት ጠበቀ።

እንግሊዝ ከህንድ፣ ከሱዳን፣ ከደቡብ አፍሪቃ፣ ከናይጄሪያ፣ ከኬንያና ከጋና የተውጣጣ 25 ሺህ ወታደሮች ይዛ የኢጣልያን የአፍሪቃ ቀንድ ግዛት ማጥቃት ጀመረች። የኢትዮጵያ አርበኞች ከመቶ ሺህ በታች ተገመቱ። ኢጣልያ በአንጻሩ በአፍሪቃ ቀንድ ግዛቷ በጥቅሉ 330 ሺህ ወታደሮች ነበሯት።

የእንግሊዝ ሰራዊት ከሰላን ካስለቀቀ በሁዋላ ድንበር ጥሶ ኤርትራ ገባ። ወደ ከረን ሲገሰግስ የሚያቆመው አልነበረም። ሌላ የእንግሊዝ ሃይል ከኬንያ ተነስቶ ወደ ሞቅዲሾ አቀና። ሶማሊያ ከገባው ከፊል ሃይል ወደ ሰሜን ተጠምዝዞ ወደ ኢትዮጵያ በመግባት ጅጅጋና ሃረርን ኢላማ አደረገ። በሻለቃ ዊንጌት የሚመራ ሌላ ሃይል አጤ ሃይለስላሴን በአንቀልባ አዝሎ በጎጃም በኩል የጎሬላ ውጊያውን መምራት ቀጠለ።

እና የእንግሊዝ ማሸነፍ ተተነበየ።

ሚያዝያ 6 ካኒንግሃም ከሃረር ተነስቶ አዲስ አበባን በመቆጣጠር ኢጣልያ በኢትዮጵያ ቅኝ ግዛቷ ላይ መሸነፏን አወጀ። አጤ ሃይለስላሴ በዊንጌት እየተገፉ ሚያዝያ 16 ደብረማርቆስ ቢደርሱም ወደ አዲስ አበባ እንዲገቡ አልተፈቀደላቸውም። ለታሪክ ፍጆታና ለግርማዊ ክብራቸው አዲስ አበባን ነጻ በማድረጉ ሂደት መካፈል ፈልገው ነበር። እንግሊዞች እድሉን ነፈጓቸው። በዚህም ለአንድ ወር ያህል ደብረማርቆስ ተወዝፈው ለመቆየት ተገደዱ። ምርጫ አልነበራቸውም። በኤርትራ የተከሰተው ግን ከኢትዮጵያ የተለየ ነበር። ከረን ላይ እንግሊዝን 53 ቀናት ቆየች።

* * *

ባቡሩ ሞተሩን እያንተከተከ የተቆጣ አውሬ መስሏል። መልሶ መላልሶ ያጓራል። የከሰል ፍሙን ከስር እየተፋ እንፋሎቱን ከላይ ሲያንበለብለው ደም የጠማው ደራጎን እንጂ በሰው የሚዘወር፤ ሰው ሰራሽ ማሽን አይመስልም።

ባቡር ጣቢያው በሰው ተጨናንቋል።

የሸኒዎችና የተሸኚዎች የመሰነባበቻ ቃላት ከባቡሩ የሞተር ድምጽ ጋር ይፎካከራል። ወላጅ የልጁን ስም፤ ወይ ደግሞ ልጅ የአባቱን ወይም የእናቱን ስም ሲጠራሩ ተደበላልቆ ይሰማል። ከባቡሩ የሞተር ድምጽ ልቆ ለመሰማት ጉሮሮ ፈተና ላይ ወደቀ። ልጆቻቸውን ለመሸኘት ወደ ባቡር ጣቢያው የነረቱ ኤርትራውያን ወዶቻቸውን ወደ ሞት መሸኘቱ ከብዷቸው፤ አንጀታቸው አልችል ብሎ ተቃቅፈው ይላቀሳሉ።

“የሊቢያ ታለፈ፣ የኢትዮጵያ ታለፈ፣ አሁን ደግሞ እንግሊዝ መጣች? መቸ ይሆን አምላክ በቃችሁ የሚለን?” እየተባባለ ርስበራስ ቢጠያየቅም ምላሽ የለውም። የእናቶች የእንባ ጅረት ብቻ።

አንድ ኢጣሊያዊ መኮንን ከወዲያ ወዲህ እየተወናጨፈ ትእዛዝ በመስጠት ላይ ነበር። ከስራ ባልደረባነት ይልቅ አገልጋይ አሽከር የሚመስሉ ኡዝባሾች፣ ሹምባሾች፣ ብሉቾባሾች፣ ሙንጣዞች ከኢጣሊያዊው መኮንን የሚቀበሉትን ትእዛዝ ለማስፈጸም እነርሱም እንደጌቶቻቸው ከወዲያ ወዲህ ይራወጣሉ። ከፊሉ ጣሊያንኛ ያወራል። ሌላው በትግርኛ ይነጋገራል። አልፎ አልፎ የአረብኛ ቃላትም ይሰማሉ። ወላጆች በተጨነቀ ድምጽ ምርቃታቸውን ለልጆቻቸው አጅጎደጎዱ፣

“በደህና ይመልሳችሁ!”

“እግዚአብሄር ከናንተ ጋር ይሁን!”

የእያሱ ታናሽ እህት ሃና ያዕቆብ ምሬቷን አሰማች፣

“አባቱን በሃሰት ወንጅለው አሰሩት። ይሄ ልጅ ደግሞ አባቱን ይተካል ብዬ ሳስብ ወሰዱት። የቀሩትን እንዴት ነው የማሳድገው? በደል! ግፍ! አደይ ማርያም! ኤህ!”

አባቷ ከራንቹን እንደተደገፈ በጸጥታ ባቡሩን ከመመልከት በቀር ሴት ልጁ ለምታሰማው ምሬት የሚሆን የማጽናኛ ቃላት አልነበረውም። የኢጣሊያ ቅኝ ገዢ አደጋ ላይ መውደቁን መረዳት ችሎ ነበር። ያም ሆኖ የፖለቲካ ጉዳይ አንስቶ የመናገር ፍላጎቱ ቀዝቅዟል። ልጁ እያሱ ኢትዮጵያ ከዘመተ ወዲህ አንድ ሁለት ጊዜ ደብዳቤ ከመላክ በቀር ተመልሶ መጥቶ አላያቸውም።

ባቡር ላይ እየተሳፈሩ ወደ ሱዳን ድንበር ለጦርነት

እየተወሰዱ ያሉት ጨቅላ ልጆች ህይወታቸው በማያውቁት ጉዳይ እንደሚቀጠፍ በማሰብ ልቡ እየጮኸበት ነበር። የልቡን የጩኸት ድምጽ በአንደበቱ የመግለጽ ልምድ ግን አልነበረውም። በአድዋ ጦርነት ጉዳት ከደረሰበት ወዲህ በኢጣልያ አስተዳደር በተደረገለት እንክብካቤ ምክንያት ለኢጣልያ ገዢ ታማኝ ሆኖ ኖሯል። ከጊዜ ወደጊዜ ግን ቅሬታዎቹን መሸሸግ ከማይችልበት ደረጃ ላይ ደረሰ። በተለይም ወጣቶች ያለማቋረጥ ወደ ጦርነት መወሰዳቸው ልቡን እያቆሰለ ያስጨንቀዋል። እየተዳከመ የሄደው ታማኝነቱ ቀስ በቀስ እየሳሳ ሄዶ አሁን ጨርሶ ጠፍቷል። ዳሩ ምንም ማድረግ እንደማይችል ይሰማዋል። ሌላው ቀርቶ ጨቅላ የልጅ ልጁ ከእንግሊዝ ጋር ለመዋጋት ተይዞ በግድ ሲወሰድ ይኸው ቆሞ ያያል።

አሁን እድሜው ገፍቷል። ጓደኞቹ የነበሩት ኤድሞንዶና ኤድዋርዶ አርፈው ሞቅዲሾና አስመራ ተቀብረዋል። የኤድሞንዶ ልጅ ሞቅድሾ ደናኔ እስር ቤት ተከርችሟል። እድሜ ይፍታህ ተፈርዶበታል። የኤድዋርዶ ልጅ እስጢፋኖስም እንዲሁ 16 አመታት ተፈርዶበታል። በቅርቡ ደግሞ የልጁ ባል ታሰረ። አሁን ደግሞ የልጅ ልጁ ወደ ጦርነት ተላከ። እንግሊዝ ጦርነቱን ካሸነፈች ጦርነቱ ይቆማል ብሎ ተስፋ አድርጓል። የታሰሩትም ይፈታሉ። የልጅ ልጁ በእንግሊዝ ጦርነት ከተገደለ ግን ትርፉ ምንድነው? በዚህ ማጣት፣ በዚያ ማግኘት። ማትረፍ ከኪሳራ ጋር?

ስለ በኩር ልጁ ስለ እያሱ አጥብቆ አሰላሰለ።

በእያሱ አእምሮ ላይ የበቀል ስሜት መዝራቱን ከተረዳ ሰነበተ። ምክንያቱም እያሱ ወደ ሸዋ የዘመተው ተገዶ ሳይሆን በፈቃዱ መሆኑን በተለያየ መንገድ በመስማቱ ስለ ልጁ ስሜት መረዳት ችሎ ነበር። ያዕቆብ አጤ ምኒልክ ባደረሱበት ግፍ ምንም አንኳ ቂም ይዞ የኖረ ቢሆንም፤ ከእርጅና ጋር አሁን በርዶለታል። ቂሙን ለልጁ ማውረሱ ግን ከነከነው። ትርፉ ምን ነበር? ብሎ ሲያስብ ልጁም ምናልባት በጎራዴ አንገቱን ተቀንጥሶ ይሆናል። በህይወቱ ለሁለተኛ ጊዜ አምርሮ ተጸጸተ።

ያዕቆብ እንዲህ በተደበላለቀና ውል ያጣ አሳብ እያሰላሰለ በትካዜ አይኖቹን ባቡሩ ላይ ተክሏል። የሴት ልጁን ማጉተምተም እንኳ መስማት አልቻለም። ደግሞ ደጋግሞ “ልጆች ወልዶ ለጦርነት

መገበር እስከመቼ?" የሚል ጥያቄ እንደ ማእበል አእምሮውን እየገጨ ይመለሳል። ምላሽ የሌለው ጥያቄ ነበር።

ለአቅመ ጠመንጃ ሳይደርሱ ጠመንጃ ያነገቱት የልጅ ወታደሮች አብዛኞቹ ባቡር ላይ ተሳፍረው ተጠናቀቁ። እስከ ወገባቸው በባቡሩ መስኮት ወጥተው በተመሳሳይ ሰቀቀን እነርሱም ወላጆቻቸውን ይሰናበታሉ። ድምጻቸው የሴት ድምጽ መምሰሉ ልጅነታቸውን ያሳብቃል።

"ማማ! በጸሎትሽ ጠብቂኝ!"

"ባባ! ምርቃትህ ምርኩዝ ይሆነኛል!"

ከፍ ባለ ድምጽ የሚዘፍኑም ነበሩ።

በማይበላ መንገድ - በሄድንበት ፈለግ
አትርሺን አስመራ!
ዞረን እንመጣለን - ተሸልመን ማዕረግ
እንግሊዝ ተቀብራ!

ባቡሩ ሲንቀሳቀስ ሃና ያዕቆብ ለዘማች ልጇ የሸኘት እሪታዋን አቀለጠችው። አባቷ ከንፈን ይዞ ባያስቀራት ከባቡሩ የብረት ጎማ ስር መግባቷ ነበር። ዛር የተነሳባት ባለ ውቃቢ መሰለች።

"ቻል አድርጊው!" ሲል አጽናናት አባቷ፣ "...ወደ ጦርነት የሄደ ሁሉ አይሞትም። መልካሙን ማሰብ ይሻላል። በአምላክ ፈቃድ በህይወት ይመለስ ይሆናል። ቻል አድርጊው!"

የባቡሩ ጭራ ከአይን ከተሰወረ በሁዋላ ሸኚው ወደየቤቱ የመልስ ጉዞ ሆነ። በመልስ ጉዟቸው ላይ ያዕቆብ ብቻውን የመለፍለፍ አይነት አንዳንድ ቃላትን ከአንደበቱ አወጣ፣

"ጥልያኖች እንግሊዞችን መቋቋም አይችሉም። ለኛ ማን እንደሚሻለን የሚያውቀው ግን አምላክ ብቻ ነው።"

ሃና እንባዋን እያባበሰች ምላሽ ሰጠች፣

"እንግሊዞች ካሸነፉ የታሰሩት ሁሉ ይፈታሉ። ባለቤቴም ይፈታል። ገብርኤልና እስጢፋኖስም ይፈታሉ። ብቻ በጦርነቱ ይሄኛው እንዳይሞትብኝ አደይ ማርያም ትጠብቀው።"

ምርር ባለ ድምጽ ስለታሰረው ባለቤቷ ብሶቷን ቀጠለች፣

“ፖለቲካ ተናገረ ብለው የወነጀሉት በሃሰት ነው። በምቀኝነት ነው። እሱ ጥልያንን ቢጠላም የልቡን በልቡ ይይዛል እንጂ ፖለቲካ ተናግሮ አያውቅም። ከረዳትነት አልፎ ትሬንታ ኳትሮ መንዳት ሲጀምር ጓደኞቹ አይናቸው ደም ለበሰ። ኮማንደቶረ ሲኞር ቡሩኖ የአበሻ ተንኮል ሳይገባው አስፈረደበት። አደይ ማርያም ትርዳን እንጂ ከሰው ምን ይጠበቃል? ሰው ክፉ! የሰይጣን ልብ!!”

ያዕቆብ አንዳች ባለመናገሩ ሃና ብሶቷን ደገመችው፣

“...አምላክ ከፈቀደው ውጭ የሚሆን ነገር የለም። የሰው ድካም ከንቱ ነው። አደይ ማርያም ብቻ ከክፉ ነገር ትጠብቀው።”

መልሳ ግን መንፈሷ ተረብሾ ማልቀስ ጀመረች፣

“ናኹራ እስር ቤት የገባ ተመልሶ ሲመጣ አላየንም። ናኹራ የገቡ ሁሉ በዚያው ቀርተዋል። በአይን ያያቸው የለም። ባለቤቴንም ይገድሉታል። ወይ ደ’ሞ የአሳ ምግብ ያደርጉታል። ወይ ወንድሜን!”

ጎን ጎኗ ሱክ ሱክ ወደሚለው የስድስት አመት ልጇ መለስ አለች። እብደት የጀማመራት ያህል ከፍ ባለ ድምጽ ተናገረች፣

“እንግዲህ ስራ ጀምር። ገበያ ሄደህ ቃሪያ መሸጥ ትጀምራለህ። ‘ሃየ ሃየ ጉዕ በርበረ፣ ዘይወዓለ ዘይሃደረ፣ ሰብአይን ሰበይትን ዘፋቐረ’ (እነሆ! ቃርያ! ያልዋለ ያላደረ! ባልና ሚስትን ያፋቀረ) እያልክ መለማመድ ነው። ካራቫንሳራልዮ ማንም አያስጠጋህም እንጂ ምድጃና መንከሽከሽ መስራት ብትለምድ ገበያ ነበረው። አባትህ ቢኖር ጥሩ ስራ ያገኝልህ ነበር።”

በዚህ ጊዜ ያዕቆብ ጠንከር ባለ ድምጽ ገሰጻት፣

“ሃና ይበቃሻል። ክፉ ክፉውን ማሰቡ ይብቃሽ። ነገ በማለዳ መኪና ይገዛ እመጣለሁ። እቃችሁን ማምሻውን አዘጋጁ። ጦርነቱ እስኪለይለት ሰምበል እኔ ዘንድ መቆየቱ ይሻላችሁዋል። አምላክ ፈቃዱ ከሆነ እያሱም ከሞት ተርፎ በሰላም ይመለስልን ይሆናል። ጸሎት ላይ ብቻ በርቺ!”

ምእራፍ 10

የመላእክት አገር - ያጎት ሳም ጓደኛ

“የተንኮል ከረጢት!”

የ አ ለ ማ ች ን ዳ ኛ

ከኬንያ የተነሳው የእንግሊዝ ሰራዊት ሞቅዲሾን በፍጥነት ተቆጣጠረ። በዚህም ደናኔ እስር ቤት በእጃቸው ገባ። ገብርኤል ኤድሞንዶም ከደናኔ እስር ቤት ነጻ ከወጡት አንዱ ለመሆን በቃ። በዚህ ጊዜ ሁለተኛ ልጁ ምህረተአብ ተወልዶ ነበር።

የእንግሊዝ ማጥቃት ፈጣን ነበር። በሁሉም ግንባሮች ኢጣልያ ልትቋቋመው አልቻለችም። ወደ እንግሊዝ ግዛት እስከ ከሰላ ገፍቶ የነበረውን የኢጣልያ ሰራዊት እንግሊዞች ጠራረጉት። ፋታ ሳይሰጡ እያሳደዱ ከረን አደረሱት። ከረን ላይ ጣልያን ጠንካራ ምሽግ መገንባት ብትችልም የእንግሊዝ ቦምብ ጣይ አይሮፕላኖች አልፈው አስመራን መደብደብ ጀመሩ።

ኢጣልያውያን የአስመራ ነዋሪዎች በየቤታቸው ደጃፍ ከአይሮፕላን ቦምብ ድብደባ ለመከለል የሚያገለግሉ ጉድጓዶችን በመቆፈር ስራ በዛባቸው። በርግጥ የእንግሊዝ አይሮፕላኖች ወታደራዊ ኢላማዎችን እየመረጡ ነበር የሚመቱት። አስመራ አይሮፕላን ማረፊያ ቀዳሚ ኢላማ ሆነ። የወታደራዊ ስንቅና ትጥቅ ማከማቻዎችንም እየተመላለሱ ለማጋየት ሞከሩ። የነጮች መኖሪያዎች አልፎ አልፎ ይደበደባሉ። ኤርትራውያን በአብዛኛው ሰፈራቸው ለብቻ ስለነበር በአውሮፕላን ድብደባው ስጋት የለባቸውም። የእንግሊዝ አይሮፕላኖች ወደ ባለ-አገሩ መንደር አይሄዱም። ይልቁን ኢጣልያውያኑ ከአይሮፕላን ድብደባ ለመሸሽ

ውሏቸው በገዛ ባንዳ ሃበሻ፣ በሃዲሽ ዓዲ፣ በእዳጋ አርቢ ሆነ። ይጠየቋት የነበረው ጌቶ መዋያቸው ለመሆን በቃ።

ኢጣሊያ የእንግሊዝ ተዋጊ አይሮፕላኖችን ለመመከት በተመሳሳይ በቂ አይሮፕላኖች ነበራት። ቪዛንቲኒ የተባለው ኢጣሊያዊ ፓይለት አስመራ ላይ እጅግ ዝነኛ ሆነ። ፖለቲካውን የማይገነዘቡ ህጻናት ባንድ በኩል የእንግሊዝን መምጣት በናፍቆት እየጠበቁ፤ በሌላ በኩል ስለ ቪዛንቲኒ በአድናቆት ሲያወሩ ይውላሉ።

ጊዜው የምጽዋ ክረምት ነበር። ምስራቃዊው የአስመራ ክፍል በጉም ተሸፍኖ ይውላል። የእንግሊዝ አይሮፕላኖች ከጉሙ ውስጥ ብቅ እያሉ ፌሮቪያን ደብድበው ሲመለሱ ክስተቱ ለአስመራ የኤርትራውያን ልጆች የመዝናኛ ያህል ሲሆን፤ የውጭ አገር ሰዎች ሰቆቃው ገደላቸው። ሌሊቱ አልፎ ጸሃይ ብቅ ብላ የአይሮፕላኖቹ የሞተር ድምጽ እስኪሰማ የደቡብ አስመራ ነዋሪዎች በናፍቆት ይጠብቃሉ። የሰሜን አስመራ ነዋሪዎች ወደ ጉድጓዳቸው ይገባሉ። አዋቂዎችም እንደ ልጆቹ በእንግሊዝ አይሮፕላኖች አይረበሹም።

የአስመራ ኢጣልያውያን ተስፋቸውን የጣሉት በቪዛንቲኒ ላይ ነበር። “ጥቁር አሞራ” የሚል ቅጽል ስም ሰጥተውታል። ቪዛንቲኒ የኢጣሊያ - ኤርትራ አየር ሃይል የተዋጊ አይሮፕላኖቹ አዛዥ ሲሆን፤ አብራሪም ጭምር ነበር። በከተማው ስለዚሁ ወጣት አብራሪ በአድናቆት ይነገራል። የእንግሊዝን አይሮፕላኖች አየር ላይ ገጥሞ እንዴት እንዳርበደበዳቸው ይወሳለታል። የእንግሊዝ ቦምብ ጣይ አይሮፕላኖች ብቅ ሳይሉ ከዋሉ፣ የቪዛንቲኒ ስም ሰማይ ተሰቅሎ ይውላል።

አንድ ማለዳ ስድስት የእንግሊዝ አይሮፕላኖች የአስመራን አየር ማረፊያ ደብድበው ወደ መንደፈራ አግጣጫ ሲመለሱ ቪዛንቲኒ ከመቅጽበት ተከተላቸው። ጸዕዳ ክርስትያን አካባቢ በተደረገ የአየር ላይ ውጊያ አምስቱ የእንግሊዝ አይሮፕላኖች “ክንፌ አውጭኝ” ብለው ሲያመልጡ፤ አንድ አይሮፕላን ግን ተቃጥላ እየነደደች ጸአዳ ክርስትያን ሁዳድ ላይ ተከስክሳ ጋየች። አብራሪው ከአውሮፕላኑ ጋር ተቃጥሎ የሞተ ሲሆን፤ ማይክል የተባለ የ22 አመት ወጣት ነበር።

የቪዛንቲኒ እና የማይክል ስቶን የጻዕዳ ክርስትያን የአየር ላይ ውጊያ መነጋገሪያ ሆኖ ሰነበተ። ፖለቲካ የቀላቀለ የጀብዱ ወሬ

እዚህም እዚያም ይሰማል። አንዳንዱ እንደወረደ ቪዛንቲኒን ያደንቃል። ሌላው የፓይለቱን ችሎታ ቢያደንቅም የአንድ ፓይለት ልዩ ችሎታ ኢጣሊያን ከመሸነፍ እንደማያድናት ያክልበታል።

ቪዛንቲኒ የማይክል ስቶንን አውሮፕላን አየር ላይ ካነደደ በሁዋላ ድል አድራጊነቱን ለመግለጽ አስመራን ሁለት ጊዜ ተሸከረከራት። በዚያን ምሽት አስመራ ከተማ በኢጣሊያውን ፌሽታ ስትደንስ አደረች። የኢጣልያኑ ደስታ ኤርትራውያን ወደሚኖሩባቸው ቀበሌዎች ጭምር ተዳረሰ። የፋሺስት ደጋፊዎች ሲፎክሩ ተሰሙ። እንግሊዝ ተዋርዳ ወደ ደሴቷ እንደምትመለስ ተናገሩ። ኤርትራውያን ሹምባሻዎች፣ ቡልቻባሾች፣ ሙንጣዞች መሎቲ ቢራ እየተጎነጩ ለኢጣሊያ ረጅም እድሜ እየተመኙ ብርጭቆ ሲያጋጩ አደሩ። ቪዛንቲኒ ሁሉን የሚችል ልዩ ፍጡር መስሎ ታየ። ደጋፊዎቹ ስሙን እየጠሩ ሲጮሁ ተሰሙ።

ቪዛንቲኒ እንደ ዝናው ብዙም በህይወት አልቆየም። አየር ላይ ከእንግሊዝ አይሮፕላኖች ጋር በእምባትካላ ሰማይ ላይ ተፋልሞ ወደ አስመራ ሲመለስ ጉም ሸፍኖት ከደብረቢዘን ተራራ ጋር ተጋጨ። የቪዛንቲኒ አይሮፕላን እየነደደች ከደብረቢዘን ተራራ ቁልቁል ስትንከባለል የነፋሲት ከተማ ነዋሪዎች ተመልከተዋል። ቪዛንቲኒ ከሚወዳት አይሮፕላን ጋር ተቃጥሎ ምድርን ተሰናበተ።

በሶስተኛው ቀን በእለተ ቅዳሜ የጥቁር አሞራው የቪዛንቲኒ አስከሬን ለቀብር ወደ ጸጸራት የካቶሊክ የመቃብር ስፍራ ሲጓዝ የከተማው ህዝብ ግልብጥ ብሎ ለቀብር ወጣ። በአስመራ የኢጣሊያ ቅኝ አገዛዝ ዘመን ታሪክ ውስጥ የቪዛንቲኒን ያህል በከፍተኛ የህዝብ ቁጥር የተቀበረ ሰው አለመታየቱ ይነገር ነበር።

የቀብሩ እለት መንገዶች ተዘጋጉ። ኢጣሊያውያን በየመንገዱ በሃዘን ነጡ። ኤርትራውያን ቪዛንቲኒን በሙያው ቢያደንቁትም በመሞቱ ያዘነ ነዋሪ አልታየም። የቪዛንቲኒ መሞት የኢጣልያ ቅኝ አገዛዝ በማክተም ላይ ስለመሆኑ የሚጠቁም ምልክት ሆኖ ታየ። በዚያን ሰሞን የባለ-አገሩ መንደሮች ወግ "ቪዛንቲኒ!" ሆነ።

ከበነጋታው ጀምሮ የእንግሊዝ አይሮፕላኖች የአስመራን አየር ይደንሱበት ጀመር። በቪዛንቲኒ አመራር ስር የነበሩ የኢጣሊያ አብራሪዎች እንደ ቪዛንቲኒ በጀግንነትና በችሎታ የሚያዋጋቸው

አላገኙም። በርግጥ የኢጣሊያ ሰራዊት የተሸነፈው መሬት ላይ እንጂ አየር ላይ አልነበረም። የቪዛንቲኒ አስተዋጽኦ የስንቅና የትጥቅ ክምችቱን ከእንግሊዝ የአየር ጥቃት ከመከላከል ያለፈ አልነበረም።

ጦርነቱ እየተፋፋመ ሄደ።

ኢጣሊያውያን መሸነፋቸው የማይቀር መሆኑ የኤርትራውያን ዋና ርእሰ ጉዳይ ሆነ። እናቶች በጸሎታቸው ጭምር እንግሊዞች ያሸንፉ ዘንድ ማርያም አስመረይቲን ተለማመኑ። በርግጥ የአስመራ ኢጣልያውያን 'እንግሊዝ ታሸንፋለች' የሚል አሳብ አልነበራቸውም። ማርሻል ሮሜል በሰሜን አፍሪቃ እየቀናው ስለነበር፤ የአክሲስ አገራት በቃል ኪዳኑ ሰራዊት ላይ እየበረቱ ስለነበር ጣልያን አስመራን ብትቆጣጠር እንኳ ከጊዜያዊ ድል ያለፈ ሊሆን እንደማይችል እምነት ነበራቸው።

ወሬውም ጦርነቱም ቀጠለ።

ጣልያኖች ከረን ላይ ጠንካራ መቋቋም ለማድረግ ሞከሩ። ሃይላቸውን ሁሉ በከረን ምሽግ ላይ አዋሉ። በአምስት አመታት የቅኝ አገዛዝ ጊዜ ውስጥ ኢጣልያ ከመላ የኢትዮጵያ ወጣቶችን በብዛት በወታደርነት ቀጥራ ማሰለፍ ችላ ነበር። በከረን ውጊያ ብቻ እንኳ በጥሩ ሁኔታ የሰለጠኑ፤ በጎንደርና በሰሜን ሸዋ ሰዎች የተገነቡ አራት ብርጌድ ታማኝ ሰራዊት ማሰለፍ ችላ ነበር። እነዚህን ብርጌዶች ከጣልያን ለመነጠል የተደረገው ሙከራ ብዙ ጊዜ ፈጀ።

ሪቻርድ ፓንክረስት "Ethiopia Obserever" ቁጥር ሁለት እትም ላይ ባቀረበው ጥናታዊ ጽሁፍ ከረን ላይ በተደረገው የኢጣልያ እና የእንግሊዝ ውጊያ በኢጣልያ ወገን ሆኖ ከተዋጋው ሃይል ውስጥ በተለይ በሰሜን ሸዋ ሰዎች የተገነቡት 2ኛ እና ዘጠኛ ብርጌዶች እንግሊዝ ኤርትራን እንዳይቆጣጠር እንቅፋት ሆነው ነበር። አማሮቹ ከምሽጋቸው እንዲኮበልሉ ለማድረግ የአጤ ሃይለስላሴን ደብዳቤ ከሰማይ መበተን አስፈላጊ ሆኖ ተገኘ። ደብዳቤውን ፓንክረስት በተጠቀሰው መጽሄት እንዳተመው፤ አጤ ሃይለስላሴ በተለይ "የኔ ዘር" የሚሉትን የሸዋ አማራ ለመሳብ የተማጸኑበት ስሜታዊ ደብዳቤ እንዲህ ይላል፣

"እናንተ የኔው ዘር፣ የኔው ወገን ናችሁ። የኔው ህዝብ

ናችሁ። ለኢትዮጵያ መንግሰት ዋና አስኳል፣ ዋና ማእከል ናችሁ። በኔ ቤት ዙሪያ ያደጋችሁ ያገሬ ልጆች ናችሁ። (You are one of my own blood, and my own people. You were the very center of Ethiopian Empire.) በራሳችሁ ባንዴራ ላይ፤ በራሳችሁ ንጉስ ላይ መተኮስ አቁሙ። ለኢጣልያ ስትሉ ለምን ትሞታላችሁ? በእንግሊዞች በኩል ወደኔ ኑ። ራስ ካሳ ከእኔ ጋር ጎጃም አለ። ጎጃም ሁሉ ከኛ ጋር ነው፤ እናንተም ወደኛ ተመለሱና ኢጣልያን ከሰላሌና ከደብረብርሃን ጠርገን እናጥፋው። እስካሁን ከሸዋ ብርጌዶች ከአንድ ሺህ በላይ ወደኛ መጥተዋል። የቀራችሁትም ወደኛ ኑና ሸዋ እና አዲስ አበባን ነጻ እናውጣ።"

በ1941 የኢትዮጵያዊነት ማንነት ገና ያልዳበረ እንደነበር የንጉሱ ደብዳቤዎች ይጠቁማሉ። ንጉሱ በከረን ግንባር በኢጣልያ ምሽግ ውስጥ ለነበሩ ጎጃሜዎች እና ሸዌዎች የተለያየ መልእክት ያላቸው ደብዳቤዎች መበተናቸው 'ለጎጃምና ለሸዋ ወታደሮች በአንድ ጠምረው መልእክት መላክ በቂ አልነበረም ወይ?" የሚል ጥያቄ ያጭራል። ፓንክረስት እንዳሰፈረው ለጎጃሜ የተላከው፣ "Gojjamis - It is in faithful Gojjam that I have set up my flag and won my first victories, come back to your homes." የሚል ሲሆን፣ እንደ ሸዋ ቀስቃሽና ልባዊ ቃላት አልነበሩበትም።

ቀደም ብለው አጤ ሃይለስላሴ "ይድረስ ለኢትዮጵያ ህዝብ" የሚል ወረቀት በትነው ነበር። በዚያ ማቆም ያልቻሉት "ኢትዮጵያ" የሚለው ቃል ከአገር መጠሪያነት አልፎ የማንነት መታወቂያነት ላይ ገና ያልደረሰ ስለነበር ይመስላል።

(በወቅቱ "ኢትዮጵያዊ ነኝ" ከማለት ይልቅ "ጎጃሜ ነኝ" "ጎንደሬ ነኝ" ማለቱ የቀለለ ነበር። የደቡብ፣ የኢጋዴን እና የከፊል ኦሮሚያ ህዝብ "ኢትዮጵያዊ ነኝ" የሚያሰኝ የስነልቦና ቁርኝት አልነበረውም። "የኢትዮጵያዊነት" ብሄራዊ አመለካከት በአገር ደረጃ እንዲጠነክር የተሞከረውና ውጤትም ያስገኘው ከመሬት ላራሹ አዋጅ በሁዋላ በመንግስቱ ሃይለማርያም ዘመነ መንግስት ነው ማለት ይቻላል። ከዚያ ቀደም ሲል ኢትዮጵያዊነት በከተሞችና "the very center of Ethiopian Empire." ለተባሉት ወገናዊ የሆነ ጠባብ ማንነት ነበር።)

በከረን ግንባር ኤርትራውያን በብዛት እየኮበለሉ ወደቤታቸው መሄድ ሲጀምሩ የመሃል አገር ሰዎችም መንቃት ጀመሩ። ሌሊት ወደ እንግሊዝ የሚጎርፈው የወታደር ቁጥር እየበዛ በመሄዱ የከረን መውደቅ የማይቀር መሆኑ ርግጥ ሆነ። ከ53 ቀናት ቆይታ በሁዋላ በመጨረሻዎቹ 16 ቀናት የእንግሊዙ የሰራዊት አዛዥ ጀኔራል ፕላት ከረንን አጥቅቶ መያዝ ቻለ። በዚህ ውጊያ የከረን ግንባር አዛዥ የነበረው ፍሩሲ ሲሆን፤ ይህ ጀኔራል ቀደም ሲል የጎንደር አስተዳዳሪ ነበር። ከረን ከተያዘች በሁዋላ የእንግሊዝ ሰራዊት አስመራን ለመያዝ ያገደው ሃይል አልነበረም። አስመራ ላይ የመሸገው ሁለት ባታሊዮን የኢጣልያ ሰራዊት እንደ ጎርፍ በመምጣት ላይ የነበረውን የብሪጣንያ ሰራዊት የመቋቋም ብቃት አልነበረውም። ለመከላከልም አልሞከረም።

የእንግሊዝ ሰራዊት በድል አድራጊነት አስመራ ከተማ ከመግባቱ በፊት በአስመራ አንዳንድ አካባቢዎች ዝርፊያዎች ተከስተው ነበር። ኢጣልያዊው የአስመራ አቡን እና የፖሊስ አዛዡ እንግሊዞች በፍጥነት አስመራ እንዲገቡ መልእክት ላኩባቸው። የአስመራ ነዋሪዎች በአብዛኛው በራቸውን ዘጋግተው ቤታቸው ተቀመጡ። የተሰጋውን ያህል አደጋ ሳይደርስ አስመራ ተያዘች።

የእንግሊዝ ሰራዊት አስመራ ሲገባ የነበረው ሁኔታ ፍጹም ሰላማዊ ነበር። የከተማው ነዋሪዎች እንግሊዞች አስመራ መግባታቸውን ያወቁት ባለ ግራ መሪ መኪኖችን ሲመለከቱ ነበር። እንግሊዞች መግባታቸው ሲታወቅ ኤርትራውያን ወደ ጎዳናዎች ዳርቻ በገፍ በመውጣት ድጋፋቸውን መግለጽ ጀመሩ።

በርግጥ በእንግሊዝ መምጣት ኤርትራውያን ምን ጥቅም እንደሚያገኙ የሚያውቁት ነገር አልነበረም። ጣልያን በመውደቁ ደስታቸውን መግለጻቸው ግን ተገቢ ሆኖ አጊኝተውታል። በጭቆና ቅኝ አገዛዝ ስር የወደቁ የአፍሪቃ ቀንድ ሰዎች ዝንተ አለም ከታሪክ የማይማሩበት አባባል ቢኖር ይኸው፣ "እነዚህ ይሂዱ እንጂ፤ የፈለገው ይምጣ" የሚለው ሆኖ ዘልቋል። "እነዚህ ይሂዱልን" ምንጊዜም ልክ ነበር። "የፈለገው ይምጣ" ግን ተሳክቶ አያውቅም። ኤርትራውያን በኢጣልያ መውደቅ ደስታቸውን ለመግለጽ ከበሮ ቢያነሱም፤ በምትኩ ምን እንደሚፈልጉ በትክክል አያውቁም ነበር።

ጦርነቱ ሲያበቃ በተለይ አስመራ ተጨናነቀች። በጦርነቱ ወላጆቻቸውን ያጡ ልጆች ወደ አስመራ ጎዳናዎች ጎረፉ። ሙያ እና ስራ አልባ ኤርትራውያን አስመራ ላይ ፈሰሱ። የሚበላና የሚጠጣ አልነበረም። ተላላፊ በሽታዎች መታየት ጀመሩ። ኤርትራውያን እጃቸውን አጣጥፈው ማንኛውንም ነገር ከእንግሊዝ ከመጠበቅ በቀር ሌላ ማሰብ የቻሉት ነገር አልነበረም።

የመናገር መብት መፈቀዱ ብርቅ ሆነ።

እንግሊዝ አስመራን ከተቆጣጠረችበት እለት ጀምሮ የኤርትራውያን መኖሪያ መንደሮችና የመጠጥ ግሮሰሪዎች አንደበታቸው ተከፈተ። የፖለቲካ ወጎች በከፍተኛ ድምጾች መነገር ጀመሩ። የፖለቲካ ወሬው ቢደምቅም ርባና ያለው አሳብ ግን አልነበረም። አንደበት ገና አልተገራም። በነጻነት የማሰብ ችሎታ አልዳበረም። በመሆኑም ወሬዎች መልክና ለዛ አልነበራቸውም። "እኛ ራሳችንን በራሳችን ማስተዳደር እንችላለን" የሚል አስተሳሰብ ገና ብቅም አላለ። ንቃት የነበራቸው አልነበሩም ባይባልም ወደ መድረክ ብቅ አላሉም። እነ ደጃዝማች ሃሰን ዓሊ እና እነ ፊታውራሪ ገብረመስቀል ወልዱ ብቅ እስኪሉ ድረስ ከማሸላው ማሳ መካከል ዘለግ ያለ አንገት አልነበረም። በሓጂ ኣደም ቁስመላህና በፊታውራሪ መሓመድ አበራ ሓሳስ መኖሪያ ቤቶች ጥቂት ኤርትራውያን በህቡእ መሰባሰብ እስኪጀምሩ ድረስ ወጎች ከግሮሰሪ ወሬ ያለፉ አልነበሩም።

ምሽት ላይ አርባዕተ አስመራ በወሬ ትነዳለች።

ግሮሰሪዎች ለወቅቱ የፖለቲካ ወግ ምቹ ሆነው ተገኙ። ኤርትራውያን የሌላ አገር ዜጋ ሳይቀላቅሉ ብቻቸውን ሊሰበሰቡበት የሚችሉበት ቦታ የመጠጥ መሸጫ ግሮሰሪዎች ነበሩ። በእነዚህ ግሮሰሪዎች የከተማዋ ምርጥ ተናጋሪዎች ዋና አክተር ሆነው ያመሻሉ። በትምህርታቸው፣ በቋንቋ ችሎታቸውና በፖለቲካ እውቀታቸው የተሻለ ደረጃ ላይ የሚገኙት መድረኩን በመቆጣጠር ጊዜው በሚፈቅደው መጠን ፖለቲካውን ያስደንሱታል።

አንዱ በድንገት ያለ ይሉኝታ በመሰለው መንገድ ቢናገር የተለመደ ነው። አንዳንድ ጊዜ አለመግባባት ሲፈጠር እስከ መደባደብ ያጋጥማል። ፖሊስ መጥቶ ገላግሎ ወደ ፖሊስ ጣቢያ እስኪወስዳቸው ድረስ ድብድቡ ይቀጥላል። በተለይ ወጣቶች

ካናቴራቸውን በማውለቅ ከወገባቸው በላይ እርቃናቸውን በመሆን፤ ደም እንደጠማው አውሬ ለገላጋይ ያስቸግራሉ። በኢጣልያ ዘመን አፈና ውስጣቸው ሲጠራቀም የከረመውን ብሶት በግሮሰሪዎች ጓዳ ያራግፉታል።

የኢጣልያ ሰላዮችም በግሮሰሪዎች አካባቢ ማንጣጥበባቸው አልቀረም። እየተዋወቁ አብረው ያመሻሉ። ወሬዎች ግን አይገደቡም። የተሸነፈችው ኢጣልያ "ተመልሳ ኤርትራን ትይዛለች" የሚል ስጋት አልነበረም። ጊዜው ራሱ በወሬ እሳት የሚነድበት፤ የለውጥ አየር የሚሸትበት የጋለ ጊዜ ነበር።

ጊዜው ኤርትራውያን ለአለም አቀፍ የፖለቲካ ጉዳዮች ትኩረት መስጠት የጀመሩበት ጊዜ ነበር። በተለይም የአስመራ ከተማ ነዋሪዎች የአለምን የፖለቲካ ሁኔታ ለመከታተል እድሉ ነበራቸው። አስመራ የብዙ የአካባቢው አገራት ስደተኞች መከማቻ በመሆኗ ከተለያዩ አገራት ዜጎች ጋር የመገናኘትና አብረው የመስራት እድሉ ነበራቸው። ይህም ከተለያዩ አግጣጫዎች ወሬ ያገኙ ዘንድ ያግዛቸው ነበር። በዚህም በዚያም ትኩስ ዜናዎች ይመጣሉ። የአፍሪቃ ቀንድ ብቻ ሳይሆን የመላው አለም ወሬ ወደ ግሮሰሪዎቹ እየመጣ ይዘረገፋል። ከጦርነት ወሬ በቀር ሌላ ርእሰ ጉዳይ አልነበረም።

ዑናይ የአርባዕተ አስመራ ግሮሰሪ ዋና አከተር ሆነ። ለሰባት አመታት ያህል በኢጣልያና በአረብ አገራት ከርሞ የመጣ በመሆኑ የተለያዩ ቋንቋዎችን ይናገራል። ዘመናዊ አለባበስና ዘመናዊ አነጋገር ያንጸባርቃል። ሆኖም ገና ከመነሻው እንግሊዝን መንቀፍ በመጀመሩ ግጭት ውስጥ ገብቶ ነበር።

"ጣልያንን ለመውቀስ ጊዜው ነው። በዚህ ጊዜ እንግሊዝን ማመስገን ግን መቸኮል ይሆናል።" አለ።

ከግሮሰሪዋ ደምበኞች አንዱ በጆሮው መከረው፣

"ዑናይ! እንግሊዝ ላይ ካላገጥክ ሊመቱህ ይችላሉ። እንግሊዝን መደገፍ ካልቻልክ በዝምታ መስማማት ይሻልሃል።"

ኢጣልያን ማጥላላት የጊዜው ፋሽን ሆነ። የእንግሊዝ ጀግንነት ተሰበከ። እንግሊዝ በቅኝ ግዛት በያዘቻቸው አገራት አስተዳደሯ ፍትሃዊ እንደሆነ የሚናገሩ ብቅ ብቅ አሉ። የእንግሊዝኛ

ቃላት የሚቀላቅሉ ሰዎችም ተሰሙ። ኢጣልያ በሃምሳ አመታት የቅኝ አገዛዝ ዘመን የፈጸሙትው በደል እየተጎረጎረ ይነገር ገባ።

ወሬው ዘንቦ ሳያባራ ተስፋው ጤዛ ሆነ።

እንግሊዝ ኤርትራውያንን ችላ ብላ የአውሮፓ ጎረቤቷን ለመታደግ ተጋች። ገቢ ለሌላቸው ጣልያናውያን ከካዝናዋ ድጎማ እስከ መስጠት ደረሰች። ለኤርትራውያን ለውጥ አልነበረውም። ኤርትራውያን በነጮች ይገዙ ነበር። ሌሎች ነጮች መጥተው ተደረቡ። ቢዝነሱም በኢጣልያውያን እንደተያዘ ቀጠለ። ኢጣልያንኛ ከሚችሉ ኤርትራውያን እንደተለመደው የአገልጋይነት ሚናቸው ቀጠለ። ቦታ አላገኙም። የነበረው ሁሉ እንደነበረው ቀጠለ። እንግሊዝ አስተዳደሩን ለኢጣልያውያን በመስጠቷ የመከዳት ስሜት ያደረባቸው ኤርትራውያን ጥቂት አልኮል ሲቀምሱ፤ እንደ እብደት ሲጀማምራቸው ታዩ። ቀስ በቀስ እንግሊዝን ማመስገን እየቀነሰ፤ ሁለቱንም አውሮፓውያን አገራት ደርቦ ማውገዝ ተጀመረ።

የእንግሊዝ ሰራዊት ከረን ሲገባ አንዲት የከበሳ ሴት እልልታዋን ስታቀልጥ የሰማ አንድ የእንግሊዝ ሰራዊት መኮንን፣ “I didn't do it for you” ሲል መናገሩ ይወሳል። ከኢጣልያዊት እናት እና ከእንግሊዛዊ አባት የተወለደችው ሚሸላ ሮንግ ይህን አባባል ተጠቅማ አሿፊ መጽሃፍ ጽፋለች። እንዲህ አለች፣

- ኤርትራውያን በቅኝ አገዛዝ የኖሩባቸውን መቶ አመታት ሲገልጹ፣ “በኢጣልያ ዘመን ጥጋብ ነበር፤ የመናገር ነጻነት ግን አልነበረም።” ይላሉ። በዘመነ እንግሊዝ የምግብ እጥረት ተከተለ፤ የመናገር ነጻነት ግን እንደልብ ሆነ። በኢትዮጵያ የቅኝ አገዛዝ ዘመን ኤርትራውያን ሁለቱንም አጡ። -

የሚሸላ ሮንግ አባባል ቀደም ብሎ በሌላ መልኩ ተገልጾ ነበር። በ20ኛው ክፍለ ዘመን አጋማሽ ላይ የኖረ አንድ ኤርትራዊ ገጣሚ እንዲህ ሲል ዘመን የተሻገረ ቅኔ አኑሯል፣

ኢትዮጵያ ወይም ሞት!” - ነበር ጥያቄያችን
ሁለቱንም ሰጠን - ቸሩ ፈጣሪያችን።”

ርግጥ ነው፤ “I didn't do it for you” ሲል እንቅጩን

የተናገረው እንግሊዛዊ መኮንን አልተሳሳተም። የኢጣልያ የቅኝ አገዛዝ እንዲወድቅ አደይ ማርያምን በጸሎት ሲያስቸግሯት የሰነበቱ ኤርትራውያን፤ ከኢጣልያ መውደቅ ቀጥሎ የገጠማቸው "ከሙሶሊኒ ምን ለየው?" የሚያሰኝ ሆኖ ተገኘ። ይህን የታዘበ ነባር አውሎኛ ባለማሲንቆ ባለ-አገሩ መንደር ብቅ ብሎ የህዝቡን ብሶት አንጎራጎረ፣

አንታ ኣነስየ ገሪሙኒ!
ማርሻንዴትሮ ንኹይድዶ መሲሉኒ?
ካብዚ ኹሉስ ሙሶሊኒዶ ምሓሸኒ?'
- - -

እኔስ በጣሙን ገረመኝ!
በሁዋላ ማርሽ የምንሄድ መች መሰለኝ?
ከዚህስ ሙሶሊኒ በተሻለኝ?

* * *

የፋሲካ በአል በተከበረበት አንድ ተስያት አርባዕተ አስመራ ግሮሰሪ ሞቃና ደምቃ ነበር። ደጃፉ ሳይቀር በጠጪዎች ተጣበበ። በዚያን ምሽት ዑናይ ወገኛ ሆኖ አመሸ። "ነገር በምሳሌ፤ ዝማሬ በሃሌ - እንዲሉ አባቶቻችን" ብሎ ከጀመረ በሁዋላ ወቅታዊውን የኤርትራ ሁኔታ የሚገልጽ ራሱ የፈጠረውን ተረት አጫወታቸው።

"...ስለ አንድ አዞ ልንገራችሁ!" ሲል ጀመረ።

"አዞው እንደልማዱ በማለዳ ከወንዝ ወጥቶ ከዳርቻው አሸዋ ላይ ተኛ። ከዚያም እስከ መጨረሻው አፉን ከፈተ። በመቀጠል አይኖቹን ጨፈኖ የአፍሪቃን ዝነኛ ደማቅ ጸሃይ መሞቅ ጀመረ። በፍጹም ስለማይንቀሳቀስ የሞተ መሰለ።

"...የአካባቢው አነስተኛና ትላልቅ አእዋፍ በአዞው ዙሪያ ተሰባሰቡ። በአዞው ጥርሶች ውስጥ የተሰገሰጉ ቁርጥራጭ ስጋዎች ይታዩ ነበርና እነርሱን ለመለቃቀም ተመኙ። ግን ደግሞ ፈሩ። ስለ አዞው ሁኔታ ማወቅ አልቻሉም። "ሞቷል ወይስ አልሞተም?" ለሚለው ተገቢ ጥያቄ መልስ ማግኘት ነበረባቸው። ለማወቅ ጥረት ቢያደርጉም ግን አልቻሉም። አባኮዳ ጆሮው ስር ተጠግቶ በሚያከላላ ድምጽ ቢጮህበትም እንኳ አዞው አልተንቀሳቀሰም።

“...በዚህ መካከል ትእግስቷን የጨረሰችና የተራበች አንዲት አነስተኛ ወፍ ዘልላ ከአዞው አፍ ገብታ ከጥርሶቹ መካከል ስጋ መለቃቀም ጀመረች። በዚህ ጊዜ ወፎቹ ተደፋፈፍረው ወደ አዞው አፍ ተሞጀሩ። ጥርሶቹ ላይ ሰፈሩበት። በዚያው ቅጽበት ግን የአዞው አፍ ተከደነ። አይኖቹ ተከፈቱ። ከጥቂት ደቂቃዎች ማኘክ በሁዋላ አዞው ተመልሶ ወደ ወንዙ ጥልቅ ገባ።

“ሌላ አዞ ደግሞ መጣ።

“እንደ ቀዳሚው አዞ አፉን ከፈተ። አይኖቹንም ዘጋ።

“...የአባቶቻቸውን ወይም የእህት ወንድሞቻቸውን የአሟሟት ታሪክ ያላወቁ ሌሎች ወፎች ደግሞ መጡና በአዞው አፍ ዙሪያ ተሰበሰቡ። እና ወግ ጀመሩ። ቀዳሚውን ታሪክ የሚነግራቸው ስላልነበረ እንደገና ተመሳሳይ ጥያቄ መጠየቅ ጀመሩ።

“አዞው ሞቷል ወይስ አልሞተም?”

በዚያው ሰሞን በኤርትራ ፖለቲካ ውስጥ የአንዳንድ ሰዎች ስም መሰማት ጀመረ። ባንድ በኩል ብቅ ያሉት ራስ ተሰማ አስበሮም፣ ደጃዝማች ሃሰን አሊ፣ ሸኽ ኢብራሂም ሱልጣን፣ ወልደአብ ወልደማርያም፣ አብዱልቃድር ከቢረ ሲሆኑ፤ በሌላ በኩል ደግሞ ፊታውራሪ ገብረመስቀል ወልዱ፣ ደጃዝማች አርአያ ዋሴ፣ ፊታውራሪ ሓረጎት አባይ፣ ብላታ ደምሳስ ወልደሚካኤል ነበሩ። እነዚህ በሁለት ጎራ ወደ ኤርትራ ፖለቲካ ብቅ ያሉት ሰዎች ወደ ተለያየ አግጣጫ እንደሚበሩ ወፎች ነበሩ። ቀዳሚዎቹ “የሃገር ፍቅር ማህበር” በሚል ስያሜ መሰባሰብ ቢጀምሩም መንገዳቸው የኤርትራን ነጻነት የሚጠይቅ ሆነ። እስከ 1944 በአገር ፍቅር ማህበር ስር የተደራጁ ኤርትራውያን ሁዋላ ተከፋፈሉ። እና “ሕብረት ከኢትዮጵያ ጋር” የሚል መፈክር የያዘ ቡድን ብቅ አለ። በአከለ ጉዛይ አካባቢ ከፍተኛ ተቀባይነት ያገኘው በራስ ተሰማ አስበሮም የሚመራ ሊብራል ፕሮግረሲቭ ፓርቲም ተመሰረተ። ያም ሆኖ ቡድኖቹ የፖለቲካ ልምድ እና ግልጽ ራእይ አልነበራቸውም።

ድጋፍና ተቃውሞ ጦፈ።

ድጋፉም ሆነ ተቃውሞው ግን የሰለጠነ አልነበረም። አንዱ

ሌላውን ለመደገፍ አላማው ሳይሆን ሃይማኖቱ የድጋፍ ምንጭ ይሆንለታል። የመረረ የጠላትነት ስሜት ግን አልነበረም።

በኤርትራ ታሪክ ውስጥ አውራጃ ለአውራጃ ወይም አንዱ ጎሳ ሌላውን የጨቆነበት፣ የገዛበት ዘመን ስላልነበረ በኤርትራዊነት ለመሰባሰብ ችግር ሳይፈጥርባቸው ቀረ። ርግጥ ነው፤ በ19ኛው ክፍለዘመን መጨረሻ አካባቢ የተከሰቱ የመዘራረፍ ታሪኮች አሉ። ቂም ትተው ያለፉ ግን አልነበሩም። የተለያየ ቋንቋ የሚናገሩ የኤርትራ ጎሳዎች የርስበርስ ችግር እንዳይኖርባቸው ካደረገው አንዱ የኢጣልያ ቅኝ ገዢ ኢትዮጵያ ላይ እንደሞኮረው ኤርትራን በዘርና በጎሳ ሊከፋፍል አለመፈለጉ ነበር። የሃይማኖት ልዩነት ይፈጥር የነበረ ቢሆንም፤ ሙስሊምና ክርስትያን በኤርትራ ደም የመቃባት ታሪክ አልነበራቸውም።

ግንቦት 5 1941 የኤርትራ የሃገር ፍቅር ማህበር ተመሰረተ። ስድስት ሙስሊም እና ስድስት ክርስትያኖች ሆነው ተደራጁ። በዚያኑ ቀን ሰላማዊ ሰልፍ ጠርተው በሺህዎች የሚደርስ ሰልፈኛ የመብት ጥያቄዎችን ይዞ ወደ አስመራ ቤተመንግስት አቀና። ወታደራዊ አስተዳዳሪ የነበረው ብርጋድየር ጄኔራል ኬኔዲ-ኩክ በሸኽ አብደልቃድር ከቢረን ተቀብሎ አነጋገረ። ከቢረ ህዝቡን ወክለው ሲናገሩ፣ "እንኳን ደህና መጣችሁ!" ካሉ በሁዋላ የኤርትራ ህዝብ የእንግሊዞችን መምጣት በተስፋ መጠበቁን ገለጹ። አያይዘውም እንግሊዞች የገቡትን ቃል ጠብቀው የኤርትራን ህዝብ ለነጻነቱ እንዲያበቁት ጠየቁ። የኬኔዲ-ኩክ ምላሽ ጥሩ አልነበረም። ጥያቄውን መስማቱን ገልጾ ሲያበቃ፤ ሰልፍ ማካሄድ የተከለከለ መሆኑን ገልጾና አስጠንቅቆ ሸኛቸው። የከተማዋ ህዝብ ግን ሲጨፍር እና ስለ ነጻነት ሲዘምር ውሎ ከምሳ በፊት ወደየቤቱ ተበታተነ። የማህበሩ መመስረት እና የእለቱ ሰልፍ በኤርትራ ታሪክ የመጀመሪያው የተደራጀ እንቅስቃሴ ነው።

እንግሊዛዊው ወታደራዊ አዛዥ ኤርትራውያን ሰልፍ እንዳያደርጉ፣ እንዳይሰበሰቡ፣ ረጅም ዱላ ይዘው እንዳይንቀሳቀሱ ከማገድ በቀር ሌላ ሊያደርግ የሚችለው ነገር አልነበረውም። ምክንያቱም ሁለተኛው የአለም ጦርነት የተፋፋመበት ጊዜ ነበር። እንግሊዝ ለህልውናዋ ከባድ መስዋእትነት እየከፈለች ባለችበት ጊዜ

የኤርትራውያንን ጥያቄ ቀዳሚ አጀንዳዋ አልነበረም። በአንድ ቀን ጊዜ ውስጥ ከኤርትራ ህዝብ ቁጥር የበለጠ አውሮፓዊ ህይወቱን የሚያጣበት የፍጅትና የእልቂት ዘመን ነበር።

ዑናይ ወሬ እየቃረመ አዲስ ወግ ስለሚያመጣ ዝናው ጨመረ። የአውሮፓን የፖለቲካ ውጥረት በተመለከተ ወሬ ያገኛል። በተለይ አውሮፓ ወደለየለት የርስበርስ ጦርነት ከገባች በሁዋላ ዑናይ ዋና የወሬ ምንጭ ሆነ። ሁሉም በየፊናው ከሰው የሰማውን እያመጣ ይዘረግፋል። አጋንነው ያቀርባሉ። በከፉም ሆነ በደግ ጀርመን ስሟ ሰማይ ነካ።

አንድ ምሽት ዑናይ እንግዳ ይዞ መጣ። በዚያን ምሽት የአርባዕተ አስመራ ግሮሰሪ ደምበኞች ከዚህ ቀደም ሰምተዋቸው የማያውቋቸውን ቃላት ሰሙ። ከእነዚህ ቃላት መካከል፣ “ኤርትራ ለኤርትራውያን” የሚል ይገኝበት ነበር።

ግሮሰሪዋ በጸጥታ ተውጣ አመሸች።

እንግዳው ሰው ረጋ ብሎ ነበር የሚናገረው። አልፎ አልፎ ግን ገጽታው እየተለዋወጠ ጠንካራ ድምጽ ያፈልቃል። ቁጭት የሚያሳድሩ፣ እንባ የሚያስደፍቁ ንግግሮቹ የግሮሰሪዋን ደምበኞች ተቆጣጠሩ። የእንግዳውን ንግግር ለማቋረጥ የደፈረ አልተገኘም። ጥያቄ እንኳ የጠየቀ የለም። እንግዳው ሰው፣ “ራስን ማክበር”፣ የሚል ቃል ደጋገመ። “ከአሽከርነት አስተሳሰብ መላቀቅ” የሚለውን ቃልም አጠነከረው። ”ከእኛ ከራሳችን በቀር ለእኛ ሊያስብ የሚችል ማንም የለም” የሚለውን የተናገረው በለሆሳስ ነበር። “እኛ በጎች አይደለንም” ያለው ግን በቁጣ ድምጽ ሆነ። “ለሌሎች ጥቅም ህይወትን መክፈል ከሞት በላይ ውርደት ነው!” ሲል ጮኸ። አስከተለናም፣ “የባርካን ከብት እንኳ ማንም አይነዳውም።” አለ። የእንግዳው ቃላት የግሮሰሪዋን ደምበኞች አእምሮ እየሰረሰሩ ገቡ።

ከዚያች እለት በሁዋላ ግን እንግዳው ወደ ግሮሰሪው ተመልሶ ሳይመጣ ቀረ። በተለያዩ ግሮሰሪዎች እየዞረ እንዲህ ያለ ንግግር እንደሚያደርግ ግን ሰሙ። እንግዳው ስሙ “ኤልያስ”’ እንደሚባል ቢሰማም ከየት እንደመጣ የሚያውቅ አልተገኘም።

እንዲህ ያሉ የማይታወቁ እና “ኤርትራ - ለኤርትራውያን”

የሚል መፈክር የያዙ ወጣቶች ወደ ግሮሰሪዎች ብቅ ማለታቸው ይደጋገም ቀጠለ። ሌላ ጊዜም እንዲሁ ደግሞ ዑናይ “ሳልሕ” የሚባል ሌላ እንግዳ ሰው ይዞ መጣ። ሕርጊጎ ከመወለዱ ያለፈ ስለዚህ ሰው ሌላ ዝርዝር ነገር አልታወቀም። ከትግርኛ ባሻገር አረብኛና ፈረንሳይኛ አንቀባሮ በመናገሩ ግን ከጅቡቲ ወይም ከሰሜን አፍሪቃ የመጣ ሊሆን እንደሚችል ገመቱ።

* * *

የአውሮፓ ጦርነት ወደ እልቂት በተሸጋገረበት ሰሞን ዑናይ የአውሮፓን ጦርነት አንስቶ ተረከ፣

- ቮልጎ ግራድ ከስድስት መቶ ሺህ ሰው በላይ በረሃብና በችጋር አልቆባት እንኳ ራሺያ እንዲህ ያለውን ከባድ ፈተና ተቋቁማ ጀርመን ላይ ድል በማድረግ ላይ ነች። ወጣቱ ትውልድ መስዋእትነት ለመክፈል ዝግጁ ስለሆነ ከፊቱ ሊቆም የሚችል የለም።

- ጎሮቼትስ በአንድ የበረራ ውጊያ ዘጠኝ የናዚ ጀርመን ተዋጊ አይሮፕላኖችን አቃጥሎ ሲያበቃ እሱም ራሱ ተቃጠለ። የሶቭየት ሰራዊት በድኔስተር እና በድኔፐር ወንዞች ዙሪያ ተዋጋ።

- አዴሳ ከተማ ነጻ ወጣች። በጥቁር ባሕር እና በከሪሚያ አካባቢ ውጊያው ተጧጡፎ ቀጠለ። እንግሊዝና አሜሪካ ፈረንሳይ መሬት ላይ በማረፍ ጀርመን ላይ ሁለተኛውን ግንባር ከፈቱ።

- የሶቪየት ሰራዊት ማጥቃቱን በመቀጠል ወደ ፊንላንድና ኖርዌይ አቀና። ምእራብ ቤላሩስያና ኡክራይና ነጻ ወጡ። ሚኒስክ ተያዘች። ልቮቭ ከተማ ነጻ ወጣ። በዚህ ግን አላበቃችም። አውሮፓን ከናዚ የማጽዳቱ ዘመቻ ቀጠለ። ፖላንድ ተከባለች።

ከግንቦት እስከ ሰኔ ባለው ጊዜ ናዚ የቮሮኔዤን ከተማ ያዘ። ብረታ ብረቶቹ ወደ ካውካሰስ ሲገሰግሱ ቮልጎ ግራድን ክፉኛ አጠቋት። ቮልጎ ግራድን ከያዙ ቮልጋ ወንዝ ከትራንስፖርት አገልግሎት ውጭ ስለሚሆን ይህ ለሶቪየት ራሺያ አደገኛ ነበር። እና በዚህ ጊዜ የሶቪየት መከላከያ ምኒስትር ምን አለ?

“አንዲት እርምጃ ወደ ሁዋላ የለም!!”

- የናዚ ጀርመን ሃይል ግን ጠነከረ። 26 ሺህ መድፎች፣ ሁለት ሚሊዮን ሰዎች እና ከ2 ሺህ በላይ ታንኮች የተሳተፉበት ውጊያ ተካሄደ። በየቀኑ አንድ ሺህ የናዚ ተዋጊ አይሮፕላኖች ቮልጎ ግራድን ደበደቡ። ከተማዋ በእሳት ተያያዘች። ናዚዎች የከተማውን ምሽግ ባንድ በኩል ጣሱ። ሩስያኖች ተሟሟቱ። "ከቮልጋ ወዲያ አገር የለንም" የሚል ድምጽ ተሰማ። ከዚህ ቁርጠኛነት በሁዋላ ሰው መሆናቸው የሚያጠራጥር ሰዎች ከጦርነቱ እሳት መሃል ተወለዱ።

- ማሺንገን ተኳሾች ታዩ። የሰው ልጅ እንዴት ጀግና መሆን እንደሚችል ለአለም ህዝብ አሳዩ።፤ ቤሎሩስያዊው ሚኻኤል ናቺንኪን፤ የሞልዶቪያ ተወላጅ አርኬ ታራኩል እና ያኮቭ ፓቭሎቭ ደረታቸውን ገልብጠው በመግባት አለቦታው የተገኘውን የጀርመን ወራሪ ረፈረፉት። ሰውነታቸው ላይ ፈንጂ እየጠመጠሙ ወደ ናዚ ታንኮች ገሰገሱ። ቮልጎ ግራድ ሳትንበረከክ ናዚ ጀርመን አፈገፈገች። -

ዑናይ ይህን ሲተርክ ከፍተኛ ጭብጨባ ተሰማ።

የከረመ፣ ቋንጣ የሆነ ዜና የሚሰሙ አልመሰላቸውም። ዑናይ አነጋገሩ በስሜት ስለነበር፣ የሶቪየት ደጋፊ ሆኖ ስለሚናገር በዚያኑ እለት የተፈጸመ ያህል አድርጎ ነበር የሚያቀርበው። አንዳንድ ጊዜ ክስተቶችን ሲገልጽ በቦታው የነበረ ይመስላል።

ቅዳሜ ዞሮ በመጣ ቁጥር ዑናይን ለመስማት የሚጎርፈው ሰው ቁጥሩ እየጨመረ ሄደ። ግሮሰሪዎች ዑናይን ለመያዝ ተሻሙ።

ጦርነት እንጂ ሌላ ወሬ አልነበረም።

በዚያው ሰሞን ዑናይ አደጋ ገጠመው። እንደተለመደው እንዲህ ከየቦታው የቃረመውን ዜና እያወጋ ነበር። ቀዩ ሰራዊት ሩማንያን ነጻ ካወጣ በሁዋላ ወደ ቡልጋርያ መሻገሩን ተናገረ።

- ቡልጋርያውያን ከቀዩ ሰራዊት ጋር ታጠቁ። ዩጎዝላቪያና ሃንጋሪ ቀጠሉ። የናዚን ወራሪ ሰራዊት ከፖላንድ ጠርጎ ለማስወጣት በተደረገው ከባድ ውጊያ ከሶቪየት በኩል 600 ሺህ ወታደር ህይወቱን እንደከፈለ ዑናይ ሲናገር፤ የባቡር ቴክኒሻን የሆኑ አንድ ሽማግሌ በያዙት ከዘራ ጭንቅላቱን መቱት። ሽማግሌውን ያስቆጣቸው ዑናይ የሚናገረው ውሸት ነው ብለው በማመናቸው ብቻ ሳይሆን፤ እንዲህ በሰው ህይወት ላይ ማላገጥ ነውር ሆኖ

ስለተሰማቸው ነበር።

ግርግሩ ረግቶ በሽማግሌውና በዑናይ መካከል እርቅ ከተደረገ በሁዋላ አዛውንቱ የተነገረውን ማመን ስላልቻሉ፣

“በአንድ ውጊያ ላይ 600 ሺህ ወታደር ካለቀ ከመነሻው ስንት ወታደር ቢኖራቸው ነው?” ብለው ጠየቁት።

“አላውቅም።” አለ ዑናይ “ብዙ ሚሊዮን ይሆናል።”

ሽማግሌው ግን ሊያምኑ አልቻሉም።

* * *

እንግሊዝ ኤርትራን በተቆጣጠረች ከጥቂት ወራት በሁዋላ ጋዜጦች በትግርኛና በአረብኛ ቋንቋዎች መታተም በመጀመራቸው በተለይ የአስመራ የኤርትራውያን ማህበረሰብ ተነቃቃ። ከግሮሰሪዎች ወግ ወደ ጋዜጦች ተሸጋገረ። ዑናይም “ሰሙናዊት ጋዜጣ” ላይ ወጎችን መጻፍ ጀመረ። ከሰሙናዊት ጋዜጣ ቀጥሎ “ኢትዮጵያ” የምትባል ጋዜጣ መጣች። “ሰውት አል ራቢጣ”፣ “ሓንቲ ኤርትራ”፣ “ዘመን”፣ እና “ደሃይ ኤርትራ” የሚል ስም የያዙ ጋዜጦች ፈሉ። ኤርትራን በተመለከተ ፖለቲካዊ ሙግት ጦፈ። የኤርትራ ጉዳይ ጦዘ። ጋዜጦች ደምበኛ ለመያዝ ተሻሙ። ለዚህም ከአገራዊና አካባቢያዊ ጉዳዮች ባሻገር አለማቀፍ ሁኔታውን ጭምር መዳሰስና መተንተን ጀመሩ። አልራቢጣ፣ ህብረት ከኢትዮጵያ፣ ኤርትራ ለኤርትራውያን፣ ፕሮ ኢጣሊያ የተባሉ የፖለቲካ ፓርቲዎች ጋዜጦች እየታተሙ የህዝቡን ንቃተ ህሊነና አዳበሩ። ፓርቲዎች የየራሳቸውን ጋዜጣ መስርተው አቋማቸው ተከታይ ያገኝ ዘንድ ጥረታቸውን ቀጠሉ። የቃላት ንክሻው ከረረ፣ መረረ። በተለይ “ህብረት ከኢትዮጵያ” ደጋፊዎች መራር ቃላትን በመጠቀም ታወቁ። ፕሮ-ኢጣልያን “የፋሽስትን ስርአት ለመመለስ” የሚል ስም ተለጠፈባቸው። አልራቢጣ፣ “የሃይማኖት አላማ ያላቸው” የሚል ታርጋ ተለጠፈላቸው። ይህን ተከትሎ የሽብር ተግባራት ይከወኑ ጀመር። “ኤርትራ ለኤርትራውያን” ደጋፊያቸው እየበረታ በመሄዱ ቀዳሚ የጥቃት ኢላማ ሆኑ። “ሓንቲ ኤርትራ” እና “ደሃይ ኤርትራ” ጋዜጦች ይበልጥ ተነባቢ ሆኑ። እሳት የላሱ የአረብኛ ቋንቋ ጸሃፊዎች “ሰውት አል ራቢጣ”ን ተነባቢ አደረጓት። “ዘመን” ጋዜጣ የመንግስት

አፈቀላጤ በመሆን ተናቀች። በትግርኛ እና በአረብኛ ትታተም የነበረችው የኢጣልያ ደጋፊዎች ጋዜጣ “የኤርትራ መብራት” (Luce Dell Eritrea) ጠንካራ አንባቢዎች ነበሯት። በተለይም የሁለተኛው የአለም ጦርነትን በተመለከተ ዘገባዎች እና የአለም ዜናዎችን ይዛ ስለምትቀርብ ፈላጊዋ ቀላል ቁጥር ያለው አልነበረም። ወልደአብ ወልደማርያም፣ ማሕሙድ አረብዕ፣ በሺር ዑስማን፣ በሺር ሓለቐ፣ መሓመድ ዑስማን ሓዩቲን፣ ያሲን መሓሙድ ባጡቅ፣ ተድላ ባይሩ፣ ዘባራቒት በሚል ቅጽል ስሙ የሚታወቀው ገብረሚካኤል ግርሙ፣ አሕመድ አልሓዩት፣ ሓስበላ ዓብደላ ረሓም፣ በጋዜጦች በኩል ግንባር ቀደም ተፋላሚዎች ሆኑ።

በተለይ በ1944 የኤርትራ አስተዳዳሪ የነበረው እንግሊዛዊ ብርጋድየር ሎንግሪን በብእር ስም ያሰፈረው ጽሁፍ አቧራ አስነሳ። አሳቡ ኤርትራ ለሁለት ተቆርሳ ቆላው ለሱዳን ደጋው ለኢትዮጵያ እንዲሰጥ የሚመክር ነበር። አሳቡ ወዲያውኑ በኤርትራውያን ውድቅ ተደረገ። መታሕት ወይ ደጋ፤ ሙስሊሙም ሆነ ክርስትያኑ የኤርትራን መከፋፈል እንደማይቀበል አሳወቀ።

በርግጥ ሎንግሪን ይህን አሳብ ለመሰንዘር መነሻ አልነበረውም ማለት አይቻልም። በወቅቱ ሙስሊሙ የኤርትራ የህብረተሰብ ክፍል “የክርስትያን ደሴት” የተባለችውን አገር እና ራሱን “የይሁዳ አንበሳ” እያለ በሚጠራ ንጉስ የምትተዳደረውን አገር ለመቀላቀል የሚቀበለው አልነበረም። ክርስትያኑ በበኩሉ የሱዳንና የግብጽ እስላማዊ መንግስት በእጅ አዙር ኤርትራን ይይዛታል የሚል ስጋት ነበረው። በመካከሉ ግራና ቀኙን ያመዛዘኑ “ኤርትራ ለኤርትራውያን” የሚል መሪ መፈክር የያዙ ወገኖች ሚዛን ደፉ።

ነጻነት ጠያቂዎች ትግራይ ያለችበትን ሁኔታ በማየት ከኢትዮጵያ ጋር መዋሃዱን አጥብቀው ይኮንኑ ነበር። ትግራይ የነበረችበት ሁኔታ መጥፎ ምሳሌ ነበር። የትግራይ ህዝብ ጤናው በፍጹም አይጠበቅለትም። ትምህርት አያገኝም። በኢጣልያ ቅኝ ግዛት ዘመን ትግራይ ላይ ከተከፈቱት 38 አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መካከል፤ ከጣልያን መልቀቅ በሁዋላ ስድስት ብቻ ቀርተው ነበር። ትምህርት ቤቶቹ ከተዘጉ በሁዋላ ቤቶቹ ፈራረሱ። ጎንደር በኢጣልያ ቅኝ አገዛዝ ዘመን ደማቅ ከተማ ወደመሆን ተለውጣ

ነበር። ጣልያን ሲሄድ በተመሳሳይ ከተማዋ ፈራረሰች። በሮችና መስኮቶች እየተገነጣጠሉ ወደቁ።

ነጻነት ጠያቂዎች የኢትዮጵያን ሁዋላ ቀር አስተዳደር በማየት ከኢትዮጵያ ጋር ከመቀላቀል ራሳችን ኤርትራን ማስተዳደር ይበጀናል ወደሚል ደረሱ። "ሙስሊሙ ኤርትራን ይውጣታል" ወይም "ኤርትራን ወደ ሳዑዲ አረቢያ ይቀላቅላታል" በሚል ቅስቀሳ የተደናገጡ የተዋህዶ አማኞች በወቅቱ ራሷን የክርስትያን ደሴት ብላ ወደ ምትጠራው ኢትዮጵያ ወደ መቀላቀሉ አዘነበሉ።

የአስመራ ፖለቲካ ከኢጣልያ መባረር በሁዋላ መልኩን ለወጠ። ኢትዮጵያ እና ኢጣልያ "የኤርትራ መሬት ይገባናል" ብለው ሲሟገቱ፤ የየራሳቸውን ደጋፊ ለመያዝ ጥረት አደረጉ። ከኢጣልያም ሆነ ከኢትዮጵያ ጋር ያልተቧደኑ ወገኖች ባንጻሩ፣

"ራሳችንን በራሳችን ማስተዳደር እንፈልጋለን።" የሚል ድምጻቸው በርትቶ ቢሰማም፤ "ህብረት ከኢትዮጵያ" የሚሉም ተጽእኖ የማድረግ ችሎታቸው ከፍተኛ ነበር። እንግሊዝ የኤርትራ ጉዳይ የሚፈታው የአውሮፓ ጦርነት ካለቀ በሁዋላ መሆኑን እያስገነዘበች፤ እስከዚያው አመለካከቶች እንዲንሸራሸሩ አበረታታች።

* * *

የተባበሩት መንግስታት በኤርትራ ጉዳይ ውሳኔውን ሰጥቶ፤ የድርጅቱ ተወካይ ኤንዞ ማትየንዞ የኤርትራን ህገ መንግስት ለማርቀቅ አስመራ በገባ ሰሞን ገብርኤል ኤድሞንዶ ለሁለተኛ ልጁ እንዲህ ሲል አጫወተው፣

"ጣልያን ብዙ አሰቃይቶኛል። አሰረኝ፣ ደበደበኝ። ብዙ ጉዳት አደረሰብኝ። ነገር ግን እንዲህ ያሰቃዩኝን ጣልያኖች አልጠላቸውም። አጥብቄ የምጠላቸው ከሞቅዲሾ እስር ቤት ነጻ ያወጡኝን እንግሊዞች ነው። በንብረት እና በሰው ላይ ብዙ ግፍ ፈጽመዋል። ለኤርትራ ጠቃሚ የነበሩ ሰዎችን በተለያየ ዘዴ ገደሉ። የደረሱበት ያልታወቀ በጣም ብዙ ናቸው። ንብረት ዘርፈው ወሰዱ። በኤርትራ የሰው አቅምና ንብረት ላይ ብዙ ጉዳት አድርሰዋል።"


በእርግጥ የእንግሊዝ ሚና ምንጊዜም መጥፎ ብቻ ሆኖ

አያውቅም። “አንዱ ብስል፣ አንዱ ጥሬ” ተብሎ ይታወቃል። ከፋፍላ በመግዛትና የተቀበረ ፈንጂ ትታ በመሄድ ችሎታዋ የምትታወቀው እንግሊዝ በኤርትራም ሁለት መልክ ነበራት። ብስልና ጥሬ።

የአውሮፓ ጦርነት በሚካሄድበት ጊዜ በኤርትራ የከተመው የእንግሊዝ ወታደራዊ አስተዳደር ስራ አልፈታም። በጎም ሆነ ክፉ ተግባራት ፈጽሟል። ባንድ በኩል የኤርትራውያን ንቃተ ህሊና እንዲዳብር ፕሬሱን ነጻ በመልቀቅ መንገድ ሲከፍት፤ በሌላ በኩል ጣልያን የገነባውን በማፍረስ አሳፋሪ ተግባር ፈጽሟል።

እንግሊዝ በጦርነት አሸንፋ ኢጣልያን ከኤርትራና ከኢትዮጵያ በማስወገዷ፤ በሁለቱ አገራት የነበረውን የኢጣልያ መንግስት ንብረት ሁሉ የመውረስ መብት እንዳላት አምናለች። ሰነድ፣ ቅርስና ወርቅ መውሰድ አልበቃ ብሏት፤ የተገነባን አፍርሳ ወደ ሌላ አገር መሸጥ ደረሰች። ይህ ድርጊት “የስልጣኔ አባት ነኝ” ብላ ለምትመካው እንግሊዝ አሳፋሪ ነበር። የመጪው ዘመን የህዝቦች ግንኙነትና ቀሪ ታሪክ እንኳ አላስጨነቃትም። ተራ የቁሳቁስ ዘረፋ ውስጥ ገብታ ዋኘች። ከምጽዋ አስመራ የተዘረጋውን የአየር ላይ ባቡር መጓጓዣ ሽቦ ጠቅልላ ወሰደች። እስከ ጎንደር ባቡር ሃዲድ ለመዘርጋት ታስቦ የተከማቹ የብረት አገዳዎች ተሸጡ።

በኢጣልያ ዘመነ መንግስት አራተኛ ክፍል ላይ ተገድቦ የነበረው ትምህርት በዘመነ እንግሊዝ እገዳው መነሳቱ አንድ እመርታ ነበር። በተመሳሳይ በእንግሊዝ ዘመን የመናገር ነጻነት ተለቆ፤ የግል ጋዜጦች በመፈቀዳቸው የህዝቡ ፖለቲካዊ ንቃተ ህሊና በፍጥነት አድጓል። እንግሊዝ የዘረፈችው ቁሳቁስ ከዚህ በጎ ድርጊቷ ጋር ሚዛን ላይ ሲቀመጥ፤ የተዘረፈው ቁሳቁስ ሳይነገር የሚዘለል አልነበረም። ሻለቃ ዳዊት ወልደጊዮርጊስ “Red Tears” በተባለ በመጽሃፉ እንደገለጸው እንግሊዝ ኤርትራ በቆየችበት አስር አመታት ጊዜ ውስጥ 62 ሚሊዮን ፓውንድ የሚገመት ንብረት ከኤርትራ ሰርቃ ሸጣለች። በአፍሪቃ ከደቡብ አፍረቃ ቀጥሎ የኢንዱስትሪ አገር ተብላ የምትታወቀውን ኤርትራ በማውደሙ ረገድ ከእንግሊዝ ቀጥሎ የአጤ ሃይለስላሴ መንግስት ተመሳሳይ ሚና ነበረው።




con l'assistenza del sottoscritto
al dibattimento della causa:

CONTRO

1°) GABRIELE EDMONDO GARAMEDIN fu Edmondo di anni 25 da Asmara detenuto
2°) MESFUN MAGASCE' di anni 24 nato in Eritrea = latitante
3°) GABREMARIANTEDROS di anni 19 da Salalé eritreo = detenuto
4°) ASGHEDON AILU' fu Ailù Imberò di anni 19 da Asmara = detenuto
5°) PITAURARI EDOARDO GARAMEDIN fu Garamedin di anni 50 da Cheren
6°) GHIDANE' ADGOI nato a Cheren resid.ad Addis-Abeba = latitante
7°) NEGASCE ABERA' di Uollariat di anni 36 da Misalim = detenuto
8°) STEFANO EDOARDO GARAMEDIN di Edoardo di anni 18 da Asmara=detenuto
9°) MESCHEBE' MACONNEN e di Lem-Lem di anni 15 da Asmara = detenuto
10°) BIGARIE' MACONNEN di Maconnen di anni 18 da Asmara = detenuto

ስለተገኘበት ደብዳቤ ምንነት ገበሪኤል ኤፍሬገደ አንዲገልጽ በመረመርና ቢጠ
የቅ ጉዳዱን ለለመገለጽ በኢጣሊተኘነት ፀና:: ሆኖም የደበዳበው ፀሐፊ ግለት የፊ
ታውራሪ ኤፍሬርደ ሊጅ ሥዒፍናስ ኤፍሬርደ የተባለ በቀታዚቭ በመንግሥት ጽ/ጤት
የመኪና ፀሐፊ የሆነ መናፈነ ከፈቢኔሪ ሰለደረሰበት፣እ.ኤ.አ. ሰቅሉ 1 ቀን 1935
ዓ.ም. አንዲያዝ ተደረገ:: በተደረገውም የቤቱ ፈተሻ ወለጅ አበቱ የፀፋለት ደበዳ
በና ኩቡም ሥዒፍናስ በቀታዚቭ ነዋሪ ከሆኑ ወጣት ኤርትራዊያን ጋር ያደረገው የነ
በረው መለዳና የሚገልጹና፣ በመከካለቸው በኢጣልያ መንግሥት ላይ ለማደም ያደርጉት
የነበረውን ሤራ የሚያጋልዋ ጽሑፍች ከመገኘታቸው በለይ መዝገበ መኩነን በተባለ ሰው
የተፈረመው በእርእስቱ " ውሱ ጊደኖቼ " በሚለ ጽሑፍ ያለበት ዘዋሪ ደበዳቤ ተገ
ኘበት:: በተጠቀሰው ዕለት ውስዋ በተደረገው ወርወራ፣ መዝገበ መኩነን፣በሰማልያ
መንግሥት ቅ/ጤት የመኪና ፀሐፊ ፣ ፍካሬ መኩነን የተባለ በሥራ ሚኒስቴር ጽ/ጤት

ንብርኤልና ጓደኞቹ የተከሰሱበት - የኢጣልያ የወታደራዊ ፍርድ ቤት ሰነዶች



አብ ዝነበሩሉ ቤት ማአሰርቲ አሱራት ክርኢ ነዓይ ዝወሰደኒ ይቅሬታ ከም
ዝገበረሎም ግን ከምዘይርስዖ ኣረጋጊጹለይ። ከም ዘይድሕኑ ድማ ነጊሩኒ።
ኢዱ ዊጥ አቢሉ ናብ ቤተ መንግስቲ ኣመልኪቱ ድማ "ኢዚ ኩሉ ጥፍኣት
ናይ"ዚ ርጉም ሰብኣይ ኢዩ" ኢሉ ረጊምዎ። አብ'ቲ በራንዳ ከይኖም ከለው
ሰላም ዝበሎም አሱራት፡ ድማ ድገዝማቲ ሶሎሞን ኣብርሃም፡ ጠቅላይ
ሚኒስትር ኣክሊሉ ሃብተወልድ፡ ኣቶ ኣካለዎርቅ ሃብተወልድን ናይ ግቦ
ሚኒስትር ኪዳነ ውልድን ካልኦትን ኔሮም። ክፍለጥ ዘለዎ አዚኦም ኩሎም
አብ ስልጣን ከለው ዘሕዘንዎ ሰባት ዮም ኔሮም።

ይርጋለም ንብርኤል ካሰፈረው ማስታወሻ



ኤድሞንዶና ኤድዋርዶ - አስመራ - 1921

ከታች - (በግራ) ሉላ እዮስአብ። (በቀኝ) - ንግስቲ ኤድዋርዶ ከልጇ ከፍስሃ ተስፋይ ጋር ሞቅዲሾ 1935






አጤ ሃይለስላሴ መኮንን



ገብርኤል ኤድሞንዶ



ኪዳነ አድነይ



በትግርኛ ቋንቋ በእጅ ከተያዙ ማስታወሻዎች



ብላታ ታከለ ወልደሃዋርያት



ብላታ መስፍን በጋሸት



ገብረማርያም ቴዎድሮስ



ከግራ ወደ ቀኝ - ጉበርኤል ኤድሞንዶ፣ ምህረት አድኃይ፣ ኤድሞንዶ ጉበረመድህን

ሚካኤል ካረፈ በሁዋላ ሙሽራዋን (የኪዳኔ አድኃይ እህት) በብሌን ባህል መሰረት ታናሽ ወንድሙ ጉበርኤል እንዲያገባት ፈልገው ነበር። ጉበርኤል ፈቃደኛ ባለመሆኑ ሌላ እንድታገባ ተሰናብታለች።

ከታች - ኤድሞንዶ ከኢጣልያውያን፣ ከሶማሊያውያንና ከኤርትራውያን የስራ ባልደረቦቹ ጋር (ሞቅዲሾ)





በግራ - ጉበርኤል ከአጎቱ ልጅ ጋር፤
በቀኝ - ጉበርኤል ደናኔ እስር ቤት
ከሶማሊያዊው ጠባቂ ጋር 1939



ከታች - ጸጋ ብርሃን መንገሻ የብላታ መስፍን
በጋሸት ባለቤት፤ የጀኔራል እያሱ መንገሻ እህት።

* * *

ብላታ መስፍንና ፊታውራሪ ጉበርኤል ሞቅዲሾ
እና ዓደን ሆነው የሰሩት የስለላ ስራ እንዲጻፍ
ለደበሳይ አደራ ሰጥታው ነበር።



ከታች - ሉላ እዮስአብ
ሞቅዲሾ 1939 - ከህጻኑ ደበሳይ ጋር





ሚካኤልና ገብርኤል ከእናታቸው ከተዋበሽ ገብራይ ጋር



ግራና ቀኝ - ገብርኤልና ሚካኤል
መካከል - ጸሃዬ ኤድዋርዶ

(ከታች) ግራና ቀኝ - ገብርኤል እና አባቱ ኤድሞንዶ።
መካከሉ ላይ ሚካኤል በታመመበት ጊዜ - ሞቅዲሾ






በቀኝ በኩል - በግራዝያኒ የትውልድ መንደር በ2016 ለግራዝያኒ ተተክሎለት የነበረ ሃውልት ሲሆን፤ ሁዋላ ግን በህዝብ ግፊት ሃውልቱ ተነቅሎ እንዲገለል ተደርጓል።



አብርሃ ደቦጭና ሞገስ አስገዶም ማርሻል ግራዝያኒን በቦምብ ካቆሰሉት በሁዋላ፤ ግራዝያኒ ሱሪውንና ቡታንቲውን አውልቆ ጉዳቱን ለጋዜጠኞች ሲያሳይ።

ክፍል ሶስት

ምእራፍ 1

የሽግግር ትውልድ
አውቆም ሆነ ሳያውቅ – ወዶም ሆነ በግድ
ጨፍኖ ወረደ – በቁልቁለት መንገድ

በነሃሴ ወር 1942 አጤ ሃይለስላሴና ከፍተኛ ሹማምንቱ በተገኙበት በራስ ሆቴል አዳራሽ አንድ ትልቅ “የምስጋና ግብዣ” ተዘጋጀ። ይህም ግብዣ ኢትዮጵያ በፋሽስት ኢጣልያ ወረራ ቅኝ አገዛዝ ስር ከመውደቋ በፊትም ሆነ በሁዋላ በአርበኛነትና በተለያዩ መንገዶች ለኢትዮጵያ ነጻነት ለታገሉ የውጭ አገር ሰዎች የተዘጋጀ ነበር። በጥቅሉ ተጋባዦች ከሶስት መቶ በላይ ነበሩ።

ሲልቪያ ፓንክረስት ዋና አስተባባሪ ሆነች። ጀኔራል ካኒንግሃምና ዊንጌት ከንጉሰነገስቱ ያላነሰ ክብር አገኙ። በርግጥ ዊንጌት አዲሳባን በመቆጣጠሩ ሂደት ደስተኛ አልነበረም። ለራሱ የተመኘውን ዝና ካኒንግሃም ቀምቶታል። ጀኔራል ካኒንግሃም የደቡብ አፍሪቃና ከኢጣልያ የከዱ ኤርትራውያን ወታደሮችን ይዞ ቀድሞ አዲስአበባ መግባቱን ዊንጌት ሲሰማ ወዲያውኑ ሁለት መልእክት ልኮ ነበር። የመጀመሪያው “እንኳን ደስ ያለህ” የሚል ሲሆን፤

ሁለተኛው መልእክት “ንጉሱን ይገፍ አዲሳባ እንድገባ አይሮፕላን ይላክልኝ” የሚል ነበር። ሞስሌይ (Mosley) እንደተረከው ለሁለተኛው መልእክት የተሰጠው ምላሽ፣ “...አዲስ አበባ ላይ 5000 ኢጣልያውያን አሉ። ሃይለስላሴ አሁን አዲሳባ ከገባ ባላገሩ ስሜታዊ ሆኖ የዘረፋ፣ የመድፈርና የግድያ ወንጀል ሊፈጽም ይችላል። So. Keep the little man out.” የሚል ነበር። አጤ ሃይለስላሴን the little man ማለታቸው ከምን አንጻር መሆኑ ግልጽ አልነበረም።

በጦርነቱ ወቅት የኢትዮጵያ ራሶች አማካሪ የነበሩ የቼክ፣ የራሻ፣ የኩባና የስዊድን መኮንኖችም እንዲሁ በደረጃቸው የክብር ቦታ፣ የምስክር ወረቀትና ሜዳልያ ተዘጋጅቶላቸዋል። በግብጣው ላይ ከተገኙት እንግዶች የሚበዙት ኤርትራውያን ነበሩ። ሁዋላ ብላቴን ጌታ የሆኑት ሎሬንሶ ታእዛዝ፣ ኤፍሬም ተወልደመድህን ቀዳሚ ነበሩ። እነ ተከስተ ሃብቴ፣ አማንሚካኤል ዓንዶም፣ ያዕቆብ ገብረልኡል፣ ኢሳይያስ ገብረስላሴ፣ ሃይሌ ባይከዳኝ፣ መስፍን አምባየ፣ መብራህቱ ፍስሃ፣ በረከት ገብረመድህን፣ ምህረተአብ ተድላ በግብጣው ላይ የተገኙ ሲሆን፤ ሁዋላ ሁሉም የጄኔራልነት ማእረግ ላይ ደርሰዋል።

ሙስሊም ኤርትራውያንም ልዩ ትኩረት አጊኝተው ነበር። ሁዋላ የአምባሳደርና የሚኒስትርነት ማእረግ ላይ የደረሱት ከሚኒፌሪ ባላባት የዓሊ በይ የልጅ ልጅ የሆኑት ዑስማን መሐመድ፣ በተመሳሳይ ሁዋላ በአምባሳደርነትና በሚኒስትርነት ማእረግ የሰሩት ሳልሕ ሂኒት፣ እነ ሼኽ አብደላ መደኒ፣ የሕርጊጎው ተወላጅ የኬክያዎች ዘር፤ ሳልሕ አሕመድ ኬክያ ፓሻ በግብጣው ላይ አይን አርፎባቸዋል።

የጄኔራል አማን ታላቅ እህት ጽዮን ዓንዶም፣ የቀኛዝማች ሰለባ ወልደስላሴ ልጅ አረፋይኔ ሰለባ፣ ኪዳነ አድጎይ፣ መስፍን በጋሸት፣ በእምነት ገብረአምላክ፣ አስፍሃ ወልደሚካኤል፣ እና ሌሎችም በርካታ ወጣት ኤርትራውያን በግብጣው ላይ ተገኝተዋል።

ከሶማሊያ የደናኔ እስር ቤት የወጡም እንዲሁ በምስጋና ግብጣው ላይ ልዩ ትኩረት አገኙ። ከእነዚህ መካከል መንገሻ ከፈላ፣ ጳውሎስ ብርሃኔ፣ የመንገሻ ብሩ ልጆች ቴዎድሮስ መንገሻ እና ሁዋላ ጄኔራል ማእረግ ላይ የደረሱት እያሱ መንገሻ፣ ፍጡር አብርሃም፣

ገብረማርያም ቴዎድሮስ፣ አበበ ተፈሪ፣ እንዲሁም ገብርኤል ኤድሞንዶ በግብጣው ላይ ተገኝተው ነበር። ከሶስት መቶ ተጋባጮች ከግማሽ በላይ የምድሪ ባህሪ ሰዎች ነበሩ።

ኤርትራውያን እንግዶች ለግብጣው ሲታጩ በአርበኛነቱ ዘመን ባደረጉት አስተዋጽኦ ብቻ ሳይሆን፤ ወደፊትም ሊያበረክቱት የሚችሉት ግምት ውስጥ ገብቶ ተመዝኗል። የአጤ ሃይለስላሴ ባለስልጣናት ኢትዮጵያ የቀይ ባሕር ባለቤት ለመሆን የምትበቃበት መስቀለኛ መንገድ ላይ መቆሟን ተገንዝበው ስለነበር፤ ይህን አንገብጋቢ ተግባር ለማስፈጸም መንገድ ጠራጊ ሊሆኑ የሚችሉ ኤርትራውያን በባትሪ እየተፈለጉ ነበር። እና የራት ግብጣው "የምስጋና ግብጣ" የሚል ስያሜ ቢሰጠውም ኤርትራን ለመጠቅለል ከወዲሁ ለተጀመረው ጥረት የኤርትራውያንን አሳብ ለማወቅና ይህን ተልእኮ ለማስፈጸም የሚችሉ ኤርትራውያንን ለመመልመል ስለላ የሚካሄድበት ድርብ ተልእኮ ያነገበ ግብጣ ነበር።

ከአጤ ሃይለስላሴ የቅርብ ባለስልጣናት መኮንን ሃብተወልድ፣ ራስ ካሳ ሃይሉ፣ እንዲሁም ሌሎች ታዋቂ የአርበኛ ትግል መሪዎች እነ ራስ አበበ አረጋይና ሌሎችም የግብጣው ዋና አክተሮች ሆነው እንግዶቻቸውን በማስተናገድ ተጉ። በዚህ ግብጣ ገብርኤል ከአንድ ትልቅ ባለስልጣን ጋር ተዋወቀ። ይህ ሰው ብላታ ታከለ ወልደሃዋርያት የሚባል ሲሆን፣ ምንም እንኳ ስልጣኑ ትልቅ ቢሆንም፤ ወሳኝ ሚና የነበረው ባለስልጣን አልነበረም።

በዚህ ግብጣ ላይ የተገኙ ትምህርትና ልምድ የነበራቸው ኤርትራውያን ሁዋላ በአብዛኛው በመንግስት ስራ ቁልፍ ቦታዎችን እንዲይዙ ተደረገ። አብዛኞቹ የመኮንንት ስልጠና እንዲወስዱ ቅድሚያ እድል አገኙ። የውጭ ጉዳይ ሚኒስትርነቱ ቦታ ለሎሬንዞ ታእዛዝ ተሰጠ። በዚያን እለት በግብጣው ላይ የተገኙ አብዛኞቹ እንደ ልምዳቸውና ዝንባሌያቸው ተደለደሉ። ገብርኤል ኤድሞንዶም በገንዘብ ሚኒስቴር በመንግስት ንብረት ክፍል ሃላፊነት ላይ ተሾመ።

ገብርኤል ከብላታ ታከለ ጋር ግንኙነቱን ያጠበቀው በጊዜ ሂደት ነበር። በግብጣው እለት የጀመረ ትውውቃቸው ረጅም ዘመን ለዘለቀው ወዳጅነታቸው መነሻ ሆነ። ወዳጅነታቸውና ግንኙነታቸው ቀስ በቀስ እየጠበቀ ሄዶ ሰንበት ዞሮ ሲመጣ ከነቤተሰባቸው

እየተጠራሩ መገባበዝ እና አብረው ማሳለፉን ልማድ አደረጉ። አንዳንድ ጊዜም በእግር ወደ እንጦጦ እየሄዱ ይናፈሳሉ።

ጨዋታቸው ምንጊዜም የፖለቲካ ጉዳይ ነበር።

በተለይ በአጤ ሃይለስላሴ አስተዳደር ላይና የኤርትራን ጉዳይ እያነሱ ያወጋሉ። ልብ-ለልብ ከመቀራረባቸው በፊት በርግጥ የራሳቸውን ያለፈ ታሪክ በዝርዝር ተጨዋውተዋል። ገብርኤል ቅድመ አያቱ ኑረነቢ ፋናን ለቆ ከወጣበት ጊዜ በመጀመር የቤተሰቡንና የራሱን ታሪክ ሲያወጋ ታከለ በተመስጦ አዳምጦታል።

ታከለም የህይወት ታሪኩን ባጭሩ አጫወተው።

- ታከለ በ1900 ከቡልጋ ባላባት ቤተሰብ ተወለደ። "ሶስቱ የሃብተወልድ ወንድማማቾች" መኮንን፣ አካለወልድና አክሊሉ የቅርብ ዘመዶቹ ናቸው። የዘር ሃረጓ ከሳህለስላሴ የሚቋጠር ሴት በማግባቱ ከንጉሳውያን ቤተሰብ አስኳል ውስጥ ገብቷል።

- በልጅ እያሱ ዘመን በአዲስ አበባ መዘጋጃ ቤት ይሰራ ነበር። ወደ ኢትዮጵያ የፖለቲካ መድረክ ብቅ ያለው በ1916 የራስ ተፈሪ መኮንን ደጋፊ በመሆን ነበር። ከተፈሪ ጋር ጥብቅ ወዳጅነትም መሰረቱ። ተፈሪ ሲነግስ ታከለ የመንግስት ስልጣን አገኘ። በአገር ውስጥ ጉዳይ፣ በትራንስፖርትና በእርሻ ሚኒስትር መስሪያ ቤቶች እየተዘዋወረ በጀኔራል ዳይሬክተርነት ማእረግ ሰራ። ሃይለስላሴ የቢሮክራሲውን መረብ ሲዘረጋ ከተጠቀመባቸው ለውጥ ፈላጊ ወጣቶች መካከል ታከለ ወልደሃዋርያት ዋናው ነበር።

- በ1935 "ብላታ" ማእረግ ተሾመ። የዘውድ ምክር ቤት ባልደረባም ሆነ። አጤ ሃይለስላሴ ወደ ማይጨው ሲዘምቱ አዲስ አበባን እንዲጠብቅ ሃላፊነት ተሰጠው። ከማይጨው ሽንፈት በሁዋላ ንጉሱ አዲሳባ ተመልሰው የዘውድ ምክር ቤቱን በሰበሰቡ ጊዜ የአጤ ሃይለስላሴን ወደ ስደት መሄድ ከተቃወሙት ሶስት ሰዎች አንዱ ብላታ ታከለ ሆነ። ንጉሱ በድምጽ ብልጫ አሸንፈው በባቡር ወደ ጅቡቲ ለመሸሽ ሲዘጋጁ ብላታ ታከለ አጅቧቸው ይሄድ ዘንድ ተጠይቆ ነበር። አልተስማማም። መትረየሱን አንግቦ ጥቂት ታጣቂ ተከታዮችን ይዞ ኢጣልያን ሊወጋ ጫካ ገባ።

- ሃምሌ 1937 የአርበኞች የፖለቲካ ጸሃፊ ሆኖ ተመረጠ።

የኢጣልያ ሃይል ሲበረታባቸው ግን በወርሃ ግንቦት 1938 ወደ ካርቱም ለማፈግፈግ ተገደደ። በካርቱም ቆይታው በኢትዮጵያ መጪ እድል ላይ ትኩረት አድርጎ ከባልደረቦቹ ጋር ተወያየ። የኢትዮጵያን ሪፑብሊክ መመስረት ከውይይት ርእሰ ጉዳዮቻቸው አንዱ ነበር። ይህን አሳቡን በጽሁፍ ለፈረንሳይ መንግስት እስከ መላክ ደርሷል። አሳቡን ወደ ተግባር ለማሸጋገርም ተንቀሳቅሷል።

- በ1939 ሱዳን ስደት ላይ የነበሩ ኢትዮጵያውያንን አሰባስቦ አንድ ጠንካራ ግንባር ፈጠረ። እናም ያደራጀውን ሃይል ወደ በጌምድርና ጎጃም አስገባ። ይህን አሳቡንም በጽሁፍ ለአጤ ሃይለስላሴ ወደ ለንደን ላከለት። ለሊግ ኦፍ ኔሽን የሚቀርብ በሚል ነበር የላከለት። ሪፑብሊክ የመመስረት አሳብ የኢትዮጵያን ነባር ባላባቶች የሚያስወግድ በመሆኑ የሃይለስላሴን ድጋፍ አላገኘም።

የብላታ ታከለ የጥናት ወረቀት በኢጣልያ ቁጥጥር ስርም ቢሆን ጎጃምና ጎንደር ላይ Federated status ለማግኘት ይጠይቃል። የብላታ ታከለ አሳብ በአጤ ምኒልክ ዘመን በጦርነት የተያዙት የኦሮሞና የደቡብ ግዛቶች ራሳቸውን እንዲያስተዳድሩ ይፈቅዳል። በዚህም በአብዛኛው የደቡብ እና የኦሮሞ ግዛቶች አጤ ምኒልክ ከተከሏቸው ግልገል ጌታ ነፍጠኞች ነጻ ይሆናሉ።

- ብላታ አሳቡን ገፍቶበት የአማራ ነባር ግዛት ራሱን በራሱ ማስተዳደር እንዲችል ከኢጣልያ እውቅና ለማግኘት እስከ መጻጻፍ ደረሰ። አማራ ሁሉንም ጠቅልሎ ከሚያጣ የራሱን ብቻ ቢያገኝ የሚል ነበር አሳቡ። ይህንኑ አሳብ በወቅቱ የጎንደር ገዢ ለነበረው ለጀኔራል ፍሩሲ ጽፎ ልኮ ነበር። ኢጣልያውያን የብላታ ታከለን የፌዴሬሽን አሳብ ሳይቀበሉት ቀሩ። በ1940 መጀመሪያ ላይ የኢጣልያ ቅኝ ገዢዎች ከልጅ እያሱ ልጆች ዮሃንስ ለተባለው የንጉስነት ማእረግ ለመስጠት በሞከሩ ጊዜ ብላታ ታከለ ማደናቀፍ በመቻሉ በተዘዋዋሪ ለአጤ ሃይለስላሴ ውለታ ሰራ።

- በጥቅሉ ግን አጤ ሃይለስላሴ የብላታ ታከለን አካሄድ አልወደዱትም። ስለዚህ እንዲገደል ወሰኑ። የአጤ ሃይለስላሴ ታማኝ ደጋፊ የሆነ ጃዝማች ውብነህ የሚባል አርበኛ የግድያውን ተልእኮ ወስዶ ነበር። ሙከራው ከሸፈ። መረጃውን ሌሎች አርበኞች ቀድመው በማወቃቸው ብላታ ታከለን ለጥቂት ከሞት አተረፉት።

- ከግድያ ሙከራው በሁዋላ ብላታ ታከለ ወደ ኬንያ በመሄድ ስደተኞችን ለትግል በመመልመል ተግባር ላይ ተግቶ ሰራ። ተስፋ ቆርጠው በስደት የፈዘዙ ሃበሾችንም እያነቃቃ አነሳሳቸው። በሺህዎች ተጨማሪ አርበኞችን ማፍራት ቻለ። በዚህ ሁኔታ ላይ ሳለ ኢጣልያ ጎራዋን ወደ ናዚ ጀርመን ጎራ በመጨመሯ አደጋ ተደቀነባት። እንግሊዝ ኢጣልያ ላይ ጦርነት በማወጇ ኢጣልያ የምስራቅ አፍሪቃ ይዞታዋን አጣች።

- ከኢጣልያ መወገድ በሁዋላ አጤ ሃይለስላሴና ብላታ ታከለ በተመሳሳይ ጊዜ አዲስ አበባ ገቡ። አጤ ሃይለስላሴ ምንም እንኳ ብላታ ታከለን ለማስገደል የሞከሩ ቢሆንም፤ ብላታ ታከለ በአስር ሺህዎች አርበኞችን አስከትሎ አዲስ አበባ ስለገባ የሞራል የበላይነት ነበረው። ንጉሰነገስቱ ብላታ ታከለን በቀላሉ ገለል ማድረግ የሚቻላቸው አልነበረም። በመሆኑም ለብላታ ታከለ የሸዋ ገዢ እና የአዲስ አበባ ከንቲባነትን ሹመት ሰጡት። ብላታ ታከለ በአንጻሩ አጤ ሃይለስላሴ ላይ ቂም መቋጠሩ አልቀረም። እና እየተጠባበቁ አብረው መስራት ቀጠሉ።

ብላታ ታከለ ረጅም ታሪኩን ባጭሩ ተርኮ ሲያበቃ፣

“ይኸው ከተፈሪ ጋር አይጥና ድመት ሆነናል።” አለ።

ገብርኤል እየሳቀ፣

“ማነው አይጥ?” ሲል ጠየቀው።

ብላታ ታከለ ፊቱን ቅጭም አደረገ፣

“ተፈሪ በደጅ እንደሚታሰበው እንዳይመስልህ። የተንኮል ብልቃጥ ነው። ድመት ለመምሰል የሚጥር አይጥ!”

ምእራፍ 2

ታሪክ እንደ ዋጣ

ዜማውን ደገመ – የሚሰማው ሲያጣ

ኤርትራ ከኢትዮጵያ ጋር በፌዴሬሽን ተዋህዳ አስር አመታት ከቆየች በሁዋላ ፌዴሬሽኑ ፈረሰ። የኤርትራ መንግስት መሪ የነበረው ተድላ ባይሩ ፌዴሬሽኑ እንዲፈርስ ፍላጎት ባለማሳየቱ በግፊት ገለል እንዲል ተደረገ። ተስፋ እስኪቆርጥ ድረስ በስራው ላይ እንቅፋት በዛበት። እንደተጠበቀውም ተዳክሞና ተሰላችቶ የስራ መልቀቂያ አቀረበ።

ተድላ ባይሩ ሃምሌ 29 1957 በፈቃዱ ስልጣኑን ሲለቅ በምትኩ አስፍሃ ወልደሚካኤል ስልጣን ያዘ። ቢትወደድ አስፍሃ በኢትዮጵያና በኤርትራን መካከል ድልድይ ሆኖ የቆየውን ፌዴሬሽን ህዳር 14 1962 በማፍረስ በሁለቱ አገራት መካከል የተለኮሰውን ግጭት ይበልጥ እንዲቀጣጠል አደረገው። በርግጥም ሙሉ ውህደት ቀርቶ፤ ፌዴሬሽኑን እንኳ ያልተቀበሉ ነጻነት ጠያቂ ኤርትራውያን የትጥቅ ትግል ከጀመሩ አስራ ስምንት ወራት አልፏቸው ነበር።

ፌዴሬሽኑ እንዲፈርስ ግንባር ቀደም ሚና የተጫወቱ ኤርትራውያን አብዛኞቹ በፈጸሙት መጸጸታቸውን ከመሞታቸው በፊት ገልጸዋል። ቢትወደድ አስፍሃ መጸጸታቸውን በቀጥታ ባይገልጹም በ1993 ሪፈረንደም ወቅት “ነጻነት” መምረጣቸውን

ለአለምሰገድ ተስፋይ እንዲህ ሲሉ ነገሩት፣

“እኛኮ ’ህብረት ከኢትዮጵያ ጋር’ ማለታችን የኤርትራ ህዝብ የሚፈልገው እንደሱ ነው ብለን በማመናችን ነው። በሄድንበት ቦታ ሁሉ የምንሰማው መፈክር ‘ህብረት ከኢትዮጵያ ጋር’ የሚል ነበር። ‘የህዝብ ፍላጎት ይሄ ነው’ ብዬ ነበር ያመንኩት። አሁን እናንተ ያደረጋችሁትን የነጻነት ትግል በወቅቱ ማሰብ የሚቻል አልነበረም። የኤርትራ ህዝብ ሰላሳ አመታት ተዋግቶ፣ ተሰውቶ ነጻነት ያመጣል ብለህ በፍጹም ልትገምተው የማትችለው ነው። እውነቱን ልንገርህ? በተለይ በኢኮኖሚ ከኢትዮጵያ ጋር መለያየቱን በፍጹም የማልፈልገው ነበር። የኤርትራ ህዝብ ታግሎና ተሰውቶ ያመጣውን ነጻነት ግን እኔ ማን ሆኜ ነው ’አይገባህም’ የምለው?”

ደርግ ለመውደቅ ሲቃረብ ቢትወደድ አስፍሃ የአዲስ አበባ መኖሪያ ቤታቸውን ሸጠው ወደ ኢጣልያ ሸሽተው ነበር። ሁዋላ በተዋህዶ ቀሳውስት አሸማጋይነት እንዲመለሱ ተፈቅዶላቸው እስከ እለተ ሞታቸው አዲስ አበባ ቆይተዋል።

በዚያን ዘመን የኤርትሮ - ኢትዮጵያን ፌዴሬሽን በማፍረሱ ረገድ ከቢትወደድ አስፍሃ ያላነሰ ሚና የነበራቸው መልአከ ሰላም ዲሜጥሮስ ገብረመድህን “ሃይለስላሴ አታለውናል” ብለው የተጸጸቱት ድልድዩን ባፈረሱ ማግስት ሲሆን፣ ለ“The collusion of Eritrea” መጽሃፍ ደራሲ እንዲህ ሲሉ ነግረውታል፣

- በሙስሊም ወንድሞቻችን ዝንባሌ ላይ ስጋት ነበረኝ። በ1946 ቤት ገርጊሽ በነበረው ስብሰባ ላይ አንዱ ተናጋሪ፣ ‘ኤርትራን አረባዊት እናደርጋለን’ የሚል አነጋገር ሲናገር ስጋት አደረብኝ። መስከረም ፣ 1961 አቆርዳት ላይ ቦምብ ሲፈነዳ በጎረቤት አገራት ግፊት ከሳዑዲ ጋር ሆነው አንድ ነገር ያደርጋሉ የሚል ስጋት ነበር። ከአቆርዳት ፍንዳታ በሁዋላ ግን ንጉሱ ፌዴሬሽኑ እንዲፈርስ በቀጥታ አዘዋል። ሁላችንም ተስማማንና ተቀበልነው። አስፍሃም፣ ተድላ ዐቅቢትም እኔም ተነጋገርንበትና አደረግነው።

- ፌዴሬሽኑን ካፈረስን በሁዋላ ግን ንጉሱ ኤርትራውያንን እየነቀሉ በምትኩ አማራ ሲሞሉበት ማመን ቸገረኝ። ቀደም ብለው ኤርትራ በኤርትራውያን እንደምትተዳደር፣ ቃል ገብተውልን ነበር።

እንዳታለሉን ገባኝ። ንጉሱ ይዋሻሉ ብዬ አላሰብኩም ነበር። ቀጠሮ ያዝኩና ላነጋግራቸው ሄድኩ። ለምን እንደዚያ እንዳደረጉ ስጠይቃቸው መልስ አልነበራቸውም። ንጉሱ እንደ ዋሹ አረጋገጥኩ። ትቼ ወጣሁ። ከዚያ በሁዋላ አላገኘሁዋቸውም። አሁን እንግዲህ ከመጻለይ በቀር ምንም ላደርግ አልችልም። ለነጻነት የሚታገሉ ልጆቻችን ለድል እንዲበቁ እየጸለይኩ ነው።"

ፌዴሬሽኑን ህገወጥ በሆነ መንገድ ማፍረሱን ትልቅ ስም በነበራቸው ኢትዮጵያውያንም አልተደገፈም። አክሊሉ ሃብተወልድና ጸሃፊ ትእዛዝ ወልደጊዮርጊስ በአብነት ይጠቀሳሉ። መስከረም 12 1954 አዲስ አበባ ላይ በተደረገ ውይይት አክሊሉ እንዲህ አሉ፣

"ርምጃው የኢትዮጵያን ስም ያጎድፋል። ለጠላቶቻችን ምቹ በር ይከፍታል። ይፍረስ ከተባለም በፓርላማው ድምጽ ሳይሆን ህዝበ ውሳኔ ተደርጎ መሆን አለበት። ታዛቢ ባለበት ይሁን።"

ጸሃፊ ትእዛዝ ወልደጊዮርጊስም የአክሊሉን አሳብ ደገፉ፣

"ኤርትራ የተለያየ የአስተዳደር አይነት ቀምሳለች። የፌዴሬሽኑ አስተዳደርም ከውጭው አለም የተወረሰ ስለሆነ አሰራሩ ከኢትዮጵያ የተለየ መልክ ያለው ነው። ይህንን ተረክቦ ከኢትዮጵያ ጋር ማዋሃድ ሌላ ችግር ያመጣል። ጊዜ ወስዶ ማጥናት ይገባል። ስለዚህ ፌደሬሽኑን እንደነበረ ማቆየቱ በአለም ላይ በሚያስከትለው የፖለቲካ ችግር ብቻ ሳይሆን ለውስጥ ችግራችንም የሚረዳ መሆኑን በጥልቀት አጥንቼ አምኜበታለሁ።"

አጤ ሃይለስላሴ የአማካሪዎቻቸውን አሳብ ለመስማት ዝግጁ አልነበሩም። አስፍሃና ዲሜጥሮስን ይዘው በጥድፊያ መጋለቡን መረጡ። የአስመራ ህዝብ በተለይ የፓርላማ አባላቱን፣ "68 አህዮች" የሚል ቅጽል ስም በመስጠት ውክልናቸውን ሰረዘው።

ፌዴሬሽኑን የማፍረሱ ድራማ ከተፈጸመ በሁዋላ ለፓርላማ አባላቱ የኮክቴል ግብዣ ተደረገ። አባላቱ በግብዣው ላይ ፈዝዘውና ደንዝዘው ታዩ። ከኢትዮጵያ የመጡ በአንጻሩ በግብዣው ላይ የፈንጠዝያ ስሜታቸውን መቆጠብ ሳይችሉ ቀሩ።

ፌዴሬሽኑ በፈረሰበት እለት በወታደራዊ ማክ መኪና ላይ የተጫኑ ወጣት ወታደሮች፣ "የሸዋ አበባ - ያብባል ገና!" የሚል

ጭፈራ እያሰሙ ኮምቢሽታቶን ቀወጡት። የዘፈኑ መልእክት ግልጽ አልነበረም። በፌዴሬሽኑ መፍረስ ድሉ ምነው የሸዋ ብቻ ሆነ? “የኢትዮጵያ ድል ነው” ለምን አልተባለም? “ለኤርትራውያንም ድል ነው” ሳይባል ለምን ቀረ?

ጉዳዩ ቂም መወጫ መሰለ።

ኢጣልያ አዲስ አበባን ሲቆጣጠር ኤርትራውያን፣ “የሸዋን ባንዴራ - ፈታው አሞራ” ብለው ማዜማቸውን በቂም ከረጢታቸው ውስጥ ሸሽገው አሁን ጊዜውን የተጠቀሙበት መስለው ታዩ። ኮምቢሽታቶ ላይ፣ ፓርላማው ፊት ለፊት “የሸዋ አበባ”ን ሲጨፍር የዋለው ሰራዊት የሸዋ አማራ ብቻ አልነበረም። ድብልቅ ነበር። የገዢው መደብ “ምርጥ ዘር” መፍለቂያ ሸዋ ነበርና ሌላው ጀሌ የታዘዘውን ሲፈጽም ውሎ ወደ ካምፑ ተመለሰ።

ጸሃፊ ትእዛዝ ወልደጊዮርጊስ ልክ ነበሩ።

ከመነሻው ኢትዮጵያ ኤርትራን ለማስተዳደር ብቃት አልነበራትም። ፌዴሬሽኑ ከፈረሰ በሁዋላ በኤርትራ ስራ አጥነቱ በረከተ። ፋብሪካዎች ስራ አቆሙ። ቀደም ሲል ያልነበረ ስደት በሰፊው ተጀመረ። ጎንደሬዎችና ትግራዮች ለስራ ፍለጋ ወደ ኤርትራ ይሰደዱ የነበረበት ዘመን ተለውጦ ተገላቢጦሽ ሆነ። የሚሰሩበት ፋብሪካ የተዘጋባቸው ኤርትራውያን ባለሙያዎች አሻግረው ኢትዮጵያን ተመለከቱ። መሰደድ በገፍ ሆነ። ኤርትራን የማዳከም ህቡእ አጀንዳ የነበረው የአጤ ሃይለስላሴ ስርአት በቴክኒክ ሙያ የሰለጠኑ፣ የዘመናዊ ንግድ ልምድ ያላቸው፤ ፖለቲካ ግን ብዙም የማያውቁ ስደተኞችን ሁለት እጆቹን ዘርግቶ ተቀበላቸው።

ከአዲስ አበባ ለራስ አስራተ ካሳ የሚተላለፍለት መመሪያ ቀጭን ነበር። ይህም “ሌላው የኢትዮጵያ ህዝብ በአስተዳደር ኤርትራ ካለችበት ደረጃ እስኪደርስ ኤርትራን ባለችበት ማቆየት ያስፈልጋል” የሚል ነበር። ኮሎኔል ፍስሃ ደስታም ባሳተመው መጽሃፍ ይህን አስተሳሰብ ሲገልጽ፣ “ሃይለስላሴ ሌሎቹን ክፍለሃገራት ኤርትራ ወደነበረችበት ደረጃ ከማድረስ ይልቅ ኤርትራን ወደ ጋሞነፋ ደረጃ መመለስን መረጡ” ብሏል። የኤርትራውያን ቅሬታ ሲበረታ፣ “ኤርትራውያን ከአዲስ አበባ መንግስት ምን ይጠብቃሉ?” የሚል

ጥያቄ በቤተመንግስቱ ተነሳ። አጤ ሃይለስላሴ በግልጽ፣ “ለጎጃምና ለጎንደር ከሚሰጠው የተለየና የተሻለ መጠበቅ የለባቸውም።” አሉ።

ፌዴሬሽኑ ከፈረሰ በሁዋላ ኤርትራውያን እንደገና ሁለተኛ ዜጋ ሆኑ። አስመራ ላይ እንደ ዳኝነት የመሳሰሉ የመንግስት ስራዎችን ለመያዝ የሸዋ አማራ መሆን አስፈላጊ ሆነ። ብዙም ግን አልዘለቀም። ቴሌቪዢን ለማየት በመጓጓት አለያም በባቡር ወደ ምጽዋ ሄዶ ቀይ ባሕር ላይ ዋኝቶ ለመመለስ እየተመኘ በዘመድ በር አስመራ ስራ የያዘ ሸዌ፤ የተኩስ ድምጽ ሲሰማ እንደገና በዘመድ በር ወደአገሩ ለመመለስ ተጣደፈ።

የሸዋ ገዢ መደብ በኤርትራ ቆይታው ለኤርትራውያን ሊያስተላልፍ የሚችለው ልምድና እውቀት አልነበረውም። ኤርትራ ላይ ነጻ ፕሬስና ፓርላማ ነበር። የተሻለ የአስተዳደር ሲስተም ነበር። የጤና ተቋማት ነበሩ። በአንጻሩ የአጤ ሃይለስላሴ ባለስልጣናት በየቤታቸው የያዟቸውን አገልጋይ ባሮች እንኳ ገና ነጻ አላወጡም። “ባርያ ነጻ ይውጣ ወይስ አይውጣ” የሚል ሙግታቸውን ለመቋጨት ተቸግረው ይንገታገቱ ነበር።

ፌዴሬሽኑ ከፈረሰ በሁዋላ...

ራስ አስራተ ካሳ የኤርትራ ወጣቶችን አዝማሚያ በቅርብ መገምገም፤ አደጋውን አሻግሮ ማየት ቻለ። የህዝቡ ልብ ወደ በረሃ መሆኑን በመገንዘብ ፌዴሬሽኑን ወደነበረበት ስለ መመለስ የቅርብ ረዳቶቹን ማወያየት ጀምሮ እንደነበር ይነገራል። ባደረገው መለስተኛ ጥናት ግን ኤርትራውያን የፌዴረየሽኑን መመለስ እንኳ እንደ መፍትሄ እንደማያዩት መረዳት ቻለ። የነጻነት ጥያቄ አየሩን ሞልቶታል። ለዚህ “አደገኛ” አዝማሚያ መፍትሄ አልነበራቸውም።

በአጤ ሃይለስላሴ ዘመን የኤርትራ ህዝብ በኢትዮጵያ መንግስት አስተዳደር ላይ እምነት አጥቶ ነበር። ከዚያም በላይ ንቆት ነበር። “የኢትዮጵያ መንግስት ኤርትራን የማስተዳደር ብቃት የለውም” የሚል እምነት ተስፋፋ። በዚህ ወቅት በራስ አስራተ ካሳ ዙሪያ የነበሩ ኤርትራውያን አማካሪዎች ጠቃሚ አሳቦችን ይመክሩት እንደነበር ቦክረጽዮን ጽፏል። ደግ አሳብ ከሚባሉት መካከል፣ “ለኤርትራውያን የአስተዳደር መብታቸውን መመለስና የኢኮኖሚ እድገት ማሳየት መፍትሄ ነው” የሚለው ይገኝበታል። በርግጥ ይህን

ማድረግ “የዘውድ ስርአቱን ማፍረስ” እንደሆነ አማካሪዎቹ አልተረዱም። በኢትዮጵያ ገዢዎች አስተሳሰብ ኤርትራ ለሌሎች ብሄሮችና ክፍለሃገሮች የነጻነት ሞዴል መሆን አልነበረባትም። በአምስት አመታቱ ኢጣልያ ቅኝ አገዛዝ ዘመን እንኳ የኢትዮጵያ ህዝብ የሰለጠነ የአስተዳደርና የፍትህ ነገር በማወቁ ለፊውዳሉ ስርአት ችግር ፈጥሮበት ነበር።

ቀውሱ እየበረታ በመሄድ ላይ ነበር። ፌዴሬሽኑ ፈርሶ ኢትዮጵያ ኤርትራን ማስተዳደር ስትጀምር በአማርኛ እንዲማሩ የተገደዱ ኤርትራውያን በአማርኛ ቋንቋ አለማወቅ ምክንያት ትምህርቱ ከበዳቸው። አስመራን ከአሰብ የሚያገናኘው የቴሌግራፍ መስመር ተቋረጠ። ምጽዋ የነበረው እንቅስቃሴ ወደ አሰብ ዞረ። አጤ ሃይለስላሴ በፌዴሬሽኑ አስር አመታት “76 ሚሊዮን ብር ኤርትራ ላይ አፍስሰናል” ቢሉም፤ በአይን የታዩት ሶስት ግንባታዎች ናቸው። እነርሱም አንድ ትምህርት ቤት፣ አንድ መስጊድና አንድ ቤተክርስትያን ነበሩ። በኤርትራ ስም የወጣ ገንዘብ እየተመነተፈ ግለሰቦች አዲሳባ ላይ ህንጻ ይገነቡበት እንደነበር መረጃዎች አሉ። ዴአፍሪቅ ሆቴልና ራስ ሆቴል ፊት ለፊት ያለው ኣፓርታማ በሙስና ገንዘብ የተገነቡ መሆናቸው ይጠቀሳል።

የኢትዮጵያ መንግስት በቃኘው ጣቢያ ምክንያት ከአሜሪካ የሚያገኘው ገቢ በአመት 12 ሚሊዮን ዶላር ነበር። በዚህ ገንዘብ የጎንደር ጤና ሳይንስ ኮሌጅና የአለማያ ግብርና ኮሌጅ ተገነባበት። ከቃኘው ጋር በተያያዘ በተዋዋሉት የስኮላርሺፕ ውል በአብዛኛው የጎሳቸውን ሰው ወደ አሜሪካ እየላኩ አስተማሩበት። የቃኘው ገቢ በኤርትራውያን ጥያቄ እንዳይነሳበት “ወታደራዊ እርዳታ” በሚል ስያሜ ተሸፍኖ ነበር። በ25 አመታት ጊዜ ውስጥ አሜሪካ ለቃኘው 287.3 ሚሊዮን ዶላር ስትከፍል ቃኘው ሲገነባ ለተፈናቀሉት ኤርትራውያን እንኳ መቋቋሚያ አልተሰጠም። ኤርትራ መጥተው የሰፈሩት 4000 አሜሪካውያን ለኤርትራውያን ያተረፉት ማህበራዊ ቀውስ ነበር። ሰው ገድለው የኤርትራ ፖሊስ ሊያስራቸው የማይችል ጥጋበኞች ነበሩ። አንድ ኤርትራዊ ገድለው ሲያበቁ፤ ለተገደለ ሰው እንዲከፈል ህግ የሚያዘውን የደም ካሳ ገንዘብ ሬሳው ላይ ሸጉጠው የሚሄዱ ዱርዬዎች ነበሩ። እንዲህ ያለ ድርጊት አስመራ ላይ መፈጸሙ በተሰማ ሰሞን ብዙ ወጣቶች የትምህርት ደብተራቸውን

እያጠፉ ለትግል ወደ በረሃ መሄዳቸው ይነገራል።

የኢትዮጵያ ሁለቱም ስርአቶች የኤርትራን ህዝብ አፍነው መሬቱንና ባሕሩን ለመቆጣጠር በሙሉ አቅማቸው ሰርተዋል።

የቆላውን ሰው ወደ ኢጋዴን፤ የደጋውን ወደ ጣና አካባቢ ለመጓጓዝ መንግስቱ ሃይለማርያም አቅዶ እንደነበር የሚጠቁሙ ጽሁፎችም ተነበዋል። በክረጽዮን እንደጻፈው በዚህ የማጓጓዝ ፕሮጀክት ሙአመር ጋዳፊ ለሰፈራው የሚውል ገንዘብ ለመስጠት ተስማምቶ ነበር። የአራብ አገራት በተለይ ሳዑዲ አረቢያ ጣልቃ በመግባታቸው ጋዳፊ የፕሮጀክቱን ድብቅ ተንኮል ለመረዳት ቻለ። እና የዘረጋውን እጅ መልሶ በመሳቡ በገንዘብ ምክንያት ፕሮጀክቱ ተቋረጠ። ደርግ እንደ እቅዱ ቢሆንለት፤ ኤርትራውያንን ወደ ጎንደር እና ወደ ኢጋዴን አዘዋውሮ ሲያበቃ በመሬት ጥበት የተጨናነቀውን የሸዋና የጎጃም ሰው ኤርትራ መሬት ላይ ለማስፈር ነበር።

ቁጥሩ ትንሽ የሆነውን የኤርትራ ህዝብ ወደ ሌላ አካባቢ ከማዛወር ባሻገር ወጣቱን ለመደምሰስ በተደጋጋሚ ተሞክሯል። የመንግስቱ ሃይለማርያም “አሳውን ለማጥፋት ባሕሩን ማድረቅ” የሚል ንግግሩ፣ ቀጥሎም፣ “የማይሆን ከሆነ አስመራ ላይ አዲስ ጎጆዎች ለመትከል እንገደዳለን” ማለቱ ትርጉሙ ግልጽ ነበር። መንግስቱም ሆነ ሃይለስላሴ ያሰቡትን ለመፈጸም ግን አልቻሉም። የጅምላ ጭፍጨፋውን ሞክረውታል። የዖና፣ የሕርጊጎ፣ የወከድባ፣ የሽዕብ፣ የአስመራ የጅምላ ግድያዎች በኤርትራ ታሪክ ውስጥ ይታወቃሉ። ከእነዚህ የጅምላ ግድያዎች ሃይለስላሴ በዖና ያካሄደው የጅምላ ግድያ የበረታው ነው።

ጭፍጨፋው ቢካሄድም ኤርትራውያን በተለያየ መንገድ ተቃውሟቸውን በመግለጽ ላይ ነበሩ። አማጽያን ወደ ከረን ይጓዝ የነበረውን ባቡር በፈንጂ አጋዩ። ጄኔራል ተሾመ እርገጤ ወደ አቆርዳት በመሄድ ላይ ሳለ በጀብሃ አሸማቂዎች ተገደለ። ይህን ለመበቀል በሚል የንጉሱ ስርአት ከረን - ዖና ላይ 600 ሰላማዊ ኤርትራውያንን ገደለ። በአመቱ አጤ ሃይለስላሴ ኤርትራን በመጎብኘት ላይ ሳሉ ደጃዝማች ፍስሃጽዮን ሃይሌ በዖና ስለተገደሉት ኤርትራውያን አንስቶ ንጉሱ ይቅርታ እንዲጠይቁ መከረ። አጤ ሃይለስላሴ በመጠየቃቸው ብቻ በጣም ስለተበሳጩ፣

“የኛን አመራር ያልተቀበለ በህይወት እንዲኖር አንፈቅድም። ለመሆኑ ይህን ለመጠየቅ እንዴት ደፈርክ?” ሲሉ ፍስሃጽዮን ላይ አተኮሩበት፣ አያያዙናም፣ “አድዋና ማይጨውን የረሳናቸው ይመስልሃል?” ሲሉ በልባቸው የተቋጠረውን ቂም ተነፈሱ።

አጤ ሃይለስላሴ አድዋና ማይጨውን ማንሳታቸው በ1896 እና በ1935 ኤርትራውያን ከኢጣልያ ጋር ሆነው ኢትዮጵያን እንደወጉ ለማስታወስ ነበር። ደጃዝማች ፍስሃጽዮን ሃይሌ የፌዴሬሽኑን መፍረስም ሆነ የንጉሱን አካሄድ ካልደገፉትና ከተቃወሙት መከካል ይመደባል። በተደጋጋሚ ለመምከርም ሞክሯል። ፌዴሬሽኑ ከመፍረሱ በፊት፣ “ፌዴሬሽኑ ከፈረሰ ህዝቡ ሊቀበለው አይችልም። ተቃውሞ ሊነሳ ይችላል።” የሚል አስተያየት ሲሰጥ ጄኔራል አብይ የሰጠውን ምላሽ በኩረጽዮን ጠቅሶታል፣

“የትኛውን ህዝብ ነው የምትለው? ይሄ ህዝብ እኮ እንደ እንስሳ ነው። የሆነ ሰው ወደፈለገበት ሊነዳው ይችላል።”

ጄኔራል አብይ የኤርትራን ህዝብ በትክክል ንቆት ነበር ማለት አይቻልም። ከአጤ ሃይለስላሴ ንግግሮች ከንቀት ይልቅ ስጋታቸው ጎልቶ ይታያል። ኤርትራውያን በተለያዩ መድረኮች ቅጽበታዊና ደፋር እርምጃዎችን በመውሰድ ይታወቁ ስለነበር ስጋታቸውን በንቀት አጎበር ለመሸፋፈን ይሞክሩ ነበር። የዘርአይ ደረስ የሮማ አደባባይ ድርጊት፣ የአብርሃ ደቦጭና የሞገስ አስገዶም ቁርጠኛነት፣ የጄኔራል ተድላ ዑቅቢት ቆፍጣናነት፣ የኮሎኔል በላይ ሃብተአብ ጀብዱ፤ ኢትዮጵያን ነጻ በማውጣት ረገድ ኤርትራውያን በኢትዮጵያ በረሃዎች የፈጸሙት ጀግንነት የቅርብ ጊዜ ትዝታዎቻቸው ስለነበሩ አብይ አበበ የልቡን ተናገረ ለማለት አይቻልም። በተለይ የጀብሃ ፈዳይን ጄኔራል ተሾመ እርገቱን መንገድ ላይ ጠብቀው እያሯሯጡ ከገደሉት በሁዋላ ወደ ምጽዋ ይመጡ የነበሩ ሹማምንት እግራቸውን ለመሰብሰብ ተገደው ነበር።

ምእራፍ 3

ከግድግዳው ጓሮ

ዝንተዓለም ነበረ - ያደፈጠ ጆሮ

ገብርኤል ከብላታ ታከለ ጋር በጀመረው ግንኙነት ምክንያት በኢትዮጵያ የጸጥታ ሃይሎች አይን ቁጥጥር ስር ወደቀ። ክትትል እንደሚደረግበት ሳያውቅ ግን ረጅም ጊዜ ቆይታል። ዳሩ ካወቀ በሁዋላም ቢሆን ግንኙነቱን አላቋረጠም። በብላታ ታከለ አስተሳሰብ ቢሳብም በተግባር ምንም አይነት ትብብር ባለማድረጉ ከብላታ ታከለ ጋር የፈጠረውን ቤተሰባዊ ዝምድና መቀጠሉ አደጋ ያስከትልብኛል ብሎ አልጠረጠረም። በርግጥ ሁዋላ የደረሰበት ችግር በቀጥታ ከብላታ ታከለ ጋር በተያያዘ ስለመሆኑ ማረጋገጫ አልነበረውም።

ከብላታ ታከለ አንደበት ወጥተው ወደ ልቡና ወደ አንጎሉ የተንቆረቆሩት አሳቦችና ህልሞች ቅዱስ ሆነው ይሰሙታል። ብላታ ታከለ ምኞቱ እንዲሰምርለትና አምላክም ከአደጋ እንዲጠብቀው ጸሎት ማድረሱም አልቀረም። ማገዝ የሚችልበት አጋጣሚ ግን አልተፈጠረም። ብላታም ከፍተኛ ቁጥር ያለው ደጋፊ ስለነበረው በምስጥራዊ ስራዎቹ ገብርኤልን የማሳተፍ ዝንባሌ አልነበረውም።

የብላታ ታከለ ዋና ዋና ጥያቄዎች ግልጽ ነበሩ። የንጉሰነገስቱ ስልጣን ተገድቦ ህገመንግስት እንዲጸድቅና ፓርላማ

እንዲመሰረት፣ ስልጣን በሹመት መሆኑ ቀርቶ በምርጫ እንዲሆን፣ የመሬት ይዞታ ላይ ጥናት ተደርጎ ክፍፍሉ ላይ ፍትሃዊ የማሻሻያ ህግ እንዲወጣ፣ የመሳሰሉ ነበሩ። አጤ ሃይለስላሴ ከስደት ተመልሰው ካርቱም ገብተው፣ የአርበኛ መሪዎችን ሰብስበው ባነጋገሩ ጊዜም ይኸው የህገመንግስትና የፓርላማ ምስረታ ጥያቄ ቀርቦላቸው ነበር። ቁርጥ አቋማቸውን ሳይገልጹ አድበስብሰው አለፉት። ከኢጣልያ መወገድ በሁዋላ ብላታ ታከለ ይህን እምነቱን በህቡእ እና በግልጽ እንደሚመቸው እየለዋወጠ ቀጠለበት። የአርበኛነት ጓደኞቹ አሳቡን ስለሚጋሩም የሞራል የበላይነት ነበረው።

አጤ ሃይለስላሴ በብላታ ቆስቋሽነት ከአርበኞች የሚቀርቡ ጥያቄዎችን ለመስማት ጆሮ አጣ። ብላታ ታከለ በሰላማዊ መንገድ ሞክሮ ሞክሮ አልሆን ሲለው ንጉሱን በሃይል ለማስወገድ ተንቀሳቀሰ። በ1943 የመጀመሪያ ሙከራውን አደረገ። ማለትም አጤ ሃይለስላሴን አውርዶ ከልጅ እያሱ ልጆች አንዱ የሆነውን ዮሃንስን ለማንገስ እቅድ ነደፈ። በዚህም ምስጢራዊ እቅድ ራስ አበበ አረጋይና ገረሱ ዱኪ ተሳታፊ መሆናቸው ይጠረጠራል።

መፈንቅለ ዙፋን ለማድረግ የታቀደው ለንጉሰነገስቱ ጥበቃ የሰለጠኑ 2000 ወታደሮች በሚመረቁበት እለት ነበር። የዜና (ወሬ) ሚኒስትሩ ወልደጊዮርጊስ እቅዱን ስለደረሰበት ብላታ ታከለ ተጋለጠና በቁጥጥር ስር ዋለ። የሁለት አመታት እስርም ተፈረደበት። የልጅ እያሱ ልጅ ዮሃንስም በግዞት ወደ ጅማ ተላከ።

የብላታ ታከለ ጥያቄ የለውጥ ጥያቄ ቢሆንም ከወጣትነት ጓደኛው ከተፈሪ መኮንን ጋር ያለው የግል ጉዳይ እንደተደባለቀበት ይታመናል። ታከለ ለተፈሪ መኮንን ወደ ስልጣን መውጣት የታገለና ያስፈጸመ ሰው ሆኖ ሳለ፤ ተፈሪ ለንደን ሆኖ ያደረገበት የግድያ ሙከራ ለቂምና ለእልህ ሳያበቃው አልቀረም። ያም ሆኖ የለውጥ ጥያቄ በህዝቡ ውስጥ ነበር። ህዝቡ በአምስት አመታቱ የኢጣልያ ቅኝ አገዛዝ ዘመን በመጠኑም ቢሆን ዘመናዊ አስተዳደር በመቅመሱ ወደ ሁዋላ መመለሱን የሚፈቅድ አልነበረም።

ብላታ ታከለ የሁለት አመታት የእስር ቅጣቱን ጨርሶ በ1945 ተፈታ። አስገራሚው መፈታቱ አልነበረም። እንደገና ምክትል አፈንጉስ ሆኖ መሾሙ ነው። ብላታ ታከለ ስልጣን ላይ እንዳለ

በ1946 እና 1947 የቀድሞ አርበኞች አመጽ ቀሰቀሱ። ጥያቄያቸው የህገመንግስትና የፓርላማ ምስረታ ጥያቄ ነበር። እንደገና ታከለ ተጠርጣሪ ሆነ። ማስረጃ ግን ሊያገኙ ስላልቻሉ አልታሰረም። ከታከለ ጋር የማይታረቅ ቅራኔ ውስጥ የገባው የዜና ሚኒስትሩ ወልደጊዮርጊስ ብላታ ታከለን ከመጠርጠር ባይቦዝንም፤ ያለ ማስረጃ እጁን ማስያዝ ሳይችል ቀረ። ሌላ ሰው ቢሆን በጥርጣሬ ብቻ በተያዘ ነበር። ብላታ ታከለ ላይ ግን ያን ማድረግ ቀላል አልነበረም። ዘመደ ብዙ፣ ወገነ ብዙ ነው። ማጉረምረም ሊያስከትል የሚችል ነው።

በ1954 የወልደጊዮርጊስ ተሰሚነት ቀነሰ። በዚህ ጊዜ ታከለ የአገርውስጥ ጉዳይ ሚኒስትርነትን ስልጣን አገኘ። ታከለ ይህን ሹመት ሲያገኝ ወልደጊዮርጊስን ለማጥቃት ተጠቀመበት። እናም ተሳካለት። አጤ ሃይለስላሴም ከወልደጊዮርጊስ ጋር ፍቅሩን ጨርሶ ስለነበር ታከለን እንደ መምቻ በትር ተጠቀመበት።

ወልደጊዮርጊስ ከተወገደ በሁዋላ ታከለ አፈንጉስነትን ያዘ። እስከ 1961 በዚሁ ስልጣን ላይ ቆየ። በመቀጠል የጂኔራል መንግስቱ ንዋይና የወንድሙ የገርማሜ ንዋይ የመፈንቅለ መንግስት ሙከራ መጣ። ብላታ ታከለ እጁ ባይኖርበትም በዚህ እንቅስቃሴም ክፉኛ ተጠረጠረ። እናም ለአምስት አመታት በቁም እስር እንዲቆይ ተፈርዶበት ከአዲስ አበባ ውጭ ተላከ። የአምስት አመታቱ የቁም እስር ካበቃ በሁዋላ ወደ አዲስ አበባ ተመልሶ፤ እዚህም እዚያም ሳይል በዝምታ መኖር ጀመረ።

በዚህ ጊዜ ከገብርኤል ኤድሞንዶ ጋር በተከታታይ ይገናኙ ነበር። በ1969 ብላታ ታከለ አጤ ሃይለስላሴን ለማስወገድ የመጨረሻውን ሙከራ አደረገ። ንጉሰነገስቱን በተቀበረ ፈንጂ ለመግደል ነበር ያሰበው። የጸጥታ ሃይሎች ድርጊቱ ከመፈጸሙ 24 ሰአታት በፊት ደረሱበት። በዚህ ተግባር የተሳተፉ ሁለት መኮንኖች ያሉበት ስምንት ሰዎች ተያዙ። በምርመራው ወቅት ከመኮንኖቹ አንዱ በእቅዱ አመንጪነት ብላታ ታከለን ጠቆመ።

ህዳር 27 1969 ምሽት ፖሊስ የብላታ ታከለን መኖሪያ ቤት ከበበ። የ74 አመቱ ሽማግሌ ታከለ እጁን ለመስጠት ፈቃደኛ ባለመሆኑ ተከቦ ቆየ። የተኩስ ልውውጥም ተደረገ። በመጨረሻ ታከለ ራሱን ይግደል አሊያ ይግደሉት በትክክል አልታወቀም።

የብላታ ታከለ አሟሟትም ሆነ የለውጥ ጥያቄ የወጣቶችን መንፈስ መሳቡ አልቀረም። የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች የመወያያ አጀንዳ ለመሆንም በቃ። ለታህሳሱ የመፈንቅለ መንግስት ሙከራም ሆነ ለመጨረሻው የተማሪዎች አብዮት የብላታ ታከለ አስተዋጽኦ ታክሎበታል። መነሻው ምንም ይሁን ምን ብላታ ታከለ በጨለማው ዘመን ነቅቶ ማንቃት የቻለ የተሻለ ራእይ የነበረው ሰው ነበር።

በርግጥ “The Dying Lion” በሚል ርእስ መጽሃፍ የጻፈው Patrick Gilkes ብላታ ታከለን አስመልክቶ ባሰፈረው አስተያየት “His forte was conspiracy not revolution. And was based on personal attitude rather than principles.” ይለዋል።

በእነዚህ ጊዜያት ውስጥ ገብርኤል በተለያዩ የሃላፊነት ቦታዎች አየተዘዋወረ ሰርቷል። በሃረር አውራጃ የጉምሩክ ምክትል ዲሬክተር፣ በኦርማ ጋራሹ ሃላፊነት፣ በክብረ መንግስት የማእድን ዳይሬክተር፣ በፓጋሞኒ የእንጨት መሰንጠቂያ ሃላፊ በመሆን እየተዘዋወረ አገልግሏል። የመጨረሻ ምድብ የስራ ቦታው በገንዘብ ሚኒስቴር የዲሲፕሊን ኮሚቴ ፕሬዚዳንትነት ነበር።

ከብላታ ታከለ ጋር በነበረው ወዳጅነት በጸጥታ ሰራተኞች ክትትል ስር እንደሆነ ከተረዳም በሁዋላ ገብርኤል አካሄዱን አልቀየረም። ብላታ ታከለ በተደጋጋሚ ሲታሰርና ሲፈታ፤ ሲሾምና ሲሻር ወዳጅነቱን ሳያጓድል ቀጠለ። የጸጥታ ሰራተኞች ከብላታ ታከለ ጋር ያለውን ግንኙነት በተመለከተ እንዲጠነቀቅ ሲልኩበትና ሲመክክሩትም “ከታከለ በላይ ለንጉሱ እኔ አልቀርብም” በሚል ነባር ልማዱን ቀጠለበት። ሲገናኙ እንደተለመደው በእግር ወደ እንጦጦ ይሄዳሉ። ግሮሰሪዎች በመግባት አፕሬቲቭ ይቀምሳሉ። የፖለቲካ ጉዳዮችንም አንስተው ይጨዋወታሉ።

* * *

በ1950ዎቹ መጨረሻ ገብርኤል የክብረመንግስት የወርቅ ማእድን መስሪያ ቤት በሃላፊነት ለጥቂት አመታት ከሰራ በሁዋላ በመካከሉ ከሃላፊነት መነሳቱ በደብዳቤ ተነገረው። በደብዳቤው ላይ ምክንያቱ አልተገለጸም። በወሬ ደረጃ ግን “ለአንድ ኢጣልያዊ

የዶማና የአካፋ ግዢ ክፍያ እንዲፈጸም ያዘዘው የጥቅም ግንኙነት ስላላቸው ነው።" የሚል ወሬ ተወራ። ገብርኤል አዲስ አበባ ተመልሶ ቤቱ ቁጭ አለ። ከጥቂት ሳምንታት በሁዋላ አንድ ሌሊት የጸጥታ ሰራተኞች ወደ መኖሪያ ቤቱ መጥተው በቁጥጥር ስር አዋሉት።

ከታሰረ በሁዋላ ያለምርመራ ጥቂት ሳምንታት አለፉ። ባለቤቱ ሉላ እና ልጆቹ እየተመላለሱ ይጠይቁታል። ስንቅ ያደርሳሉ። አስረው በወሰዱት እለት መኖሪያ ቤቱን አበጥረው መፈተሻቸውን ባለቤቱ ነገረችው።

ሉላ እንደነገረችው....

የተደበቀ የውጊያ መሳሪያ የሚፈልጉ ነበር የሚመስሉት። ታንክ የተቀበረ ይመስል ግቢውን በእግራቸው እየሙቱ ዋሻ ይፈልጉ ነበር። ወረቀቶችን ፈተሹ፤ ሳጥኖችን በረበሩ። ከደናኔ እስር ቤት ጀምሮ በኢጣልያንኛ ቋንቋ የተጻፉ የግል ማስታወሻዎቹን ግን አላገኟቸውም። የሉላ የቅመማቅመም ማስቀመጫ ጠርሙሶች ውስጥ ወረቀት ይኖራል ብለው አልጠረጠሩም። ሌላ ርባና የሌለውን ወረቀት ሰብስበው ወሰዱ። በታሰረ በሁለተኛው ወር አካባቢም የወሰዱትን ወረቀት ሁሉ መለሱ።

የወሰዷቸውን ወረቀቶች ከመለሱ በሁዋላ ለምርመራ እንደሚጠሩት ወይም በነጻ እንደሚለቁት ገብርኤል ጠብቆ ነበር። አልጠሩትም። አልመረመሩትም። አልደበደቡትም። ዝም ብለው ተውት። ለምን እንደታሰረ ደጋግሞ ቢጠይቅም ምላሽ የለም። የተነገረው ነገር የለም። የሚያውቃቸው ባለስልጣናትም ሊጠይቁት አልመጡም። ሊመጣ ይችል የነበረው ወዳጁ ብላታ ታከለ ነበር። እሱም ራሱ ከአዲስ አበባ ውጭ በቁም እስር ላይ ነበር።

ገብርኤል ጤንነቱን ለመጠበቅ ተጋ።

የእስር ጊዜውን በስፖርት፣ በማንበብና ማስታወሻ በመያዝ ለማሳለፍ ወስኖ በዚሁ በረታ። ሞቅዲሾ ደናኔ እስር ቤት ያሳለፈውን ጊዜ በማስታወስ የራሱን ልምድ መልሶ ተጠቀመበት። ደናኔ ታስሮ ሳለ በርግጥ መንፈሱ ብርቱ ነበር። ቢያንስ ለምን እንደታሰረ ያውቅ ነበር። ከታሰረበት እለት ጀምሮ ጠበቃ ቆሞለት ተሟግቶ ተፈርዶበታል። ከተፈረደበት በሁዋላም ባለስለጣናት አሳቡን

ለማወቅ እየመጡ አነጋግረውታል። መጽሃፍ እንዲያነብ፣ ዜና እንዲሰማ፣ ስፖርት እንዲሰራ፣ ፈቅደውለታል። በስለላ ወንጀል እጅ ከፍንጅ ይዘውት ሳለ እንኳ ክፉ ፊት አላሳዩትም።

ህይወቱን የሰጠላት ኢትዮጵያ ባንድ በኩል ስሜታዊ መገሳ ደርድራለት ስታበቃ፤ ይሽው ወረቷ ሲያልቅ ደግሞ አለምክንያት እስር ቤት ወርውራ ረስታዋለች። ከመታሰሩ ይልቅ ለምን እንደታሰረ አለማወቁ ይበልጥ መንፈሱን ጎዳው። ደጋግሞ ራሱን የሚጠይቀው፣ "ለምን ታሰርኩ?" ሳይሆን "እውነት ካላቸው ለምን ፍርድ ቤት አያቀርቡኝም?" የሚል ነበር። እና ለምን እንደታሰረ ለመገመት ሞከረ? በብላታ ታከለ ምክንያት ሊሆን ይችላል? በኤርትራ ጉዳይ ይሆን? "ጫማ አለመሳም ይሆን?"፣ በስርቆት ያልተባበራቸው ባለስልጣናት ይሆኑ?

ደጋግሞ ቢያስበውም በቂ ምክንያት ሆነው አልታዩትም።

ብላታ ታከለ በተደጋጋሚ ንጉሱን ከስልጣን ለማውረድ ሞክሯል። ቢሆንም ግን ንጉሱ ከእስር ቤት እየፈቱ መልሰው ሲሾሙት ታይተዋል። የቅርብ አማካሪና ወዳጃቸው ነው። መካሪ እንጂ የሚመከር ሰው አይደለም።

በኤርትራ ጉዳይ ላይ መጀመሪያ አካባቢ ገብርኤል ተሳትፎ አሳይቶ ነበር። ኢትዮጵያ እና ኤርትራ በፌዴሬሽን እንዲዋሃዱ ከደገፉት አንዱ ነበር። አስፍሃ ወልደሚካኤል ምክትል እንደራሴ ሆኖ ወደ ኤርትራ ከሄደ በሁዋላ ግን ሁኔታዎች ደስ አላሉትም። በተለይ ፌዴሬሽኑን የማፍረስ እንቅስቃሴ ሲጀመር ራሱን ከኤርትራ ፖለቲካ አገለለ። ሆኖም በተቃውሞ እንቅስቃሴ አልተሳተፈም። የልብ እምነቱን ማወቅ ስለማይችሉ በኤርትራ ጉዳይ ሊያስሩት አይችሉም።

በክብረመንግስት የማእድን ስራው ላይ ሳለ ስርቆት ላይ እንዲተባበራቸው የሞከሩ ባለስልጣናትን ተቋቁሚቸዋል። በዚህ ጥብቅነቱ ተመስግኖ ሙሉ ስልጣን ተሰጥቶታል። "አይበላ ወይ አያስበላ - ርጉም ትግሬ!" እያሉ ከጀርባው እንደሚያሙት ሰምቷል። አባባሉን ከቁምነገርም አልቆጠረውም። "እነዚህ መብላት ያልቻሉ ሹማምንት በሃሰት ወንጅለው አሳስረውኝ ይሆን?" ሲል አሰላሰለ። ዳሩ መኖሪያ ቤቱ ተፈትሾ፣ ምንም ነገር ሲያጡ ሊፈቱት ይገባ ነበር። ሳይመረመር ወይ ሳይለቀቅ እንዴት እንደዚህ በእንጥልጥል ተተወ?

ንጉሱን ሲያገኝ አጎንብሶ እጅ ይነሳል እንጂ ጫማ አይስምም። በዚህ በተደጋጋሚ ተወቅሶ ነበር። የንጉሱን ጫማ የማይስመው አክብሮት ለመንፈግ ሳይሆን የህይወት መርሁ ስለማይፈቅድለት መሆኑን አስረድቷል። ንጉሱን ግን እንደ አባት እንደሚወድና እንደሚያከብር ገልጾአል። ንጉሱ የክብራቸው ጉዳይ በጣም የሚያስጨንቃቸው ቢሆንም፤ ይህን የመሰለ ተራ ነገር ይፈጽማሉ ብሎ ማመን ቸገረው።

“ለምን ታሰርኩ?” ለሚለው የራሱ ጥያቄ ምላሽ አጣ።

መጽሃፍ ማንበብ እና ስፖርት መስራት ዋና ጊዜ ማሳለፊያዎቹ ሆነው ቀጠሉ። አልፎ አልፎም ጠንቀቅ እያለ ማስታወሻ እየጻፈ በሻይ ፔርሙስ ውስጥ በመክተት ለሉላ ማቀበሉን አልረሳም። ከኢጣልያ ኮሚኒቲ በኢጣልያ ቋንቋ የተጻፉ መጻህፍትን በብዛት ያገኛል። ስድስተኛው ወር ላይ አንዳንድ ጊዜ ምሽት ላይ በጠባቂ ከተማ እንዲወጣ ይፈቅዱለት ጀመር። በህክምና ሰበብ ከእስር ቤት ግቢ ወጥቶ ውሎ ይመለሳል። ሊያገኙት የሚፈልጉም ይህን አጋጣሚ ይጠቀሙበታል።

* * *

አንድ ቅዳሜ ምሽት ያልተጠበቀ እንግዳ ሊጎበኘው መጣ። ገብርኤል እስከ እኩለ ሌሊት ከእስር ቤት ውጭ በጠባቂ እንዲያሳልፍ የፈቃድ ወረቀት ጭምር ይዞ መጥቷል። ይህ ሰው እያሱ ያዕቆብ ነበር። ገብርኤል በጣም ተደነቀ። እያሱ ከፋሽስት ኢጣልያ ጋር በነበረው ጥብቅ ቁርኝት ምክንያት ኢትዮጵያ ለመግባት ይፈቀድለታል ብሎ አስቦ አያውቅም ነበር። ከዚያም አልፎ በህይወት ስለመኖሩም እንኳ መረጃ አልነበረውም። በጦርነቱ ወቅት ተገድሎ ይሆናል የሚለው ግምቱ ያየለ ነበር። ተቃቅፈው ሲሳሳሙ አንድ ቃል እንኳ ማፍለቅ አልቻለም ነበር።

አንድ ጠባቂ ፖሊስ አስከትለው ወደ ራስ ሆቴል ሄዱ። ገለልተኛ ቦታ መርጠው ሲያበቁ የሚፈልጉትን ምግብና መጠጥ አዘዙ። ጠባቂ ፖሊሱ ፈንተት ብሎ ቁጭ ሲል፤ ለእሱም መጠጥና ምግብ አዘዙለት። አጠገባቸው ቢቀመጥም የሚያሳስባቸው አልነበረም። በአማርኛ ቋንቋ ስላልተጠቀሙ የፖሊሱ በአጠገባቸው

መኖር አላስቸገራቸውም።

እያሱ እየሳቀ አላገጠበት፣

“እንደገና እስር ቤት ተገናኘን?”

“በህይወት ያለህ አልመሰለኝም ነበር።” ሲል ወሬ ለወጠ።

“ሮማ ነበርኩ።”

“አባትህ ማረፉን መርዶ በሰማን ሰሞን ሃናን በስልክ አጊኝቻት ነበር። ስላንተ ምንም ወሬ እንደሌላት ስትነግረኝ በጦርነቱ ተገድለሃል ብዬ ደመደምኩ።”

እያሱ ትክዝ አለ፣

“በዚያን ጊዜ አስመራ ነበርኩ። አባቴን አገኘው ነበር። የእንግሊዝ አስተዳደር ስሜን በጥቁር መዝገባቸው ይዘው ስለነበር ሃና ስለኔ እንዳታውቅ አደረግን። እንደምታውቃት ሃና ስሜታዊና ችኩል ናት። ምስጢር መያዝ አታውቅም። እንደናፈቀችኝ ሳላገኛት ተመልሼ ከኤርትራ ወጣሁ። እስካሁን አላየሁዋትም። በስልክ ብቻ አናገርኳት። ለመሆኑ ባሏ መሞቱን ሰምተሃል?”

“አልሰማሁም።” አለና እዝን አለ። “.... ኤርትራ ካሉ ሰዎች ጋር ምንም ግንኙነት የለኝም። ጠቅላላውን ተቆራርጫለሁ።”

ከጥቂት ዝምታ በሁዋላ፣

“እንዴት ኢትዮጵያ መግባት ቻልክ?” ሲል ጠየቀው።

እያሱ ሳቀ። በጣም ሳቀ።

“ስልጣን ላይ ያሉት አብዛኞቹ ከኢጣልያ ጋር በምስጢር ይሰሩ የነበሩ የቀድሞ ጓደኞቻችን ናቸው።” እናም አላገጠበት፣ “አርበኛ የተባላችሁት ይኸው በየእስር ቤቱ ናችሁ።”

ገብርኤል የሚናገረው ጠፍቶት ዝም በማለቱ፣

“ለምን አሰሩህ?” ሲል ጠየቀው።

“አላውቅም። ክብረመንግስት በወርቅ ማምረቻው ዳይሬክተር ነበርኩ። አካፋና ዶማ በጨረታ ገዛን። ጨረታውን ያሸነፈውና እቃውን ያቀረበው ኢጣልያዊ ከኔ ጋር የቅርብ ግንኙነት

ነበረው። በዚህ ምክንያት መታሰሬን ደጅ ደጁን ያወራሉ። ክስ ግን አልመሰረቱም። የሚያወሩትን ቢያምኑበትና ማስረጃ ቢኖራቸው ክስ ይመሰርቱ ነበር። የታሰርኩበት ሌላ ጉዳይ ካለም አልነገሩኝም። ከወርቅ ምርቱ መስረቅ የሚፈልጉ ባለስልጣናት ነበሩ። አልፈቀድኩላቸውም። መስረቅ ከፈለጉ መፍትሄው በኔ ምትክ ሌላ ሰው መሾም ነበር። የሚደረገው ሁሉ በንጉሰነገስቱ እውቅና ነው ብዬ ለማመን ተቸግሬያለሁ። ንጉሱ አያውቁም ማለትም አልቻልኩም። ምንድነው እየተደረገ ያለው? አልገባኝም?"

"ምን ያህል ጊዜ ሆነህ ከታሰርክ?"

"አስራ አራት ወራት።"

"ምርመራ አላደረጉም?"

"ማንም የጠየቀኝ የለም። ቢቸግር ሉላ እቴጌ መነን እና አቡነ ቴዎፍሎስን ሄዳ አነጋገረች። ራስ እምሩም ጉዳዩን እንዲያውቁ ተደርጓል። መልስ የለም። ያነጋገረኝ ሰው የለም።"

"መነን ምናለች?"

"ለንጉሰነገስቱ እነግራለሁ ብላለች ተባለ። አቡነ ቴዎፍሎስም ተመሳሳይ መልስ ሰጥተዋል። ይኸው ሁለት ሳምንት ሆነው። ዝም ዝም። በቃ። ረስተውኛል።"

"ለምን እንደታሰርክ የምትጠረጥረው ነገር አለ?"

ገብርኤል አመነታ፣

"እንጃ! አላውቅም።"

እያሱ ሳቀ።

"ሞቅዲሾ ላይ ስትታሰርም ይህን ጥያቄ ጠይቄህ ነበር።"

"ያ ሌላ ጉዳይ ነው። ልነግርህ አልችልም ነበር።"

"ትንሽ ምን ትጠረጥራለህ?"

"እንጃ ባክህ! ምናልባት የንጉሱን ጫማ አልስምም ብዬ ነበር። እሱ ይሆን? እላለሁ። እንደ መናቅ ወይ እንደ አመጽ ቆጥረውት እንዳይሆን ብዬ አሰብኩ። ንጉሱን በዚያ ደረጃ ዝቅ

አድርጌ ማሰብ ደግሞ አልቻልኩም። ብላታ ታከለ የሚባል ወዳጅ ነበረኝ። ንጉሱ ላይ አደጋ ለማድረስ ያስባል ተብሎ በግዞት ነው ያለው። በዚህ በኤርትራ ፌዴሬሽን መፍረስም ቅሬታ ነበረኝ። እንግዲህ ይሄን ይሄን ደማምረው 'ይሄ ትግሬ ጠግቧል፤ እናብርድለት' እያሉ እንዳይሆን እላለሁ።"

እያሱ ራሱን ላይ ታች ወዘወዘ፣

"እውነትክን ነው። እስካልነገሩህ ድረስ በምን እንደታሰርክ ማወቅ አትችልም። የሚቀርህ መገመት ብቻ ነው።"

"ግምት ነው የወሰድኩት።"

እያሱ ሲያቅማማ ቆየና፣

"እኔ ከሮማ ገስግሼ የመጣሁት በዚሁ ባንተ ጉዳይ ነው። መታሰርህን በአንድ አጋጣሚ ሰማሁና ከኛ ጋር ይሰራ ለነበረ አንድ ባለስልጣን ደወልኩለት። ወንድሜ መሆንህን ስነግረው በጣም ደነገጠ። ያንተ ጉዳይ ደግሞ በአጋጣሚ ከዚሁ ሰው ጋር የተያያዘ ነበር። እና ይኸው ለሁለተኛ ጊዜ ባንተ እስር ጉዳይ ላይ እጄን እያስገባሁ ነው። በጣም ገርሞኛል።"

እያሱ ጉዳዩን ሊያስረዳው ሞከረ፣

"እቴጌ መነን እና አቡነ ቴዎፍሎስ ንጉሱን አነጋግረው ነበር። ንጉሱ 'እኔ መታሰሩን አላውቅም። እሰሩት ብዬም አላዘዝኩም። 'ጓደኛው ጨረታ እንዲያሸንፍ አደረገ' ብለው ሲነግሩኝ፣ 'አጣሩና እውነት ከሆነ በደሞዝ ቅጡት' ብዬ ነው ያዘዝኩት። አሁንም ያለፈው አልቋል፤ ለምን እንደታሰረ አጣርተው እንዲነግሩኝ አደርጋለሁ። ጊዜ ስጡኝ' ሲሉ መልስ ሰጡ። እቴጌ መነን እና አቡነ ቴዎፍሎስም የንጉሱን ምላሽ እየጠበቁ ነው። እንግዲህ ጉዳይህ እዚህ ሁኔታ ላይ ነው ያለው።"

ገብርኤል መገረም አደረበት።

"ንጉሱ ካላሰሩኝ ማን ሊያስረኝ ይችላል?"

እያሱ ቅጭም ብሎ ነገረው፣

"እዚህ አገር አንድ ከባድ ጠላት አለህ።"

“ጠላት!? የኔ ጠላት?”

እናም ገብርኤል በማጥላላት እንዲህ አለ፣

“ወርቅ ሊሰርቁ የሞከሩትን ማለትህ ነው?”

“አይደለም። ሌላ ትልቅ ጠላት! አንተ የማታውቀው እሱ ግን የሚያውቅህና በጣም የሚፈራህ ሰው አለ። እንግዲህ ከዚሁ ሰው ጋር በተያያዘ ምክንያት ነው ለሽምግልና የመጣሁት። ረጋ ብለህ ስማኝ። ንጉሱ ከእስር ቤት እንድትለቀቅ ፍላጎት አሳይተዋል። ጠላትህ ግን አንተ ከእስር እንዳትለቀቅ ማድረግ ይችላል። ወይ ደግሞ በንጉሱ ትእዛዝ ከእስር ለቆህ ሲያበቃ ባልጠበቅኸው መንገድ እንደገና ሊያጠቃህ ይችላል። እንዳትለቀቅ ሊያደናቅፍም ይችላል። በሽምግልናው ካልተገባባን ሊገድልህም ይችላል።”

ገብርኤል እያሱን በዝምታ ተመለከተው።

እያሱ ቀጠለ፣

“ከሞቅዲሾ ለንጉሱ የላክኸውን መረጃ ከቤተመንግስት አውጥቶ ለኢጣልያ ቆንስል የሰጠው ሰው አሁን ከፍተኛ የስልጣን ቦታ ላይ አለ። ልክ እንደርሱ ለኢጣልያ ያገለገሉ በብዛት ስልጣን ይዘዋል። የሚያጠቃቸው ከመጣ ይተባበራሉ። ሃይል አላቸው። አንተ ደግሞ የዚህን ሰው ማንነት ለማወቅ መፈተሽ ጀምረህ ነበር። በዚህ ምክንያት ይኸው እዚህ እስርቤት ቁጭ ብለሃል።”

በዱላ ጭንቅላቱን የተመታ ያህል ነዘረው። ጨለመበት። ጨርሶ ጨለመበት። አቀርቅሮ ጥቂት ከቆየ በሁዋላ ቀና አለ። ለመረጋጋት እየሞከረ አይኖቹን በዝግታ ገለጠ።

“እውነት ነው የምታወራው?”

“ለምን ገረመህ? ሰውየውን ለማወቅ ፍለጋ አልጀመርክም?”

“አልጀመርኩም።”

“እሱ ግን የተጨበጠ መረጃ አለው። የእንግሊዝ ኤምባሲ በጠራው የራት ግብዣ ላይ በአንድ ጠረጴዛ ዙሪያ ለነበራችሁ ሰዎች የተናገርከውን ሰምቷል። መረጃውን ለኢጣልያ አሳልፎ የሰጠውን ሰው ለማወቅ ፍለጋ ላይ መሆንህን ተናግረሃል። ይህን ትክዳለህ?”

ገብርኤል አስታወሰ። እና የሆነውን ነገረው፣

“በግብጥው ላይ በኢጋጣሚ ጉዳዩ ተነስቶ ስንጨዋወት ነበር። እንዳልከው እንግሊዞች ባዘጋጁት የእራት ግብጥ ላይ ይመስለኛል። እንዲህ ከብበን እየተጫወትን ሳለ እኔም በእግረመንገድ ‘መረጃውን አሳልፎ የሰጠው ሰው ማን እንደሆነ ለማወቅ እንደምፈልግ ገልጬ ሊሆን ይችላል። ቃል በቃል ምን እንዳልኩ እንኳ አላስታውስም። ከዚያ በሁዋላ የሰውዬውን ማንነት ለማወቅ ግን ስራዬ ብዬ አላጠያየቅሁም። በድንገት የተናገርኩት ነው።”

እያሱ ትከዝ ብሎ ከቆየ በሁዋላ መናገር ቀጠለ፣

“እንግዲህ ይህ ወሬ ተጋንኖ እሱ ዘንድ ደርሷል ማለት ነው። ምናልባትም እዚያው አጠገብህ ሆኖ ሰምቶህ ሊሆን ይችላል። እያወቅህ እንዳላወቅህ ሆነህ አሸሙር የተናገርክ መስሎት ሊሆን ይችላል። ስለዚህ ራሱን ለማዳን አንተን ወደ ማጥቃት ገባ። አለመገደልህም እድለኛ ብትሆን ነው። ደንብሮ ሊገድልህ በቻለ ነበር። አንተ ሳትሞት እሱ የሰላም እንቅልፍ መተኛት የማይችል ከሆነ የሚቀረው ምርጫ አንተን መግደል ብቻ ይሆናል። ይህን ለማድረግ ደግሞ አቅሙ አለው።”

እያሱ በትኩረት እንዲህ ሲል ጠየቀው፣

“እውነቱን ንገረኝ? ሰውየው ማን እንደሆነ አውቀኸዋል?”

“አላወቅሁም።” ሲል መለሰ፣ “...ለማወቅ ብዙም አልተንቀሳቀስኩም። በኢጋጣሚ የተናገርሁት ነው። ይልቁን አሁን ለማወቅ እንድጓጓ አደረግኸኝ። የኢጣልያ ሰላይ የነበረ ሰው እንዴት በዚህ ጊዜ ስልጣን ላይ ለመገኘት ቻለ? ንጉሱ ይህን አያውቁም?”

እያሱ ሳቀ፣

“ያውቁ ይሆናል፤ ያላወቁ መምሰሉን ግን ሊመርጡ ይችላሉ። የሞራል የበላይነት የሚኖራቸው በእንደነዚህ አይነት ሰዎች ላይ ስለሆነ ይፈልጓቸዋል። እነርሱም ይታዘዛሉ። እንግዲያው አለማወቅህን ማረጋጠኔን እነግረዋለሁ። አንተም ስለዚሁ ጉዳይ ለዘልአለሙ ትረሳለህ። ለማጣራትና ለማረጋገጥ ከሞከርክ በተለየ መንገድ ሊያጠፋህ ይችላል።”

ገብርኤል እያሱ ላይ አተኮረ፣

“በ1936 ማይጨው ላይ ድል እንድናደርግ ብዙ ያገዘን ሰው ነው። የውስጥ አርበኛ ተብሎ ነው የሚታወቀው። ምናልባት ዝም ብሎ ከሃዲና ተራ ልክስክስ ሰው እንዳይመስልህ። አዋቂና አደገኛ ሰው ነው። የሚያደርገውን የሚያውቅ ሰው ነው። ጉዳዩ የቂምና የስልጣን ጉዳይ ነው። ከንጉሱ ጋር ግላዊ ሽኩቻ አለው። መኳንንቱ ርስበርስ በሚያደርጉት የስልጣን ሽኩቻ የአገር ክህደት የሚባል ነገር የለም። ክህደት የሚለው ቃል የሚመለከተው ተራውን ባላገር ብቻ ነው። ገባህ? አትጃጃል። ከፈለገ በአንድ ሰአት ጊዜ ውስጥ ባንድ ጥይት ሊያሰናብትህ ይችላል። ማንነቱን ለማወቅ ጥረት እስካላደረግህ ድረስ ግን እሱ ጨርሶ ይረሳሃል። ይህን እንድነግርህ አስጠንቅቆኛል። ስለዚህ መምረጥ ያንተው ፈንታ ነው።”

ገብርኤል በትካዜ አቀርቀሮ ብዙ ቆየ።

እያሱም ወጉንና ምክሩን ቀጠለ፣

“ሰውየው ጉዳዩ ከተፈሪ ጋር እንጂ ካንተ ጋር አይደለም። አንተ በዝሆኖች ሽኩቻ መሃል ገብተህ የተረገጥክ ምስኪን ዶሮ ነህ። ከዚህ በሁዋላም የተፈሪ መጠቀሚያ የምትሆን ከሆነ ቀድሞ ሊያጠፋህ ይችላል። አሁን እንግዲህ ንጉሱ ያንተ ጉዳይ እንዲጣራ አዟል። በእስር ቤት እንድትቆይ ለማድረግ ለነሱ በጣም ቀላል ነው። ከኤርትራ ነጻ አውጪዎች ጋር ግንኙነት እንዳለህ ከነገሩት ሃይለስላሴ ምንም ሊያደርግልህ አይችልም። ጫማ አልስምም ማለትህ ለሃይለስላሴ የተነገረው አይመስለኝም። ልዩ ትርጉም ሰጥተው ሊነግሩት ይችላሉ። ከብላታ ታከለ ጋር ያለህ ግንኙነት ተቀምሞ ሊቀርብ ይችላል። የሚሻለው በርግጥ ማን መሆኑን አውቀህ ከሆነ እንደማታውቀው መምሰል ነው። ሚሰት፣ ልጆች፣ ጓደኛ ማንም ማወቅ የለበትም። እኔም እንደማታውቀውና ማወቅም እንደማትፈልግ እነግረዋለሁ። ከእስር ተፈተህ በሰላም ትኖራለህ። ቃልህን እስከጠበቅህ ድረስም ማንም አይነካህም።”

ገብርኤል ምላሽ አልሰጠም።

“ተግባብተናል?” ሲል ጠየቀው።

“ገብቶኛል።”

ዋናውን ርእሰ ጉዳይ ከቋጩ በሁዋላ ረጋ ብለው ሌሎች ያለፉ ነገሮችን እያነሱ ተጨዋወቱ። መጠጥ በጨማመሩ መጠን ዘና ረጋ አሉ። በወጋቸው መካከል እያሱ የራስ ካሳ ልጆች ሲገደሉ የነበረውን ሁኔታ ተረከለት። ኢጣልያ በተሸነፈች ጊዜ ሰላሌ ላይ ተከቦ እንደነበርና ለጥቂት ማምለጡንም አጫወተው።

እያሱ እንዳጫወተው - ከበባውን ሰብረው በመውጣት ወደ ሱዳን አግጣጫ ማፈግፈግ እንደሚሻል አሳብ ያቀርባል። ይመራቸው የነበሩ አንድ ባታሊዮን ወታደሮች ግን እጅ መስጠቱን መረጡ። እንዳልሆነለት ሲያውቅ እያሱ አስራ አራት ታማኞቹን ይዞ ከመንጋቱ በፊት ከከበባው ሾልኮ በመውጣት ሱዳን መግባት ቻለ። ማለዳ ላይ እጃቸውን የሰጡት ወታደሮችም በአስራተ ካሳ ትእዛዝ በሙሉ እንደተረሸኑ መስማቱን አጫወተው። አስራተ ካሳ የወንድሞቹን ደም ለመበቀል በሚል በቀጥታ በማይመለከታቸው ወታደሮች ላይ ስሜታዊ ርምጃ መውሰዱን እያዘነ ተናገረ።

ወጋቸው ሲቀጥል ገብርኤልም በበኩሉ ስለ አጤ ሃይለስላሴ ድብቅ የክፋትና የተንኮል ሰብእና አንስቶ መናገሩ አልቀረም። በጦርነቱ ወቅት ኢትዮጵያን ለመርዳት በከፈለው መስዋእትነት ግን እንደማይጸጸት ገለጸ። በተለይ ለኢጣልያ ገብረው የነበሩ መኳንንት "የውስጥ አርበኛ" እየተባሉ ሲሾሙ፤ በአርበኛነት ጸንተው የቆዩ በአንጻሩ ሰበብ እየተፈለገ እንደሚመቱ ታዝቦ ማዘኑን አጫወተው። አጤ ሃይለስላሴ ከስደት ተመልሰው ስልጣን ላይ ሲቀመጡ ጣልያን የዘረጋውን ዘመናዊ አስተዳደር ሊያንቀሳቅስ የሚችል የተማረ ሰው እንዳልነበራቸው፣ ኤርትራውያን በሁሉም ቦታ ተመድበው ጎዶሎውን ሸፍነው ሲሰሩ እንደቆዩ፣ ቀስ በቀስ ግን ንጉሱ የአገሩን ሰዎች እያስተማረ መተካት እንደጀመረ አንስቶ አወጋው።

የኤርትራን ጉዳይ አንስተው መጨዋወታቸውም አልቀረ። ገብርኤል፣ "ፌዴሬሽኑ መፍረስ አልነበረበትም" ሲል እያሱ ደግሞ፣ "ከነጻነት በቀር ሌላ አማራጭ የለም።" ሲል አከርሮ ተናገረ። እንደወትሮውም ባመለካከት አልተግባቡም።

ገብርኤል ርእሰ ወሬያቸውን እንዲህ ሲል ለወጠ፣

"በአምስቱ አመታት የአዲሳባ ቆይታህ እንዴት ነበር?"

“ጥሩም መጥፎም ነበር።” ሲል መለሰ።

“በአማራ ላይ ያደረብህ ጥላቻ በረደልህ?”

እያሱ የለበጣ ሳቅ ሳቀ፣

“ይኩኖ አምላክ በተከለው ተረት ላይ ከቆመው ስርአት እንጂ እኔ ከአማራ ህዝብ ጋር ጠብ የለኝም።” ካለው በሁዋላ እንዲህ ሲል አከለበት፣ “...በአምስቱ አመታት የአዲሳባ ቆይታዬ ብዙ አማራ ወዳጆች አፍርቼ ነበር። ግራዝያኒ የካቲት 20 አዲሳባን ሲጨፈጭፍ በቻልኩት አቅም ተከላክያለሁ። ከጥቂት በላይ ኢጣልያውያንም ጭፍጨፋውን ለማስቆም ጥረዋል። እስር ላይ ባትሆን ከሞት ያተረፍኳቸው አማሮች ቤት ወስጄ በጋበዝኩህ ነበር። የአማራ ጠላት መሆኔን ብትነግራቸው ተቆጥተው ይደበድቡሃል!”

ገብርኤል ጠብ ፈላጊ በሚያስመስለው የእያሱ አነጋገር ሳቀ፣

“ሰላሳ ሺህ ሰው ተገድሏል መባሉ እውነት ነው?”

“አይመስለኝም።” አለ እያሱ። “በወቅቱ በቦታው ነበርኩ። ከሶስት ሺህ በላይ የተገደሉ አይመስለኝም።” ፋታ ወሰደና አከለበት፣ “...ሶስት ሺህም ቢሆን ግን ብዙ ነው። ኢላማ የነበሩት አማሮችና ወጣቶች ነበሩ። ግራዝያኒ ያን ያህል ደደብና ጅል አይመስለኝም ነበር። በስሜታዊ ውሳኔው ኪሳራ እንጂ ትርፍ አላገኘም።”

“ግራዚያኒ እድሜ ልክ እስራት ተፈርዶበታል የሚል ሰምቼ ነበር? እውነት ን ወይስ ቀልድ?”

እያሱ ሳቀ፣

“ቀልድ ነው። ከናዚ ጋር በመተባበሩ ሰላሳ ምናምን አመት ፈርደውበት ነበር። ከአራት ወር እስር በሁዋላ ግን ለቀቁት።”

“በህይወት አለ?”

“እንጃ። ሞቶ ይሆናል።”

“መጽሃፍ አልጻፈም?”

“አላውቅም። አልሰማሁም። እኔ ገጠር ነው የምኖረው።”

“ምን ትሰራለህ ገጠር?”

“የጓሮ አትክልት አመርታለሁ።”

“አላገባህም?”

“ከአንዲት ክልስ የአስመራ ልጅ ጋር አብረን እንኖራለን። ጋብቻ ሊባል አይችልም። ሱዳን ሳለሁ ግን ከአንድ ትግረ ሴት ወንድ ልጅ ወልጂያለሁ። ፈዳይ ይባላል። ከእናቱ ጋር ሱዳን አለ። ወደ ኢጣልያ ልወስደው ፈልጌ እናቱ አልተስማማችም። ካርቱም የንግድ ስራ ትሰራለች። ጎበዝ ሴት ናት። እንዴት ያለች ቆንጆ....”

እንዲህ እየተጨዋወቱ እስከ እኩለ ሌሊት ከቆዩ በሁዋላ ተሰነባበቱ። ገብርኤል ወደ አለም በቃኝ ሲመለስ፤ እያሱ በሶስተኛው ቀን ወደ ሮማ ሄደ። ከዚህ በሁዋላ እያሱና ገብርኤል ከመሞታቸው በፊት የተገናኙት አንድ ጊዜ ብቻ ሲሆን፤ እሱም በስልክ ነበር።

* * *

ከእያሱ ጋር በተነጋገረ በሁለተኛው ሳምንት ገብርኤል ከአለም በቃኝ ተለቀቀ። ሉላ በከፍተኛ ደስታ እግዚአብሄርን አመሰገነች። ለምን እንደታሰረና እንዴት ሊፈታ እንደቻለም፤ ለገብርኤል ብቻ ሳይሆን፣ ለመላ ቤተሰቡ፣ ለጎረቤቶች፣ ለዘመዶች ሁሉ በተደጋጋሚ አወጋች። ከእስር ቤት ተፈትቶ ወደ ቤት በመሄድ ላይ ሳሉ ለራሱ ለገብርኤል እንዲህ ነበር ያለችው፣

“ከክብረ መንግስት ወርቅ አላስበላ ያልካቸው ሌቦች ናቸው ያሳሰሩህ። ‘የንጉሱን ጫማ አልስምም ብሏል’፣ ‘ዘውድ ለብላታ ታከለ ይገባል ብሏል’ ብለው አስወሩብህና አሳሰሩህ። እቴጌ መነን፣ አቡነ ቴዎፍሎስና ራስ እምሩ ዘንድ ሄጄ ያለፍርድ ከታሰርክ አመት ማለፉን ስነግራቸው በጣም አዘኑ። ሄደው ለንጉሱ ነገሩ። ንጉሱም ‘ጉዳዩ ይታይለት’ ብለው አዘዙ። ጉዳይህ ሲታይ ምንም የተጨበጠ ነገር ጠፋ። እናም ይኸው ፍትህ አጊኝተህ ለቤትህ በቅተሃል። አምላክ ይመስገን!! እግዚአብሄር በመጨረሻ እውነትን ያያል።”

“እንኳን ለቤትህ አበቃህ” ለማለት የሚመጡ ጎረቤቶች፣ ዘመዶችና ጓደኞች ሁሉ ሉላ ደጋግማ የምትናገረውን የመታሰርና የመፈታት ታሪክ እስኪሰለቻቸው ሰሙ። ጠያቂ እንግዶች “ለምን ታሰርክ? እንዴት ተፈታህ?” ብለው ሲጠይቁት ገብርኤል በአገጩ

ወደ ሉላ ያመለክታቸዋል።

ሉላ አትደክምም።

ከስር መሰረቱ ሰፋ በማድረግ ታብራራለች። አልፎ አልፎም በስሜት ተውጣ፣ “ይሄ ትግሬ አላስበላ አለን ብለው በክፋት አሳሰሩት!” ብላ በቁጭት ራሷን ላይ ታች ትንጣለች። ወይም ደግሞ፣ “አንድ ትግሬ ወርቁ ላይ ተቀምጦበት አስቸገረን” ብለው ይናገሩ ነበር። ሌቦች!!” እያለች ታክልበታለች። ስትናገር ትንፋሿ ይግላል። ቁጣዋ እየበረታ ገጽታዋ ይለዋወጣል። አስፈሪ አውሬ ትመስላለች።

* * *

እለቱ ሰንበት ነበር።

ገብርኤል ከእስር በተፈታ በሁለተኛው ወር ምሽት ላይ የደጁ በር ተንኳኳ። ደበሳይ ሄዶ ሲከፍት ብላታ ታከለ በሩ ላይ ቆሟል። ረጅም ካፖርትና የቡሽ ባርኔጣ አድርጎ፣ ከዘራ ይዟል፣

“አባትህ አለ?”

“አለ። ሬድዮ እየሰማ ነው።”

“ውጣ በለው። በዚህ መንገድ እየሄድኩ እጠብቀዋለሁ።”

ከግማሽ ሰአት በሁዋላ ሁለት ሰዎች እንጦጦ አካባቢ በእግር ሲያዘግሙ ታዩ። ብላታ ታከለ በግዞት ላይ ቢሆንም፤ የገብርኤልን መፈታት ሲሰማ ህጉን ጥሶ አዲስ አበባ ገባ። እንዲህ ያለ የማያልፈው ጉዳይ ሲገጥመው ጠባቂዎቹን እያግባባ ወደ አዲስ አበባ ብቅ ማለቱ አልቀረም ነበር። ከአንድ ሌሊት በላይ ግን አያድርም። በገባበት መንገድ ሹልክ ብሎ ይመለሳል።

በማዘገም ላይ ሳሉ ታከለ በጉጉት ጠየቀው፣

“እስኪ ንገረኝ ወዳጄ? ለምን ነበር ያሰሩህ?”

ገብርኤል ፈገግ አለ፣

“አንድ የማላውቀው ሰው ለሁለተኛ ጊዜ አሳሰረኝ።” ሲል ጀመረና ከእያሱ ያእቆብ ጋር ያደረጉትን ንግግር ዘርዝሮ ተረከለት።

ገብርኤል ተርኮ ሲጨርስ ብላታ ታከለ በረጅሙ ሳቀ።

“በርግጥ ይህ ሰው ማን እንደሆነ አላወቅህም?” አለው።

“አላወቅሁም። ማነው?”

የባለስልጣኑን ስም ነገረው!!

ገብርኤል ባለበት ቆመ። እጁን ወደ ካፖርቱ ኪስ ከተተና Caravel A የሲጋራ ፓኬት ከኪሱ አወጣ። እጆቹ እየተንቀጠቀጡ ሲጋራ ለኮሰ። ደጋግሞ ሳበለት። ደግሞ ደጋግሞ ከሳበ በሁዋላ የሚንቀጠቀጥ እጁ ረጋለት።

ምእራፍ 4

ጦርነት ዘነበ - እንደ ሙሴ መና
ከማን ጎጆ አናት? - አልታወቀም ገና
ምህለላ ይደረግ - ጸሎተ ቀኖና

ገብርኤል ከአለም በቃኝ እስር ቤት ከተለቀቀ በሁዋላ ፓጋኖኒ የእንጨት መሰንጠቂያ ሃላፊ ሆኖ ተሾመ። ይህም መስሪያ ቤት ወደ ገንዘብ ሚኒስቴር ሲታጠፍ አብሮ በመዘዋወር በመንግሰት ንብረት ክፍል ከፍተኛ የሃላፊነት ቦታ ተሰጠው። ያለምክንያት የደረሰበትን እስርና መጉላላት ለማካካስ በሚመስል መልኩ ቀጣዮቹ አመታት ለገብርኤል የሹመት እና የሽልማት አመታት ሆኑለት።

አጤ ሃይለስላሴ የ1953 የሃምሌ 16 የልደት በአላቸውን ሲያከብሩ፤ ባለአምበሉን የመኮንንነት ኒሻን ሸለሙት። በማከታተል የዳግማዊ ምኒልክን ባለአምበል ኒሻን ተሰጠው። ንጉሰነገስቱ በዚያም ሳያበቁ የፊታውራሪነት ማእረግ አለበሱት። ይህን የመሰለው የስጦታ ጎርፍ ግን ያደረበትን ቅሬታ ሊፍቀው አልቻለም።

ፖሊስ አንድን ሰው አስሮ እንደፈለገ ሊያደርገው የመቻሉ እውነት የቅሬታው አንጓ ሆነ። በኢጣልያ የቅኝ አገዛዝ ስርአት ውስጥ እንኳ እንዲህ ያለ ነገር ባለማየቱ መደነቅ አደረበት። አንዱ ያሰረውን ሌላው ደፍሮ አይፈታም። አንድ ሹም በግል የተጋጨውን ሰው አስሮ ሲያበቃ፤ ፍርድ ቤት ሳያቀርበው ለአመታት ዝም ብሎ ሊጎልተው መቻሉ ክፉኛ አስደነገጠው። በራሱ ላይ ደርሶ እስኪገነዘብ ድረስም እንዲህ ያለ ነገር ሊፈጸም ስለመቻሉ አያውቅም ነበር። ይህን

ባለማወቁም ራሱን ታዘበ።

አንድ ጊዜ ተፈራ ሹምዬ የሚባሉ የንጉሱ ዘመድ መኖሪያ ቤቱ ድረስ መጡና ወቀሱት፣

“ጃንሆይ የልደት በአላቸውን ሲያከብሩ ለምንድነው ያልተገኘኸው? እንዲህ ያለ ነገር እንደሚያስቀይማቸው አታውቅም? ቅሬታም ካለህ በግንባር መጠየቅ ነውይ መሸሽ ላንተ አይበጅም። አሁን የምመክርህን ስማ። የፊታችን ቅዳሜ የአየር ሃይል ሰልጣኞች ምረቃ ይካሄዳል። ደብረ ዘይት ብቅ በልና ፊት አስመታ።”

ገብርኤል በተነገረው መሰረት ደብረዘይት ሄዶ ፊቱን አስመታ። አጤ ሃይለስላሴ አጠገቡ ሲደርሱ በመጠኑ ከወገቡ ጎንበስ በማለት እጅ ነሳ። ንጉሰነገስቱ ቆሙ፣

“ገብርኤል ደህና ነህ?”

“ደህና ነኝ ጃንሆይ።”

“ምነው ጠፋህ?”

“ደጅ ጠኚ ይበዛቦታል ብዬ ነው።”

“መሬት አግኝተሃል ለመሆኑ?”

“መሬት የለኝም፤ ጃንሆይ።”

“እኛ እስክንጠይቅህ ነበር የምትጠብቀው?”

“አይ! ለስንቱ መሬት አድለው ይችላሉ?” ብሎ ሳቅ አለ።

“ልጆችህ ደህና ናቸው?”

“ሁሉም ደህና ናቸው ጃንሆይ!”

ገብርኤል ስለ ልጆቹ ሲጠይቁት ለጃንሆይ እውነት አልተናገረም። ማለትም ከልጆቹ አንዱ ደህና አልነበረም። የተለየ መንገድ መከተል እንደጀመረ ገብርኤል ከተገነዘበ ጥቂት ወራት አልፈው ነበር። ይህ በርግጥ ለጃንሆይ የሚነገር ወግ አልነበረም።

ነገሩ ወዲህ ነው.....

መኮነን ገብርኤል በ1953 ተወለደ። እስከ ሰባተኛ ክፍል

ካቴድራል ተማረ። ሰባተኛ ክፍል ላይ ከአንድ የክፍሉ ልጅ ጋር ተጣልቶ በቴስታ አፍንጫውን ስለሰበረው ከትምህርት ቤቱ ተባረረ። ምኒልክ ወደ ተባለው ትምህርት ቤት ቀይሮ እስከ አስራ ሁለተኛ ክፍል ከተማረ በሁዋላ ኮሌጅ ገባ። የመጀመሪያውን አመት ትምህርት ተከታትሎ ነበር። አልቀጠለም። በመካከሉ ፓይለት ለመሆን ይመኝ ስለነበረ ሞከረ። የተጠየቀውን መስፈርት ማሟላት መቻሉን በማወቁ በተስፋ ነበር ለምዝገባ የሄደው። "ምዝገባ አቁመናል" ብለው መለሱት። ከእርሱ በሁዋላ አንድ የሚያውቀው ሰው ሄዶ መመዝገቡን አረጋገጠ። እንደገና ሰነዶቹን ይዞ በመሄድ ለመመዝገብ ጠየቀ። መዝጋቢው ኮስተር ብሎ አናገረው፣

"ምዝገባ ማቆማችንን ነግረንህ ነበር።"

"ትናንት ሰዎች መመዝገባቸውን ሰምቼ ነው የመጣሁት።"

"ውሸት ነው፤ ምዝገባ አቁመናል።"

መኮነን እውነትና ውሸቱን መለየት የሚችልበት መንገድ አልነበረም። ውሸት እንዳልሆነ ግን ጠረጠረ። ስለዚህ ጉዳይ ከኤርትራውያን ጋር ሲጨዋወት፣ በአየር መንገዱ ትግሬ ስለበዛ "ትግሬዎችን አይመዘግቡም።" የሚል ወሬ መኖሩን ጠቆሙት። በዚያን ቀን ምሽት ወደቤቱ ሲገባ አባቱን ለብቻ ነጥሎ አነጋገረ፣

"ኤርትራዊ በመሆኔ ምክንያት ለፓይለትነት እንዳልወዳደር መመዝገቡን ከለከሉኝ። ይህ የተረጋገጠ ነው።"

የሆነውንና የሰማውን ለአባቱ ዘረዘረለት። ገብርኤል ሰምቶ ሲያበቃ ለመፍረድ ስለ ተቸገረ፣ "እስኪ እናጣራለን።" አለው።

መኮነን ጠባይ ቀየረ። ተናዳጅ መሆን ብቻ ሳይሆን መጠጥ ጠጥቶ መምጣት ጀመረ። ጊዜው የፖለቲካ ግርግር የበዛበት ጊዜ ነበር። አከሊሉ ሃብተወልድ ከጠቅላይ ሚኒስትርነት ተሽረው እንዳልካቸው መኮንን የተተኩበት ጊዜ ነበር። በርግጥም "በየመስሪያ ቤቱ ኤርትራውያን በዝተዋል።" የሚል ቅሬታ እየተሰማ ነበር። ቁልፍ በሚባሉ መስሪያ ቤቶች ኤርትራውያን እንዳይቀጠሩ ትእዛዝ መተላለፉ እየተወራ ነበር። መኮነን እየቀማመሰ እየመጣ ይሀንኑ ርእሰ ጉዳይ በማንሳት የሃይለስላሴን ስርአት ማውገዝ፣ "ሽማግሌው መውረድ አለበት።" እስከማለተት ደረሰ።

አንድ ጊዜ ደግሞ፣ “ሁለተኛ ዜጋ ከሆንን ንጉሱን ጠይቀውና አገራችንን እንፈልግ!” ሲል አባቱን ጠየቀው። ይህን ሲጠይቀው ገብርኤል አዝኖ አንገቱን አቀርቅሮ ብዙ ቆየ።

በዚህ ሁኔታ ላይ ሳሉ መኮነን እንደገና ጠባይ ቀየረ።

እየቀማመሰ መምጣቱን ተወ። በግልባጩ ሚነበቡ መጻህፍትና በራሪ ወረቀቶች ይዞ መታየት ጀመረ። ዝምተኛ ሆነ። በደም ፍላት መናገሩን ተወ። በዚህ ጊዜ ገብርኤል የመኮነንን የጠባይ ለውጥ ምክንያት በመጠርጠሩ ስጋት አደረበት።

በዚያው ሰሞን ገብርኤል ልጆቹን ሰብስቦ መከረ፣

“ከቻላችሁ ፖለቲካ ውስጥ አትግቡ። ወደ ፖለቲካ ጉዳይ መግባት ከወሰናችሁ ደግሞ ለህይወታችሁ መሳሳት አይገባም። ፖለቲካ መስዋእትነትን ይጠይቃል።”

በገብርኤል ንግግር ላይ አስተያየት የሰጠ አልነበረም።

መኮነን ፖለቲካ ውስጥ መግባቱ ግን በመላ ቤተሰቡ ታውቆ ነበር። ከቤተሰብ የማታ ወጎች ተገለለ። ሲያነብ ያድራል። ምን እንደሚያነብ ማንም አልጠየቀውም።

ቅዳሜ ዞሮ ሲመጣ የምሳ ሳህን እያስቋጠረ ወደ እስር ቤት መሄድ ጀመረ። ገብርኤል ይህ ሁኔታ ሲደጋገምበት ሉላን ጠየቃት፣

“ለማነው ስንቅ የሚያመላልሰው?”

“አለምበቃኝ ለታሰሩ ኤርትራውያን ነው ብሎኛል።”

ምሽት ላይ ገብርኤል ከልጁ ጋር አወጋ። ወደ አለምበቃኝ ስንቅ የሚወስደው ለማን እንደሆነ ሲጠይቀውም በቀጥታ መለሰለት፣

“ለማሕሙድ ክዳን ነው።”

ገብርኤል ትከዝ አለ። ከሃያ የማያንሱ ኤርትራውያን ከጀብሃ ጋር በተያያዘ ተወንጅለው አለምበቃኝ መግባታቸውን ገብርኤል ያውቃል። ሄዶ ግን አላያቸውም። እንዳይሄድ ያደረገው በጸጥታው መስሪያ ቤት ክትትል ስለሚደረግበት ነበር። በርግጥ አዲስ አበባ ነዋሪ የሆኑ ኤርትራውያንና የዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ተራ ገብተው እስረኞቹን እንደሚጠይቁ ያውቅ ነበር። ከገብርኤል መኖሪያ ቤት

ለማሕሙድ ስንቅ መቋጠር ግን በራስ አንገት ላይ የመሰቀያ ገመድ እንደማጥለቅ እንደሚቆጠር ገብርኤል ረጋ ብሎ ለመኮነን አስረዳው።

ገብርኤል ስለ ማሕሙድ በዝርዝር ያውቅ ነበር።

ማሕሙድ ክዳን በ1948 ከረን ተወለደ። ትውልዱ ከሓልሓል ማርያም ሩኽ ሲሆን፤ ከፋና ጋር ይጋባሉ፣ ይዛመዳሉ። ስልጣኑኽ፣ ህዳዱኽ የማርያም ሩኽ ኩታገጠም ናቸው። ማርያም ሩኽ ሄደው ሄደው እንደ ኑረነቢ የዘር ሃረግ ከጣውቀ ይቋጠራሉ። ለነርሱም ሰመረጽዮን ቅድመ አያታቸው ነው። ሲጠሩት ግን "ሰመረኤን" ይላሉ።

ማሕሙድ ገና በ16 አመቱ ከሰላ ሄደ። እና በተመሳሳይ እድሜ ላይ ከነበሩ የአገሩ ልጆች ጋር ሆነው በጀብሃ የትግል እንቅስቃሴ ለመታቀፍ ጠየቁ። ወደ በረሃ ላኳቸው። ኤርትራ በረሃ ሲንቀሰሳቀስ የነበረው ጀብሃ "ለአቅመ ትግል አልደረሳችሁም" ብሎ መለሳቸው። ማሕሙድ አስቸግሮና ለምኖ ትግሉ ውስጥ ቀረ።

ራስ አስራተ ካሳ በ1963 ኤርትራ ከተመደበ በሁዋላ እስከ ሱዳን ድንበር እየተጓዘ ይጎበኝና ይቀስቅስ ነበር። በየመንገዱ ዳር ኤርትራውያን የኢትዮጵያን ባንዴራ ይዘው እንዲዘምሩ የሚገደዱበት ጊዜ ነበር። የጀብሃ አመራር ይህን ካስተዋለ በሁዋላ የአስራተ ካሳ እንቅስቃሴ ላይ አደጋ በመጣል እግሩን እንዲሰበስብ ለማድረግ አቀዱ። እና አንድ ቡድን ወደ ከረን ለመላክ ተወሰነ። ለዚህ ተግባር ወደ ከረን የሚላኩት ትግርኛ መቻል አለባቸው ስለተባለ ማሕሙድ የመመረጥ እድል ገጠመው። በዚያን ጊዜ አብዛኛው የጀብሃ ተዋጊ ትግርኛ ቋንቋ መናገር የሚችል አልነበረም።

ጥቂት ቦምብና አንድ ሽጉጥ ተሰጥቷቸው ወደ ከረን ተላኩ። 15 ቀናት ከረን እንደሰነበቱ ማሕሙድ የተሰጠው የራሱ ትጥቅ ስላልነበረው ከባልደረቦቹ ላይ ሁለት ቦምብና አንድ ሽጉጥ ሰረቀ። ከዚያም በማለዳ ተነስቶ፣ "የተሰጠንን ተልእኮ ብቻዬን ሄጀ እፈጽማለሁ።" አላቸው። ቦምብና ሽጉጥ መውሰዱን ሲያውቁ ሊነጥቁት አስበው ነበር። "እንዳትጠጉኝ" ብሎ ሲያስፈራራቸው ተውት። ማሕሙድ ወደ ከረን ከተማ ዘልቆ አጂፕ ነዳጅ ማደያ አጠገብ ሲደርስ የወታደር መኪና ነዳጅ ሲሞላ አየ። ወደ ባርካ በመጓዝ ላይ የነበሩ እስራኤል ያስለጠነቻቸው ፈጥኖ ደራሽ ፖሊሶች

ነበሩ። ማሕሙድ ተጠጋቸውና ሁለቱን ቦምቦች እየነቀለ ወረወረባቸው። አንደኛዋ ስትፈነዳ ሌላዋ ከሸፈች። አራት ወታደሮች ተመትው ሲወድቁ ሌሎቹ ተበታኑ። ማሕሙድ በግርግሩ አመለጠ።

ከረን መውጫ ላይ ኬላ ጠባቂዎች እንዲቆም ጠየቁት። ሽጉጡን ሲመዝባቸው ተሯሩጠው ወደ መከለያቸው ገቡ። የታጠቀው ወታደር መልሶ ብቅ ብሎ፣ "ቁም ብዬሃለሁ" ሲለው ተኮሰበት። እንደገና ብቅ ሲል ተኮሰበት። ማሕሙድ ለማምለጥ ራመድ ሲል ብቅ ይልበታል። ወታደሩ ማሕሙድን መግደል ቢፈልግ ይችል ነበር። አንድ ሽጉጥ ብቻ መያዙን ተረድቶ ብቅ ጥልቅ እያለ ጥይቱን አስጨረሰው። ማሕሙድ ጥይቱን ሲጨርስ ወታደሩ ተዝናንቶ መጣበት። ማሕሙድ በደም ፍላት ሽጉጡን ወደ ወታደሩ ወረወረ። ጎንበስ ብሎ አሳለፋት። ድንጋይ አነሳና መወርወር ጀመረ። የመፈንከት አደጋ ከማድረሱ በፊት ተሯሩጠው ያዙት።

"ማነህ? ምንድነህ?" ጥያቄ ሲያቀርቡለት፣ ማሕሙድ ሊያስፈራራቸው በማሰብ እንዲህ ሲል ጉራ ቀላቅሎ ነገራቸው፣

"ጀብሃ ነኝ። አማራን ከአገራችን ጠራርገን እናስወጣለን። መጀመሪያ የምንቀጣው ግን ኤርትራዊ ሆነው ሳለ ከአማራ ጋር የተሰለፉትን ነው። ከፍተኛ ሃይል አለን።"

ወታደሮቹ በአነጋገሩ ተዝናኑ። ከልምዳቸው እንዲህ የሚናገር አይተውም ሆነ ሰምተው አያውቁም። ጀብሃዎች ሌሊትና ቀን እየተደበደቡ እንኳ ጀብሃ መሆናቸውን አያምኑም። ይሄ ልጅ ጀብሃ መሆኑን ከማመን አልፎ ሊያስፈራራቸው ቃጣ።

ወታደሮቹ ጠየቁት፣

' "ፈጥኖ ደራሽ ፖሊሶች ላይ ቦምብ ያፈነዳው ማነው?"

"እኔ ነኝ! ሁለት ቦምብ ወርውሬ ነበር። አንዷ ከሸፈች።"

በነጋታው አስራተ ካሳ ወደ አስመራ እየተመለሰ ከረን ሲደርስ ማሕሙድ ክዳንን አቀረቡለትና አነጋገረው። በተመሳሳይ መንገድ ተናገረ። አስራተ ካሳን፣ "አማሮች ከዚህ አገር መውጣት አለባችሁ። ይሄ የኛ አገር እንጂ የናንተ አገር አይደለም።" አለው።

አስራተ ካሳ በማሕሙድ አነጋገር በጣም ስለተገረመ በዚያኑ

እለት ወደ አስመራ እንዲላክ አዘዘ። ይህን ያደረገው ከረን ላይ በድብዳባ ጉዳት እንዳያደርሱበት በመስጋቱ ነበር።

ከጥቂት ወራት በሁዋላ ራስ አስራተ ካሳ ከገብርኤል ኤድሞንዶ ጋር አዲስ አበባ ላይ ተገናኝተው ሲጨዋወቱ፣ "ስለ አንድ ያገርህ ልጅ ላጫውትህ" ብሎ ስለ ማሕሙድ የነገረው ሲሆን፤ መጀመሪያ ማሕሙድ በድብደባ ብዛት አእምሮውን ስቶ የሚለፈለፍ መስሎት እንደነበር፤ ሁዋላ ግን ድብደባ እንዳልደረሰበት መረዳቱንና ልጁ እንደ አንበሳ ደፋር ልብ እንዳለው አጫውቶታል።

ራስ አስራተ ካሳ ማሕሙድን በቅርብ ይከታተል ነበር።

አስመራ ሲደርስ ማሕሙድን የተቀበለው ፖሊስ፣ "እነዚህ ናቸው እኛ ላይ ፈንጂ የሚወረውሩ ወሮበሎች?" ብሎ በጥፊ መታው። በዚያች ቅጽበት ማሕሙድ እንደ አነር ከመሬት ነጥሮ ፖሊሱን ተመሳሳይ ጥፊ ደረገመበት። ፖሊሱ አጓርቶ ማሕሙድን ለመግደል ሲቃጣ ገላጋዮች ገቡ። ፖሊሱ ተወቀሰ። ፖሊሶቹ በማሕሙድ ጉዳይ ተከፋፈሉ። እዚያው በዚያው ሊገድሉት የፈለጉ ነበሩ። ሌሎች ደግሞ 'ፍርድ ቤት ሳይቀርብ አናስነካም' አሉ።

ጉዳዩ አስራተ ካሳ ዘንድ ሲደርስ ማሕሙድ የፖለቲካ እስረኛ በመሆኑ፣ መረጃ የመደበቅ ዝንባሌም ስለሌለው የሃይል ምርመራ እንዳይደረግበት አዘዘ። ማሕሙድ እስር ቤት እንደገባ፣ "ቀድመን የምናጠቃው ከአማራ ጋር ሆነው የሚያስመቱን ኤርትራውያንን ነው።" እያለ መናገር ቀጠለ። እንዲህ ሲናገር ፖሊሶቹ አንዳንዶቹ እንደ መዝናኛ ሌሎቹ ደግሞ በቁምነገር ይሰሙት ነበር። ማሕሙድ የጀብሃን አላማ ደብለቅ እያደረገ ይናገራል። በተለይ የፖሊስ ጣቢያው አዛዥ ሻለቃ "ወዲ አርባዕተ አስመራ" ማሕሙድን በበጎ መንፈስ አስተናገደው።

ማሕሙድ ፍርድ ቤት ሲቀርብ ዳኛው ከበደ የሚባል ሰው ነበር። ትግርኛ ስለማይችል የፍርድ ቤቱ ሂደት በአስተርጓሚ የሚፈጸም ነበር። አቃቤ ህጉ ባራኺ ይባላል። ዳኞቹ የሞት ፍርድ ለመወሰን ተዘጋጅተው ሳለ አቃቤ ህጉ "ተከሳሹ ልጅ ስለሆነ ከእድሜው በላይ መፍረድ ተገቢ አይመስለኝም።" ሲል ተናገረ።

ዳኞች ወደ ውስጥ ገብተው ከተነጋገሩ በሁዋላ "የሞት

ፍርድ ለመፍረድ አስበው የነበረውን እንደገና በማየት በሃያ አመት እስራት እንዲቀጣ መወሰናቸውን አሳወቁ።

ማሕሙድ በፍርዱ ጉዳይ ምን ሊል እንደሚችል ሲጠብቁ፣

“ሃያ አመት አትቆዩም። እንዴት ሃያ ትፈርዳላችሁ?” አለ።

ከፍተኛ ሳቅ ሆነ።

ዳኛው ምን እንደተባለ ስላልሰማ የሳቁ ተካፋይ አልሆነም ነበር። ተርጉሙው ሲነግሩት ዳኛው በጣም ተቆጣ። የፍርዱን ውሳኔ መቀልበስ ባይችልም ከሃያ አመታቱ የእስር ውሳኔ ባሻገር ለብቻው በልዩ የመቅጫ ክፍል ውስጥ ለሁለት ወራት እንዲታሰር ወሰነበት። የእስር ቤቱ ሃላፊ ግን ማሕሙድን ከተረከበ በሁዋላ ተጨማሪ ልዩ ቅጣቱን አላስፈጽምም ብሎ ውሳኔውን ውድቅ አደረገ።

ማሕሙድ እና ሌሎች የጀብሃ እስረኞችን አስመራ ማቆየት አደጋ መሆኑን የበላይ ባለስልጣናት ገመገሙ። የጀብሃ ድርጅታዊ መዋቅር በአስመራ ጠንካራ ሊሆን እንደሚችል ስለሚጠረጥሩ እስረኞቹ የተሻለ ጥበቃ ወደሚደረግበት ወደ ዓዲኺላ እንዲላኩ ተወሰነ። በዓዲካላ ቆይታቸውም ማሕሙድ እና ሌሎች የጀብሃ እስረኞች የእስር ጊዜያቸውን ጨርሰው የሚወጡ እስረኞችን እየመለመሉ ወደ ትግል ሜዳ እንደሚልኩ በመረጋገጡ 21 ኤርትራውያን እስረኞች ወደ አዲስ አበባ ተላኩ።

ማሕሙድ እና ጓደኞቹ ወደ አዲስ አበባ በመጓዝ ላይ ሳሉ የአዲስ አበባ እስር ቤት ከኤርትራ የተሻለ እንደሚሆን ግምት ነበራቸው። ኢትዮጵያም እንደ እንግሊዝ ባትሆን እንኳ ገዢ ለመሆን በቅታ ኤርትራን በማስተዳደር ላይ ስለነበረች የሰለጠነች አገር ልትሆን እንደምትችል ግምት ነበራቸው። አለምበቃኝ ሲገቡ በተመለከቱት ሁኔታ ግን በጣም ደነገጡ። ከሁሉም በላይ ያስደነገጣቸው የእስር ቤቱ ቆሻሻነት እና ትውከት የሚቀሰቅሰው ሽታ ነበር። የዓዲኺላ እስር ቤት ንጹህና ስርአትና ህግ የነበረው ነበር። በአዲስ አበባ አለምበቃኝ ሌሊት ሽንቱን ለመሸናት የሚነሳ እስረኛ የተኛውን እስረኛ እየረገጠ ይሄዳል። የሚያዩትን ለማመን ተቸገሩ። ማሕሙድ ምንም እንኳ አሳፋሪ እስር ቤት ቢገጥመውም በአስራአንድ አመታት የአለምበቃኝ ቆይታው ድንቅ ኢትዮጵያውያንና

ኤርትራውያን እስረኞችን ለመተዋወቅ በቅቷል።

* * *

በዚያን ቀን ገብርኤልና መኮነን ሲጨዋወቱ፣

“ከማሕሙድ ጋር ተገናኝታችሁዋል?” ሲል ጠየቀው።

“ሁለት ጊዜ ብቻ ነው ያገኘሁት።” አለ።

“ሞራሉ እንዴት ነው?” ሲል ጠየቀው።

“ቀልደኛ ነው። በጣም ደስ ይላል። በተስፋ የተሞላ ነው። አንድ ቀን የታሰረ እንኳ አይመስልም። ጠያቂዎቹ ማለቂያ የላቸውም። ብዙ ወዳጅ አለው።”

ገብርኤል ትከዝ አለና እንዲህ አለው፣

“በአባቴ ወገን ዘመዳችን ነው።”

መኮነን በመደነቅ አባቱን አፍጥጦ አየ።

“ከነማን ጋር ነው የተደራጀኸው ለመሆኑ?” ሲል ጠየቀው።

“በድርጅት ደረጃ አልተደራጀሁም። እስረኞችን የመርዳት ነገር ነው የምንሰራው። ሌላ አይደለም።”

መናገር አለመፈለጉን ታዝቦ ገብርኤል አልተጫነውም።

(ማሕሙድ በእስር ቤት ከተዋወቃቸው መካከል ዱላ አብዱ፣ ማሞ መዘምር፣ ጀኔራል ታደሰ ብሩ፣ እምሩ ወንዴ፣ ዋለልኝ መኮንን፣ መለስ ተክሌ፣ ተፈሪ ብርሃኔ፣ የከበደ ተሰማ ልጅ ሻምበል ጠና ከበደን በልዩ ሁኔታ ኢይረሳቸውም። ከሸፍቶች ደግሞ አገሪ ቱሉ፣ አዳሙ ዘውዴ፣ አሊ በለው እና ሌሎችንም ተዋውቆ ነበር። ማሕሙድ በጠበቃ ተፈሪ ብርሃኔ ጥረት በህክምና ሰበብ በምህረት ከእስር ከተፈታ በሁዋላ ወደ ጅብሃ በመመለስ ትግሉን የቀጠለ ሲሆን፤ ጅብሃ ከትግል ሜዳው ገለል ካለ በሁዋላ ማሕሙድ በሱዳን ቆየ። ኤርትራ ነጻነቷን አጊኝታ ሉአላዊ አገር ከሆነች በሁዋላም “በዚያም ሆነ በዚህ ፍላጎታችን ኤርትራን ነጻ አገር ማድረግ ነበር” በሚል እምነት ወደ ኤርትራ ተመለሰ። በጡረታ እስኪገለል ድረስም በግብጽ፣ በስዊድን እና በጀርመን የኤርትራ ዲፕሎማት በመሆን አገልግሏል።)

ምእራፍ 5

ሳይበረዝ በደም
ሰማያዊ ነበር - የባሕሩ ቀለም

በማሕሙድ ክዳን ጉዳይ ላይ ከተነጋገሩ በሁዋላ ገብርኤልና መኮነን ይበልጥ ተቀራረቡ። መኮነን ግልጽ ሆኖ ለአባቱ ብዙ ጥያቄዎች ማቅረብ ጀመረ። ገብርኤልም ልቡ ከሸፈተ ልጁ ለሚቀርቡለት የፖለቲካና የታሪክ ጥያቄዎች በተቻለው መጠን ሚዛናዊ ሆኖ ለማብራራት ጥረት አደረገ። በቀጥታ ከፈዴሬሽኑ መፍረስ ጋር ለተያያዙ የህግ ጉዳዮች ግን በቂ ምላሽ አልነበረውም።

የኤርትራ ብቻ ሳይሆን የመላ ኢትዮጵያ የፖለቲካ ጉዳዮች መቀጣጠል የጀመሩበት ጊዜ ስለነበር ገብርኤል ስለ ልጁ በጣም ሰጋ። አሳቡን ቢከፍልለት በሚልም ስራ ፈለገለት። እና በመሬት ይዞታ መስሪያ ቤት የካርታ ክፍል ውስጥ ስራ አገኘለት። ስራውን የሚሰሩት እንግሊዞች ነበሩ። በሄሊኮፕተር እየዞሩ ካርታ ያነሱ ስለነበር መኮነን ረዳት ሆኖ አብሯቸው ሲዞር ይውላል። መጀመሪያ ላይ በስራው በጣም ተደስቶ ታየ። ስራ ውሎ ማታ ሲመለስ ሄሎኮፕተር ላይ ሆኖ ያየውን መልከአ ምድር ሲናገር በጣም ደስተኛ እና ስሜታዊ ነበር።

አንድ ቀን እንዲሁ ስራ ውሎ ሲመለስ ከገብርኤል ጋር ቁጭ

ብለው ስለስራው ጠየቀው። መኮነን በስሜት ተውጦ መለሰ፣

“የኢትዮጵያ ለም መሬት ሁሉ በጥቂት ባላባቶች የተያዘ ነው። የአንድ ባላባትን መሬት በሄሊኮፕተር ለማቋረጥ ግማሽ ሰአት ይፈጃል። ጠረፍ ጠረፉን ስንዞር ለሰአታት ስንበር የእርሻው መሬት የንጉሱና የዘመዶቻቸው መሆኑን ነገሩን። አገሩ በሙሉ በጥቂት ሰዎች ንብረትነት የተያዘ ነው። ደሃው የደቡብ ገበሬ በእጁ የቀረ መሬት የለውም።”

በዚህ ንግግር ገብርኤል ተጨነቀ፣

“እዚህ የምትናገረውን ውጭ ሄደህ አትድገም፤ ተጠንቀቅ፤ የመሬት ጉዳይ በዚህ አገር አደገኛ የፖለቲካ ርእሰ ጉዳይ ነው።” አለው። አያያዘናም አከለበት፣ “.....ድሃና ብዙሃኑን የገፋና የበደለ ዘልአለም በምኞት ሊኖር አይችልም። ድሃው ሽክሙ ሲበዛበት አንድ ቀን ተቆጥቶ ይነሳል። ያን ጊዜ ለህይወታቸውም ዋስትና አይኖራቸውም። በፈረንሳይ አብዮት የታየ ነው። በሩስያም የሆነው ተመሳሳይ ነው።” ሲል ተናገረ።

መኮነን በተፈጥሮው ቀልድና ጨዋታ የሚወድ፣ በተጫዋችነቱ የብዙ ሰዎች ጓደኛ ነበር። በማህበራዊ ህይወት ውስጥ በጠባዩ ብዙ ሰዎች በቀላሉ ያቀርቡታል። ገብርኤልና ሉላ ወደ ሰርግ ሲሄዱ መኮነንን ይዘው መሄድን ያዘወትራሉ።። ትግርኛ ዘፈን ሲጀመር ነጠላው ወገቡ ላይ ጠምጥሞ ቀድሞ ይነሳል። የገንዘብ ሽልማት በገፍ ያገኛል። የተሸለመውን ደግሞ ቢያንስ ግማሹን ለሌሎች ይሸልማል። “መኮነን ካለ ሰርግ ይደምቃል” እስኪባል በኤርትራውያን ማህበረሰብ ውስጥ የታወቀ ነበር። ኤርትራውያን ሉላና ገብርኤልን ሰርግ ሲጠሩ፣ “አደራ መኮነን አንዳይቀር” ይሏቸው ነበር።

ታህሳስ ወር 1976 ላይ መኮነን ሲዳሞ ክፍለሃገር ስራ ማግኘቱን ለቤተሰቡ ተናገረ። በዚያን ጊዜ ደበሳይ ከሚሰራበት የመተሃራ ስኳር ፋብሪካ ተመልሶ ለሰንበት እረፍት አዲሳባ ነበር።

“ገንዘብ እፈልጋለሁ ስጠኝ።” አለው።

“ለምንድነው የፈለግኸው?”

“ስራ አጊንቼ ወደ ሲዳሞ እየሄድኩ ነው።”

“ምን ያህል ልስጥህ?”

“ሶስት ወይም አራት መቶ?”

“ይሄ ሁሉ ምን ያደርግልሃል?”

“እኔ ህጻን ልጅ አይደለሁም። የምትሰጠኝ ከሆነ ስጠኝ።”

ደበሳይ 400 ብር ሰጠው።

ዛሬ ነገ እያለ ጥቂት ቀናት ቆየ።

በርግጥ መኮነን ወደ በረሃ ለመሄድ ማሰቡን ለእናቱ የነገራት፤ የጉዞ ሰአቱ ግማሽ ሰአት ብቻ ሲቀረው ነበር። በቤቱ ውስጥ ልጆች አልነበሩም። ገብርኤል ከቁርስ በሁዋላ ለመንሸራሸር ወጣ ብሏል። ሉላ ምሳ ለማዘጋጀት ወጥቤት ነበረች። እለቱ አርብ ነበር፣ መኮነን ኩሽና ከገባ በሁዋላ ወንበር ስቦ ተቀመጠ፣

“አሁን መሄዴ ነው።” ሲል ተነፈሰ።

ዘወር ብላ አየችው፣

“ቅዳሜ ብለህ ነበር።” አለች።

“ዛሬ የግል መኪና ስላገኘሁ ነው።”

ከዚያም ረጋ ብሎ አጫወታት፣

“ወደ ሲዳሞ እንደምሄድ የተናገርኩት እውነት አይደለም። ወደ በረሃ ነው የምሄደው።”

ታለቀልቀው የነበረውን ብርጭቆ የእቃ ማጠቢያው ገንዳ ውስጥ ተወችው። የሰማችውን መዋጥ ተቸግራ አጠገቡ ወንበር ስባ ተቀመጠች። እንዲደግምላት ፈልጋ አይን አይኑን አየችው። ትንፋሽ አልነበራትም። እንደምንም አቃስታ የልጇን አሳብ ተከላከለች፣

“መኮነን ወደይ! ለዚያስ አልደረስክም። ገና ልጅ ነህ።”

ሳቀ። ሳቁ ደስ አላላትም።

“ከኔ ያነሱ ወጣቶች በረሃ ገብተዋል።” አላት።

“አይ! አንተ ትንሽ ነህ። ብትማር ይሻላል።”

ጥቂት በዝምታ እንደቆዩ ሉላ ሰውነቷ ተንቀጠቀጠባት፣

“አትሂድ እባክህ። ስቃዩን አልችለውም።”

ዝምታ ሆነ እንደገና።

“የማውቅሽ ሉላ አልሆንሽብኝም። በረሃ ስለሚታገሉት ታጫውቺኝ ነበር’ኮ። ትኮሪባቸው የለም እንዴ?”

በዚህ ጊዜ ሉላ እንባዋ ተዘረገፈ።

“ምን ላድርግ? ልጄ እኮ ነህ? ሳትነግረኝ ብትሄድ ይሻለኝ ነበር። እንዴት አድርጌ ሂድ ብዬ እሸኝሃለሁ?”

“ባልነግርሽ ትጎጃለሽ ብዬ ነው የነገርኩሽ?”

“ልጄ ነህ። እንዴት ይሆናል?”

ከተቀመጠችበት ለመነሳት ሞከረች። አልቻለችም። መልሳ ቁጭ አለች። ሰውነቷ ይንቀጠቀጣል። አይነ ውሃውን አይታ አወቀች። መኮነን እንደሚሄድ አወቀች። ልታቆመው እንደማትችል የእናትነት መንፈሷ ሹክ አላት። ሁለት እጆቿን ፊቷ ላይ ሸፍና እንባዋን ለመግታት ጥረት አደረገች። መንፈሷን አበረታታች፣ ግን አልሆነላትም። አጥንቷ የደቀቀ ያህል ሆነባት፣

“እኔው ነኝ የገፋፋሁህ?”

“አይ አይደለም። ግኝኑነት ነበረኝ።”

“ከማን ጋር? ከበረኸኞቹ?”

እንባዋ ከአይኗ ጠፋ። ልጇን ትክ ብላ ስታጤነው ትንሽ ልጅ እንዳልሆነ አየች። ለካስ ጢም አብቅሏል። ምስጢሮችም አሉት። ለካስ ሌላ ሰው ነው። ለካስ ልጇ መሆኑ አብቅቶለታል። ለካስ ልቡ እንደ አለት ሆኗል። እናቱ ስታለቅስ ሆድ አይብሰውም።

“ከነማን ጋር ነው የተገናኘኸው?”

“ከምታውቂያቸው ጋር ነዋ።” ብሎ ሳቅ አለ።

“ስማቸው ማን ይባላል?”

“ምን ያደርግልሻል?”

“እውነትክን ነው። ምንም አያደርግልኝም።”

እንደገና ጠየቀችው፣

“ግን ምንድነው የምትሰሩት?”

“ባልሽ ይሰራው የነበረው አይነት ስራ።” ብሎ ሳቀ።

ልቧ እንደገና ቀጥ ሊልባት ደረሰ።

መስማት አልቻለችም። የተሰማትን የተደበላለቀ ስሜት ማስተናገድ ተቸገረች። ቁጭቷን የሚፈውስ መድሃኒት ያገኘች ያህል ደሟ በሰራ አካላቷ ሲራወጥ ተሰማት። በተቃራኒው ደግሞ ፍርሃት አርበደበዳት። ከተቀመጠችበት ተነሳችና ወደ ደጅ ብቅ አለች። በአካባቢው ሰው መኖር አለመኖሩን ካጣራች በሁዋላ ተመልሳ መጥታ የኩሽናውን በር ጥርቅም አድርጋ ዘጋች። ወደ ልጇ ተንደርድራ ሄዳ አጠገቡ ከተቀመጠች በሁዋላ እንደገና ተማጸነችው፣

“አንድ ሁለት ቀን ቆይና ትሄዳለህ።”

“አደይ! አሁን እየሄድኩ ነው።”

ሉላ በእጆቿ አፏን ግጥም አድርጋ ያዘች።

እጇ ይንቀጠቀጣል፣

“አሁን አትሄድም። አባትህ መምጣት አለበት። ከአባትህ ጋር ሆነን እንመክርበታለን። ወላጆህ የሚሉህን መስማት አለብህ።”

“አሁን እሄዳለሁ። ለአያይ ብቻ ንገሪ።”

ከተቀመጠበት ተነሳና እናቱን አቅፎ ሳመ። ጉንጮቿ ረጠቡት። ላለመላቀቅ ያደረገችው ሙከራ አልሆነም። ልጇ እጁ እንደ ወይራ መሆኑን አስተዋለች። በቀላሉ አስለቀቃትና ትንሽ የእጅ ቦርሳውን አነሳ። ሉላ ከመቅጽበት ወደ መኝታ ክፍሏ ገባች። ተመልሳ ለመምጣት ደቂቃም አልወሰደባት። የተጠቀለለ ገንዘብ ኪሱ ውስጥ ጨመረችለት። ሊከላከል ሲሞክር በግድ ወሸቀችለት። በድጋሚ እናቱን ስሞ ፈትለክ ብሎ ወጣ።

ሉላ ተከትላው ወጣች።

ሮጣ ስትወጣ ከግቢው ደጃፍ ላይ ከቆመች ፔጮ 404 መኪና ውስጥ ሲገባ አየችው። መኪናዋ ከአይኗ ራቀች። ስትታጠፍ ከአይኗ ተሰወረች። ልብዋ ከበዳት። ደጃፉ ላይ ካለ አንድ ድንጋይ ላይ አረፍ አለች። የሚንቀጠቀጥ ጉልበቷን ለማቆም ሞከረች። አልሆነላትም።

መኮነን ከሄደ ከሁለት ሳምንት በኋላ ‘‘ማላካል ደቡብ ሱዳን ገብቻለሁ።” ብሎ ደብዳቤ ላከ። አንድ ወር ቆይቶ እንደገና ከካርቱም ደብዳቤ ላከ። ገንዘብ ለመላክ ሰው በማፈላለግ ላይ ሳሉ ግን በመካከሉ የመኮነን ድምጽ ጠፋ። ከጥቂት ወራት በሁዋላ ወደ ኤርትራ የትግል ሜዳ መሻገሩን ሰሙ።

በሚቀጥለው ሰንበት ገብርኤልና ሉላ ቤተክርስትያን ሄደው ረጅም ጸሎት አደረጉ። እግዚአብሄር አምላክ መኮነን እና ጓደኞቹን እንዲጠብቃቸው፤ ከቅን ልብ የመነጨ ጥያቄያቸውንም እንዲሰማ ለመኑት። የኤርትራ ህዝብ ከጦርነት ወደ ጦርነት መገላበጡ እንደበዛበት አስታውሰው ሲያበቁ፤ የአምላክን ምህረት ጠየቁ።

* * *

በዚያው ሰሞን አንድ ማለዳ ገብርኤል አዲስ አበባ ከሚገኝ መኖሪያ ቤቱ በረንዳ ላይ ተቀምጦ ከስምንተኛ ልጁ ከሃብተአብ ጋር እየተጨዋወተ ሳለ ከደጅ የደወል ድምጽ ተሰማ። ሃብተአብ ሄዶ የግቢውን መዝጊያ ከፈተ።

ደጃፉ ላይ ወረቀት የያዘ ሰው ቆሟል።

“ፊታውራሪ ገብርኤልን ፈልጌ ነበር።” ሲል ጠየቀ።

ሃብተአብ እንግዳውን እየመራ ወደ ውስጥ ዘለቀ። ሰውየው ሰላምታውን ካቀረበ በሁዋላ በእጁ የያዘውን ቴሌግራም አስፈርሞ አስረከበ። ገብርኤል እንግዳውን አሰናብቶ ሲያበቃ ቴሌግራሙን እንደዋዛ ተመለከተ።

በዚያችው ቅጽበት ገጽታው ተለዋወጠ። እንባው በጎንጮቹ ላይ መውረድ ጀመረ። ሃብተአብ በድንገተኛው የአባቱ የስሜት ለውጥ በመደናገጡ ስለ ቴሌግራሙ ምንነት ለማወቅ አባቱን ወተወተ። ገብርኤል ስሜቱን ለመቆጣጠር እየጣረ ነበር። አይኖቹን

በኢጣልያ ቋንቋ ከተጻፈው ቴሌግራም ላይ ሳይነቅልም እንዲህ አለ፣

“አቮካቶ ካታንዮ ቪንቸንሶ ማረፉን ይህ ቴሌግራም ይናገራል። እናትህን ጥራትና ይህን አሳዛኝ መርዶ ልንገራት። እኔን ከሞት አትርፎ ህይወት የሰጠኝ ወዳጄ ካታንዮ አረፈ።”

ሉላ በገብርኤል ያልተለመደ ድምጽ ተስባ ወደ በረንዳው በመምጣት ምን እንደገጠመው በሶማሊኛ ቋንቋ ጠየቀችው። እሱም ስሜት ባሸነፈው ድምጽ መለሰላት፣

“ካታንዮ አረፈ ሉላ። ልክ አሁን ሰማሁ። ይኸውልሽ የደረሰኝ ቴሌግራም። ‘ጓደኛህ ካታንዮ አረፈ።’ ይላል። የቀብር ስነስርአቱም ከአንድ ሳምንት በፊት ተፈጽሟል። ሉላ! ወዳጃችን፣ ጓደኛችን ካታንዮ አረፈ።“

በስሜት መናገሩን ቀጠለ፣

“ካታኒዮ ለጥቂት አመለጠን ሉላ። በሚቀጥለው የበልግ ወር ኢጣልያ ሄጄ ላየው፤ ከዚያም ወደዚህ ይገፍው ልመጣና ልጆቼን ላስተዋውቀው አሳብ ነበረኝ። ካታንዮ ቀደመኝ። በልጆቼ ፊት በድጋሚ ላመሰግነው ብርቱ ፍላጎት ነበረኝ። አልሆነም። ካታንዮ ሄደ። አህ! ካታንዮ ለዘልአለሙ ሄደ። ሉላ! በይ እርምሽን አውጪ። ከአምላክ በታች የምታከብሪው ሰው ዳግም ሳታይው አረፈ። ቤተሰባዊ ደስታችንን ሳያይ፣ የሰጠንን የህይወት ስጦታ ሳያይ አመለጠን። ካታንዮ ለጥቂት አመለጠን። ከሶስት ወራት በሁዋላ ኢጣልያ ሄጄ ላየው . . . ”

ገብርኤል ፊቱን በሁለት እጆቹን ሸፍኖ ማልቀሱን ቀጠለ። ሉላ የካታንዮን መሞት እንደሰማች አንዳች ቃል ሳትተነፍስ በረንዳው ላይ ከነበረው ወንበር ላይ ቁጭ አለች። እሷም እንደ ባለቤቷ እጇን ግንባሯ ላይ አኖረች። እንባዋም ፊቷን አጠበው።

ምእራፍ ፮

በተራ ጥፊ - በተራ እርግጫ

ተንከባለለ እንደ ሙቀጫ

* * *

ቀይ ድምጽ ተሰማ

ከናቅፋ ተራራ - ከሳህል ባድማ

እነሆ! አጤ ሃይለስላሴ ዙፋናቸውን አጡ። ህዝባዊ አመጽ ገፍቶ ሁሉን አሳጣቸው። ሁሉን ፈለጉ፤ ሁሉን አጡ ሆኑ። “ደርግ” የተባለ የወጣት መኮንኖች ቡድን የተማሪዎቹን አብዮት በጁ አስገባ። የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች የሚያነሱትን ጥያቄዎች ካፋቸው እየቀለበ ምላሽ ሰጠ። ዋናው ህዝባዊ ጥያቄ “መሬት” ነበር። “የእርሻ መሬት - ለአራሹ ገበሬ” ታወጀለት። በዚህ አንጀቱ የራሰው ህዝብ “ዋይ! ዋይ! ባላባት! - ከእንግዲህ ቀረ - ሳይሰሩ መብላት!” እያለ ባላባቱ ላይ አፏጨበት።

ንጉሳውያን ቤተሰቦች እና ባለስልጣናት ተሰብስበው እስር ቤት ከገቡ በሁዋላ ፊታውራሪ ገብርኤል ከልጆቹ አንዱን ይዞ ሊጠይቃቸው ሄዶ ነበር። “በዘመድ በር” ሳይሆን፣ “በጓደኛ በር” በኩል ነበር ፈቃድ አጊኝቶ መግባት የቻለው።

የሚያውቃቸውን የቻለውን ያህል ለማነጋገር ጥረት አደረገ። እስረኛ ጥየቃውን ጨርሶ ሲያበቃ በህይወቱ ውስጥ እንቅፋትና

ጋሬጣ ሆኖ የኖረውን አንድ ባለስልጣን ለብቻ በቆይታ ለማናገር ተገፋፋ። ይህን አለማድረግ አልቻለም። በመሆኑም ጉብኝቱን ባመቻቸለት ወዳጁ በኩል ሞቅዲሾና አዲስ አበባ ላይ ለስቃይና ለእስር ከዳረገው ሰው ጋር ለብቻ ለመገናኘት እድል አገኘ።

ባለስልጣኑ ወደ መጠየቂያ ክፍሉ ሲገባ ቱታ እንደለበሰ ነበር። ገብርኤልን ሲያይ ድንግጥ አለ። ገብርኤል ከተቀመጠበት ተነሳና ጨበጠው። አይን ለአይን ተጋጩ። ሁለቱም ከተቀመጡ በሁዋላ ባለስልጣኑ ቀድሞ ተናገረ፣

'እኔ መሆኔን እንዴት አወቅህ?"

"ብላታ ታከለ ነገረኝ።"

እስረኛው የለበጣ ሳቅ ሳቀ። እና መሬትና ጣርያ አየ።

"ደስ ብሎሃል? ልትበቀለኝ ታስባለህ?"

"አይ! በቀለኛ አይደለሁም።"

"ምን ፈልገህ አስጠራኸኝ ታዲያ?"

"ማወቄን እንድታውቅ ብቻ ነው።"

ከዚህ በሁዋላ የሚያወሩት ነገር አልነበረም። ገብርኤል ያመጣለትን መጽሃፍ ሰጥቶት ሲያበቃ ለመሄድ ተነሳ። ሊወጣ ሲል፣

"ቆይ! አንድ ነገር ልንገርህ?" አለው።

ገብርኤል ቆም አለ፣

"ደበሳይ የተባለ ልጅህን አውቀዋለሁ።"

"የት አወቅኸው?"

"ከልጄ ጋር ማድሪድ አብረው ነው የተማሩት። ልጄን ለማየት ሄጄ ሳለ እዚያ አጊንቼው ነበር። ከልጄ ጋር ጥሩ ወዳጆች እንደነበሩ አስታውሳለሁ።"

ምን ሊለው እንደፈለገ አልገባውም።

ዝም ብሎ ጠበቀ፣

"ልጆቹ ባያውቁ ይሻላል። አይጠቅማቸውም። በሰላም

ቢኖሩ ይሻላቸዋል። ቂምና ቁጭት ወይም መሳቀቅና ሃፍረት እኩል ጎጂ ናቸው። እስካሁን ካልነገርካቸው ወደፊትም ባትነግራቸው ይሻላል። አንተም ብትረሳው ይሻላል። አለቦታህ ተገኝተህ ነው....”

ጣራ ጣራውን ሲያይ ቆየና እንዲህ አለ።

“...ያንተን ጉዳት ባለማሰቤ አዝናለሁ። ይቅርታም እጠይቅሃለሁ። እያሱ ነግሮህ ከሆነ አላውቅም። ብቻ ከንጉሱ ጋር ነገር ነበረኝ። ከአገር የሚቀድም ጉዳይ ነበረን። ይኸው ለማናችንም ሳይጠቅም እዚህ ታጉረናል።”

ገብርኤል ለአፍታ በጸጥታ አሰላሰለ። እና እንዲህ አለ፣

“ከዚህ ሁሉ በሁዋላ በህይወት ዘመኔ የተማርኩት ነገር ቢኖር የፖለቲካን አስቀያሚና ቆሻሻ ገጽታ ብቻ ነው። እኔም ብሆን አልመጻደቅም። በተመሳሳይ የበደልኩት ሌላ ሰው ሊኖር ይችላል። የሃጢአት ትንሽ ትልቅ የለውም።”

ፋታ ወሰደና ተሰናበተው፣

“እግዚአብሄር ይርዳችሁ።”

በዚያን ዘመን ብዙ ነባርና አዳዲስ ዜማዎች እየተሰሙ ነበር። ደግ ከሚመኙ ዜማዎች አንዱ የዮፍታሄ ንጉሴ ነበር፣

ወላድ ኢትዮጵያ - ለልጆቿ ብላ
ስንዴውን ጠብቃ - እንክርዳዱን ነቅላ
ስትመግበን ኖረች - በጸሃይ አብስላ

ስለማንኛዋ ኢትዮጵያና ስለየትኞቹ ልጆች እንደሚያወጋ ግጥሙ ግልጽ አላደረገም። በተቀረ አብዛኛው ኢትዮጵያዊ ገበሬ በጸሃይ አብስላ የምትመግበውን ሳይሆን፤ በላቡ ያበሰለውን ከምትነጥቅ ጨካኝ ኢትዮጵያ ጋር ነበር የሚተዋወቀው። የኢህአፓ አባላት ከደርግ ከባድ በትር ሲያርፍባቸው ገጣሚዎቻቸው ተሳቀቁ። በምሬት ያቀነቀኑት ተገላቢጦሽ ቅኔ በርግጥ መራር እውነት ነበር፣

አባት ኢትዮጵያ - ለልጆቹ ብሎ
አረሙን ኮትኩቶ - አበባውን ነቅሎ።
ጥላቻ መገበን - በባሩድ ቀቅሎ

በዚያን ዘመን የጎጃም እረኛ ለደርግና ለመኳንንቱ አንዳንድ ነጠላ ዜማ ለቀቀ። ትእዝብቱን በቅኔው ገለጸ። ደርግን አለው፣

ወጣ ወጣና - እንደሸንበቆ
ዙፋኑን ያዘ - ጎራዴ ታጥቆ

መሳፍንቱን ደግሞ አላገጠባቸው፣

በተራ ጥፊ - በተራ እርግጫ
ተንከባለለ - እንደ ሙቀጫ

የመኢሶን አባላት እንደ ኢህአፓ በግጥም ችሎታ አይታወቁምና የራሳቸውን ቅኔ ማፍለቅ ባይችሉም ከጎጃም እረኛ ቅኔዎች አንዳንድ ስንኝ መንትፈው በራሳቸው እድል ላይ አንጎራጎሩ።

ወጣ ወጣና እንደ ሸንበቆ
ተንከባለለ እንደ ሙቀጫ

ግጥሙ ቤቱን አልመታም። የተማሪዎች ተራማጅ አመጽ፣ ጥያቄና እንቅስቃሴም እንደ ግጥሙ ኢላማውን ሳተ።

ጊዜው የውዥንብር ጊዜ ነበር።

አንድ የአምባሰል አዝማሪ የጊዜውን ፖለቲካ አካሄድ ባለማስተዋል አበጀሁ ብሎ በራስ ሆቴል የፎቁ ላይ አዳራሽ እንዲህ ሲል በማቀንቀኑ የወቅቱ አብዮተኛ ፖሊሶች ወደ እስር ቤት ላኩት፣

በታንክ መጥተውበት - እጅ ስጥ ቢሉት
አማን አንዶም ጀግና - ተኩሶ ሲሞት
ያላንዳች መትረየስ - ያላንዳች ጥይት
እንደ በግ ተነዳ - ሸዌ መኳንንት

አጤ ሃይለስላሴ ወድቆ ደርግ ሲመጣ ታዋቂው የአማርኛ ገጣሚ ሰይፉ መታፈሪያ ፍሬው መንግስቱ ሃይለማርያምን ከአጤ ቴዎድሮስ ጋር በማመሳሰል የገጠመው ቅኔ ተቀባይነት አገኘ፣

የቋራው አንበሳ - ካሳ
በመቶ አመቱ ቢያገሳ
ስንቱን! - ስንቱን ቀሰቀሰውሳ

በርግጥ ኮሎኔል መንግስቱና አጤ ቴዎድሮስ የሚመሳሰሉበት ነገር ቢኖሩ የሸዋ ነገስታት ላይ በወሰዱት የጭካኔ ርምጃቸው ብቻ ነበር። ሁለቱ የአቢሲንያ ንጉሶች አሟሟታቸው ላይ ሊመሳሰሉ እንደሚችሉ “ብዙሃን” በጣም ጠብቀው ነገር። ኮሎኔል መንግስቱ ሃይለማርያም በብዙሃኑ ምኞት በጣም ተገረመ። ዳሩ ግን ምንም አላላቸው። ታዝቦ ሲያበቃ፣ ዝም ብሎ ወደሚሄድበት ሄደ። የእሪ በከንቱ አዝማሪ ታዲያ ነጠላ ዜማ ለቀቀ፣

የሰው የለው ሞኝ - የአውሊያ የለው ቀኝ
ብላቴ አጠቃቅሶ - ሓራሬ ሲገኝ

ኢትዮጵያ በጥያቄዎች ጎርፍ ተጥለቀለቀች። የኤርትራ ጥያቄ፣ የኦሮሚያ ጥያቄ፣ የብሄረሰቦች ጥያቄ፣ የመለዮ ለባሹ ጥያቄ፣ የዴሞክራሲ ጥያቄ፣ የማህበራዊ ፍትህ ጥያቄ፣ የሶማሊያ የመሬት ጥያቄ፣ የአይዲዮሎጂ ጥያቄ፣ የሙስሊሞች የእምነት እኩልነት ጥያቄ፣ የሴቶች ጥያቄ፣ የኮሪያና የኮንጎ ዘማቾች ጥያቄ፣ ማቋረጫ የሌላቸው ጥያቄዎች አዲስ አበባን አንቀው ያዟት።

ልምድ የሌላቸውን መስመራዊ መኮንኖች ለመርዳት ምሁራን ከያግጣጫው ተሰባሰቡ። መርዳቱ ቀረና እነርሱ ራሳቸው አስታራቂ ረዳት ፈለጉ። እና ኢትዮጵያ የጦርነት አውድማ ሆነች። የቃላት ኮረት አናቷን ቀወራት። ቦርቧሪዎች፣ ተገንጣዮች፣ ቀኝ መንገደኞች፣ አሻጥረኛ ነጋዴዎች፣ ፊውዳሎች፣ ቡርዣዎች፣ የፒየትሮ ዶላር ቅጥረኞች፣ ጠባብ ብሄረተኞች፣ ፍረጃው ማቋረጫ አጣ።

ገጣሚው ፈላ። አብዮታዊ ዘፈኖች ጆሮ አደነቆሩ። ፈጣን ነው ሞተሩ፣ ፈጣን ነው ሻለቃው፣ ፈጣን ነው ባቡሩ ተዘፈነ። ፈጣን ያልሆኑ ተጨፈለቁ። የነበረው እንዳልነበረ ሆነ። የታሰበው ወዳልታሰበው ተገለበጠ። ህልም እንዳልታለመው ተፈታ። እናም በጊዜ ሂደት ነገሮች ከእጅ አፈተለኩ።

ኮሎኔል መንግስቱ ከአጤ ሃይለስላሴ የሰለጠነና ባለሙያ ወታደር ወርሶ ነበር። ቀስበቀስ ግን እየተዋጠና እየተዳከመ መጣ። 40ሺህ የነበረው የአጤ ሃይለስላሴ ወታደር ባጭር ጊዜ ውስጥ ቁጥሩ ወደ 140ሺህ ሲያሻቅብ የጥራት ደረጃውም የዚያኑ ያህል ቁልቁል

ወረደ። እንደ ብዛቱ የኤርትራን የነጻነት ታጋዮች ሃይል መቋቋም ባለመቻሉ ቁጥሩ በፍጥነት ወደ 170 ሺህ አሻቀበ። በኮሎኔል መንግስቱ ዘመነ መንግስት የኢትዮጵያ ወታደር ስነልቦና የተገነባው "ኤርትራን የጨመረ አንድ ታላቅ ኢትዮጵያ መገንባት" በሚል ነበር።

* * *

መኮነን ገብርኤል ወደ ሻእቢያ ከገባ በሁዋላ ለአንድ ወር ያህል ባህሪ ባራ ወታደራዊ ስልጠና ወሰደ። ከዚያም በቀጥታ ብርጌድ 44 ተመደበ። በፊሊጶስ ወልደዮሃንስ የምትመራ፤ አዲስ የተቋቋመች ብርጌድ ነበረች። 44ኛ ብርጌድ ሶስት ባታልዮን ነበራት። መኮነን በሶስተኛው ባታልዮን፤ የመስርዕ አዛዥ ከመሆኑ በፊት በተራ ተዋጊነት ጥቂት አሳልፏል።

የመጀመሪያ የተካፈለበት ውጊያ ምጽዋን ማጥቃት ነበር። በአመቱ ትግራይ ገርሁስርናይ በመሄድ በሴሮ በኩል ከመጣው የኢትዮጵያ ሃይል ጋር ጦርነት ላይ ሰነበቱ። በዚያው አመት ወደ ምጽዋ አካባቢ በመሄድ በዶጋሊ እና በማዕሚደ አካባቢ እየተዋጉ ቆዩ። ወራት ያህል ከጠላት ጀርባ በቡድን ተከፋፍለው የኢትዮጵያን ሰራዊት በማዳከም ውጊያ ላይ ተጠመዱ።

ዓዲንፋስ፣ ዛግር፣ እምባትካላ፣ ባልዋ፣ በረኸ (ሰራየ) እየተንቀሳቀሱ የሽምቅ ውጊያ ሲያካሂዱ ከቆዩ በሁዋላ፤ በሰኔ ወር 1979 ደርግ 5ኛውን ወረራ ሲጀምር ወደ ሳሕል ህዳቸ ወደተባለ ቦታ ተጠርተው በመሄድ እንዲሁ በከባድ ውጊያ ላይ ከረሙ።

ይህን የህዳቸ ቆይታ ወይም መእደነ የተባለውን ኮረብታ የመያዝ ኦፕሬሽን በወቅቱ የብርጌድ 44 አዛዥ የነበረው ጄኔራል ፊሊጶስ ወልደዮሃንስ "መፈጸምታ" በሚለው መድበል ላይ "ጦርነት ከስነእውቀት በላይ ስነ ጥበብ ነው" በሚል ርእስ ተርኮታል። በዚህ አስደናቂ ውጊያ በኢትዮጵያ በኩል የግንባሩ አዛዥ የነበረው፤ በወታደራዊ ሳይንስ ብቃቱና ጀግንነቱ ስሙ በተደጋጋሚ የሚነሳው ኮሎኔል ካሳ ገብረማርያም ህይወቱን ከፍሏል።

(የኮሎኔል ካሳ ሴት ልጅ ዶክተር ሰንታየሁ በወርሃ መጋቢት 2017 ስለ አባቷ ባሳተመችው መጽሃፍ "አባቴ ራሱን ገደለ እንጂ በጠላት

አልተገደለም።" ስትል አስተባብላች። ጀኔራል ፊሊጶስ እንደተረከው ግን ውጊያው በእጅ ቦምብ፣ በሞትረየስ፣ በጠመንጃና በአርፒጂ የተከናወነ ድንገተኛ ስለነበር ኮሎኔል ካሳ በውጊያው መሃል መገደሉን ይገልጻል። ቀድመው የኮሎኔሉን ሬሳ ያገኙት ታጋዮች በሬዲዮ የላኩለት ሪፖርትም ኮሎኔሉ በውጊያው መገደሉን የሚጠቁም ነው። ኮሎኔል ካሳ ከመገደሉ በፊት መእደነን የመቆጣጠር ተልእኮ ይዞ ታጋዮቹን እየመራ ተራራው ላይ የወጣው ወልደአብ ገብረልዑል ጭምር መሰዋቱ ተተርኳል።)

መኮንን አባል የሆነባት ብርጌድ 44 ሶስተኛ ቦጦሎኒ በህዳቹና በመእደነ ውጊያ ከተካፈለች በሁዋላ በአመቱ፤ ማለትም በ1980 ደርግ "ቀይ ኮከብ" ሲል የሰየመው 6ኛው ወረራ ከመጀመሩ በፊት ናቹፋ ገባች። "ቀይ ኮከብ ዘመቻ" ዛሬ ነገ ይጀመራል እየተባለ ይጠበቅ ስለነበር ከጥር 1980 እስከ ወርሃ ሰኔ ብርጌድ 44 በተለያዩ የማጥቃት ውጊያዎች ላይ ከሰነበተች በሁዋላ፤ በወርሃ ሰኔ ወደ ቋሚ መከላከያ ቦታዋ ተመለሰች።

በ1981 ታህሳስ ወር መኮነን ወደ 16ኛው ዙር የካድሬ ስልጠና በመላኩ ከብርጌድ 44 ተለያያ። ስልጠናው የሚካሄደው ዓራግ አካባቢ ግልዕ በተባለ ቦታ ነበር።

ሻእቢያ "የጠላት ወረራዎች" ብሎ በተለምዶና በጥቅሉ የሚጠራቸው ውጊያዎች በጠቅላላ ስምንት ናቸው። "ሶስቱ ወረራዎች" ሻእቢያ ወደ ናቅፋ በማፈግፈግ ላይ በነበረበት ጊዜ የተፈጸሙ ውጊያዎች ሲሆኑ፤ መኮነን ገብርኤል በአራቱ ወረራዎች ላይ በቀጥታ ተካፍሏል። በብርጌድ 44 የአባልነት ቆይታው በትምህርት ደረጃውና በፖለቲካ ንቃቱ የተሻለ ደረጃ ላይ ከነበሩት አንዱ ስለነበረ በታጋዮች ዘንድ በመምህርነት ይታወቅ ነበር። ርስበራስ በሚደረገው የአካዳሚ መማማር ዋና ተሳታፊ ነበር። በካድሬ ስልጠና ላይ ሁለት ወራት እንደቆየ ደርግ "ቀይ ኮከብ" ሲል የጠራው 6ኛው ወረራ ተጀመረ። ጦርነቱ ሲጀመር በ16ኛው የካድሬ ስልጠና ላይ የነበሩት ሁሉ ወደ ግንባር ገቡ።

እልህ አስጨራሽ ውጊያ የሚደረግበት ጊዜ ነበር።

ከ1977 እስከ 1978 ባለው ጊዜ ምጽዋ፣ አስመራ፣ ዓዲቀይሕ፣ ባረንቱና አሰብ በነጻነት ታጋዮች ተከበው ነበር።

በመካከሉ ግን ሶቪየት ህብረት ኢትዮጵያን ለመርዳት በመወሰኗ የሃይል ሚዛኑ ተለወጠ።

ደርግ በአጭር ጊዜ ውስጥ “ወንበዴዎችን” ጠራርጎ ለመደምሰስ ወሰነ። የነጻነት ታጋዮች ደግሞ ስልታዊ ማፈግፈግ በማድረግ በተራዘመ ጦርነት የኤርትራን ነጻነት ማረጋገጥ እንደሚቻል ስትራቴጂ ነደፉ። ስትራቴጂው “ስትራቴጂያዊ ማፈግፈግ ማድረግ፤ ከማፈግፈግ ወደ መከላከል፤ ከመከላከል ወደ ማጥቃት። በመጨረሻ ወደ መደምሰስ።” የሚል ነበር።

በዚህ መሰረት ደርግ ስምንት ተከታታይ ኦፕሬሽኖችን አካሄደ። የመጀመሪያዎቹ ሶስቱ ውጊያዎች ታጋዮቹ በማፈግፈግ ላይ ሳሉ ስለተፈጸሙ ጊዜና ቦታው ለኢትዮጵያ ሰራዊት የሚመች ነበር። ቀሪዎቹ ሻእቢያ ናቅፋ ላይ ምሽጉን ከያዘ በሁዋላ የተፈጸሙ ነበሩ።

ሻእቢያ የማፈግፈግ ስራውን ካጠናቀቀ በሁዋላ ለአስር አመታት ናቅፋ ላይ እለታዊ ሊባሉ የሚችሉ ውጊያዎች ተካሂደዋል። በ1988 ሻእቢያ ናደው እዝን እስኪደመሰስ ድረስም የሃይል የበላይነቱ ተለዋዋጭ ነበር። ደርግ የፕሮፓጋንዳ የበላይነት ስለነበረውና የሰውና የገንዘብ ምንጩ በገፍ ስለነበር ግን ለቀሪው አለም የማይደፈር ሃይል መስሎ ይታይ ነበር።

ደርግ ከሶቭየት እርዳታ ማግኘት ሲጀምር በቅድሚያ ከተሞችን የመቆጣጠር አቅሙን አጎለበተ። በምስራቅ ሶማሊያ፤ በመሃል አገር በኢህአፓ በመወጠሩ ከዚህ ችግር ለመላቀቅና ለማንሰራራት ጣረ። የሶማሊያ በፍጥነት ቀናው። በኩባና በየመን ተደጋግፎም ቢሆን ጦርነቱን በድል አጠናቀቀ። የምስራቁ ሲጠናቀቅ፣ “ሁለተኛው ነጻ አውጪ አብዮታዊ ሰራዊት” በሚል ስያሜ ፊቱንም ጓዙንም ወደ ኤርትራ አዞረ። ዘመናዊ የውጊያ መሳሪያ ታጥቆ፤ የሰለጠነና የተመገበ 120 ሺህ ወታደር ይዞ ኤርትራ ገባ።

የመጀመሪያው ውጊያ 1978 ሃምሌና ነሃሴ ላይ የተካሄደ ነበር። ከጎንደር የተነሳው ግብረሃይል በሁመራ በኩል ኡምሓጀር ገባ። ከዚያም ወደ ተሰነይ ገስግሶ ባረንቱ ደረሰ። ሽሬ ላይ ከቀዳሚ መምሪያው ማታ የተለየ፤ ዓዲዳእሮና ሻምብቆን ተሻግሮ ሌሊቱ ሲነጋ ባረንቱ ታየ። ከአድዋ የተነሳ ሌላ የሰራዊት ጎርፍ ራዛ እንደ ተባለው ወፍ ያገኘውን እየበላና እየተጸዳዳ መንደፈራ ገባ። ከገርሁ ስርናይ

የተነሳ ሌላ ሃይልም እንዲሁ በተመሳሳይ እየፈጸመ ጾረና እና ማይ አይኒን ተሻግሮ ደቀምሃረ ገባ። ሌላው በሩቁ ምጽዋን እየቃኘ ዶጋሊ ላይ ሰፈረ። በዚህ በመጀመሪያው የኢትዮጵያ ሰራዊት ጎርፍ ሻእቢያ ሙሉ በሙሉ ሳይጋፈጥ እየተከላከለ ማፈግፈጉን ቀጠለ።

ደርግ በዚህ መልኩ ራሱን ካጠናከረ በሁዋላ በሶቪያት ራሽያውያን አማካሪነት የውጊያ ስልት ነድፎ ሁለተኛውን ኦፐሬሽን ጀመረ። የሎጀስቲክ አቅሙና አፈጻጸሙ የተደራጀና የሰለጠነ ነበር። ጥቃቅን መረጃዎች ሳይቀሩ በፍጥነት ወደ "ብሄራዊ አብዮታዊ ዘመቻ መምሪያ" ይጎርፉ ጀመር። የመገናኛ አቅሙ የሰለጠነ ነበር።

ሻእቢያ በዚህ ጊዜ ሲመቸው ተመልሶ እያጠቃና ጉዳት እያደረሰ፤ ቀስ በቀስ ወደ ናቅፋ አግጣጫ ማፈግፈጉን ቀጠለ።

የኢትዮጵያ ሰራዊት ተሰነይ ባሬንቱና አቆርዳትን ከተቆጣጠረ በሁዋላ ሃይሉን አቀናጅቶ ወደ ከረን ገሰገሰ። አስመራ ላይ ተከቦ በከተማ ጥበቃ ላይ የነበረው ሰራዊትም እንዲሁ ጥቂት የከተማ ጥበቃ አስመራ ላይ ትቶ ወደ ከረን አመራ። ምጽዋ ላይ የነበረውም ፋታ በማግኘቱ ዶጋሊ ከሰፈረው ጋር ተቀናጅቶ ዳገታማውን መንገድ እየፈተሸና እየተቆጣጠረ ወደ አስመራ ገሰገሰ።

ሻእቢያ አስቀድሞ በነደፈው ስልቱ እየተዋጋ ማፈግፈጉን ቀጠለ። በዚህ በሁለተኛው የደርግ ኦፐሬሽን እንገርነ እና ዶጋሊ ላይ ጠንካራ ውጊያዎች ተካሂደዋል። በመቀጠል ደርግ ከረንን ያዘ። ከረንን በመያዙ ከፍተኛ ሞራል አገኘ። ፉከራው ጣራ ነካ። "የምስራች! - ከረን ተለቀቀች!" የሚል ዜማ በከፍተኛ ድምጽ ሬድዮና ቴሌቪዥኖችን አጥለቀለቀ። ሻእቢያ በከረን የማፈግፈግ ሂደት ሰራዊቱን ካስወጣ በሁዋላ ኢሳይያስ አፈወርቂ በመጨረሻ በሞተር ብስክሌት ከረንን ለቆ እንደወጣ ሙሉጌታ ሉሌ ከደርግ ውድቀት በሁዋላ ጦቢያ መጽሄት ላይ ጽፎ ነበር።

ሶስተኛው ኦፐሬሽን የካቲት 1979 ተካሄደ። ሻእቢያ ማእሚደ እና ገንፈሎም አካባቢ መሬት ይዞ ነበር። ከረንን በእጁ ያደረገው የኢትዮጵያ ሰራዊት ከረንን ከስጋት ነጻ ለማድረግ ከፍተኛ ሃይል አንቀሳቅሶ ገንፈሎምና ከረን አካበቢ ያለውን የሻእቢያ ሃይል አጠቃ። ሻእቢያ በህዳር ወር 1979 ገንፈሎምን ለቆ ወደ ቆጋይ አፈገፈገ። የኢትዮጵያ ሰራዊት ከባድ መሳሪያዎችን ሊጠቀም

ወደማይችልበት አግጣጫ በማፈግፈጉ የኢትዮጵያ ሰራዊት ሙሉ ሃይሉን እንዳይጠቀም አደረገው። ማእሚደ በሻእቢያ እጅ ነበር። ደርግ እዚህ ላይ ጥሩ ወታደራዊ ጥበብ መጠቀሙ ይታመንለታል። ማእሚደን ያጠቃል ተብሎ ሲጠበቅ፤ ወደ መርሳ ተከላይ አቀና። በዚህም የማእሚደና የቆጋይ ስትራቴጂካዊነት አከተመለት። ሻእቢያ በወርሃ ግንቦት 1979 ናቕፋ ግንባርን መስርቶ መከላከያ ምሽጉን ደህና አድርጎ ገነባ። ቆጋይ የነበረው የሻእቢያ ሰራዊት በእግረመንገድ አነስተኛ ውጊያዎችን እያደረገ ናቕፋ ደረሰ። የኢትዮጵያ አመራር በበኩሉ የናቕፋ መያዝ ከወታደራዊ ፋይዳው ይልቅ ፖለቲካዊ ጠቀሜታውን በመረዳት ሙሉ ሃይሉን ወደ ናቕፋ አደረገ።

በ1979 ቀንና ሌሊት ያለማቋረጥ ከፍተኛ ውጊያዎች ተካሄዱ። በተለይም የደንደን ተራራ ታሪካዊ ትዝታ ሊኖረው የበቃው በተደጋጋሚ የሞት ሽረት ትንቅንቅ ስለተካሄደበት ነበር። “ደንደን ተራራ ከተያዘ ናቕፋ ከተማ እንደተያዘ ይቆጠራል።” የሚል ግምገማ ስለተደረገ በሁለቱም ወገን ደንደን ተራራ ላይ ተረባረቡ። ሻእቢያ ደንደንን ላለመልቀቅ፤ ደርግ ደንደንን ይዞ ናቕፋን ለመቆጣጠር በተደረገ ትንቅንቅ፤ በቀን እስከ 15 ጊዜ ያህል የጨበጣ ውጊያዎች የተደረጉበት ሁኔታ ነበር። አስር አመታት ሙሉ ግን ደንደን ተራራ ወደ ኢትዮጵያ እጅ አልገባም። ተራራው ላይ ብዙ መስዋእትነት ተከፈለ። የደርግ “ሶስተኛው ኦፕሬሽን” ወይም በሌላ ስሙ “ራዛ ዘመቻ” ሳይሳካ ከሸፈ።

በዚያው አመት መጋቢት ወር ላይ “አራተኛው ኦፕሬሽን” ተጀመረ። ሶስተኛው ሲከሽፍ ሻእቢያ የመልሶ ማጥቃት ርምጃ ወስዶ የኢትዮጵያን ሰራዊት ሰላሳ ኪሎሜትር ያህል ወደሁዋላ እንዲያፈገፍግ አደረገው። ከባድ ኪሳራም አደረሰበት። የኢትዮጵያ ሰራዊት እንደገና ተደራጅቶ ለአራተኛ ጊዜ ማጥቃት ሰነዘረ። ሆኖም የመሳሪያ የበላይነቱ ብዙም አላገዘውም። መልከአ ምድሩ ሜዳ አልነበረውም። ውጊያዎች የሚካሄዱት ተራሮች ላይ ነበር። ደርግ በዚህ ውጊያ ናቕፋን ለመያዝ ቢያቅድም አልተሳካለትም። በብዛት በከባድ መሳሪያ ድብደባ ያካሂድ ነበር። አንድ ሳምንት ሙሉ ያለማቋረጥ ደብድቦ ሲያበቃ፤ ድንገተኛ ማጥቃት ሞከረ። ደርግ ምን ሊያደርግ እንደሚችል ሻእቢያ ቀድሞ በማወቁ የውስጥ ለውስጥ መተላለፊያ ምሽጉን ቆፍሮ ራሱን ሙሉ በሙሉ ተከላከሎ ቆየ።

ይህም የደርግን ድንገተኛ ማጥቃት ድንገተኛ እንዳይሆን አደረገው። የናቅፋን ምሽግ መጣስ የማይቻል መሆኑን ደርግ ቢረዳም ለአምስተኛ ጊዜ እንደገና ሰፊ ዝግጅት አድርጎ ውጊያ አካሄደ። እሱም ባለመሳካቱ ደርግ ለቀይኮከብ ዘመቻ ሰፊ ዝግጅት ማድረግ ጀመረ።

በኢትዮጵያና በኤርትራ የጦርነት ታሪክ ውስጥ የቀይ ኮከብ ዘመቻ እንደ ናደው እዝ መደምሰስና እንደ ፈንቅል ጦርነት ተደጋግሞ ይጠቀሳል። አልፎ አልፎ ፈጠራ ተደባልቆበት ሲነገርም ይሰማል።

የኢትዮጵያ መንግስት የኤርትራን ጉዳይ መቋጫ ሊያበጅለት በጥንቃቄ ሲያስብበት ቆይቶ ነበር። በአሉ ግርማ “የቀይ ኮከብ ጥሪ” በሚል ርእስ ካሳተመው ሶስተኛ መጽሃፉ ስሙን በመቅዳት “ቀይ ኮከብ” ሲል የሰየመውን ዘመቻ ለማካሄድ ለሰላሳ ወራት ያህል በሙሉ አቅሙ ዝግጅት አድርጎበት ነበር። ዋና የዘመቻ አላማው የነጻነት ተዋጊዎቹን ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ለመደምሰስ ነበር።

በርግጥ ተገቢ ዝግጅት አደርጎ ነበር። ከዝግጅቶቹ ዋናው ያለ ተዋጊ አይሮፕላኖችና ያለ ታንኮች እገዛ በራሱ አቅም መዋጋት የሚችል የተራራ ክፍለጦሮች ማሰልጠን ዋናው ነበር። 18ኛ፣ 19ኛ፣ 21ኛ እና 22ኛ እየተባሉ ይታወቁ የነበሩት እነዚህ ክፍለ ጦሮች በረሃና ውሃ ጥም መቋቋም እንዲችሉ ተደርገው የሰለጠኑ ነበሩ። ለተራራ ክፍለጦሮች ስልጠና የሶቪየት ህብረት ወታደራዊ ባለሙያዎች ሙሉ እገዛ አድርገዋል። ስሙ በተለየ ሁኔታ ገንኖ ይታወቅ የነበረው “18ኛ” የተባለው ክፍለ ጦር በሁለተኛው የአለም ጦርነት ናዚ ጀርመን ላይ ጀብዱ የሰራው የሶቪየት 18ኛ ክፍለ ጦር በሊዮኔድ ብሬዥኔቭ የፖለቲካ አመራር ስር ስለነበረ ትኩረቱን ለመሳብ በሚል ስሙ የተገነባ ክፍለ ጦር ነበር።

ሻእቢያ በተለይ ከዚሁ ከ18ኛ ክፍለ ጦር ጋር በተደጋጋሚ የእጅ በእጅ የሳንጃ ውጊያ አካሂዷል። በቅድሚያ 18ኛ ክፍለ ጦር ጠንካራ ውጊያ አድርጎ ግሎብ ነጥብ 1742ን በቁጥጥር ስር አዋሎ ነበር። የኤርትራ ታጋዮቹ እንደገና ተናንቀው ተራራዋን አስመለሱ። 18ኛ ክፍለ ጦር እልህና ጀግንነትን ቀላቅሎ በጠባብ ቦታ ላይ መስቀለኛ ተኩስ እየዘነበበት፤ በሞርታርና በፈንጂ እየተጨፋጨፈ ባደረገው ውጊያ ግማሽ ያህል ተዋጊ ሃይሉን አጣ። ትንቅንቁ ጊዜ ወሰደ። ተራራው ላይ የእጅ በእጅ ውጊያ ተያያዙ። በሳንጃ ብቻ

ሳይሆን፤ በቡጢና በቴስታ፣ በድንጋይ ጭምር በተደረገው ውጊያ የኤርትራ ተዋጊዎች እንደገና ተራራውን ተቆጣጠሩ። ከዚያ በሁዋላ ተራራው 18ኛ ዝናው ቀነሰ። ከሞት የተረፉት ወታደሮች ወደ ሁዋላ ተሳቡ። መኮንኖች ወደ ማሰልጠኛ ጣቢያዎች በአሰልጣኝነት ተላኩ።

በቀይ ኮከብ ዘመቻ ደርግ ተዘጋጅቶ ነበር።

አየር ሃይል በሙሉ ሃይሉ መስራት እንዲችል ከደብረዘይት ወደ አስመራ ተዛወረ። ዘመናዊ የውጊያ ሄሊኮፕተሮች ቀረቡ። "እቅድ መምሪያ" በሚል ስያሜ የሚጠራ የማዘዣ እዝ ቆመ። የነጻነት ተዋጊዎችን ለመደምሰስ አራት እዞች ተዋቀሩ። እነሱም "ውቃው"፣ "መክት" "ናደው" እና "መብረቅ" የሚል ስያሜ ተሰጣቸው። ውቃው - በሰሜናዊ ምስራቅ ሳህል፤ መብረቅ - በባርካ ግንባር፤ ናደው - ናቅፋ፤ መክት - ከበሳ እና ማእከል ላይ ቦታ ቦታቸውን ያዙ።

እነዚህ ሶስቱ እዞች የየራሳቸውን ተልእኮ ፈጽመው የደጅን ማእከል ከሆነው አዶብሃ ሊገናኙ ቀጠሮ ያዙ። በዚህ መሰረት ናደው እዝ ናቅፋን ተቆጣጥሮ ወደ አዶብሃ መሄድ አለበት። ዳሩ ጦርነቱ ሲጀመር ወዲያውኑ መብረቅ እዝ በመደምሰሱ የተበታተኑት ክፍለ ጦሮች ወደ ናቅፋ ተጨማሪ ሆነው እንዲገቡ ተደረገ።

ውቃው ደምቦቤትን ይዞ ጥቂት ተስፋ ያለው እንቅስቃሴ ያደረገ ቢሆንም፤ መቀጠል ሳይችል ክፉኛ ተመትቶ ወደ ሁዋላ አፈገፈገ። የሁለቱ እዞች ሙከራ ሲከሽፍ "አዶብሃ እንገናኝ" የተባባሉት ቀጠሮም አብሮ ፈረሰ። ስለዚህ ሃይላቸውን ሁሉ ናቅፋን መያዝ ላይ አደረጉ። የመጀመሪያው እቅድ መፍረሱ ሲታወቅ ተቀያሪ ተብሎ የቀረበው እቅድ ናቅፋ ከተማን ሙሉ በሙሉ መቆጣጠር የሚል ነበር። ሰባት ክፍለጦሮች ናቅፋ ላይ ደምአፋሳሽ ውጊያ አደረጉ። በጨበጣ - ሳንጃ ጭምር ትንቅንቅ ተደረገ።

የኢትዮጵያ ወታደሮች መንደአት 2059፤ አርው 1702 (ሳልፈር) በነጥብ 1702 ጥሰው ከፍተኛ መሬት የያዙበት አጋጣሚ ተፈጥሮ ነበር። ጉበታ 1725፣ 1755 የተባሉትን ጨምር ተቆጣጥረው ነበር። እዚህ ቦታ ላይ ሆነውም የኢትዮጵያ ወታደሮች የናቅፋ ከተማን በሩቅ ርቀት ለማየት ችለዋል። የ17ኛ ክፍለ ጦር አባላት የኢትዮጵያን ባንዴራ ተራራው ላይ ተክለው፣ "ናቅፋ ትታየናለች!!" ሲሉ መልእክት ላኩ። እውነት ነበር። ናቅፋን በሩቅ አይተዋታል።

በርግጥ ናቅፋ ላይ ጠንካራ ተከላካይ ሃይል አልነበረም። በከተማዋ የነበሩ ጥቂትታጋዮች ግን ናቅፋን በአይናቸው ለማየት የቻሉ ወታደሮችን ተጋፈጧቸው። አንድ ሰው ብዙ እየገደለ፤ ወደ ናቅፋ በመገስገስ ላይ የነበረውን ሰራዊት ገትሮ ያዘ። በእሩምታ የመረፍረፍ አይነት ነበር ውጊያው። ከተራራው ወደ ናቅፋ እየጎረፈ የነበረው ሃይል ከፊት ምን እየጠበቀው እንዳለ የሚገምትበት መረጃ አልነበረውም። እና ከብዙ ኪሳራ በሁዋላ ወደሁዋላ አፈገፈገ።

በናቅፋ ጦርነት 3ኛ ክፍለ ጦር የተመሰከረለት የጀግንነት ተግባር ፈጽሟል። የሻእቢያን ምሽግ ጥሶ ወደ ናቅፋ ከተማ መግባት ግን አልተሳካለትም። ደብረ ጥሉል እና ናሮ በተባሉ ቦታዎች በኩል ሁለቱም ወገኖች በሚያስደንቅ ጀግንነት ቢዋጉም የኢትዮጵያ ሰራዊት በኤርትራውያን ላይ ውጤት አላገኘም። የኢትዮጵያ አየር ወለዶች ለእግረኛ ተዋጊዎቻቸው ሞራል ለመስጠት ከግንባር በስተጀርባ ብዛት ያለው ፓራሹት ለቀው ነበር። ፓራሹቱን እየነተቱ የሚወርዱት ግን ሰዎች ሳይሆኑ አሸዋ የተሞሉ ከረጢቶች ነበሩ። ይህ መረጃ ወዲያውኑ በሬድዮ ለሻእቢያ ተዋጊዎች እንዲደርስ በመደረጉ ደርግ የጠበቀው ሳይከሰት ቀረ። ደርግ መርዛማ ጋዝ ሊጠቀም እንደሚችል የተሰማው መረጃ ተፈጻሚ አልሆነም። ሆኖም በምሽጎች ላይ በተወሰነ ቦታ አይን የሚያስጨፍን ጋዝ ቢጤ ለመጠቀም ሞክረው ነበር። እንደታቀደለት ግን ውጤታማ አልሆነም።

መኮነን ገብርኤል ደርግ “ቀይ ኮከብ” ሲል በሰየመው በዚህ ዘመቻ ደንቦቢት ላይ በጀቶች የቦምብ ድብደባ ጊዜ ደረቱ ላይ ተመቶ ክፉኛ ቆሰለ። እለቱም የካቲት 16 1982 ነበር።

(የደርግን ሰራዊት ከመመከት አንጻር ሀማሌኤና ህወሓት በተለያዩ ጊዜያት ትብብር ነበራቸው። በ6ኛው ወረራ የህወሓት ሶስት ብርጌድ የደርግን ሰራዊት መክቶ በጀግንነት የተዋጋ ሲሆን፤ ከፍተኛ መስዋእትነትም ከፍሏል። ናቕፋ ሄደው የቀይ ኮከብን ዘመቻ ከመከቱት መካከል አርከበ ዑቅባይና ሳሞራ የኑስ ሰማቸው ይነሳል። በአጻፋው በሸሬ ውጊያ የህግሓኤ አመራርና መድፈኞች ወሳኝ ሚና ነበራቸው። ሻእቢያ በደብረታቦር ውጊያ በእግረኛ ጭምር ሲዋጋ፤ አዲሳባን ለመያዝ በተደረገው ጉዞም ሻእቢያ በአመራርና በከባድ መሳሪያ መሳተፉን ሰለሙን በርሀ “ወፍሪ ሰግሪ ዶብ” በተባለ መጽሃፉ የራሱን ልምድ ተርኳል። ህወሃት ከ6ኛው ወረራ በሁዋላ ኤርትራ ላይ በተካሄደ ጦርነት የሚሳተፍበት አጋጣሚ አልነበረም። የትብብሩ ትኩረት አዲሳባን መያዝ ነበር።)

ምእራፍ 7

አፍንጫህ ረዘመ?

አማራጭ የለህም! ያንተው ነው ተሸከም

ሉላ እና ገብርኤል የአዲስ አበባ መኖሪያ ቤታቸውን ሸጠው ጠቅልለው አስመራ ገቡ። በርግጥ ዘመኑ ሰዎች ከኤርትራ የሚሸሹበት ዘመን ነበር። ኤርትራ የሞት አገር የተባለችበት፤ የጦርነት ሜዳ የሆነችበት ዘመን ነበር። "ኤርትራ የገባ አይመለስም" የሚባልበት ዘመን ነበር። በኤርትራ ምድር በስራ መመደብ እንደ ሞት ፍርድ የሚቆጠርበት ዘመን ነበር።

በምክክራቸው ወቅት ሉላ፣ "ልጆቻችን ድል ያደርጋሉ። የኤርትራ ነጻነት መምጣቱ የማይቀር ነው። መሄድ ይሻለናል" አለችው። ገብርኤል የባለቤቱን አሳብ ተቀበለ። በርግጥ የደህነቱ ሹም ኮሎኔል ተስፋዬ ወልደስላሴ ቢሮው ጠርቶ ካነጋገረው በሁዋላ አዲስ አበባ የመቆየት ፍላጎቱ ጨርሶ ሞቶ ነበር።

በርግጥ ኮሎኔል ተስፋዬ ፊታውራሪ ገብርኤልን ወደ ቢሮው ያስጠራው ለመተናኮል አልነበረም። ጥሪውም አክብሮት የታከለበት ነበር። ማለትም ማክሰኞ ማለዳ ወደ ገብርኤል መኖሪያ ቤት ሰልክ ተደወለ። በአጋጣሚ ስልኩን ገብርኤል ራሱ አነሳው።

አንዲት ሴት ከአገርውስጥ ጉዳይ መደወሏን ነግራ ስታበቃ ሚኒስትሩ ሊያነጋግራቸው እንደሚፈልግ ገልጻ፣ "ዛሬ ይችላሉ፤ ከምሳ ሰአት በፊት?" ሰትል ጠየቀች። ገብርኤል ቀጠሮውን ተቀበለ።

ኮሎኔሉ በተመሳሳይ አክብሮት ተቀበለው። ቡና ጋብዞ ስለጤንነቱና ስለ ቤተሰብ ሁኔታ ጠያየቀው። ከዚያም ቀጥ ብሎ ወደ ጉዳዩ ገባ፣

“ሻእቢያ ሰሞኑን በሬድዮ በሚያደርገው ቅስቀሳ የእርሶን ስም ጠቅሷል። ኤርትራውያን ለኢትዮጵያ ነጻነት ያበረከቱትን አስተዋጽኦ በራሳቸው ቅኝት ለፕሮፓጋንዳ ፍጆታ እያዋሉት ነበር። የርሶን ታሪክ ማወቄ የበለጠ ትኩረቴን ሳበው። ማለቴ ምንድነው? የኢንተሊጀንስ ባለሙያ በመሆኔ ሊሆን ይችላል። በኢትዮጵያ የኢንተሊጀንስ ታሪክ ውስጥ እርሶ የፈጸሙት ተግባር ልዩ ስፍራ ሊሰጠው የሚገባ ነው። ለማስተማርያነት የሚያገለግል ነው።”

ኮሎኔሉ ምን እንደፈለገ እስኪያውቅ ገብርኤል ተጠነቀቀ። ለማጣራት ያህል ግን ጥያቄ ጣል አደረገ፣

“ስሜን በምን መልኩ ጠቀሱት?”

ኮሎኔል ተስፋዬ ወረቀት አነሳና ሰጠው፣

ገብርኤል ወረቀቱን ተቀብሎ አነበበ፣

“ኤርትራውያን ኢትዮጵያን መደገፍ የጀመሩት ከኢጣልያ ወረራ በፊት ጀምሮ ነበር። ለአብነት ሶማሊያ ይኖር የነበረ ገብርኤል ኤድሞንዶ የተባለ ኤርትራዊ የኢጣሊያን የወረራ እቅድ የሚመለከት ሰነድና መረጃ መርከብ ላይ በሚሰሩ ኤርትራውያን በኩል ወደ ኤደን በመላክ መረጃው የኢትዮጵያ መንግስት ዘንድ እንዲደርስ ለማድረግ ሞክሮ ነበር። ሆኖም ኢጣሊያውያን ድርጊቱን ስለደረሱበት ፍርድ ቤት አቅርበው ሞት ፈረዱበት። ሁዋላ የሞት ፍርዱን ወደ እድሜ ልክ ለውጠው ወደ ናኹራ ደሴት ላኩት። ከገብርኤል ኤድሞንዶ ጋር የተባበሩት ረጅም የእስር አመታት ተፈርዶባቸው በእስር ማቀዋል።”

ገብርኤል ቀና ሲል ኮሎኔሉ በስሜት መናገር ጀመረ፣

“እንደ ርስዎ ያሉ ለኢትዮጵያዊነት ክብር ሲሉ ህይወታቸውን የከፈሉ ምርጥ ዜጎች ባሉበት አገር በኤርትራ ጉዳይ እንዲህ ያለ ችግር ውስጥ መግባታችን በጣም የሚያሳዝን ነው።”

ገብርኤል ተጠንቅቆ ምላሽ ሰጠ፣

“ናኹራ ማለታቸው ልክ አይደለም። የታሰርኩት ሞቅዲሾ ደናኔ ነበር።” ትንፋሹን ሰበሰበና ቀጠለ፣ “....በእኛ ዘመን መቸም

ባመንበት መንገድ ታግለናል። አሁን ወጣቶቹ እየወቀሱን ነው። ተሳስታችሁዋል ይሉናል። በዚያም ተባለ በዚህ ግን በአንድ አካባቢ አብረን መኖራችን የማይቀር ነው። እንደኔ ቢሆን ደም መፋሰሱን መቀነስና በሽምግልና መስማማት ይበጃል።"

ኮሎኔሉ በፈገግታ ተዋጠ፣

"የእኔም አሳብ ልክ እርስዎ እንደሚሉት ነው። መነጋገር አለብን። ጦርነቱ መቀጠል የለበትም። በንግግር ስምምነት ላይ መድረስ የተሻለው መንገድ ነው። በዚህም ከአማጽያኑ ጋር በምስጢር ንግግር መጀመር እንፈልጋለን። እርስዎ እነርሱ ወደሚገኙበት አገራት በመሄድ እንዲያገኟቸው ልናመቻች እንችላለን። ሻእቢያ እንዲህ ስምዎን ባክብሮት ማንሳቱ ጠቃሚ መንገድ ሊሆነን ይችላል። በተጨማሪ ታሪኮን እንዳየሁት ወጎኖችዎ ከቆላው ናቸው። የቆላው ጎሳዎች ኢትዮጵያዊነትን እንዳይጠራጠሩ ምን ማድረግ ይገባል የሚለውንም ማጥናት እንፈልጋለን።"

ገብርኤል ጥቂት አሰበና መልስ ሰጠ፣

"ማገዝ የምችለው ነገር ቢኖር ምን ገዶኝ? ግን ከፖለቲካ ጉዳዮች ርቄያለሁ። አሁን ያነሱት የቆላና የደጋ ነገር በጣልያንም በእንግሊዝም ሁዋላም በሃይለስላሴ ጊዜ ብዙ የተጠናና ያሟገተ አጀንዳ ነው። ሁሉም ያላስተዋሉት ነገር በኢጣልያ ቅኝ አገዛዝ ዘመን በጋራ ጭቆናው ስር አንድ ማንነት መዳበር መቻሉን ነው። ከሃይማኖቱም ሆነ ከአውራጃዊነት በላይ ይህ ማንነት ከፍ ብሏል። መታሕትም ሆነ ከባሳ በዚህ ማንነት ዙሪያ ሲገናኙ ይግባባሉ። ማንነቱ ለአንደኛው ጠቃሚ ለሌላው ጎጂ የነበረበት ዘመን አልነበረም። እና ከተቻለ መፍትሄ መፈለግ ያለበት በጥቅሉ ነው። እርስዎ እንዳሉት ግን በባለሙያ ማስጠናቱ ጠቃሚ ነው። እኔን በተመለከተ ከቆላ ዘመዶቼ ከተራራቅሁ ረጅም ጊዜ ሆኖኛል። ከኢጣልያ መባረር በሁዋላ ወደ ኤርትራ የሄድኩት ሁለት ጊዜ ብቻ ነው። ኮሎኔል! ብዙም የማግዝዎ አይመስለኝም። በፖለቲካ ምክንያት የደረሰብኝ የአካልና የመንፈስ ጉዳት ገለልተኛ እንድሆን አድርጎኛል። ይልቁን በኢጣልያ ዘመን በወጣትነት ዘመናችን በደመነፍስ የፈጸምነው የኢንተሊጀንስ ስራ ቢጻፍ ጥሩ አሳብ ነው።"

ንግግራቸው በዚሁ አበቃ።

ኮሎኔሉ የፈለገው ባይሳካለትም ፊታውራሪ ገብርኤልን መልሶ በአክብሮት ሸኘ። ቤቱ የሚያደርሰው መኪና ጭምር መድቦለት ነበር። ገብርኤል፣ "በእግሬ ይሻለኛል" ብሎ ተሰናበተ።

ገብርኤል ከደህንነቱ መስሪያ ቤት ባለስልጣን ጋር መነካካቱ ምኞት ከልክሎት ከሰነበተ በሁዋላ ወደ ኤርትራ የመመለሱን ጉዳይ ሉላ ስታነሳ አሳቡን ሳያመነታ ተቀበለው።

ኤርትራ ላይ ገብርኤል ምንም ስራ አልነበረውም።

ማለዳ ተነስቶ የቡሽ ባርኔጣውን ደፍቶ፤ ከዘራውን ይዞ በአስመራ ጎዳናዎች ይዘዋወራል። በአስመራ ጎዳናዎች ሲዘዋወር ቀድሞ የሚያውቃትን አስመራ እያሰበ ያዝናል። ያቺ እንቁ የመሰለች ከተማ ፈራርሳ፣ ህግና ስርአት ጠፍቶ ሲመለከት ልቡ ይነካል።

ሲዘዋወር በመንገድ ላይ የሚያውቀው ሰው አያገኝም። ተወልዶ ባደገባት ከተማ የከተሙት ሌሎች ሰዎች ናቸው። በየማእዘኑ የታጠቁ ሰዎች በንቃት ይጠብቃሉ። ሰው ቀርቶ እንስሳ እንኳ ይጠረጥራሉ። የሚያውቃቸውን ሰዎች የሚያገኘው ጸጸራት ብቅ ሲል ነበር። ኢጣልያውያንና ኤርትራውያን ጓደኞቹ እዚያ በጸጥታ አርፈዋል። ከአንዱ ወደ ሌላው እየሄደ ያወጋል። ቀደም ሲል የተጨዋወታቸውን ቀልዶች ጭምር እያነሳ ይስቃል።

* * *

ገብርኤል አንድ ማለዳ ወደ ሰምበል ሄዶ ወደ እያሱ ቤተሰብ የእርሻ ቦታ ጎራ አለ። ሃና በህይወት የለችም። ከሶስት ልጆቿ የመጀመሪያው ከእንግሊዝ ጋር በተደረገው ጦርነት ሱዳን ድንበር ላይ ተገድሏል። ሁለተኛው ልጇ ጀብሃ ነበር፤ ተሰውቷል። ሶስተኛዋ ልጇ ከሻእቢያ ጋር በረሃ ናት። በህይወት መኖር አለመኖሯ አይታወቅም። የሰምበል ንብረታቸውን ከቅርብ ዘመዶች አንዱ በውክልና ተረክቦ ስራውን በማካሄድ ላይ ነበር።

ገብርኤል ከእርሻ ቦታው ሲደርስ በትዝታ ነጎደ።

በልጅነታቸው ዘመን መዝናኛቸው እምባ አውሊዕ ተራራ ነበር። በጥቂት ደቂቃዎች ውስጥ ላፍ አድርገውት ጫፉ ላይ ይደርሱ እንደነበር አስታወሰ። በፈረስ እየጋለቡ ተራራውን ለመዞር አንድ

ሰአት ብቻ ይበቃቸው ነበር። አሁን እርሻው ተዳክሟል። በህድሞዎቹ ዙሪያ ብቻ ጥቂት የሰላጣ ችግኞች ይታያሉ። ዶሮዎች በራፉ ላይ ጥራጥሬ ይለቃቅማሉ። ላሞች የሉም። ወተት የለም። ደጃፉ ላይ የያዕቆብ መኪና አጽሟ ቆሟል።

የጎበጡ አንድ ሴት ብቅ ብለው አናገሩት፣

“አቦይ! ማንን ፈልገው ነው?”

“የሩቅ ዘመድ ነኝ። አያውቁኝም። ገብርኤል እባላለሁ።”

“ገብርኤል!? ስምዎን ሰምቻለሁ።” አሮጊቷ ተርበተበቱ። “.....ይግቡ እባክዎ! ወደ ቤት ይግቡና አረፍ ይበሉ። ስለ እርስዎ በደንብ አውቃለሁ። ጋዜጣ ላይ ስለርስዎ የተጻፈውን ልጆቼ አንብበውልኛል። ስለ አቦይ ኤድሞንዶም አውቃለሁ። ስለ ሁለተኛ ቀብራቸው ሰምቼ ነበር። ብቻ ያን ጊዜ አስመራ አልነበርኩም።”

አሮጊቷ ከንፈራቸውን ደጋግመው እየመጠጡ ጠየቁ፣

“ከየት መምጣትዎ ነው? ሮማ ነበሩ?”

“የለም! አዲስ አበባ ነበርኩ።”

ደጃፉ ላይ ቡና ተፈላና ብዙ ተጨዋወቱ። ገብርኤል በልጅነቱ ከእያሱ ጋር የቦረቀበትን ሁዳድ አሻግሮ እያየ ከአንድ ሰአት በላይ ቆየ። በወጋቸው መሃል ስለ እያሱን ጠየቀ፣

“አቦይ እያሱ ሮማ ናቸው። ደብዳቤ ከጻፉ ግን ብዙ ጊዜ ሆናቸው። በፊት በየሶስት ወሩ ይጽፉልን ነበር።” አሉት።

እያሱ ሱዳን ሳለ የወለደው ልጅ ወደ በረሃ መግባቱን ያውቅ ነበር። ስሙ ፈዳይ እንደሚባልም እያሱ ነግሮት እንደነበር ትዝ አለውና እያመነታ ጠየቀ፣

“ስለ ልጁ ስለ ፈዳይ ወሬ አላችሁ?”

“ምንም ወሬ የለንም።”

“እያሱ ደብዳቤ ከጻፈ ምን ያህል ጊዜ ሆነው?”

“ሁለት አመት ያልፋል።”

ሶስተኛው ቡና ተጠጥቶ ከተባረከ በሁዋላ ገብርኤል ቆቡንና

ከዘራውን አነሳ። አሮጊቷ እስከ መንገዱ ሲሸኙት እንባ ይፈታተናቸው ነበር። እንባ ግን አልታየም። ጦርነት እና የግፍ አገዛዝ የተፈራረቀበት ህዝብ እንባውን ከጨረሰ ብዙ ዘመናት አልፈውት ነበር።

አንድ ቅዳሜ ከምሳ በሁዋላ እንደተለመደው ቡና በመጠጣት ላይ ሳሉ ጎረቤታቸው አንዲት ወይኒ የተባለች እንግዳ ሴት አስከትላ ብቅ አለች። ወይኒ ከወከድባ የመጣች ነበረች። ጥር 1975 በወከድባ የተፈጸመውን እልቂት አወጋቻቸው። በርግጥ በወግ መካከል እንባ እየደፈቃት፣ እየተንቀጠቀጠች መናገር ተቸግራ ነበር።

ወይኒ ለገብርኤል እንዲህ ስትል ገለጸች፣

“ሃንስ ከነልጁ፤ አቦይ ገብረማርያም ከልጁ ጋር፤ ተስፋይ ዐቅባ ጊዮርጊስ ከተባለ ወንድሙ ጋር ተገድለው ወድቀው አየሁ።”

ከእልቂቱ በሁዋላ ሸሽታ አስመራ አክስቷ ቤት ተቀምጣ ነበር። አሰቃቂውን ትዝታ መርሳት አልቻለችም። ቡና እየጠጡ ሳለ ሴትየዋ የምትናገረውን ገብርኤል በጥሞና ሰምቶ ሲያበቃ፤ ቡናውን ሳይጨርስ ተነስቶ ከቤት ወጣ።

ነገሩ የሆነው እንዲህ ነበር።

ጥር 4 1975 ቅዳሜ ማለዳ የኢትዮጵያ ወታደሮች በመኪናና በታንክ ወከድባ ደረሱ። ገና ወደ መንደሪቷ ዘልቀው ሳይገቡ ከፊት ያገኙት ሰው ላይ ተኩስ ከፈቱ። በየቤቱ እየገቡ በጥይትና በሳንጃ ያገኙትን ገደሉ። በጥቂት ደቂቃዎች ውስጥ ሬሳዎች በየደጃፉ ላይ ተሰጡ። እድል ያገኙ ከጥይትና ከሳንጃ አምልጠው እየሾለኩ ቤተክርስትያን ውስጥ ተከማቹ።

ወታደሮቹ ቤቱን ቆልፎ ቁጭ ያለውን በር እየበረገዱ በየጓዳው ገቡበት። በየህድሞው ደጃፍ ሁለት ወይንም ሶስት ሬሳ ተዘረጋ። ከዚያም ማክ በተባለው መኪና ላይ ጠቃሚ የሚሉትን ንብረት ጫኑ። የቀረውን እሳት ለቀቁበት። እስከ እኩለ ቀን ይህን ከፈጸሙ በሁዋላ ምሳ ሰአት ላይ ወደ መስክ ሄዱና ከተሰማሩት ከብቶች እየመረጡ በጥይት እየጣሉ ማረድ ጀመሩ።

እለቱ ቅዳሜ እንደመሆኑ በዚያች ቀን ጋብቻቸውን የሚፈጽሙ ሙሽሮች ነበሩ። ወደ ድግሱ ቦታ ገብተው የተጋገረውን

አንጀራ ወሰዱ። ጠላውን ጫኑና በሰርገኞች አሸክመው ወደ ሰፈራቸው ወሰዱት። ሰርገኞቹ ስጋና እንጀራውን ከወታደሮቹ ካምፕ ካደረሱ በሁዋላ ጉድጓድ አንዲቆፍሩ ታዘዙ። ቆፍረው ሲያበቁ ረሽነው ቀበሯቸው። የእለቱ እልቂት ግን በዚህ አላበቃም።

ሁዋላ Massacre At Wekidiba በሚል ርእስ ሃብቱ ገብረአብ ባሳተመው መጽሃፍ በዝርዝር እንዳወጋው፣ ከሰአት በሁዋላ ሶስት ሰአት ላይ ወታደሮቹ ቤተክርስትያን ውስጥ ተሸሽገው ወደነበሩ ነዋሪዎች ሄዱ። እግረመንገዳቸውን ቤት ያቃጥሉ፤ ሰው ሲያገኙ ይገድሉ ነበር። ቤተክርስትያን ሲደርሱ ወደ ውስጥ ዘልቀው በመግባትም ልጆችና ሴቶችን መደብደብ ጀመሩ። በዚህ ጊዜ ቄስ ገብረህይወት "ታቦት ይገፍ እለምናለሁ" በሚል ታቦት ተሸክመው ብቅ ሲሉ ግንባራቸው ላይ ተመተው ወደቁ።

በመቀጠል ወታደሮቹ የምእራቡን የቤተክርስትያን በር ሰበሩት። ከዚያም እንዲወጡ አዘው ከአርባ አመት በታች የሆኑትን ለየብቻ ለዩ። ከዚያም አንድ ወታደር ጥይት አዘነበባቸው። ብዙዎች ተደራርበው ወደቁ። በዚህ ጊዜ ሽማግሌዎቹ በደም ተጨማልቃ የወደቀችውን ታቦት አንስተው፣ "እግዚኦ! እግዚኦ!" እያሉ የቤተክርስትያኗን ግቢ ይዞሩ ጀመር። ሁለት ጊዜ እንደዞሩ እየተኮሱ ሽማግሌዎችን የኢላማ መለማመጃ ያደርጓቸው ጀመር። ቤተክርስትያኗ በውስጥና በደጅ በሬሳ ተሞላች። እንዲህ ሲፈጽሙ ስለመሸና ገድለው ስለጠገቡ ተመልሰው ወደ ካምፓቸው ሄዱ።

* * *

በዚያን ቀን ገብርኤል ከቤት እንደወጣ በኤርትራ ሰላማዊ ህዝብ ላይ የተፈጸሙ ተከታታይ እልቂቶችን እያሰላሰለ በእግር አዘገመ። የኤርትራ የወደፊት እድል እያሳሰበው ነበር።

ኑረነቢ ፋናን ለቀቀ። እሱ ደግሞ ኤርትራን ለቆ ነበር። ልጆቹ አንድ ባንድ አፍሪቃን መልቀቅ ጀምረዋል። ኑረነቢ ለሓልሓል ቦጎስ፤ ለትውልድ አገሩ ለፋና የነበረውን ፍቅርና አክብሮት በማሰብ ተከዘ። "እልቂት ሲበዛ ህዝቡ ሞራሉ ወድቆ ይሰበር ይሆን? አማጽያን እስከ ድል መቋቋም ይችሉ ይሆን?" የሚሉ ጥያቄዎች መልሰው መላልሰው ረበሹት። "አንድ ትውልድ፣ በአባቶቹ መሬት፣

በአያቶቹ መሬት ላይ መቆየት ካልቻለ፤ ትውልድ ቀጠለ ሊባል አይችልም።" ሲል ከራሱ ጋር አወጋ።

እንደወትሮው ከጸጸራት የመቃብር ቦታ ደርሶ አረፍ ካለ በሁዋላ ወረቀትና ብእር አወጣ። አንዳንድ አሳቦችንም አሰፈረ። ከዚያም የከዘራውን መያዣ በመፍታት ወረቀቱን በመካከሉ ባለው ቀዳዳ ውስጥ ጠቅልሎ አስቀመጠው። በዚያን ቀን እንዲህ አሰሰፈረ፣

- ያሳለፍነውን ዘመን "የጨለማ ዘመን" ብዬ ለመጥራት የሞከርኩበት ጊዜ ነበር። ርግጥ ነው፤ ድቅድቅ ጨለማ ውስጥ ነን። በሩቅ ርቀት ግን ብርሃን ይታየናል። ሆኖም ህልም ሳይሳካ ሊቀር የሚችልበት እድል አለ። -

* * *

ፊታውራሪ ገብርኤል እንደ ጎርጎሳውያን አቆጣጥር ነሓሴ 27 1983 አስመራ አርፎ፤ የቀብር ስነስርአቱ ጸጸራት ተፈጸመ። የገብርኤል እረፍት እንደተሰማ በአስመራ ከተማ በአማርኛ ይታተም የነበረው የኢትዮጵያ መንግስት ጋዜጣ እንዲህ ሲል ዘገበ፣

"በባዕድ ወረራ ዘመን ለእናት አገራቸው ኢትዮጵያ ከፍ ያለ ሙያ የፈጸሙት ፊታውራሪ ገብርኤል ኤድሞንዶ አረፉ። የፊታውራሪ ገብርኤል የቀብር ስነስርአት ነሓሴ 20 ቀን 1975 በጸጸራት መካነ መቃብር በተፈጸመበት ወቅት አጭር የህይወት ታሪካቸው ተነቧል።"

ጋዜጣው "ከፍ ያለ ሙያ" ያለውን የስለላ ታሪክም ዘረዘረ፣

ኤርትራ ላይ በነበረው የጦርነት ውጥረት ምክንያት በቀብር ስነስርአቱ ላይ ልጆቹ ሁሉም እንዲገኙ አልተፈቀደላቸውም። አዲስ አበባ የሚገኙ ልጆቹ በቀብር ስነስርአቱ ላይ የሚገኝ አንድ ወኪል ብቻ እንዲመርጡ ስለተነገራቸው በኢትዮጵያ አየር መንገድ ሆስተስ የነበረችው አይዳ ገብርኤል ተወከላ ለቀብር ወደ አስመራ ሄደች።

ምእራፍ 8

የጦርነት ቋንቋ

የዓዲ ሸሩም ሲቃ - የስጋለት ላንቃ

የፊታውራሪ ገብርኤል ሙት አመት ከተከበረ በሁዋላ አንድ ቀን ሉላ ባለቤቷ ይጽፉቸው የነበሩ ወረቀቶችን በመልከ መልካቸው እያያዘች በስርአት አስቀመጠቻቸው። በኢይነታቸው እየለየች፣ በመርፌና በክር አያይዛ እየሰፋች በሳንዱቅ ውስጥ አኖረቻቸው። የገብርኤልን የመጨረሻ ዘመን ጽሁፎች ሊያነብላት የሚችል ግን በአጠገቧ ማንም አልነበረም። ዋና ጭንቀቷ ወረቀቶቹ ጠላት እጅ እንዳይገቡ መጠንቀቅ ስለነበር ይዘቱ ብዙም አላስጨነቃትም። እርግጥ ሁዋላ እንደተረዳችው ገብርኤል ወደሁዋላ ተመልሶ አንዳንድ ነገሮችን እያስታወሰ ያሰፍር ነበር።

"Il file di Nur-Nebi" በሚል ርእስ ማስታወሻዎቹን በብእር እየጻፈ ለማስባሰብ ሞክሮ ነበር። ከደርዘን ቅጠሎች በላይ አልቀጠለም። ህመሙ ሲበረታበት ተወው። አንዳንድ ትዝታዎቹን ግን ያሰፍር ነበር። ስለ ኑረነቢ፤ ስለ አባቱና አጎቱ፤ ስለ ኤርትራ እና ስለኢትዮጵያ በማስታወሻው ለማስፈር ሞክሯል፤ አብዛኞቹ ጽሁፎቹ በኢጣልያንኛ ነበሩ፣

- እነሆ! ውሎዬ CAIOA (ኮንቺሴኔ አልቤርጎ ኢታሊያኖ ኦሬንታል አፍሪቃ) ሆቴል ሆኗል። የአስመራ ሰዎች CIAO (ቻዎ) ሆቴል ይሉታል። ከምሳ ሰአት በሁዋላ እዚህ የሚመጡ ያገኙኛል። ከአመታት በፊት ከአቡነ አብርሃ ጋር እዚህ ሆቴል ረጅም የእራት ላይ ቆይታ ነበረን። መቸም ሃይለኛ ሰው ነበሩ። ወለም ዘለም

አያውቁም። የካቶሊክ ጳጳስ ሲሆኑ፤ እሳቸው ይናገራሉ ከተባለ ሙስሊሙ ሳይቀር ይሰበሰብ ነበር።

- አንድ ጊዜ አስታውሳለሁ፤ አስመራ ዩኒቨርሲቲ ወጣቶችን በተመለከተ ሴሚናር አዘጋጅቶ ነበር። አበምኔቶች፣ ካህናትና ሊቃውንትን ሰብስበው ስለ ኤርትራ ክርስትያን ወጣቶች መከሩ። ጋብዘውኝ ነበር፤ ስላልቻልኩ አልሄድኩም። እንደሰማሁት የደብረ ቢዘን ገዳም አበምኔት ከተራራው ወርደው ሲመጡ ፖለቲካው አልገባቸውም። የተነገራቸው 'እግዚአብሄር የለም የሚሉ ወጣቶች ተነስተዋል።' የሚል ነበር። ቄሶቹ 'ሶሻሊዝም' እና 'ኮሚኒዝም' ለሚባሉት ቃላት 'በሽተኛው ነፋስ' የሚል ቅጽል ስም ሰጡ። የኤርትራን የነጻነት ትግል በመስጋት የተደረገ ነበር።

- አቡነ አብርሃ ገብቷቸው ነበር። ሲናገሩ፣ 'ጌታችን እየሱስ ክርስቶስ ወልደአብ ወልደማርያም ሆኖ ክልኤ ልደት እንዳለው፤ እንዲሁም ክርስትያን ሁሉ ወልደአብም በስጋው ከመሆኑም በላይ ወልደ ክርስቶስ በጸጋ ነው" አሉ። በወቅቱ ወጣቶች የወልደአብ ወልደማርያም አስተሳሰብ ደጋፊ ነበሩ። ሊቃውንቱ ተሰብስበው የወልደአብ ወልደማርያምን ተከታዮች እንዲያወግዙ ሲጠበቅ አቡነ አብርሃ በቅኔ ወልደአብን አሞገሱ።

- ፕሮፌሰር ፋብዮ መተሊ ከፓዶቫ ዩኒቨርሲቲ የመጣ ሰው ነው። እሱ ያንጊዜ የወጣቱ አካሄድም አልገባውም። ትሩካ ደግሞ የነጻነት ትግሉ ጅማሬ አልተስማማውም። ሁለቱም 'የኤርትራ ወጣቶች በኮሚኒስቶች አሳብ ተስበዋል' ብለው አምነው ነበር። ክርስትያኑ ወደ ትግሉ እንዳይገባ ለማቆም ነበር አሳባቸው። ሶስተኛ ስብሰባቸውን ሳያካሂዱ ጀብሃና ሻእቢያ አስመራን ከበቧት። በዚያን ጊዜ ወጣቶች ከአሜሪካና ከአውሮፓ ጭምር ወደ በረሃ ይገቡ ነበር።

- አንድ አስተሳሰብ ሲያረጅ የሚተካውን ራሱ ይወልደዋል። ሙሴ በእየሱስ መተካቱ ግድ ነበር። የኤርትራ ወጣቶች፣ 'ኮትህን ሲነጥቅህ ሱሪህን ጨምርለት' የሚለውን ምክር ለመስማት ጆሮ አልነበራቸውም። የቱርክ - የኢጣልያ - የእንግሊዝ እና የኢትዮጵያን አገዛዝ በታሪክና በአካል አይተናል። እና በሌሎች መገዛት የማይሆን ነበር። አሮጌውን አስተሳሰብ የሚተካ የግድ መወለድ ነበረበት።

- በእራት ቆይታችን ላይ አቡነ አብርሃ፣ አዱሊስ

በአርኪዮሎጂስቶች እንዳይቆፈር አጤ ሃይለስላሴ ይከላከሉ እንደነበር አውቅ እንደሆን ጠየቁኝ። እንደማላውቅ ነገርኳቸው። ምክንያቱን ስጠይቃቸው እንዲህ አሉኝ፣

“ባለሙያዎች ከአንዴም ሁለት ጊዜ መጥተው አጉላልተው መልሰዋቸዋል። የተለያየ ምክንያት በመስጠት ተስፋ አስቆርጠው አባረሯቸው። ምናልባት ከቁፋሮ የሚገኘው መረጃ ‘አክሱም የአዱሊስ እናት’ የሚለውን ነባር አፈታሪክ እንዳያፈርስባቸው ሊሆን ይችላል። ሌላ ምክንያት ሊኖር አይችልም። ጋላቨቲ እና ካፑቺኒ ለሸማግሌው ጽሁፍ እየላኩ ይመክሩ ነበር።” አሉኝ።

- ዘርአይ ደረስ በጸጋዬ የድራማ መጽሃፍ ረቂቅ ውስጥ፣ “ይቅርታ አድርጊልኝ ኢትዮጵያ - ይቅርታ አድርጊልኝ አገሬ - ኮረም የእትብት ሰፈሬ - የህጻንነት መንበሬ” ሲል ጽፎ አነበብኩ። ይህ ስህተት ነው። ስህተቱን ለጸጋዬ እንዲነግረው ለንርዓዮ ሰጥቼው ነበር። ዘርአይ ወደ ሮማ ከመሄዱ በፊት የኮሎኒው መንግስት የፖስታ ቤት ሰራተኛ ሆኖ ወደ ትግራይ - ኮረም ለአንድ አመት ሄዶ ነበር። በተቀረ ዘርአይ ደረስ ሃዘጋ ተወልዶ ማደጉን ነው የማውቀው። የተማረውም አስመራ በኢጣልያ የመንግስት ትምህርት ቤት ነው። ዘርአይ በወቅቱ እንደማንኛችንም ወጣቶች ጸረ አውሮፓውያን ቅኝ ገዢዎች አቋም ሊኖረው ይችላል። ጸጋዬ በብእሩ የገለጸው አይነት ስሜት ሊኖረው የሚችል ግን አይመስለኝም።

- ጸጋዬ በአጤ ቴዎድሮስ ምናብ ስለ ኢትዮጵያውያን ባህል የገለጸው በጣም መስጦኛል። ትእዝብቱ እውነት ነው። የመሰጡኝ አባባሎች እንዲህ የሚሉት ነበሩ፣

“ኢትዮጵያ እኛስ ልጆቿሽ ምንድነን? አመንኩሽ ማለት የማንችል፤ ፍቅራችን የሚያስነውረን፤ እዳችን የሚያስፎክረን፣ ግፋችን የሚያስከብረን፤ ቅንነት የሚያሳፍረን፤ ቂማችን የሚያስደስተን፣ ኸረ ምንድነን? አሜኬላ እሚያብብን፣ ፍግ የሚለመለምብን፤ ከአረም ጋር ያፈራን ጊንጦች፣ ከእንክርዳድ ያልተለየ ዘር፤ ግርዱ ከምርቱ ተማትቶ ከቶ ያልተበራየን መከር፤ ምንድነን? ምንድነን ኮ?”

- ጸጋዬ አገሩን በትክክል ታዝቧል። በተለይም የኢጣልያ

ወረራ የብዙዎችን አይን መክፈት ችሏል። በመሬት ይዞታ ዳይሬክተር ሆኜ እየሰራሁ ሳለ “ለአርበኛ ልጆች” በሚል ስም ምርጥ መሬት ማደል ዋና ስራችን ነበር። አንድ ጊዜ በመሰብሰቢያ ክፍል ገብተን ቫይስ ምኒስትሩ ንጉሴ ፍትህ አወቅ እስኪመጡ እየጠበቅን ነበር። እኔና ሁለት የህግ ባለሙያ ወጣቶች ነበርን። አንደኛው ዘገየ አስፋው ይባላል። ሌላው ጠአመ በየነ የሚባል ኤርትራዊ ነበር። የለውጥ መንፈስ የነበራቸው ሃይለኛ ወጣቶች ነበሩ። ቫይስ ምኒስትሩ እስኪመጡ ድረስ በመጨዋወት ላይ ነበርን። እና “እነዚህ ሁሉ መሬት የምናድላቸው በርግጥ የአርበኛ ልጆች ናቸው?” ሲሉ ጠየቁኝ። ሳላስበው አሳቁኝ። ሳላስበው አናገሩኝ። መሬት በመስጠት ላይ ያለነው ለባንዳ ልጆች መሆኑን ነገርኳቸው። በርግጥም ከኢጣልያ ጋር በምስጢር ይሰሩ የነበሩና አርበኛ የነበሩትን ለያይቼ አውቃቸው ነበር። ንጉሱን እያስፈረሙ መሬት ለመውሰድ ከሚመጡት መካከል አንድ እንኳ የአርበኛ ልጅ ባለማየቴ በጣም ሲደንቀኝ ኖሯል። ጸጋዬ ገብረመድህን ኢትዮጵያን “አመንኩሽ ማለት የማንችል?” ያላት ይህን ግርዱና ምርቱ የተማታበትን መከር ተረድቶ ይሆን? እነዚህ ከኔ ጋር ይሰሩ የነበሩ ሁለት ወጣቶች ሁዋላ የመሬት ላራሹን አዋጅ በማርቀቅና በስራ ላይ በማዋል ግንባር ቀደም ተሳታፊ መሆናቸውን ስሰማ አልተገረምኩም።

- የጸጋዬ ብእር የሰለጠነ ነው። በርግጥ ጸጋዬ ጎበዝ ጸሃፊ ነው። ምናቡ ሰፊ ነው። ብርቱ ሂስ ያቀርባል። ምንጊዜም አደንቀዋለሁ። ወጣት ነውና ገና ብዙ ሊሰራ ይችላል። አሸዋን ስንዴ ብሎ ማሳመን የሚችል ብእረኛ ነው። ንርአዮ ኢሳይያስ የጸጋዬ ወዳጁ ነበር። ንርአዮ ከትግራይና ከኤርትራ ቤተሰብ የተወለደ ሲሆን፤ የተማረ እና በተፈጥሮውም በሳል ሰው ነው። ምንም ይሁን ምን ያመነበትን በቀጥታ የመናገር ችሎታ ነበረው። ጸጋዬን የተዋወቅሁት በንርአዮ በኩል ነበር። አንድ ጊዜ ጸጋዬ ባለበት ተገናኝተን ረጅም የራት ላይ ቆይታ አድርገናል።

- ሁለት ጊዜ አሜሪካ ሄጀ ልጆቼን አየሁ። ደህና ናቸው። ስራ መስራትና መማር፣ መተኛትና መነሳት ደህንነት ከሆነ ደህና ናቸው። ከዚህ በሁዋላ ወደ አሜሪካ ጉዞ የማደርግ አይመስለኝም። ታምሜያለሁ። በጣም ታምሜያለሁ። የአሜሪካ ሃኪሞች እንደነገሩኝ

ህመሜ የመርሳት በሽታ ነው። ሰው እረሳለሁ። ሉላን ግን ረስቻት አላውቅም። በሽታው እንደማይድን ነግረውኛል። እንግዲህ ወደ አምላክ የመሄጃዬ ጊዜ ደረሰ ማለት ነው። የኤርትራን ነጻነት ከማየቴ በፊት አምላክ ይወስደኝ ይሆናል። -

- ክፉ ድርጊቶች ሁሉ ተረስተው አዲሱ ትውልድ በንጹህ አእምሮ ያድግ ዘንድ እመኛለሁ። ክፉ ድርጊቶችን መርሳት ካልተቻለ ደግሞ ቂምና በቀል በማይቀጥልበት መንገድ ቢታወስ እመኛለሁ። “ክፉ ድርጊቶችን መርሳት” የሚለው ነገር ፈታኝ እንደሆነ አውቃለሁ። ለአብነት ለማርሻል ግራዝያኒ አሳልፎ የሰጠኝ ባለስልጣን ብዙ ልጆች አሉት። አንድ ሁለቱን አውቃቸዋለሁ። በአባታቸው በጣም ይኮራሉ። ይመካሉ። የዚህን ሰው ስም ለታሪክ አሳልፎ ስለመስጠት ደግሜ ደጋግሜ አስቤ ነበር። ልጆቹን፣ የልጅ ልጆቹን ከማሳቀቅ በቀር ምን ይጠቅማል?

- መኮነን ልጄ በህይወት ይኖር ይሆን?

* * *

ሰኔ 1990 ከአሜሪካ የመጣ አንድ እንግዳ ከመሸ በሁዋላ ካርቱም ደርሶ፤ ከአንድ ግሪካዊ ሆቴል አረፈ። ይህ ሰው ሃብተአብ ገብርኤል ሲሆን፤ በ1976 ወደ ትግል ሜዳ የገባ ወንድሙን ለመፈለግ መምጣቱ ነበር። ማለዳ ላይ ቁርስ በመመገብ ላይ ሳለ የሻእቢያ ታጋዮች ሌሎች እንግዶችን ፈልገው ወደ ሆቴሉ መጥተው አገኛቸው። ጊዜ ሳያጠፉ አጋጣሚውን ተጠቀመበት። ኤርትራዊ መሆኑን ተናግሮ ሲያበቃ፣ በትግል ላይ ያለ ታላቅ ወንድሙን ለማየት መምጣቱን ገለጸላቸው። ታጋዮቹ ከሆቴል አስወጥተው ወደ ERA (Eritrean Relief Association) ቢሮ ወሰዱት።

ማምሻው ላይ በሱዳን የተወለዱ ኤርትራውያን ወደሚማሩበት ቦታ ይዘውት ሄዱ። እዚያም የሚያውቃቸውን ሰዎች አገኘ። ከእነዚህም አንዱ ሻለቃ ከሰተብርሃን ገብረህይወት ነበር። ይህ ከፍተኛ መኮንን በአጤ ሃይለስላሴ ስርአት በፈረንሳይ የወታደራዊ ስለላ ስልጠና ከወሰደ በሁዋላ ትግሉን የተቀላቀለ መኮንን ነበር።

ሻለቃ ከሰተብርሃን የመንገዱን ነገር ጨረሰለት። እና ወደ

ሰሜን ኤርትራ ሸኘው። ሃብተአብ ለኤርትራ እንግዳ አልነበረም። ከአመታት በፊት ወደ አሜሪካ የሄደው በኑረነቢ አገር በሓልሓል በኩል ሲሆን፤ የፋና ዘመዶቹ አሾልከው ነበር ሱዳን ያደረሱት።

በታጋዮቹ መኪና ተጭኖ ሌሊቱን ተጓዘ። ቃሮራ የደረሱት ከመሸ በሁዋላ ነበር። ኦሮታ አድሮ በነጋታው ከቁርስ በሁዋላ ወደ ናቅፋ ለጉዞ ተነሳ። ወደ ናቕፋ የሚሄዱ አውቶብሶች ነበሩ። ሃብተአብን ያስተናገዱት ሰዎች ወደ አውቶብስ ማቆምያው ወስደውት አውቶብስ በመጠበቅ ላይ ሳለ አዜብ ፍስሃዬን አገኛት። አዜብ የሻለቃ ከሰተብርሃን ባለቤት ነበረች። በሞቀ ሁኔታ ተሳሳሙ።

እየተጨዋወቱ ሳለ መኮነንን ለማየት ከአሜሪካ መምጣቱን ነገራት። በዚያች ቅጽበት መርዶ እንዳይሰማ በመስጋት ሊፈነዳ ደረሰ። አይን አይኗን በፍርሃት ተመለከታት።

“ጊንዳዕ ግንባር መኖሩን ሰምቻለሁ።” አለችው።

በዚህ በጎ ዜና ሃብተአብ ከፍተኛ ደስታ ተሰማው። ምጽዋ በታጋዮች በመያዟ ዋናው ግንባር ጊንዳዕ ሆኖ ነበር። መኮነን ከአዜብ ገጽታ ላይ አጠራጣሪ ስሜት ባለማየቱ ተረጋጋ። ወንድሞቹና እህቶቹ፣ በተለይም እናቱ ስለ መኮነን ወሬ ለመስማት እየጠበቁ ስለነበር አስደሳች ዜና ይዞላቸው እንደሚሄድ በማሰብ ራሱን እንደ እድለኛ ቆጠረ። ከአዜብ ጋር እስከ ናቅፋ አብረው ተጓዙ።

ናቕፋን አቋርጠው ካለፉ በሁዋላ ግን መለያየታቸው ግድ ነበር። አዜብ ሃብተአብን ወደ ሰራተኞች ማህበር ጽህፈት ቤት ካደረሰችው በሁዋላ ወደ ስራዋ ሄደች። “የሰራተኛ ማህበር” የሚለው አነጋገር ሃብተአብን በጣም አስገረመው። በትግሉ ሜዳ ከውጊያና ከተዋጊዎች በቀር ሌላ እንቅስቃሴ ያለ አልመሰለውም ነበር።

ሻእቢያ በትግል ላይ ሳለ አስራ አንድ ክፍሎች ነበሩት። ትምህርትና ባህል፣ ዜናና ፕሮፓጋንዳ፣ አስተዳደር፣ የፖለቲካ ጉዳይ፣ አርሚና የውጭ ግንኙነት ዋናዋናዎቹ ነበሩ። በወታደራዊ ኮሚቴው ስር ስለላ፣ ወታደራዊ ስልጠና የመሳሰሉ ሲካተቱ እንደ ማህበራዊ ጉዳይ፣ ኢኮኖሚና ህክምና ራሳቸውን የቻሉ ተነጣይ ክፍሎች ነበሩ።

በትግሉ ሜዳ የኢኮኖሚ ክፍሉ ጠንካራ ነበር። አህጉር አቋራጭ የሚጓዙ የንግድ መርከቦች እንደነበሯቸው የሚነገር ሲሆን፤

በዚያው በኤርትራ ምድር ላይ ለህክምና አገልግሎት የሚውሉ ክኒኖች፣ ኢንፊውዥን፣ እንዲሁም ሌሎች የሚቀቡና ፈሳሽ መድሃኒቶች ያመርቱ ነበር። እስከ 1984 ብቻ እንኳ ከመቶ በላይ የአንደኛ ደረጃና የመለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ነበሯቸው። ከደርግ የጅምላ ጭፍጨፋ ተርፈው የሚመጡ ልጆች እና እናቶችን እየተቀበሉ ያቋቁማሉ። በመጠለያዎች አስቀምጦ መመገብ ብቻ ሳይሆን ከመሃይምነት እንዲላቀቁ ያስተምራሉ። አምራች እንዲሆኑ እድሜና ዝንባሌ እያዩ የሙያ ትምህርት ይሰጣሉ። በፖርት ሱዳንና በዓራርብ ጉዳተኞችን የሚንከባከብና እንደ ጉዳታቸው መጠን የሙያ ስልጠናዎችን የሚሰጥ ተቋም ነበራቸው። ሆስፒታሎች ከድርጅቱ አባላት ባሻገር በነጻ መሬት ላይ ለሚገኘው ነዋሪ ሁሉ አገልግሎት ይሰጣሉ። በሺህዎች የሚቆጠሩ ምርኮኞችን ጤንነት የመቆጣጠር ሃላፊነትም ተሸክመው ነበር። ማተሚያ ቤቱ ጋዜጦች፣ መጽሄቶችንና ቀላል መጻህፍትን ያትማል። ስሙን ከሆንግ ኮንግ እንደወረሰ የሚነገርለት "ኮንጎ ጫማ" የመኪና ጎማ እያቀለጡ እዚያው በረሃ ውስጥ ያመርቱታል። ብቃት ያላቸው ጋራጆችም ነበሩ። የውጭ ምንዛሪ ወጪ ለመቀነስ ቀላል ምርቶችን ሸለቆና ዋሻዎች ውስጥ ያመርታሉ።

የበረሃው የሰራተኛ ማህበር ሃብተአብን ፍየል አርዶ በጥሩ አቀባበል አስተናገደው። አንድ ቀን እና አንድ ሌሊት ከእነርሱ ጋር አሳለፈ። በቆይታውም ታጋዮቹ ያሳለፉትን ከባድ ጊዜና መጪውን ተስፋ እየቀላቀሉ አጫወቱት። በሁለተኛው ቀን አዜብ ተመልሳ መጣችና ይዛው ወደ ዓንበርበብ ሄደች።

በዓንበርበብ ቆይታው አዲስ አበባ ሳለ በቅርብ የሚያውቀውን ሰው አገኘ። ደበሳይ ሃይሌ ይባላል። በሞቀ ሁኔታ ተቃቅፈው ሰላምታ ተለዋወጡ። ያነከስ ስለነበረ ስለ እግሩ አንስቶ ጠየቀው። ወዲ ሃይሌ ቀለል አድርጎ እስመራ አካባቢ በተደረገ ውጊያ እንደ ተመታ አጫወተው። እንዲህ እየተጨዋወቱ ሳለ ሃብተአብ እየተሳቀቀ የመኮነንን ስም አነሳ። ደበሳይ እንዲህ አለው፣

"መኮነንን ለረጅም ጊዜ አላየሁትም። አንድ ቦታ ይኖር ይሆናል። የትግል ሜዳው ሰፊ ስለሆነና የማያቋርጥ ጦርነት ስለሚካሄድ በቀላሉ መገናኘት አይቻልም።"

የመኮነን ጉዳይ በዚሁ ከተዘጋ በሁዋላ ስለ ትግሉ አንስተው ተጨዋወቱ። ደበሳይ የታጋዮች ጽናት ላይ ትኩረት ሰጥቶ ተናገረ፣

“ታጋዩ ሲሰዋ የሁዋላውን እያመነ ነው።” ሲል ለሃብተአብ ነገረው፣ “.... ይህ እምነት ሃይል ሆኖታል። ከእምነት ጋር ጽናት አለ። ጽናት ከትእግስት ጋር አብሮ የሚሄድ ነው። ‘እኔ ምናገባኝ? ኤርትራ የኔ ብቻ አይደለችም። ብቻዬን ለምን እጨነቃለሁ?’ የሚል አስተሳሰብ ፈልገህ ልታገኝ አትችልም።”

እንዲህ ያሉ ነገሮችን እየተጨዋወቱ እስኪመሽ ቆዩ። ለአይን ያዝ ሲያደርግ ወዲ ሃይሌ፣ “ነገ እመጣለሁ” ብሎት ሄደ። በርግጥም እንዳለው በነጋታው መጣ። እና “ወደምናውቀው ሰው ልውሰድህ” ብሎ ይዞት ሄደ። ማን እንደሆነ ግን አልነገረውም ነበር። በሸለቆዎች መካከል እየተጠማዘዙ ከተጓዙ በሁዋላ መኪናዋ አንድ ተዳፋት ስር ቆመች። የተባለው ሰው ጸሃዬ ፋሲል ሆኖ ተገኘ።

የፋሲል ቤተሰብ በአዲስ አበባ የተቻለው ቤተሰብ ነበር። ልጆቹም በጥሩ ስነምግባር ያደጉ ለትምህርት ክፍት የሆነ አእምሮ የነበራቸው ነበሩ። ከፋሲል ልጆች አራቱ ወደ ትግሉ ሜዳ የገቡ ሲሆን፤ ሞገስ ፋሲል ቀዳሚው ነበር። ይህ ቤተሰብ በአዲሳባ ከገብርኤል ኤድሞንዶ ቤተሰብ ጋር የቀረበ ግንኙነት ነበረው።

ሃብተአብ ጸሃዬ ፋሲልን በማግኘቱ ስሜታዊ ሆነ።

በጨዋታ መሃከል እየተሳቀቀም ቢሆን የመኮነንን ስም አነሳ። ስለ ጊንዳዕ ግንባር አዜብ እንደነገረችው ከጠቀሰ በሁዋላ፣

“አጊኝተኸው ታውቃለህ?” ሲል ጠየቀው።

እንዲህ ሲጠይቅ አንድ ሌላ ታጋይ አብሮ ነበር። ይህ ሰው መኮነንን የሚያውቅ ነበር። የሃብተአብን ጥያቄ ሲሰማ ተነስቶ ወጣና ሄደ። በዚህ ጊዜ ሃብተአብ ስቅቅ አለ። ስለ መኮነን ከሰውየው ለመስማት ጓግቶ ሳለ ተነስቶ ሲወጣ ሃብተአብ ልቡ ጠረጠረ።

“ምን ሆኖ ሄደ?” ሲል ጸሃዬን ጠየቀው።

“ስራ ስላለው ነው።” ሲል መለሰ። አያይዞም፣ “መኮነንን አጊንቼው አላውቅም። አዜብ እንደነገረችህ ግን ጊንዳዕ ግንባር ሊኖር ይችላል።” ሲል መለሰለት። ሃብተአብ አልረካም። ጥርጣሬ አሳደረ።

እና ግን በአጠቃላይ ስለ ትግሉ ሂደት ተጨዋወቱ። ስለ ቤተሰብ ሁኔታ እያነሱ ተጠያየቁ። ሲመሽ ወዲ ሃይሌ ሃብተአብን ሊወስድ ተመልሶ መጣ። የሙዚቃ ትርኢት ወደሚካሄድበት ቦታ ይዞት ሄደ። ሃብተአብ ወደ ኤርትራ ነጻ መሬት ከገባበት እለት ጀምሮ በእጅጉ ካስደነቁት ገጠመኞች ዋናው ይህ የሙዚቃ ትርኢት ነበር። የናደው እዝ አባላት የነበሩና በጦርነት ላይ የተማረኩ የኢትዮጵያ ወታደሮች ያዘጋጁት ኮንሰርት የተዋጣለት ነበር። ከታጋዩም፣ ከሲቪሉም፣ ከምርኮኞችም ታዳሚዎች ተቀላቅለው ሲዝናኑ አመሹ። የናደው እዝ ትዝታና ፍቅር ያልወጣላቸው አንዳንዶች በጭፈራው መካከል የናደውን ስም እየጠሩ ስሜት ውስጥ ሲገቡ ይታይ ነበር።

* * *

መጋቢት 1988 የኤርትራ ነጻ አውጪ ታጋዮች ከመከላከል ወደ ማጥቃት የተሸጋገሩበት ልዩ ጊዜ ነበር። አስር አመታት ከሰንሰለታዊው መከላከል ወርደው የኢትዮጵያ ሰራዊት ላይ የመብረቅ ዶፍ አዘነሙ። ጦርነቱ የወታደራዊ ሳይንስ ጥበብ የተበንጸባረቀበት ነበር። በኢትዮጵያ በኩል የነበሩት የሰራዊት አዛዦች በበርካታ ውጊያዎች የተፈተኑ፤ የተከፈለው ተከፍሎ ኤርትራን የጨመረች ኢትዮጵያ ለመመስረት ቆርጠው የሚሰሩና የሚሰው ነበሩ። ጀግንነት በተለምዶ ለአሸናፊ ብቻ ቢሰጥም፤ ተሸናፊዎቹም ድንቅ ጀግኖች ነበሩ።

ሰለሞን በርሀ “የናደው ቀበር ትዝታዎች” በሚል ትረካው ላይ እንደገለጸው ኢትዮጵያ በመላ ኤርትራ 94 ሺህ ሰራዊት ነበራት። በሻእቢያ ኢላማ ውስጥ የገባው ናደው እዝ ደግሞ 16 500 ወታደር ይዞ ቀዳሚ መምሪያውን አፍዓበት ተክሎ ነበር። ሻእቢያ በአንጻሩ ናደው እዝን ቀለበት ውስጥ አስገብቶ ሙሉ በሙሉ ለመደምሰስ ሲያቅድ በጥቅሉ 10 400 የሰው ሃይል ያቀፉ አምስት ክፍለ ሰራዊቶች ነበሩት።

መጋቢት 17 ሻእቢያ በአምስት አግጣጫ ማጥቃት ከፈተ። በሶስት ቀን ውጊያም ናደው ሙሉ በሙሉ ተደመሰሰ። ከ70 በላይ ተሽከርካሪዎች ወደ አፍዓበት አግጣጫ ሸሽቱን ተያያዙት። የአማጽያኑ የብርጌድ 34 አንዲት ታንክ የተኮሰችው ቁምቡላ፣

እየሸሸች ዓዲሽሩም አንገት ላይ ደርሳ የነበረችውን ቢኤም-21 ሮኬት ወንጫፊ ኢጋየቻት። ከሁዋላዋ የነበረች ሌላ ታንክ ተደገሙች። በዚህም ኢትዮጵያ ተሽከርካሪዎችና ታንኮች መተላለፊያ በማጣት በያሉበት ተገተሩ። የናደው አዛዥ ጀኔራል ውበቱ ጸጋዬ ዓዲሽሩም አንገት ላይ የተከማቹ ከባድ መሳሪያዎች በአየር እንዲደበደቡ ማዘዝ የመጨረሻ ስራው ነበር። ሶስተኛው ቀን ሲነጋ ወደ አፍዓበት ተጠግቶ ያደረው የኤርትራ ነጻ አውጪ ግንባር በማለዳው አፍዓበትን በእጁ አደረገ። በዚህ እለት በተደረገ ትርፍራፊ ውጊያ ሶስት የሱቭየት አማካሪዎች ከሌሎች መኮንኖች ጋር እጃቸውን ሰጡ። ተስያት ላይም የናደው እዝ ጉዳይ ጨርሶ ተጠናቀቀ።

ናደው ተጠቃሎ በተደመሰሰበት እለት ጋዜጠኛው እና ታሪክ ጸሃፊው ባሲል ዴቪድሰን ከግርማ አስመሮም ጋር ናቕፋ ነበር። ግርማ አስመሮም ዴቪድሰንን ወደ ዶክተር ተኽስተ ፍቓዱ ይዞት ሄዶ በመነጋገር ላይ ሳሉ፣ ከፍተኛ የተኩስ ደምጽ ሰሙ። ባሲል ዴቪድሰን ምክንያቱን ሲጠይቅ ናደው እዝ ሙሉ በሙሉ ተደምስሶ አፍዓበት ከተማ ነጻ መውጣቷን ነገሩት። ግርማ እና ዴቪድሰን ዶክተር ፈቃዱን ተሰናብተው ወደ አፍዓበት ግንባር ገሰገሱ ። በዚያኑ እለት ሽማግሌው ዴቪድሰን ለቢቢሲ ሲዘግብ የቬትናም ነጻ አውጪ ታጋዮች የፈረንሳይ ሰራዊትን Dian Bien phu ላይ ከደመሰሱበት ውጊያ ጋር አመሳሰለው። ዶክተር ተኽስተ ፍቓዱ ዜናውን ከሰማ በሁዋላ፣ “ባሲል እስካሁን ስለ ኤርትራ ትግል አልጻፍከም ነበር። ‘ስላረጀሁ ልጽፍ አልቻልኩም’ ብለኸኝ ነበር።’ በዚህ ክንዋኔ ግን ‘በጥቂት ቃላት’ አንድ ግዙፍ መጽሃፍ ጻፍክ።” እንዳለው ጽፏል።

* * *

በነጋታው ሃብተአብ ወደ አፍዓበት ተጓዘ።

አፍዓበት ሳሉ የኢትዮጵያ ጀቶች መጥተው ደበደቡ። ቀን ቀን ኢትዮጵያ አየር ሃይል ሲያንጣብብ ስለሚውል የከተማው ህዝብ ከተማውን ለቆ በተቦረቦረ የተራራ ወገብ ስር ተሸሽጎ ይውላል። ጸሃይ ስታዘቀዝቅ ተመልሶ ወደ ቤቱ ይገባል። ሃብተአብም በአፍዓበት ቆይታው ከህዝቡ ጋር ይህንኑ ፈጸመ። በአፍዓበት ቆይታው ወልደንኬኤል የሚባል የሚያውቀውን ታጋይ አገኘ።

የአፍዓበት የህዝብ ክፍል ሃላፊ ነበር። መኮነንን ማየት የእግረመንገድ ጉዳይ አድርጎ ሲያበቃ፤ በጥቅሉ የትግሉን ሁኔታ ለማየት መምጣቱን ገለጸ። ወልደንኬኤል መኪና ከነ ሾፌር መደበለት።

እና ከአፋበት በሸዕብ በኩል ወደ ምጽዋ ተጓዘ። ምጽዋ ነጻ ከወጣች ገና ጥቂት ወራት ብቻ ነበር። "የስጋለትን ላንቃ አልፎ፤ ምጽዋን የመቆጣጠሩ ጀብዱ" በርግጥ ስለመፈጸሙ ለኢትዮጵያ መሪዎች ገና ለማመን ያስቸገረ ህልም መሰል ክስተት ነበር።

በቀን መጓዝ አደገኛ ነበር። የኢትዮጵያ ጀቶች አሰሳ እረፍት አልነበረውም። ሌሊቱን ሲጓዙ አድረው በነጋታው ከእኩለ ቀን በፊት ምጽዋ ገቡ። ምጽዋ በጣም ይሞቅ ነበር። በቀጥታ ከመሎቲ ቢራ ቅርንጫፍ ቤት ሄደው አረፉ። ማቀዝቀዣው አይሰራም ነበር። ሌሊት ጣራው ላይ እየተኙ ሁለት ሳምንት ያህል አለፈ።

ምጽዋን ለመያዝ ስለተደረገው ጦርነት አጫወቱት። "ፈንቅል" ተብሎ ስለተጠራው ኦፕሬሽን ሲያጫውቱት የጀብዱ ፊልም የሚተርኩለት መሰለው። በተለይም "ስጋለት ቀጣን" ተብላ የምትታወቀውን ወደቡ ወደሚገኝበት ደሴት የምታመራውን መንገድ ለመቆጣጠር የተደረገው ተጋድሎ በውን የተፈጸመ የማይመስል ሆነበት። መስዋእትነት በገፍ የሆነባቸውን አስደናቂ ታሪኮች ሲሰማ እየዋለ፤ ሃብተአብ ስለ ወንድሙ ማንሳት አልቻለም ነበር። ቢሆንም በእግረመንገድ ማንሳቱ ግን አልቀረም። የጠየቃቸው ሁሉ እንደማያውቁት ነገሩት። የተማከሩ ይመስል "ጊንዳዕ ግንባር ይኖር ይሆናል።" ይሉታል። የሻእቢያ ዋና ግንባር ጊንዳዕ ስለነበር የግንባሩ ዋና ሃይል ሁሉ ጊንዳዕ ተከማችቶ ነበር።

በየቀኑ ማጥቃትና መከላከል፣ መልሶ ማጥቃትና የከባድ መሳሪያ ድብደባ ይካሄዳል። የኢትዮጵያ ጀቶች ሰማዩን ሲዋኙበት ይውላሉ። ኢትዮጵያ ቢሊዮናት ዶላር ከስክሳ ከሶቪየት ሩስያ የሸመተችው የጦር መሳርያ የብረት ጎርፍ ታጋዮቹን መደምሰስ እንዳልቻለና እንደማይችል ታውቋል። ኮሎኔል መንግስቱ መሳሪያ ለመለመን ሞስኮ ሲሄድ፤ የሶቪየት ራሺያ መሪ፣ "በተዘዋዋሪ የነጻነት ታጋዮችን ጭምር በማስታጠቅ ላይ መሆናቸውን" በመጥቀስ ኮሎኔል መንግስቱን በሽሙጥ ጥፊ እንዳጮለው ወሬው ተሰምቷል። በጥቅሉ ሶቪየት ራሺያ ከፊሉ ባልተከፈለ እዳ ኢትዮጵያን ላይ በላይ

ማስታጠቅ አሰልችቷታል። ከአፍዓበት ድል በሁዋላ አለም ጆሮውን ከፍቶ ስለ ኤርትራ ትግል መስማት ላይ ነበር። የምጽዋ ሲደገም የኤርትራ ነጻነት የማይቀር መሆኑ ግልጽ ሆነ።

ጋዜጠኞችና ታሪክ ጸሃፊዎች ሱዳን የሚያደርሳቸውን ትኬት ቆረጡ። ከዚያም በሌሊት ጉዞ ወደ ኤርትራ ገቡ። በርግጥ ቀደም ሲል ጀምሮ ብዙዎች ጎብኝተዋታል። ብዙዎች ጽፈውላታል። Roy Pateman *"Even The Stones Are Burning"* የሚል መጽሃፍ በ1990 አስነበበ። ይበልጥ ተወዳጅ የሆኑት የConnel *"Against All Odds"* እና የKeneally *"Towards Asmara"* ነበሩ።

(ቶማስ ኬኔሊ በመጽሃፉ እንዲህ አሰፈረ፣ "You know what I think? They are brave to the point of folly and they're clever to the point of being dumb. No one absolutely no one, from Washington to Moscow, wants them to succeed. No one. … God's even taken the rain away from them, for Christ's sake. Even he thinks they're wrong-headed. The sin of pride … the sin of being sharp when no one wants them to be.")

ሃብተአብ በምጽዋ ቆይታው አንድ ቀን ከስብሃት ኤፍሬም ጋር ለመገናኘት እድል አገኘ። አጋጣሚውን በመጠቀም ወደ ጊንዳዕ ሄዶ ወንድሙን ለማየት ይችል እንደሁ ፈቃድ ጠየቀው። ፈቃድ ግን አላገኘም። "አደገኛ ነው፤ መሄድ አይቻልም።" አለው።

ከዚህ በሁዋላ ሃብተአብ ስለ መኮነን አላነሳም።

ውጊያ የተደረገባቸውን የምጽዋ ቦታዎች እየተዘዋወረ ጎበኘ። ባሕሩ ላይ በብዛት በአሳ የተጋጠ የሰው አጥንት ተንሳፎ ይታይ ነበር። የኢትዮጵያ የባሕር ሃይል ተዋጊ መርከቦች ወደ ምጽዋ እየቀረቡ መተኮሳቸው አልቀረም ነበር። ሆኖም ከፋይበር ግላስ የተሰሩት የሻእቢያ ፈጣን ጀልባዎች በቀላሉ ያባርሯቸው ነበር። ሃብተአብ በማጉያ መነጽር የኢትዮጵያን መርከቦች በርቀት ለማየት ቻለ። ተኩሳቸው ኢላማ አልባ ተስፋ የመቁረጥ ተኩስ ነበር።

አንድ ምሽት እራት በልተው እንዳበቁ ቴሌቪዥኑ ሰበር ዜና አመጣ። በመፈንቅለ መንግስት ሙከራ ጉዳያቸው በሰራዊት ፍርድ ቤት ሲታይ የከረሙ ጀኔራሎች መገደላቸው ተገለጸ። ታጋዮቹ በጣም ተደነቁ። በማንኛውም መለኪያ ለኤርትራ ትልቅ የምስራች ነበር። የተገደሉት ጀኔራሎች ልምድ የነበራቸው እንደመሆናቸው በአንድ አዳር የሚተኩ አልነበሩም። ኮሎኔል መንግስቱ ጀኔራሎቹን መረሸኑ ስልጣኑን ለማራዘም የሚረዳውም አልነበረም።

ዜናውን ሰምተው እንዳበቁ ከታጋዮች አንዱ፣ “መንግስቱ ራሱ ነው የሚያግዘን።” ሲል ተናገረ። ወደ ሃብተአብ መለስ ብሎም፣ “....ውጊያው አልቋል። አስመራን አይተህ ትሄዳለህ።” አለው።

ሃብተአብ አንድ ወር ከአንድ ሳምንት የኤርትራን የትግል ግንባር ከጎበኘ በሁዋላ እህቱ ዙፋን ገብርኤል ወደ ምትኖርበት አገር ወደ ኔዘርላንድስ ሄደ። እናቱ ሉላ ከእየሩሳሌም ተመልሳ አምስተርዳም ነበረች። እህቱና እናቱ በጉጉት ተቀበሉት።

የሉላ የመጀመሪያ ጥያቄ የተጠበቀ ነበር።

ሃብተአብ ግን የማይፈለግ ምላሽ ሰጠ፣

“መኮነንን አላገኘሁትም።” ሲል ነገራቸው፣ “...ጊንዳዕ ግንባር እንዳለ ግን ነግረውኛል። ወደዚያ መሄድ አልተፈቀደልኝም። ጊንዳዕ መኖሩን የነገረችኝ አዜብ ፍስሃዬ ናት።”

ዜናው ለሉላ ከበዳት።

ግን መልሳ ደግሞ ሃብተአብን፣ “እንኳን አንተ በደህና ለመመለስ በቃህ” አለችው። ስለ መኮነን ግን ከዚያ ያለፈ አንስተው ሊነጋገሩ የሚችሉት ነገር አልነበረም።

ሃብተአብ የመኮነንን ጉዳይ በመተው በአጠቃላይ ትግሉ የደረሰበትን ደረጃ ነገራቸው። የኤርትራ ነጻነት የማይቀር መሆኑን አበሰረላቸው። በትግል ሜዳ ስላገኛቸው፣ ስለ አዜብ፣ ስለ ሻለቃ ከሰተብርሃን፣ ስለ ወዲ ሃይሌ፣ ስለ ጸሃዬ ፋሲል እያነሳ ሲያወጋቸው፤ መኮነንም በህይወት ሊኖር ይችላል ብለው ተስፋ አደረጉ። ሉላ በዚያን ሌሊት አልተኛችም። ጋቢ ተከናንባ ከበረንዳው ላይ ቁጭ ብላ አነጋች. . .

ምእራፍ ፱

አንዲት ሴት ነበረች

ጉንጫ ርሶ በእንባ - ጥርሷ የሳቅ አምባ

ሉላ ስለ ልጇ የጠበቀችውን ሰማች።

“ህይወትህ ሞት ከሚሆን፣ ሞትህ ህይወት ይሁንልህ” ብለው እየመረቁ ልጆቻቸውን ወደ በረሃ የላኩ ብዙ ኤርትራውያን እናቶች የጠበቁትን የልጆቻቸውን መስዋእትነት ሲሰሙ እሪ ብለው አልጮሁም። እየሳቁ አነቡ። ሉላ የልጇን የመስዋእትነት የምስክር ወረቀት ስትቀበል ጉንጫ በእንባ ታጥቦ እየታየ የሚስረቀረቅ እልልታ አሰማች። ማንበብና መጻፍ ስለማትችል ወረቀቱ ላይ የተጻፈውን ማወቅ አልቻለችም ነበር። እና አጠገቧ የነበሩ ዘመዶች አነበቡላት።

ሰም - መኮነን ገብርኤል ኤዶምንዶ
ወደ ትግል የገባበት እለት - 07 1976
ዓዲ - ሓልሓል
አሃዱ - ብርጌድ 44
የተሰዋበት እለት - 16 - 02 - 1982
የተሰዋበት ቦታ - ደንቦቢት

አበቃ። ይኸው ነው። በርግጥ ማንኛውም ጦርነት ኪሳራ አለው። ከጦርነት ትርፍ ብቻ አይገኝም። አሸናፊውም ሆነ ተሸናፊው በተመጣጣኝ ይከስራል። የድል ሌላው መልክ ሃዘን ነው። በሁለተኛው የአለም ጦርነት ሶቪየት ራሺያ ናዚ ጀርመንን ድል ካደረገች በሁዋላ 13.6 ሚሊዮን ሰዎች መሰዋቷን ተረዳች። ጀርመን በተመሳሳይ 10.3 ሚሊዮን ዜጎቿን ለጦርነት ከርስ መግባ ነበር።

የመንግስቱ ሃይለማርያም ስርአት በአስራሰባት የጦርነቱ

አመታት ከሶቪየት ህብረት የብዙ ቢሊዮን ዶላር የውጊያ መሳሪያ ገዝቶ ነበር። ራሱ በገዛው መሳሪያ እየተደበደበ ከ250 እስከ 300 ሺህ የሰው ህይወት ከፈለ። የኤርትራ ህዝብም በጥቅሉ በሰላሳ አመታቱ ጦርነት 65 ሺህ የሰው ህይወት ከፈለ። ከዚህ ሁሉ ኪሳራ በሁዋላ "ጦርነት ታሪክ ይሆናል" ተብሎ መገመቱ ስህተት ሆነ።

በዚያን ቀን ሉላ በዘመዶች ታጅባ ወደ ቤቷ ሄደች። ጎረቤትም ተሰበሰበ። ከምሳ በሁዋላ ቡና ተፈላ። ያልተጠበቁ እንግዶችም መጡ። ከእነዚህ አንዱ በአንድ ጎልማሳ የታጀበ ሽማግሌ ሰው ሲሆን፤ ፈገግ ሲል ሉላ አወቀችው። እያሱ ያዕቆብ ነበር።

እስከ ምሽት ድረስ አወጉ።

የእያሱ ልጅ ፈዳይ በትግሉ ዘመን መኮነንን በተለያዩ አጋጣሚዎች አጊኝቶት እንደነበረ ገለጸ። መኮነን በጦርነቱ ውስጥ በኢትዮጵያ ወገን ሆነው ሲዋጉ የነበሩ አብሮ አደግ ጓደኞቹን እንዳገኘ እንደነገረው ፈዳይ ለሉላ አጫወታት።።

ትዝታዎቻቸው ማቋረጫ አልነበራቸውም። ከሞቅዲሾ አንስቶ እስከ አዲስ አበባ እያስታወሱ ብዙ አወጉ። እያሱ የእርጅና ዘመን ላይ ቢሆንም መንፈሱ ገና የጎረምሳ ነበር።

ስለ መኮነን መስዋእትነት ሲጨዋወቱ ሉላ፣

"በአምላክ የተጻፈለትና የተወሰነለት ቀን ነበር።" አለች።

እያሱ ግን በዚህ አባባል አልተሰማማም።

"የእድል ጉዳይ ነው።" ሲል ሞገተ። "አምላክ እንዲህ ባለ የግለሰቦች የሞትና የህይወት ጉዳይ ውስጥ እጁን አያስገባም። እያንዳንዱ ሰው የሚወለድበትና የሚሞትበት ቀን አስቀድሞ የተወሰነ ከሆነማ ለመኖር ምን ትግል ያስፈልጋል?"

አባባሉን የሚቀበለው ሲያጣ እያሱ ያዕቆብ "አታውቁም!" እንደማለት እጁን አወናጨፈ። ሉላ እየሳቀች እንዲህ አለችው፣

"እድሜ አልቀየረህም። ምንም አልተለወጥክም። ሞቅዲሾ ወደ ቤታችን ስትመጣም አነጋገርህ ልክ እንደዚሁ ነበር።"

ብዙ ርእሰ ጉዳዮችን እያነሱ ተጨዋወቱ።

በጨዋታቸው መካከል ገብረማርያም ቴዎድሮስ ከረን ላይ ለኤርትራ ፓርላማ ተወዳድሮ እንደነበር አነሱ። ብላታ መስፍን በጋሸት በፓሪስ የኢትዮጵያ አምባሳደር ሆነው ይሰሩ እንደነበር ጠቀሱ። ኪዳኔ አድነይ ከረን ላይ ስመጥር ሃብታም ነጋዴ እንደነበሩ አወጉ። አጤ ሃይለስላሴ በከረን - ዖና ከ600 በላይ ኤርትራውያን ላይ ስለፈጸሙት አሰቃቂ ግፍ አንስተው ረገሟቸው። ነፍሳቸው ሲኦል ገብታ ሊሆን እንደሚችልም ሉላ በርግጠኛነት ተናገረች።

ርእሰ ወጋቸው ማቋረጫ አልነበረውም።

የናደው ዕዝ ውድቀት፤ ምጽዋን ለመያዝ የተደረገው የፈንቅል ኦፕሬሽን ጀብዱ፤ እንዲህ ያለ ርእሰ ጉዳዮችን እያነሱ ተጨዋወቱ። ሉላ የኤርትራን ነጻነት ለማየት ያበቃትን አምላክ አመሰገነች። ባለቤቷ ገብርኤል የኤርትራን ነጻነት ሳያይ ወደ ገነት በመወሰዱም አምላክን አማረረች።

እንዲህ ሲጨዋወቱ እኩለ ሌሊት ሆነ።

እያሱ ሰምበል በሚገኘው የአያቱ የእርሻ ቦታ የሽምግልና ዘመኑን ለማሳለፍ አዲስ ኑሮ ከጀመረ ሰነበተ። የግብርና ስራዎችን ሲሰራ ለሚያየው የዘጠና ፊሪ አይመስልም። በሳምንት አንድ ጊዜ ቅዳሜ ከምሳ በሁዋላ ከጎብኚ እንግዶች ጋር መጨዋወት ለምዷል። እነዚህ ጎብኚ እንግዶቹ በአብዛኛው ጡረታ የወጡ የአስመራ ኢጣልያውያን ናቸው። በተቀረ በየእለቱ ለአይን ያዝ ሲያደርግ በሁዳዱ ዳርቻ የመንሸራሸር ልማድ አለው። የሰሌን ባርኔጣውን ደፍቶ፤ ከዘራውን እየተከለ በኩራት ይራመዳል።

በርግጥ ከዚህ የሰምበል ርስት የሰነበተ ሰው ጤንነትና የአእምሮ መታደስን በዝቆሽ ያገኛል። አየሩ ምንጊዜም ነፋሻ በመሆኑ ቀኑን ሙሉ ተቀምጦ ቢዋል አያሰለችም። የፍራፍሬው ሽታ አይጠገብም። የቅጠላቅጠሎቹ መአዛ ማቋረጫ የለውም። የእንስሳቱ ህብረ ድምጽ ከሩቅ እንደሚሰማ ሲንፎኒ ነው።

ሚለና አጠገቡ አለች። የሩቅ ዘመዱ ናት። ከብቸኛ ልጁ ከፈዳይ በቀር ሌላ የቅርብ ዘመድ ኤርትራ ላይ የለውም። ከፊሉ በጦርነት ሲሰዋ፤ ሌላው በስደት ርቆ ሄዷል። እያሱ ዘወትር ከምሳ በሁዋላ ከሚለና ጋር የጀበና ቡና የመጠጣት ልማድ አዳብሯል።

ለዚሁ ተግባር የምታገለግል ጣሪያዋ በሳር የተሸፈነ፣ ግድግዳ አልባ መናፈሻ አለች። እያወጉ ከሚለና ጋር ቡና ያጣጥማሉ። ከቡናው ጋር ምንጊዜም የበቆሎ ጥብስ ይቀርባል።

እያሱ ከእርጅናው በቀር ጤነኛ ነበር። ከብቸኛ ልጁ ጋር ያለው ግንኙነት የቀረበ ባይሆንም ሲገናኙ የሚያወጉትን አያጡም። በተቀረ እያሱ ከጥቁሩ እምባ አውሊዕ ተራራ ጋር የበለጠ መግባባት ነበረው። የህይወት መንገድ ላይ ያለፈ ትዝታው ተመልሶ እየመጣ እንደ ፊልም ትርኢት ከፊቱ ሲዘረጋ የሰሌን ባርኔጣውን ጭንቅላቱ ላይ ጣል አድርጎ፤ ከዘራውን እየተከለ ወደ እምባ አውሊዕ ይሄዳል። እናም ግርጌው ላይ አረፍ ብሎ ሲያበቃ እንደ ልብ ወዳጅ ያወጋዋል።

የኤርትራ ሪፈረንደም ከተካሄደ ከጥቂት ወራት በሁዋላ እያሱ እንደ ልማዱ ወደ እምባ አውሊዕ ተራራ ሄዶ ነበር። በከዘራው እየተደገፈ እንደምንም ጥቂት ወደ ላይ ወጣ።

አረፍ ካለ በሁዋላም እንዲህ አለ፣

“ወዳጄ ሆይ! ይኸውልህ እዚህ ደረስን። በመጨረሻ ወደ ነበርንበት ተመለስን። እንግዲህ ከጎረቤቶቻችን ጋር በሰላም መኖር ከተቻለ በጎ ነው። በርግጥ የሚሻላቸው ተከባብረው በእኩል መንፈስ መኖር ነው። ማንም ቢሆን ገፍትሮ አልጣላቸውም። አንገታቸውን የቆረጠው በውርስ ያገኙት ትምክህተኛ አመለካከታቸው ነበር።”

ከእርጅናው ተቃራኒ በሆነ ድምጽ ቀጠለ፣

“....የተሳሳተ እምነታቸውን እንደ ወተት ለልጆቻቸው መገቡ። ከጡጦ ጋር የተሞሉትን ስህተት፣ ከዘመናዊ ትምህርት የሚገኝ እውቀት ሊገራው አልቻለም።”

አይኖቹን ጥርት ካለው የሰማይ ደረት ላይ ተክሎ ቀጠለ፣

“....በተረት የተገነባውን ስርአት በጥገና ለውጥ ማቆየት ይሻላቸው እንደነበር የተገነዘቡት ከረፈደ በሁዋላ ሆነ። አብረው ካፈረሱ በሁዋላ ተገላምጠው ሲያዩ መሳሳታቸውን አወቁ። ወደሁዋላ መመለስ ግን አልቻሉም። ጊዜ አልነበራችም።”

ሽማግሌው እያሱ የጎረምሳ ፈገግታ ብልጭ አድርጎ ቀጠለ፣

“....የራሳቸውና የግላቸው የነበረውን እንኳ ማቆየት ሳይችሉ

ቀሩ። በጦርነት ጀምረው በጦርነት ተገላገሉት።"

እያሱ እንዲህ ያሉ ወጎችን ከእምባ አውሊዕ ጋር እያወጋ ጥቂት ቆየ። በቆይታው ማብቂያም እንዲህ አለ፣

"አብሮ መኖርን የሚጠላ አልነበረም። ትልቅ አገር መሆን ጥቅሙ ይበልጣል። ትልቅ አገር መሆን ብቻውን ግን ትልቅነት አይደለም። ከልብ የመነጨ ቅን እርምጃ ያስፈልግ ነበር....."

ጥቂት ፋታ ከወሰደ በሁዋላ፣ "...የአንዱ ውድቀት ለሌላው ትርፍ ሊሆነው አይችልም።" አለ። እና እንዲህ ሲል ደመደመ፣ "....በአንጻሩ ጦስ ይሆናል። የጎረቤት ቤት እየተቃጠለ፤ ዳር ቆሞ መመልከት አይቻልም። ይህን ለመረዳት የሚችሉ ራዕይ ያላቸው መሪዎች ግን መኖር አለባቸው። ካልሆነ አዙሪቱ ይቀጥላል..."

በዚያው ሰሞን የኤርትራ የኢቫንጀሊካል ቤተክርስትያን ቄሶች ሰምበል ወደሚገኘው የእያሱ መኖሪያ ቤት ሲመላለሱ ታዩ። እያሱ እርጅና ባመጣው ህመም በመያዙ የስንብት ጸሎት እያደረጉለት ነበር። በጸሎት ወቅት እያሱ አይኖቹን ጨፍኖ ታየ። እጆቻቸውን ግንባሩ ላይ አሳርፈው ረጅም ጸሎት በማድረግ መንግስተ ሰማያት ይገባ ዘንድ ምህረት ለመኑለት።

እንዲህ ሰነባብተው የኤርትራ ሪፈረንደም በተካሄደ በሰባተኛው ወር አካባቢ በእለተ ማክሰኞ ማለዳ እያሱ አረፈ። የቀብር ስነስርአቱም በነጋታው እኩለ ቀን ላይ ጸጸራት እንደሚፈጸም ሲነገር ዋለ። የእያሱ እረፍት ግን በአስመራ ከተማ ትልቅ ወሬ ለመሆን አልበቃም። አዲሱ ትውልድ እያሱን አላወቀውም። ለቀብር የመጡት አብዛኞቹ የፈዳይ ጓደኞች የግንባሩ አባላት ነበሩ።

በቀብሩ ላይ የለቅሶ ድምጽ አልተሰማም። አንዲት በእድሜ የገፉች ሴት ግን ሴቶቹ ከነበሩበት አካባቢ ተገንጥላ በጉድጓዱ ዙሪያ ቆማ ነበር። ደጋግማ በነጠላዋ ፊቷን አበሰች። አልፎ አልፎም ፈገግ ስትል ታየች። እንዲህ በቅጽበት ስሜቷ የሚለዋወጠው ይህች ሴት ማን እንደሆነች ፈዳይ ማወቅ ተቸግሮ ቆየ። ዘግይቶ ግን ሉላ እዮስአብ - የመኮነን እናት መሆኗን አስታወሰ።

ድህረ ታሪክ

በወርሃ ነሃሴ 2016 አጋማሽ ከደበሳይ ገብርኤል ጋር አስመራ ከተማ - ጸጸራት ወደሚገኘው የመቃብር ስፍራ ሄድን። የመጨረሻ ጉዟችን ነበር። ቀደም ብለን ፋና፣ ኡምኩሉ፣ ድባርዋ፣ አዶምዘማትና ደቀምሓሬ ሄደን ነበር። ለታሪክ ቁፋሮ የሚደረግ ጉዞ - እንደ ተቀበረ ሃብት አሳሾች ጉዞ ልብ ይሰቅላል።

ጸጸራት ግቢው በአበቦች ደምቋል። በመቃብሮቹ መካከል የሚገኝ ሰው በሙታን መካከል የቆመ አይመስለውም። በተለይም የኢጣልያውያን መቃብር እጅግ ድንቅ ስነጥበብ በተንጸባረቀበት የቅርጽ ስራ አሸብርቋል። ሟቾች በህይወት ያሉ ይመስላሉ።

ደበሳይ እየመራ ወስዶ ከአድም መቃብር አደረሰኝ። በመቃብሩ ላይ "ኤድሞንዶ ገብረመድህን" የሚል ሰፍሯል። ብዙም ባልራቀ ርቀት ታላቅ ወንድሙ እድሪስ አርፎአል። በርግጥም እነዚህ ሁለቱ የሓልሓል ቦጎስ ወንድማማቾች በኢጣሊያ ቅኝ አገዛዝ ዘመን ያለፉበት በጎም ሆነ ክፉ የህይወት መንገድ፣ የተቀያየረ ስማቸውና ሃይማኖታቸው የግማሽ ምእተ አመት ማሳያ መስታወት ነበር።

ብዙም ባልራቀ ርቀት የፊታውራሪ ገብርኤል እና የወይዘሮ ሉላ እዮስአብ መቃብር ይታያል። ገብርኤል ከጓደኞቹ ጋር ተባድኖ በህቡእ ኢትዮጵያን ከኢጣሊያ ወረራ ለማዳን ያደረገው ትግል የጸረ ቅኝ አገዛዝ ትግል አካል ነበር። ውጤቱ ግን ተገላቢጦሽ ሆነ። እና የገብርኤል ትውልድ ቅሬታውን ለልጆቹ አወረሰ።

ጊዜው በፈቀደው መጠን የመኮነን ገብርኤል ዘመን ወጣቶች ጠመንጃ ይዘው በአመጽ ተነሱ። ኤርትራውያን አገራቸውን ራሳቸው መምራት እንደሚገባቸው አምነው መራር መስዋእትነት ከፈሉ።

መኮነንና ጓደኞቹ የታሪክ አጋጣሚ ሆኖ ሲጀመር መንገዳቸው ቀይ ነበር። መንገዱን በሸፈነው ቀይ የታሪክ ባሕር ላይ ዋኝተው ማለፍ የትውልድ ግዴታቸው ሆነ።

መካነ መቃብሩን ለቀን ስንወጣ ደበሳይ በስሜት ተናገረ፣

“ከልጅነቴ ጀምሮ የማውቃቸውና የማከብራቸው ሰዎች አብዛኞቹ እዚህ አርፈዋል። ብላታ መስፍን በጋሸት፣ ቀኛዝማች ፍጡር አብርሃም፤ ካፒሌር እያሱ ያዕቆብ፣ ወይዘሮ ጸጋ ብርሃን መንገሻ፣ አባቴና እናቴ ሌሎችም ሞቅዲሾ የነበሩ የአንድ ዘመን ጓደኛሞች በመጨረሻ ከያሉበት እየመጡ ኤርትራ አርፈዋል። አምላክ ነፍሳቸውን በገነት ያኑር። የንቃት ደረጃቸውና አቅማቸው በፈቀደው መጠን እምቢታ ማሳየታቸው መነገሩ ተገቢ ነው።”

ዘግየት ብሎ እንዲህ ሲል አከለ፣

“ዘምህረት ዮሃንስ በመጽሃፉ Foot Note ላይ ’የገብርኤል ኤድሞንዶ ታሪክ ብዙ አይታወቅም። መጠናት አለበት’ ብሎ የጠቀሰውን ዘግይቼ እስካነብ ድረስ ሰመመን ውስጥ ነበርኩ። እና ጉዳዩን በቅድሚያ ከልጇ ከናሆምና ከባለቤቴ ከሰላማዊት ጋር ተወያየሁበት። እንድገፋበት ሞራል ሰጡኝ። የወንድሞቼና የእህቶቼ ማበረታቻም ተጨመረበት። እና ካንተ መጻህፍት የተወሰኑትን አንብቤ ስለነበር ትሰራዋለህ ብዬ በማመን ወዳንተ መጣሁ....”

በዝምታ ጥቂት እንዳዘገምን፣

“ገብርኤልን ሁለት ጊዜ ለእስር ያበቃው የአጤ ሃይለስላሴ ባለስልጣን ማነው ስሙ?” ስል ጠየቅሁት።

ጥቂት በተመስጦ ቆየና፣

“ሰውየው ደጃዝማች ነበር።” ሲል መለሰ፣ “...አባቴ የደጃዝማቹን ስም ለልጆቹ ለመናገር ፈቃደኛ አልነበረም። ይቅርታ ጠይቆት፤ ይቅር ብሎታል። እንደሚመስለኝ ከይቅርታ በሁዋላ ስሙን ለኛ መንገር ተገቢ ሆኖ አልታየውም።”

“ስሙን ግን ታውቀዋለህ?”

“ግምት አለኝ። ርግጠኛ ግን አይደለሁም።”

ለደቂቃ ያህል ተከዞ ከቆየ በሁዋላ የደጃዝማቹን ስም ነገረኝ። እናም ስለ ደጃዝማቹ እያወጋን አዘገምን።

እነሆ! የቀረኝ ነገር አልነበረም።

መጽሃፉ ገና ድሮ በጭንቅላቴ ውስጥ ተጽፎ አልቆ ነበር። በርግጥም ከጭንቅላቴ እየቀዳሁ ኮምፕዩተር ላይ ከመገልበጥ በቀር የቀረኝ ሌላ ስራ አልነበረም። ከመካነ መቃብሩ ደጃፍ አካባቢ ቆም ብለን ሳለ ግን እንደዋዛ የቤተሰብ ጉዳይ አንስቼ ጠየቅሁት፣

“ከገብርኤል ልጆች ኤርትራ የሚኖር አለ?”

“በኢጋጣሚ ሁሉም ውጭ አገር ናቸው።”

“የልጅ ልጆች ስንት ደረሱ?”

“ብዙ ናቸው።”

“ኤርትራ መጥተው ያውቃሉ?”

“በተለያዩ ኢጋጣሚዎች ይመጣሉ። ሃገራዊ አገልግሎት ለመስጠት ወይም ለእረፍትና ለጉብኝት ወደ ኤርትራ ይመላለሳሉ። ተቆርጠው አልቀሩም። በአገራዊ ጉዳዮች ላይ እንሳተፋለን። ልጆቻችን ታሪካቸውንና ባህላቸውን እንዲያውቁ እንጥራለን።”

እና ደበሳይ እየሳቀ አከለበት፣

“ዋናው ነገር . . . ኑረነቢ አልከሰረም።”


የጸጸራትን መካነ መቃብር ለቀን ወጣን።

ቀና ብዬ ሳየው ሰማዩ ጠቁሯል።

ነጎድጓድ ያጉረመርማል። የተመሰገነ ዝናብ እየሰጠ የዘለቀው የ2016 ክረምት ዛሬም እንደወትሮው ጓዙን፣ ወዙን ጭኖ መጥቷል። አየሩ በፍጥነት ቀዘቀዘ። አእዋፍ ወዲያ ወዲህ ተወናጨፉ። የተረበሹ ይመስላሉ። እያንጣበቡ የሚያሰሙት ልብ የሚያባባ ዜማ እንዳጀበን ወደ ቲራ-ኣ-ቮሎ አግጣጫ ተጣደፍን . . .



ጉበርኤል እና ሉላ ከልጆቻቸው ጋር
ከግራ ወደ ቀኝ - ዙፋን፣ ምንያ፣ መኮነን፣ ፈቃዱ፣ ይርጋዓለም፣ ምህረተአብ፣ አይዳ፣ ሃብተአብ፣ አጀባ







በግራ - መኮነን ጉበርኤል፣ በቀኝ - ሃብተአብ ጉበርኤል - አዲስአበባ - ልጅነት



የመኮነን ጉበርኤል ጓደኞች የድል ጉዞ

ማ ጣ ቀ ሻ ዎ ች
(R e f e r e n c e s)

- ኢጣልያዊ መግዛእቲ ኣብ ኤርትራ - ዘምህረት ዮውሃንስ
- መኽተ ኣንጻር ኢጣልያዊ መግዛእቲ ኣብ ኤርትራ - ዘምህረት ዮውሃንስ
- ኣይንፈላለ - ኤርትራ 1941 - 1950 - ኣለምሰገድ ተስፋይ
- ኤርትራ፡ 1955 - 1962 - ኣለምሰገድ ተስፋይ
- ተዘክሮ ናቕፋ፡ ጥብቆ - ጋይም ተስፋሚካኤል (ኮሎኔል)
- ታሪኽ ኤርትራ - ሚካኤል ራካ ሃሳማ
- ታሪክ ኤርትራ ካብጥንቲ ክሳብ ናጽነት
- ጥንተ ኣሚን ዘኢትዮጵያ - ርእሰ ደብር ዐቅበ እንድርያስ
- ካብ ሪቅ ህፍንቲ - ተክኤ በየነ
- ሰውራ ኤርትራ - ኣልኣሚን መሓመድ ሰኢድ
- ኤርትራን ቃልሳን - ህዝባዊ ግንባር ፕሮፓጋንዳ ክፍል።
- ስብሃት ኤፍሬም (ጀኔራል) - ቃለመጠይቅ ታዓጠቕ መጽሄት 2008
- ዛንታ ከተማ ኣስመራ - ይስሃቅ ዮሴፍ
- ህዝብታት መረኒ ፍጥረተ ገሸናሸም - ኣባ ይስሃቕ ገብረእየሱስ
- ማሰን መልቐስን ቀዳምት - ሰለሙን ጸሃዬ
- ሓመድ ደብ ናደው፡ ዛንታታት ተሞክሮ ገድሊ - ሰለሙን በርሀ
- ወፍሪ ስግሪ ዶብ - ሰለሙን በርሀ
- ኤርትራ፡ ብዘመን ባሕሪ ኒጋሲ - ኣልቫረዝ 1520፡ ትርጉም ሃይለ በኹረ
- *Abaa Gammachiis (Oneesimos Nasib) Biography By Rev. Tasgaraa Hirphoo (1999), Rev. Magarsaa Guutaa (2007)*
- *Evanjelical Pioneers In Ethiopia - Gustav Aren*
- *Kenisha The Roots and Development of The Evangelical Church of Eritrea Lundstrom, Ezra Gebremedhin.*
- *Ethiopian Obserever Vol XII No.2 (Megazine)*
- *The Collusion on Eritrea Bocresion Haile*
- *Italian Colonialism - Yemane Mesghenna*
- *The dying lion - Gillks*
- *Eritrea and Ethiopia The Federal Experience - Tekeste Negash*
- *Massacre At Wekidiba - Habtu (Fr. Athanasius) Ghebreab.*

- *Eritrea: Even the stones are burning. - Pateman*
- *The Camel in Somlia oral Tradition - Axmed Cali Abokor*
- *Haile Sellassie's War - Mockler*
- *I did't do it for you - Michela Wrong*
- *The Ebullient phoenix a history of the vicariate of Abyssinia 1839-1916 - Revised as one book, Kevin O'mahoney*
- *Campbell, 2010, Testimony. Interview conducted by Roman Herzog April 19th 2010,*
- *42 Laws of Power - Green*
- *Ethiopia Under Mussolini: Fascism and the Colonial Experience - Sbacchi, Alberto, 1986.*
- *Sbacchi, Alberto, 1997, Legacy of Bitterness: Ethiopia and Fascist Italy, 1935-1941, Trenton: Red Sea Press*
- *የኢትዮጵያና የኤርትራ የድንበር ግጭት - ዘውዴ ገብረስላሴ*
- *ዳግማዊ አጤ ምኒልክ - አፈወርቅ ገብረእየሱስ 1901 ሮማ*
- *ዐጼ ምኒልክ እና የኢትዮጵያ አንድነት - ተክለጻድቅ መኩሪያ*
- *ዐጼ ዮሃንስና የኢትዮጵያ አንድነት - ተክለጻድቅ መኩሪያ 1982*
- *የታሪክ ማስታወሻ - ደጃዝማች ከበደ ተሰማ።*
- *የኤርትራ ጉዳይ - ዘውዴ ረታ*
- *ቹ በለው - ብላቴን ጌታ ማህተመ ስላሴ ወልደመስቀል*
- *የውጎና ድርሰቶችና የታሪክ እውነቶች - ታቦር ዋሚ*

ቃለመጠይቅ እና ማስታወሻዎች

- *ሃብተአብ ገብርኤል (ማስታወሻ)*
- *መሓመድ አሊ አፋ (ቃለመጠይቅ)*
- *መብራህቱ ገብረወልድ (ቃለመጠይቅ)*
- *ማሕሙድ ከዳን (ቃለመጠይቅ)*
- *እንድርያስ ሃብተ (ቃለመጠይቅ)*
- *አባ እዮብ ገብረስላሴ (ቃለመጠይቅ)*
- *አጀባ ገብርኤል (ቃለመጠይቅና ማስታወሻ)*
- *ገብርኤል ኤድሞንዶ (ማስታወሻ እና የፍርድ ቤት ሰነድ)*
- *ዙፋን ገብርኤል (ማስታወሻ)*
- *ደበሳይ ገብርኤል (ቃለመጠይቅ)*
- *ይርጋአለም ገብርኤል (ቃለመጠይቅና ማስታወሻ)*

መጠቁም
Index of Names

ሂካ አዋጂ 71፣ 76-79
ሃብተአብ ገብርኤል 347፣ 374-383፣ 394
ሃብቱ ገብረአብ 394
ሃብተጊዮርጊስ ዲነግዴ 167
ሃይለሚካኤል ኪዳኑ 76
ሃይለስላሴ ጉግሳ (ራስ) 50፣ 236፣ 239
ሃይሉ ተክለሃይማኖት (ራስ) 167፣ 240፣ 246፣ 250-255
ሃይሉ ተወልደመድህን (ደጃዝማች) 108
ሃይሉ ከቢደ (ደጃዝማች) 242
ሃዲስ አለማየሁ 236
ሄርዞግ፣ ሮማን 394
ህወሓት 361
ህዝቅኤል ጋቢሳ (ፕሮፌሰር) 79
ለጥ ይበሉ ገብሬ (ቢጅሮንድ) 264
ሉላ እዮስአብ 190፣ 227-390
ላዛሪስት 55፣ 64፣ 113፣ 129፣ 164፣ 189፣ 220
ሎሬንዞ ታእዛዝ (ብላቴን ጌታ) 239፣ 303
ሐምድ ሃሰን (ከንቲባይ) 37-40
ሓነስ (ራስ) 33
ሓረጎት አባይ (ፊታውራሪ) 285
ሓድግ አምበስ ባልወት (ደጃች) 35፣ 108
ሓስበላ አብደላ ረሓም 291
መሓመድ አሊ አፋ 394
መሪየም በኺት 13-179
መስፍን ቢጋሾት (ብላታ) 198-214፣ 385
መስፍን ወልደሚካኤል 120
መስፍን ወልደማርያም 246
መብራህቱ ገብረወልድ 394
መብራህቱ ፍስሃ 302
መንግስቱ ሃይለማርያም (ኮሎኔል) 150፣ 279፣ 313፣ 352፣ 353፣ 380
መንግስቱ ንዋይ 317
መንገሻ ብሩ 302
መንገሻ ከፈላ 302
መንገሻ ዮሃንስ (ራስ) 42-65፣ 128፣ 135-138፣ 144፣ 165፣192፣ 242
መኢሶን 352
መኮንን ሃብተወልድ 245፣ 303-304
መኮነን ገብርኤል 334-344፣ 374-392
መኮንን ወ/ሚካኤል (ራስ) 136፣ 139፣ 151፣ -166
መዘገበ መኮነን 187፣ 188፣ 207-208
ሙሉጌታ ሉሌ 357
ሙሉጌታ (ራስ) 168፣ 242፣ 244
ሙንዚንገር፣ ዌርነር 65፣ 70-78፣ 108
ሚለና 385
ሚሸላ፣ ሮንግ 283፣ 394
ሚካኤል ራካ ሃሳማ 393
ሚካኤል ኤድሞንዶ 169፣ 170፣ 220
ሚካኤል እምሩ (ራስ) 139፣ 167
ማህተመስላሴ ወልደመስቀል (ብ.ጂ.) 33
ማሕሙድ ከዳን 333-335፣ 394
ማሕሙድ አረብዕ 291
ማስያስ (አባ) 31
ማርቲኒ፣ ፊርዲናንዶ 222፣ 224
ማርኮ ፖሎ 32
ማትየንዞ፣ ኤንዞ 292

ምህረተአብ ገብርኤል 395
ምህረት ሃይሉ 79
ምንትዋብ ተክለሃይማኖት 44፣ 46
ምንያ ገብርኤል 391
ሞሆኒ፣ ኬቨን 394
ሞራማርቸዮ (ኮሎኔል) 257
ሞከለር 394
ሞገስ አስገዶም 256-265፣ 314፣ 300
ሞገስ ፋሲል 377
ሰለሙን በርሀ 361፣ 378፣ 393
ሰለሞን አብርሃም (ደጃዝማች) 294
ሰለሙን ጸሃዬ 393
ሰለባ ወ/ሰላሴ (ኢቻ) 240፣ 259፣ 302
ሰላማዊት አርአያ 389
ሰንጋል ሓነስ (ቀኛዝማች) 118፣ 120፣ 121፣ 125፣ 134፣ 135፣ 163
ሰይፉ መታፈሪያ ፍሬው 352
ሱምቡሩጠሰ 95
ሳሌታ፣ ታንክሬዲት (ጄ/ል) 28-33፣ 85
ሳልህ አሕመድ ከኪያ ፓሻ 302
ሳሞራ የኑስ (ጀኔራል) 361
ሳባቺ አልቤርቶ 394
ሳንማርኮ (ኮማንዳቶር) 192፣ 210-232፣ 261
ስብሃት ኤፍሬም (ጀኔራል) 381፣ 393
ስዩም መንሻ (ራስ) 50፣ 242-256
ሻእቢያ 353-356፣ 371፣ 373-382
በላይ ሃብተአብ (ኮሎኔል) 260፣ 314
በላይ ዘለቀ 33
በአሉ ግርማ 359
በኩረጽዮን ሃይሌ 138፣ 314
ባልዲሴራ፣ ኦሬሮ (ጄኔራል) 80
ባህታ ሓነስ (ደጃዝማች) 35-37፣ 50፣ 66፣ 81፣ 101-143
ባዶሊዮ ፒየትሮ (ጄኔራል) 236፣ 247፣ 262፣ 263
ብእምነት ገብረአምላክ 302
ቦረቲ (ማጆር) 32
ቪዛንቲኒ 276፣ 277፣ 278
ተሰማ አስበርም (ራስ) 285
ተስፋዬ ወልደስላሴ (ኮሎኔል) 362፣ 363
ተክለሃይማኖት (አጤ) 44፣ 46፣ 47፣ 66
ተክለ አውግስቲኖ 212
ተክለጻድቅ መኩሪያ 47፣ 138፣ 394
ተክኤ በየነ 393
ተድላ ባይሩ 291፣ 307
ተዋበሸ ገብራይ 170፣ 179
ተፈሪ ብርሃኔ 341
ተፈራ ሹምዬ 334
ታቦር ዋሚ 394
ታከለ ወልደሃዋርያት (ብላታ) 236-248፣ 303-306፣ 315-332፣ 350
ታደሰች እስጢፋኖስ 261
ቴዎድሮስ ካሳ (አጤ) 12፣ 39፣ 80፣ 149፣ 150፣ 240፣ 352፣353፣372
ቴዎድሮስ ገብርኤል 227
ቴዎፍሎስ (አቡነ) 323፣ 324፣ 330
ትግረ ትግርኛ 92
ቶዘሊ ፒየትሮ 128፣ 129
ቸርሚሰይድ (ኮሎኔል) 32
ኑረነቢ በቪት 1-404
ናሆም ደበሳይ 389
ናፖሊዮን 33
ንርአየ ኢሳይያስ 372፣ 373
ንጉሴ ፍትሕ አወቅ 373
አህመድ ቃሊ አቦከር 394
አሕመድ ኢብራሂም (ግራኝ) 246
አለምሰገድ ተሰፋይ 308፣ 393
አሉላ ቁቢ (ራስ) 32-50፣ 63፣ 125-128፣ 143፣ 156
አልአሚን መሃመድ ሰዒድ 393
አልቫሬዝ 88፣ 89፣ 105
አማኑኤል ቪቶርዮ 210፣ 229፣ 230፣ 247
አረይ አገባ (ሼክ) 37
አርአያ (ራስ) 125
አርአያ ዋሴ (ደጃዝማች) 285
አርከበ ዑቅባይ 361
አሰፋ ባህታ 259
አስመሮም ለገሰ (ፕሮፌሰር) 79
አስራተ ካሳ (ራስ) 310፣ 311፣ 328-339
አስገዶም ሃይሉ 210፣ 211
አስፋወሰን ካሳ (ደጃዝማች) 251፣ 252-255፣ 261-262
አስፍሃ ወልደሚካኤል (ቢትወደድ) 81፣ 302፣ 307-309፣ 320

አበራ ካሳ (ደጃዝማች) 251፣ 252-255፣ 261-262
አበራ ካሳ ተወልደመድህን (ልጅ) 23
አበበ አረጋይ (ራስ) 248፣ 249፣ 251፣ 254
አብዱልቃድር ከቢረ 285፣ 286
አብርሃ (አቡነ) 371
አብርሃ ደቦጭ 256-265፣ 314፣ 300
አብደላ መደኒ 302
አብዱላሂ (አሚር) 166
አብይ አበበ (ጀኔራል) 314
አካለወልድ ሃብተወልድ 304
አክሊሉ ሃብተወልድ (ጸ.ትእዛዝ) 304፣ 309፣332፣ 335
አንዶም ተስፋጽዮን (ሹምባሽ) 241፣ 259
አይዳ ገብርኤል 391
አጀባ ገብርኤል 391፣ 394
አዜብ ፍስሃዬ (ዶክተር) 375- 382
አፈወርቅ ገብረእየሱስ 13፣ 123፣ 240፣ 394
ኡምኩሉ 32፣ 56-79፣ 181፣ 391
ኢህአፓ 351
ኢብራሂም ሱልጣን (ሼኽ) 238፣ 285
ኡምቤርቶ (ንጉስ) 38፣ 123
ኢሚሊዮ ደ ቦኖ (ማርሻል) 235
ኢሳይያስ አፈወርቂ 357፣ 382
ኢዜት ቤይ 30፣ 32
ኤፍሬም ተወልደመድህን (ብ.ጌ.) 239፣ 302
እምሩ ሃይለስላሴ (ራስ) 236፣ 241-248፣ 260፣ 323፣ 330
እምባየ አርአያ 125
እስጢፋኖስ ኤድዋርዶ 187-189፣ 198፣ 207-209፣ 211፣ 212
እንድርያስ ሃብተ 394
እያሱ መንገሻ (ጀኔራል) 302
እያሱ ሚካኤል 166፣ 167፣ 168፣ 179፣ 304፣ 305፣ 316
እያሱ ያእቆብ 179-196፣ 231-256፣ 271፣ 321-328፣ 350፣ 365-389
እዮብ ገብረስላሴ (አባ) 394
እዝራ ገብረመድህን 71፣ 393
አሊቪየሪ፣ ኢሚሊዮ 59፣ 61፣ 62
አነሲሞስ ነሲብ (አባ ገመቺስ) 64-79
ከሰተብርሃን ገብረሀይወት (ጀኔራል) 374፣ 382
ከበደች ስዩም (ወይዘሮ ሆይ) 256
ኪይሚ ፒየትሮ 31፣ 32
ኪዳነ አድኅይ 206፣ 207፣ 214፣ 296፣385
ካሕሱ ሓጎስ 118፣ 125
ካምፐቤል 394
ካሳ ሃይሉ (ራስ) 242፣ 243፣ 261፣ 303
ካታንዮ ቪንቸንሰን 212፣ 231፣ 348፣ 386
ካፐራ ፈርዲናንዲን 212
ካፍል ነፋር (ባለምባራስ) 34፣ 36፣ 40፣ 65፣ 80፣ 104፣ 117፣ 120፣ 156
ኬኔሊ፣ ቶማስ 381
ኬኔዲ ኩክ (ብርጋድየር ጀኔራል) 286
ኮርስቶፈርስ ደ ቶማስ (ኮሎኔል) 32
ኮርቴዜ፣ ጉዊዶ 264
ኮኔል፣ ዳን 381
ዑመር ኢል ሙክታር (ሼኽ) 172-175
ዑቻባሚካኤል ጠቋሬ 96
ዑናይ ጹናማይ 61፣ 62፣ 282-290
ወልደሚካኤል (ደጃዝማች) 264
ወልደንኬኤል 380
ወልደአብ ወልደማርያም 285፣ 291፣ 371
ወልደአብ ገብረልዑል 354
ወልደጊዮርጊስ (ጸ.ትእዛዝ) 309፣ 310፣ 316፣ 317
ወንድ በወሰን ካሳ (ደጃዝማች) 255
ውብቱ ጸጋዬ (ጀኔራል) 378
ውብነህ (ደጃዝማች) 305
ዘማት ወድ እኩድ 156፣ 157
ዘምህረት ዮሃንስ 44፣ 81፣ 125፣ 157፣ 389፣ 393
ዘርኢይ ደረስ 260፣ 314፣ 372
ዘርአጽዮን ሙሴ 65፣ 70፣ 76፣ 791 26፣ 163
ዘገየ አስፋው 373
ዘውዲቱ ምኒልክ 166፣ 167፣ 168
ዘውዴ ረታ 394
ዘውዴ አስፋው 245
ዘውዴ ገብረስላሴ (ዶክተር) 240፣ 394
ዙፋን ገብርኤል 382፣ 391፣ 394
ዛህራ ዑስማን 9-15፣ 74
የማነ ምስግና 393
ያሲን መሐመድ ባጡቾ 291
ያዕቆብ ተወልደ 108-146፣ 07፣ 271
ይስሃቅ ዮሴፍ 393

ይርጋአለም ገብርኤል 391፣ 394
ዮሃንስ ምርጫ (አጤ) 32፣ 50-66፣ 109፣ 126
ዮሃንስ ኩልቦ (አባ) 36-133፣ 219፣ 220
ዮሃንስ ኮልመዬን 124
ደምሰስ ወልደሚካኤል 285
ደስታ ዳምጠው (ራስ) 245፣ 257
ደበሳይ ሃይሌ 376፣ 378፣ 382
ደበሳይ ገብርኤል 7፣ 8፣ 164፣ 234፣ 331፣ 343፣ 344፣ 350፣ 391- 394፣ 394
ደግሊል አሊ ሃሰን 37
ዲሜጥሮስ ገብረማርያም 308፣ 309
ዳቦርሚዳ (ጀኔራል) 137፣ 140
ዳዊት ወልደጊዮርጊስ (ሻለቃ) 293
ዳውዲያቺ (ንቨርናቶረ) 223
ዴላ ፖርታ 264
ዴቪድሰን፣ ባሲል 379
ድሩይ ፍጋግ 95
ድራር ተክላይ 259
ጀብሃ 313፣ 314፣ 336-341፣ 365፣ 371
ጁሴፔ ሳፔቶ 31
ጄኔ ካርሎ (ጀኔራል) 32
ጆቴ ጁሉ 165
ገረሱ ዱኪ (ደጃዝማች) 248፣ 316
ገርማሜ ንዋይ 317
ገሰሰ በለው (ደጃዝማች) 236
ገብረመስቀል ወልዱ 281፣ 285
ገብረመድህን ባህታ 118-159
ገብረሚካኤል ግርሙ (ዘባራቂት) 291
ገብረማርያም ቴዎድሮስ 187፣ 189፣ 190፣198፣ 207፣ 212፣ 234፣ 257፣ 385
ገብረአብ ሓጎስ 241፣ 242
ገብረእዝጊእ ሰብሃት 259
ገብራይ ገብረማርያም 259
ገብራይ (ግራዝማች) 241
ጉሳታቭ ቢያንኪ 31
ጉሳታቭ አረን 71
ጉግሳ ወሌ (ራስ) 167፣ 168
ጊልክስ 393
ጋላቮቲ 372
ጋስፓሪኒ (ጀኔራል) 223
ጋሪባልዲ ጆሴፍ 178
ጋኪ ሻረቶ 165
ጋይም ተስፋሚካኤል (ኮሎኔል) 393
ግራዝያኒ፣ ሮዶልፎ 175፣ 183-235፣ 250-256፣ 261-265፣ 286
ግርማ አስመሮም (አምባሳደር) 379
ጎበና ዳጪ 39፣ 166
ጠአመ በየነ 373
ጣይቱ ብጡል (እቴጌ) 69፣ 143፣ 144
ጳውሎስ ብርሃኔ 260፣ 302
ጸሃዬ ፋሲል 377፣ 377፣ 382
ጸጋ ብርሃን መንገሻ 298፣ 389
ጸጋዬ ገብረመድህን (ሎሬት) 372፣ 373
ጸጋይ ንጉሴ 196፣ 240-241፣ 257-259
ጹናማይ 59፣ 60፣ 61፣ 62
ፈካክ አሊ 152፣ 153
ፈዳይ ኢያሱ 330፣ 366፣ 385፣ 384፣ 386
ፊሊጶስ ወልደዮሃንስ (ጄኔራል) 354
ፋብዮ፣ መተሊ 371
ፍስሃ ተክሌ 206
ፍስሃ ደስታ (ኮሎኔል) 310
ፍስሃ ጽዮን ሃይሌ 313-314
ፍራንኬቲ 102፣ 158፣ 222
ፍቓዱ ተከስተ (ዶክተር) 379
ፍቓዱ ገብርኤል 391
ፍካሬ መኮነን 187፣ 188፣ 208
ፍጡር አብርሃም (ቀኛዝማች) 187፣ 204 - 208፣ 302፣ 389
ፒየትሮ ዛናኒ 202-205
ፓላቪሲኖ 264
ፓንክረስት፣ ሲልቪያ 301
ፓንክረስት፣ ሪቻርድ 278
ፓትማን፣ ሮይ 381፣ 394

ውድ አንባቢያን

ስለዚህ መጽሃፍ ያላችሁን አስተያየት ለመላክ፣
ወይም መጽሃፉን ለማከፋፈል
የሚከተሉትን አድራሻዎች ተጠቀሙ!

አስተያየት ለደራሲው

Email: ttgebreab@gmail.com
www.tgindex.blogspot.com

መጽሃፉን ለማከፋፈል ወይም በON LINE ለመግዛት

Gabriel and Son Publishing, LLC.
6301 Stevenson Ave. # 717
Alexandria, VA 22304
USA

E-mail: gdebessay@msn.com
Office: 703-566-6589

www.nurenebi.blogspot.com
nurenebi@gmail.com